# አኰቴተ ቍርባን

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት፣ ታሪካዊ እድገት እና ይዘት



ቀሲስ መብራቱ ኪሮስ ገብሩ (ዶ/ር)

መጋቢት፣ ፳፻፲፮ ዓ.ም.

# አኰቴተ ቍርባን፡

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት፣ ታሪካዊ እድገት እና ይዘት

**ቀሲስ መብራቱ ኪሮስ ገብሩ (ዶ/ር)**

**መጋቢት ፳፻፲፮ ዓ.ም. (2024 European Calendar)**

Graphic Design & Printing
San Diego, California
USA

© 2016 ዓ.ም. መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

© 2024 All Rights Reserved.

አኰቴተ ቍርባን፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት፣ ታሪካዊ እድገት እና ይዘት

*Akkʷåtetä Qʷərban:*

*Yä-Ityoṗəya Orətodokəs Täwaḥədo Betäkərəstyan Śərə'atä Qəddase*

*Mäśärät, Tarikawi Ǝdəgät Ǝna Yəzät*

By፡ Fr. Mebratu Kiros Gebru, Ph.D.

መጀመሪያ እትም፡- ኅዳር ፳፻፲፪ ዓ.ም. (2019) - አዲስ አበባ

ሁለተኛ እትም፡- የካቲት ፳፻፲፪ ዓ.ም. (2020) - አዲስ አበባ

ሦስተኛ እትም፡- ጥር ፳፻፲፫ ዓ.ም. (2021) - አዲስ አበባ

አራተኛ እትም፡- ሰኔ ፳፻፲፫ ዓ.ም. (2021)

ጣና ማተሚያ ቤት - Tana Printing Enterprise Ltd.

633 Vaughan Road – Toronto, Canada.

አምስተኛ እትም፡- መጋቢት ፳፻፲፮ ዓ.ም. (2024)

Graphic Design & Printing, San Diego, CA – 619-206-0921

ISBN: 978-99944-77-59-3

በመጽሐፉ ላይ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላችሁ:-

Email: mebratukiros@gmail.com

Cell: +1-647-772-4601.

# መታሰቢያ

ተወልጄ ባደግሁበት አዲስ አባባ በሚገኘው በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን የግእዝ ንባብን ከማስተማር በተጨማሪ፥ ቅድስናን በተመላው መንፈሳዊ ሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ፍቅር ላሳዩኝ ለመምህሬ አባ ክፍለ ዮሐንስ ዘወልደ ማርያም (1911 - 2011 ዓ.ም.) ይሁንልኝ።



ዲያቆን እያለሁ፥ አባ ክፍሌ ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን እቃ ቤት ውስጥ በብራና የተጻፈ መጽሐፈ ስንክሳር ሲያስነብቡኝ፡፡
፲፱፻፹፯ ዓ.ም. (1995 European Calendar)

# ምስጋና

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "አቀድም አእኵቶቶ ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ኵልክሙ" (አስቀድሜ ስለሁላችሁ በኢየሱሰ ክርስቶስ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ [ሮሜ 1፥8]) እንዳለ፥ በቅድሚያ ለምስጋና ያሰብኳቸውን ሰዎች በአንድም በሌላም መልኩ ወደ እኔ ሕይወት በምክንያትና በዓላማ ለላከውና በምሕረቱ ባለጸጋ ለሆነው አምላካችን "ስብሐት ወክብር" (ምስጋና እና ክብር) ይሁን፡፡

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ካሰብኩበት ጊዜ ጀምሮ ሲያበረታቱኝ የነበሩትን ብፁዕ አቡነ ድሜጥሮስ፥ የምሥራቅ ካናዳ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ፥ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅና የካቴድራሉ ዋና አስተዳዳሪን ለማመስገን እወዳለሁ፡፡ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ዳላስ፥ ቴክሳስ በነበሩበት ጊዜ የመጽሐፉን የመጀመሪያ ምዕራፍ ልኬላቸው እጅግ በሚደንቅ መልኩ መልክዐ ፊደላቱን በጥንቃቄ በማረም ለቀጣይ ሥራዎቼ ታላቅ ትምህርት ሰጥተውኛል፤ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላም በቀሪዎቹ ምዕራፎች ላይ ተመሳሳይ እርማቶችን አድርገውልኛል፡፡ ለአባታዊ ፍቅራቸው እና ለበጎ ትብብራቸው ብፁዕ አባታችንን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የመጽሐፉን የመጀመሪያ እትም አንብበው እርማቶችንና ገንቢ አስተያየቶችን የሰጡኝ መልአከ ሕይወት ሐረገ ወይን ብርሃኑ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

የኢትዮጵያ ጥናት፥ ታሪክ እና ሥነ ጽሑፍ ተጠያቂ ሊቅ እና ዘመን ተሻጋሪ በሆኑት ሥራዎቻቸው ዓለም አቀፋዊ እውቅናን ያገኙትና በቅርቡ ያረፉት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የመጽሐፉን የመጀመሪያ እትም ረቂቅ አይተው የተሳሳቱ አገላለጾቼን እንዳስተካክልና መጽሐፉ ብሔራዊ ይዘቱን እንዲጠብቅ ምሁራዊ እርማት ሰጥተውኛል፡፡ በዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱት የፕሮፌሰር ጌታቸው መጻሕፍትና ጥናታዊ ጽሑፎች ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ታላቅ ግብአት ነበራቸው፡፡ በምሕረቱ ባለጸጋ የሆነው አምላክ የፕሮፌሰር ጌታቸውን ነፍስ ሰማያዊ ሐሴት ባለበት በመካነ ቅዱሳን ያሳርፍልን፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ በርካታ ጥናቶችን ያካሄዱት ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ ያለምንም መሰልቸት በስልክ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች መልስ በመስጠትና ለዚህ መጽሐፍ ሥራ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎችን በመላክ ታላቅ እገዛ አድርገውልኛል፤ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ "መምህር በአማን ነጸረ"

በሚል የብዕር ስም የሚጽፈው የቅኔ፥ የዜማና የሕግ ባለሞያ፥ በአካል ሳላገኘው በኢሜይል በሚደረግ የመልእክት ልውውጥ ብቻ የመጽሐፉን ረቂቅ አንብቦ ያገኛቸውን ክፍተቶች በመሙላት፥ ታሪካዊ ዘገባዬ ላይ ሚዛናዊ እንድሆን በማንቃትና የግእዝ ትርጒሞቼን በማረም ረድቶኛል፡፡ እንደ አባቶቻችን ቡራኬ "ዐስበ መምህራንን ያድልልኝ" ከማለት የተሻለ የምስጋና ቃል የለኝም፡፡

እንደ ታላቅ የሥጋ ወንድሜ የማየው፥ በምንም ነገር የማይቀየር ወዳጅነትና ራስን እየጎዱ ሌላውን የመጥቀም ልዩ ሥጦታ የተሰጠው፥ የቂርቆሱ መምህር ኤልያስ እሸቱ፥ የመጽሐፉ ፍጻሜ አካባቢ መንፈስን የሚረብሹ ፈተናዎች በገጠሙኝ ጊዜያት ሁሉ ካጠገቤ መሆኑ ሳያንሰው ከቤተሰቡ ጊዜ ቀንሶ በመጽሐፉ ረቂቅ ላይ የቃላት እርማት በማድረግ ያግዘኝ ነበር፡፡ ወንድሜ ሆይ፥ ልጆችህ ለቁም ነገር ደርሰው ታይ ዘንድ ረጅምና ሰላማዊ ዘመናትን ያድልህ፡፡ በእነዚህ ፈታኝ ጊዜያት የመንፈስ ጥንካሬ እንዲኖረኝ ወንድማዊ እገዛው ያልተለየኝ መምህር ተመስገን ዮሐንስንም አመሰግናለሁ፡፡ ሌላው ኤልያስ (የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የአምስተኛ ዓመት የማታ ዲግሪ መርሐ ግብር ተማሪ ኤልያስ ገብረ ሥላሴ) የሥራና የትምህርት ጊዜውን አጣቦ ረቂቁን በማረምና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት ተባብሮኛል፤ ቅንነት ለተሞላው ትብብሩ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ የቂርቆሱ ሰባኬ ወንጌል መምህር ሰሎሞን ዮሐንስ፥ የበርካታ መጻሕፍት ደራሲ ስለሆነና መጽሐፍ ጽፎ የማሳተም ድካምን ስለሚረዳ፥ ስለ መጽሐፉ የመጀመሪያ ኅትመት ጠቃሚ አስተያየቶችን ስለለገሰኝና ለፍጻሜ እስኪደርስ ድረስ በቅርበት በመከታተል ስለረዳኝ እርሱንም አመሰግነው ዘንድ እወዳለሁ፡፡

ከግማሽ በላይ የሚሆነው የመጽሐፉ ክፍል የተጻፈው በቤተ ክርስቲያን ጥሪ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጊዜያዊ ዋና ዲን በመሆን ለማገልገል በ2011 ዓ.ም. በጥር ወር መጀመሪያ ላይ ከቶሮንቶ፥ ካናዳ ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ ነው፡፡ ከቢሮ ሥራና ከማስተማር ተግባር ውጪ በማገኘው ጊዜ ይህን መጽሐፍ ስጽፍ፥ ውዷ ባለቤቴ ሔለን ብርሃኔ ቶሮንቶ ውስጥ የሙሉ ቀን ሥራ (full-time job) እየሠራች ሁለቱን ልጆቻችንን (ዮሐና እና ሳሙኤልን) ብቻዋን ታሳድግ ነበር፡፡ ስለ ፍቅሯ እና የእናትነት ትጋትዋ በልቤ የሞላውን ሐሤት ለመግለጽ ጒልበት ያላቸውን ቃላት ማግኘት አልቻልኩም፤ ለረጅም ዘመናት ኑሪልኝ! በራሱ ጥበብ አንቺን ልዩ ሥጦታ አድርጎ የሰጠኝ አምላክ፥ ቅዱስ ስሙ ለዘላለም ይባረክ፡፡

# ምኅጻረ ቃላት (አኅጽሮት)

| | |
|---|---|
| ኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን። ቤተ ክርስቲያናችን ከምትጠራበት ከዚህ ሙሉ ስያሜ በተጨማሪ አንዳንድ ቦታዎች ላይ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" የሚል መጠሪያን ተጠቅሜአለሁ። ይህን ያደረግሁት፥ በዚህ ስም ልትጠራ የሚገባት የኢትዮጵያ ብቸኛና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን ለመጠቆም ነው። |
| እ.አ.አ. | እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር፤ የእንግሊዝኛ ጽሑፎችን አንደ ምንጭነት ስጠቅስ ከመካከለኛው ዘመን (Medieval Period, 12 C.) በኋላ ላሉት ጊዜያት ይህን ምኅጻረ ቃል ተጠቅሜአለሁ፡፡ |
| ወዘተ. | ወዘተርፈ ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን፥ እንደ ላቲኑ *et cetera (etc.)* ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ የቀሩ ተጨማሪ ነገሮች እንዳሉ ይጠቁማል፡፡ |
| ዓ.ም. | ዓመተ ምሕረት፤ የአገራችን ኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር ያመለክታል፡፡ |
| ዓ. እ.* | ዓመተ እግዚእ (የጌታ ዓመት)፥ የላቲኑ A.D. (*Anno Domini* - in the year of the Lord) አቻ፤ በእንግሊዝኛ ምንጮች የተጠቀሱ የጥንት መዛግብትንና እስከ 8ኛው ምእት ዓመት የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ዘመናት ለማመልከት "እ.አ.አ." የሚለውን ሳይሆን ይህን ምኅጻረ ቃል መርጫለሁ፡፡ |
| CE | The Coptic Encyclopedia. |
| CSCO | Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium. |
| EA | Encyclopedia Aethiopica. |
| EMML | Ethiopian Manuscript Microfilm Library. |
| HMML | Hill Monastic Manuscript Library. |
| JES | Journal of Ethiopian Studies. |
| JSS | Journal of Semitic Studies. |
| NCE | New Catholic Encyclopedia. |
| OC | Oriens Christianus. |
| OCa | Orientalia Christiana. |
| OCA | Orientalia Christiana Analecta. |
| OCP | Orientalia Christiana Periodica. |
| PO | Patrologia Orientalis. |

*ይህን ምኅጻረ ቃል የወሰድኩት ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ መጽሐፍ ነው፡- *የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፡ ኦሮሞችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር* (ኮሌጅቪል፡ ሚኒሶታ፡ 1995 ዓ.ም.) ገጽ 11፡፡

# ማውጫ

✷መታሰቢያ ........................................................................ iii
✷ምስጋና ............................................................................ v
✷ምኅጻረ ቃላት ...................................................................... vii
✷መቅድም ........................................................................... xiv
✷መግቢያ ............................................................................ xvi

## ምዕራፍ አንድ

## ቅዳሴ ምንድን ነው? 1

**1.1 የቅዳሴ መገለጫ ባሕርያት**.......................................................... 3
☞፩. የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት የሚቀርብበት ዐቢይ ሥርዓተ አምልኮ...... 4
☞ ቅዱስ ቊርባን ፥ አማናዊ መሥዋዕት ....................................... 7
☞ቅዱስ ቊርባን ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ ............... 18
☞ ፪. የክርስቶስን የማዳን ሥራ እውን የሚያደርግልን የምስጋና አገልግሎት ........................................................................ 21
☞ ፫. በምድር ላይ ያለ ሰማያዊ አገልግሎት ...................................... 23
☞ ፬. የሰማያዊው አምልኮ ነጸብራቅ ................................................ 26
☞ ፭. በደስታና በሐሤት የሚከናወን አምልኮ ................................. 29
**1.2. የቅዳሴ ውበት**.......................................................................... 31
**1.3. የቅዳሴ መንፈሳዊ ዕሴቶች (ጥቅሞች)** ............................................ 34
☞ ምሪት ወደ ቅዳሴው መሥዋዕት ................................................... 34
☞ የአማንያን ኅብረት.......................................................................... 36
☞ ክርስቶስን የመሰለ ሕይወት ......................................................... 39
☞ በጸሎትና በምስጋና ሕይወት ማደግ ............................................. 41
☞የቅዳሴው አገልግሎት ለምን አልለወጠኝም?............................. 43
👍 መደምደሚያ ............................................................................... 49

## ምዕራፍ ሁለት

**የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ 51**

**2.1. የምሥጢረ ቍርባን አመሠራረት** ........................................ 52

☞ የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ ........................................ 53

☞ ወንጌላት፤ መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ........................ 57

☞ አጋፔ (የፍቅር ማዕድ) እና ቅዱስ ቍርባን ........................ 61

☞ የቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ መልእክታት ........................ 68

**2.2. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት** ........................................ 70

**፩. የአንደኛው እና ሁለተኛው ምእት ዓመታት መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን** ........................................ 72

☞ ዲዳኬ: ትምህርተ ሐዋርያት ........................................ 72

☞ የሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ (+165 ዓ.እ.) ምስክርነት ........................ 77

☞ ቅዱስ ሄሬኔዎስ ተላዊሆሙ ለሐዋርያት (+202 ዓ.እ.) ........................ 80

**፪. የ3ኛው ምእት ዓመት ሥርዓተ ቍርባን ጠቋሚ ምንጮች** ........................ 83

☞ ሐዋርያዊ ትውፊት ........................................ 85

☞ አኰቴተ ቍርባን ዘሐዋርያት ታዴዎስ ወማሬስ ........................ 91

☞ ቅዳሴ ማርቆስ ወንጌላዊ ........................................ 94

**፫. የ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት** ........................................ 98

☞ የቅዱስ ሰራጵዮን መጽሐፈ ቅዳሴ ........................................ 99

☞ ትምህርተ ንኡስ ክርስቲያን ዘቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም (+386 ዓ.እ.) ........................................ 103

☞ አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ባስልዮስ ........................................ 107

☞ ቅዳሴ ቀሌምንጦስ ዘሮሜ ........................................ 110

☞ ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም) ........................ 113

☞ ቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያ ........................................ 116

☞ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ........................................ 118

፬. የ5ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት ........................................ 121
☞ አኰቴተ ቍርባን ዘመጽሐፈ ኪዳን (ቅዳሴ እግዚእ) ........................ 121
☞ አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘሰላሚስ ............................ 125
👍 መደምደሚያ ........................................................ 126


## ምዕራፍ ሦስት
## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት እና ታሪካዊ እድገት 128


3.1. አጭር ታሪካዊ ዳሰሳ ................................................ 129
፩. ሥርዓተ ቅዳሴ ዘዘመነ አክሱም .......................................... 132
☞ አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ሄጶሊጦስ/አቡሊዲስ ዘሮሜ ወይስ ቅዳሴ ሐዋርያት? ........ 142
☞ "ጻድቃን ዘመጥራ" እና ተስዐቱ ቅዱሳን ................................. 172
☞ የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት ........................................ 177
☞ ከአክሱም መንግሥት ውድቀት በኋላ ...................................... 180
፪. ሁለተኛው የትርጉም ሥራ፡- ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ............................ 182
፫. የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ወርቃማ ዘመናት ...................................... 187
☞ በእንተ ስግደት ለሥዕል ወለመስቀል ...................................... 188
☞ ውዝግቡ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ላይ ያስከተለው ለውጥ ........ 196
☞ መጽሐፈ ሥርዓት ዘወጽአ እመንበረ ማርቆስ፡ መቅድመ ተአምረ ማርያም ............ 197
☞ መልክዐ ሥዕል ወማኅሌተ ጽጌ .......................................... 199
☞ መስተብቍዕ ዘማርያም ወዘመስቀል ...................................... 206
☞ በእንተ አክብሮ ሰንበታት ............................................ 208
☞ በእንተ ምሳሐ ደብረ ጽዮን ........................................... 213
☞ አልቦቱ ለእግዚአብሔር መልክዐ ከመ መልክዐ ሰብእ ........................... 219

**3.2. ቅዳሴያቱ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መደረሳቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች** ........ 230
☞ ፩. ቅዳሴያቱ በተሰየሙባቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሥራዎች ውስጥ አለመገኘታቸው ........ 233
☞ ፪. በተለምዶ ከግብፅ መጡ የሚባሉት ቅዳሴያት በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አለመታወቃቸው ........ 234
☞ ፫. የአፄ ዘርአ ያዕቆብ አዋጅ ........ 235
☞ ፬. በቅዳሴያቱ ውስጥ ያሉ ጠቋሚ ምልክቶች ........ 236
☞ ፭. አንድ አይነት የጸሎት ክፍሎች እና ዐረፍተ ነገሮች በቅዳሴያቱ ውስጥ መገኘታቸው ........ 237
☞ ፮. ኢትዮጵያዊ የአጻጻፍ ዘዴ ........ 239
**3.3. የቅዳሴያቱ ስያሜያት እንዴት ተመረጡ?** ........ 242
♁ መደምደሚያ ........ 250

## ምዕራፍ አራት
## የቅዳሴ አጠቃላይ ይዘት **252**

**4.1. ሦስቱ የቅዳሴ ክፍሎች** ........ 253
**፩. ሥርዓተ ቅዳሴ** ........ 255
☞ የዝግጅት ክፍል ........ 255
☞ የመግቢያ ዝማሬያት ........ 258
☞ ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት ........ 259
☞ አግብኦተ ግብር ........ 260
☞ አሐዱ አብ ቅዱስ ........ 261
☞ ጸሎተ አኰቴት፤ ጸሎተ መባእ ዘሐዋርያት ........ 262
☞ ጸሎተ እንፎራ ........ 263
☞ በእንተ ቅድሳት ........ 264
☞ ማዕጠንት ዘወርቅ ........ 266

☞ የትምህርት ክፍል .................................. 267

☞ መልእክታተ ሐዋርያት........................................................ 267

☞ ተፈሥሒ ኦ ዘንስእለኪ ዳኅና .................................................. 269

☞ ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት........................................................ 269

☞ ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል ፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት (ሠለስቱ ቅዳስያት) ................................................. 270

☞ ጸሎት በእንተ ኵሉ ዓለም ................................................. 274

☞ ቅድመ አኰቴተ ቍርባን........................... 275

☞ ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን ......................................................... 275

☞ ጸሎት እንዘ ይቀርብ ኀበ ታቦት ............................................. 276

☞ ጸሎት በእንተ ቤተ ክርስቲያን፥ በእንተ ጳጳስ ወበእንተ ማኅበር ........ 277

☞ ጸሎተ ሃይማኖት.............................................................. 278

☞ ተሐፅቦተ እድ ................................................................... 280

☞ አምኃ ቅድሳት ................................................................. 281

**፪. ፍሬ ቅዳሴ፡ ቅዳሴያት ዘኢትዮጵያ** ...................................... 283

☞ አውሥኦ (ምልልስ)................................................................. 287

☞ ተዝካረ ቅዱሳን ወጸሎት በእንተ እለ ኖሙ .................................... 289

☞ ጸሎተ ቡራኬ........................................................................ 291

☞ ዝማሬ ሱራፌል ..................................................................... 292

☞ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ .............................................................. 295

☞ ዝከረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ.............................................. 299

☞ ሠለስቱ ቅዳስያት ዘአኰቴተ ቍርባን............................................. 300

☞ ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ ............................................................. 301

☞ ጸሎተ ፈትቶ፥ ኅዳፌ ነፍስ ወአንብሮ እድ ....................................... 304

**፫. ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በፊት እና በኋላ** .................................. 307

☞ ቅድሳት ለቅዱሳን.................................................................. 308

☞ ጸሎት እምቅድመ ተመጥዎ ቍርባን .............................................. 310

☞ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢ.ይትነገር ..................................... 311
☞ እምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን ........................................................ 312
**4.2. የሥርዓተ ቅዳሴ ምሳሌዎች እና ትምህርታዊ መልእክቶቻቸው** ............... 314
**፩. ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እና ቅዱሳት ሥዕላት** ...................................... 316
☞ ቅዱሳት ሥዕላት .............................................................. 322
**፪. ምሳሌያት ዘቅዳሴ** ................................................................ 324
☞ ልኡካን ........................................................................ 325
☞ ዕጣን ........................................................................... 326
☞ መንጦላዕት ................................................................... 328
☞ ፵ወ፪ቱ ቡራኬያት ............................................................ 329
☞ ፲ወ፩ዱ እማሬያት ............................................................ 334
☞ ፯ቱ ዑደታት ................................................................... 335
☝ መደምደሚያ ................................................................... 337
**✷ ማጠቃለያ** ........................................................................ 338
**✷ መፍትሔ ቃላት** ................................................................. 344
**✷ ዋቢ መጻሕፍት፡ የግእዝና የአማርኛ መጻሕፍት ዝርዝር** ........................ 351
**✷ የእንግሊዝኛ መጻሕፍት እና ጥናታዊ ጽሑፎች** ..................................... 355

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ በዋነኝነት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ) ካህናት፥ ዲያቆናት እና ምእመናን የተዘጋጀ ነው፡፡ በታሪካዊቷና ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን ለከፍተኛ ተቋማት ለማቅረብ ለሚሹ ሰዎችም መጠነኛ እገዛ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ፡፡ በመጽሐፉ፥ መሠረታቸው (ጥንታቸው) ግሪክ፥ ላቲን ወይም ግእዝ የሆኑ በርካታ የሥርዓተ አምልኮ ቃላት ስለተጠቀሱ፥ ለአንባብያን ግልጽ ለማድረግ፥ የመጽሐፉ መጨረሻ ክፍል ላይ መፍትሔ ቃላት (የቃላት መፍቻ) ተዘጋጅቷል፡፡

የአማርኛ ቃላትን መልክዐ ፊደላት (ፊደላት ምርጫ) እና ሥርዓተ ነጥብን በተመለከተ አብነት ያደረግሁት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1980 ዓ.ም. ለኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ የታተመውን መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ለምሳሌ በተለምዶ የአማርኛ መጻሕፍት ውስጥ “ሐሳብ” የሚል አጻጻፍ እናገኛለን፡፡ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ቅዱስ ግን “አሳብ” ይላል፤ ኤፌ 1፡11ን ይመልከቱ፡- “እንደ እርሱ አሳብ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን።” ስለዚህ ይህን ጥቅስ በምጠቅስበት ቦታ ላይ ብቻ ሳይሆን “አሳብ” የሚለውን ቃል በተጠቀምኩባቸው ቦታዎች ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱሱን መልክዐ ፊደል መርጫለሁ። በተመሳሳይ መልኩ፥ በልምድ የምንጽፈውን “ቁጥር” ሳይሆን በጥንቃቄ የተቀመጠውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን አጻጻፍ ዘዴ ማለትም “ቍጥር” የሚለውን ተጠቅሜአለሁ፤ “የአውሬውን ቍጥር” የሚለውን ይመልከቱ (ራእ. 13፥18)። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሲጠቀሱም ምኅጻረ ቃላቱን እና ሥርዓተ ነጥቦቹን ያስቀመጥኩት የአማርኛው ትርጒም አዲስ ኪዳን ኅዳግ ላይ ያለውን በመከተል ነው። ለምሳሌ፡- ዘፍጥ. 4፥4፤ ዮሐ. 1፥26፤ 1ጴጥ. 2፥23-23፤ ዕብ. 5፥ 6-10 ፤1ነገሥ. 18፥30-38 ወዘተ.።

በቅርቡ እየተለመደ የመጣ አጻጻፍ፡- ኹለት፥ ኹሉ፥ ከኾነ ወዘተ. (በ”ሀ” ቦታ “ኸ”ን የመተካት) ልምድ ይስተዋላል፡፡ ከላይ የጠቀስኩት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ግን፥ ለምሳሌ በእነዚህ ጥቅሶች (“ይህም” ሮሜ. 1፥4፤ “ሁላችሁ” 1 ቆሮ. 1፥10፤ “ይህ በመጀመሪያው… ሁሉ በእርሱ…” ዮሐ. 1፥2-3) “ሀ”ን በ “ኸ” አይተካም። ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ፥ እነዚህ ቃላት በዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ የቃላት ምርጫ መሠረት ተቀምጠዋል፡፡ የግእዝ ቃላትን በተጠቀምኩባቸው ቦታዎች ሁሉ ጥቅሶቹ የተወሰዱባቸውን የግእዝ መጻሕፍት (መጽሐፈ ቅዳሴ፥ መጽሐፈ ሰዓታት፥ ሃይማኖተ አበው፥ መጻሕፍተ ሐዲስ ኪዳን ወዘተ.) መልክዐ ፊደላትን ለማስቀመጥ ሙከራ

ተደርጓል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ እትም ላይ የተገደፉ ወይም በስሕተት የገቡ መልክዐ ፊደላት፥ በዚህኛው ኅትመት በተቻለ መጠን እርማት ተደርጎባቸዋል፡፡

በሥርዓተ አምልኮ ጥናት የሚታወቁትን የግሪክ እና ላቲን ስያሜያት[1] በግእዝ ፊደል የመጽሐፉ ዋና ክፍል ላይ ከጠቀስሁ በኋላ፥ የእንግሊዝኛ አቻ መጠሪያዎቻቸውን የኅዳግ ማስታወሻዎች[2] ላይ አስቀምጫለሁ፡፡ ከመጻሕፍት ወይም ጥናታዊ ጽሑፎች የተጠቀሰ ጥቅስ መሃል፥ የላቲኑ ተውሳከ ግስ [*sic*] ከተቀመጠ፥ ከዚህ ምልክት በፊት ያለው ቃል ስህተት ቢሆንም ጥቅስ ውስጥ ስላለ ሳይቀየር መቀመጡን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ ሦስተኛ ምዕራፍ ውስጥ ከግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት[3] የተወሰደ ጥቅስ በዚህ መልኩ ተቀምጧል፡- "ዘተውህበ በፈቃዱ ለሕማም ከመ ሞተ ይሥዓር፥ ወማእሠረ ሰይጣን ይብትክ፥ ወይኪድ ሲኦለ፥ ወቅዱሳነ ይምራሕ፥ ሥርዓተ ይትክል፥ ወትንሣኤሁ ያዕቅ [*sic*]::"[4] "ያዕቅ" ከሚለው ግስ አጠገብ [*sic*] የገባው፥ ግሱ ስሕተት እንዳለበትና ነገር ግን ጥቅስ ውስጥ ስለሚገኝ አንዳለ መቀመጡን ለማሳየት ነው፡፡ የታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ የተሳሰተውን ግስ አርሞ "ወትንሣኤሁ ያዑቅ"[5] (ትንሣኤውን ያሳውቅ ዘንድ) ይላል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወይም ቅዱሳን ስም አጠገብ "+" ምልክት ከዓ.ም. (ዓ.እ.) ጋር ሲቀመጥ ደግሞ፥ በተጠቀሰው ዓመት ማረፋቸውን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ "ቅዱስ ዮስጢኖስ ሰማዕት (+165 ዓ.እ.)" የሚለው አገላለጽ ሰማዕቱ ያረፈው በ165 ዓመተ እግዚእ መሆኑን ለመጠቆም ነው፡፡ በመጨረሻም፥ በኅዳግ ማስታወሻዎች፥ ለላቲኑ *Ibidem (Ibid*) አቻ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን "ዝኒ ከማሁ"[6] ተጠቅሜአለሁ፡፡ እነዚህ ቃላት አንድ ምንጭ (መጽሐፍ ወይም ጥናታዊ ጽሑፍ) ቀድሞ ከተጠቀሰ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው ጥቅስ ወይም አሳብ ከዚያው ምንጭ የተወሰደ መሆኑን ለማመልከት ያገለግላሉ፡፡

---

[1] Liturgical terminologies.

[2] Footnotes.

[3] Apostolic Tradition.

[4] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11-12።

[5] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 37፣ ገጽ 93።

[6] ይህን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ እና ግእዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሙት ታላቁ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ናቸው። *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* (አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ 1948 ዓ.ም.) ገጽ 253 "በድው" ከሚለው ቃል ቀጥሎ የመጣውን ቃል ማብራሪያ ይመልከቱ።

# መግቢያ

"አኰቴተ ቍርባን" በተሰኘው ስያሜ ውስጥ ያሉት ሁለት የግእዝ ቃላት፥ ምስጋና እና መሥዋዕት የሚሉትን ቃላት ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ መሥዋዕት ሆኖ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው (የቅዱስ ቍርባን) ምስጋና የሚል ትርጒም ይሰጡናል፡፡ "አኰቴተ ቍርባን" የቅዳሴው ሦስተኛ እና ዋነኛ ክፍል (ፍሬ ቅዳሴ) ውስጥ የሚገኘውን ጸሎተ ቍርባን የሚያመለክት መጠሪያ ነው፡፡ እያንዳንዱ አኰቴተ ቍርባን፡- አውሥኦ፥ መቅድም፥ በሕይወት ስላሉትና ስላረፉት የሚደረግ ጸሎት፥ ዝማሬ ሱራፌል፥ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ፥ ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ፥ ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ፥ ጌታ ያስተማረው ጸሎት (አቡነ ዘበሰማያት) እና የማጠቃለያ ምስጋና የተሰኙ ክፍሎች አሉት፡፡[7] በሌላ መልኩ "አኰቴተ ቍርባን" የቅዳሴው ክፍል ቢሆንም "ቅዳሴ" የሚለውንም ስያሜ ይተካል፤ "አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት" በሚለው ምትክ "ቅዳሴ ሐዋርያት" እንደምንለው ማለት ነው፡፡ እንዲሁም "አኰቴተ ቍርባን" የሚለውን ነጠላ ስያሜ፥ በብዙ ቍጥር ለመጠቀም "ቅዳሴያት" ብሎ መጻፍ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ላይ የሚደነቅ ጥናት ያደረገው ጀርመናዊው ኧርንስት ሃመርሽሚት፥ የግሪኩ ቃል *አናፎራ*[8] አቻ የሆነው የግእዙ "አኰቴተ ቍርባን" የግሪኩን *ኤቭኻሪስቲያ*[9] እና የላቲኑን *ሳክሪፊሰም*[10] እንደሚያስተረጒም ገልጾ፥ እነዚህ ሁለት ቃላት ምስጋና[11] እና መሥዋዕት ማለት ስለሆኑ ስያሜው የቅዳሴውን ዋነኛ ዓላማ እንደሚያስረዳ ጽፏል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፥ ቅዱስ ቍርባንን ለማክበር የምትጠቀምበትን ጸሎት "አኰቴተ ቍርባን" ብላ መጥራቷ ተገቢ መሆኑንና ይህ ስያሜ ሌሎች የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ለጸሎተ ቍርባኑ ከሰጡት መጠሪያ በተሻለ መልኩ የሥርዓተ አምልኮውን ምንነት እንደሚገልጽ

---

[7] የእነዚህን ክፍሎች ትርጒም ለመረዳት "መፍትሔ ቃላት" የሚለውን ከገጽ 344-350 ይመልከቱ፡፡

[8] Anaphero = to lift up (ከፍ ማድረግ፥ ማቅረብ) ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን anaphora የሚለው ቃል Eucharistic prayer (ጸሎተ ቍርባን) ማለት ነው፡፡

[9] *Evcharistia.*

[10] *Sacrificium.*

[11] Thanksgiving.

ጠቁሟል፡፡[12] ስለዚህ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክን ሥርዓተ ቅዳሴን ታሪካዊ ሂደት እና በውስጡ ያለውን የአምልኮ ውበት ለማስረዳት የተዘጋጀው ይህ መጽሐፍ "አኰቴተ ቊርባን" የሚል ዐቢይ ርእስ ተሰጥቶታል፡፡

ቅዳሴ በዘልማድ የሚደጋገም ሥርዓት ሳይሆን ለኃጢአታችን ቤዛ እና መሥዋዕት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላችን ሆኖ፥ በዓይን ከማይታዩ ቅዱሳን መላእክት ጋር ኅብረት የምናደርግበት በምድር ላይ ያለ ሰማያዊ አምልኮ ነው፡፡ በቅዳሴ ልዩና ፍጹም፥ ንጹሕና ቅዱስ የሆነውን ስመ እግዚአብሔር የማታመሰግን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ልትኖር አትችልም፡፡ ቅዳሴ፥ እግዚአብሔር አብ በአንድ ልጁ በጌታችንና በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላደረገው የማዳን ሥራ ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን ምስጋና የምታቀርብበት ምሥጢራዊ ሥርዓተ አምልኮ ነው፡፡ በክርስቶስ ደም የተቀደሰች አካሉና ሙሽራው የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አምልኮዋን ብቻ ሳይሆን እምነቷንም በቅዳሴ ትገልጻለች፡፡ ስለሆነም ቅዳሴ በዚህ ምድር ላለችው ማንኛዋም ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮዋ ማዕከልና የሕልውናዋ መሠረት ነው፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዋነኛ ዓላማ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ካህናትና ምእመናን ከልጅነት እስከ እውቀት ተሳታፊ በመሆን ያደጉበትን ሥርዓተ ቅዳሴ ውበት መግለጽና ስለ ቅዳሴው ጣዕም ያላቸውን መረዳት እንዲያስተውሉት ማድረግ ነው፡፡ ስለቅዳሴ መገለጫ ባሕርያት በምዕራፍ አንድ የተዘረዘሩት ነጥቦችና የቅዳሴውን ልዩ ልዩ ክፍሎች በዝርዝር የሚያስረዳው የመጽሐፉ የመጨረሻ ምዕራፍ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ያላትን ሰማያዊ ሀብት ልብ እንድንለውና እንድናደንቀው ያደርገናል ብዬ አምናለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ እንደምንታዘበው፥ የቅዳሴ ተሳታፊ በሆንን ቍጥር፥ ድምፃውያን ካህናትና ዲያቆናት ሲቀድሱ የድምፃቸውን ማማር ከማድነቅ በስተቀር በቅዳሴው ልባችን ተነክቶ ስለተሰማን ስሜት ስንናገር አንሰማም፡፡ ዲያቆኑ፡- "ንነጽር ሥነ ስብሐቲሁ ለአምላክነ"[13] (የአምላካችንን የምስጋናውን ውበት እንመልከት) እያለ፥ ዓይኖቻችን ሰዎችን ብቻ ያያሉ፡፡ የቅዳሴው ዓላማ ግን "አቤቱ የዕውቀት ዓይኖችን ስጠን፤

[12] Ernst Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras* (Stuttgart : Franz Steiner Verlan Wiesbaden GMBH, 1987) p. 38.

[13] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 9፣ ገጽ 270፡፡

ዘወትር አንተን ያዩ ዘንድ"[14] እንዲል፥ በውስጥ ዓይን (በዓይነ ልቡና) መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን ጌታ አይተን፥ ልባችንን (ልቡናችንን) ወደ አምላካችን ከፍ አድርገንና እርሱን አግኝተን ወደ ቤታችን እንድንመለስ ማድረግ ነው፡፡ ካህናቱና ዲያቆናቱ ለዘመናት የቀደሱትን፥ ምእመናንም ተሳታፊ የሆኑበትን ቅዳሴ ጣዕም ያውቁት እንደሆነ ይህ መጽሐፍ ይጠይቃል፤ አዳዲስ አሳቦችንም ያቀርባል፡፡ የዜማ ባለሞያ የሆኑ አንዳንድ ሊቃውንትም የቅዳሴውን አገልግሎት "የሰሞነኛ ሞያ ነው" እያሉ ችላ ስለሚሉት፥ ሥርዓተ ቅዳሴው በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምሥጢረ ቊርባን የሚፈጸምበት ሰማያዊ አምልኮ መሆኑን ተገንዝበው ተገቢውን ክብር እንዲሰጡት መጽሐፉ ይጠቁማል፡፡

ምእመናን በተለምዶ "ቅዳሴ ላስቀድስ ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ" ሲሉ እንሰማቸዋለን፡፡ ይህ አባባል ግን የቅዳሴው ተመልካቾች እንጂ ተሳታፊዎች እንደሆኑ አያመለክትም፤ ስለዚህ ልናርመው ይገባል፡፡ የቤተ ክርስያናችን ቅዳሴ-ተሰጥዎ ምእመናን ለዲያቆናቱ ትእዛዛትና ለካህኑ ጸሎታት በዜማ ሊመልሷቸው የሚገቡ ብዙ ዝማሬያትን ይዟል፡፡ ስለዚህ ምእመናን የቅዳሴው አካልና ተሳታፊዎች እንጂ ዳር ቆመው የሚመለከቱ አይደሉም፡፡ እንዲያውም ካህናቱ የቅዳሴው ተሳታፊ ለመሆን የመጡ ምእመናን መኖራቸውን ሳያረጋግጡ ቅዳሴ አይገቡም፡፡ በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት አንድ ካህን ብቻውን ሊጸልይ ይችላል፤ ብቻውን ሊቀድስ ግን አይችልም፡፡ ቅዳሴ ከምድራውያን ሰዎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሰማያውያን መላእክት ጋር ኅብረት የምናደርግበት በምድር ላይ የሚከናወን ውብ እና ሰማያዊ አምልኮ ነው፡፡ እንዲያውም *ሊቱርጊያ*[15] የሚለው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስያሜ፥ ቅዳሴ ለሕዝብ (የአንዲቷ ማኅበር አባላት ለሆኑ ምእመናን) የሚደረግ አገልግሎት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ምእመናን የቅዳሴው ተመልካቾች ብቻ ከሆኑ ራሳቸውን ከአማንያን ማኅበር (*ኤክሊሲያ*)[16] አገለሉ ማለት

---

[14] "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 81፣ ገጽ 137-138፡፡

[15] *Leitourgia* የሚለው ቃል የተገኘው *laos* (ሕዝብ) እና *ergon* (ሥራ) ከተሰኙ ሁለት የግሪክ ቃላት ሲሆን ማንኛውንም ዓይነት ማኅበራዊ አገልግሎት ያመለክታል። ከፊቱ *Theia* (መለኮታዊ/አምላካዊ) የሚለው ቅጽል ሲጨመርበት ግን፥ ቃሉ የሚውለው የቅዱስ ቊርባን ምሥጢር ለሚከናወንበት የተቀደሰ አገልግሎት (Divine Liturgy/ ቅዳሴ) ብቻ ነው። ለዝርዝሩ "Liturgy" በሚለው መግቢያ ሥር የካቶሊክ መዝገበ ቃላት ውስጥ የተጻፈውን ይመልከቱ፡- *NCE,* Vol. 8 (Washington D.C.: Catholic University of America, 2009) p. 727.

[16] ἐκκλησία [ekklēsia/ ecclēsia].

ነው፡፡ አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን የቅዳሴው ተመልካቾች (አስቀዳሾች) መሆን በቂ ስለሚመስላቸው የቅዳሴው መሥዋዕት (ቅዱስ ቍርባን) ተሳታፊዎች ሳይሆኑ (ሳይቆርቡ) ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ የቅዳሴው ዋነኛ ዓላማ ምእመናንን ወደ ሕይወት መድኃኒት (የጌታ ሥጋና ደም) መጥራት ስለሆነ፥ ቅዱስ ቍርባንን በሚቀበሉ ምእመናን ቍጥር ካቴድራሎቻችን እስኪጣበቡ ድረስ መሠረታዊ ግንዛቤዎችን የመፍጠርና የማስተማር ብዙ ሥራ ይጠብቀናል፡፡

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን ስናጠና፥ ስማቸው ባልተገለጸ ሰዎች ተደርሰው በሐዋርያትና ዓለም አቀፋዊ እውቅናን ባገኙ አባቶች ስም የተጠሩ ድርሳናትና ጸሎታተ ቍርባን እንዳሉ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ፥ በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ እና "እኁሁ ለእግዚእነ" (የጌታ ወንድም) ተብሎ በሚጠራው ቅዱስ ያዕቆብ ስም የተሰየሙ ጥንታውያን ቅዳሴያት አሉ፤ ነገር ግን በስማቸው ስለተጠሩ ብቻ የቅዳሴያቱ ደራስያን እነዚህ ሐዋርያት ናቸው ማለት አይደለም፡፡ በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ ቅዳሴ ማርቆስ በቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ስም ይጠራል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ግን ቅዱስ ቄርሎስ ቅዳሴውን ስለደረሰው ሳይሆን መጠነኛ ማሻሻያዎችን ስላደረገበት ነው፡፡ በተጨማሪ "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት"[17] በሚል ስያሜ የሚታወቀው የቅብጥ (ኮፕቲክ) ቅዳሴ በስሙ ተሰየመ እንጂ የዚህ አባት ድርሰት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ከታላላቆቹ ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል በእርግጠኝነት በስሙ የሚጠራውን አኰቴተ ቍርባን እንደደረሰ የሚነገርለት ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ሦስተኛ ምዕራፍ፥ የተለያዩ ታሪካዊና ጥናታዊ ማስረጃዎችን በመጥቀስ እንደ ሚሞግተው፥ አባዛኞቹ የቤተ ክርስያናችን ቅዳሴያት በ14ኛው እና 15ኛው ምእት ዓመታት በአገራችን ኢትዮጵያ ይካሄዱ የነበሩ የነገረ መለኮት ውጤቶች እንደሆኑና ለትሕትና ሲሉ ስማቸውን ባልነገሩን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ተደርሰው በቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም (አኰቴተ ቍርባን ዘአትናቴዎስ፥ ዘቄርሎስ፥ ዘዲዮስቆሮስ፥ ዘጎርጎርዮስ ወዘተ.) እንደተሰየሙ ስናነብ ግራ ልንጋባ አይገባም፡፡

የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ መግቢያው ላይ "[እንደ አባቶቻችን እንደ ግብፃውያን] ሥርዓት፥ ለቄስና ለዲያቆን ለሕዝቡም ሁሉ . . . የሚገባ የቅዳሴ

[17] Liturgy of St. Gregory the Theologian.

ሥርዓት”[18] ይላል፡፡ ይህ ማለት ግን የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ፥ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ኮፒ (ከግብፆች የተቀዳ) ነው ማለት አይደለም፡፡ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ የሾመልን የመጀመሪያው ጳጳስ አባ ሰላማ የተወሰኑ መጻሕፍተ ሥርዓትን ከግብፅ ይዞ እንደመጣ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ዘመን ተሻጋሪ ሥራ የሠሩልን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከመጽሐፈ ሲኖዶስና ከመጽሐፈ ኪዳን የተለያዩ ጸሎታተ ቅዳሴን በመውሰድ፥ ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍትና ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ጭምር አንዳንድ ዝማሬያትን መርጠው የቅዳሴው አካል በማድረግ ለቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ የተለየ ቅርጽና መልክ ሰጥተውታል፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ እና በኮፕቲክ ቅዳሴ መካከል ግልጽ የሆኑ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፤ ይህንንም የሁለቱን አብያተ ክርስቲያን መጻሕፍተ ቅዳሴ በማነጻጸር መረዳት ይቻላል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ሌላኛው ዓላማ ሥርዓተ ቅዳሴን በተመለከተ ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶቻችን ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ እውቅና እንድንሰጥ ጥሪ ማቅረብ ነው፡፡ ትሑታን የሆኑ ምሁራን አባቶቻችን ከውጪ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተተረጐሙ ቅዳሴያትን መሠረት አድርገው የሥነ መለኮት እሳቤያቸውን የሚያንጸባርቁ ቅዳሴ ያትን በመድረስ፥ ለሥርዓተ ቅዳሴው ማከናወኛ የሚሆኑ ትእዛዛትን[19] በመጽሐፈ ቅዳሴው በማስቀመጥ፥ በማኅሌትና በቅዳሴ አገልግሎት ለሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥቅስ ማውጫ (መጽሐፈ ግጻዌ) በማዘጋጀት የምንኮራበትን ኢትዮጵያዊ (ብሔራዊ) ሥርዓተ ቅዳሴ አስረክበውናል፡፡ ይህ መጽሐፍ የአገራችንን ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረታዊ ታሪኩንና እድገቱን ከአጠቃላይ ይዘቱ ጋር ጥናታዊ በሆነ መልኩ ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት እና የነገረ መለኮት ምሁራን መጽሐፉ ባቀረባቸው አሳቦች ላይ ዐውደ ጥናቶች በማካሄድና በመጽሐፉ ውስጥ የተመለከቷቸው ክፍተቶች ካሉም እነርሱን የሚሞሉ ቀጣይ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን በማዘጋጀት የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓተ ቅዳሴ አስመልክቶ ተጨማሪ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ቀሲስ መብራቱ ኪሮስ ገብሩ (Ph.D.)

[18] “ሥርዓተ ቅዳሴ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 1፣ ገጽ 4፡፡
[19] Rubrics.

# ምዕራፍ አንድ

## ቅዳሴ ምንድን ነው?

በ1960ዎቹ ከአውሮፓ ወደ ራሽያ የተጓዘ አንድ ጋዜጠኛ የራሽያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አሌክሲን (+1970 እ.አ.አ.) ቤተ ክርስቲያናቸውን ምን ብለው እንደሚገልጿት ጠይቋቸው ነበር። ፓትርያርኩም በአጭሩ፡- “ቅዳሴ የምትቀድስ ቤተ ክርስቲያን”[1] ሲሉ መልስ ሰጡ። ይህ መልስ በዓለም ውስጥ ያሉ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያንን በሙሉ ሊገልጽ የሚችል ትክክለኛ አባባል ነው። በማንኛውም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚፈጸሙት ምሥጢራት መካከል ምሥጢረ ቍርባን ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፤ በቅዱስ ቍርባን ሳይታተም የሚጠናቀቅ ምንም ዓይነት ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን የለምና። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ኅብስትና ወይን አቅርባ፥ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም ወደ መሆን የሚለወጥበት የቅዳሴ ሥርዓት፥ ከምታካሂዳቸው የአምልኮ አገልግሎቶች ሁሉ የላቀውንና ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል። ለኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፥ በቅዳሴ አገልግሎት ለሥሉስ ቅዱስ ምስጋና እያቀረበች መኖር ሕይወቷ ነው፤[2] ከዚህ ውብ የሆነ አምልኮ ውጪ ሌላ ሕይወት ሊኖራት አይችልም።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን “ቅዳሴ” የሚለው ቃል ቅዱስ ቍርባን የሚከብርበትን አገልግሎት ሲያመለክት፥ “ምስጋና” የሚለው ትርጒሙ

---

[1] የእንግሊዝኛው ትርጒም “A Church that celebrates the Divine Liturgy” ይላል፡፡ Robert Taft, *Beyond East and West: Problems in Liturgical Understanding* (Washington: Pastoral Press, 1989) p. 111.

[2] በመጽሐፈ ቅዳሴ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የምናገኘው ለሥሉስ ቅዱስ የሚቀርብ ምስጋና (trinitarian doxology)፡- “በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም - በአንድ ልጅህ በእርሱ ያለ ክብር ጽንዕ [ብርታት/ ኃይል - ራእ. 7፥12] ላንተ [ለእግዚአብሔር አብ] ይገባል፤ ከእርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፥ አሜን።” *መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ እና በአማርኛ ከነምልክቱ* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡ 2000 ዓ.ም.) ቊ. 117፡ ገጽ 61-62።

ደግሞ የግሪኩ (ጽርእ) ቃል *ኤቭኻሪስቲያ*[3] አቻ ነው። ከምስጋና ባሻገር "ቅዳሴ" የሚለው ቃል፥ "ቅድሳት"[4] በመባል የሚታወቀውን የጌታን *ሥጋውንና* ደሙን ተቀብለው ካህናቱና ምእመናኑ የሚያገኙት የቅድስና ሕይወትን ያመለክታል። ስለዚህ "ቅዳሴ" የሚለውን ቃል በሰማን ቍጥር፥ "መቀደስ፣ መለየት" የሚሉ ቃላትም አብረው ወደ አእምሮአችን ይመጣሉ። በንባብም ሆነ በትርጉም ለግእዙ በቀረበ አጠራር የግብፅ (ቅብጥ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ ቅዳሴን *ቊዳስ*[5] ብላ ስትጠራው፥ በተመሳሳይ መልኩ የም*ሥ*ራቅ ሶርያ ቤተ ክርስቲያን[6] ደግሞ *ቊዳሻ*[7] ትለዋለች። የአንጾኪያ መንበር ወራሽ በሆነችው የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴው አገልግሎት *ቊርባና*[8] ይባላል። የም*ሥ*ራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሚል የጋራ ስም የሚጠሩ አብያተ ክርስቲያን፥ የቢዛንቲን *ሥ*ርዓተ አምልኮ[9] ተከታዮች ሲሆኑ፥ እኛ "ቅዳሴ" ብለን የምንጠራውን ውብ አምልኮ፥ *ሊቱርጊያ* ይሉታል። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፥ በላቲን ቋንቋ *ኢቴም አሊያ ሚሳ*[10]

---

[3] Ευχαριστία = thanksgiving.

[4] "በእንተ ቅድሳት ሰላማዊት ሰላመ ናስተበቍዕ" በማለት የሚጀምረውን የልመና ጸሎት ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን ቅዳሴው መጀመሪያ ክፍል ውስጥ ያነባል። "ቅድሳት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥ*ጋውንና ደሙን ነው። ሠራዒው ካህንም "ቅድሳት ለቅዱሳን" ብሎ ሲያዜም "ቅድሳት" ብሎ የሚጠራው የጌታን *ሥ*ጋና ደም ነው። "በእንተ ቅድሳት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 66፣ ገጽ 51፤ "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 90፣ ገጽ.118።

[5] *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory, and Cyril* (Los Angeles: Coptic Orthodox Diocese of Southern United States, 2001) p. 75.

[6] The Assyrian Church of the East.

[7] Stephen B. Wilson, "The anaphora of the Apostles Addai and Mari," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Paul F. Bradshaw (Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1997) p. 20.

[8] እኛ "ቍርባን" የሚለውን ቃል ከሶርያ ቋንቋ ነው የወሰድነው። ቃሉን የምንጠቀምበት ግን ለእግዚአብሔር የቀረበ ወይም የሚያቀርቡት (offering) በሚል ትርጉም ለመሥዋዕቱ ብቻ ሲሆን፥ ሶርያውያን ይህን ቃል ለመሥዋዕቱ እና መሥዋዕቱ ለሚቀርብበት አገልግሎት (ለቅዳሴው) ያውሉታል። "Glossary," *Dionysius Bar Salibi: Commentary on the Eucharist*, trans. Baby Varghese (Kottayam: Anaswara Printers, 1998) xvi.

[9] Byzantine Liturgy.

[10] "*Item alia missa*." "Mass" የሚለውን ማውጫ ይመልከቱ፡- *The Catholic Encyclopedia: An International Work of Reference on the Constitution, Doctrine, Discipline and History of the Catholic Church* (New York: Robert Appleton Company, 1910) p. 791.

ከሚለውና የሕዝቡን ማሰናበቻ (ሥርሖተ ሕዝብ) ከሚያመለክተው ዓረፍተ ነገር ተነስታ፥ በአቀራረቡም ሆነ በምሥጢሩ ከኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያን የተለየውን የቅዳሴ አገልግሎቷን *ሆሊ ማስ*[11] በማለት ትጠራዋለች።

በዚህ ምዕራፍ፥ የሥርዓተ ቅዳሴ መለያ ባሕርያትን፣ በውስጡ ያለውን የአምልኮ ውበትና የቅዳሴው ሙሉ ተሳታፊ ስንሆን የምናገኛቸውን መንፈሳዊ ዕሴቶች (ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ያለውን ጥቅም) ለማሳየት እሞክራለሁ።

## 1.1. የቅዳሴ መገለጫ ባሕርያት

በመንበረ ቍስጥንጥንያ በ398 ዓ.እ. ጵጵስና ተሹሞ የነበረው ታላቁ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በማቴዎስ ወንጌል ላይ በጻፈው ድርሳን ስለ ቅዳሴው መሥዋዕት ታላቅነት ሲናገር፦ “መላእክት ከክብሩ ነጸብራቅ የተነሣ ያለ ፍርሃት ሊያዩት የማይቻላቸውንና የሚንቀጠቀጡለትን እኛ እንመገበዋለን፤ ከክርስቶስ *ሥጋ* ጋርም አንድ አካል እንሆናለን”[12] ብሏል። ይህ ታላቅ ምሥጢር የሚፈጸምበት አገልግሎት ከልዑል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ የፍቅር ስጦታ ነው። ስለሆነም ቅዳሴ የክርስቶስን ሕማም፥ ሞትና ትንሣኤ እያሰብን፥ እግዚአብሔር አብ በአንድ ልጁ ሞት ላሳየን ዘላለማዊ ፍቅር ምስጋና የምናቀርብበት አምልኮ ነው። የዚህን ታላቅ አምልኮ መገለጫ ባሕርያት በሚገባ ለመረዳት የሚከተሉትን አምስት ነጥቦች በቅደም ተከተል እንመለከታለን፦

- ቅዳሴ የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት የሚቀርብበት ዐቢይ ሥርዓተ አምልኮ ነው።
- ቅዳሴ የክርስቶስን የማዳን ሥራ እውን የሚያደርግልን የምስጋና አገልግሎት ነው።
- ቅዳሴ በምድር ላይ ያለ ሰማያዊ አገልግሎት[13] ነው።
- ቅዳሴ የሰማያዊው አምልኮ ነጸብራቅ ነው።
- ቅዳሴ በደስታና በሐሤት የሚከናወን አምልኮ ነው።

---

[11] Holy Mass.

[12] *The Homilies of St. John Chrysostom on the Gospel of Matthew*, Homily 82, Part V, trans. Members of the English Church (Oxford: John Henry Parker, 1851) p. 791.

[13] በእንግሊዝኛ “heaven on earth service” ይባላል፡፡

## ፩. የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት የሚቀርብበት ዐቢይ ሥርዓተ አምልኮ

ከአዳም ጀምሮ እስከ ዘመነ ነቢያት ድረስ፥ የሰው ልጅ በቀዳማዊው አዳም በደል ምክንያት የእግዚአብሔር ጸጋ ከራቀው በኋላ የስንዴና የወይንን ቍርባን እንዲሁም የእንስሳትን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በማቅረብ የአምላኩን ፊት ይፈልግ እንደ ነበር ቅዱሱ መጽሐፍ ያስተምረናል።[14] በብሉይ ኪዳን ይቀርቡ ከነበሩ የተለያዩ የመሥዋዕት ዓይነቶች፥ በዋነኝነት "የእግዚአብሔር በግ" ተብሎ በዮሐንስ መጥምቅ ለተገለጸው (ዮሐ. 1፥26) ለአዲስ ኪዳኑ መሥዋዕት ምሳሌ የነበሩት፡-

- የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ አብራምን[15] በባረከ ጊዜ ያቀረበው ኅብስትና ወይን (ዘፍጥ. 14፥18-20)፥
- በልጁ በይስሐቅ ፈንታ አብርሃም ለመሥዋዕትነት ያቀረበው በግ (ዘፍጥ. 22፥ 1-13)፥
- እስራኤላውያን (በመጀመሪያው ወር፡ በአሥረኛው ቀን) ይሠዉት የነበረው የፋሲካው በግ (ዘጸ. 12፥1-14) እና
- "ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ" ባለው መሠረት እግዚአብሔር ለእስራኤላ ውያን የሰጣቸው የሰማይ እንጀራ (መና) ናቸው። (ዘጸ. 16፥ 4-16) ።

ካህኑና ንጉሡ መልከ ጼዴቅ የዘላለማዊው ሊቀ ካህናት የክርስቶስ ኢየሱስ ምሳሌ (መዝ. 109፥4፤ ዕብ. 5፥ 6-10) በመሆንና የአዲስ ኪዳኑን መሥዋዕት በምሳሌነት የሚያሳይ ኅብስትና ቍርባን በማቅረብ ወደ ፊት የሚመጣውን በዘመኑ እንደ ተፈጸመ ሆኖ አይቷል ። በይስሐቅ ፋንታ አብርሃም በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ የመጣውን በግ እንደሠዋው፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የእኛን ኃጢአት ተሸክሞና ዕዳችንን ከፍሎ ጸጉሩን በሚሸልተው ሰው ፊት ዝም እንደሚልና እንደማይናገር በግ[16] መከራ መስቀልን ተቀብሎ በደሙ ከኃጢአታችን አጠበን። (1ጴጥ. 2፥23-

[14] ለምሳሌ፡- ዘፍጥ. 4፥4፤ ዘፍጥ. 8፥20-21፤ መሳ. 6፥25-26 እና 1ነገሥ. 18፥30-38።

[15] በዚህ ጊዜ ስሙ "አብራም" ነበር። ስሙ የተቀየረው የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው ከሆነ በኋላ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶ "ከዛሬ ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና" (ዘፍ. 17፥5) ያለው ጊዜ ነው።

[16] "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 129፣ ገጽ 260።

25፤ ራእ. 1፥6)። አይሁድ የፋሲካውን ጠቦት ሠውተውና ሥጋውን የሚበሉበትን ቤት መቃን በደሙ ቀብተው ግብፃውያን ከተቀሠፉበት ከሞተ በኵር እንደ ዳኑ፥ እኛም ክብርና ምስጋና ይግባውና በታረደልን በፋሲካችን ክርስቶስ (1ቆሮ. 5፥7) ከዘላለማዊ ሞት ድነናል። እንዲሁም እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ከሰማይ የላከላቸውን እንጀራ (መና) በምድረ በዳ እንደ በሉ፥ "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ" (ዮሐ. 6፥51) ተሰጥቶናል። እስራኤላውያን በልተውት ሞትን ካስከተለው መና በእጅጉ የሚበልጠው፥ ሰው በልቶት እንዳይሞት (በሕያውነት እንዲኖር) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን ኅብስተ ሕይወት ሥጋውን እንደ ሆነ፡- "ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው" ሲል በግልጽ ነግሮናል (ዮሐ. 6፥51)።

ከሞት የምንድንበት መድኀኒት አድርጎ ሥጋውን እንደ ሰጠን የነገረንና "ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" (ዮሐ. 6፥54) ብሎ ያስተማረን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ፥ ሥጋውንና ደሙን የምንቀበልበትን ሥርዓተ ቍርባን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን ለማድረግ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ መሥርቶልናል (ማቴ. 26፥17-29)። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘው ታላቁ አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ በምሴተ ኀሙስ የቍርባንን ሥርዓት የመሠረተው ጌታ አሁንም ቅዱስ ቍርባንን እንደሚያከብር ሲያስረዳ፡- "በመጨረሻው እራት ላይ ያን [የቅዱስ ቍርባን] ምሥጢር ያከናወነውና ኅብስቱንና ወይኑን ለውጦ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው፥ አሁንም ያንኑ ያደርጋል . . . ይህ [ምሥዋዕ] ከምሴተ ሐሙሱ ጠረጴዛ ጋር አንድ ነው፤ በምንም ነገር ከዚያ አያንስም"[17] በማለት ጽፏል። በሰው እጅ በተሠራችው ቅድስተ ቅዱሳን ስለ ራሳቸውና ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የእንስሳት መሥዋዕት ያቀርቡ እንደነበሩት እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሊቃነ ካህናት ሳይሆን፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት ዘላለማዊ ክህነት ያለው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ሥጋ አንድ ጊዜ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረቡ ተቀድሰናል (ዕብ. 10፥10 እና 7፥27)። ይኸውም መሥዋዕት በአባቱ በእግዚአብሔር (በእግዚአብሔር አብ) እጅግ የተወደደና መልካም መዓዛ ያለው

[17] *The Homilies of St. John Chrysostom on the Gospel of Matthew*, Homily 82, V, p. 1092.

*መሥዋዕት* ነው። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ “*ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ - ራሱን ያማረ መሥዋዕትና ዕጣን አድርጎ ለአባቱ ያሳረገ*”[18] እንዲል።

የኑሲስ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ጎርጎርዮስ እንደጻፈልን፥ መድኃኒታችን ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን የተሠዋው “[የ*መሥዋዕቱ* በግ] እርሱ ነው ፤ የሚሠዋ (*መሥዋዕቱን* የሚያሳርግ) ካህን እርሱ ነው ፤ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፥ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም *መሥዋዕት* የሚቀበል እርሱ ነው።”[19] ስለዚህ ምንም እንኳ በቤተ መቅደሱ ካህናት *መሥዋዕተ* ቅዳሴውን ቢያቀርቡም የቀራንዮው *መሥዋዕትና* የ*መሥዋዕቱ* ብቸኛ አሳራጊ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን አሳብ በዝርዝር ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡- “አሁንም [የቅዳሴው ጊዜ] እርሱ ክርስቶስ ያለበት ያ የመጨረሻው እራት እንደሆነ እመኑ፤ ይህ ከዚያ በምንም የተለየ አይደለምና። የአሁኑን *መሥዋዕት*፥ ሰው [ምድራዊ ካህን]፥ የዚያኛውን ደግሞ ክርስቶስ ያደረገው አይደለም፤ ሁለቱም የራሱ የክርስቶስ *ሥራዎች* ናቸው እንጂ። ስለዚህ ካህኑ [ቅዱስ ቍርባንን] በሚያቀብላችሁ ጊዜ፥ [በካህኑ አድሮ የተዘረጋው] የክርስቶስ እጅ እንደሆነ እንጂ፥ ካህኑ እንዳቀበላችሁ አታስቡ።”[20] ከላይ የተጠቀሱትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳቦችንና የኦርቶዶክሳውያን አበው አስተምህሮን መሠረት በማድረግ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር በቅዳሴ የአዲስ ኪዳኑን *መሥዋዕት* (የጌታን *ሥጋ*ና ደም) እየሠዋች ልጆቿን ወደ ሕይወት መድኃኒት ትጠራለች።

ወደ ሁለተኛው የቅዳሴ መገለጫ ባሕርይ ከማለፋችን በፊት ስለቅዳሴው *መሥዋዕት* (ቅዱስ ቍርባን) ሁለት ነጥቦችን እንመለከታለን።

---

[18] “*ሥርዓተ ቅዳሴ*” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 122፣ ገጽ 62-63።

[19] “ዘጎርጎርዮስ” *ሃይማኖተ አበው* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1986 ዓ.ም.) ምዕራፍ 36፡ ክፍል 3፡ ቍ. 26፣ ገጽ 126።

[20] *The Homilies of St. John Chrysostom on the Gospel of Matthew*, Homily 82, V, p. 683.

## ቅዱስ ቊርባን፡ አማናዊ መሥዋዕት

ቅዱስ ቊርባን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቀራንዮ የተሠዋው አማናዊው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቀራንዮው መሥዋዕት የተለየ ሌላ መሥዋዕት በቅዳሴ ጊዜ በፍጹም አትሠዋም። ይህንን አቋም ግልጽ የሚያደርግልንና ሠራዒው ካህን በቅዳሴ ጊዜ ቅዱስ ቊርባንን ከመቀበሉ በፊት የሚጸልየው ጸሎት መጀመሪያው ላይ (ሲጀምር) እንዲህ ይላል፦

> አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፥ ደስ የሚያሰኝህ መሥዋዕት የልጅህ ሥጋ እነሆ፤ በዚህም ኃጢአቴን ሁሉ አቃልልኝ፥ ስለእኔ አንድ ልጅህ ሙቷልና። ስለእኔ በቀራንዮ የፈሰሰ ንጹሕ የሚሆን የመሚሕህም ደም፥ እነሆ ስለ እኔ ይጮኻል። ይህ የሚናገር ደም የእኔን የባሪያህን ኃጢአት የሚያስተሠርይ ይሁን።[21]

ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስ ክርስቶስ "አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ" (ዕብ. 10፥10) ሁለመናችንን ከቀደሰበት የሥጋውና የደሙ መሥዋዕት ሌላ የተለየ መሥዋዕት ቤተ ክርስቲያናችን የላትም። በየዕለቱ ካህናቱ በቀደሱ ቊጥር በተደጋጋሚ መሥዋዕቱ ቢቀርብም፥ ያው አንድ ጊዜ በቀራንዮ ኮረብታ ላይ የተሠዋው መሥዋዕት ነው።

እውነታው ይህ ሲሆን፥ አግዛቸው ተፈራ የተባለ ግለሰብ "ጥላና አካል" በተሰኘው መጽሐፉ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ኪዳኑን መሥዋዕት ያቀረበው ብቸኛው ሊቀ ካህናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እንደምታምን ከገለጸ በኋላ፥ "ሆኖም ግን በተጨማሪነት ክርስቶስ አንድ ጊዜ እንዳቀረበው ያለ መሥዋዕት ቀሳውስት ዛሬ እንደሚሠዉ፥ ይህም መሥዋዕት ሥጋና ደሙ እንደሆነ ይታመናል"[22] ይላል። ቅዱስ ቊርባን "የጌታ እራት መታሰቢያ ነው" የሚለውን ፕሮቴስታንታዊ ትምህርት የሚደግፍለት ስለመሰለውም፥ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሳን[23] "እመቦ ዘይብል 'አኮኑ ናዐርግ መሥዋዕተ ኵሎ ዕለተ?' ንብሎ ንሠውዕ ለተዝካረ ሞቱ ለልዑል፥ መሥዋዕተ አሐተ፥ ወአኮ ብዙኀ"[24]

---

[21] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 2000፣ ቊ.105-106፣ ገጽ 122-123።

[22] አግዛቸው ተፈራ፡ *ጥላና አካል* (አዲስ አበባ፡ [የማተሚያ ቤቱ ስም ያልተጠቀሰ] 1995 ዓ.ም.) ገጽ 131።

[23] በዕብራውያን መልእክት ላይ የጻፈው ትርጓሜ፡፡

[24] *ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ* "አሥራ ሰባተኛ ድርሳን"፡ (አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.) ቊ.121-122፣ ገጽ 308።

የሚለውን ጠቅሶ ያልተሟላ የአማርኛ ትርጉሙን እንዲህ ሲል ያስቀምጣል፡- "እኛስ በየዕለቱ ሁሉ መሥዋዕት እንሠዋ የለምን?' የሚል ሰው ቢኖር፥ እኛስ ለልዑል ጌታ ለሞቱ መታሰቢያ እንሠዋለን እንለዋለን።"[25]

እዚህ ላይ አግዛቸው ተፈራ በሁለት ነገር እንደ ተቸገረ እንረዳለን። አንደኛ፥ ኦርቶዶክሳዊው አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ቤተ ክርስቲያን የምታቀርበውን ቅዱስ ቍርባን "*መሥዋዕት*" ብሎ መጥራቱ ሊያስተላልፈው ለፈለገው መልእክት አልመች ብሎታል። ይኸውም ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ጠቅሶ ሲጽፍ፥ ይህ አባት "ቅዱስ ቍርባንን "*መሥዋዕት*" በማለት የሚጠራው ቢሆንም"[26] በሚለው አገላለጹ፥ አግዛቸው ቅዱስ ቍርባን አማናዊ *መሥዋዕት* መሆኑን አንደማያምን አሳይቶናል። ሌላው፥ አግዛቸው የጠቀሰውን የቅዱሱን አባት ጥቅስ ስንመለከት፤ ትርጉሙ አግዛቸው ለፈለገው ዓላማ እንዲመች አድርጎ እንደተረጐመው ሳይሆን፥ "እኛስ በየዕለቱ *መሥዋዕት* እንሠዋ የለምን?" ብሎ ለሚጠይቅ ሰው ዮሐንስ አፈወርቅ የሰጠው መልስ፡- "እኛስ ለልዑል ጌታ ለሞቱ *መታሰቢያ* ልትሆን ብዙ ያይደለች፥ አንዲት *መሥዋዕት* ዕለት ዕለት እንሠዋለን እንለዋለን"[27] የሚል ነው። ጸሐፊው "*መሥዋዕተ* አሐተ፥ ወአኮ ብዙኀ"[28] የሚለውን የግእዝ ሐረግ የአማርኛ ትርጉም ቆርጦ ያወጣበት ምክንያት፥ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ የምትሠዋው *መሥዋዕት* ያው በቀራንዮ የተሠዋው አንዱ *መሥዋዕት* እንጂ ሌላ የተለየ *መሥዋዕት* አለመሆኑን በግልጽ ስለሚያመለክት ነው። አግዛቸው ደግሞ ይህን አሳብ ይቃወማል፤ ስለሆነም የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አባባል የሚያሳየው፥ የኦርቶዶ-ክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት እንጂ ጸሐፊው ሊያስተላለፈው የፈለገውን የተዛባ መልእክት አይደለም።

እንዲያውም እዚሁ ድርሳን ላይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ከቀራንዮው *መሥዋዕት* የተለየ ሌላ *መሥዋዕት* በፍጹም እንደማንሠዋ በዝርዝር ሲያስረዳ፡- "*መሥዋዕቱ* በየዕለቱ [ዛሬ በቤተ ክርስቲያን] እየተሠዋ እንዴት አንድ *መሥዋዕት* ሊባል ይችላል?"

---

[25] አግዛቸው ተፈራ፡ *ጥላና አካል*፡ ገጽ 132።

[26] ዝኒ ከማሁ።

[27] *ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ*"ዐሥራ ሰባተኛ ድርሳን"፡ ቍ. 122፣ ገጽ 308።

[28] አንዲት እንጂ፥ ብዙ ያይደለች *መሥዋዕት*፡፡

ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር "በመስቀል አንድ ጊዜ ስለተሠዋ ነው ብዬ" [29] እመልስለታለሁ ይላል። ስለዚህ እንደ ቅዱስ አባታችን ዮሐንስ አፈ ወርቅ ትምህርት፥ "በመስቀል አንድ ጊዜ የተሠዋውን መሥዋዕት ሁል ጊዜ እንሠዋለን" [30] እንጂ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን የሚነቅፉ ሰዎች እንደሚናገሩት "ዛሬም ነገም ለዋውጠን ልዩ ልዩ *መሥዋዕት* የምንሠዋ አይደለንም፡፡"[31] ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ራሱን *መሥዋዕት* አድርጎ በቀራንዮ እንዳቀረበ፥ "ዛሬ [የምንሠዋው *መሥዋዕት*] ያን ጊዜ የተሠዋው ነው"[32] እንጂ የብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት "ለክርስቶስ ምሳሌ ሊሆን ላም፣ በግ ይሠዉ እንደ ነበር ለክርስቶስ ምሳሌ የሚሆን [ሌላ] *መሥዋዕት* አንሠዋም።"[33]

በተጨማሪም ይህ አባት፥ ምንም እንኳ ክርስቶስ በዓራቱ ማዕዘን (በመላው ዓለም) በተለያዩ ክርስቲያኖች በምሥጢረ ቊርባን አማካይነት ለመሥዋዕትነት ቢቀርብም፥ "በዓራቱ ማዕዘን የሚሠዋው *ሥጋው* አንድ ነው"[34] ብሎ በአጽንዖት ይናገራል። በተዋሕዶ *ሥጋ* የመለኮትን ባሕርይ፥ ይኸውም ምሉዕ በኵለሄ (በዓለሙ መልቶ መገኘትን) ገንዘቡ (የራሱ) ስላደረገ፥ በዚህ ምድር በተለያየ ቦታ ቅዳሴ ሲቀደስ፥ *መሥዋዕት* ሆኖ የሚቀርበው በሁሉም ቦታ መገኘት የሚችለው አንዱ የክርስቶስ *ሥጋ* ነው ማለት ነው። የዚህን ቅዱስ አባት ትምህርት መሠረት በማድረግ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን በመልክዐ ቊርባን የሚከተለውን ዘምረዋል፡-

- እንዘ ብዙኃን ንሕነ እም *ፆታ* ዘመን ዘዚአሁ
- ነአምን ሞቶ ወንሴፎ ትንሣኤሁ
- ለእግዚእ ክርስቶስ ዘኢይትአተት ጿጋሁ
- መለያልየ አሐደ ይረስየነ ምስሌሁ
- በአጽናፈ ዓለም ይጠባሕ አሐዱ *ሥጋሁ* ። [35]

---

[29] *ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ* "ዐሥራ ሰባተኛ ድርሳን"፡ ቊ.124፣ ገጽ 308.።

[30] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ.124፣ ገጽ 309.።

[31] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ.125፣ ገጽ 309.።

[32] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ.132፣ ገጽ 309.።

[33] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ.136፣ ገጽ 309.።

[34] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ.126 እና 129፣ ገጽ 309.።

[35] *መጽሐፈ ሰዓታት ምስለ ኵሉ ጸዋትዊሁ ወባሕረ ሐሳብ፡* "መልክዐ ቊርባን" (*አሥመራ*፡ ኮከበ ጽባሕ ቤተ ማኅተም፡ 1975 ዓ.ም.) ገጽ 515

ይህም ወደ አማርኛ ሲተረጐም፦ ከእርሱ [ከክርስቶስ] ዘመን ወገን የሆንንና ብዙዎች ስንሆን፥ ጸጋው የማይጎድል የክርስቶስን ሞት እናምናለን፥ ትንሣኤውንም ተስፋ እናደርጋለን። ከእርሱ ጋር አንድ አካል ያደርገን ዘንድ[36] አንዱ ሥጋው በዓለም ሁሉ ይታረዳል [ይሠዋል][37] ማለት ነው። እውነት ነው፤ በዕለተ ዓርብ ኃጢአታችንን ተሸክሞና ስለ መተላለፋችን ቆስሎ ለኃጢአት ይቅርታ የራስ ቅል ስፍራ በሆነው በጎልጎታ ኮረብታ መስቀል ላይ የተሠዋው የእግዚአብሔር በግ (1ቆሮ. 5፥7) አሁንም በዓለሙ ሁሉ ተበትና ባለችው በአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ፥ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል።

ምናልባት "በመስቀል ላይ ሥጋው ሲቆረስ፥ ደሙ ሲፈስስ ታይቷል፤ በቅዳሴ ላይ በሚሠዋው መሥዋዕት ግን ይህንን አናይም" የሚል አስተሳሰብ ቢነሣ፥ ሊቃውንት አባቶቻችን እምነታቸውን በግልጽ በማሳየት በመልክዐ ቍርባን የቋጠሯቸው ስንኞች ጥሩ መልስ ይሆናሉ፦

- ጊዜ ይሠዋዕ ኅብስተ ሥጋከ እመልክዐ ሥጋ ፍሉጥ
- ወደምከ ወይን እምደመ ጠባይዕ ውሉጥ
- መሥዋዕተ መድኃኒት ክርስቶስ ለሥርየተ ኃጢአት ሥሉጥ
- ንሕነሰ እግዚኦ በዓይነ ሕሊና ምሱጥ
- ፍጹመ ሥጋዌከ ንሬኢ እምውስጥ ።[38]

የዚህም የአማርኛ ትርጉም፦ "ከሥጋ መልክ የተለየው የሥጋህ ኅብስት፥ ከደምም ባሕርይ ልዩ የሆነው ደምህ [በአርአያ ኅብስትና ወይን የሚቀርበው ሥጋህና ደምህ] በተሠዋ ጊዜ፥ ኃጢአትን ለማስተስረይ ሥሉጥ የሆንክ (ሥልጣን ያለህ) የድኅነት (የመዳን) መሥዋዕት ክርስቶስ ሆይ! አቤቱ እኛስ ፍጹም ሰው መሆንህን በውስጡ የሕሊናችን ዓይን (የእምነት ዓይን) ተመስጠን እናያለን" የሚል ነው። ይህም የአባቶቻችን አገላለጽ በቅዳሴ ሰዓት ስለ ኃጢአታችን የታረደውን በግ በውስጥ ዓይናችን እያየን የሥጋውና ደሙን ምሥጢር በእምነት መቀበል እንደሚገባ እንጂ

---

[36] "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ" (1ቆሮ. 12፥27)፤ "የአካሉ ብልቶች ስለ ሆንን . . ." (ኤፌ. 5፥30)።
[37] "ሠ" ጠበቅ ብሎ መነበብ አለበት።
[38] *"መልክዐ ሕማማተ መስቀል፥ መልክዐ መድኃኔ ዓለም፥ መልክዐ ቍርባን፥ ወመልክዐ እግዚአብሔር አብ"* ([የታተመበት ከተማ ያልተጠቀሰ]፡ ቀይ ባሕር ማተሚያ ቤት፡ 1977 ዓ.ም.) ገጽ 33።

እምነት-አልባ በሆነ አመለካከት በውጪያዊው ዓይናችን የሚታይ ሥጋና ደም መጠበቅ እንደሌለብን ያስተምረናል።

እዚህ ላይ በተጨማሪ ልብ ልንለው የሚገባ አንድ ነጥብ አለ። የቅዱስ ቊርባን ምሥጢር የሚከናወነው የፍጡራን አእምሮ ሊገነዘበው በሚችለው መልኩ ስላለሆነ ሠራዒው ካህን፥ መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና በወይኑ ላይ እንዲወርድ ጠይቆ መሥዋዕቱ ከተለወጠ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር መለወጡን አምነን "ሥጋሁ ወደሙ" (የጌታ ሥጋውና ደሙ) እንለዋለን እንጂ በፍጹም ኅብስትና ወይን ብለን አንጠራውም።[39] እንዲያውም ጻጋ እግዚአብሔር በዝቶላቸው የቅድስና ደረጃ ላይ የደረሱና በሚቀድሱበት ሰዓት እኛ ልናየው የማንችለውን ድንቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተረዱ፥ እንዲሁም የቅዳሴውን መሥዋዕት (የታረደውን በግ) በግልጽ በምሥዋዑ ላይ ያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ነበሩ። ለምሳሌ፥ በእኛ ቤተ ክርስቲያን "አረጋዊ መንፈሳዊ" በሚል መጠሪያ የሚታውቀውና በ8ኛው ምእት ዓመት የነበረው የምሥራቅ ሶርያ አባት አባ ዮሐንስ ዘዳልያታ[40] መሥዋዕተ ቅዳሴ እያቀረበ ሳለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበግ ጠቦት እና በሕፃን መልክ ይገለጽለት እንደ ነበር ሲጽፍ፦ "እቀድስ ዘንድ በጀመርኩ ጊዜ ስለሁሉ ቤዛ ራሱን የሠዋ ጌታን በማይመረመር ብርሃን በግዕ [የበግ ጠቦት]፤ [እንዲሁም] ሕፃን መስሎ አየሁት . . . ሳየውም ደነገጥሁ፥ አደነቅሁም። ልቡናዬ ተለወጠ፥ ነፍሴና ሥጋዬም በፍቅሩ እንደ

[39] ለዚህም ነው ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን ካህናቱና ምእመናኑ የቅዳሴውን መሥዋዕት ከተቀበሉ በኋላ "ተመጠነ እምሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ - ከክርስቶስ ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ተቀበልን" እያለ የሚያዜመው። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "እም ድኅረ ተመጠዉ ሕዝብ" ቍ 132፣ ገጽ.129። ሠራዒው ካህንም በሚያቀብልበት ጊዜ እንደተቀደሰው ቅዳሴ ዓይነት በተለያየ መልኩ፦ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ"፥ "የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ" ወይም "ከሁላችን እመቤት ከማርያም የነሣው እውነተኛ የሚሆን የአምላካችን የአማኑኤል ሥጋ" በማለት የተለወጠውን መሥዋዕት እንደሚጠራውና ንፍቁ ካህን ደግሞ ጽዋውን ይዞ ሲያቀብል፦ "ይህ የሕይወት ጽዋ ከሰማይ የወረደ የክርስቶስ ክቡር ደሙ ነው" እንደሚል ልብ ልንል ይገባል። ዝርዝሩን በመጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 115 እና 120፣ ገጽ 125 እና 127 ላይ ይመልከቱ።

[40] "ዳልያታ" ማለት የወይራ ቅርንጫፎች ማለት ሲሆን በ690 ዓ.እ. በኢራቅ ሰሜናዊ ምሥራቅ ግዛት የተወለደው አባ ዮሐንስ፥ ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ ከመነኮሰባትና ቱርክ ድንበር ላይ ከምትገኘው ከቃርዱ ገዳም ወጥቶ ጾጥታ በሰፈነበት "ዳልያታ" በሚባል ሥፍራ እስካረፈበት ጊዜ (780 ዓ.እ.) በብሕትውና ስለኖረ፥ ዮሐንስ ዘዳልያታ (John of Dalyatha) በመባል ይታወቃል። ይህ አባት ከደረሰበት የፍጹም መንፈሳዊነት ደረጃ የተነሣ "አረጋዊ መንፈሳዊ - The Spiritual Elder" ተብሎም ተጠርቷል። See "Introduction," The Letters of John of Dalyatha, trans. Mary T. Hansbury (New Jersey: Gorgias Press, 2006) vii.

እሳት ተቃጠለ። ከዚህ ድንቅ ነገር የተነሣ የምሠራውን አላወቅሁትም። ልቡናዬ በፍቅሩ ስለተቃጠለ መልኩ ያማረ ጌታን አቅፈው ዘንድ ወደድሁ"[41] ብሏል። የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ወንድም የሆነው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፥ በሚቀድስበት ጊዜ "መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ሲወርድ እያየ ተመስጦ ይመጣበት እንደ ነበር" በስሙ የተደረሰው ቅዳሴ አንድምታ ያስረዳል።[42] እንግዲህ፥ እንደነዚህ አባቶች በቅዳሴ የሚከናወነውን ምሥጢር የመረዳት ብቃቱ ባይኖረንም የቀረበውን ኅብስት እና ወይን፥ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም ወደመሆን እንደሚለውጠው ያለምንም ጥርጥር እናምናለን።

በቅዳሴ የሚቀርበው ኅብስቱ ተለውጦ "*ሥጋ መለኮት*"፥ ወይኑም ተለውጦ "*ደመ መለኮት*" የሚሆንበትን አምላካዊ ግብር እኛ በሚገባን ምሳሌ ለመግለጽ ጥንታውያን አባቶቻችን ምሥጢረ ቍርባንን ከምሥጢረ ሥጋዌ ጋር በማነጻጸር ያስረዳሉ። በምሥጢረ ተዋሕዶ እንደምናምነው፥ አካላዊ ቃል ሥጋ ሲሆን የቃልነቱ ባሕርይ ማለትም ምሉዕነቱን (በሁሉ ቦታ የሚገኝ መሆኑን) እና ረቂቅነቱን ሳያጠፋ ሥጋ እንደ ሆነ፥ ሥጋም የሥጋ ባሕርይ (የሚዳሰስና በቦታ የሚወሰን መሆኑን ሳያጠፋ ቃል እንደ ሆነ፥ በቅዳሴ የሚቀርበው ኅብስትና ወይንም "ኅብስትነቱን [እና] ወይንነቱን ሳያጠፋ ፍጹም ሥጋ መለኮት፥ ደመ መለኮት ይሆናል።"[43] ይህም ማለት፥ "በኅብስትና በወይን አርአያ"[44] የምንቀበለው ቅዱስ ቍርባን፥ እኛ በዓይናችን ልናየው የምንችለው የባሕርይ ለውጥ ባይኖረውም፥ የወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሥጋና ፍጹም ደም ነው ማለት ነው። ቅዱስ ቍርባን "ምሥጢር" የተባለበትም ምክንያት ከተለወጠ በኋላ እኛ በዓይናችን እንደምናየው (ኅብስትና ወይን) ስላልሆነ ነው፤[45] ሊመረመር በማይችል የመንፈስ

[41] "አረጋዊ መንፈሳዊ" *መጻሕፍተ መነኮሳት፡- ማር ይስሐቅ፥ ፊልክስዩስ (ገብረ ክርስቶስ)፥ አረጋዊ መንፈሳዊ* (አዲስ አበባ፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1988 ዓ.ም.) ገጽ 168-169።

[42] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ"፡ *መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው* (ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ 1988 ዓ.ም.) ቊ. 3፣ ገጽ 360።

[43] *መጽሐፈ ጥበብ ዘአስተጋብእዎ አኀው ማኅበረ ቢዘን* (አሥመራ፡ ማኅተመ ኮከበ ጽባሕ፡ 1969 ዓ.ም.) 24-25።

[44] አባ ገብርኤል (ሊቀ ጳጳስ) *ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊ፡ ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ* (አዲስ አበባ፡ አዲስ አሳታሚዎች፡ 1993 ዓ.ም.) ገጽ 149።

[45] *Dionysius Bar Salibi: Commentary on the Eucharist*, trans. Baby Varghese, p.70.

ቅዱስ አሠራር፥ ኅብስትና ወይን መስሎ የሚታየን፥ እውነተኛ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር እና ደመ ወልደ እግዚአብሔር ወደ መሆን የተለወጠው ነው።

ከኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ውጪ የሆኑ ሰዎች እንደሚያስተምሩት፥ ቅዱስ ቊርባን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ[46] ሳይሆን፥ ጌታ ኅብስቱን አንሥቶ ከባረከውና ከቆረሰው በኋላ "እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው"፤ እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶ ካመሰገነ በኋላ "ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴ. 26፥26-27) ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ስለሰጣቸው፥ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም ነው። ጌታችን ግልጽ በሆነ አነጋገር "ይህ ሥጋዬ ነው ... ይህ ደሜ ነው" እንዳለ በቅዱስ ወንጌል እያነበቡ፥ "ምሳሌ ነው" ማለት የጌታን ቃል ከመቃረን ውጪ ሌላ ምንም ትርጒም ሊኖረው አይችልም። ይህን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚጠቅሱት ሉቃ. 22፥19 ላይ ያለውን "ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" የሚለውን ዓረፍተ ነገር ነው። ነገር ግን ጌታ ይህን ያለው "እንጀራውን አንሥቶ [አመስግኖ] ቈርሶም ከሰጣቸውና፥ ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው" ካለ በኋላ ነው። ስለዚህ የኋለኛውን አባባል ለብቻ ነጥለን ሳይሆን ሁለቱንም ዓረፍተ ነገሮች አንድ ላይ ማየት አለብን። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንሥቶ የባረከውን ኅብስት "ሥጋዬ ይህ ነው" አለ እንጂ "ይህ የሥጋዬ ምሳሌ ነው" አላለም። እውነተኛ ሥጋው መሆኑን ከነገረን በኋላ "ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" ብሎናል።

ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሉቃስ ወንጌል የተጠቀሰውን የጌታችንን ሙሉ ቃል ከዘረዘረ በኋላ (1ኛ ቆሮ. 11፥23-26) ቊጥር 26 ላይ "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ" ይለናል። ስለዚህ ጌታችን "ይህ ሥጋዬ ነው ... ይህ ደሜ ነው" ያለውን እውነተኛ ሥጋውንና ደሙን የምንቀበለው፥ ለቤዛችን የተደረገውን የጌታን ሕማሙንና ሞቱን እያሰብን ነው ማለት ነው።[47] ለዚህም ነው ቅዱስ ቊርባን በሚከብርበት የቅዳሴ ጸሎት ምእመናን "ንዜኑ ሞተከ

[46] Symbol.
[47] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ንባቡና ትርጓሜው፡ 1988፣ ቊ. 19፣ ገጽ 125።

እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ - አቤቱ ሞትህን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም እንናገራለን"[48] በማለት የሚያዜሙት። ገባሬ ሠናይ ካህኑም ይህን የምእመናኑን ምስክርነት ተከትሎ፦ "አሁንም አቤቱ ሞትህንና ትንሣኤህን [እያሰብን] እናምንሃለን፣ እያመሰገንህ ይህን ኅብስት፣ ይህንም ጽዋ እናቀርብልሃለን"[49] ይላል። ስለሆነም "ለመታሰቢያ አድርጉት" የሚለው የጌታ ትእዛዝ የሚያመለክተው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች እንደሚሉት እንደ ትዝታ ያለፈን ድርጊት ለማሰብ ብቻ የሚደረግ አፍአዊ (የተርእዮ) ክንውንን ሳይሆን፥ ያ አንድ ጊዜ የተፈጸመው ድርጊት (የጌታ የማዳን ሥራ) ዛሬም ሕያውና የሚሠራ መሆኑን አምኖ ምሥጢሩን በገቢር መፈጸምን ነው፡፡

በቅዳሴ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የምታቀርበው ኅብስትና ወይን እውነተኛ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር እና ደመ ወልደ እግዚአብሔር ወደመሆን እንደሚለወጥ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ በማለት ያስረዳናል፦

> ዳግመኛም የሚያድን[50] የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ [እና] ደም እንደ ሆነ በከበረ ቍርባን እናምናለን። ቄሱ ሳያከብረው ኅብስት እና ወይን የነበረው፤ ቄሱ ባከበረው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በላዩ [ላይ] ይወርዳል። ኅብስት ከመሆንም የወልደ እግዚአብሔር ቃል አማናዊ ሥጋ ወደ መሆን ይለወጣል። ወይኑም እንዲሁ ወይን ከመሆን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ አምላካዊ ደም ወደ መሆን ይለወጣል።[51]

የቀረበው ኅብስትና ወይን የጌታችን ሥጋና ደም ወደመሆን የሚለወጠው፥ ሠራዒው ካህን እግዚአብሔር አብን "አቤቱ በዚህ ኅብስትና በዚህ ጽዋ ላይ መንፈስ ቅዱስን ኃይልንም ትልክ ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም፥ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን [እና] ደሙን ያደርገው ዘንድ"[52] ብሎ በሚጠይቅበትና "ፍሬ ቅዳሴ" ወይም "የአማንያን ቅዳሴ" ተብሎ በሚታወቀው ክፍል ነው።[53]

---

[48] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 47፣ ገጽ 109።

[49] ዝኒ ከማሁ፣ ቍ. 48፣ ገጽ 109።

[50] "ድ" ላልቶ ይነበብ፡፡

[51] "ዘቅዱስ አትናቴዎስ" *ሃይማኖተ አበው፡* ምዕራፍ 28፥ ክፍል 14፡ ቍ. 22፣ ገጽ 86።

[52] "ቅዳሴ እግዚእ (የጌታ ቅዳሴ)"፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 47-48፣ ገጽ 151።

[53] ኅብስቱና ወይኑ የጌታችን ሥጋና ደም ወደመሆን የሚለወጠው በየትኛው ጊዜ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ሁለት አይነት አመለካከት እንዳላቸው ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በመጽሐፋቸው ጠቍመዋል። እንዳንዶቹ ከላይ የተጠቀሰውን ጸሎት (*Epiclesis*) ሠራዒው ካህን በሚጸልይበት ጊዜ ነው ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ "ይህ ሥጋዬ ነው…ይህ ደሜ ነው" የሚለውንና መድኃኒታችን

መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና በወይኑ ላይ ወርዶ ምሥጢራቱን እንዲያከናውን ካህኑ የሚጠይቅበት የቅዳሴ ጸሎት፥ በግሪኩ *ኤፒክሌሲስ*[54] በመባል ይታወቃል። ይህ ጸሎት፥ *አናፎራ* ወይም በእኛ ቤተ ክርስቲያን "አኰቴተ ቊርባን (የቊርባን ምስጋና)" ተብሎ የሚታወቀው የቅዳሴው ሦስተኛ ክፍል ውስጥ የሚገኝ መሠረታዊና ወሳኝ ጸሎት ነው። ይህን ዓለም አቀፋዊ ትምህርት የተረዱ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አባቶች፥ ይህን ጸሎት ለማመልከት ሲሉ ይረስዮ ያላቸውና "ይረስዮ የሌላቸው"[55] ቅዳሴያት የሚል አገላለጽ ተጠቅመዋል። ይህም ማለት፥ በግእዙ "ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቊዐከ ከመ ትፈኑ መንፈሰ ቅዱሰ ወኃይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ወላዕለ ዝ ጽዋዕ **ይረስዮ** *ሥጋሁ* ወደሞ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ - አቤቱ ቅዱስ መንፈስን ኃይልንም በዚህ ኅብስት ላይ፥ በዚህም በጽዋው ላይ [ትልክ] ዘንድ እንለምንሃለን፥ እንማልድሃለንም፤ የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋና* ደም **ያደርገው ዘንድ**"[56] የሚለው ጸሎት ያላቸውና የሌላቸው ቅዳሴያት ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያናችን

---

ኢየሱስ ክርስቶስ *ሥርዓተ* ቊርባንን *የመሠረተባቸውን ቃላት* (Institution Narrative) ካህኑ በሚደግምበት ሰዓት ነው ይላሉ። ሊቀ *መዘምራን* ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ፡ *መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት*፡ ሁለተኛ እትም (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1988 ዓ.ም) ገጽ 18። ሁለተኛውን አሳብ የሚደግፉ ምሁራን ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን አብነት አድርገው ይጠቅሳሉ፡- "በአሪት አምላካችን 'ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት' ብሎ አንድ ጊዜ በተናገረው ቃል፥ በዓለም የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ ሲዋለዱና ሲራቡ እንደሚኖሩ፥ አሁንም እንደዚሁ [ጌታ] 'ይህ *ሥጋዬ* ነው፥ ይህ ደሜ ነው' ብሎ የተናገረው ቃል በታቦት ላይ የሚቀመጠውንና በየቤተ ክርስቲያኑ የሚቀርበውን *መሥዋዕት*፥ *ሥጋ* ወልደ እግዚአብሔር፡ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ወደ መሆን ይለውጠዋል።" አባ ገብርኤል (ሊቀ ጳጳስ) *ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊ*፡ ገጽ 139። ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ደግሞ ኅብስቱና ወይኑ የክርስቶስ *ሥጋና* ደም ወደ መሆን የሚለወጠው መንፈስ ቅዱስ በመሥዋዕቱ ላይ ይወርድ ዘንድ ካህኑ ከላይ የተጠቀሰውን ጸሎት ሲጸልይ እንደሆነ ጽፎልናል፡- "ኅብስትኒ ወጽዋዓ ወይን ይከል ከዊነ *ሥጋሁ* ወደሙ ለክርስቶስ በርደተ መንፈስ ቅዱስ ሶበ ይጸርሕ ካህን ወይብል ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቊዓከ ከመ ትፈኑ ቅዱሰ መንፈሰ [ወኃይለ] ዲበ ዝ ኅብስት ወላእለ ዝ ጽዋዕ ይረስዮ *ሥጋሁ* ወደሞ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።" *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, "ምንባብ ዘሰዱሰ ፋሲካ," Vol. 532, Tom. 97. Scriptores Aethiopici, ed. Yaqob Beyene, (Louvain: Aedibus E. Peeters, 1993) ገጽ 88።

[54] Επίκλιση ከሚለው ቃል ተወስዶ *Epiclesis* (Invocation of the Holy Spirit/ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ) የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

[55] *መጽሐፈ* ቅዳሴ፡ 2000፣ ገጽ 441።

[56] "ቅዳሴ ሐዋርያት"፡ *መጽሐፈ* ቅዳሴ፡ 2000፣ ቊ. 48፣ ገጽ 109-110።

ባጠቃላይ *ሀያ* ቅዳሴያት[57] ያሏት ሲሆን፥ እስካሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያኒቷ ካሳተመቻቸው *አሥራ* አራት ቅዳሴያት መካከል፥ ሰባት ቅዳሴያት "ይረስዮ" የሚለው ጸሎት የላቸውም፤[58] የተቀሩት ሰባት ቅዳሴያት ግን የተለመደውን የ"ይረስዮ" ጸሎት ይዘዋል። ነገር ግን "ይረስዮ" የሚለው ግስ የያዘው ጸሎት የሌላቸው ሰባቱ ቅዳሴያት በሙሉ *ኤፒክሌሲስ* (ጽዋዔ *መንፈስ* ቅዱስ) የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ቅዳሴ ቄርሎስና ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ "ይረስዮ" የሚለው ግስ የሌላቸው፥ ነገር ግን "ሜሎስ ሰይፈ እሳት" የተባለው መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና በጽዋው ላይ እንዲወርድ የሚጠይቁ ጸሎታትን ይዘዋል፡፡[59]

በቅዳሴ የሚቀርበው ኅብስትና ወይን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋ*ና ደም ወደ መሆን የሚለወጥበት ምሥጢር የሚከናወነው ከአእምሮ በላይ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ስለሆነ፥ "የሚለወጠው እንዴት ነው?" ብለን ልንጠይቅና የምድራዊውን ሳይንሳዊ አሳብ መሠረት አድርገን በፍጹም ልንመራመር አይገባም ። ይልቅ ይህን ዕጹብ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ *ሥራ* በእምነት ተቀብለን እያደነቅን፥ የቅዳሴው *መሥዋዕት* ተካፋይ በመሆን ኃጢአትን የሚጸየፍና የተቀደሰ ሕይወት ሊኖረን ይገባል። ሠራዒው ካህን የተለወጠውን የመድኃኒታችንን *ሥጋ*ና ደም ራሱ ከመቀበሉና አብረውት ለሚቀድሱት ልኡካንም ሆነ ተዘጋጅተው ለቀረቡት ምእመናን ከማቀበሉ በፊት በወልደ እግዚአብሔር *ሥጋ*ና ደም ላይ ያለውን እምነት እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

> በእውነት ክቡር የሚሆን የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋ* ይህ ነው፣ አምነው ከእርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተሥረያም ሊሆን የሚሰጥ፤ በእውነት አምነው ከእርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተሥረያም ሊሆን የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን [የመድኃኒታችን] የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ ነው፤ . . .

---

[57] ስለእነዚህ ቅዳሴያት ዝርዝር እና ታሪካዊ አመጣጥ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሦስት ላይ የተጻፈውን ይመልከቱ።

[58] እነዚህ ቅዳሴያት፡- ቅዳሴ ማርያም፥ ቅዳሴ ፫፻፲፰፥ ቅዳሴ አትናቴዎስ፥ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (የባስልዮስ ወንድም) ፥ ቅዳሴ ቄርሎስ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ("ተአምራት አድራጊው" ተብሎ በሚታወቀው የኒዮ ቂሣርያ [Neo-Caesarea] ኤጲስ ቆጶስ በሆነው በቅዱስ ጎርጎርዮስ ስም የተሰየመው ቅዳሴ) ናቸው። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ገጽ 441።

[59] "ቅዳሴ ቄርሎስ"፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 70፣ ገጽ 333፤ "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 53፣ ገጽ 348።

አምናለሁ፡ አምናለሁ፡ አምናለሁ፣ እስከ መጨረሻዪቱ እስትንፋስ እታመናለሁ፣ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ማርያም የነሣው የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደ ሆነ፣ ያለመቀላቀልና [ያለመነጣጠል]፣ ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር አንድ ያደረገው፣ በጰንጤናዊ ጲላጦስም ዘመን ባማረ ምስክርነት ምስክር የሆነ፥ ስለ እኛና ስለሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው።[60]

ይህ የካህኑ የእምነት መግለጫ፥ ጲላጦስ የሮማው ቄሣር ወኪል ሆኖ በኢየሩሳሌም የይሁዳ ክፍለ-ከተማ ገዢ በነበረበት ዘመን (ዮሐ. 18፥28) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ መሥዋዕት እነደሆነና አሁንም በቅዳሴው ሥርዓት በየዕለቱ መሥዋዕት ሆኖ እንደሚቀርብ በግልጽ ያመለክታል። በአሉታ አንቀጽ የተጠቀሱት አራቱ የግእዝ ተውሳከ ግሶች፡ “ዘእንበለ ቱስሕት ወኢትድምርት[61]፣ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ” ደግሞ፥ አካላዊ ቃል ከትስብእት (ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከነሣው ሥጋና ነፍስ ጋር) ሲዋሐድ፥ ምንም አይነት መቀላቀል (መጠፋፋት) ወይም መለያየት፤ መለወጥም ሆነ መለየት[62] ሳይኖርበት መዋሐዱን የሚያመለክቱ የምሥጢረ ሥጋዌ (የምሥጢረ ተዋሕዶ) አገላለጾች ናቸው። ይህም ማለት ከሦስቱ የሥላሴ አካላት አንዱ አካል ወልድ፥ በተለየ አካሉ የእኛን ባሕርይ ተዋሕዶ ሰው ሲሆን፥ መለኮታዊ ባሕርዩ ሰው ወደ መሆን አልተለወጠም፤ የነሣው ሥጋም ባሕርዩን ለቆ (ትቶ) መለኮት ወደ መሆን

---

[60] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 2000፣ ቍ. 98-101፣ ገጽ 120-121።

[61] “ወኢትድምርት” ከሚለው ይልቅ ብዙ ጊዜ የሚመረጠው “ወኢቡዐዴ” የሚለው ቃል ነው። ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ “ቡዐዴ” የሚለውን ቃል ትርጕም ሲያስረዱ፡- የቃልና የሥጋን ተዋሕዶ ለመግለጽ “ቡዐዴ” የሚለውን ቃል መጠቀም፥ ተዋሕዶው “ተላጽቆ እና ተቃርቦ” መሆኑን የሚያሳይ የተሳሳተ አገላለጽ መሆኑን ጠቅሰው፥ በብሎን የተጣበቁ የእንጨትንና ብረትን ምሳሌ ይሰጣሉ። ብሎኑ ሲፈታ ብረቱና እንጨቱ እንደሚለያዩ “ቡዐዴ” መለያየትን የሚያመለክት ቃል ነው። ስለዚህ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ “ዘእንበለ ቡዐዴ” (ያለመለያየት) ነው። መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፡ *መድሎተ ኣሚን፡ የሃይማኖት ሚዛን፡ ሁለተኛ እትም* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1990 ዓ.ም.) ገጽ 105። ሌላው የቤተ ክርስቲያናችን ምሁር ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ደግሞ፥ “ትድምርት” የሚለውን ቃል ለመግለጽ ምሳሌ ሲሰጡ፡- የተደራረበ እንጀራ እነደሚነጠል፣ ወይም የተደረበ ልብስ እንደሚወልቅ፥ የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ እንደዚህ አይደለም ይላሉ። ስለዚህ ተዋሕዶው “ዘእንበለ ትድምርት” ነው ሲባል መለያየት ወይም መነጣጠል የለበትም ማለት ነው። ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ፡ *መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት*፣ ገጽ 15።

[62] “ለ” ጠበቅ ብሎ መነበብ አለበት። በዚህ አጋጣሚ የማንኛውም ቋንቋ ሥነ ጽሑፍ በየጊዜው የሚያድግ ስለ ሆነ፥ በአማርኛ ጽሑፍ ጠብቀውና ላልተው የሚነበቡ ፊደሎችን የምንለይባቸውን ሥርዓተ ነጥቦች የቋንቋው ባለሙያዎች ሊፈጥሩልን ይገባል።

አልተቀየረም ማለት ነው። በአንዱ ሥግው ቃል (በክርስቶስ) ውስጥ የመለኮት ባሕርይ የሥጋን ባሕርይ ሳያጠፋው፥ በሰው አንደበት ሊገለጽ በማይችል ተዋሕዶ ጸንተው ይኖራሉ፤ ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው፥ ፍጹም አምላክ ነው። ከተዋሕዶ በኋላ መለኮቱ ከትስብእቱ (ከሰውነቱ) "ለዓይን ቅጽበት (የዓይን ጥቅሻ ያህል እንኳ)[63] አልተለየም። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ቤዛ ሆኖ በቀራንዮ በተሰቀለ ጊዜ፥ ነፍሱን ከሥጋው በሥልጣኑ ለይቶ በአካለ ነፍስ "በወኅኒ [የነበሩ] ነፍሳትን" (1 ጴጥ. 3፥19) ነጻ ለማውጣት ወደ ሲኦል በወረደበት ሰዓት እንኳ፥ መለኮቱ መስቀል ላይ ከነበረው ሥጋው በፍጹም አልተለየም። ስለዚህ እንደ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ትምህርት የቅዳሴው መሥዋዕት ይኸው የቀራንዮ መሥዋዕት ነውና፥ በቅዳሴ የምንቀበለው ሥጋ "ነፍስ የተለየው፥ መለኮት የተዋ ሐደው"[64] ይባላል።

## ቅዱስ ቍርባን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳኑን የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት በመሠረተበት ጊዜ በፋሲካው ማዕድ አብረውት ለተቀመጡት ደቀ መዛሙርቱ፥ ኅብስቱንና ጽዋውን ባርኮ "እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው…ከእርሱ ጠጡ… የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ብሎ ከሰጣቸው በኋላ፥ "…በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣውም" ብሏቸው ነበር (ማቴ. 26፥26-29)። ይህን የጌታችንን አገላለጽ መሠረት በማድረግ ኦርቶዶክሳውያን የነገረ መለኮት ምሁራን፥ ቅዱስ ቍርባን ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን የምትሠዋው መሥዋዕት ብቻ ሳይሆን፥ በምልዓት የምትገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ [65] እንደ ሆነም ያስተምራሉ። ጌታ "በእግዚአብሔር መንግሥት እስኪፈጸም ድረስ ከዚህ አልበላም … ከወይኑ ፍሬ አልጠጣም" (ሉቃ. 22፥16-18) ያለው፥ የእርሱ ሥጋና

---

[63] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 2000፣ ቍ. 102፣ ገጽ 121።

[64] አባ ቄርሎስ (ሊቀ ጳጳስ) *ፍሬ ሃይማኖት* (አሥመራ፡ ኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ማተሚያ ቤት፡ 1976 ዓ.ም) ገጽ 26።

[65] ይህ አሳብ በእንግሊዝኛ "Banquet of the Kingdom" ተብሎ ተገልጿል፡፡ Fr. Emmanuel Hatzidakis, *The Heavenly Banquet: Understanding the Divine Liturgy* (Chicago: Orthodox Witness, 2010) ገጽ 41 ይመልከቱ፡፡

ደም እንደ ሆነ በግልጽ ተናግሮ የሰጣቸውን የአዲሱን ኪዳን መሥዋዕት እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህ ኪዳን ዘላለማዊ ከመሆኑ ባሻገር ሰማያዊውን መንግሥት ስለሚያመለክት፥[66] የዚህ የአዲሱ ኪዳን ቅዱስ ቍርባን የዘላለማዊው መንግሥት ማዕድ ነው ማለት ነው። በሌላ መልኩ ቅዱስ ቍርባን የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ ነው ማለት እንችላለን። እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥትም የቅዱስ ቍርባንን ባሕርይ ሊገልጽልን የሚችል ነገር ከቶ የለም።[67]

ስለዚህ ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ቅዱስ ቍርባን የሚከብርበትን ቅዳሴ በቀደሰች ቍጥር በእግዚአብሔር መንግሥት የምትጠግበውን ሰማያዊ ሕይወት አስቀድማ በዚህ ምድር ትለማመደዋለች፤ ይህም የሚሆነው የመንግሥቱ ማዕድ ከሆነው ከቅዱስ ቍርባን የተነሣ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ያተረፈው ኦርቶዶክሳዊው ካህንና የነገረ መለኮት ሊቅ አሌክሳንደር ሽሜማን ይህን አሳብ ሲገልጸው፡- "ቅዱስ ቍርባን ይህ ዓለም የተጀመረበትም ሆነ በእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ የሚያገኝበት ምሥጢር[68] ነው፤ ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የልቧ መሻትና ናፍቆት ወደሆነው ወደ ሰማይ - [ማለትም] በመንግሥቱ ውስጥ የክርስቶስ መሢሐዊ ማዕድ ወደሆነው - ስታርግ ፍጻሜ ያገኛል"[69] ብሏል። ለዚህም ነው ጌታችን በቅዱስ ወንጌል ለአማንያን ልጆቹ በመንግሥቱ ይህ እንደሚፈጸምላቸው ቃል የገባላቸው፡- "አባቴ እኔን እንደሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ…እሾማችኋለሁ" (ሉቃ. 22፥29-30)።

ቅዱስ ቍርባን የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድና የመንግሥቱ መገለጫ መሆኑን የሚጠቁሙ ምንባባትን በቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ውስጥ እናገኛለን። የቅዳሴው የመጀመሪያ ክፍል በሆነው የዝግጅት ክፍል (በቅዱሳቱ ንዋያቱ ላይ ከሚደረጉት ጸሎታት በአንዱ)፥ ገባሬ ሠናዩ ካህን የጌታ የእጆቹ በረከት በፃሕሉ ላይ እንዲያድር እየጠየቀ፥ ይህች ፃህል "ቅዱስ ስምህን የሚወዱ ሰዎች የሺህ

---

[66] Metropolitan John D. Zizioulas, "The Eucharist and the Kingdom of God, Part II" *Sourozh: A Journal of Orthodox Life and Thought*, 59 (1995) p. 23.
[67] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 3፡፡
[68] ከላቲኑ የተወሰደው የእንግሊዝኛ አቻ sacrament የሚል ነው፡፡
[69]Alexander Schmemann, *The Eucharist: Sacrament of the Kingdom* (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1974) p. 36.

ዘመን ምግብን በላይዋ የሚያዘጋጁባት ናት"[70] ይላል። እዚህ ላይ "ሺህ ዘመን" ተብሎ የተጠቀሰው ፍጹም የሆነው (ፍጻሜ የሌለው) እና ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ጊዜ ሲሆን፥ "የሺህ ዘመን ምግብ" የሚለውን ቃል ሲተረጉሙ፥ ሊቃውንት አባቶቻችን "የሺህ ዘመን ምግብ የሚሆን ሥጋው"[71] ማለት ነው ብለዋል። በዚህ ዓለም እኛ በምንረዳው መልኩ የምንቀበለው ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር በመንግሥቱም ምግብ ሆኖን ይኖራል።[72]

ሠራዒው ካህን የዝግጅት ክፍል ጸሎታትን ከማድረሱ በፊት "ቄስም ቢሆን፣ ዲያቆንም ቢሆን በቅዳሴ ጊዜ መጀመሪያ ይህን ቃል በግድ ያንብብ፣ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉም ሁሉ በማስተዋል ይህን ይስሙ"[73] በማለት መጽሐፈ ቅዳሴ ትእዛዝ የሠራለት ጸሎት አለ። ጸሎቱ በዋነኝነት ምእመናን የቅዳሴውን ጸሎት በማስተዋል እንዲሰሙና ቅዳሴውን አቋርጠው እንዳይወጡ የሚያሳስብ ሲሆን፥ ስለ ጌታችን ሥጋና ደም ሰማያዊ ምሥጢር እንዲህ ይላል፦

> በሠርጉ ጊዜ ሥጋውን የሚሠዋና ፈጽሞ ምግብ የሚሆን ሙሽራን ያየ ማን ነው? የእግዚአብሔር ልጅ [ኢየሱስ ክርስቶስ] ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ከእርሱ በቀር እንደርሱ ያደረገው የሌለ እንግዳ ሥርዓትን በዚህ ዓለም ሠራ፤ በሠርጉ ጊዜ በሐዋርያት ፊት ቅዱስ ሥጋውን [እና] ክቡር ደሙን ማዕድ አድርጎ ሠራ፣ ከእርሱ ይበሉ ዘንድ፣ ያመነበትም ለዘላለም ይድን ዘንድ፤ በሠርጉ ጊዜ መብል መጠጥ የሆነውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።[74]

ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ የሠርግ ማዕድ ተብሎ እንደ ተጠራ ልብ እንበል። ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያንን የራሱ ባደረገበት በሠርጉ ቀን፥ ሥጋውን የሠርጉ ማዕድ አድርጎ ያቀረበ ብቸኛው ሙሽራ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህም ሠርግ በዮሐንስ ራእይ 19፥6-7 ላይ የተጠቀሰው ነው፦ "ሃሌ ሉያ፥ ሁሉን የሚገዛ አምላካችን ነግሦአልና። የበጉ ሠርግ ስለ ደረሰ፡ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን፡ ሐሤትም እናድርግ፡ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።" የሰው ዘሮች ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ወደሚከናወነው ወደ በጉ ሠርግ እራት (ራእ. 19፥9)

[70] "ጸሎት ላዕለ ፃሕል" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 43፣ ገጽ 25።
[71] "ሥርዓተ ቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ንባቡና ትርጓሜው፡ 1988፣ ገጽ 30።
[72] ዝኒ ከማሁ።
[73] "ሥርዓተ ቅዳሴ ዘይደሉ ለቀሲስ ወለዲያቆን ወለኵሉ ሕዝብ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 1፣ ገጽ 5።
[74] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 8-10፡ ገጽ 6-7።

ተጠርተዋል፤ ጥሪውን የተቀበሉት ልጆቹም፥ ጌታችን እንደ ተናገረው፦ “ከምሥራቅና ከምዕራብ ከሰሜንና ከደቡብ ይመጣሉ፥ በእግዚአብሔርም መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ” (ሉቃ. 13፥29)። ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ ቅዱስ ቊርባን እንደሆነ ያምናሉ።[75] በጽዮን ተራራ ላይ ቆሞ የታየው የእግዚአብሔር በግ (ራእ. 14፥1) የዚህ ሰማያዊ ማዕድ ተካፋይ ያደርገን ዘንድ ቤተ ክርስቲያናችን በሰዓታት ጸሎት፡ “አ በግዕ ዘአርያም በርእሰ ደብረ ጽዮን ዘቆምከ፤ ኢትፍልጠነ እም ከብካበ ቅዱስ መርዓከ[76] - በጽዮን ተራራ ራስ ላይ የቆምህ ሰማያዊ በግ ሆይ፥ ከቅዱሱ ሠርግህ አትለየን” በማለት ትዘምራለች። ከሰማያዊው እንጀራ (ከክርስቶስ - ዮሐ. 6፥51) በስተቀር በእግዚአብሔር መንግሥት ሌላ መንፈሳዊ ማዕድ ከቶ ሊኖር አይችልም፤ ስለ ሆነም “በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ የሚበላ ብፁዕ ነው” (ሉቃ. 14፥15)።

ከላይ በዝርዝር በተጠቀሰው በመጀመሪያው ነጥብ፥ ቅዳሴ የአዲስ ኪዳኑና ዘላለማዊው መሥዋዕት የሚቀርብበት ታላቅ የኅብረት አምልኮ እንደሆነ ተምረናል። በመቀጠል የዚህን ውብና ድንቅ የሆነ አምልኮ ተጨማሪ መገለጫዎችን በቅደም ተከተል እንመለከታለን።

## ፪. የክርስቶስን የማዳን ሥራ እውን የሚያደርግልን የምስጋና አገልግሎት

“ቅዳሴ” የሚለው የግእዝ ቃል ትርጒም እንደሚያመለክተው፥ በዚህ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር አብ ዓለሙ ሁሉ እንዲድን እንጂ እንዳይጠፋ ወድዶ አንድ ልጁን በመላክ ስላደረገው የማዳን ሥራና ስለገለጸልን ዘላለማዊ ፍቅር

[75] Metropolitan Athanasios (Yievtich) የተባሉ ኦርቶዶክሳዊ ሊቀ ጳጳስ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት የሚጠብቀን ዘላለማዊ አምልኮ ማዕከሉ ክርስቶስ እንደ ሆነና ከቅዱስ ቊርባን በስተቀር ሌላ ማዕድ እንደሌለ ውብ በሆነ አገላለጽ ሲገልጹ፦“The eschatological Kingdom of heaven will be nothing different than the Eucharistic Lord’s Supper of the Kingdom, the Eternal Liturgy that is the divine and eternal Communion of God the Father in the *Theanthropos* [God-man] Christ through the Holy Spirit with all of us” ብለዋል። See “Metropolitan Athanasios (Yievtich)” quoted in Hatzidakis, *The Heavenly Banquet*, p. 41.

[76] መጽሐፈ ሰዓታት ምስለ ኵሉ ጸዋትዊሁ ወባሕረ ሐሳብ፡ “ተዘከር ካዕበ” (አሥመራ፡ ኮከበ ጽባሕ ቤተ ማኅተም፡ 1975 ዓ.ም) ገጽ 164።

ምስጋና ታቀርባለች። ይህንን የቅዳሴ ዋነኛ ዓላማ ግልጽ በማድረግ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ተብሎ የሚጠራው የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ "አቤቱ በተወደደው ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ እናመሰግንሃለን። በኋለኛው ዘመን የምክርህን አበጋዝ መድኃኒትና ቤዛ የሚሆን ልጅህን ሰደድህልን"[77] ይላል። በቅዳሴ ውስጥ ያሉ ድርጊቶች (ዑደት፥ ቡራኬ፥ እማሬ፥ ፈትቶ) የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከልደት እስከ ዕርገት ያለውን የማዳኑን ሥራ የሚገልጡ ናቸው። በቅዳሴ ጊዜ የምንገለገልባቸው ንዋያተ ቅድሳት (ፃሕል፥ ጽዋ፥ ጽንሐሕ ወዘተ.) እንዲሁም የዕጣኑ፣ የጧፉና የዑደቶቹ ትርጒም ገብቶን በማስተዋል የምስጋናው አገልግሎት ተሳታፊ የምንሆን ከሆነ መድኃኒታችን ስለእኛ ሲል የተቀበለውን ሕማም፥ ለቤዛነት ኃጢአታችንን ወስዶ መሞቱን እና መቀበሩን እንዲሁም ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን በምሳሌ የሚያስረዱ ናቸው። ስለዚህ ቅዳሴ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን የሠራቸውን ሥራዎች ባንድ ላይ ጠቅልሎ ያቀርብልናል፡፡[78]

የቅዳሴው አገልግሎት ተሳታፊ በሆንን ቊጥር፥ የሕሊናችንን አሳብ ከመበታተን ጠብቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ ሲል "ባለጸጋ ሲሆን ራሱን ድሀ"[79] ማድረጉንና የእኛን ኃጢአት ተሸክሞ የተቀበለውን ሕማምና ጸዋትወ መከራ በተመስጦ ልናስብ ይገባል። እንዲሁም የቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደራሲ በሞት የተገለጸውንና ከአእምሮ በላይ የሆነውን፥ መድኃኒታችን ክርስቶስ እኛን የወደደበትን ፍቅር፦ "ይህን ያህል ሰውን ማፍቀር እንደ ምን ያለ ፍቅር ነው!"[80] በማለት ካደነቀ በኋላ "ብክይዎ ወላህውዎ እለ ታፈቅርዎ - የምትወዱት ሰዎች አልቅሱለት"[81] ብሎ እንዳዘዘን፥ የተከፈለልንን ውድ ዋጋ እያሰብን በዕንባና በተሰበረ መንፈስ ልናመልክ ይገባል። ጌታ ስለእኛ ፍቅር የተቀበለው መከራ ሲገባን እኛም ለእርሱ ያለንን ፍቅር

---

[77] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቊ. 4፣ ገጽ 101።

[78] ይህ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ በእንግሊዝኛ - "a recapitulation of the entire economy of salvation" ይባላል።Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy: A Commentary in the Light of the Fathers*, trans. Elizabeth Theokritoff (Mount Athos: Cell of St. John the Theologian, Koutloumousiou Monastery, 2009) 15; Constantine N. Tsirpanlis, *The Liturgical and Mystical Theology of Nicolas Cabasilas* (New York, [No Publisher], 1979) p.18.

[79] "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቊ. 126፣ ገጽ 210።

[80] "ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቊ. 52፣ ገጽ 361።

[81] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ. 59፣ ገጽ 362።

ከምንገልጽባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው የቅዳሴውን መሥዋዕት (ቅዱስ ቍርባንን) መቀበል ነው። የቅዳሴው ዋነኛ ዓላማ አማንያን "ጸጋ[82] ሁኖ የተሰጠንን ሥጋውንና ደሙን"[83] በመቀበል ወደ ሕይወት መድኃኒት እንዲቀርቡ ማድረግ ስለሆነ፥ ይህን የተረዱ የእግዚአብሔር ልጆች ራሳቸውን አዘጋጅተው በተቻለ መጠን ቅዱስ ቍርባንን እየተቀበሉ የቅዳሴው ሙሉ ተሳታፊ ይሆናሉ። ከምስጋና በተጨማሪ "ቅዳሴ" የሚለው የአምልኮው (የምስጋናው) ስያሜ የካህናቱንና የምእመናን መቀደስ (ቅድስና) ስለሚያመለክት፥ የቅዳሴውን መሥዋዕት በተደጋጋሚ የሚቀበሉ አማንያን በቅዱስ ቍርባን ያጌጠ ሕይወት ይኖራቸዋል።

## ፫. በምድር ላይ ያለ ሰማያዊ አገልግሎት

ቅዳሴ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሥዋዕትነት የሚቀርብበት ምሥጢራዊ አገልግሎት እንደሆነ አይተናል። ስለዚህ "አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" (ራእ. 22፥13) ያለው ጌታ የሚገኝበት የቅዳሴው ቦታና ሰዓት[84] እኛ ከምናውቀው ምድራዊ ሥፍራና የጊዜ መለኪያ ፈጽሞ የተለየ ነው። በቅዳሴ ሰዓት በዓለሙ የሒሳብ ቀመር የሚቈጠረው፥ ውሱን የሆነው፥ መጀመሪያና ፍጻሜ ያለው ጊዜ ዘላለማዊ (መነሻና መድረሻ የሌለው) ጊዜ (ሰዓት) ወደመሆን ይቀየራል።[85] ለዚህም ነው የቅዳሴው መጀመሪያ ላይ ሠራዒው ካህን፡ "ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት? ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት? መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድባት፤ ይህን መሥዋዕቱን የሚሰውርባትና የሚያከብርባት"[86] የሚለው። ለአምልኮ የቆምንበት መቅደስም የተለየ የአምልኮ ሥፍራ ስለሆነ፥ በምድር ላይ ብንሆንም በሰማይ ነን፤ ዲያቆኑ ይህን አሳብ ባገናዘበ መልኩ፥ ቅዳሴ እግዚእ (የጌታ ቅዳሴ) እና ቅዳሴ ያዕቆብ

---

[82] ዋጋ ሳንከፍልበት፥ በጌታ በቸርነት (በነጻ) የተሰጠን፡፡

[83] "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 13፣ ገጽ 145።

[84] ይህ በእንግሊዘኛ "liturgical space and time" በመባል ይታወቃል።

[85] እነዚህ የተለያዩ ጊዜያት፡- temporal time (chronos) እና eternal time (kairos) በሚሉ ስያሜያት ይታወቃሉ፡፡

[86] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 1፣ ገጽ 35

ዘሥሩግ በሚቀደሱበት ጊዜ፡- “በሰማይ የሀሉ ልብክሙ - ልቡናችሁ በሰማይ ይኑር”[87] እንዲል።

ፍጥረቱን ሁሉ የሚጠቀልለው ንጉሡ ክርስቶስ ባለበት፥ ሠራዊቱ ቅዱሳን መላእክት ስላሉ፥ “ቅዳሴ” በማለት የምንጠራው አገልግሎት ሰማይና ምድር አንድ የሚሆኑበትና መላእክት ከሰው ልጆች ጋር አብረው ምስጋናን የሚያቀርቡበት አገልግሎት ነው። ስለሆነም ቅዳሴ በምድር ላይ ቢፈጸምም፥ በባሕርዩ ግን ሰማያዊ የሆነ አምልኮ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ስለ ክህነት በጻፈው መጽሐፍ፥ ምሥጢረ ክህነት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሚከናወንና ምድራውያን ካህናትን በንጽሕና እና በአገልግሎት ከሰማያውያን መላእክት ጋር እንደሚያመሳስላቸው ገልጾ፥ በቅዳሴ ሰዓት ቅዱሳን መላእክት የአገልግሎቱ ተሳታፊ መሆናቸውን እንደሚከተለው ያስረዳል፡-

> [ካህኑ] መንፈስ ቅዱስ [በኅብስቱና ወይኑ ላይ እንዲወርድ] እየጠየቀ መሥዋዕቱን በሚያቀርብበትና የሁሉን ጌታ በእጁ በሚይዝበት ሰዓት፥ ንገሩኝ [ለካህኑ] ምን ዓይነት ማዕረግ እንሰጠዋለን? ከእርሱስ ምን ዓይነት ንጽሕና እና በጎ ምግባር ነው የሚጠበቀው? እነዚህን ምሥጢራት የሚያከናውኑ ምን ዓይነት እጆች ናቸው? [የምስጋናውን] ቃላት የሚናገርስ ምን ዓይነት አንደበት ነው? ይህን ታላቅ መንፈስ የሚቀበል ነፍስ፥ በዓለም ላይ ካለ ማንኛውም ነገር ይልቅ ንጹሕና ቅዱስ መሆን የለበትምን? [በቅዳሴ ጊዜ] መላእክት ከካህኑ ጋር ይቆማሉ፤ መንበሩ አካባቢ ያለው ቦታና መቅደሱ በሙሉ [ለመሥዋዕትነት በቀረበው በግ] ክብር በሰማያውያን ኃይላት ይመላል።[88]

ከመላእክት ጋር የአምልኮ ኅብረት እንዳለን የተረዱ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን የሚከተለውን ቡራኬ በመጽሐፈ ቅዳሴ አዘጋጅተዋል፡- “ልዑል እግዚአብሔር ሁላችንን ይባርክ፣ በመንፈሳዊም በረከት ሁሉ ያክብረን፣ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መግባታችንንም ዘወትር በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከሚያገለግሉትና በየጊዜውና በየሰዓቱም ሁሉ ከሚያመሰግኑት ቅዱሳን መላእክት ጋር በአንድነት ያድርግ።”[89] እንግዲህ ለነቢዩ ኢሳይያስና (ት. ኢሳ. 6፥1-3) ለቅዱስ ዮሐንስ

[87] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 2፥ገጽ 143 እና ቍ. 51፡ ገጽ 399። የ፫ቱ፻ እና የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴያት በሚቀደሱበት ጊዜም ሠራዒው (ዋናው) ዲያቆን “ሕሊናችሁ (አሳባችሁ) ወደ ላይ ይሁን፣ ልቡናችሁ በሰማይ ይኑር” ይላል። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 50፣ ገጽ 228 እና ቍ.3፣ ገጽ 353።

[88] *St. John Chrysostom: Six Books on the Priesthood,* Book VI: No. 4, trans. Graham Neville (London: S.P.C.K., 1964) p. 141.

[89] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 185፣ ገጽ 77-78.

ወንጌላዊ (ራእ. 4፥8) እንደተገለጸላቸው፥ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች"[90] የሚለውን የቅዱሳን መላእክትን ሰማያዊ ዝማሬ በቅዳሴ ሰዓት ስንዘምረው፥ የማይታዩ ቅዱሳን መላእክት ከእኛ ጋር የቅዳሴው ተሳታፊ ይሆናሉ። ለዚህ ነው፥ ሠራዒው ካህን እግዚአብሔርን ዘወትር ያለማቋረጥ ከሚያመሰግኑ ቅዱሳን መላእክት ጋር "በአንድነት"[91]፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጹም አሸናፊ[92] እግዚአብሔር፥ የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው" እያልን የምናቀርበውን ምስጋና እንዲቀበልልን የሚለምነው።[93]

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ማለትም "ወደ እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል" ካለ በኋላ፥ በሰማያዊቷ ከተማ ያሉትን ሲዘረዝር፡- አእላፍ መላእክት፥ የበኵራት ማኅበር፥ የጻድቅን መንፈሶች፥ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነው ጌታ ኢየሱስ በማለት ጽፏል (ዕብ. 12፥22-24)። እንደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ቅዳሴ የአዲስ ኪዳኑ መሥዋዕት (የእግዚአብሔር በግ) የሚሠዋበት አገልግሎት ስለሆነና ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት ሠራዊቱ ስለሚገኙ ከላይ የተዘረዘሩት ቅዱሳን ሁሉ የሚሳተፉበት ጉባኤ ነው። በሰማያዊቷ ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) ቍጥር የሌላቸው ቅዱሳን መላእክት፣ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም፣ ነቢያትና ሐዋርያት፣ የጌታ ምስክሮች የሆኑ ሰማዕታትና ቡሩካን የተባሉ ጻድቃን አሉ። እነዚህ ቅዱሳን የምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ተሳታፊ መሆናቸውን ስለምናምን፥ በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ "በጸሎታቸውና በልመናቸው" ያስቡን ዘንድ በሕይወት ካሉት ቅዱስ ፓትርያርኩና ሊቃነ ጳጳሳቱ ጀምረን የቅዱሳኑን ስም እንጠራለን።[94]

---

[90] ይህ የመላእክት ዝማሬ በእንግሊዝኛ (ከላቲን ቋንቋ ተወስዶ) *Sanctus* በመባል ይታወቃል።

[91] "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.19፣ ገጽ 394።

[92] "አሸናፊ" ተብሎ መጽሐፈ ቅዳሴ ላይ በአማርኛ የተተረጐመው ቃል "ጸባዖት" ያለውን ነው። *Tzevaot* ወይም *Saba-oth* የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ብዙ ጊዜ የሚተረጐመው "Hosts" ወይም "ሠራዊት" ተብሎ ሲሆን፤ "Lord of *Sabaoth*" ወይም "Lord of Hosts" በመባል የሚታወቀው "የሠራዊት ጌታ" እግዚአብሔር ነው። ይህም በት.ኢሳ 6፥3 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ይስማማል። See "Liturgy of Saint Basil," *Holy Euchologion* (Kitchener: St. Mary's Coptic Orthodox Church, 2004) p. 92; Gregorios, *The Divine Liturgy,* p. 343.

[93] "ቅዳሴ ሐዋርያት"፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.29-32፣ ገጽ 106-107።

[94] ሠራዒው ዲያቆን "በእንተ ብፁዕ" እያለ በማዜም የሚጀምረውንና በለኆሳስ (በዝግታ፡ ድምጽ ሳያሰማ) የሚጨርሰውን የጸሎት ክፍል ይመልከቱ። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 6-9፣ ገጽ 101-103።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእዩ ቍጥራቸው እጅግ የበዛ ቅዱሳን መላእክት "የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት፣ ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል" (ራእ. 5፥12) እያሉ አዲስ ቅኔ ሲቀኙ እንደሰማ፥ እንዲሁም በምድር ላይና በባሕር ውስጥ ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ይህንኑ ምስጋና እንደደገሙት፥ ፍጥረታትን በሙሉ በሚያስተባብረው ቅዳሴ ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያን በምድር ሆና፦ "አምላካችን ክርስቶስ የሁላችን ንጉሥ አንተ ነህ፥ ከፍ ያለ ምስጋናንና ክብርን ስግደትንም ላንተ እንልካለን፤ ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ ጋራ፥ ካንተ ጋራ ከሚተካከለው ከማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ጋራ፥ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፥ አሜን"[95] እያለች ታመሰግናለች። ከቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት መካከል፥ በወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ስም የተሰየመው የአባቶቻችን አኰቴተ ቍርባን (የቍርባን ምስጋና)፥ እግዚአብሔርን ደስ ካሰኙ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን መካከል፦ አቤል፣ ኖኅ፥ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ እና ሙሴን፤ ከሐዲስ ኪዳን ደግሞ ጴጥሮስ፥ ጳውሎስ እና እስጢፋኖስን ካነሣ በኋላ፥ "ስማቸው በሰማያት ባለች [እና] ነጻ በምታወጣው በኢየሩሳሌም በሕይወት መጽሐፍ" የተጻፉት ቅዱሳኑ ሁሉ ማኅበር የሆነችውን ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን "በእውነት እናታችን ናት፥ በቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ አመን[ን]ባት" ይላል። አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ለሙሽራዋ ለኢየሱስ ክርስቶስ የምታቀርበውን ምልጃና የአምልኮ ምስጋናንም፦ "አቤቱ አምላካችን፥ ቤተ ክርስቲያንህ ትማልድሃለች ትሰግድልህማለች፤ ሙሽራህ ታከብርህማለች፥ ሕዝብህም ይገዙልሃል"[96] በማለት ይገልጸዋል። ስለሆነም ቅዳሴ ሰማያዊቷ እና ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን የቀራንዮውን መሥዋዕት (የታረደውን በግ) ከብበው በኅብረት ምስጋና የሚያቀርቡበት ውብና ድንቅ አምልኮ ነው።

## ፬. የሰማያዊው አምልኮ ነጸብራቅ

ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊው ዓለም ምሳሌ እንደ ሆነች ሲያስተምሩን፥ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን በሕፃንነታችን "ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም" በማለት የተቀደሰውን ሥፍራ እጅ እየነሣን እንድናድግ

[95] "ጸሎተ እንፎራ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.50፣ ገጽ 47።

[96] "ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 93-99፣ ገጽ 176-178።

አድርገውናል። በምድር የምናያት ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊው መቅደስ፤ ዲያቆናቱ እና ካህናቶቿ ደግሞ የተለያዩ መዐርጋት ያሏቸው ቅዱሳን መላእክት ምሳሌዎች መሆናቸውን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ ሰግላ (ጋስጫ) ተብላ በምትታወቀው ገዳም አበምኔት የነበረው ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ (1357-1417 ዓ.ም.) በመጽሐፈ ሰዓታት እንዲህ ይላል፡-

> ይህች ቤተ ክርስቲያን በሰማያት [ባለው] አምሳል የመላእክት ሥርዓት አላት። ቤተ ክርስቲያን በላይ በሰማይ ባለው መቅደስ ትመሰላለች። …[ሱራፌል ተብለው በሚታወቁ ነገደ መላእክት] ፋንታ ንጹሑን መሥዋዕት [ሥርየተ ኃጢአት የሚያስገኘውን ቅዱስ ቍርባን]፥ መዓዛው ያማረንና ተቀባይነት ያለውን ዕጣን የሚያቀርቡ ላእካነ ምሥጢር ካህናት አሉን። [ሊቃናት ተብለው በሚታወቁ ነገደ መላእክት ፈንታ] በዚህች መሠዊያ ላይ [ለምሥጢረ ቍርባን ተልእኮ] የሚፋጠኑ ንጹሐን ዲያቆናት አሉን።[97]

ይህ “ኵሎሙ” በሚል ርእስ የሚታወቀው የመጽሐፈ ሰዓታት ዝማሬ፥ ቤተ ክርስቲያን በባሕርይዋና በአገልግሎቷ ሰማያዊት እንደሆነች ያመለክታል። አባቶቻችን “ሥርዓተ ሰማይ ተሠርዓ በዲበ ምድር - የሰማይ ሥርዓት በምድር ላይ ተሠራ”[98] እንዲሉ፥ በዚህ ምድር የሚከናወነው የአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ በሰማይ በብርሃናውያን መላእክት በጸጋው ዙፋን ዙሪያ የሚካሄደው አምልኮ (አገልግሎት) አርአያና አምሳል ነው። ወደ ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንገባ የምናያቸው ቅዱሳት ሥዕላት፣ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ሻማው፥ መቅረዙ፥ ዕጣኑ የልቡናችንን አሳብ ወደ ሰማያዊው ዓለም ከመውሰድ ባሻገር፥ መንፈሳዊው ዓለም በመካከላችን የመገኘቱ እውነተኛ ምልክቶች ናቸው።

---

[97] መጽሐፈ ሰዓታት፡ “ኵሎሙ ዘዘወትር”፣ ገጽ 119 እና 121፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሌሊትና በቀን በየሰዓቱ እንዲደርስ አድርጎ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይዘት፡- “ስብሐታተ መኃልይ ዘይደሉ በመዐልት ወበለያልይ” (በቀንና [በሌሊት ሊደርሱ የሚገባቸው] የዝማሬ ምስጋናዎች) ሲል ገልጾ፥ “መጽሐፈ ብርሃን” በማለት ሰይሞታል። በ1528 እ.ኤ.አ.የተጻፈውን የብራና መጽሐፍ የማይክሮ ፊልም ቅጂ EMML 4493, f. 66b ላይ ያለውን ገለጻ ይመልከቱ። “ኵሎሙ ሠራዊተ መላእክት መንፈሳውያን” በማለት የሚጀምረው ዝማሬ፥ “በእንተ ቅኔ ሠራዊተ መላእክት” የሚል ርእስ ተሰጥቶት EMML 4493, f.48b-49a ላይ ይገኛል። ስለዚህ የብራና መጽሐፍ ቅጂ፥ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ያዘጋጁትን ዝርዝር ገለጻ በሚከተለው ካታሎግ ላይ ይመልከቱ፡- Getatchew Haile, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville*, Vol. X: Project Numbers 4001-5000 (Collegeville: MN: HMML, 1993) pp. 181-187.

[98] “የቅዳሴ ታሪክ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ንባቡና ትርጓሜው፡ 1988፣ ገጽ. 7።

ስለዚህ በእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ፊት ከቅዱሳን መላእክት ጋር የምንፈጽመውን አምልኮ አሁን በምድር ላይ እንለማመደዋለን ማለት ነው። በቅዳሴ የሚሠዋው መሥዋዕት፥ የምትገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ ስለሆነና ዘላለማዊ የሆነው ሰዓት ወደእኛ ስለ መጣ፥ የቅዳሴው አገልግሎት በሰማያዊው መንግሥት የሚደረግ አገልግሎት ነው ማለት እንችላለን።[99] ስለዚህ ለቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ከቤታችን ስንነሣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ጉዞ እንደምናደርግ እናስባለን፤ በቤተ ክርስቲያን የምንፈጽመውን አምልኮ ደግሞ በአባታችን መንግሥት ውስጥ እንደምናደርገው እያሰብን በደስታና በሐሤት ሰማያዊ አባታችንን በቤተ መቅደሱ እናመልከዋለን። መንግሥተ ሰማያት ምንም እንኳ በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ባትገለጥም፣ በአማንያን መካከል ሕልው ስለሆነች እንደ ተሰጠችን እናስባለን። ይህን የተረዱ ጥንታውያኑ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ በተተረጐመው "መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት"[100]፡- "ወሶበ ቆምነ ውስተ ጽርሕከ ቅዱስ፥ ንሔሊ ከመ ንሕነ ቀዋምያን በውስተ ሰማያት[101] - በቅዱሱ [መቅደስህ] ውስጥ በቆምን ጊዜ፥ በሰማያት የምንቆም መሆናችንን እናስባለን" ብለዋል። በተጨማሪም፥ ካህናት ዘወትር በኪዳን ጸሎት፡- "ለከ እንዘ ንዌድስ ወኢናዕርፍ (ወኢነዐርፍ) ለዝሉፉ በአልባቢነ ናስተማስል አምሳለ መንግሥትከ ቦቱ"[102] እንደሚሉት፥ ዘወትር ሳናቋርጥ (ሳናርፍ) ሰማያዊ መንግሥቱን በሕሊናችን እየሣልን[103] እግዚአብሔር አብን ከውድ ልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ እና

---

[99] ኦርቶዶክሳዊው ምሁር Nicolas Cabasilas በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ምሥጢረ ቍርባን አፈጻጸም ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚገለጥ በአጽንዖት ሲጽፍ፡ "the Kingdom itself is none other than this chalice and this bread" – [የእግዚአብሔር] መንግሥት ራሱ ከዚህ ጽዋና ኅብስት ሌላ (የተለየ) አይደለም" ይላል። See Nicolas Cabasilas, "Divinae Liturgiae Interpretatio, Ch. 43, 461CD," quoted in Constantine N. Tsirpanlis, *The Liturgical and Mystical Theology of Nicolas Cabasilas*, (New York, [No Publisher],1979) p. 18።

[100] ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰት ለመለየት ይህ መጽሐፍ "ሰዓታት ዘግብፅ" ይባላል።

[101] *መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት*፡ "ሰዓታት ዘመንፈቀ ሌሊት" (ቫቲካን ማተሚያ ቤት፡ ሮም፡ 1944 ዓ.ም) ገጽ 238።

[102] "ኪዳን [ዘሠርክ]" መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፡ 1988፣ ቍ. 17፣ ገጽ.41።

[103] "Testament of the Lord" በሚል ርእስ ከሶርያ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመው ይህ የጸሎተ ኪዳን ክፍል፥ ግእዙ "ናስተማስል አምሳለ መንግሥትከ" ያለውን "picturing your Kingdom" ሲል ይተረጕመዋል። *The Testament of Our Lord: Translated into English from the Syriac*

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እናመሰግነዋለን። ስለዚህ በምድራዊው መቅደስ የሚካሄደው ቅዳሴ ወደ ሰማያዊ ዓለም የሚወስደንና ያለማቋረጥ ለልዑል እግዚአብሔር የሚቀርበው የመላእክት ቅዳሴ መገለጫ ነው።

## ፳. በደስታና በሐሤት የሚከናወን አምልኮ

በሰማያት በዙፋኑ ለተቀመጠውና ለታረደው በግ (ራእ. 5፥6-12) ያለ ዕረፍት ቍጥራቸው እጅግ የበዛ ቅዱሳን መላእክት ምስጋና እንደሚያቀርቡ፥ እኛም በምድር ሆነን ያን የመላእክት ምስጋና ስንደግመው በቃላት ሊገለጽ የማይችል ሐሤት ይሰማናል። በመለኮታዊ ባሕርዩ በዓለሙ ሁሉ ምሉዕ የሆነውና በሰማያት ከባሕርይ አባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚመሰገነው ጌታ ክርስቶስ፥ ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን መሥዋዕቱን እየሠዋች ስታመልከው በመካከላችን ስለሚገኝ የመንፈሳዊው እርካታችን ምንጭ እርሱ ነው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያናችን በጸሎተ ቅዳሴ ፦ "በፊትህ እንቆም ዘንድ፥ አንተንም እናገለግል ዘንድ በእርሱ [በቅዳሴው መሥዋዕት] ተድላን አደረግህልን"[104] ትላለች። ይህ መንፈሳዊ ደስታና ሐሤት ካልተሰማን፥ አምላካችንን እንደሚገባው እያመለክነው አይደለም ማለት ነው። የውስጣችንን ደስታ ከሚነጥቀንና በእግዚአብሔር ፊት አጸያፊ ከሆነው ከኃጢአታችን እንዲያነጻን፥ እንዲሁም በቅዳሴው አገልግሎት የሚገኘውን መንፈሳዊ ሐሤት እንዲያጎናጽፈን አምላካችንን እየለመን ሠራዒው ካህን ምሥዋዑ ፊት ቆሞ ይህን ጸሎት ይጸልያል፦

> የአባታችንን የአብርሃምን መሥዋዕት የተቀበልህ አምላካችን እግዚአብሔር ፥ ስለ ልጁ ስለ ይስሐቅም ፈንታ ቤዛ ሊሆነው በጉን አዘጋጅተህ ያወረድህለት ፥ አቤቱ እንዲሁ መሥዋዕታችንንና የዚህን የዕጣናችንን መዓዛ ተቀበል ፤ በእርሱም ፈንታ የይቅርታህንና የቸርነትህን ብዛት ከላይ ላክልን ፥ ከክፉ ኃጢአታችን ሽታ ሁሉ ንጹሐን እንሆን ዘንድ ፤ ሰውን የምትወድ ሆይ ፥ በንጽሕናህ ምስጋና ፊት እናገለግል ዘንድ የበቃን አድርገን ፥ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ ፥ በእውነትና በንጽሕና በደስታና በሐሤት ።[105]

በንጽሕና የሚመለከውን አምላክ በደስታና በሐሤት ከማምለክ በላይ በዚህ ምድር የሰውን ልጅ የሚያስደስት ምን ነገር አለ? "ቅዳሴ" ብለን በምንጠራው ውብ የሆነ አምልኮ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ጌታ ደስታ እንድንገባ ትጋብዘናለች።

---

*with Introduction and Notes*, trans. James Cooper and Arthur John Maclean (Edinburgh: T. & T. Clark, 1902) p. 96።

[104] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 48፣ 109።

[105] "ሥርዓተ ቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.151-152፣ ገጽ 71-72።

በቅዳሴው የተሠዋውን የክርስቶስን *ሥጋውን*ና ደሙን የተቀበለ ማንኛውም አማኝ፥ "ሰውን ለማዳን ሰው ከሆነ ከአምላካዊ ምሥጢር በተቀበልሁ በእኔ በአንደበቴ ምስጋናህን፥ በልቡናዬ ሐሤትን፥ በሰውነቴም ደስታን ምላ"[106] በማለት ይጸልያል። እንደ ቅዳሴው ዋነኛ ዓላማ የአገልግሎቱ ተሳታፊ የሆኑት በሙሉ *ሥጋውን*ና ደሙን ሲቀበሉ ደግሞ ይህ ሐሤት የቤተ ክርስቲያኒቷ ይሆናል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በተሰጠው መክሊት ያተረፈውን እያንዳንዱን አገልጋይ፥ "ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" (ማቴ. 25፥31) ሲለው፥ ወደ እግዚአብሔር *መንግሥት* ግባ ማለቱ ነው። የምእመናን ኅበረት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን "የጌታ ደስታ" ተብሎ ወደ ተጠቀሰው ወደ እግዚአብሔር *መንግሥት* የምትወሰድበት *መንገድ* ከቅዱስ ቍርባን ውጪ ሌላ ሊሆን አይችልም ። የደስታዋ ምንጭና ፍጻሜ መንፈሳዊ ሐሤትን የሚያጎናጽፈው ምሥጢር ቅዱስ ቍርባን ነው፡፡ [107] ስለዚህ ቅዱስ ቍርባን የሚከብርበት አገልግሎት (የቅዳሴው) ዋነኛ ዓላማ በእግዚአብሔር *መንግሥት* የምንጠግበውን የጌታን ደስታ በዚህ ምድር እንድንለማመድ ማድረግ ነው። በቅዳሴው አገልግሎት መንፈሳዊ ሐሤት እየተሰማቸው በእውነትና በንጽሕና የሚያገለግሉ የእግዚአብሔር ልጆች፥ በዚህ ምድር አስቀድመው የቀመሱትን የእግዚአብሔርን *መንግሥት* መንፈሳዊ ጣዕም፥ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ ቤት (ዮሐ. 14፥1-3) ከወሰዳቸው በኋላ ለዘላለም ይጠግቡታል፦

> ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ያን ጊዜ [በጌታ ዳግም ምጽአት] ለመረጣቸው ለወዳጆቹና ለጻድቃኖቹ የብርሃን ድንኳን ይተከላል፥ ሰባት መሠወሪያ ያለው የእሳት መጋረጃ ይዘረጋል፤ የካህናት አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስም ከዚያ ወደዚህ ምሥጢር ይገባል፥ ለግብር ሥርዓት ቀሳውስትን በቀኙ፥ ዲያቆናትንም በግራው ያቆማቸዋል፤ የምሥጢርን ሥርዓት ያሳያቸው ዘንድ።[108]

ወደ *መንግሥቱ* ተነጥቃ የሰማያዊው ማዕድ ተካፋይ የምትሆነው ከዓለሙ ተለይታ የተጠራችው የምእመናን ኅብረት (*ኤክሊሲያ*)[109] ናትና፥ ሁላችንንም ለዚህ ሰማያዊ ምሥጢር የበቃን ያድርገን።

---

[106] "እም ድኅረ ተመጥዎ ቍርባን" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 119፣ ገጽ 126።

[107] Alexander Schmemann, *For the Life of the World: Sacramnets and Orthodoxy* (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1982) p. 25.

[108] "ቅዳሴ አትናቴዎስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.93-93፣ ገጽ 262።

[109] በግሪኩ ἐκκλησία [ekklēsia or ecclēsia] የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከዓለም ተለይታ የተጠራችውን የምእመናን ጉባዔ (ኅብረት) ነው፡፡ ይህም በእኛ ቋንቋ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡ ይህ ቃል

## 1.2. የቅዳሴ ውበት

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ብትታነጽም፥ በባሕርይዋ ሰማያዊት ስለ ሆነች በውስጥዋ በሚደረገው የአምልኮ ሥርዓት በሙሉ ወደ ሰማያዊው ዓለም ትወስደናለች። ወደ ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንገባ፥ የምናያቸው ቅዱሳት ሥዕላትና የመቅደሱ ውበት፥ የቆምንበትን የተቀደሰ ሥፍራ "በምድር ላይ ያለ ሰማይ" ብለን እንድንጠራው ያስገድዱናል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፥ በእናቱ በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፥ በቅዱሳን መላእክትና በሌሎች የእግዚአብሔር ወዳጆች በሆኑ ቅዱሳን ሁሉ ሥዕላት ታጅበን የቅዳሴው አገልግሎት ተሳታፊ ስንሆን፥ የማይታየው ሰማያዊ ዓለም በመካከላችን እንዳለ እናስተውላለን።[110] ስለዚህ የምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ከሰማያዊው የመላእክት ቅዳሴ ጋር ኅብረት እንዳለው ልብ እያልን፥ የልቡናችን ዓይኖች ተከፍተው ማየት ከቻሉ ግልጽ የሆነውን የዚህን ሰማያዊ አምልኮ (የቅዳሴን) ውበት እናያለን።

በዓለም ሁሉ የምትገኘው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንደየአገሩ ቋንቋና ባህል መጠነኛ የሥርዓተ አምልኮ ልዩነት ቢኖራትም፥ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ኅበረት ያለው የቅዳሴው አገልግሎት የራሱ የሆነ ልዩ ውበት እንዳለው በአሕዛብ እንኳ ተመስክሮለታል። በ10ኛው ምእት ዓመት የኪይቭ መስፍን ቭላድሚር የራሽያን (ሩሲያ) ብሔራዊ እምነት አድርጎ እንዲቀበል ከላቲኖች፥ ከአይሁድ፥ ከሙስሊሞችና ከግሪኮች ጥያቄ ቀርቦለት ነበር። የመስፍኑ አማካሪዎችም "የራሱን አምልኮ የሚያከፋፋ ስለሌለ መልእክተኞችህን ወደ ሁሉም ላክና እንዴት እንደሚያመልኩ ይመልከቱ"[111] ብለው መከሩት፤ መስፍኑም ምክሩን በተግባር ላይ አዋለ። የመስፍኑ መልእክተኞች በአይሁድ፥ በሙስሊሞችም ሆነ በሮማ ካቶሊክ የአምልኮ ሥርዓቶች አልተማረኩም። ወደ ቍስጥንጥንያ ሂደው ሥነ-ሕንጻዋ እጅግ

---

የሐዋ. 11፥26 እና 1ቆሮ. 15፥9 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን፥ ይህች የምእመናን ጉባዔ ከዓለሙ ተለይታ የተጠራችው፥ ከዓለሙ ርኵሰት ጋር ኅብረት የሌላትና የተቀደሰች እንድትሆን ነው (2ቆሮ. 6፥17፣ 1ጴጥ. 1፥16)።

[110] Kallistos Ware, *The Orthodox Church* (New York: Penguin, 1993) p. 271.

[111] Taft, *Beyond East and West*, p. 111.

በሚማርከው *በአጊያ ሶፊያ*[112] ካቴድራል ስለ ተመለከቱት የግሪኮች ኦርቶዶክሳዊ አምልኮ ግን የሚከተለውን ብለው ነበር፡-

> ግሪኮቹ አምላካቸውን ወደሚያመልኩበት ካቴድራል ወሰዱን፤ ከዚያም በሰማይ ወይም በምድር ላይ መሆናችንን አላወቅንም። በምድር ላይ እንደዚህ ዓይነት አንጸባራቂ ውበት የለም፤ እንዴት እንደምንገልጸውም ቃላት ያጥረናል። እግዚአብሔር በዚያ ቦታ በሰዎች መካከል እንደሚያድር ብቻ እናውቃለን፥ አገልግሎታቸውም ከሌሎች ዜጎች ሥርዓቶች የበለጠ ነው። ያን ውበት መርሳት አንችልም።[113]

የቭላድሚር መልእክተኞች እንደ መሰከሩት በእያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ  በቃላት ሊገለጽ የማይችል የአምልኮ ውበት (ጣዕመ ቅዳሴ) አለ።

በኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ያለውን ውበት የተረዱ ጥንታውያን አባቶቻችን በቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስም በሰየሙት የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ፥ "ንነጽር ሥነ ስብሐቲሁ ለአምላክነ - የአምላካችንን [የምስጋናውን ውበት እንመልከት]"[114] ብለውናል። የፈጣሪያችንን ጌትነቱንና ድንቅ ሥራውን እጅግ ውብ አድርጎ በፈጠረው ክቡር ፍጥረቱ[115] እንደምናይ፥ የአምልኮ ሥርዓቱም አምላካችን የሚወደስበትንና የሚመለክበትን የምስጋናውን ውበት ይገልጽልናል። ስለዚህ በጸሎተ ቅዳሴ በኅብረት የምናመሰግሰው፥ እንዲሁ የልምድ አገልግሎት አድርገነው ሳይሆን በፍጥረታት ሁሉ ለሚመሰገነው ለልዑል እግዚአብሔር ክብርን ሁሉ እየሰጠንና በቅዳሴው የሚንጸባረቀው የምስጋናው ውበት (ጣዕመ ቅዳሴው) ልባችንን በሐሤት እየመላው ሊሆን ይገባል። በዚህ መልኩ አምላካቸውን ያመልኩ ዘንድ፥ ካህኑ ጸሎተ ዕጣንን ካደረሰ በኋላ ምእመናንን፡- "እግዚአብሔርስሙን መፍራትን፥ የአምልኮቱን ውበትና የረድዔቱን ጸጋ ይስጣችሁ"[116] እያለ ይባርካቸዋል። እኛ ልንገነዘበው በማንችለው መንገድ ይህ ግዙፍ ዓለም፥ እንደ አንድ ትልቅ መቅደስ ሆኖ ፍጥረታትን ሁሉ በልጁ ቃልነት ለፈጠረው ለእግዚአብሔር አብ፥ ለአንድ ልጁ እና ሕይወት ሰጭ (ማሕየዊ) ለሆነው ለቅዱሱ መንፈስ ምስጋናን ያቀርባል። በፍጥረቱ ሁሉ ለሚመለከው አምላክ ቤተ ክርስቲያናችን፡- "ስብሐት

---

[112] እነዚህ ሁለት የግሪክ ቃላት (Αγία Σοφία – *Agia/Hagia Sophia*)  በአማርኛ "ቅድስት ጥበብ" የሚል ትርጉም ይሰጡናል።

[113] Taft, *Beyond East and West*, p. 112.

[114] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ" *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 2000፣ ቍ. 9፣ ገጽ 311።

[115] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ" *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፡ 1988፣ ቍ. 9፣ ገጽ 362።

[116] *ጸሎተ ዕጣን* (አዲስ አባባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.) ገጽ 63።

ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ - ልዩ ሦስት ለሚሆኑ ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይገባል"[117] እያለች የአምልኮ ምስጋና ከምታቀርብበት የሥርዓተ ቅዳሴ ውበት የበለጠ፥ የእግዚአብሔር ልጆችን ልብ ሊማርክ የሚችል ምንም ነገር በዚህ ምድር የለም።

በቅዳሴ አገልግሎት የምናየው የራሱ የሆነ ውበት ያለው የአምልኮ ሥርዓት፥ በስሜት ሕዋሳቶቻችን በሙሉ እንድንቀደስ የሚያደርገን ነው። በቅዱሳት ሥዕላት የተዋበውን ቤተ መቅደስ፥ ጽላቱ የተቀመጠበትን መንበረ ታቦት፥ በመንበሩ ላይ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት፥ የካህናቱንና የዲያቆናቱን ልብሰ ተክህኖ፤ ካህናቱ ጽንሐዎችንና የእጅ መስቀሎችን፥ ዲያቆናቱ ደግሞ ጧፍና በመጾር የተያዘ ትልቅ መስቀል ይዘው የሚያደርጉትን ዑደት ዓይኖቻችን ይመለከታሉ። በዚህም ዕይታችን ንጹሕና የተቀደሰ ይሆናል። ጆሮዎቻችን ደግሞ የቅዳሴውን ጸሎት፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ንባባት እንዲሁም ያማረ የቅዳሴውን ጣዕመ ዜማ ያደምጣሉ። የቅዳሴው ተሳታፊ የሆኑ ምእመናን በትሑትና በዓቢይ ዜማ ለካህናቱና ለዲያቆናቱ ትእዛዛት እንዲሁም ለተለያዩ ንባቦች የሚሰጧቸው መልሶች (የሕዝብ ተሰጥዎ) ደግሞ፥ አንደበታቸው ለምስጋና እንዲከፈት ያደርገዋል። የዕጣኑ ያማረ መዓዛ ሁለመናችንን ሲያውደው፤ መስቀሉን፥ ቅዱሱን መጽሐፍና ቅዱሳት ሥዕላትን በእጃችን እየዳሰስን እንሳለማ ቸዋለን። የቅዳሴው ፍጻሜ ላይ ዘላለማዊ ሕይወት የሚያስገኘውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበላላን። ስለዚህ ቅዳሴ እንደ ቃሉ ትርጉም "ምስጋና" ብቻ ሳይሆን በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ የምንቀደስበት ውብ የሆነ አምልኮ ነው። በቅዳሴ ዲዮስቆሮስ እና በቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ሠራዒው ካህን፥ "ደምር ፈሪሆተከ ውስተ አልባቢነ፥ ወሥነ አምልኮትከ ውስተ ሕሊናነ - አንተን መፍራትን በልቡናችን፥ [የአምልኮትህን ውበት] በሕሊናችን ጨምር"[118] በማለት በጎ የሆነ አምልኮ እንዲኖረንና የቅዳሴውን ውበት የምናይበትን ጸጋ እንዲሰጠን እግዚአብሔርን ይለምናል።

---

117 "ሥርዓተ ቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 126፥ ገጽ 64።

118 "ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 82፡ ገጽ 425፤ "ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ" ቍ. 110፡ ገጽ.351።

## 1.3. የቅዳሴ መንፈሳዊ ዕሴቶች (ጥቅሞች)

*መድኃኒታችን* ኢየሱስ ክርስቶስ በሁለት ወንበዴዎች መካከል በተሰቀለበት ሰዓት፥ የሮማ ወታደሮች (ጭፍሮች) የሁለቱን ወንበዴዎች ጭኖችን ሲሰብሩ፥ ከጭፍሮቹ አንዱ የጌታን "ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ" (ዮሐ. 19፥34)። እንደ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ትምህርት፥ ከጌታ ጎን የፈሰሱት ደምና ውኃ የጥምቀትና የቅዱስ ቍርባን ምሳሌዎች ናቸው። ጌታ ከጎኑ ውኃና ደም አፍስሶ ቤተ ክርስቲያንን ወለዳት።[119] ከውኃና ከመንፈስ ተወልደው (ዮሐ. 3፥5) በምሥጢረ ጥምቀት አማካይነት ልጅነትን ያገኙ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የዘላለማዊ ሕይወት ምግብ የሆነውን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በቤቱ እየተመገቡ ያድጋሉ።[120] ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት መካከል፥ የተጠመቁ አማንያንን ክርስቲያናዊ ሕይወት እውን የሚያደርገው ቅዱስ ቍርባን ስለሆነ፥ ይህን የሕይወት መድኃኒት መቀበል እስካላቆሙ ድረስ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ሕያው ነው። ጸሎተ ቅዳሴውን በማስተዋል የሚያዳምጡና ተሰጥዎውን በመመለስ የአገልግሎቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ምእመናን የቅዳሴውን መሥዋዕት (ቅዱስ ቍርባን) ሳይቀበሉ መኖር አይችሉም። ስለዚህ የቅዳሴው የመጀመሪያ መንፈሳዊ ዕሴት የአገልግሎቱን ተሳታፊዎች በሙሉ ወደ መሥዋዕቱ መምራት መቻሉ ነው።

### ምሪት ወደ ቅዳሴው መሥዋዕት

*መድኃኒታችን* ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል፡- "ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው … ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፥ እኔም በእርሱ እኖራለሁ" (ዮሐ. 6፥54-56) ብሎ ቃል እንደገባልን፥ የቅዳሴውን መሥዋዕት የሚቀበሉ የእግዚአብሔር ልጆች ጌታን ተዋሕደውና የእርሱ ማደሪያዎች ሆነው ይኖራሉ። ክርስቶስ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ (ኤፌ. 5፥23)፥ አማንያን ደግሞ አካሉ የተባለች የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለሆኑ፥ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ የተለየ ሕይወት በፍጹም ሊኖራቸው አይችልም። የቅዱስ

---

[119] ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ላይ የጻፈው ትርጓሜ፡- See "St. Cyril of Alexandria, On John, 12, PG 74.677B," quoted in Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy,* p. 25.

[120] "ሥርዓተ ቅዳሴ ዘይደሉ ለቀሲስ ወለዲያቆን ወለኵሉ ሕዝብ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፤ ቍ.9፤ ገጽ 7።

ዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀ መዝሙርና የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ አግናጥዮስ፥ ለኤፌሶን ምእመናን በላከው ጦማር ቅዱስ ቍርባንን፦ ከዘላለማዊ ሞት አምልጠን በክርስቶስ ለዘላለም ሕያዋን ሆነን የምንኖርበት መድኃኒት[121] በማለት ይገልጸዋል። ሠራዒው ዲያቆን ቅዱስ ቍርባን በሕያውነት የሚያኖር መድኃኒት መሆኑን በግልጽ እያወጀ ቅዳሴ እግዚእ በሚቀደስበት ጊዜ ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰደውን ትእዛዝ እንዲህ በማለት ያስተላልፋል፦ "ወደ ሕይወት መድኃኒት እንቅረብ፥ ጸጋ ሆኖ የተሰጠንንም ሥጋውንና ደሙን በእግዚአብሔር ጥበብ እንቀበል።"[122] ይህ ግልጽ የሆነ የቅድስና ጥሪ ነው። "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" (1ጴጥ. 1፥15) ያለን የአምላካችን ፈቃድ የእኛ መቀደስ (ቅድስና) ነውና፥ ማንም በራሱ ቅድስናን ማግኘት ስለማይችል፥ ጸጋ (ስጦታ) ሆኖ የተሰጠንን የጌታን ሥጋና ደም በመቀበል በቅድስና እንድንኖር ይህ የቅዳሴ አዋጅ ያስተምረናል።

በቅዱስ ዮሐንስ መልእክት፦ "የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል" ተብሎ እንደ ተጻፈ (1ዮሐ. 1፥7) ለኃጢአታችን ይቅርታ የተሠዋውን መሥዋዕት የቅዳሴው ተሳታፊ በመሆን ስንቀበል ሥርየተ ኃጢአትን እናገኛለን። ከባድ ሸክም ከሆነብን ኃጢአት ነጽተን ዕረፍት ስናገኝ ደግሞ፥ ኃጢአት ካመጣብን የሥጋ ድካሞችም እንላቀቃለን፦ "አቤቱ [አምላካችን ሆይ፦] ፈቃድህን በሁላችን ልቡና ሙላ፤ ከኃጢአትም ሁሉ፥ [ከመዳራትም] ሁሉ፥ ከቂምና ከቅንዓት ሁሉ፥ ከክፉም ሥራ ሁሉ፥ ሞትን ከምታለብስ ክፉን ነገር ከማሰብ አንጻን።"[123] የክርስቶስ ደም ከሞተ ሥራ ሕሊናን ያነጻልና (ዕብ. 9፥14) በእርሱ ሕሊናችን ከክፉ አሳብ ነጽቶ፥ ልባችንም ከቂምና ከበቀል ነጻ ሆኖ ሁለመናችን የተቀደሰ ይሆናል። ከቅዱሱ

[121] የእንግሊዝኛው ትርጉም፦ "the medicine of immortality, and the antidote which prevents us from dying, [ . . . ] that we should live in God through Jesus Christ leading to life in Jesus Christ forever" ይላል፡፡ "Epistle of Ignatius to the Ephesians, Chap. XX," *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* eds. Alexander Roberts and James Donaldson, Vol. 1 (Michigan: WM. B. Eerdmans Publishing Company, 1979) ገጽ 57 ይመልከቱ፡፡

[122] "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 13፣ ገጽ 145. Robert Beylot ያሳተመውን "መጽሐፈ ኪዳን" ይመልከቱ፦*Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Robert Beylot (Louvain: Peeters, 1984) p. 34.

[123] "ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 56፣ ገጽ 99።

ምሥጢር እንድንቀበል የፈቀደልንን እግዚአብሔር እያመሰገነ፥ ሠራዒው ካህን የተቀበልነው መሥዋዕት "ነፍስን፥ ሥጋንና መንፈስን ለማደስ"[124] ይሆን ዘንድ አምላካችንን ይለምናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ምእመናንን፦ "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፥ ነፍሳችሁም፥ ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ" በማለት እንደባረካቸው (1ተሰ. 5፥23) ራሱን ስለእኛ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበውን የሰላም ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስን በቅዱስ ቊርባን ስንቀበል በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ እንቀደሳለን።

## የአማንያን ኅብረት

ቅዱስ ቊርባንን በመቀበል የአንዱ የክርስቶስ አካል ክፍሎች (ብልቶች - 1ቆሮ. 12፥27) ከመሆናችን በተጨማሪ በምሥጢረ ቊርባን አማካኝነት፥ እርስ በርሳችን መንፈሳዊ ኅብረትና አንድነት ይኖረናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅበረት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለ ሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና" ሲል ለቆሮንቶስ ምእመናን እንደጻፈው (1ቆሮ. 10፥16-18)፥ በቅዱስ ቊርባን ያለን ሱታፌ አንድነታችንን ያረጋግጣል። በቅዱስ ቊርባን ኅብረት ያላቸው አማንያን፥ "በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል" ተብሎ አንደ ተጻፈ (1ቆሮ. 12፥13) ከመንፈስ ቅዱስ የሆነውን አንድነት ያገኙ ናቸው። ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ ባገናዘበ መልኩ፥ ሠራዒው ካህን ሥርዓተ ፈትቶን በሚፈጽምበት ሰዓት፦ "የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን፤ በዚህም ጽርስፎራ (በሥጋው በደሙ) አድነን፤ ለዓለሙ ሁሉ በምትሆን በአንተ ለዘለዓለሙ ሕያዋን እንሆን ዘንድ"[125] ይላል። የተጠመቁ አማንያን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ያላቸው ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ሲጠራ፥ ይህ አንድነት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ

---

[124] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 140፣ ገጽ 131።
[125] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 54፣ ገጽ 111።

አካል መሆኗን እውን ያደርጋል።[126] በቍጥር ብዙዎች ብንሆንም የክርስቶስ አካል የሆነችው የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለሆንን፥ የአንዱ የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎችም ነን፤ ሐዋርያው "እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን" በማለት እንደ ጻፈው (1ቆሮ. 10፥17)። ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ የተረዱ አባቶቻችን፥ "ክርስቶስ ከነበረበት ዘመን የራቅንና ብዙዎች ስንሆን"[127]፥ የአንዱ የክርስቶስ አካል አባላት (ከእርሱ ጋር አንድ) ያደርገን ዘንድ በመልክዐ ቍርባን፡ "እንዘ ብዙኃን ንህነ እም ጾታ ዘመን ዘዚአሁ … መለያልየ አሐደ ይረስየነ ምስሌሁ"[128] በማለት ዘምረዋል። እንዲሁም የቅዳሴው መሥዋዕት (የጌታችን ሥጋና ደም) "አንድ የሚያደርግ" መሆኑን እየመሰከረ ሠራዒው ዲያቆን ከመጽሐፈ ኪዳን በተወሰደው ጸሎት፥ ይህን ኅብረት ይሰጠን ዘንድ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ልመና ያቀርባል፡- "አንድ ስለምታደርግ ሥጋውና ደሙ፥ እግዚአብሔር በይቅርታው አንድ ያደርገን ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን።"[129]

ከላይ በተጠቀሰው የሥርዓተ ፈትቶ ጸሎት ሠራዒው ካህን በመንፈስ ቅዱስ ስለሚሆነው አንድነታችን ብቻ ሳይሆን፥ "ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርስፎራ" (በዚህ ቍርባን ፈውሰን) በማለት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ከሚያናጋ የመከፋፈል ደዌ እንፈወስ ዘንድ ይጸልያል።[130] ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናንን በቅዱስ ቍርባን ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ እንደሚሆኑ ከነገራቸው በኋላ (1ቆሮ. 10፥16-17) ቅዱስ ቍርባንን ለማክበር በማኅበር ሲሰባሰቡ መከፋፈል ስለተፈጠረ ገሥጿቸው ነበር (1ቆሮ. 11፥18-22)። "አጋፔ" በመባል የሚታወቀው የፍቅር

[126] José L. Bandrés Urdániz, M. Afr., *A Glance Behind the Curtain: Reflections on the Ethiopian Celebration of the Eucharist* (Adigrat: Master Printing Press P.L.C., 2008) p. 84.

[127] "እንዘ ብዙኃን ንህነ እምጾታ ዘመን ዘዚአሁ" የሚለውን የግእዙ ዐረፍተ ነገር፥ ቃል በቃል ሳይሆን የዐውደ ንባቡን አሳብ በመውሰድ እዚህ ላይ እንደ ተጠቀሰው በJosé Urdániz መጽሐፍ ላይ ተተርጕሟል። See Urdániz, *A Glance Behind the Curtain*, p. 87.

[128] "መልክዐ ቍርባን" መጽሐፈ ሰዓታት፡ 1975 ዓ.ም.፣ ገጽ 515።

[129] "በእንተ ቅድሳት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 66፣ ገጽ 51. Robert Beylot ያሳተመውን "መጽሐፈ ኪዳን" ይመልከቱ፡-*Testamentum domini éthiopien,* ed and trans. Robert Beylot (Louvain: Peeters, 1984) p. 79.

[130] Urdániz, *A Glance Behind the Curtain*, p. 89.

ማዕድ ላይ ሀብታሞቹ ከድሆቹ ተለይተው የሚበሉትን የራሳቸውን ምግብ ስላመጡ፥ በዚህ መለያየትን በፈጠረው ሥራቸው "የእግዚአብሔርን ማኅበር" ወይም ቤተ ክርስቲያንን እንደናቁና እንዳቃለሉ ነግሯቸዋል (1ቆሮ.11፥22)። ነገር ግን በክርስቶስ አንድ ነን ብለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስን ኅብረት አግኝተው በአንድ አሳብ የተስማሙ መሆን አለባቸው (ፊል. 2፥ 1-3)። ከ5ኛው ምእት ዓመት (451 ዓ.እ.) ጀምሮ፥ በየዘመናቱ ኑፋቄና መለያየት በተባሉ ደዌያት (በሽታዎች) ምክንያት ክርስቲያኖች ተከፋፍለው የክርስቶስ አካል ከሚሆኑበት ኅብረት አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ይህም የሚታወቀው የእምነት ልዩነት ያላቸው ክርስቲያኖች በአንድ ላይ የቅዱስ ቍርባን ተሳታፊ መሆን ባለመቻላቸው ነው። ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን፥ ከዚህ የመለያየት ደዌ ተፈውሰን የክርስቶስ ሙሽራና አካል የሆነችው የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እውን ይሆን ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው ጸሎት አምላኳን ዘወትር ትለምናለች።

ከዚህ ጸሎት በተጨማሪ፥ የቍርባኑ ኅብስት የሚያመለክተውን አንድነት መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን ስለአንድነታችን ትጸልያለች። በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ስም የተሰየመው የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ እንዲህ ይላል፡-

> አቤቱ አምላክ ሆይ እንማልድሃለን፥ ይህች ኅብስት በተራራና በኮረብታ፥ በበረሓና በቈላ መካከል የተበተነች ስትሆን እንደ ተሰበሰበች፥ ተሰብስባም አንዲት ፍጽምት ኅብስት እንደ ሆነች፥ እንዲሁ እኛንም በመለኮትህ ከክፉ የኃጢአት አሳብ ሁሉ ለይተህ በፍጹም ሃይማኖትህ ሰብስበን።[131]

ይህ ጸሎት የተወሰደው ዲዳኬ[132] ወይም ትምህርተ ሐዋርያት በመባል ከሚታወቀው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ 9ኛ ምዕራፍ ላይ፡- "ይህ በተራራዎች ላይ ተበትኖ የነበረው ኅብስት ተሰብስቦ አንድ እንደሆነ፥ ቤተ ክርስቲያንህም ከምድር ዳርቻ ወደ መንግሥትህ ትሰብሰብ"[133] የሚል ጸሎት ይገኛል። ለቍርባን የሚሆነው ኅብስት የሚዘጋጅበት

[131] "ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 91፣ ገጽ 176።

[132] *Didache* በእኛ ቤተ ክርስቲያን "ዲድስቅልያ" በመባል ከሚታወቀው መጽሐፍ ጋር አንድ አይደለም። "ዲዳኬ" እና "ዲድስቅልያ" በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስለ ነበራቸው ድርሻ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተጻፈውን ገለጻ ይመልከቱ።

[133] *The Didache: Text, Translation, Analysis, and Commentary*, trans. Aaron Milavec (Collegeville, MN: Liturgical Press, 2003) Ch. 9:4, p. 23.

የስንዴው መባዕ የሚሰበሰበው ደግሞ በተለያየ ቦታ (በኮረብታ ወይም በሜዳ) ተበትኖ ከተዘራው የስንዴ ዘር ስለሆነ፥ በዓለሙ የተበተነችው አንዲቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማያዊ መንግሥቱ እንድትጠቀለል የሚጠይቅ ጸሎት ነው። ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ይህን ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ጸሎት መሠረት አድርገው በተለያየ ክፉ አሳብ የተለያየን የቤተ ክርስቲያን ልጆችን አምላካችን በእምነት አንድ አድርጎ ወደ ቅዱስ ቍርባን ኅብረት ይጠራን ዘንድ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ልመና አቅርበዋል። እንዲሁም በቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ላይ እንደምናነበው፥ ይህንኑ የዲዳኬ ጸሎት በመጥቀስ የቅዳሴው ደራሲ አኰቴተ ቍርባን በሚከናወንበት ሰዓት ከካህናት ወይም ከምእመናን መካከል አሳቡ የተበታተነ ሰው ካለ፥ ሕሊናውን ወደ እርሱ በመውሰድ እንዲረዳው ለአምላኩ ልመና ያቀርባል።[134] ስለዚህ ቅዳሴ ኅብረታችንንና አንድነታችንን ከማጽናት በተጨማሪ፥ በአንድ ልብና አሳብ አምላካችንን እንድናመልክ የሚያደርገን ሥርዓተ አምልኮ ነው።

## ክርስቶስን የመሰለ ሕይወት

የቅዳሴው ዋነኛ ዓላማ ገብቶትና የቅዳሴውን መልእክት በማስተዋል ሰምቶ ቅዱስ ቍርባን የሚቀበል አማኝ በቅድስና ከመኖር ጋር አምላኩን ክርስቶስን ወደሚመስልበት ሕይወት ያድጋል። ለክርስቲያኖች የክርስቶስን ሥጋና ደም ተቀብሎ ከእርሱ ጋር አንድ ከመሆን የበለጠ ምን ቅድስና አለ? ይህ እውነት የገባቸው ቅዱሳን፥ በቅዱስ ቍርባን "የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎች እንሆናለን . . . [ሁለመናችን] ክርስቶስን ይሆናል"[135] ብለዋል። በቅዳሴ አገልግሎት ካህኑ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ የሚለምነው በኅብስቱና ጽዋው ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ሁለመናችንን ይቀድስ ዘንድ በቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ላይም ጭምር ነው። ለዚህም ነው በቅዳሴ ባስልዮስ፥ ሠራዒው ካህን፡- "አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ … በፊትህ ወደ ተሠራው ወደዚህ ቍርባን በአባትህ ፈቃድ መንፈስ ቅዱስን ትልክ ዘንድ፥ ታነጻው ዘንድ እኛንም በቅድሳትህ ታከብረን ዘንድ [እንለምንሃለን]"[136] የሚለው። ይህን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተቀብለው በጌታ ሥጋና ደም የተቀደሱ የእግዚአብሔር ልጆች፥ በሥራና በአንደበት በሚያሳዩት ነገር ብቻ ሳይሆን በሕሊናቸው ጭምር

[134] "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 67-68፣ ገጽ 402።

[135] St. Symeon the New Theologian, quoted in Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy*, p. 24.

[136] "ቅዳሴ ባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 40፣ ገጽ 284።

እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ ይለምኑታል፡- "አቤቱ አምላካችን ሆይ ስለ ስምህ አንተን ደስ ከማያሰኝ አሳብ እንለይ [እንርቅ] ዘንድ መለየቱን[137] ስጠን።"[138] እንዲሁም፥ በቅዳሴው አገልግሎት በዕለቱ የተገኙት ምእመናን በሙሉ ከቆረቡ በኋላ፥ የቅዳሴው መሥዋዕት ተሳታፊ መሆናቸው በሕይወታቸው የሚያመጣውን ለውጥ በሚያመላክት አገላለጽ የሚከተለውን ውብ ጸሎት ይጸልያሉ፡-[139]

> አቤቱ ጌታዬና አምላኬ . . . መንጋህን የወደድህ ቸር ጠባቂ፣ ለበጎችህ ቤዛ ሰውነትህን የሰጠህ . . . ይህ የተቀበልሁት ሥጋህና ደምህ ሥጋዬንና ነፍሴን እንዳያስነቅፍና እንዳያሳድፍ እለምንሃለሁ፣ እማልድሃለሁ። ፈጽሞ የሚያድነኝ፣ አንተን መፍራትንም የሚያስረዳኝ እና ፍቅርህንም የሚያስተምረኝ ይሁን እንጂ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ላንተ አደላ ዘንድ፣ ያለማቋረጥ አመሰግንህ ዘንድ። አቤቱ [ነፍሴን] አንጻት፥ ላንተ መሥዋዕት ትሆን ዘንድ ዳግመኛም አጥራት። ልቡናዬንም እንዲድን መንፈስ ቅዱስ እንዲያድርበትና እንዲመላበት አድርገው፤ ሥጋህንና ደምህን አምኜ ተቀብያለሁና፥ ከካህናቱም እጅ ተቀብዬ በላሁ፥ ላንተ ምስጋና ይገባል፥ ለዘለዓለሙ፡ አሜን።

በቅዱስ ቍርባን የመኖር ሕይወት፥ ለኃጢአት ሞተን (ሮሜ 6፥11) እኛን ለተዋሐደውና በውስጣችን ላለው ለክርስቶስ እንድንኖር ያደርገናል። በኃጢአት ላይ ድልን ስለሚያጎናጽፈንም፥ ሁለመናችን ተቀድሶ፡- "ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፤ ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያ ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ" (ቈላስ. 3፥3-4) ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የገለጸው እውነተኛ መንፈሳዊነትን የተመላ ሕይወት ይኖረናል። ስለሆነም እያንዳንዳችን እንደ ሐዋርያው፡- "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፥ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ፥ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" ማለት እንችላለን (ገላ. 2፥20) ።

137 "ለ" ጠበቅ ብሎ መነበብ አለበት።

138 "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 51፣ ገጽ 152።

139 "ጸሎት እም ድኅረ ማየ መቍረር" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 145-145፣ ገጽ 133-134።

## በጸሎትና በምስጋና ሕይወት ማደግ

ከላይ እንደተመለከትነው ቅዱስ ቊርባንን በመቀበል የቅዳሴው ሙሉ ተሳታፊ ከሆንን፥ የቅዳሴው አገልግሎት በእኛ ላይ አዎንታዊ የሆነ መንፈሳዊ ለውጥ በማምጣት የጸሎትና የምስጋና ሕይወታችንን ያሳድገዋል። በቅዳሴው የትምህርት ክፍል የምንሰማቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት እና የቅዳሴው የተለያዩ ጸሎቶች የቃሉ ሙላት በውስጣችን እንዲኖር ከማድረግ ጋር፥ ምስጋናን የተመላ የጸሎት ሕይወት ያስተምሩናል። ለምሳሌ ከታች የተጠቀሰውንና ሠራዒው ካህን የሚጸልየውን የጸሎተ ወንጌል የመጨረሻ ክፍል በማስተዋል የሚሰማ ሰው፥ ስለሌሎች አስቦ መጸለይንና በነገር ሁሉ አምላኩን ተስፋ ማድረግን ይማራል፡-[140]

> አቤቱ ካንተ ዘንድ የምንሻውን በምንለምንበትና በምንጸልይበት ጊዜ እናስባቸው ዘንድ አስቡን ያሉንን ዳግመኛ አስብ። አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ከእኛ አስቀድመው የሞቱተን አሳርፋቸው፣ የታመሙትንም ፈጥነህ አድናቸው፤ የሁላችን ሕይወት፥ የሁላችንም ተስፋ፥ የሁላችንም አዳኝ፥ የሁላችንም አሥነሽ አንተ ነህና፥ ላንተ ምስጋና እስከ አርያም ድረስ እንልካለን።

በቅዳሴ የምንሰማቸውና እኛም አብረን ተሳታፊዎች የምንሆንባቸው ልብን የሚነኩ የምስጋና ዓይነቶች ደግሞ፥ ሳናቋርጥ በነገር ሁሉ የምናመሰግን ሰዎች እንድንሆን ይረዱናል። ለዚህ "ጸሎተ አኰቴት" በመባል የሚታወቀው የሠራዒው ካህን የምስጋና ጸሎት ዋነኛ ምሳሌ ነው፡-[141]

> ለእኛ በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፥ ይቅር ባይ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሰውሮናልና፥ ረድቶናልና፥ ጠብቆ አቅርቦናልና፥ ወደ እርሱም ተቀብሎናልና፥ አጽንቶ ጠብቆናልና፥ እስከዚህችም ሰዓት አድርሶናልና፤ አሁንም ክብርት በምትሆን በዚች ዕለት በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ይጠብቀን ዘንድ እንለምነው።

በየጊዜው ይህን የምስጋና ጸሎት እየሰማና አብሮ እያመሰገነ ያደገ የቤተ ክርስቲያናችን አባል በነገር ሁሉ አመስጋኝ መሆን ካልቻለ፥ በምንም መልኩ የምስጋናን ሕይወት ሊማር አይችልም።

ቅዳሴ የሚያስገኝልንን መንፈሳዊ ዕሴቶች (ጥቅሞች) ለማጠቃለል ያህል፥ ለቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንሄድበት ዋነኛው ምክንያት ገብቶን በንስሐ እየተዘጋጀን

[140] "ጸሎተ ወንጌል" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 182-183፣ ገጽ 77።

[141] "ጸሎተ አኰቴት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 31-31፣ ገጽ 42።

ለኃጢአታችን ይቅርታ መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም በመቀበል የምንኖር ከሆነ፡-

- የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባልነታችን ይረጋገጣል፣
- በተፈጠርንበት የእግዚአብሔር አርአያና አምሳል እናድጋለን፣
- የጌታን ሕማምና ሞት እያሰብን በምናደርገው የቅዳሴ አገልግሎት ምክንያት የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን በዝቶ ይፈስልናል (ሮሜ 5፥5)፣[142]
- "ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ - የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክልን"[143] እያልን በቅዳሴው አገልግሎት ዘወትር ስንለምን፥ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በየጊዜው እንቀበላለን፣
- በሥጋውና በደሙ የምንቀበለው መድኃኒታችን ክርስቶስ በውስጣችን ህልው ስለሚሆን፥ ወደተፈጠርንበት ዓላማ፥ ይኸውም ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ ኅብረት ወደ ማግኘት[144] እናድጋለን፣
- እንደ እኛ ቅዱስ ቍርባንን ከሚቀበሉ አማንያን ጋር ኅብረት ይኖረናል፣
- በጥምቀት የተቀበልነውን የልጅነት ጸጋ ጠብቀን እንድንኖር ያደርገናል፣
- ሥርየተ ኃጢአትን (የኃጢአት ይቅርታን) እናገኛለን (1ዮሐ. 1፥7)፤ እንዲሁም ለኃጢአት ሞተን ድል አድራጊ ሕይወትን እንጎናጸፋለን ። (ሮሜ 6፥11)
- ክርስቶስን የመሰልን ወይም ክርስቶስን የተሸከምን (ጸዋርያነ ክርስቶስ) እንሆናለን፣
- በክርስቶስ የተሰጠን ዘላለማዊ ሕይወት እውን ይሆንልናል፣
- በመጨረሻም ቅዱስ ቍርባንን መቀበል የመንፈሳዊ ሕይወታችን መገለጫ ይሆንልናል፤ ይህን ሰማያዊ ማዕድ ሳንቀበል በፍጹም መኖር አንችልም። ስለሆነም በቅዱስ ቍርባን የምንቀበለው መድኃኒታችን ክርስቶስ ሕይወታችን ይሆናል።[145] ይህ በቅዱስ ቍርባን የከበረ ሕይወት መለኮታዊ ጸጋን አልብሶ፥

---

142 "ስ" ጠብቆ መነበብ አለበት።

143 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 55፣ ገጽ 111።

144 Union with God – *theosis*.

145 ይህን አሳብ ኦርቶዶክሳዊው ካህን እና ፕሮፌሰር Stanley Harakas በእንግሊዝኛ ሲገልጹት፡- "We live the Sacramental Life or the Mystical Life in Christ" ይላሉ። Stanley S. Harakas, *Living the Liturgy: A Practical Guide for Participating in the Divine Liturgy of the Eastern Orthodox Church* (Minneapolis, MN: Light and Life Publishing Company, 1974) p. 20.

የእግዚአብሔርን አርአያና አምሳል በሕይወታችን ውስጥ ወደምናሳይበት መንፈሳዊ ደረጃ ያሳድገናል።

በልምድ ሳይሆን በማስተዋል ሆነው ልባቸው በፍቅረ እግዚአብሔር ተነክቶ በመቅደሱ የሚያገለግሉ ልዑካን (ካህናትና ዲያቆናት)፥ እንዲሁም የጸሎተ ቅዳሴውን ተሰጥዎ በመመለስና ቅዱስ ቊርባንን በመቀበል የቅዳሴው አካልና ዋነኛ ተሳታፊዎች የሆኑ ምእመናን፥ ከላይ የተዘረዘሩት መንፈሳዊ መገለጫዎች የሚታዩባቸውና የቅዳሴው አገልግሎት በእውነት መንፈሳውያን ያደረጋቸው ሰዎች ናቸው።

## የቅዳሴው አገልግሎት ለምን አልለወጠኝም?

ይህን መጽሐፍ የሚያነብ (የምታነብ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኝ በርእሱ ላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ መጠየቁ (መጠየቋ) አይቀርም። "ቅዳሴ ከላይ የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ ሀብታት እያጎናጸፈ በተሳታፊዎቹ ላይ የሕይወት ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ፥ እኔን ለምን አልለወጠኝም?" የሚለው ጥያቄ መፈጠሩ መልካም ነው። ነገር ግን "ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው (የምትጠይቀው) የቤተ ክርስቲያናችን አባል ለመጨረሻ ጊዜ የቆረበው መቼ ነው?" የሚለውም ጥያቄ አብሮ መመለስ አለበት። በጣም በሚያሳዝን መልኩ አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ለቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ሳይቆርቡ ወደ ቤታቸው እንደሚመለሱ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ለአንዳንዶቹ ምእመናን፥ ቅዱስ ቊርባንን መቀበል የልጅነት ጊዜ ትውስታ ሆኖ ቀርቷል። ስለዚህ ከሚለውጠንና የቅድስናን ሕይወት ከሚያጎናጽፈን ቅዱስ ቊርባን ርቀን እየኖርን፥ "ቅዳሴው ለምን አልለወ ጠኝም?" ማለት አንችልም። እውነተኛ የሆነ የመንፈሳዊ ሕይወት ለውጥ ከፈለግን፥ ወደአቋረጥነው የቅዱስ ቊርባን ሕይወት በንስሐ መመለስ አለብን።

ብዙ ጊዜ ምእመናን ቅዱስ ቊርባንን ላለመቀበላቸው እንደ ዋነኛ ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት፥ ሠራዒው ካህን ወደ ፍሬ ቅዳሴ ከመግባቱ በፊት "እጁን እየታጠበ የሚያውጀው አዋጅ ስለሚያስፈራን ነው" የሚል ነው። ካህኑ፦ "ንጹሕ የሆነ ከቊርባን ይቀበል፣ ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል፤ ለሰይጣንና ለመላእክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል፤ በልቡናው ቂምን የያዘ፣ ልዩ አሳብና

ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ…"[146] የሚለው ለማስፈራራት ሳይሆን፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት" (1ቆሮ. 11፥27) ባለው መሠረት ራሳችንን መርምረንና ኃጢአታችንን ለንስሐ አባታችን ተናዝዘን መቅረብ እንዳለብን ለማስገንዘብ ነው። ይህን ሳያደርግ፥ በልቡ የኑፋቄ አሳብ (በጌታ ሥጋና ደም ያለማመን ወይም ሌላ የትምህርተ ሃይማኖት ክህደት) ይዞ፥ የበደለውን ወንድሙን ይቅር ሳይል በቂምና በበቀል መንፈስ ሆኖ (ማቴ. 18፥21-35) ወይም፥ ያያትን ሴት ሁሉ በዝሙት መንፈስ እየተመኘ ከእርሷ ጋር በልቡ የሚያመነዝር ሰው (ማቴ. 5፥28) በንስሐ የልብ ለውጥ ሳያገኝ ቢቆርብ፥ እንደሚገባው ሆኖ ስላልቀረበ ዕዳና መፈራረጃ ይሆንበታል ማለት ነው። መጽሐፈ ቅዳሴውም ሠራዒው ካህን ይህን አዋጅ ካወጀ በኋላ ምን ማለቱ እንደሆነ ለምእመናን ግልጽ ለማድረግ፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ "በዳዊት መዝሙርና በጳውሎስ [መልእክታት]፥ በሐዋርያት [መልእክታት] እና በግብረ ሐዋርያት በወንጌልም ሕዝቡን [ይምከር]"[147] የሚል ትእዛዝ አስቀምጧል።

በተደጋጋሚ ከምእመናን የምንሰማው፦ "ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል ብቁ አይደለሁም" የሚለው የትሕትና አነጋገር ጥሩ ቢሆንም፥ ይህን ቅዱስ ምሥጢር ለመቀበል ማንም በራሱ ንጹሕ ሊሆን እንደማይችል ልናውቅ ይገባል። በትሕትና ሁነን፥ የኃጢአት በሽታ ነፍሳችንን እንዳደከማት አምነን ወደሚፈውሰን መድኃኒት እንቀርባለን እንጂ፥ የጌታችንን ሥጋና ደም ለመቀበል ማንም ብቁ አይደለም። ከላይ የተጠቀሰውን አዋጅ የሚያውጀው ሠራዒው ካህን፥ ለሥርዓተ ቅዳሴው ራሱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የዚህ ቅዱስ ምሥጢር አገልጋይ ለመሆን ብቁ አለመሆኑን በመግለጽ የሚከተለውን ጸሎት ይጸልያል፦

> የሁሉን ልቡና እያንዳንዱን የሚያውቅ፣ በቅዱሳንም የሚያድር ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ ብቻውን ኃጢአት የሌለበት [ሁሉን ቻይ] እና ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ነው። አቤቱ እኔ ላንተ አገልግሎት ንጹሕ እንዳይደለሁ፣ ወደ አንተ የምቀርብበትና

[146] "ሥርዓተ ቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.46፣ ገጽ 96-97።
[147] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 51፣ ገጽ 98።

*በቅዱስ ጌትነትህም ፊት አንደበቴን [የምከፍትበት] ገጽ [ሞገስ] እንደሌለኝ አንተ ታውቃለህ፤ ነገር ግን በቸርነትህ ብዛት ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ፥ ኃጥእ ነኝና።*[148]

ስለዚህ ሁላችንም ወደ ሥጋውና ደሙ ስንቀርብ ለዚህ ታላቅ ምሥጢር ብቃት የሌለን እንደ ሆንን አምነንና እጅግ ብዙ የሆነውን የአምላካችንን ምሕረት ተስፋ አድርገን ነው። ለቅዱስ ቍርባን የተዘጋጁ ካህናትና ምእመናን ከመቀበላቸው በፊት እንዲጸልዩት የታዘዘው ጸሎት እንደሚያስተምረንም፥ ብላቴናው እንዲፈወስለት ወደ ጌታ በትሕትና የቀረበውን መቶ አለቃ አብነት አድርገን (ማቴ. 8፥8)፡-"አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ርኵስት ከሆነች ከቤቴ [ከሰውነቴ] ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለም"[149] እያልን፥ በደለኛነታችንን በመናዘዝ እንቀርባለን። ጌታችን ስለእኛ የተቀበለውን መከራ መስቀሉን ተስፋ አድርገንም፥ "ነገር ግን [እኔን] ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለመሆንህ፣ ስለክቡር መስቀልህም፣ ማሕየዊት ስለምትሆን ስለ ሞትህ፣ በሦስተኛው ቀን ስለ መነሣትህም፥ ጌታዬ ሆይ ከበደልና ከመርገም ሁሉ፥ ከኃጢአትና ከርኵሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፣ እማልድሃለሁም"[150] ብለን እየጸለይን፥ የምንቀበለው የቅድስናው ምሥጢር ለወቀሳና ለፍርድ እንዳይሆንብን እንማፀነዋለን።

"ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነው" (ያዕ. 5፥11) ተብሎ የተነገረለት አምላካችን የሁላችንንም መዳን የሚወድ፥ በምሕረቱ ባለጸጋ የሆነ አምላክ ነው። ንስሐ እስከገባን ድረስ መሐሪው አምላካችን ይቅር የማይለው ኃጢአት የለም (ት. ሕዝ. 18፥21):: ስለዚህ በኃጢአታችን ተስፋ ቆርጠን ከቅዱስ ቍርባን ከመራቅ ይልቅ ምድርን ሁሉ በመላው የአምላካችን ምሕረት ተጽናንተን ወደ እርሱ ልንቀርብ ይገባል። "መተላለፍህን፥ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም አላስብም" (ት. ኢሳ. 43፥25) በማለት የምሕረቱን ብዛት የገለጸልን ይቅር ባይ አምላክ ስላለን፥ የቀድሞው ያለማወቅና የስንፍና በደላችን እንደ ተተወልን አምነን የሕይወት መድኃኒትን መቀበል ይኖርብናል። ለዚህም ነው ካህናቱ ድርገት ሲወርዱ፥ በአንደበት ሊነገርና ሊመረመር የማይችል ሦስትነትና አንድነት ያለው የቅዱስ አምላካችንን ምሕረትና አባትነት አምነን እንዲህ እያልን በዝማሬ የምንጠራው፡-

[148] "ጸሎት እምድኅረ አስተናብሮ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 53-54፣ ገጽ 27-28።
[149] "ጸሎት እምቅድመ ተመጥዎ ቍርባን" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 110፣ ገጽ 123።
[150] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 111፣ ገጽ 124።

> የማይነገር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሦስት የምትሆን፣ ይህን ሥጋና ደም ሕይወት ሊሆነኝ ሳይፈረድብኝ እቀበል ዘንድ ስጠኝ፤ በጌትነትህ እገለጽና ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ እሠራ ዘንድ ስጠኝ፣ የአንተንም ፈቃድ እየሠራሁ እኖርልህ ዘንድ ስጠኝ፣ በማመን አባት ብዬ እጠራሃለሁ፣ መንግሥትህንም እጠራለሁ፣ አቤቱ ስምህ በእኛ ላይ ይመስገን፥ ምስጉንና ክቡር የምትሆን ኃያል አንተ ነህና፥ ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘለዓለሙ።[151]

ኃጢአቱ እንደተተወለት የሚያምንና ኃጢአትን በመጥላት ወደ አምላኩ የተመለሰ የቤተ ክርስቲያናችን አባል ከላይ የተጠቀሱትን ውብና ድንቅ የንስሐ ጸሎቶች እየጸለየ ወደ ጌታችን ሥጋና ደም ይቀርባል። ብዙ ሰዎች ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል የዓመታት ቀጠሮ የሚይዙበት ምክንያት፥ የሰይጣንን ተስፋ አስቆራጭ ድምጽ በመስማትና እግዚአብሔር ይቅር እንደማይላቸው በማሰብ ገደብ የሌለውን የእግዚአብሔር ምሕረት ስለሚጠራጠሩ፥ ወይም ኃጢአትን ጠልተው ከአስከፊው የኃጢአት ባርነት ነጻ ለመሆን ራሳቸውን ስላላዘጋጁ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፥ ስለ ቅዱስ ቊርባን ያለው ግንዛቤ የተሳሳተ ካልሆነ በስተቀር፥ የኃጢአትን ይቅርታ ከሚቀበልበት የጌታ ሥጋና ደም ለመራቅ በቂ ምክንያት ያለው አንድም የቤተ ክርስቲያናችን አባል የለም።

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር፥ የቅዳሴው አገልግሎት ዋነኛ ዓላማ፥ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ወደሚያሰጠንና ለዘላለማዊ ሕይወት ወደሚያበቃን ወደ ጌታ ሥጋና ደም አማንያንን በሙሉ መጥራት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ለሆነ ሰው ሁሉ፥ ቅዱስ ቊርባንን መቀበል በፍጹም ጥያቄ ሊሆን አይገባም። ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ዘወትር የምትቀድሰው ምእመናን ቆመው፥ ካህናቱ ሲቀድሱ አይተውና መጨረሻ ላይ የቅዳሴ ጸበል ጠጥተው ብቻ እንዲሄዱ ሳይሆን፥ በየዕለቱ የሚሠዋው መሥዋዕት (የጌታ ሥጋና ደም) ተሳታፊ እንዲሆኑ ነው። በቅዳሴው ሰዓት ምእመናን፥ ስገዱ ሲባል በመስገድ፥ የሚነበቡ ምንባባትን በመስማት፥ መልስ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ደግሞ በንባብ ወይም በዜማ መልስ በመስጠት (ተሰጥዎውን በመቀበል) አብረው አመስጋኞች (የስሙ ቀዳሾች) እንደሆኑ ሁሉ፥ ካህናቱና ዲያቆናቱ መቅደስ ውስጥ ቆርበው ምእመናንን ለማቊረብ ሲወጡ ደግሞ የተሠዋውን መሥዋዕት በመቀበል የቅዳሴው ሙሉ ተሳታፊዎች ሊሆኑ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን፥ የቅዳሴው ዋነኛ ዓላማ አልገባንም፥ እንዲሁም ምእመናኑ የቅዳሴው ተጠቃሚ አልሆኑም ማለት ነው።

---

151 "እምድኅረ ተመጥዎ ቊርባን" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቊ. 117፣ ገጽ 126።

በአሁኑ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ የምናየው አሳዛኝ ሁኔታ (ቅዳሴ ላይ ተገኝቶ ሳይቆርቡ መመለስ) ከመፈጠሩ በፊት ጥንታውያን አባቶቻችን ምእመናን የቅዳሴው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቃለ-ምዕዳን አስተላልፈው ነበር። በምዕዳን (ምክር) መልኩ የተጻፈው፥ ከቅዳሴ በፊት ሊነበብና ምእመናን ሊሰሙት የሚገባው የመጽሐፈ ቅዳሴ ንባብ ሲጀምር፡-"ወንድሜ ሆይ ኃጢአትህን እያሰብህ በዚህ ልቡና ኑር፤ [ካህናቱ ስለአንተና ስለራሳቸው] ንጹሕ የሚሆን መሥዋዕቱን በሚያቀርቡበትና በሚያሳርጉበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ሳትወጣ ይቅርታን ታገኝ ዘንድ ሥርየትን ለምን" ይላል። [152] እንዲሁም በቅዳሴ ሰዓት በማስተዋል የካህኑን ቃል ማዳመጥ እንደሚገባ እንጂ፥ በተበታተነ አሳብ የቅዳሴው ተሳታፊ መሆን ወይም ቅዳሴውን አቋርጦ መውጣት "[በሰማያዊው ሙሽራ] በክርስቶስ ማኅተም ከታተመ" [153] ክርስቲያን ፈጽሞ እንደማይጠበቅ በአጽንኦት ይናገራል። በዚህ ትምህርታዊ ምዕዳን፥ የቅዳሴው መሥዋዕት እንደሚከተለው ውብ በሆነ መልኩ ተገልጿል፡-

> በሠርጉ ጊዜ ሥጋውን የሚሠዋና ፈጽሞ ምግብ የሚሆን [ሥጋውን ለምግብነት የሚያቀርብ] ሙሽራን ያየ ማን ነው? ወልደ እግዚአብሔር [ኢየሱስ ክርስቶስ] ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ከእርሱ በቀር እንደ እርሱ ያደረገው የሌለ እንግዳ ሥርዓትን በዚህ ዓለም ሠራ። በሠርጉ ጊዜ በሐዋርያት ፊት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ማዕድ አድርጎ ሠራ፤ ከእርሱ ይበሉ ዘንድ፥ ያመነበትም ለዘለዓለም ይድን ዘንድ። በሠርጉ ጊዜ ሙብል መጠጥ የሆነውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቅዱስ ሥጋውን፣ ክቡር ደሙን የሰጠን አምላካችን ቡሩክ ነው ። የኃጢአት ማስተሥረያ ሊሆንና ለዘለዓለም እንድንበት ዘንድ፥ ለእርሱ ምስጋና ይግባው ለዘለዓለሙ አሜን።[154]

ይህ ምዕዳነ አበው በዋነኝነት የሚያስተምረን፥ በተከፈለ ልብ ሁነን የቅዳሴው ተሳታፊ እንዳንሆን ወይም በቸልተኝነት ቅዳሴውን አቋርጠን እንዳንወጣ ቢሆንም፥ ቅዳሴው እስኪያልቅ ድረስ የቆዩ፥ ነገር ግን ቅዱስ ቍርባን ያልተቀበሉ አባላትም አቋርጠው እንደሚወጡት ሰዎች የቅዳሴው ተጠቃሚ አለመሆናቸው ነው። በቅዳሴ ተገኝቶ አለመቍረብ፥ ከላይ የተጠቀሰው የአባቶቻችን ትምህርት እንደ ሚያስተምረን፥ ሠርግ ላይ ተገኝቶ ሳይበሉ እንደ መመለስ ይቈጠራል። ቅዳሴ የሚቀደስበት ዋነኛ ዓላማ መንፈሳዊ ምግባችን የሆነውንና በዘላለማዊነት ሕያው

---

[152] "ሥርዓተ ቅዳሴ ዘይደሉ ለቀሲስ ወለዲያቆን ወለኵሉ ሕዝብ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 2፣ ገጽ 5።

[153] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 3፣ ገጽ 5።

[154] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 8-10፣ ገጽ 6-7።

ሆነን እንድንኖር የሚያደርገንን ማዕድ (የክርስቶስን ሥጋና ደም) እንድንቀበል ነውና።

ለቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂደን የአገልግሎቱ ተሳታፊ በሆንን ቍጥር ሲዜሙና ሲነበቡ የምንሰማቸው መልእክቶች በሙሉ እኛን ወደ ቅዳሴው መሥዋዕት በመጋበዝ የቅዳሴው ተጠቃሚ እንድንሆን ያደርጉናል። ቅዳሴው ልክ እንደ ተጀመረ ምእመናን ከካህናቱ ጋር የሚያዜሙት፥ “ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ እምእመናን…” ብሎ የሚጀምረው ትእዛዝ በአማርኛ ትርጒሙ እንዲህ ይላል፡-

> በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ፣ **ከቍርባንም ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይለይ**፥ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፤ የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃልሏልና፥ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን።[155]

የግእዙ ንባብ ሲጨርስ፡ “ከመዝ መሀሩነ ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ”[156] ይላል፥ ምክንያቱም ይህ ትእዛዝ የተወሰደው “አብጥሊስ ሲኖዶስ” ተብሎ ከሚታወቀውና አባቶቻችን ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ ዘሮሜ ነግረውት እርሱ ጽፎታል ተብሎ ከሚታመነው “መጽሐፈ ሲኖዶስ” (የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ) አንዱ ክፍል ስለሆነ ነው።[157] ይህ ትእዛዝ በግልጽ የሚያመለክተው ቅዱስ ቍርባን የማይቀበሉ ሰዎች የቅዳሴው ተሳታፊ መሆን እንደማይችሉ ነው። የተጠመቁ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ለቅዳሴ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ፥ የቅዳሴው መሥዋዕት የሚሠዋው እነርሱ እንዲቀበሉት ስለሆነ ለመቀበል ተዘጋጅተው መሄድ አለባቸው። ያልጠመቁ ሰዎች (ንኡሰ ክርስቲያን) የምሥጢሩ ተካፋይ መሆን አይችሉም፤ ስለዚህ የአማንያን ቅዳሴ (ፍሬ ቅዳሴ) በመባል የሚታወቀው የቅዳሴው ሦስተኛ ክፍል ሊጀመር ሲል ዲያቆኑ ያልተጠመቁትን፡-“ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን - የክርስቲያን ታናሾች

---

[155] “ሥርዓተ ቅዳሴ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.3፣ ገጽ 35።

[156] ዝኒ ከማሁ።

[157] በመጽሐፈ ቅዳሴ የተጠቀሰው ይህ ትእዛዝ፥ በአብጥሊስ ሲኖዶስ 9ኛው አንቀጽ ላይ ይገኛል። “CANONI APOSTOLICI ‘I RECENSIONE DEGLI ABṬELISÂT” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ፡- *Il Senodos Etiopico: Canoni pseudoapostolici: Canoni dopo l’Ascens ione, Canoni di Simone Cananeo, Canoni Apostolici, Lettera di Pietro,* CSCO, Vol. 552, Scriptores Aethiopici, Tom. 101, ed. Alessandro Bausi (Louvain: Aedibus Peeters, 1995) p. 186.

ውጡ"[158] በማለት ያሰናብታቸዋል። የተቀሩት የቤተ ክርስቲያን አባላት ግን እስከ ቅዳሴው ፍጻሜ ድረስ ሊቆዩና የቅዱስ ቊርባን ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል። እንዲያውም በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ያልተጠመቁ (ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ ያሉ) ሰዎች ከቅዳሴው ሲሰናበቱ፥ በዕለቱ ለቅዱስ ቊርባን ያልተዘጋጁ አማንያንም አብረዋቸው ይወጡ ነበር።[159] ታዲያ በዘመናችን እንደምናየው እንደ ንኡሰ ክርስቲያን ከቤተ ክርስቲያን ሳይወጡ ወይም ተዘጋጅተው እንደሚመጡት አማንያን ሳይቆርቡ ቤተ ክርስቲያን ደርሶ ብቻ መመለስ ምን ይባላል? ቤተ ክርስቲያን መግቢያዋ ራሱ "ደጀ ሰላም" ተብሎ የሚጠራ የሰላምና የምሕረት ቤት ስለሆነች፥ የማይቆርቡ አባላቶቿን ከቅዳሴ አታስወጣም፤ በንስሐ ውስጥ ያሉትንም ንስሐቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ትጠብቃቸዋለች። ነገር ግን ተጠምቀውና የቤተ ክርስቲያን አባላት ሆነው ቅዱስ ቊርባን መቀበል ያቆሙ ሰዎች፥ የአንዱ የክርስቶስ አካል አባላት መሆናችን የሚረጋገጠው የጌታን ሥጋውንና ደሙን በመቀበላችን ስለ ሆነ፥ የአማንያን ጉባዔ ተብላ ከምትታወቀው ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን እንደ ለዩ ሊገነዘቡ ይገባል። የወይን ግንድ ከሆነው ከክርስቶስ የተለየ ቅርንጫፍ ደግሞ ስለሚደርቅና ወደ ውጭም ስለሚጣል (ዮሐ. 15፥1-7) ከቅዱስ ቊርባን ተለይተን በራሳችን ሕይወት ሊኖረን በፍጹም አይችልም።

## *መደምደሚያ*

በዚህ ምዕራፍ የቅዳሴን ዋና ዋና መገለጫ ባሕርያትንና የሚያስገኝልንን መንፈሳውያን ዕሴቶች ተመልክተናል። ቅዳሴ ከቤተ ክርስቲያናችን ምሥጢራት ሁሉ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው ቅዱስ ምሥጢር (ቅዱስ ቊርባን) የሚከብርበት ታላቅ ሥርዓተ አምልኮ መሆኑንም ተረድተናል። ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር በቅዳሴ የምትሠዋው መሥዋዕት፥ ሊደጋገም የማይችለውና አንድ ጊዜ በቀራንዮ የተሠዋው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። በካህናቱ አድሮ መሥዋዕቱን የሚያቀርበውም የአዲስ ኪዳኑ ብቸኛ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያን ሙሽራዋና ራሷ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መጥቶ ወደ መንግሥቱ እስኪጠቀልላት ድረስ፥ ዘላለማዊ ፍቅሩን የገለጠበትን

---

[158] "ሥርዓተ ቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ምዕራፍ 4፡ ቊ. 1፣ ገጽ 87።

[159] Fr. Lawrence Farley, *Let Us Attend: A Journey through the Orthodox Divine Liturgy* (Chesteron, Indiana: Conciliar Press, 2007) p. 48.

መሥዋዕት እየሠዋች ትጠብቀዋለች። በሰማያዊው ሠርግ ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያን ለሙሽራው ስትሰጥም[160] "የበጉ ሠርግ ዕራት" (ራእ. 19፥9) የሚሆነው፥ "ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ማዕድ አድርጎ"[161] የሠራውና ስለ ኃጢአታችን የተሠዋው የእግዚአብሔር በግ ስለሆነ የመንግሥቱን ዘላለማዊ ሕይወት በዚህ ምድር አስቀድማ ስትለማማደው ትኖራለች። ስለዚህ ከሰማያዊው ማዕድ ዘወትር የሚመገቡ ልጆችዋ ብፁዓን ናቸው።

የቅዳሴው መሥዋዕት የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት ሠራዊቱ ቅዱሳን መላእክት አብረው አሉ፥ "የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮች የሚሆኑ የመላእክት ሠራዊት በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ"[162] እያልን በቅዳሴ እንደምናዜመው። ስለዚህ ቅዳሴ የሰው ልጆች ከቅዱሳን መላእክት ጋር በኅብረት የሚያቀርቡት ዝማሬ፥ እንዲሁም ምድራዊቷና ሰማያዊቷ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሆነው በፍጥረታት ሁሉ የሚመሰገነውን ልዑል እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት ታላቅ አምልኮ ነው። ምሉዕ በኵለሄ (በሁሉ ቦታ መልቶ የሚገኘው) እና አልፋና ዖሜጋ (ራእ. 22፥13) የሆነው ጌታና አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በቅዱስ ቍርባን ህልው ሆኖ የሚገኝበት የቅዳሴው ቦታና ሰዓት እኛ ከምንረዳው ቁስ-አካላዊ ቦታና የጊዜ ቀመር የተለየ ስለ ሆነ፥ ቅዳሴ በምድር ላይ ያለ ሰማያዊ አገልግሎት በመባል ይታወቃል። የቅዳሴው አገልግሎት የለወጣቸውና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ያስጌጠላቸው የእግዚአብሔር ልጆች፥ በዓይነ ሕሊና የሚታየውን የቅዳሴውን ውበት ማየት ይችላሉ። በሚቀጥለው ምዕራፍ በአዲስ ኪዳን ምሥጢረ ቍርባን እንዴት እንደተመሠረተ፥ የመጀመሪያዎቹ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ይዘት ምን ይመስል እንደ ነበርና ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ከመድረሳቸው በፊት በየዘመናቱ ያሳዩትን እድገት በአጭሩ እንመለከታለን።

---

160 "ሰ" ጠብቆ ይነበብ፡፡

161 "ሥርዓተ ቅዳሴ ዘይደሉ ለቀሲስ ወለዲያቆን ወለኵሉ ሕዝብ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ.9፣ ገጽ 6-7።

162 "ሠራዊት ዘቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 63፣ ገጽ 113።

# ምዕራፍ ሁለት

## የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቲያናዊ አምልኮ ይውሉ የነበሩ ጽሑፎች[1] በየዘመናቱ ተገኝተዋል፤ ጥናትም ተደርጎባቸዋል። እነዚህ ታሪካዊ ምንጮች፡- በጽርእ (ግሪክ)፥ በሱርስት፥ በቅብጥ (ኮፕቲክ)፥ በግእዝ እና በዐረብኛ ቋንቋዎች ተጽፈው የተገኙ ሲሆን፥ ከአንዱ ጥንታዊ ቋንቋ ወደ ሌላው የተተረጐሙ ናቸው። ሆኖም ግን አንዱን መጽሐፈ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን[2] ለምሳሌ ወስደን በእነዚህ ቋንቋዎች የሚገኙትን የተለያዩ ቅጂዎች እያነጻጸርን ብንመለከት፥ በይዘታቸው መጠነኛ ልዩነት ያሳያሉ፤ አንዱ ላይ የሚገኘው ጸሎት ወይም ትእዛዝ ሌላው ላይ አይገኝም። ምንም እንኳ ጥንታውያን ምንጮቹ በየትኛው ዓመት ወይም ክፍለ ዘመን እና በማን እንደተጻፉ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም፥ የተለያዩ ሊቃውንት ባደረጓቸው ጥናቶች መሠረት ጽሑፎቹ የተደረሱባቸውን ጊዜያት ለመገመት ተችሏል።

ደራሲዎቻቸው በእርግጠኝነት የሚታወቁ የተወሰኑ የምሥጢራተ ጥምቀትና ቊርባን መፈጸሚያ መጻሕፍት አሉ። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ ደራሲዎቻቸው የራሳቸውን ስም ሳይገልጹ ታዋቂ በሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም የሰየሟቸውን ደግሞ፥[3] ድርሰቶቹ በስማቸው ቢሰየሙም አማናውያን ደራስያኑ እነርሱ አለመሆናቸውን ምሁራኑ በጥናታቸው አረጋግጠዋል። ነገር ግን፥ ሁሉም ጽሑፎች የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ስለሚያንጸባርቁ ያላቸው ታሪካዊ አስተዋጽዖ የጎላና የተረዳ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጥንታውያንና ታሪካዊ ጽሑፎች ግምጃ ቤት ስለሆነችና የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ እስካሁን ድረስ ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ ስለምትጠቀምባቸው፥ የቤተ ክርስቲያናችንን ቅዳሴ ታሪካዊ እድገት በዝርዝር ከማጥናታችን በፊት በዚህ ምዕራፍ

---

[1] Liturgical texts (writings).

[2] Church order.

[3] እንደዚህ አይነት ጽሑፎች "pseudo-writings" ይባላሉ፡፡

የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮና ጸሎታተ ቍርባን[4] በመጠኑ እንመለ-ከታለን።

## 2.1. የምሥጢረ ቍርባን አመሠራረት

የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሙሉ ለሙሉ ለመረዳትና በመጻሕፍቱ ፍጻሜ ያገኙትን ትንቢታት ከምንጮቻቸው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማንበብ (ማገናዘብ) እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቍርባንን ለማጥናት መሠረት ከሆነው የአይሁድ አምልኮ መጀመር ያስፈልጋል። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ላይ ጥናት ያደረጉ የተለያዩ ሊቃውንት ይህንኑ እውነታ አረጋግጠዋል።[5] እንዲያውም የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን[6] ሥርዓተ አምልኮ ላይ የጻፉ ምሁራን፥ በዚህ ስም የሚታወቀው ሥርዓተ ቅዳሴ የአይሁድ ቤተ መቅደስና ምኵራብ አምልኮን መሠረት አድርጎ የቀጠለና አይሁዳዊውን ሥርዓት በግልጽ የሚያንጸባርቅ እንደሆነ አመልክተዋል።[7] ነገር ግን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደምንመለከተው፥ የአይሁድን የአምልኮ ሥርዓት ልዩ የሆነ የአዲስ ኪዳን ትርጉም

---

[4] Eucharistic prayers ወይም anaphoras.

[5]ለምሳሌ እነዚህን ጥናቶች ይመልከቱ፦ R.C.D. Jasper and G. J. Cuming, *Prayers of the Eucharist: Early and Reformed Texts translated and edited with Commentary,* 3rd ed. (Collegeville, Minnesota, 1990) pp. 7-12; Alistair Stewart-Sykes and Judith H. Newman, *Early Jewish Liturgy: A Sourcebook for use by Students of Early Christian Liturgy,* Alcuin/GROW Joint Liturgical Studies, Vol. 51 (Cambridge: Grove Books Limited, 2001); ሀብተሚካኤል ኪዳነ (ዶ/ር)፡ *ታሪኻዊ ኣመጻጽኣን ምዕባለን ናይ "ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ"* (ኣሥመራ፡ ፍራንሲስካና ማተሚያ ቤት፡ 1997/98 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 2005) ገጽ. 55-56.

[6] Eastern Orthodox Church የሚለው ስያሜ በ451 ዓ.እ. የተካሄደውን የኬልቄዶንን ጉባኤ የእምነት መግለጫ የተቀበሉ፦ የግሪክ፥ ራሽያ፥ ሮማንያ፥ ሰርቢያ፥ ቡልጋሪያ፥ ፖላንድ፥ ጆርጂያ፥ ዩክሬን፥ ቆጵሮስ (Cyprus) እና ፊንላንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን የጋራ መጠሪያ ነው። ሁሉም አንድ ዓይነት ትምህርተ ሃይማኖት ስላላቸውና Byzantine Liturgy የተሰኘውን ሥርዓተ ቅዳሴ ስለሚከተሉ በአንድ ስም ተጠርተዋል። ራስ-ገዝ (autonomous/ autocephalous) የሆነ አስተዳደር ስላላቸው እያንዳንዲቷ ቤተ ክርስቲያን የራስዋ የሆነ ፓትርያርክ ቢኖራትም "Ecumenical Patriarch" በመባል የሚታወቀው ርእሰ አበው መንበሩ ቱርክ ግዛት ውስጥ በምትገኘው የጥንቷ ቍስጥንጥንያ (Constantinople) ወይም በዘመናዊ አጠራር Istanbul ውስጥ ነው።

[7] ለምሳሌ ይህን መጽሐፍ ይመልከቱ፦ Benjamin Williams and Harold Anstall, *Orthodox Worship: A Living Continuity with the Synagogue, the Temple and the Early Church* (Minneapolis, MN: Light and Life Publishing Company, 1990).

በመስጠት ምሳሌያዊ ድርጊቶችን ከምሥጢር ጋር በማዛመድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የምትስተካከል ቤተ ክርስቲያን በዓለም ስለሌለች፥ ከላይ የተገለጸው የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን አባባል ከምንም በላይ እውን የሚሆነው ለእናት ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ ነው ቢባል ማጋነን አይሆነም። መንበሩ ላይ የምታስቀምጠውን ጽላት የአዲስ ኪዳን አማናዊ *መሥዋዕት* (ቅዱስ ቍርባን) *መሠዊያ* (ምሥዋዕ) ያደረገች፥ እንዲሁም የጌታንና የቅዱሳኑን በዓላት በዑደተ ታቦት የምታከብር በዓለም ብቸኛ ቤተ ክርስቲያን ናት። በአብዛኛው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ፥ አልፎ አልፎም በከተሞች የምናያቸው ከመቅደሱ ጀምሮ ሦስት ክበብ ያላቸው አብያተ ክርስቲያን የንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን የሥነ ሕንጻ ጥበብ የተከተሉ ናቸው።[8] ስለዚህ የአይሁድንም ሆነ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮ ጽሑፎችን በዚህ ምዕራፍ ስናጠና፥ እነዚህ ጥንታውያን ምንጮች በቤተ ክርስቲያናችን የተሰጣቸውንም ቦታ ለማሳየት እሞክራለሁ።

## የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ

የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ ሦስት ክፍሎች አሉት፡- በቤተ መቅደስ ይቀርብ የነበረው *መሥዋዕት*፥ የምኵራብ አገልግሎት እና የቤተሰብ ጸሎት ናቸው።[9] አይሁድ ለሰባት ቀናት ቂጣ እየበሉ በሚያከብሩት የፋሲካው በዓል የሚሰዉት ጠቦት (ዘጸ. 12፥1-20) የዓለምን ኃጢአት በደሙ ፈሳሽነት ያስወገደው የእግዚአብሔር በግ (የኢየሱስ ክርስቶስ) ምሳሌ ነው (ዮሐ. 1፥36፤ 1 ቆሮ. 5፥7)።[10] *ቢርካት ሃማዞን*[11] ተብሎ በሚታወቀው የአይሁድ ፋሲካ ጸሎተ ቡራኬ፥ ኤሎሂም ብለው ለሚጠሩት አምላክ በዋነኝነት ዓለሙን ስለመፍጠሩ እና ለወገኖቹ ለእስራኤል ምግብን ስለመስጠቱ ምስጋና ያቀርባሉ፤ እንዲሁም በኦሪት ዘዳግም 8፥10 ላይ “ትበላማለህ፥ ትጠግማለህ፥ ስለ ሰጠህም ስለ መልካሚቱ ምድር አምላክህን እግዚአብሔርን

---

[8] ለተጨማሪ ማብራሪያ እነዚህን ጽሑፎች ይመልከቱ፡- Edward Ullendorff, “Hebraic-Jewish Elements in Abyssinian (Monophysite) [*sic*] Christianity” *JSS* 1 (1957) pp. 216-256; Marilyn Heldman, “Architectural Symbolism, Sacred Geography and the Ethiopian Church” *Journal of Religion in Africa,* 22/3 (1992) pp. 222-241.

[9] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 7.

[10] St. John Chrysostom, *On the Betrayal of Judas,* 1.4, PG 49.378-9, quoted in Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy,* p. 4.

[11] *Birkat ha-mazon*.

ትባርካለህ" ተብሎ የተጠቀሰውን ቡራኬ ይዘምራሉ።[12] *ቢርካት ሃማዞን* ከማእድ በኋላ የሚቀርብ ምስጋና[13] ሲሆን፥ የምስጋናው ሦስተኛ ክፍል ኢየሩሳሌም ወደ ቀደመ ክብሯ ትመለስ ዘንድ ጸሎትንና ልመናን ያቀርባል።[14] በ*ቢርካት ሃማዞን* ውስጥ የተካተቱት፡- ውብ አድርጎ ስለፈጠረው ፍጥረት እና ለወገኖቹ ስላደረገው የማዳን ሥራ እግዚአብሔርን ማመስገን በእያንዳንዱ ጥንታዊ አኰቴተ ቍርባን ውስጥ የሚገኙ ዋነኛ ክፍሎች ናቸው። በአይሁድ የማስተስርያ ቀን[15] የሚጸለየው *ኣታህ ኮናንታ*[16] በመባል የሚታወቀው ጸሎት፥ ሥነ ፍጥረትንና የሰው ልጅ ውድቀትን የሚዘግቡ ክፍሎች ስላሉት ይህ ጸሎት ለምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ቅዳሴያት እንደ ምሳሌ የተወሰደ መሆኑን ምሁራኑ ይስማማሉ።[17] ከአይሁድ የጸሎት መጻሕፍት ለየት ባለ መልኩ ደግሞ፥ የቀደምት ክርስቲያኖች የቅዱስ ቍርባን ማክበሪያ ጸሎታት፥ በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ላደረገው የማዳን ሥራ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ያቀርባሉ።

በዚህ የአይሁድ ጸሎተ ቡራኬ *(ቢርካት ሃማዞን*) ውስጥ የምናገኘው ሌላው የሥርዓተ አምልኮ መሠረታዊ ጽንሰ አሳብ "ተዝካር"[18] የተሰኘው ነው። ኤሎሂም መሢሑንና ቤተ እስራኤልን እንዲያስብ "ተዘከር እግዚኦ (አቤቱ አስብ) . . ." ብለው የሚጀምሩ ጸሎታት ይቀርብለታል። አንዳንድ ምሁራን በምሴተ ኀሙስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ ፋሲካ የቀረበውን ኅብስትና ጽዋ አንሥቶ ከባረከ በኋላ "ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" (ሉቃ. 22፥19) ማለቱ በ*ቢርካት ሃማዞን* ለመሢሑ የሚደረገውን መታሰቢያ (ተዝካር) ያመለክታል ይላሉ።[19] በግሪኩ

[12] Enrico Mazza, *The Origins of the Eucharistic Prayer* (Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1995) p. 9.
[13] በእንግሊዝኛ "grace after meals" ይባላል፡፡ Paul F. Bradshaw, "Introduction: The Evolution of Early Anaphoras," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Paul F. Bradshaw (Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1997) p. 4.
[14] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 8.
[15] Day of Atonement.
[16] *Attah Konanta.*
[17] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 9.
[18] Remembrance.
[19] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 9.

*አናምኔሲስ*[20] የተሰኘው ጸሎት የማንኛውም ክርስቲያናዊ የቊርባን ማክበሪያ ጸሎት (አኰቴተ ቊርባን) ዋነኛ ክፍል ስለሆነ፥ በ*ቢርካት ሃማዞን* ያለው ተዝካረ መሢሕ ያገኘውን ክርስቲያናዊ ትርጒም መረዳት እንችላለን። በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ በዝርዝር እንደተመለከትነው፥ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ የተሠዋው አንዱ አማናዊው መሥዋዕት (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) በቅዳሴ፥ መሥዋዕት ሆኖ በቀረበ ቊጥር የመሢሑ ኢየሱስን ሕማም፥ ሞትና ትንሣኤን እናውጃለን።[21]

ሌላው ለክርስቲያናዊ አኰቴተ ቊርባን መሠረት እንደሆነ የሚነገርለት *ኪዱሽ ካፓ*[22] በመባል የሚታወቀው የአይሁድ ቅዱስ ጽዋ ቡራኬ ነው። በጽዋው ላይ ቡራኬ የሚካሄደው ከምግብ በፊት ሲሆን፥ ወንጌላዊው ሉቃስ እንደዘገበልን፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን አንሥቶ ከመባረኩ በፊት በጽዋው ላይ አመስግኖ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው (ሉቃ. 22፥ 17-20) በለመዱት አይሁዳዊ የቡራኬ ሥርዓት ሳይሆን አይቀርም። ከጽዋው ቡራኬ ቀጥሎ የሚመጣው የማዕድ ጸሎት፥ የዓለማት ንጉሥ የሆነውን አምላክ ስለ መግቡቱ የሚያመሰግን ነው፤ በተጨማሪ፥ ስለኢየሩሳሌም የሚከተለውን ቡራኬ ያካትታል፦

> አምላካችን ኤሎሂም፡ በሕዝብህ በእስራኤል፥ በከተማህ በኢየሩሳሌም፥ በቤተ መቅደስህና በማደሪያ ቦታህ፥ የክብርህ ማደሪያ በሆነችው በጽዮን እና ስምህ በሚጠራበት በታላቁና ቅዱሱ ቤትህ ላይ ምሕረትህን አድርግ። በእኛ ዘመን የዳዊት ቤት መንግሥትን መልስልን፥ ኢየሩሳሌምንም በፍጥነት አንጻት።[23]

በቤተ ክርስቲያናችን "ቅዳሴ እግዚእ" በመባል የሚታወቀው የቊርባን ምስጋና በ5ኛው ምእት ዓመት እንደተዘጋጀ ከሚነገርለት መጽሐፈ ኪዳን የተወሰደ ሲሆን፥

---

[20] Ανάμνηση ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደው *Anamnesis* = remembrance/ recollection (ተዝካር/መታሰቢያ) የሚል ትርጒም አለው፤ በዚህ የአኰቴተ ቊርባን ክፍል የጌታን ሕማም፥ ሞትና ትንሣኤ እናስባለን፡፡

[21] በቅዳሴ ሐዋርያት ሕዝቡ፦ "ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ፥ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ - አቤቱ ሞትህን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም እንናገራለን፤ ዕርገትህን፥ ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን" ብለው ካዜሙ በኋላ፥ ሠራዒው ካህን፦ "ይእዜኒ እግዚኦ እንዘ ንዜክር ሞተከ ወትንሣኤከ፥ ንትአመነከ ወናቄርብ ለከ ዘንተ ኅብስተ፥ ወዘንተ ጽዋዐ እንዘ ነአኵተከ - አሁንም አቤቱ ሞትህንና ትንሣኤህን [እያሰብን]፥ እናምንሃለን፤ እያመሰገንህ ይህን ኅብስትና ጽዋ እናቀርብልሃለን" በማለት ይጸልያል። መጽሐፈ ቅዳሴ "ቅዳሴ ሐዋርያት"፡ ቊ. 47-48፤ 129።

[22] "*kiddush-cup"* - Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 9.

[23] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p.10. ("ን" ጠበቅ ብሎ ይነበብ)።

ስለ ኢየሩሳሌም፡- "ሐውጻ ለኢየሩሳሌም እምሰማያት፥ እግዚኦሙ ለሥልጣናት አርእስተ መላእክት ወኃይለ አጋዕዝት - የመላእክት አለቆች የሚሆኑ ሥልጣናት ጌታቸው፥ የአጋዕዝትም ኃይል [ሆይ፡] በሰማያት ሆነህ ኢየሩሳሌምን ጎብኛት"[24] የሚል ጸሎት አለው። ይህ ጸሎት የአይሁድ የማዕድ ቡራኬን መሠረት በማድረግ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ውስጥ ከገቡ ጸሎታት መካከል እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል።

በዕብራይስጥ ቋንቋ *ዮጼር*[25] የተሰኘው ጸሎት ለነቢያቱ ኢሳይያስና ሕዝቅኤል የተገለጹላቸውን የመላእክት ራእይና ሰማያዊ ዝማሬ ያካትታል። ጸሎቱ ሲጀምር፡- "ቅዱሳንን የፈጠርህ ዓለታችን፥ ንጉሣችንና ቤዛችን [ሆይ፡] ተመስገን። መላእክትን የፈጠርህ ንጉሣችን [ሆይ፡] ስምህ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን"[26] ይላል። የሰውን ዘሮች ጨምሮ የተፈጠሩ ፍጥረታት በሙሉ የፍጥረታት ፈጣሪን እንደሚያመሰግኑ ከጠቆመ በኋላ፥ ይህ ጸሎተ ቡራኬ የመላእክትን ሰማያዊ ዝማሬ እንዲህ ይገልጸዋል፡-

> ሁሉም [ቅዱሳን መላእክት] በራሳቸው ላይ የሰማያዊውን መንግሥት ቀንበር ይሸከማሉ፤ በየተራ ጸጥ ባለ አእምሮ፥ በብሩህ አንደበት፥ በተቀደሰ ሁኔታ ቅዱሱን ፈጣሪ በፍርሃት፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች" [ት. ኢሳ. 6፥3] እያሉ ያመሰግናሉ፥ ክብሩንም ያውጃሉ። ከሌላ በኩል ደግሞ፥ መንኰራኵሮቹና ቅዱሳንና ሕያዋን እንስሶቹ [ት. ሕዝ. 1፥4-28] ከታላቅ ነጐድጓድ ጋር፡- "ከማደሪያው ቦታ የአምላካችን ክብር የተመሰገነ ነው" እያሉ ስሙን ይባርካሉ።[27]

*ሳንክተስ*[28] (ዝማሬ ሱራፌል) ተብሎ የሚታወቀው የክርስቲያናዊ ቅዳሴ ክፍል ከዚህ የአይሁድ ጸሎተ ቡራኬ የተወሰደ ነው። ይህ ዝማሬ ሱራፌል በ4ኛው ምእት ዓመት የአኰቴተ ቍርባን ክፍል መሆን እንደጀመረ ይታመናል፤ ለዚህም ነው በዚህ ዘመን የተደረሱ ጸሎታተ ቍርባን ይህን ዝማሬ ይዘው የሚታዩት። ለምሳሌ ቅዳሴ

---

[24] መጽሐፈ ቅዳሴ "ቅዳሴ እግዚእ"፡ ቍ. 26፣ 147። እንዲሁም Robert Beylot በግእዝና ፈረንሳይኛ ያሳተመውን መጽሐፈ ኪዳን ይመልከቱ፡- *Testamentum domini éthiopien,* ed. and trans. Robert Beylot (Louvain: Peeters, 1984) p. 36.

[25] *Yōtser*.

[26] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 11-12.

[27] ዝኒ ከማሁ፡ 12።

[28] *Sanctus*.

ማርቆስ ከላይ የተጠቀሰውን ጸሎተ አይሁድ በሚያንጸባርቅ መልኩ፥ ቍጥራቸው ሊቈጠር የማይችል እልፍ አእላፋት የሆኑ ቅዱሳን መላእክትና ሊቃነ መላእክት፥ ዓይኖቻቸው ብዙ የሆኑ ኪሩቤልና ስድስት ክንፎች ያሏቸው ሱራፌል (ራእ. 4፥7-8) በልዑል እግዚአብሔር ፊት እንደሚቆሙ ገልጾ፥ "በ፪ ክነፊሆሙ ይከድኑ ገጽሙ፥ በ፪ ክነፊሆሙ ይከድኑ እገሪሆሙ፥ ወበ፪ ክነፊሆሙ ይሰሩ [ወይጸርሑ] በበይናቲሆሙ በአፍ ዘኢያረምም ወበቃለ ስብሐት ዘኢይጸራዕ" (በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፥ በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍናሉ፥ በሁለት ክንፋቸው ይበራሉ፤[29] እርስ በእርሳቸውም ዝም በማይል አፍና በማይቋረጥ የምስጋና ቃል ይጮሃሉ)[30] ይላል። የማያቋርጠው ምስጋናቸውም፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ"[31] (ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር፥ የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው) የሚል እንደሆነ ይነግረናል።

## ወንጌላት፤ መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ

ወንጌላውያኑ ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ በቂጣው በዓል መጀመሪያ ቀን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ፋሲካን አዘጋጅተውለት የፋሲካው እራት ላይ የቅዱስ ቍርባንን ሥርዓት እንደመሠረተ ጽፈውልናል (ማቴ. 26፥17-29፣ ማር. 14፥12-25፣ ሉቃ. 22፥7-23)። የአራተኛው ወንጌል ጸሐፊ፥ ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር ቅዱስ ዮሐንስ ግን ከሦስቱ ወንጌላውያን በተለየ መልኩ፥ ጌታ የመጨረሻውን እራት ከደቀ መዛሙርቱ ይበላ ዘንድ የተቀመጠው "ከፋሲካው በዓል በፊት" (አንድ ቀን ቀደም ብሎ) እንደሆነ ይነግረናል (ዮሐ. 13፥1)። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በ13ኛው የወንጌሉ ምዕራፍ፥ አይሁድ "ፔሳህ"[32] ብለው በሚጠሩት የፋሲካ በዓላቸው ጠቦቶችን እየሠዉ ባሉበት ጊዜ አማናዊው የፋሲካ በግ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ለኃጢአታችን ቤዛ ሆኖ እንደተሠዋ አድርጎ

---

[29] "ራ" ጠበቅ ብሎ ይነበብ።

[30] ትርጒም የእኔ።

[31] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum* [Ethiopian Missal (Book of Liturgy)] (Rome: Vatican Printing Press, 1945) p. 120።

[32] በእንግሊዝኛ Passover ወይም *Pascha* ይባላል።

ያቀርበዋል።[33] ይህንን አሳብ ግልጽ በማድረግ አባቶቻችን መተርጕማን፡- “ኢየሱስም ከፋሲካ በዓል በፊት፥ ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ ደረሰ አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው” (ዮሐ. 13፥1) የሚለውን ጥቅስ ሲተረጕሙ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ እንደ ደረሰ አውቆ፥ ደቀ መዛሙርቱንና በዓለም ያሉትን ወገኖቹን (አማንያንን) “እሰቀልላችኋለሁ አላቸው” ብለዋል።[34] ይሁዳ ቍራሹን ተቀብሎ ከወጣም በኋላ፥ ጌታችን ኢየሱስ ስለራሱ ሲናገር፡- “አሁን የሰው ልጅ ከበረ፥ እግዚአብሔርም ስለእርሱ ከበረ፤ እግዚአብሔር ስለእርሱ የከበረ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ደግሞ እርሱን ራሱን ያከብረዋል” ያለውን ደግሞ “እግዚአብሔር በመስቀል ይገልጸዋል”[35] ማለት እንደሆነ ተርጕመው ነግረውናል።

ሦስቱ ወንጌላውያን፥ ጌታችን ኢየሱስ ኅብስቱን፡- “አንሥቶ፥ ባርኮ፥ ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው”፤ ጽዋውን ደግሞ፡- “አንሥቶ፥ አመስግኖ፥ ሰጣቸው” ሲሉ ጽፈውልናል። በዚህም በኅብስቱ ላይ አራት ድርጊቶችን (ነሥአ፥ ባረከ፥ ፈተተ፥ ወሀበ)፤ በጽዋው ላይ ደግሞ ሦስት ድርጊቶችን (ነሥአ፥ ባረከ፥ ወሀበ) መፈጸሙን እንገነዘባለን። ማቴዎስና ማርቆስ አንድ ዓይነት አገላለጽ ሲጠቀሙ፥ ሉቃስ ግን ከእነርሱ ይለያል። ማቴዎስና ማርቆስ፥ ደቀ መዛሙርቱ የፋሲካውን እራት እየበሉ ሳለ፥ ጌታ ኢየሱስ ከጽዋው በፊት ኅብስቱን አንሥቶና ባርኮ “እንካችሁ ይህ ሥጋዬ ነው” ብሎ አንደሰጣቸውና ወዲያው ጽዋውንም አንሥቶና አመስግኖ “ከእርሱ ጠጡ” ብሎ እንደሰጣቸው ጽፈዋል (ማቴ. 26፥26-29፤ ማር. 14፥22-24)። ሉቃስ ግን፥ ጌታችን መጀመሪያ ኅብስቱን ሳይሆን ጽዋውን አንደባረከና “ይህን እንካችሁ በመካከላችሁ ተካፈሉት” እንዳላቸው ይነግረናል። ቀጥሎም ኅብስቱን አንሥቶ፥ አመስግኖና ቆርሶ፡- “ስለ፡ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ

[33] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 14.

[34] “ዮሐንስ ፲፫፥፩” *ወንጌል ቅዱስ ዘእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘዜነዉ ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ዮሐንስ፡ ከቀድሞ አባቶቻችን ጀምሮ ቃል ለቃል ሲነገር የመጣው ንባቡና ትርጓሜው፤ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደ ተረጐሙት* (አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1985 ዓ.ም) ገጽ 76።

[35] ዝኒ ከማሁ፡ “ዮሐ. ፲፫፥ ፴፪” ገጽ. 79።

አድርጉት'' ብሎ እንደሰጣቸው ከነገረን በኋላ፥ ከማቴዎስና ማርቆስ አገላለጽ በተለየ መልኩ፦ "ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፦ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው'' ሲል ይጽፋል (ሉቃ. 22፥17-20)። እዚህ ላይ፥ ጌታ ስለ ሥጋውና ስለ ደሙ (ጽዋው) የተናገረውን ሲዘግቡ በወንጌላውያኑ አገላለጽ ላይ ልዩነት እንዳለ ልብ እንበል፤ ማቴዎስና ማርቆስ፥ ጌታችን ኅብስቱን ባርኮ ሲሰጣቸው ሉቃስ እንደጻፈው "ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት'' እንዳላቸው አልጻፉም። ስለ ጽዋው ሲጽፉ ደግሞ፦ "ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው'' የሚል አገላለጽ ተጠቅመዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ከሦስቱ ወንጌላውያን የቅዱስ ሉቃስን አገላለጽ ይከተላል። ጌታ ኅብስቱን አንሥቶ ካመሰገነና ከቆረሰ በኋላ "እንካችሁ ብሉ፥ ይህ ስለ፡ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት'' የሚለውን ዓረፍተ ነገር ከሉቃስ ወስዷል (1 ቆሮ. 11፥ 23-26)። ስለ ጽዋውም የማቴዎስንና ማርቆስን አገላለጽ ሳይሆን፥ የሉቃስን በመከተል ጌታ ኢየሱስ "ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው'' ብሎ እንደሰጣቸው ይነግረናል። በአጠቃላይ፥ ከኅብስቱ በፊት ጽዋው እንደተባረከ በሉቃስ መጠቀሱ፥ እንዲሁም ማቴዎስና ማርቆስ እንደጻፉልን የቍርባኑ ሥርዓት መጨረሻ ላይ ደቀ መዛሙርቱ መዝሙር መዘመራቸው (ማቴ. 26፥30፣ ማር. 14፡26) ከላይ እንደተመለከትነው፥ የአይሁድ አምልኮ ሥርዓት እየተካሄደ በነበረበት የፋሲካው እራት ላይ ጌታችን ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን ሥርዓተ ቍርባንን እንደመሠረተልን በግልጽ ያሳያል።

ወንጌላቱ በተጻፉባቸው ጊዜያት እንደተደረሱ የሚነገርላቸው መጻሕፍት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ስላሉ፥ ከወንጌላቱና ከመጻሕፍተ ሥርዓቱ የትኞቹ ቀድመው እንደተጻፉ እስካሁን ድረስ ሊቃውንቱን ያከራክራሉ።[36] ለምሳሌ፥ በ60 ዓ.እ. ሶርያ ውስጥ እንደተደረሰ የሚነገርለትና መግቢያው ላይ በግሪኩ "*ዲዳኺ*''[37] በማለት

[36] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 13.
[37] "Διδαχὴ'' - በእንግሊዝኛ "*Didache*'' ተብሎ የተወሰደው ይህ የግሪክ ቃል Training (ሥልጠና) ማለት ነው።

የሚጀምረው ዲዳኬ፥ እንደ ሉቃስ ወንጌል አገላለጽ ከኅብስቱ በፊት ጽዋው እንደሚባረክ ይነግረናል። የጽዋውም ጸሎተ ቡራኬ፡- “አባታችን [ሆይ]፡ በልጅህ በኢየሱስ ስለገለጽከው ስለባሪያህ ዳዊት ቅዱስ የወይን ግንድ እናመሰግንሃለን፤ ክብር ለአንተ ይሁን፥ ለዘላለሙ” የሚል እንደነበር ዘግቦልናል።[38] በተጨማሪም ጥንታውያኑ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት የወንጌላቱን አገላለጽ ከመከተል ባሻገር፥ አንዳንድ ሐረጋትንና ዐረፍተ ነገሮችን አክለው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ስም የተደረሰው ቅዳሴ “ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት . . . ነጸረ ሰማየ ኀበ አቡሁ አኃዜ ኵሉ”[39] ይላል። ይህም በአማርኛ፡- በተቀደሱ (ንዑዳት) በሆኑ እጆቹ ኅብስቱን አንሥቶ ያዘ፤ ሁሉን ወደያዘ ወደ አባቱ ወደ ሰማይ ተመለከተ ማለት ነው።

በተመሳሳይ መልኩ፥ “የጌታ ወንድም” ተብሎ የሚታወቀው የኢየሩሳሌሙ ኤጲስ፡ቆጶስ የያዕቆብ ቅዳሴ ደግሞ፡- “ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እለ እንበለ ነውር፤ … አንቃዕደወ ኀበ አብ፤ አእኰተ፥ ባረከ፥ ወቀደሰ፥ ወፈተተ”[40] ይላል። በተለምዶ ቅዱስ ሄጶሊጦስ/አቡሊዲስ ዘሮሜ ደርሶታል ከሚባለው ሐዋርያዊ ትውፊት[41] የተወሰደውና በቤተ ክርስያናችን “ቅዳሴ ሐዋርያት” በሚል ስም የሚታወቀው አኰቴተ ቍርባን፥ ከቅዳሴ ያዕቆብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጌታችን ሥርዓተ ቍርባንን የመሠረተባቸው ቃላት (ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ)[42] ይጠቀማል፡- “እርሱን በያዙበት በዚያች ሌሊት፡ ነውር በሌለባቸው፥ ንዑዳት፥ ክቡራት፥ ብፁዓትም በሚሆኑ እጆቹ ኅብስቱን አንሥቶ ያዘ፤ . . . ወደ አንተ ወደ አባቱ፥ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ፡ አመሰገነ፥ ባረከ፥ ቈረሰ።”[43] ልዩነቱ፥ የጌታ ወንድም የያዕቆብ ቅዳሴ፥ “አእኰተ (አመሰገነ)፥ ባረከ፥ ወቀደሰ” የሚሉ አንድ ዓይነት ትርጉም

---

[38] *The Didache: Translation, Analysis, and Commentary,* trans. Aaron Milavec (Collegeville, Minnesota: Liturgical Press, 2003) Ch. 9:2, p. 23.

[39] “አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ,” *Missale Ethiopicum,* p. 121።

[40] “አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ”፡ ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 108።

[41] Apostolic Tradition.

[42] Institution Narrative.

[43] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ “ቅዳሴ ሐዋርያት”፡ ቍ. 39-41፣ ገጽ 108።

ያላቸውን ሦስት ግሶች ሲጠቀም፥ ቅዳሴ ሐዋርያት ደግሞ "ቀደሰ" የሚለውን ትቶ "አእኰተ፥ ባረከ" ማለቱ ነው።

## አጋፔ (የፍቅር ማዕድ) እና ቅዱስ ቍርባን

በሐዋርያት እና እነርሱን በተኳቸው ሐዋርያውያን አበው[44] ዘመን፥ የክርስቲያኖች የፍቅር ማዕድ[45] እና የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት አንድ ላይ ይካሄድ እንደነበር የተለያዩ ጥንታውያን መዛግብት ያመለክታሉ። በበዓለ ኀምሳ የቅዱስ ጴጥሮስን ስብከት ሰምተው ቃሉን የተቀበሉ ሦስት ሺህ ነፍሳት (ሰዎች) ተጠምቀው የሐዋርያትን ማኅበር እንደተቀላቀሉ ቅዱስ ሉቃስ ጽፎልናል (የሐዋ. 2፥14-42)። እነዚህ የመጀመሪያዎቹ አማንያን "አንድ ልብ፥ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው" (የሐዋ. 4፥32) እስኪባልላቸው ድረስ ገንዘባቸውን ሐዋርያት እግር ሥር እያስቀመጡና እንጀራንም በኅብረት እየቆረሱ ይኖሩ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ፥ ደቀ መዛሙርትም እጅግ በዝተው፥ "የወንዶች ቍጥር አምስት ሺህ ያህል" እንደሆነ ሉቃስ ዘግቦልናል (የሐዋ. 4፥4)። ቍጥራቸው እየበዛ ሲሄድ ግን አንድ ችግር ተፈጠረ። ከግሪክ አገር የመጡ አይሁድ፥ በይሁዳ በሚኖሩ ወገኖቻቸው ላይ "መበለቶቻችንን ችላ አላችሁብን" ሲሉ አንጐራጎሩባቸው። ወቀሳው የመጣው በማዕድ አገልግሎት ጉዳይ ስለሆነ፥ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በማዕድ ምክንያት በተፈጠረው አለመግባባት ቃለ እግዚአብሔር እንዳይበደል፦ "የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም" ሲሉ ችግሩን ለመፍታት መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ዲያቆናት ለዚሁ ጉዳይ (ለማዕድ አገልግሎት) ሾሟቸው (የሐዋ. 6፥1-6)።

ቅዱስ እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ካረፈ በኋላ በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን[46] ታላቅ ስደት ስለሆነ የመጀመሪያዎቹ አማንያን ወደ ይሁዳና ሰማርያ

---

[44] Apostolic Fathers.

[45] Αγάπη (አጋፒ) ከሚለውና "ፍቅር" የሚል ትርጉም ካለው ቃል ተወስዶ "*agape* meal" (የፍቅር ማዕድ) ይባላል፡፡

[46] *ἐκκλησία*/ ecclēsia/ ማኅበረ ምእመናን፡፡

አገሮች ተበተኑ። አንዳንዶቹም እስከ ደሴተ ቆጵሮስ እና አንጾኪያ[47] ድረስ ተሰደዱ፤ በአንጾኪያ የክርስቶስ ተከታዮች "ክርስቲያን" የሚለው የመጠሪያ ስም ተሰጣቸው (የሐዋ. 8፥1፤ 11፥19-26)። የጌታን ደቀ መዛሙርት (ክርስቲያኖችን) ያሳድድ የነበረው የቀድሞው ሳውል፥ ደማስቆ መንገድ ላይ በጌታ ከተማረከ በኋላ በሐናንያ ተጠምቆ በበርናባስ አማካኝነት የሐዋርያትን ኅብረት ተቀላቀለ (የሐዋ. 8፥2፤ 9፥1-27)። በርናባስና ሳውል የኢየሱስን ወንጌል በጠርሴስና አንጾኪያ መሰከሩ (የሐዋ. 11፥22-26)። ሄሮድስ አይሁድን ደስ ለማሰኘት ብሎ የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ሲያስገድለው፥ ጴጥሮስን ደግሞ ወደ ወኅኒ (እስር ቤት) አስገባው። ሰርግዮስ ጳውሎስ የተባለው የቆጵሮስ አገረ ገዥ የበርናባስንና ሳውልን ትምህርት ሰምቶ፥ እንዲሁም ሳውል  በጠንቋዩ በርያሱስ (ኤልማስ) ላይ ያደረገውን ተአምራት አይቶ ካመነ በኋላ ሳውል በዚሁ አገረ ገዢ ስም "ጳውሎስ"[48] ተብሎ ተጠራ (የሐዋ. 13፥4-12)።

ሐዋርያት ለወንጌል አገልግሎት በተሰማሩባቸው ቦታዎች ሁሉ አማንያን ሊጋፔ ተብሎ ለሚጠራው የፍቅር ማዕድና ለቅዱስ ቍርባን አገልግሎት ይሰባሰቡ ነበር። ለምሳሌ ጢሮአዳ በምትባል የግሪክ ከተማ ጳውሎስ ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቍረስ የተሰበሰቡትን እስከ መንፈቀ ሌሊት ድረስ ያስተምራቸው እንደ ነበር የሐዋርያት ሥራ 20፥7 ላይ ተገልጿል። "የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን" የተባለው እሑድ ሲሆን፥ "እንጀራ መቍረስ" ተብሎ የተገለጸው ደግሞ ከፍቅር ማዕድ ጋር አብሮ ይካሄድ የነበረው የቅዱስ ቍርባን አገልግሎት ነው። የጄርጋሞን ሊቀ ጳጳሳት ጆን ዚዙለስ፥ ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መሠረት በማድረግ

---

[47] በአሁኑ ዘመን ይህች ከተማ Antakya በሚል ስም ለሶርያ ድንበር ቅርብ በሆነው ደቡባዊ ቱርክ ግዛት ውስጥ ትገኛለች።

[48] መተርጕማን አባቶቻችን አገረ ገዢው ሰርግዮስ ጳውሎስ፥ የሳውልን አስደናቂ ትምህርት ሰምቶ፥ ጳውሎስ ማለት ብርሃን ማለት ነውና "እኔ ሰውን አፍአዊ (የውጪ) አእምሮውን በአፍአዊ ጥበብ ብሩህ ባደርግ እናቴና አባቴ ጳውሎስ ብለውኝ ነበር፤ የሰውን ውስጣዊ አእምሮውን በውስጣዊ ጥበብ ብሩህ ለምታደርግ ላንተ ጳውሎስ መባል ይገባሃል ሲል" ስሙን አበረከተለት ይላሉ። "መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ሮሜ"፥ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ 1988 ዓ.ም.) ገጽ 18.

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሮአዳ በምትባለው ከተማ በዕለተ እሑድ የተካሄደውን የቅዱስ ቊርባን አገልግሎት መርቷል ብለን መናገር እንደምንችል አስረድተዋል።[49]

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በዕለተ እሑድ ለአምልኮና ለትምህርተ ወንጌል ሲሰባሰቡ፥ ቅዱስ ቊርባንን የሚቀበሉት የፍቅር ማዕዳቸውን በጥሩ ልብና በሐሤት አብረው ከተካፈሉ በኋላ ነበር።[50] መድኃኒታችን ክርስቶስ "በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው" ተብሎ እንደተጻፈ፥ ለደቀመዛሙርቱ ቅዱስ ቊርባንን የሰጣቸው ዘላለማዊ ፍቅሩን የገለጸበት ማዕድ አድርጎ ነው (ዮሐ. 13፥1-4፤ 21-25)። የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴም፦ "ወልደ እግዚአብሔር ... በሠርጉ ጊዜ በሐዋርያት ፊት ሥጋውንና ክቡር ደሙን ማዕድ አድርጎ ሠራ"[51] ይላል። ለዚህም ነው በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፥ አማንያን ቅዱስ ቊርባንን ከፍቅር ማዕድ (*አጋፔ*) ጋር ይቀበሉ የነበሩት[52]። በመጀመሪያው ምእት ዓመት የነበሩ ክርስቲያኖች ተጋብኦተ ቊርባን የሚያደርጉት በዕለተ እሑድ እንደሆነ የሚጠቁሙ ጥንታውያን መዛግብት ቢኖሩም፥ [53] በዘመናችን እንደሚደረገው በጠዋት (ምንም ነገር ሳይበሉ) ይሰባሰቡ ነበር ማለት ግን አይደለም። በዚያን ዘመን፥ ክርስቲያኖች የሚሰባሰቡት በቀዳሚት ሰንበት (ቅዳሜ)[54] ማታ እንደነበርና የቅዱስ

[49] John Zizioulas, *Eucharist, Bishop, Church* (Brookline, MA: Holy Cross Orthodox Press, 2001) p. 62.

[50] Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy*, p. 4.

[51] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ሥርዓተ ቅዳሴ ዘይደሉ ለቀሲስ ወለዲያቆን ወለኵሉ ሕዝብ"፡ ቊ 9፤ ገጽ 6-7።

[52] Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy*, p. 4.

[53] ለምሳሌ ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ (St. Justin Martyr) በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያኖች በዕለተ እሑድ ይሰባሰቡ እንደነበር ሲገልጽ እንዲህ ይላል፦ "And on the day called Sunday all who live in cities or in the country gather together in one place, and the memoirs of the Apostles or the writings of the prophets are read, as long as time permits." *Ancient Christian Writers: St. Justin Martyr: The First and Second Apologies,* trans. Leslie Willian Barnard (New York: Paulist Press, 1997) Apology I, 67, p. 71.

[54] በአይሁድ የቀን አቆጣጥር ሥርዓት ማንኛውም ዕለት የሚጀምረው በዋዜማው 11፡00 ሰዓት (5፡00 PM) ላይ ነው። ለምሳሌ፥ አይሁድ ሰንበትን የሚያከብሩት ከአርብ 11፡00 ሰዓት (5፡00 PM) ጀምሮ ነው። በኢየሩሳሌም የነበረችው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባላት፥ የቀድሞ አይሁድ ስለነበሩ ይህን ሥርዓት በመጠበቅ ጌታ ሞትን ድል አድርጎ በተነሳባት በክርስቲያኖች ሰንበት (እሑድ) ለአምልኮ የሚሰባሰቡት ዕለተ እሑድ በሚጀምርበት ቅዳሜ ማታ (ከ11፡00 ሰዓት ወይም 5፡00 PM) በኋላ ነበር ማለት ነው።

ቍርባን ሥርዓት ከፍቅር ማዕድ ጋር አብሮ ይከናወን እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ።[55]

በመጀመሪያው ምእት ዓመት አማንያን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ሲሰባሰቡ የነበራቸው የጸሎት ሥርዓት ምን እንደነበር በግልጽ ማወቅ ባይቻልም፥ ፍንጭ የሚሰጡ መረጃዎችን ማግኘት ግን አያዳግትም። ቅዱሳን ሐዋርያት ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መልእክት ይጽፉ የነበረው መልእክቱ በምእመናን ጉባኤ እንዲነበብ ነበር። ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ፡- "ይህች መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ፥ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር[56] ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ" ብሏቸዋል (ቈላስ. 4፥16)። ተመሳሳይ ሐዋርያዊ ትእዛዝን 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥27 ላይ እናነባለን። ስለዚህ የሐዋርያትን ጦማር ማንበብ የሥርዓተ ቍርባኑ አንዱ ክፍል ነበር ማለት ነው። "በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ" (ሮሜ 16፥16፤ 2 ቆሮ. 13፥12) በሚለው ትእዛዝ መሠረት ደግሞ አማንያኑ የፍቅር ሰላምታን ይለዋወጡ ነበር። ይህ ሥርዓት የሐዋርያትን ትውፊት በተከተሉ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ እስካሁን ድረስ ይከናወናል፤ በእኛ ቤተ ክርስቲያን "አምኃ ቅድሳት - የተቀደሰች እማኄ/እጅ መነሳሳት"[57] በሚል ስያሜ ይታወቃል።[58]

---

[55] Bradshaw, "Introduction: The Evolution of Early Anaphoras" *Essays on Eucharistic Prayers,* p. 1.

[56] እዚህ ላይ አማርኛው "ማኅበር" የሚለውን፥ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉበት ግሪኩ "*ἐκκλησία* - ekklēsia (ecclēsia)" ይለዋል፤ ትርጉሙ "ቤተ ክርስቲያን" ማለት ሲሆን፥ ይህም የሚያሳየው በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን የሚባለው ማኅበረ ምእመናን (የአማንያን ጉባኤ) እንደሆነ ነው። *The New Testament Greek and English: The Greek Text prepared by the United Bible Societies,* eds. Kurt Aland and others, 2nd ed., (New York: American Bible Society, 1981) p. 703 ይመልከቱ።

[57] ለዚህም ነው ሠራዒው ዲያቆን ወደ ሦስተኛው የቅዳሴ ክፍል (ፍሬ ቅዳሴ/ የአማንያን ቅዳሴ) ከመግባታችን በፊት፡- "ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት - እርስ በርሳችሁ በተለየች እማኄ እጅ ተነሳሱ" የሚለን። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ጸልዩ በእንተ ሰላም" ቍ. 58፤ ገጽ 110። ነገር ግን ተገቢው ትምህርት ለምእመናን ስላልተሰጠ፥ እንደ ዲያቆኑ ትእዛዝ ምእመናን እርስ በእርሳቸው ሰላም መባባል (እጅ መነሳሳት) ሲገባቸው፥ ፊታቸውን ወደ ቤተ መቅደሱ አራት አቅጣጫ እያዞሩ ጎንበስ ሲሉ እናያለን።

[58] በእንግሊዝኛ holy kiss ወይም kiss of peace ይባላል፡፡

የጥንት ክርስቲያኖች የፍቅር ሰላምታን ከተለዋወጡ በኋላ የሥርዓተ ቊርባኑ መሪ[59] በሐዋርያዊ ቡራኬ ይባርካቸው ነበር። ቡራኬውም በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፥ 14 ላይ ተጠቅሷል፦ "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።" *አኰቴተ ቊርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ* በሚል ስም የሚታወቀው የጌታ ወንድም የያዕቆብ ቅዳሴ በዚህ ሐዋርያዊ ቡራኬ ይጀምራል፦ "ፍቅረ እግዚአብሔር አብ፥ ወጸጋ ዘዋሕድ ወልድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወሱታፌ መንፈስ ቅዱስ የሀሉ ምስሌክሙ።"[60] ከቡራኬው በኋላ፥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በጻፈው የመጀመሪያው ጦማር ላይ ጌታችን ኢየሱስ "አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት" ወይም በምሴተ ኀሙስ ለደቀ መዛሙርቱ ኅብስቱንና ጽዋውን ባርኮ ስለመስጠቱ የጻፈው ገለጻ (ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ) ይነበባል (1 ቆሮ. 11፥23-26)። አማንያኑም የጌታን ሕማምና ሞት እያሰቡ ቅዱስ ቊርባንን ይቀበሉ ነበር።

የቀደምት ክርስቲያኖች የፍቅር ጉባኤ ከኢአማንያንና አሕዛባዊ ባሕርያቸው ካልለቀቃቸው አዲስ አማንያን በኩል ፈተና ገጠመው። ክርስትና በሮማ ግዛት ውስጥ እውቅና እስካገኘበት እስከ 4ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ድረስ የክርስትና እምነት በአሕዛብ ዘንድ ሕገ-ወጥ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በሮማ ቄሣሮች አዋጅ በክርስቲያኖች ላይ ስደትና አሰቃቂ መከራዎች ይደርሱባቸው እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስተምረናል። ስለሆነም ክርስቲያኖች በየሳምንቱ እሑድ ተጋብኦተ ቊርባን የሚያደርጉት በድብቅ በየግለሰቦች ቤት ነበር። ሮሜ 16፥ 5 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጵርስቅላና አቂላ ቤት ውስጥ "ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ" ይላል። ተመሳሳይ ሰላምታ በፊልሞና ቤት ውስጥ ለነበረቻው ቤተ ክርስቲያንም (ማኅበረ ምእመናን) ያቀርባል (ፊልሞ. ቊ. 2)። ክርስቲያኖች በድብቅ በቤት ውስጥ እንደሚሰባሰቡና የፍቅር ማዕድን ተሳትፈው የክርስቶስን ሥጋና ደም እንደሚቀበሉ በሮማ ግዛት የነበሩ አሕዛብ ሲሰሙ፥ በተለያዩ የሐሰት ውንጀላዎች

[59] Celebrant.

[60] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 90; "አኰቴተ ቊርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ" in *Missale Ethiopicum,* p. 107.

ይከስሷቸው ነበር።[61] ለክስ እንዲያመቻቸው፥ ሳያምኑበት ለመታዘብ ብቻ የክርስቲያኖችን የፍቅር ማዕድ የተቀላቀሉ አሕዛብ ነበሩ። የያዕቆብ ወንድም ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ ቍ. 12 ላይ እነዚህን እምነት-አልባ ሰዎች ሳይሆን አይቀርም "በፍቅር ግብዣችሁ [አጋፔ] እንደ እድፍ ናቸው" የሚለው።[62]

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የፍቅር ማዕዱ ከስያሜው ጋር አብሮ የማይሄድ አሕዛባዊ ልምምድን ይዞ ብቅ ስላለ የቅዱስ ጳውሎስን ጠንካራ ተግሣጽ አስከተለ። ምንም እንኳ ሐዋርያው የመጀመሪያውን የቆሮንቶስ መልእክት በጻፈበት ጊዜ "የፍቅር ማዕዱና ቅዱስ ቍርባን አንድ ላይ ነበር የሚካሄዱት ወይስ ተለያይተው ነበር?" የሚለው ጥያቄ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሊቃውንትን ቢያከራክርም፥ በ1ቆሮ.11፡17-44 የምናነበው የሐዋርያው መልእክት የሚጠቁመው አጋፔ የተሰኘው የፍቅር ማዕድ ከሥርዓተ ቍርባን ጋር አብሮ ይከናወን እንደነበር ነው።[63] የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ወደ ማኅበር[64] ሲመጡ ተጠባብቀው በኅብረት የፍቅር ማዕዱን መመገብ ሲገባቸው "እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላ" ነበር። ስለሆነም በትዕግሥት የጸሎቱን ፍጻሜ የሚጠብቁት ሲራቡ፥ ሥርዓት አልበኞቹ ደግሞ መስከር ጀመሩ (1 ቆሮ. 11፥22)። ይህን የሰማው ጳውሎስ የፍቅር ማዕዱን ለመብላትና ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል በሚሰባሰቡበት ጊዜ "እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ" ሲል አዘዛቸው፤ መጠበቅ ያልቻለና የራበው ካለ ግን "ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ" አላቸው (ቍ. 33-34)። በ1 ቆሮ. 10፥ 16 ላይ

---

[61] ከክሶቹ መካከል፥ የሕፃናት ጥምቀትን እና የጌታን ሥጋና ደም መቀበልን በተሳሳተ መልኩ የተረጐሙ ነበሩ። ይህም ማለት፥ ክርስቲያኖች ሕፃናትን በመሥዋዕትነት እንደሚያቀርቡ ተደርጎ በሕፃናት ግድያ (child murder) እና "የሰውን ሥጋ ይበላሉ" (cannibalism) በሚሉ የሐሰት ወንጀሎች ይከሰሱ ነበር። በተጨማሪም ሮማውያን እንደ አማልክት የተቀበሏቸውን ጣዖታት ክርስቲያኖች ስለማያመልኩ፥ አምላክ-አልባ (atheists) እንደሆኑ ተደርገውም ተወንጅለዋል። See "Introduction," *St. Justin Martyr: The First and Second Apologies,* p. 1.

[62] በግሪኩ መጠነኛ ልዩነት ቢያሳይም የ"ፍቅር ግብዣ" የሚለው ቃል 2 ጴጥ 2፥13 ላይም ተጠቅሷል። ለዝርዝሩ Dom Gregory Dix, *The Shape of the Liturgy*: *New Edition with an Introduction by Simon Jones* (London: Bloomsbury T&T Clark, 2015) p. 99 ይመልከቱ።

[63] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ. 98።

[64] የግሪኩ አዲስ ኪዳን *ἐκκλησία* – (ኤክሊሲያ) የሚለውን ቃል ይጠቀማል፡፡

“የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?” ሲል እንደጻፈላቸው፥ አማንያኑ የሚያደርጉት ተጋብኦተ ቍርባን ዓላማው የጌታን ሥጋና ደም ለመቀበል ስለሆነ እንደሚገባው ሆኖ ያልተቀበለ ወይም ሥርዓት አልባ በሆነ መልኩ የሚቀበል ሰው ጽኑ ፍርድ እንደሚጠብቀው ጻፈላቸው። የሐዋርያው የማስጠንቀቂያ መልእክት እንዲህ ይላል፡- “ስለዚህ ሳይገባው[65] ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ፡ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና” (1 ቆሮ. 11፥ 27-30)።

በዚህ ችግር ምክንያት ምእመናን የፍቅር ማዕዱን ከተመገቡ በኋላ ቅዱስ ቍርባንን መቀበላቸው ቀርቶ፥ የፍቅሩ ማዕድ (*አጋፔ*) ቅዱስ ቍርባን ከሚከብርበት አገልግሎት (አኰቴተ ቍርባን) ተለየ። ይህ የሆነበትን ጊዜ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም፥ በመጀመሪያው ምእት ዓመት መጨረሻ ወይም በሁለተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ የቅዳሴው አገልግሎት ማታ መሆኑ ቀርቶ በዕለተ እሑድ በጠዋት መካሄድ ጀመረ።[66] እየቆየም ቅዱስ ቁርባንን ከመቀበል በፊት መጾም እንደሚያስፈልግ የሚደነግጉ ቀኖናዎች ተሠሩ። ከሐዋርያት ዕረፍት በኋላ፥ እነርሱን በተኳቸው ተላውያነ ሐዋርያት[67] ወይም ሐዋርያውያን አበው ዘመናት፥ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ፍቅር በጎደለው የመለያየት በሽታ እንደተፈተነች[68]

---

[65] “ባ” ጠበቅ ብሎ ይነበብ።

[66] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 21.

[67] የሐዋርያት ተከታዮች ማለት ሲሆን በቅዱሳን ሐዋርያት መናብርት ላይ የተሾሙና እነርሱን ተከተው የአንዲቷን ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትና ትውፊት የጠበቁ አባቶች የሚጠሩበት ስያሜ ነው። ለምሳሌ “ሃይማኖተ አበው” የተባለውና የጥንታውያን አባቶችን ትምህርት ሰብስቦ የያዘ መጽሐፍ፥ በአንደኛው እና ሁለተኛው ምእት ዓመታት የነበሩ አባቶችን፡- “ዲዮናስዮስ ተላዊሆሙ ለሐዋርያት፥ የአቴና ኤጲስ ቆጶስ”፥ “አግናጥዮስ ተላዊሆሙ ለሐዋርያት፥ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት” “ሄሬኔዎስ ረድአ ሐዋርያት፥ የኤዶም ኤጲስ ቆጶስ” በማለት ይጠራቸዋል። *ሃይማኖተ አበው* (3ኛ እትም)፥ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ 1986 ዓ.ም.፣ ገጽ 29፥ 34 እና 36 ይመልከቱ።

[68] ቅዱስ ጳውሎስ መለያየታቸውን ወቅሶ ለቆሮንቶስ ምእመናን እንደጻፈላቸው (1 ቆሮ. 1፥10-17)፥ ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮሜም (St. Clement of Rome) ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልእክት ጽፎላቸው ነበር። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ 4፥2 ላይ “በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ከቀሌምንጦስና ደግሞ ከእኔ ጋር

የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት የሚያናጉ ተግዳሮቶች ስለተፈጠሩ፥ በሐዋርያት መናብርት ላይ የተሾሙ አባቶች በቅዱስ ቊርባን ኅብረት የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዴት እንደሚጠበቅ የሚያስተምሩ መልእክቶችን ይጽፉ ነበር፡፡ ከእነዚህ መልእክታት መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት የቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ጦማራት ናቸው፡፡

## የቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ መልእክታት

በመንበረ አንጾኪያ ሦስተኛ [69] ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ የተሾመውና በ107 ዓ.እ. ያረፈው አባት፥ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን "ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ" (ለአንበሳ የተሰጠ)[70] በሚል ስያሜ ይታወቃል። ቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ፡-

---

አብረው ከሠሩት" የሚለውን ይዘው በ57 ዓ.እ. ቀሌምንጦስ ዘሮሜ ከጳውሎስ ጋር በፊልጵስዩስ እንዳገለገለ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይናገራሉ። ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮሜ ለቆሮንቶስ ምእመናን በጻፈው መልእክት፥ ከመከፋፈላቸው በፊት ስለነበራቸው እምነት፥ እውቀትና እንግዳን የመቀበል ባህል ካመሰገናቸው በኋላ በመካከላቸው ክፍፍልና መለያየት በመፈጠሩ ደግሞ በአጽንኦት ይገስጻቸዋል። የክፉ ነገር ሁሉ መንስዔው ምቀኝነትና ቅንዓት (envy and jealously) መሆኑን ጠቁሞ፥ የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጠር አድመኝነትንና መለያየትን ደግሞ፡- "አሳፋሪ፥ የተጠላ እና በእግዚአብሔር ምርጦች የተወገዘ" ሲል ይገልጸዋል። See "The First Epistle of Clement to the Corinthians," *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* eds. Alexander Roberts and James Donaldson, Vol. 1 (Michigan: WM. B. Eerdmans Publishing Company, 1979) p. 5-6.

[69]"አግናጥዮስ ሰማዕት ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያ፤ ወውእቱ ሣልስ እምድኅረ ጴጥሮስ" የሚለውን *ሃይማኖተ አበው፥* "ዘአግናጥዮስ" ምዕራፍ 11፥ ክፍል 1፣ 1986 ዓ.ም.፣ ገጽ 36 ይመልከቱ።

[70] ቅዱስ አግናጥዮስ "ምጥው ለአንበሳ" የተባለበት ምክንያት በሮማ አደባባይ ለአናብስት (ለአንበሶች) ተሰጥቶ ሰማዕትነትን በመፈጸሙ ነው። በወታደሮች ታስሮ ወደ ሮም (ሮሜ) እያመራ በነበረበት ወቅት፥ እጅግ የሚወዱት የሮሜ ምእመናን እንዳይሞት በማከላከል የሰማዕትነት አክሊልን እንዳያሳጡት፡- "የአናብስቱ ምግብ እንድሆን አትከልክሉኝ፥ በእነዚህ አውሬዎች አማካኝነት አምላኬን አገኘው ዘንድ እወዳለሁ። እኔ የእግዚአብሔር ስንዴ ነኝ፤ በአውሬዎቹ (በአንበሶቹ) ጥርሶች ተፈጭቼ ለእግዚአብሔር የቀረበ ንጹሕ ኅብስት እሆን ዘንድ" በማለት ጽፎላቸዋል። "Epistle of Ignatius to the Romans, Chap. IV" *The Ante-Nicene Fathers*, p. 75. በተጨማሪ ቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ፥ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን (Eastern Orthodox Church) ዘንድ "*Theophoros*" በሚል ስም ይታወቃል። ይህም "ጸዋሬ አምላክ (አምላክን የተሸከመ)" ማለት ነው። ይህ ስም ለዚህ አባት የተሰጠው፥ ቅድስናን በተላበሰው ሕይወቱ አምላኩን ያሳይ ስለነበር ሲሆን፥ እንዲሁም በማቴዎስ ወንጌል 18፥2-3 ላይ እንደተጠቀሰው፡- "እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም" የሚለውን ትምህርት ጌታችን ኢየሱስ በሚያስተምርበት ጊዜ፥ ጠርቶና አቅፎ በደቀ መዛሙርቱ መካካል ያቆመው ሕፃን ቅዱስ አግናጥዮስ ነበር ተብሎ ስለሚታመን ነው።

በኤፌሶን፥ ማግኔዥያ፥ ትራሊያ፥ ሮም፥ ፊልድልፍያ እና ሰምርኔስ[71] ለነበሩ ክርስቲያኖች፣ እንዲሁም ለሰማዕቱ የሰምርኔስ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ፖሊካርፕ የተለያዩ መልእክቶቹን ጽፏል። ለእርሱ ከነበራቸው ፍቅር የተነሣ በአንበሶች ተበልቶ የክርስቶስ ሰማዕት ከመሆን እንዳይከለክሉት የሮም ክርስቲያኖችን ከተማጸነበት መልእክት በስተቀር፥ የቅዱስ አግናጥዮስ ጦማሮች ባጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር[72] እና የክርስቶስ እንደራሴ በሆነው ጳጳስ መሪነት ሊጠበቅ ስለሚገባው የቤተ ክርስቲያን አንድነት ላይ ያተኮሩ ናቸው። እንደ አግናጥዮስ ትምህርት፥ በአንድ ጳጳስ ሥር ሆና ቅዱስ ቍርባንን የማታቀርብና መከፋፈል የሰፈነባት የክርስቲያኖች ማኅበር በፍጹም ቤተ ክርስቲያን ተብላ ልትጠራ አይገባም።

ትራሊያ በምትባለው ከተማ ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ ክርስቲያኖች በጻፈው ጦማር፥ አንድ ጳጳስና በእርሱ ፈቃድ የቅዳሴውን መሥዋዕት በማቅረብ የሚያገለግሉ ቀሳውስት የቤተ ክርስቲያን መዋቅር መሠረቶች እንደሆኑ በግልጽ ይናገራል። የእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ጳጳስ፥ የክርስቶስ መልእክተኛ እንደመሆኑ ክብር ይገባዋል፤ "ቀሳውስቱ ደግሞ የእግዚአብሔር ጉባኤ ሐዋርያት ናቸው፤ ያለእነዚህ፥ የቅዱሳን ማኅበር የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የለችም።"[73] አግናጥዮስ "በሕያውነት የሚያኖርና ከዘላለማዊ ሞት የሚያድን"[74] በማለት የሚጠራው ቅዱስ ቍርባንን ለማክበርና ለመቀበል አዘውትረው መሰባሰብ እንዳለባቸው የኤፌሶን ምእመናንን አዟቸዋል። እንደርሱ አባባል፥ ካህናትና ምእመናን አብዝተው በተሰባሰቡ ቍጥር "የሰይጣን ኃይል ይደክማል፥ ለኃጢአት የሚያነሣሡ ነበልባላዊ ፍላጻዎቹም መክነው ይወድቃሉ።"[75] ነገር ግን ጠላት ሰይጣን በቅዱሳን ማኅበር (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ቦታ እንዳያገኝ፥ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ጠብቆ እያንዳንዷ

---

[71] ከእነዚህ መካከል ሁለቱ ከተሞች፡- ሰምርኔስና ፊልድልፍያ በዮሐንስ ራእይ 2፥8 እና 3፥7 ላይ ተጠቅሰዋል። በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ሰምርኔስ የሚለው፥ በእንግሊዝኛ "Smyrna" የተባለውን ነው።

[72] Ecclesiastical hierarchy.

[73] "Epistle of Ignatius to the Trallians," *The Ante-Nicene Fathers,* Chap. III, p. 67.

[74] "Epistle of Ignatius to the Ephesians, Chap. XX" *The Ante-Nicene Fathers,* p. 57.

[75] "Epistle of Ignatius to the Ephesians, Chap. XIII" *The Ante-Nicene Fathers,* p. 55.

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከበላይ ጠባቂዋ (ጳጳሱ)፥ ቀሳውስትና ዲያቆናት ጋር አንድነትዋ የሚገለጽበትን አንድ ቅዱስ ቊርባን[76] ልታቀርብ ይገባል። ይህን አስተምህሮ በአጽንኦት የገለጸባቸው ሁለቱ የፊልድልፍያና ሰምርኔስ መልእክቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

> አንድ አሳብ እንደምትሆኑ በጌታ እተማመንባችኋለሁ። በእግዚአብሔር ዘንድ በቅቶ ለተገኘው ፍቅራችሁ በድፍረት እየጻፍሁ አንዲት እምነት፥ አንድ አይነት ስብከት፥ አንድ ቊርባን እንዲኖራችሁ እማፀናችኋለሁ። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አንድ ነው፥ ስለእኛ የፈሰሰው ደምም አንድ ነው፤ [ለሚቀበሉት] ሁሉ አንድ ኅብስት ተቈርሷል፥ አንድ ጽዋ ታድሏቸዋል። ለአንዲቷ [የክርስቶስ] ቤተ ክርስቲያን አንድ መንበር፥ አብረውኝ አገልጋዮች ከሆኑ ቀሳውስትና ዲያቆናት ጋር ደግሞ አንድ ጳጳስ አለ።[77]

> በጳጳሱ ወይም እርሱ በወከለው [ካህን] አማካኝነት የቅዱስ ቊርባን አገልግሎት ይፈጸም። ክርስቶስ ባለበት ሰማያውያን ሠራዊት (መላእክት) እንዳሉ፥ ጳጳሱ ባለበት ማኅበረ ምእመናን (ቤተ ክርስቲያን) አለች። [. . .] ያለጳጳሱ [ፈቃድ] ማጥመቅ ወይም የቅዳሴ መሥዋዕት ማቅረብ ወይም የፍቅር ማዕድ ማዘጋጀት ሕጋዊ አይደለም።[78]

## 2.2. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እምነቷ በመንግሥት ደረጃ እውቅናን አግኝቶ ሰላም እስካገኘችበት እስከ ታላቁ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ (የ4ኛው ምእት ዓመት የመጀመሪያው አጋማሽ) ድረስ በስደት ላይ ነበረች። ጣዖት የሚያመልኩና ራሳቸውም እንዲመለኩ የፈለጉ የሮማ ቄሣሮች ክርስትና ሕገ-ወጥ እምነት እንደሆነ እያወጁ በክርስቲያኖች ላይ አሰቃቂ መከራ ያደርሱባቸው ነበር። በእነዚህ ሦስት መቶ የስደት ዓመታት ክርስቲያኖች አምልኳቸውን የሚፈጽሙት በቤቶቻቸው፥ በዋሻ እና ግበበ-ምድር (መሬት ሥር የተቆፈሩ ጉድጓዶች) እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስተምረናል። ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል የተሰባሰቡ ክርስቲያኖች፥ የቅዳሴውን መሥዋዕት በሰማዕታት መቃብር ላይ ያቀርቡ እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎችም

---

[76] One Eucharist.
[77] "Epistle of Ignatius to the Philadelphians, Chap. IV" *The Ante-Nicene Fathers,* p. 81.
[78] "Epistle of Ignatius to the Smyrneans, Chap. VIII" *The Ante-Nicene Fathers,* p. 89-90 (ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ)፡፡

አሉ።[79] የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በአደባባይ መጥራት ያስገድል ስለነበር፥ በዚያን ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለኢአማንያን ግልጽ ባልሆኑ ምሥጢራዊ ምልክቶች ለማሳየት ተገደዱ። ከምልክቶቹ መካከል ዋነኛው፥ ሁለት የክብ ግማሾችን[80] በማገጣጠም የተሠራ የዓሣ ምልክት ነበር፤ ይህ ምልክት የተመረጠበትም ምክንያት በጥንታዊው ግሪክ ቋንቋ[81] ዓሣ የሚለው ቃል አቻ፦ "*ኢኽሢሰ*"[82] ሲሆን፥ እያንዳንዱ ፊደል የሚወክለው ቃል ለክርስቲያኖች የሚከተለውን ትርጉም በመስጠቱ ነው፦ "*ኢሱስ ኽሪስቶስ ሴኡ ኢዮስ ሶቲር*[83] - ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መድኅን።"

ታዲያ በእነዚህ ዘመናት "ክርስቲያኖች ምን ዓይነት የሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ መጻሕፍት ነበሯቸው?" የሚለው ጥያቄ መፈጠሩ ግድ ነው። የአይሁድ ቅድመ-ማዕድ እና ድኅረ-ማዕድ መባረኪያ ጸሎቶችን መሠረት አድርገው የተጻፉ፥ እንደ ዲዳኬ ያሉ መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ። ነገር ግን እነዚህ ጥንታውያን የሥርዓተ አምልኮ ምንጮች በተጻፉበት ዘመን ስለነበረው የቅዱስ ቊርባን አገልግሎት ዝርዝር መረጃ አይሰጡንም። ለምሳሌ ዲዳኬ፥ በመጀመሪያው ምእት ዓመት ክርስቲያኖች የፍቅር ማዕድ ተካፍለው ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል በሚሰባሰቡበት ጊዜ፥ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ሰባክያን[84] እና ነቢያት የአምልኮውን ሥርዓት ሲመሩ "እንደወደዱ መጠን ምስጋና እንዲያቀርቡ" ይጠየቁ እንደነበር ይነግረናል።[85] ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ[86] ደግሞ፥ እሑድ[87] በተባለው የሳምንቱ

---

[79] Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy*, p. 5.
[80] Arcs.
[81] Koine Greek.
[82] ΙΧΘΥΣ.
[83] "Ιησοῦς Χριστός, Θεοῦ Υἱός, Σωτήρ" - "IXTHYS" የሚለውን ማውጫ በሚከተለው መዝገበ ቃላት ይመልከቱ፦ *Historical Dictionary of the Orthodox Church*, *Religions, Philosophies, and Movements*, No. 9 (London: Scarecrow Press, Inc., 1996) p. 174.
[84] Itinerant preachers.
[85] Milavec, *Didache,* 10:7, p. 25.
[86] St. Justin Martyr.
[87] ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ "Apology" በሚል ስም የሚታወቀውንና ክርስትናን ደግፎ የጻፈውን የዕቅበተ እምነት (እምነትን የመጠበቂያ) ጽሑፍ በ150 ዓ.እ. አካባቢ ሲጽፍ የተጠቀመው የወቅቱን ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ (ግሪክ) ሲሆን፥ በግሪከኛ ይህች ቀን "ἡ Κηρίακή εμερα [ኢ ኪሪያኪ ኢሜራ] ወይም

የመጀመሪያ ቀን በከተማና በገጠር የሚኖሩ ክርስቲያኖች በተለያዩ የአምልኮ ስፍራዎች እንደሚሰባሰቡ ገልጾ፥ "[በቀረበው] ኅብስትና ወይን ላይ መሪው የቻለውን ያህል ጸሎትንና ምስጋናን ያቀርባል፤ ሕዝቡም አሜን በማለት ይመልሳሉ"[88] ሲል ጽፎልናል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በአንደኛውና ሁለተኛው ምእት ዓመታት፥ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ መጻሕፍት ስላልነበሩ የክርስቲያኖች የማኅበር ጸሎትን የሚመሩት ኤጲስ ቆጶሳት፥ ነቢያትና ወንጌላውያን (ሰባክያን) በቃላቸው ይጸልዩ እንደነበር ነው። በሂደት ግን፥ በየዘመናቱ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ብቅ ማለት ጀመሩ። በ3ኛውና በ4ኛው ምእት ዓመታት እንደተደረሱ የሚነገርላቸውና በአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነትን ያገኙ፥ አኰቴተ ቍርባን ተብለው ሊጠሩ የማይችሉ ከፊል የቅዳሴ ድርሰቶች እና ሙሉ ቅዳሴያት አሉ። በመቀጠል፥ እነዚህን ጸሎታተ ቍርባን እንደተደረሱባቸው ዘመናት ቅደም ተከተል በአጭሩ እንመለከታለን።

## ፩. የአንደኛው እና ሁለተኛው ምእት ዓመታት መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

### ዲዳኬ፡ ትምህርተ ሐዋርያት

ይህ የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ ዲዳኬ የሚለውን ስያሜ ያገኘው፥ ርእሱ ላይ ካለው የመጀመሪያ ቃል "*ዲዳኺ*"[89] ነው። ይህም ሥልጠና ወይም ትምህርት ማለት ሲሆን፥ ርእሱ፡- "የ12ቱ ሐዋርያት ትምህርት" የሚል ትርጉም አለው። ነገር ግን፥ 12ቱ የጌታ ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች መመሪያ እንዲሆናቸው ጽፈው ሰጧቸው ማለት አይደለም። በጥንት ዘመን የተጻፉ ጽሑፎችን ከሐዋርያት ጋር ማገናኘት ወይም እነርሱ እንደደረሱት አድርጎ ማቅረብ የተለመደ ነው። ለምሳሌ፥ ከዘመነ ሐዋርያት በኋላ (በ3ኛውና 4ኛው ምእት ዓመታት) የተደረሱ ሐዋርያዊ ትውፊት[90] እና ሐዋርያዊ ሕግጋት[91] የተባሉ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት

"የጌታ ቀን" ትባላለች። See "Notes to the First Apology," *St. Justin Martyr: The First and Second Apologies,* p. 183.

[88] See *Ancient Christian Writers: St. Justin Martyr,* Apology I, 67, p. 71.

[89] Διδαχὴ.

[90] Apostolic Tradition.

አሉ። እነዚህን ሁሉ ሐዋርያት እንዳልጻፏቸው ግልጽ ነው፤ ነገር ግን ጥንታዊነታቸውን ለማሳየትና የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን ለመግለጽ ከላይ የተጠቀሱት ስያሜዎች ተሰጥቷቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ፥ በተለምዶ በ3ኛው ምእት ዓመት የነበረው ቅዱስ ሄጶሊጦስ (አቡሊዲስ) ዘሮሜ[92] እንዳዘጋጀው ከሚነገርለት ሐዋርያዊ ትውፊት የተወሰደው አኰቴተ ቍርባን፥ በቤተ ክርስቲያናችን "ቅዳሴ ሐዋርያት" ተብሎ ይጠራል።

ዲዳኬን ማን እንደደረሰው ባይታወቅም፥ ይዘቱን በጥልቀት ያጠኑ ምሁራን በ60 ዓ.እ. አካባቢ እንደተደረሰ ገምተዋል።[93] ይህ የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ ወደ ግእዝ ስለመተርጎሙ ምንም ዓይነት መረጃ አላገኘሁም። ነገር ግን፥ 7ኛው የሐዋርያዊ ሕግጋት መጽሐፍ ከዲዳኬ የተወሰዱ ጸሎታትን በብዛት ስለያዘና[94] ወደ ግእዝ የተተረጐመው መጽሐፈ ዲድስቅልያ የሐዋርያዊ ሕግጋት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ስለሆነ፥ ሁለቱን መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ብናነጻጽር ተወራራሽነት ያላቸው ንባባት አይጠፉም። በተጨማሪም ከዲዳኬ የተወሰዱ አንዳንድ ጥቅሶች በመጽሐፈ ቅዳሴና በመጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ፥ ዲዳኬ 9፥4[95] በቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ[96] እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ[97] ውስጥ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። የቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ

---

[91] Apostolic Constitutions.

[92] የሄጶሊጦስ (አቡሊዲስ) ዘሮሜ (St. Hippolytus of Rome) ማንነት እስካሁን ድረስ ምሁራንን ያከራክራል። አንዳንዶቹ በሰማዕትነት የሞተ ቅዱስ ነው ሲሉ፥ ሌሎቹ ደግሞ በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ላይ የሮማ ፓፓ በመሆን ተሹሞ እንደነበር ይናገራሉ። Apostolic Tradition የሚባለው የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ በዚህ አባት እንደተደረሰ ይታመን የነበረ ቢሆንም፥ በቅርብ ጊዜ የተደረጉ የምሁራን ጥናቶች፥ ድርሰቱ የእርሱ እንዳልሆነና ስማቸውን ያልገለጹ ሰዎች ያዘጋጁትን ጽሑፍ በእርሱ ስም እንደሰየሙት አረጋግጠዋል። ለምሳሌ Mazza, *The Origins of the Eucharistic Prayer,* p. 98; Paul Bradshaw, *Eucharistic Origins* (Oxford: Oxford University Press, 2004) p. 19 ይመልከቱ።

[93] Jasper and Cuming, *Eucharistic Prayers,* p. 20.

[94] ዝኒ ከማሁ፡ p. 100.

[95] የእንግሊዝኛው ትርጉም እንዲህ ይላል፦ "Just as this broken [loaf] was scattered over the hills [as grain], and, having been gathered together, became one; in like fashion, may your church be gathered together from the ends of the earth into your kingdom." Milavec, *Didache* 9:4, p. 23.

[96] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 68፣ ገጽ 402 ።

[97] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 27፣ ገጽ 431-432።

ነገድጓድ ንባብ፡- “ይህች ኅብስት በተራራና በኮረብታ፥ በበረሓና በቈላ መካከል የተበተነች ስትሆን  እንደ ተሰበሰበች፥ ተሰብስባም አንዲት ፍጽምት ኅብስት እንደ ሆነች፥ እንዲሁ እኛንም በመለኮትህ ከክፉ የኃጢአት አሳብ ሁሉ ለይተህ በፍጹም ሃይማኖትህ ሰብስበን”[98] ይላል። በተጨማሪ፥ እንደ አይሁድ ሰኞና ኀሙስ ሳይሆን፥ ክርስቲያኖች ረቡዕና ዓርብ መጾም እንዳለባቸው የሚያዘው የዲዳኬ 8ኛ ምዕራፍ ቍጥር 1፥ የትእዛዝ ሲኖዶስ አንቀጽ 50 ላይ ተጠቅሷል፡- “ጾምክሙ ኢይኩን ከመ መደልዋን እስመ እሙንቱ ይጸውሙ በሰኑየ ሰንበት ወበኀሙስ። ወአንትሙሰ ጹሙ ረቡዓ ወዓርበ[99] - ጾማችሁ እንደ ግብዞች አይሁን፤ እነርሱ በክርስቲያኖች ሰንበት ማግስት (ሰኞ) እና ኀሙስ ይጾማሉና። እናንተ ግን፥ ረቡዕ እና ዓርብ ጹሙ።”[100]

የዲዳኬ 9ኛ፥ 10ኛ እና 14ኛ ምዕራፎች የክርስቲያኖች ፍቅርና ኅብረት ስለሚገለጽበት ማዕድ (*አጋፔ*) እና ስለ ቅዱስ ቍርባን መጠነኛ ግንዛቤን የሚሰጡ የምስጋና ጸሎቶችን ይዟል። የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ለአጋፔ ማዕድ ወይም ለቅዱስ ቍርባን አገልግሎት የተዘጋጁ ስለመሆናቸው በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፤ እነዚህን ምዕራፎች በጥልቀት ያጠኑ ምሁራን የተለያዩ አመለካከቶችን ሰንዝረዋል።[101] በሁለቱ ምዕራፎች ውስጥ ተመሳሳይ የምስጋና አቀራረብ የሚታይ ሲሆን፥ ከአይሁድ የጸሎት መጻሕፍት እንደተወሰዱ ሁሉም ምሁራን ይስማማሉ። ለምሳሌ፥ የዲዳኬ 9ኛው ምዕራፍ በጽዋው ላይ የሚደረገውን ጸሎት እንዲህ በማለት ይጀምራል፡- “አባታችን ሆይ፥ በልጅህ በኢየሱስ ስለገለጽከው የባሪያህ የዳዊት

---

[98] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 91፣ ገጽ 176።

[99] *The Statutes of the Apostles or Canones Ecclesiastici*, trans. G. Horner (London: Williams and Norgate, 1904) p. 55.

[100] የእንግሊዝኛው ትርጒም እንዲህ ይላል፡- “And let your fasts not stand with the hypocrites, for they fast on the second and on the fifth [day] of the week; you fast, on the other hand, during the fourth and during the [Sabbath] preparation [day].” See Milavec, *Didache* 8:1, p. 21.

[101] ለምሳሌ በ*Didache* Ch. 9 እና 10 ላይ Prof. Paul F. Bradshaw የተለያዩ ምሁራን አስተያየቶችን ጠቅሰው ያቀረቡትን ገላጻ *Eucharistic Origins* በሚለው መጽሐፋቸው ከገጽ 26-32 ላይ ይመልከቱ።

ቅዱስ የወይን ግንድ እናመሰግንሃለን፤ ለአንተ ለዘላለም ክብር ይሁን።”[102] ሁለተኛው ክፍልና በኅብስቱ ላይ የሚደረገው ጸሎት ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለተገለጸው ሕይወትና እውቀት ለእግዚአብሔር አብ ምስጋና ሲያቀርብ፥[103] የምዕራፉ ሦስተኛ ክፍል ደግሞ በዓለም ላይ የተበተነችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር እንድትሰበሰብ ይለምናል። ይህ ምዕራፍ ከላይ እንደተመለከትናቸው የአይሁድ የማዕድ ቡራኬያት ሦስት ክፍሎችን መያዙ፥ ከኅብስቱ በፊት ጽዋው መባረኩ፥ ሕዝበ እስራኤልን የሚያመለክተው “የወይን ግንድ” የሚለው ቃል በጸሎቱ ውስጥ መጠቀሱና ስለ እውቀት እግዚአብሔርን ማመስገኑ የጸሎቱ ምንጭ አይሁዳዊ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።[104]

የዲዳኬ 10ኛው ምዕራፍ፥ እንደ 9ኛው ሦስት ክፍሎች አሉት። ነገር ግን፥ “የፍቅር ማዕዱን ከመመገብ በኋላ እንዲህ ብለህ አኰቴት አቅርብ”[105] ብሎ ስለሚጀምር 9ኛው ምዕራፍ የአጋፔ ጸሎት፥ 10ኛው ደግሞ የቍርባን ምስጋና እንደሆነ ይጠቁማል። በመጀመሪያው ክፍል፥ በአንድያ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር አብ “በልባችን ላይ ስላሳደረው ቅዱስ ስሙ፤ ስለተገለጸልን እውቀት፥ እምነትና ዘላለማዊ ሕይወት” ምስጋና ያቀርባል።[106] በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለቅዱስ ስሙ፥ ሁሉን ነገር ፈጥሮ ለሰው ዘር ሥጋዊና መንፈሳዊ ምግብን በመስጠቱ ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ያመሰግናል። በሦስተኛው ክፍል፥ ስለ አንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሚከተለው ጸሎት ቀርቧል፦

---

102 “*Didache*, 9:1-4,” quoted in Hieromonk Gregorios, *The Divine Liturgy*, pp. 5 & 6. የMilavec ትርጒም “through Jesus your servant” ይላል - Milavec, *Didache* 9፡2, p. 23.

103 Milavec, *Didache* 9፡3, p. 23.

104 Jasper and Cuming, *Eucharistic Prayers,* p. 21.

105 Milavec, *Didache* 10፡1, p. 25. “አኰቴት አቅርብ” የሚል ትርጒም የሰጠሁት εὐχαριστήσατε [*evcharistisate*] የሚለውን የግሪክ ግስ ነው። ይህ ቃል ማንኛውንም ዓይነት ምስጋና ሳይሆን፥ በተለይ የቍርባን ምስጋናን (አኰቴተ ቍርባን) ማቅረብን ያመለክታል። በእንግሊዝኛ፥ ቅዱስ ቍርባን “Holy Eucharist” የሚለውን ስያሜ ያገኘው ይህን የግሪክ ቃል መሠረት በማድረግ ነው።

106 Milavec, *Didache* 10፡2, p. 25.

ጌታ ሆይ፥ ቤተ ክርስቲያንህን አስባት፤ ከክፉ ሁሉ ታድናት ዘንድ፥ በፍቅርህ ፍጹም ታደርጋት ዘንድ፥ ከአራቱ ነፋሳት [ለይተህና] የተቀደሰች አድርገህ ለእርሷ ወዳዘጋጀህላት ወደ መንግሥትህ ትሰበስባት ዘንድ። ኃይልና ክብር የአንተ ነውና፥ ለዘላለሙ።[107]

ይህ ምዕራፍ የተቋጨው የጌታን ዳግም ምጽአት በሚያመለክት አገላለጽ ነው። በምድር ያሉ ክርስቲያኖች ሰማያዊ ማዕድ የሆነውን ቅዱስ ቍርባንን ተቀብለው፥ ድል የነሡና በሰማያት ያሉ የጻድቃን ነፍሳትን (ዕብ. 12፥24) ይቀላቀሉ ዘንድ[108]፦ "[የእግዚአብሔር መንግሥት] ጸጋ ሆይ ና! ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ! ቅዱስ የሆነ ይምጣ (ይቀበል)፤ ያልሆነ ግን [ንስሐ ይግባ]።[109] *ማራናታ*[110] (ጌታ ሆይ ና)፥ አሜን።"[111]

የዲዳኬ 14ኛ ምዕራፍ በጌታ ቀን "እንጀራ ለመቍረስ" (የሐዋ. 20፡7) እና ለቍርባን ምስጋና ክርስቲያኖች ሲሰባሰቡ በንጹሕ ሕሊና ሆነው መሥዋዕታቸውን ማቅረብ እንዳለባቸው ይናገራል። ዲዳኬ 14፡1 "መሥዋዕታችሁ ንጹሕ ይሆን ዘንድ አስቀድማችሁ ውድቀታችሁን ተናዘዙ" ይላል።[112] ተመሳሳይ ትእዛዝ ዲዳኬ 4፡14 ላይ አለ፤ በኃጢአት የወደቁ ክርስቲያኖች ንስሐ ሳይገቡ "በመጥፎ ሕሊና" ለጸሎት መቆም እንደማይገባቸው ይናገራል።[113] የዲዳኬ 14ኛው ምዕራፍ በመጀመሪያው ምእት ዓመት ክርስቲያኖች "የጌታ ቀን" (ራእ. 1፥10) ተብላ በምትጠራው በዕለተ

---

[107] ዝኒ ከማሁ፡ *Didache* 10፡5, p. 25 (ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ)፡፡

[108] Bradshaw, *Eucharistic Origins,* p. 37.

[109] ግሪኩ የተጠቀመው "*metaniote*" የሚል ግስ ነው – Milavec, *Didache* 10:6, p.24. ይህ ቃል ከልብ መመለስን፥ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣትንና ንስሐ መግባትን ያመለክታል።

[110]*Maran 'athâ'* - ማራን፡አታ (Aramaic: אתא מרן) - በዚህ መልኩ ከተጻፈ "ጌታችን መጥቷል" የሚል ትርጉም አለው። *Maranâ thâ'* - ማራናታ (Aramaic: מרנא תא) ከሆነ ደግሞ "ጌታ ሆይ ና" ማለት ነው። ሁለቱንም ትርጉሞች በመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን። 1 ቆሮ. 16፥22 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን" ካለ በኋላ፥ "*Maran 'athâ'* " (ጌታችን መጥቷል) የሚለውን ቃል የእምነት መግለጫ አድርጎ ይጠቀምበታል። በራእ. 22፡20 ላይ ግን ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ "*Maranâ thâ'* የሚለውን ቃል ስለመረጠ፥ "ጌታ ሆይ ና" ተብሎ ተተርጉሟል።

[111] Milavec, *Didache* 10፡6, p. 25.

[112] ዝኒ ከማሁ፡ *Didache* 14፡1, p. 35.

[113] ዝኒ ከማሁ፡ *Didache* 4፡14, p. 15.

እሑድ ይሰባሰቡ እንደነበር መረጃ ከሰጡን ሰነዶች መካከል እጅግ ጥንታዊ ሲሆን፥ ቅዱስ ቍርባንን "መሥዋዕት" ብሎ በመጥራትም የመጀመሪያው ሆኗል። [114] እንዲሁም፥ ክርስቲያናዊ አምልኮ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ መሥዋዕት መሆኑን ለማስገንዘብ ቍጥር 3 ላይ ትንቢተ ሚልክያስ 1፥ 11ን[115] ይጠቅሳል። ባጠቃላይ ዲዳኬ በመጀመሪያው ምእት ዓመት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስለነበረው አምልኮ መጠነኛ ፍንጭ የሚሰጥ መጽሐፈ ሥርዓት ነው።

## የሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ (+ 165 ዓ.እ.) ምስክርነት

ከላይ እንደገለጽኩት፥ ከአሕዛብ በኩል በክርስቲያኖች ላይ ይሰነዘሩ የነበሩ ክሶችን የሮማ ቄሣሮች በቸልተኝነት ስላልተመለከቷቸው ለክሶቹ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነበር። ስለሆነም በሁለተኛው ምእት ዓመት የአሕዛብን ክሶች ተቃውመውና የክርስትናን አምልኮ ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር ደግፈው መልስ የሚሰጡ የእምነት ጠበቆች (ዐቃብያነ እምነት) ተነሡ። ከእነዚህ ጠበቆች መካከል አንዱ፥ በ165 ዓ.እ. አካባቢ በማርቆስ አውሬሊየስ ዘመነ መንግሥት በሰማዕትነት ያረፈው ቅዱስ ዮስጢኖስ ነበር።[116] ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ ሰማርያ ውስጥ ተወልዶ እንዳደገና በ130 ዓ.እ. የክርስትናን እምነት እንደተቀበለ ይነገርለታል፡፡ [117] የግሪኮችን ፍልስፍናንም ስለተማረ በጻፋቸው እምነትን የመጠበቅ (ዕቅበተ እምነት) ጽሑፎች፥ የክርስትና እምነት በፍልስፍና ትምህርት ትልቅ ቦታ ያላቸውን አመክንዮ[118] እና እውነትን የማግኘት ጥረት ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሳቸው ለማሳየት ሞክሯል።[119] ኤፌሶን ውስጥ በ135 ዓ.እ. የጻፈውና ትራይፎ ከተባለ አይሁዳዊ ጋር ያደረገው ውይይት[120] የክርስቲያኖች መሥዋዕት (ቅዱስ ቍርባን) የእንስሳትን ደም በማፍሰስ ከሚደረገው የአይሁድ መሥዋዕት እንደሚበልጥ በግልጽ ያስረዳል። ለምሳሌ፥

---

[114] Bradshaw, *Eucharistic Origins,* p. 41.

[115] "ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፥ ንጹሕም ቍርባን ያቀርባሉ"።

[116] "Introduction," *St. Justin Martyr: The First and Second Apologies,* ገጽ 3 ይመልከቱ፡፡

[117] Jasper and Cuming, *Eucharistic Prayers,* p. 25.

[118] Reasoning.

[119] See "Introduction," *St. Justin Martyr: The First and Second Apologies,* p. 3.

[120] Dialogue with Trypho the Jew.

በ41ኛው የውይይቱ ምዕራፍ፥ በኦሪት ዘሌዋውያን 14፥10 የተጠቀሰውና ለምጻሙ ሰው ከለምጹ ይነጻ ዘንድ ወደ ካህኑ የሚወስደው "ከመልካም ዱቄት" የተዘጋጀው "የእህል ቍርባን" ክርስቲያኖች የክርስቶስን ሕማምና መከራ እያሰቡ የሚያቀርቡት የሐዲስ ኪዳኑ ኅብስተ ቍርባን ምሳሌ እንደሆነ ይጽፋል።[121] እንዲሁም ዲዳኬ ውስጥ የተጠቀሰውን የነቢዩ ሚልክያስን ትንቢት መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ዘግቧል፦

> አስቀድሜ እንዳልኩት፥ እግዚአብሔር ከ12ቱ ነቢያት አንዱ በሆነው በሚልክያስ አፍ በዚያን ዘመን በእናንተ [በአይሁድ] ይቀርብ ስለነበረው መሥዋዕት እንዲህ ሲል ተናገረ፦ "በእናንተ ደስ አይለኝም፥ ቍርባንንም ከእጃችሁ አልቀበልም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፥ ንጹሕም ቍርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። እናንተ ግን . . . አስነቀፋችሁት" [ት. ሚል. 1፥10-12]። ስለዚህ፥ በማንኛውም ቦታ ለእርሱ መሥዋዕት፥ ይኸውም ኅብስተ ቍርባንን እና ጽዋዓ አኰቴትን ስለሚያቀርቡለት አሕዛብ (ስለእኛ) ተናገረ። በዚህም እናንተ [አይሁድ] ስሙን እንዳስነቀፋችሁ፥ እኛ ግን እንዳከበርነው በእርግጠኝነት አስረዳ።[122]

ቅዱስ ዮስጢኖስ ሰማዕት፥ በ150 ዓ.እ. የጻፋቸው ሁለት የዕቅበተ እምነት ጽሑፎች ክርስቲያኖች ላይ ይቀርቡ ለነበሩ የሐሰት ውንጀላዎች በዝርዝር መልስ ይሰጣሉ። ክርስቲያኖች "የዓለማት ፈጣሪ"[123] የሆነውን አምላክ ስለሚያመልኩ በእምነተ አልባነት በፍጹም መከሰስ እንደሌለባቸው፤ ከወንጀል የራቁ ስለሆኑም ምግባረ ብልሹነት እንደማይመለከታቸውና የሰማያዊው መንግሥት ዜጎች በመሆናቸው ለሮማ ቄሣሮች መንግሥት አለመታመን ለክርስቲያኖች ጥያቄ ሊሆን እንደማይችል አስረድቷል። በክርስቲያኖች ሥርዓተ አምልኮ ላይ ለተነሣው ጥያቄም፥ በመጀመሪያው የዕቅበተ እምነት መጽሐፉ ከምዕራፍ 61-67 ዝርዝር መረጃዎችን ጽፎልናል። እነዚህ ምዕራፎች ዮስጢኖስ በኖረበት በሁለተኛው ምእት ዓመት፥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጥምቀትና ቍርባን ምን ይመስል እንደነበር ፍንጭ

[121] "Dialogue with Trypho," *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* Chap. 41, p. 215.

[122] ዝኒ ከማሁ። (ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ)፡፡

[123] የእንግሊዝኛው ትርጉም "Maker of this Universe" ስለሚል "ገባሬ ሰማያት ወምድር" ወይም "ፈጣሬ ዓለማት" ብሎም መተርጎም ይቻላል። See "The First Apology, 13:1" *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* p. 30.

የሚሰጡ ናቸው። የዚህ መጽሐፍ 65ኛው ምዕራፍ፡- "*ያመነውንና በሰጠነው መመሪያ የተስማማውን ሰው ካጠብነው [ካጠመቅነው] በኋላ፥ ወደተሰባሰቡ ወንድሞች እንወስደዋለን፤ ከዚያም 'ምሥጢረ ብርሃን'*[124] [ጥምቀት] *ከተቀበለው ጋር የጋራ ጸሎት እናቀርባለን*" በማለት ስለሚጀምር ከሥርዓተ ጥምቀት በኋላ የሚከናውን አኰቴተ ቊርባንን ያሳያል።[125] 67ኛው ምዕራፍ ግን በዕለተ እሑድ ይካሄድ የነበረውን ጉባኤ ቊርባን ይዘት በዝርዝር ያስረዳል። ከእነዚህ የዮስጢኖስ የምስክርነት ገለጻዎች በመነሣት፥ በዚያን ዘመን ክርስቲያኖች ጉባኤ ቊርባን ሲያደርጉ በቅደም ተከተል የሚከተሉትን ያከናውኑ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡-[126]

- ምንባባት (ከነቢያት ትንቢት ወይም ከሐዋርያት መልእክታት)
- በምንባባቱ ላይ አጭር ትምህርት በሥርዓተ ቊርባኑ መሪ
- የጋራ ጸሎቶች (ሁሉም እንደቆሙ)
- አምኃ ቅድሳት (በተቀደሰ አሳሳም እጅ መነሣሣት/ ሰላምታ መለዋወጥ)
- አግብኦተ ግብር:- ሕዝበ ክርስቲያኑ ያመጡትን ኅብስትና ወይን ዲያቆናቱ መርጠው ያቀርባሉ[127]
- ጸሎተ አኰቴት:- "*መሪው እንደቻሎታው መጥን [በቃሉ] ጸሎትንና ምስጋናን ያቀርባል*"[128]
- ሕዝቡ "አሜን" በማለት መስማማታቸውን ይገልጻሉ
- ተመጥዎ ቅዱስ ቊርባን (እያንዳንዱ ምእመን ቅዱስ ቊርባንን ይቀበላል)[129]
- ለቅዳሴ ላልመጡት ምእመናን፥ ዲያቆናት ቅዱስ ቊርባንን ይወስዱላቸዋል።[130]

---

[124] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፣* ገጽ 62. በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀት "illumination" ወይም አብርሆት ይባል ነበር፤ ዶ/ር ሀብተሚካኤል "ምሥጢረ ብርሃን" የሚል ስያሜ የሰጡት ለዚህ ነው።

[125] "The First Apology, 65:1" *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* p. 70.

[126] Jasper and Cuming, *Eucharistic Prayers,* p. 25-26.

[127] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፣* ገጽ. 64.

[128] "The First Apology, 67፡5" *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* p. 71.

[129] የእንግሊዝኛው ትርጉም፡- "distribution and partaking of the eucharistized elements to each" ይላል። ዝኒ ከማሁ፡ "The First Apology, 65:1" *The Ante-Nicene Fathers,* p. 70.

[130] ዝኒ ከማሁ።

## ቅዱስ ሄሬኔዎስ ተላዊሆሙ ለሐዋርያት (+ 202 ዓ.እ.)

በጥንታዊቷ ከተማ በሰምርኔስ[131] በ120 ዓ.እ. አካባቢ ተወልዶ ያደገው ቅዱስ ሄሬኔዎስ ከከተማዋ ጳጳስ (ከቅዱስ ፖሊካርፐ ዘሰምርኔስ)[132] ተምሯል። [133] እስካረፈበት እስከ 202 ዓ.እ. ድረስ ፈረንሳይ ውስጥ በነበረች ደቡባዊ ከተማ (ልዮን) በጵጵስና አገልግሏል። [134] በሁለተኛው ምእት ዓመት የአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ራስ ምታቶች የሆኑ ኖስቲኮች [135] የተለያዩ ኑፋቄያትን (የክህደት ትምህርቶችን) በማስተማር ሁከት ሲፈጥሩ፥ ቅዱስ ሄሬኔዎስ በአምስት ክፍሎች የተከፈለና ለኑፋቄያቱ ዝርዝር መልስ የሰጠ ጸረ ኑፋቄ (መድፍነ ኑፋቄ) መጽሐፍ ጻፈ።[136] እስካሁን ድረስ የዚህ አባት ድንቅ ሥራ ወደ አማርኛ አልተተረጐመም።

---

[131] ይህች ከተማ በዘመናችን ቱርክ (Turkey) ውስጥ የምትገኝ ስትሆን ስመ-ተፋልሶ ደርሶባት፥ "Izmir" በሚል ስያሜ ተጠርታለች። የከተማዋ ጥንታዊነት የሚታወቀው መንፈሳዊው ዮሐንስ በራእዩ ከጠቀሳቸው 7 አብያተ ክርስቲያን መካከል በመሆኗ ነው፤ የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ "Smyrna" የሚለውን፥ አማርኛው "ሰምርኔስ" በሚል ስም ይጠራዋል - ራእ. 2፥8ን ይመልከቱ።

[132] St. Polycarp of Smyrna.

[133] "Notes on Sources," *A New Eusebius: Documents Illustrative of the History of the Church to A.D. 337,* ed. J. Stevenson (London: SPCK, 1983) p.402.

[134] ስለሆነም በዓለም አቀፍ ደረጃ St. Irenaeus of Lyons በሚል ስያሜ ይታወቃል፡፡

[135] "Gnostics" (*ኖስቲክስ*) የሚለው ስያሜ የተሰጣቸው "*gnosis*" (*ኖሲስ*) ወይም "እውቀት" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ "መዳን በእውቀት ነው" የሚል ትምህርት ነበራቸው። እንደነርሱ አስተምህሮ፥ ለመዳን የሚያበቃው "እውቀት" የሚገለጸው ለተመረጡትና ለጥቂቶች (ለኖስቲኮች) ስለሆነ፥ ይህ "እውቀት" ያልተገለጸላቸው መሃይማን ለጥፋት የተዘጋጁ ናቸው። በተጨማሪም የሁለት አማልክትን (Dualism) ፍልስፍናን እያስተማሩ ከቍስ አካል (matter) ጋር የተያያዘው ግዙፉ ዓለምና ሥጋ በክፉው/ተወራጅ አምላክ (Demiurge) የተፈጠሩ ሲሆኑ፥ መንፈስ (spirit) ደግሞ በመልካሙ (ደጉ) አምላክ የተፈጠረች ናት ይሉ ነበር። ስለዚህ፥ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ "ክቡርና መኝታው ንጹሕ" (ዕብ. 13፥4) ያለውን ጋብቻን እንደ ርኵስ ነገር ከመጸየፍ ባሻገር፥ "ነፍስ በሥጋ እስር ቤት ውስጥ ትኖራለች" የሚል የተሳሳተ ትምህርት ነበራቸው። Apostolic Creed ወይም በኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ "አመክንዮ ዘሐዋርያት" ተብሎ በሚታወቀው የእምነት መግለጫ፡- "እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደ ሆነ የሚጣልም እንደሌለ እንናገራለን፤ የሥጋ ሕይወት የምትሆን ነፍስ ግን ንጽሕት ቅድስት ናት፤ እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደ ሆነ ልደትም ርኵሰት እንደሌለበት እንናገራለን" ተብሎ የተጻፈው የኖስቲኮችን ክህደት ለመቃወም እንደሆነ ግልጽ ነው። "አመክንዮ ዘሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ: 2000፣ ቍ. 39-40፣ ገጽ 95 ይመልከቱ።

[136] *Against Heresies* የተሰኘውን የቅዱስ ሄሬኔዎስን መድፍነ ኑፋቄ መጽሐፍ በማድነቅ፥ መድበሉን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመው መቅድም ያዘጋጁለት ምሁራን፡- "The work of Irenaeus *Against Heresies* is one of the most precious remains of early Christian antiquity" ብለዋል።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሄሬኔዎስ የሚታወቀው "ሃይማኖተ አበው" በተሰኘው የጥንታውያን አባቶች ሥራዎች መድበል ውስጥ በስሙ በሚገኘው አጭር የነገረ ክርስቶስ ጽሑፍ ብቻ ነው። የጽሑፉ መግቢያ፡- "ይቤ ሄሬኔዎስ ኤጲስ ቆጶስ ዘሀገረ ኤዶም ረድኦሙ ለሐዋርያት ወተላዊሆሙ - የሐዋርያት ደቀ መዝሙራቸውና ተከታያቸው፥ ኤዶም በምትባል አገር ኤጲስ ቆጶስነት የተሾመ ሄሬኔዎስ እንዲህ አለ"[137] ይላል። "የሐዋርያት ደቀ መዝሙር" የተባለው፥ ከላይ እንደገለጽኩት ከቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ የተማረው የቅዱስ ፖሊካርፕ ደቀ መዝሙር ስለነበረ ነው፤ "ኤጲስ ቆጶስ ዘሀገረ ኤዶም" የተባለበት ምክንያት ግን ግልጽ ባይሆንም፥ ልዮን የጥንቷ ሉግዱነም[138] ክፍለ ግዛት ዋና ከተማ ስለነበረች ሃይማኖተ አበውን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተረጐሙልን ሊቃውንት ከከተማው ይልቅ የክፍለ ግዛቱን ስም ስለመረጡና በስመ-ተፋልሶ ሉግዱነም የሚለው ኤዶም ስለተባለ ሊሆን ይችላል።

የቅዱስ ሄሬኔዎስ ጸረ ኑፋቄ መድበል ዋነኛው ዓላማ የኖስቲኮችን ኑፋቄያት አጋልጦ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት መከላከል በመሆኑ፥ ከላይ እንደተመለከትናቸው የቅዱስ ዮስጢኖስ ሰማዕት የዕቅበተ እምነት መጻሕፍት በሁለተኛው ምእት ዓመት የነበረውን የአኰቴተ ቊርባን ዝርዝር ዘገባ አይሰጠንም። ነገር ግን ቅዱስ ሄሬኔዎስ ከቤተ ክርስቲያን የእምነት ጠበቆች (ዐቃብያነ እምነት) መካከል አንዱና ዋነኛ እንደመሆኑ መጠን፥ በዝነኛው ሥራዎቹ ውስጥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስለ ቅዱስ ቊርባን የምታምነውን ትምህርተ ሃይማኖት እናገኛለን። ለምሳሌ፥ ጸረ ኑፋቄያት (መድፍነ ኑፋቄያት) በተሰኘው መጽሐፉ 4ኛ ክፍልና 17ኛ ምዕራፍ ውስጥ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት የመጀመሪያ ምርት (ቀዳምያት) የሆነውን ስንዴውንና ወይኑን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡ እንዳዘዛቸው ይጽፍና፥ ጌታ ይህንን ያዘዛቸው አስቀድሞ እርሱ ራሱ ከስንዴ የተዘጋጀውን ኅብስት አንሥቶ፡- "ይህ ሥጋዬ ነው"፥ እንደዚሁ የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆነውን ወይኑን የያዘውን ጽዋ፡- "ይህ ደሜ ነው" ብሎና የአዲሱ ኪዳን መሥዋዕት መሆኑን ተናግሮ እንደሰጣቸው በዝርዝር ያስረዳናል። በተጨማሪም፥

---

"Introductorty Note to Irenaeus Against Heresies," *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* p. 311.

[137] *ሃይማኖተ አበው* (3ኛ እትም)፡ "ዘሄሬኔዎስ"፥ ምዕራፍ 7፥ ክፍል 1፣ ገጽ 29.

[138] Lugdunum.

ከላይ እንደተመለከትነው፥ ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ ትንቢተ ሚልክያስ 1፡10-11ን ጠቅሶ የነቢዩ ትንቢት የክርስቲያኖችን *መሥዋዕት* እንደሚያመለክት ትራይፎ ለተባለው አይሁዳዊ እንደጻፈለት ሁሉ፥ ቅዱስ ሄሬኔዎስም ይህንኑ ጥቅስ በመጥቀስ "ከ12ቱ ነቢያት አንዱ የሆነው ሚልክያስ በትንቢት እንደተናገረው፥ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት የተቀበለችውን የአዲስ ኪዳን *መሥዋዕት* በዓለሙ ዳርቻ ሁሉ ትሠዋለች (*ታቀርባለች*)" ሲል ጽፏል።[139]

በሁለተኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ ጸረ ኑፋቄያት (መድፍነ ኑፋቄያት) በሆነው ድንቅ *ሥራው* ውስጥ ሄሬኔዎስ ካነሣቸው የተለያዩ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርቶች መካከል፥ የሥርዓተ አምልኮ ሊቃውንት እንደ መመሪያ የሚጠቀሙበት ፅንሰ-አሳብ ይገኝበታል። ኦርቶዶክሳዊው ትምህርተ ሃይማኖት የተመሠረተው በቅዱስ ቍርባን ላይ ባለን እምነት መሆኑን በአጽንኦት ሲገልጽ፡- "የምናምነው [በትምህርተ] ቍርባን ላይ የተመሠረተ ነው፤ ቅዱስ ቍርባን ደግሞ እምነታችንን ያጸናዋል" ይላል።[140] የቅዱስ ሄሬኔዎስንና የሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አባቶችን አስተምህሮ መሠረት በማድረግ በዓለም ያለችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ቅዱስ ቍርባን የሚከብርበትን የቅዳሴ አገልግሎት የሕልውናዋ መሠረት አድርጋዋለች። በቅዳሴ አምልኮዋን የማትገልጽ ቤተ ክርስቲያን፥ በፍጹም ኦርቶዶክሳዊት ልትባል አትችልም። ለኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ቅዳሴ የልምድ *ሥራ* ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት በዚህ ምድር የምትለማመድበት ሰማያዊ አምልኮዋ ነው። ስለዚህ መሠረታዊ ትምህርቶችዋ በሙሉ በመጽሐፈ ቅዳሴዋ ይገኛል። ከቅዱስ ሄሬኔዎስ የተማሩ የሥርዓተ አምልኮ ሊቃውንትም በላቲን ቋንቋ ፡- "*ሌክስ ኦራንዲ፥ ሌክስ ክሪዴንዲ*"[141] ብለዋል፤ ይህም የምንጸልየውን እናምነዋለን፥

[139] "Against Heresies, Book IV, Chap. 17, no. 5," *The Ante-Nicene Fathers: The Writings of the Fathers down to A.D. 325,* p.484.

[140] ዝኒ ከማሁ፥ "Against Heresies," Book IV, Chap. 18, no. 5, p. 486.

[141] "*lex orandi - lex credendi*" ወይም "*legem credendi lex statuat supplicandi*." Kevin W. Irwin, "The Sacramentality of Creation and the Role of Creation in Liturgy and Sacraments," *And God Saw That It Was Good*: *Catholic Theology and the Environment*, ed. Drew Christiansen and Walter Grazer (Washington, D.C. : United States Catholic Conference, 1996) ገጽ 10 ይመልከቱ፡፡

የምናምነው የምንጸልየው ነው ማለት ሲሆን፥ የቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረቱ ሰማያዊው ማዕድ (ቅዱስ ቊርባን) የሚከብርበት ጸሎተ ቅዳሴዋ እንደሆነ ያስረዳል።

## ፪. የ3ኛው ምእት ዓመት ሥርዓተ ቊርባን ጠቋሚ ምንጮች

በመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት የነበረውን የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ቊርባን ሥርዓት "በእርግጠኝነት ይህን ይመስል ነበር" ብሎ ለመናገር እንደማይቻል ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይስማማሉ።[142] ምሁራኑ የመረጡት በተለያዩ ጥንታውያን ቋንቋዎች (ግሪክ፥ ቅብጥ/ኮፕቲክ፥ ሱርስት እና ግእዝ) የተጻፉ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮችን ፥ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መልእክታትንና የሮማ ግዛት አገረ ገዢዎች ለቄሣሮቻቸው የጻፏቸውን ጦማሮች በማጥናት ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት ይካሄድ ለነበረው የአምልኮ ሥርዓት መጠነኛ ሥዕላዊ መግለጫ መስጠት ነው። ነገር ግን የእነዚህ ጥናቶች ውጤት ፍጹም ስላልሆነ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥናቱ ይቀጥላል።

ከላይ እንደተመለከትነው፥ የቅዳሴ አገልግሎት *አጋፔ* ተብሎ ከሚታወቀው የፍቅር ማዕድ ተለይቶ እሑድ ጠዋት መቼ መከበር እንደጀመረ አይታወቅም። አንዳንድ ምሁራን "በመጀመሪያው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ የቅዱስ ቊርባን አገልግሎት (ቅዳሴ) እና *አጋፔ* አንድ ላይ መካሄዱ ቀርቶ ቅዳሴ በጠዋት መቀደስ ተጀመረ" የሚል መላምት ቢያስቀምጡም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ ዝነኛ ሊቃውንት ግን በዚህ አይስማሙም።[143] ለተቃውሟቸው የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች በጥንታውያን ምንጮች መረጃነት የተደገፉ ናቸው። ለምሳሌ፥ በሁለተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ (107 ዓ.እ.) ያረፈው ቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ለሰምርኔስ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ ቊርባን እና *አጋፔ* የሚሉትን

[142] ለምሳሌ Paul F. Bradshaw, "Redating the Apostolic Tradition: Some Preliminary Steps," *Rule of Prayer, Rule of Faith: Essays in Honor of Aidan Kavanagh, O.S.B.,* eds. Nathan Mitchell and John F. Baldovin (Collegeville, MN: The Liturgical Press, 1996) ገጽ 5 ይመልከቱ፡፡

[143] Paul F. Bradshaw and Maxwell E. Johnson, *The Eucharistic Liturgies: Their Evolution and Interpretation* (London: SPCK, 2012) p. 25.

ቃላት አንድ ዓይነት መልእክት እንዲያስተላልፉ አድርጎ ይጽፍ ነበር።[144] ይህ የሚያሳየው በዘመነ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ሁለቱ አገልግሎቶች አንድ ላይ ይፈጸሙ እንደነበር ነው። በተመሳሳይ መልኩ፥ ካርቴጅ[145] ተብላ ትጠራ በነበረው የሮማ ግዛት ውስጥ ይኖር የነበረው የክርስትና እምነት ጠበቃው (ዐቃቤ እምነት) ጠርጡሊያኖስ ዘካርቴጅ[146] (+240 ዓ.እ.) በሁለተኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ በጻፈው ጽሑፍ፥ ክርስቲያኖች ከማንኛውም የወንጀል *ሥራ የራቀ የአምልኮ ሥርዓት* እንደነበራቸው ገልጾ፥ እንደ ቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ቅዱስ ቍርባን እና *አጋፔ* የሚሉትን ቃላት እያቀያየረ በተመሳሳይ መልኩ ጠቅሷቸዋል።[147]

የቅዱስ ቍርባን አገልግሎት ከፍቅሩ ማዕድ ተለይቶ እሑድ ጠዋት ይካሄድ እንደነበር በግልጽ የሚያሳዩት በ3ኛው ምእት ዓመት የተጻፉ መዛግብት ናቸው። ቅዱስ ቆጵርያኖስ ዘካርቴጅ[148] (+258 ዓ.እ.) ክርስቲያኖች ውኃን ከወይን ጋር ቀላቅለው ለቅዱስ ቍርባን አገልግሎት መጠቀም እንዳለባቸው በጻፈው መልእክት፥ ይህን የሚያደርጉት አምላካቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ኀሙስ ለደቀ መዛሙርቱ ያሳያቸውን ሥርዓተ ቍርባን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ያስረዳል። ነገር ግን፥ "ክርስቶስ ሥርዓተ ቍርባንን ለደቀ መዛሙርቱ ያሳያቸው ኀሙስ ማታ ሲሆን፥ እናንተ ለምን እሑድ ጠዋት ትቀድሳላችሁ?" የሚለውን ጥያቄ ሲመልስ፦ "የፋሲካውን በግ 'የእስራኤል ማኅበር ሲመሽ ይረዱት'" ተብሎ በኦሪት ዘጸአት 12፥6 ላይ እንደተጻፈ፥ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን በምሽት አደረገ፤ በምሽት (ፀሐይ በምትጠልቅበት ሰዓት) መሆኑም የብሉዩ መሥዋዕት ማለፉን

[144] "Epistle of Ignatius to the Smyrnaeans," *The Ante-Nicene Fathers,* Chap. VIII, pp. 89-90; Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p. 26.
[145] ይህ ቦታ በአሁኑ ጊዜ የሰሜን አፍሪካ አገር በሆነችው ቱኒሲያ ውስጥ ይገኛል።
[146] Tertullian of Carthage.
[147] See "Apoloteticum 39," quoted in Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* pp. 30-31.
[148] St. Cyprian of Carthage.

ያመልክታል። እኛ ግን የጌታን ትንሣኤ ለማክበር ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን [እሑድ] ጠዋት እንቀድሳለን"[149] ሲል መልሷል።

በ3ኛው ምእት ዓመት የቅዳሴው አገልግሎት ከአጋፔ ተለይቶ በእሑድ ጠዋት ከመካሄዱ ባሻገር፥ ለቅዳሴ አገልግሎት የተዘጋጁና አኰቴተ ቍርባን ተብሎ ለመጠራት የሚያስችላቸውን መሥፈርት የያዙ ጸሎታተ ቍርባን ብቅ ማለት ጀመሩ። እነዚህ ጥንታውያን ምንጮች የተደረሱበት ጊዜ በሊቃውንቱ ዘንድ አከራካሪ ቢሆንም፥ ከላይ ከተመለከትናቸው መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን (ለምሳሌ ዲዳኬ) እና የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ መጻሕፍት ጋር ያላቸው ተቀራራቢነት በ3ኛው ምእት ዓመት የተደረሱ እንደሆኑ ይጠቁማል። ከእነዚህ ጥንታውያንና ታሪካዊ መረጃዎች መካከል ሐዋርያዊ ትውፊት የሚል ስያሜ የሰጠሁት መጽሐፈ ሥርዓት በዋነኝነት ይጠቀሳል።

## ሐዋርያዊ ትውፊት

በግሪክ ቋንቋ *ሊፖሊቶስ*[150] ፥ በዐረብኛ ደግሞ *ባልዳስ* በሚሉ ስሞች የሚታወቅ የሮም ሰው በ3ኛው ምእት ዓመት ይኖር ነበር። እነዚህን ሁለት ስያሜዎች በመከተል የዚህን ሰው ሥራዎች ወደ ግእዝ የተረጎሙ ሊቃውንት፥ "ሄጶሊጦስ" ወይም "አቡሊዲስ" ዘሮሜ ብለው ይጠሩታል። ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የቀኖና እና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጽሑፎች ላይ አስደናቂ ጥናቶችን ያደረገው ጣልያናዊው ሊቅ አሌሳንድሮ ባውሲ፥ በግእዝ ሥነ ጽሑፍ፥ ሄጶሊጦስ ዘሮሜ "መጽሐፈ ምሥጢር ዘሄጶሊጦስ በእንተ ክርስቶስ ወበእንተ ሐሳዌ መሢሕ" በተባለው መጽሐፉ እንደሚታወቅ ነግሮናል። ነገር ግን፥ በሃይማኖተ አበው "አቡሊዲስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜ"[151] ተብሎ በስህተት የተጠቀሰው "ዮልዮስ" የተባለው የሮሜ ኤጲስ ቆጶስ እንጂ የተለያዩ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን እንደጻፈ የሚነገርለት ሄጶሊጦስ ወይም አቡሊዲስ ዘሮሜ እንዳልሆነ ያስረዳል፡፡[152] የዚህ ጣልያናዊ ምሁር

[149] See "*Ep.* 63.16.2-4" quoted in Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies*, p. 34.
[150] Ἱππόλυτος.
[151] *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 132.
[152] Alessandro Bausi, "Hippolytus," *EA*, Vol 3, p.36.

እርማት ትክክል እንደሆነ የሚጠቁም ፍንጭ እዚያው ሃይማኖተ አበው ውስጥ ይገኛል። በመጀመሪያው የሃይማኖተ አበው ክፍል፥ ድርሳናቸው የተዘገበላቸው ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ በሁለተኛው ክፍል ያስተላለፉት "ቃለ ግዝት" ሰፍሯል። በመጀመሪያው ክፍል ከተጠቀሱት አባቶች መካከል "አቡሊዲስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜ" አንዱ ሲሆን፥ የቃለ ግዝቱ ክፍል ላይ ግን ስሙ ተቀይሮ "ዮልዮስ ርእሰ ኤጲስ ቆጶሳት ዘሮሜ"[153] ይላል። ስለዚህ አሌሳንድሮ ባውሲ እንዳለው በመጀመሪያው ክፍል "አቡሊዲስ ዘሮሜ" የተባለው "ዮልዮስ ዘሮሜ" ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲሁም፥ ሄጶሊጦስ ወይም አቡሊዲስ ዘሮሜ ሃይማኖተ አበው ውስጥ ለእርሱ የተሰጠውን የነገረ ክርስቶስ ጽሑፍ እንደጻፈ የሚጠቁሙ መረጃዎች በሌሎች አብያተ ክርስቲያን ምንጮች ውስጥ ስለማይገኝ ከላይ የተሰጠውን እርማት ለመቀበል እንገደዳለን።

ቅዱስ ሄጶሊጦስ/አቡሊዲስ ዘሮሜ[154] በሚል ስም የሚታወቁ በ3ኛው ምእት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የተነሡ ሁለት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ነበሩ። አንደኛው ካህን እና ፓፓ ፖንቲያነስ[155] ከተባለው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፓፓ ጋር በ235 ዓ.እ. እንዳረፈ የሚነገርለት ነው፤ በቤተ ክርስቲያኒቱም ነሐሴ 13 ቀን ይታሰባል። ሁለተኛው ደግሞ፥ ቅዱስ ሄጶሊጦስ ጳጳስ ዘሮማውያን[156] በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ጳጳስ ነው። አንዳንድ ጸሐፍያን ይህ ጳጳስ በ253 ዓ.እ. በሰማዕትነት እንዳረፈና ነሐሴ 22 ቀን በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደሚዘከር ሲጽፉ፥[157] ታሪኩን ውስብስብ የሚያደርገው፥ ሌሎች ጸሐፊዎች ጳጳሱ በሰማዕትነት ያረፈው በ235 ዓ.እ. እንደሆነ መዘገባቸው ነው።[158] ይኸው ጳጳስ በመንበረ ጴጥሮስ ከ217-227 ዓ.እ. የተቀመጠው ፓፓ አውክዮስ ቀዳማዊ[159] ተቃዋሚ እንደነበር

---

[153] *ሃይማኖተ አበው*፣ ገጽ 575.
[154] St. Hippolytus of Rome.
[155] Pope Pontianus.
[156] St. Hippolytus, bishop of Portus Romanus.
[157] Geoffrey J. Cuming, *Hippolytus: A Text for Students with Introduction, Translation, Commentary and Notes,* Grove Liturgical Studies, Vol. 8 (Nottingham: Grove Books Limited, 1987) p. 5.
[158] Alessandro Bausi, "Hippolytus," *EA*, Vol 3, p.35.
[159] Pope Callistus I (First).

የሚዘግቡ መረጃዎች እንዳሉ ሁሉ፥[160] "ክሱ የሐሰትና የፈጠራ ነው" ብለው ያስተባበሉም አልጠፉም።[161] ከዐረብኛ የተተረጐመው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ስንክሳር፥ ሊቀ ጳጳሳት አውክዮስ ዘሮሜን ተክቶ የተሾመና በንጉሥ ከላድያኖስ[162] *ዘመነ መንግሥት* (253-268 ዓ.እ.) የካቲት 6 ቀን *ያረፈ*፥ "አቡሊዲስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሀገረ ሮሜ" የተባለ አባት እንደነበረ ይነግረናል። ስንክሳሩ በተጨማሪ፥ አቡሊዲስ ዘሮሜ የተለያዩ ድርሳናትን እንደጻፈና ስለሕገ ቤተ ክርስቲያን የሚያትቱ 38 ቀኖናዎችን እንደደረሰ ዘግቧል።[163] ይህ የሚያሳየን መጽሐፈ ስንክሳር፥ "አቡሊዲስ ዘሮሜ የተባለው አባት የፓፓው ተቃዋሚ ነበር" የሚለውን ክስ እንደማያውቀውና የሰማዕትነቱን ጊዜ አስመልክቶ ከተዘገቡት ሁለት አሻሚ ዓመታት (በ235 እና 253 ዓ.እ.) ከኋለኛው ጋር እንደሚስማማ ነው።

"ቅዱስ ሄጶሊጦስ/አቡሊዲስ ዘሮሜ ማን ነው?" የሚለውን ጥያቄ እስከ አሁን ድረስ በእርግጠኝነት ማወቅ አልተቻለም።[164] ይህ ስም በተለምዶ "በ3ኛው ምእት ዓመት ተደርሷል" ተብሎ ከሚታመን መጽሐፈ ሥርዓት ጋር የተያያዘበት ታሪካዊ ምክንያት ግን አለ። ሮም ውስጥ እ.አ.አ. በ1551 ተቆፍሮ የወጣ ሐውልት ሥር የተለያዩ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ስም ዝርዝር ተገኝቶ ነበር። ሐውልቱ ሥር ከተጠቀሱት መጻሕፍት መካከል በግሪኩ፡- *አፖስቶሊክ ፓራዶሲስ*[165] እና *ዲዳስካሊያ ቶን ሀጊዮን አፖስቶሎን*[166] የተሰኙ ይገኙበታል፡፡[167] የመጀመሪያው ሐረግ ሐዋርያዊ ትውፊት የሚል ትርጒም ያለው ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ከሐዋርያት ትምህርት ተውጣጥቶ የተዘጋጀውን መጽሐፈ ዲድስቅልያን የሚገልጽ

---

[160] Alessandro Bausi, "Hippolytus," *EA*, Vol 3, p.35.
[161] Cuming, *Hippolytus,* p. 5.
[162] Emperor Gallienus.
[163] መጽሐፈ ስንክሳር "ዘወርኀ የካቲት" (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ 1994 ዓ.ም.) ገጽ 740-741.
[164] በዚህ ምሥጢራዊ ሰው ማንነት ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች የተለያዩ ሊቃውንት ያደረጓቸውን አድካሚ ጥናቶች Enrico Mazza በዝርዝር አቅርቧቸዋል። Mazza, *Origins of the Eucharistic Prayer,* p.98, footnote 1.
[165] Apostolike Paradosis.
[166] Didascalia ton hagion apostolon.
[167] Cuming, *Hippolytus,* p. 4.

ርእስ ነው። በፍትሐ ነገሥት "ቀኖናተ አቡሊድስ" ተብለው አልፎ አልፎ የተጠቀሱትና በዐረብኛው ትርጒም በአንድ ላይ ተሰብስበው በ38 አንቀጾች የሚገኙት ቀኖናዎች "ቀኖናተ አቡሊዲስ"[168] በሚል ስያሜ ስለሚታወቁ፥ የሮሙ ሐውልት ሥር ስማቸው የተጠቀሱት ጽሑፎች ሁሉ በተለምዶ የምሥጢረኛው "ሄጶሊጦስ/አቡሊዲስ ዘሮሜ" ሥራዎች እንደሆኑ ይነገር ነበር።[169] በ1848 ዓ.እ. በብራና የተገኘ መጽሐፈ ሥርዓት ከቅብጥ (ኮፕቲክ) ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጐም "ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዘግብፅ"[170] የሚል ርእስ ተሰጠው።[171] ይህን ትርጒም ተከትለው ጥናት ያጠኑ ምሁራን፥ የተተረጐመው መጽሐፈ ሥርዓት ሐዋርያዊ ትውፊት[172] በሚል ስያሜ የሮሙ ሐውልት ሥር የተጠቀሰውና ደራሲውም (ቅዱስ ሄጶሊጦስ ዘሮሜ) እንደሆነ ለማረጋገጥ ሞከሩ።[173]

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተወሰኑ ምሁራን ይህን መላምት አምነው ተቀብለው ነበር።[174] በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች ግን ሐዋርያዊ ትውፊት የተሰኘው መጽሐፈ ሥርዓት፥ ሄጶሊጦስ ዘሮሜ እንደደረሰው ተደርጎ የሚነገረው ስሕተት መሆኑን በእርግጠኝነት ማስረዳት ችለዋል።[175] ሐዋርያዊ ትውፊት በውስጡ የያዛቸውን አኰቴተ ቍርባን፥ ሥርዓተ ጥምቀት እና ጸሎታተ ሢመት በጥልቀት በማጥናትም፥ በተለምዶ በ215 ዓ.እ. እንደተደረሰ ተደርጎ ይነገር የነበረውን መላምት ጥያቄ ውስጥ ከትተውታል።[176] ነገር ግን እነዚሁ ጥናቶች ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያለው አኰቴተ ቍርባን በአንደኛውና በሁለተኛው ምእት ዓመት ከነበሩ የቅዱስ ቍርባን ማክበሪያ ጸሎታት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው አልካዱም። ነገር ግን በ4ኛው ምእት

[168] Canons of Hippolytus.
[169] Alessandro Bausi, "Hippolytus," *EA*, Vol 3, p.36.
[170] The Egyptian Church Order.
[171] Cuming, *Hippolytus,* p. 3.
[172] ወይም በእንግሊዝኛ፡- Apostolic Tradition.
[173] ለምሳሌ ይህን ጥናታዊ መጽሐፍ ይመልከቱ፡- R. Hugh Connolly, *The So-called Egyptian Church Order and Derived Documents* (Cambridge: Cambridge University Press, 1916).
[174] Cuming, *Hippolytus,* p. 3.
[175] Bradshaw, *Eucharistic Origins,* p. 19.
[176] Bradshaw, "Redating the *Apostolic Tradition*," p. 3-17.

ዓመት የተደረሱ ቅዳሴያት አካል የሆኑ የአኰቴተ ቍርባን ክፍሎች[177] ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ስለሚገኙ "በ215 ዓ.እ. ተደረሰ" የሚለውን ግምት ለመቀበል እንደተቸገሩም ጠቁመዋል። [178] በአንጻሩ ደግሞ፥ ይህ መጽሐፈ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን (ሐዋርያዊ ትውፊት) በ4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመታት እንደተዘጋጁ ለሚነገርላቸው መጻሕፍተ ሥርዓት (ለምሳሌ፥ ሐዋርያዊ ሕግጋት እና መጽሐፈ ኪዳን) መሠረት እንደሆነ በጥናቶቻቸው ያረጋገጡ ሊቃውንት፥ በአብዛኞች ዘንድ እንደሚታመነው የ3ኛው ምእት ዓመት ሥራ ነው የሚለውን አሳብ ደግፈዋል።[179]

ሐዋርያዊ ትውፊት ሁለት ዓይነት የቅዳሴ አገልግሎትን ይዟል። የመጀመሪያው ንኡሰ ክርስቲያን ከተጠመቁ በኋላ የሚከናወን ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ሥርዓተ ጥምቀት በሌለበት ቀን የሚፈጸም ቅዱስ ቍርባንን የማክበር አገልግሎት ነው። ሁለቱንም አገልግሎቶች አጣምረን የሚከተለውን ቅደም ተከተል እናገኛለን፡-[180]

- የመግቢያ ጸሎታት
- አምኃ ቅድሳት
- አግብኦተ ግብር[181]

---

[177] ለምሳሌ፥ ካህኑ መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና ወይኑ ላይ ወርዶ የጌታችን ሥጋና ደም ወደመሆን ይቀይረው ዘንድ የሚጠይቅበትና *epiclesis* ተብሎ የሚታወቀው።

[178] Bradshaw, "Redating the *Apostolic Tradition*," p. 8.

[179] ለምሳሌ፥ Enrico Mazza በመጽሐፉ 4ኛ ምዕራፍ: "The Anaphora of Hippolytus," ከገጽ 98-102 የጻፈውን ይመልከቱ። Mazza, *Origins of the Eucharistic Prayer*, pp. 98-102.

[180] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 31.

[181] በእንግሊዝኛ፡- "Offering/ Offertory" ይባላል፡፡ ሥርዓተ ጥምቀት ባለበት ቀን ለቅዳሴ ከሚቀርቡት ኅብስትና ወይን በተጨማሪ ማር፥ ወተትና ውሃም ይዘጋጁ ነበር። ይህም ያስፈለገበት ምክንያት ንኡሰ ክርስቲያኑ ከተጠመቁ በኋላ ማርና ወተት ስለሚሰጣቸው ነው፤ ምሳሌነቱም፥ እግዚአብሔር አምላክ "ሕዝቤ" ብሎ ለመረጣቸው እስራኤላውያን፡- "ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ፥ ከዚያችም አገር ወተትና ማር ወደምታፈስሰው አገር፥ ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር . . . አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ" (ዘጸ. 3፥8) ብሎ ቃል እንደገባላቸው፥ የተጠመቁ ክርስቲያኖችም ሰማያዊ ርስት ወደሆነው መንግሥተ ሰማያት መግባታቸውንና የሕይወት እንጀራ የሆነውን የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል መመረጣቸውን ያመለክታል። ይህን አሳብ ግልጽ በማድረግ ወደ ግእዝ የተተረጐመውና የትእዛዝ ሲኖዶስ ክፍል የሆነው Apostolic Tradition በ34ኛው ምዕራፉ እንዲህ ይላል፡- "ወሐሊብሰ ወመዓር፥ [ቱሱሐን] በበይናቲሆሙ፥ ወያስትይዎሙ እምኔሁ በእንተ ተፍጻሜተ ተስፋ ዘአሰፈዎሙ ለአበዊነ እንዘ ይብል፡- 'እሁበክሙ ምድረ እንተ [ታውሕዝ] ሐሊበ ወመዓረ'። ዝንቱ ውእቱ ሥጋ ክርስቶስ ዘወሀበነ በዘቦቱ ነአምን ከመ ሕፃናት ንኡሳን እለ ተወልዱ እምኔሁ።" (የእኔ ትርጉም፡- ለአባቶቻችን 'ወተትና ማር የምታፈስሰውን ምድር እሰጣችኋለሁ' ሲል ስለሰጣቸው ተስፋ ወተትና ማር ቀላቅለው ያጠጧቸው። ይህ ከእርሱ እንደተወለዱ ሕፃናት ለምናምንበት የሰጠን የክርስቶስ ሥጋ ነው) - Hugo Duensing, *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt* (Göttingen: Vandenhoeck and Ruprecht, 1946) p. 60.

- አኰቴተ ቍርባን
- ትምህርት በኤጲስ ቆጶሱ
- ፈትቶ[182]
- ተመጥዎ ቍርባን (ቅዱስ ቍርባን መቀበል)

የሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቍርባን ደግሞ የሚከተሉትን ክፍሎች ይዟል፡-[183]
- አውሥአ[184] (ምልልስ)[185]
- የቍርባን ምስጋናው መቅድም
- ሠራዔ ቃል ዘእግዚአነ (ጌታ ቅዱስ ቍርባንን የመሠረተባቸው ቃላት)[186]
- ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ
- ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኅብስት ወወይን
- የማጠቃለያ ምስጋና።[187]

---

[182] Fraction of the Eucharistic bread.

[183] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* p. 32.

[184] ታላቁ ሊቅ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "ምልልስ፥ ምላሽ መስጠት" የሚሉት የአማርኛ ቃላት የግእዝ አቻዎቻቸው "ወሢእ፥ ወሢኦት" እንደሆኑና የቃላቱ መነሻ ግስ በተለምዶ የሚታወቀው "አውሥአ" ሳይሆን፥ "ወሥአ" እንደሆነ ያስረዳሉ። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ*፣ ገጽ 394 ይመልከቱ።

[185] ይህ ምልልስ (Dialogue) የሚጀምረው የቅዳሴው መሪ (celebrant):- "እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ - እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን" ሲል ነው። ነገር ግን "አልዕሉ አልባቢክሙ - ልቡናችሁን ከፍ አድርጉ" የሚል ትእዛዝን ስለሚጨምር፥ በቅዳሴ ጊዜ ልብን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር የማንሳትን (የመክፈትን) አስፈላጊነት ለማመልከት በላቲን ቋንቋ "ልብ" የሚለው ቃል የተጠቀሰበትን ሐረግ በመያዝ፥ Dialogue ከሚለው ስያሜ በተጨማሪ *Sursum corda* በመባል ይታወቃል። በግእዝ ልብ/ልቡና የሚለው ቃል የሁለመናችን ማእከል ከሆነው የሰውነት ክፍላችን በተጨማሪ ማስተዋል ማለትም ይሆናል፡፡ የቃሉ መገኛ ግስ፡- ለበወ = አስተዋለ፥ ልብ አለ፥ አሰበ፥ አተኮረ ነው፡፡ ስለዚህ "ልቡና" ሲባል አሳብ፥ ማስተዋል፥ ልብ ማለት፥ ትኵረት ማድረግንም ያመለክታል፡፡ በቅዳሴ ካህኑ "አልዕሉ አልባቢክሙ" የሚለው አሳባችሁን ወደ ተመስጦ ከፍ አድርጉት ለማለት ነው፡፡

[186] በእንግሊዝኛ፡- "Institution Narrative" ይባላል፡፡ ጌታ ኅብስቱን አንሥቶ፥ ባርኮ "እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው . . ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴ. 26፥26-28፤ ማር. 14፥22-25፤ ሉቃ. 22፥18-20) በማለት ለደቀ መዛሙርቱ እንደሰጣቸው የሚገልጹትን የወንጌላቱን ክፍሎች ያመለክታል፡፡

[187] Δόξα (ዞክሳ = ክብር፥ ምስጋና) እና λόγια (ሎጊያ= ቃላት፥ ንግግር) ከሚሉ ሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘው *Doxology* ለእግዚአብሔር ክብር የሚቀርብ አጭር ምስጋናን ያመለክታል፡፡

ሐዋርያዊ ትውፊት የተሰኘው መጽሐፈ ሥርዓት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ከፍተኛ ቦታ፥ የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓተ አምልኮ መሠረትና እድገት በምናጠናበት በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር እንመለከታለን።

## አኰቴተ ቍርባን ዘሐዋርያት ታዴዎስ ወማሬስ[188]

የሦስተኛው ምእት ዓመት ድርሰት እንደሆኑ ከሚታመኑት ቅዳሴያት መካከል እስካሁን ድረስ የምሥራቅ ሶርያ ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ በአገልግሎት ላይ ያለው የሐዋርያቱ ታዴዎስ እና ማሬስ አኰቴተ ቍርባን ነው።[189] የዚህ አኰቴተ ቍርባን ምንጭ በሰሜን ምሥራቅ ሶርያ የምትገኘው ጥንታዊቷ ከተማ ኤዴሳ ስትሆን[190]፥ ወደዚህች ከተማ ለወንጌል አገልግሎት በተላከው በሐዋርያው ታዴዎስ እና በደቀ መዝሙሩ ማሬስ ስም ቅዳሴው ተሰይሟል። ቅዱስ ታዴዎስ ዘኤዴሳ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለወንጌል አገልግሎት ሾሞ ከላካቸው 70 አርድእት (ሉቃ. 10፥ 1) መካከል አንዱ እንደነበር ይታመናል። በኤዴሳ ወንጌልን ሰብኮ በአገልግሎት እንዲያግዘው ማሬስ የተባለውን ደቀ መዝሙሩን ስለሾመው፥ ሁለቱ ሐዋርያት በምሥራቅ ሶርያ *ሊዴዎስ* እና *ማሬስ* ወይም *ሊዳይ* እና *ማሪ* በተሰኙ መጠሪያዎች ይታወቃሉ፤ ለዚህም ነው ቅዳሴው የሐዋርያቱን ሶርያዊ መጠሪያ ስም የያዘው።

በቅዱሳን ታዴዎስ ወማሬስ የተሰየመው አኰቴተ ቍርባን የጥንታውያን ቅዳሴያትን ባሕርያት በግልጽ ያንጸባርቃል። በውስጡ ያሉት ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች፡- ምስጋና ለዓለማት ፈጣሪ፥ አኰቴት በክርስቶስ ስለተደረገው የማዳን ሥራ፥ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መታሰቢያ ናቸው። በዚህ ምዕራፍ ከላይ እንደተመለከትነው፥ እነዚህ ሦስት ክፍሎች ደግሞ ሰማዕቱ ዮስጢኖስ በዘመኑ የነበረውን የቅዳሴ ሥርዓት አስመልክቶ ከሰጠው ገለጻ ጋር አብረው የሚሄዱ እንደሆነ እንረዳለን። [191] በተጨማሪ የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ጸሎታት በዚህ አኰቴተ ቍርባን ውስጥ መገኘታቸው

[188] The Anaphora of the Apostles Addai and Mari.
[189] Kenneth W. Stevenson, *Eucharist and Offering* (New York፡ Pueblo Pub. Co., 1986) p. 30.
[190] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, 39.
[191] ዝኒ ከማሁ፡ 40.

ጥንታዊነቱን ያጠናክራሉ። [192] አኰቴተ ቊርባን ዘታዴዎስ ወማሬስን ከሌሎች ቅዳሴያት ለየት የሚያደርገው፥ የአኰቴተ ቊርባን ዋነኛ ክፍል የሆነውንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቊርባንን በደቀ መዛሙርቱ ፊት ሲመሠርት የተጠቀመባቸውን የመባረኪያ ቃላት ማካተት አለመቻሉ ነው።[193] መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና ጽዋው ላይ እንዲወርድ ከሚጠይቀው ክፍል ቀደም ብሎ "ጌታ ሆይ በትውፊት ከአንተ የሆነውን አብነት ተቀብለናል"[194] የሚል ዐረፍተ ነገር አለ። ይህ ዐረፍተ ነገር ቀጥተኛና ግልጽ ባልሆነ መልኩ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ[195] የተባለውን የአኰቴተ ቊርባን ክፍል ያመለክታል የሚልን አሳብ ያንጸባረቁ ምሁራን ቢኖሩም[196]፥ በአንጻሩ ደግሞ ይህ የአኰቴተ ቊርባን ወሳኝ ክፍል እንደሚጎድለውም የጻፉ አልጠፉም። [197] የዚህ ቅዳሴ ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ [198] የመንፈስ ቅዱስን መምጣት የሚጠይቀው ኅብስቱንና ወይኑን የጌታ ሥጋና ደም ወደመሆን እንዲለውጥ ሳይሆን፥ ቅዱስ ቊርባንን ለሚቀበል ሁሉ የኃጢአት ይቅርታን ይሰጥ ዘንድ ነው። እንደሌሎቹ የ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት "መንፈስ ቅዱስን ላክ"[199]

---

[192] Stephen B. Wilson, "The Anaphora of the Apostles Addai and Mari," *Essays on Early Eastern Eurcharistic Prayers*, ed. Paul F. Bradshaw (Collegeville, MN: Liturgical Press, 1997) p. 26.

[193] በአንጻሩ፥ በዚሁ በ3ኛው ምእት ዓመት እንደተደረሰ የሚነገርለት የApostolic Tradition አኰቴተ ቊርባን (anaphora) የሚከተለውን Institution Narrative ይዟል፦ "ነሢኦ እንከ ኅብስተ አእኰተ፥ ወይቤ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ ዘበእንቲአክሙ ይት[ፌ]ተት፤ ወከማሁ ጽዋዐኒ ይቤ ዝ ውእቱ ደምየ ዘበእንቲአክሙ ይትከአው። ሶበ ትገብርዎ ለዝ ለተዝካረ ዚአየ ትገብሩ" (የእኔ ትርጉም፦ ከዚያም ኅብስቱን አንስቶ አመሰገነ፥ "ይህ ስለእናንተ የሚቆረስ ሥጋዬ ነው፥ ውሰዱ ብሉ" አለ፤ እንዲሁ ጽዋውንም [አንሥቶ]፦ "ስለእናንተ የሚፈስስ ደሜ ይህ ነው" አለ። ይህን በምታደርጉት ጊዜ ለመታሰቢያዬ ታደርጋላችሁ), *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing፣ አንቀጽ 21፣ ገጽ 22።

[194] የእንግሊዝኛው ትርጉም፦ "Lord, . . . [we] have received through tradition the form (example) which is from you" ይላል። Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 43.

[195] Institution Narrative.

[196] Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 40.

[197] Wilson, "The Anaphora of the Apostles Addai and Mari," p. 33.

[198] Epiclesis.

[199] ለምሳሌ ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም) እና ቅዳሴ ባስልዮስን ይመልከቱ። "አኰቴተ ቊርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ" in *Missale Ethiopicum*, ገጽ 110፤ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ባስልዮስ" ቊ. 40፣ ገጽ 284።

በማለት እግዚአብሔር አብን በመጠየቅ ፈንታ፥ “ቅዱስ መንፈስህ ይምጣ፥ በዚህ መሥዋዕትም ላይ ይረፍ”[200] ይላል። እነዚህ ሁሉ ነጥቦች ቅዳሴው ከ4ኛው ምእት ዓመት በፊት መደረሱን የሚያመላክቱ እንደሆኑ ይታመናል።[201]

የምሥራቅ ሶርያን ሥርዓተ ቅዳሴ በምትከተለው የማሮን ቤተ ክርስቲያን፥[202] የቅዱስ ጴጥሮስ ሦስተኛ አኰቴተ ቊርባን በሚል ስያሜ የሚታወቅ ቅዳሴ አለ። ይህ ቅዳሴ በሐዋርያቱ ታዴዎስና ማሬስ ከተሰየመው አኰቴተ ቊርባን ጋር ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ፥ ሁለቱም ከአንድ ምንጭ እንደተቀዱ ይታመናል።[203] የቅዱስ ጴጥሮስ ሦስተኛ አኰቴተ ቊርባን፥ *ሻራር* በሚል ተጨማሪ ስያሜም ይታወቃል። *ሻራር* የሚለው ቃል አኰቴተ ቊርባኑ የሚጀምርበት ቃል ስለሆነ ነው በዚህ ስም የተጠራው፤ በእኛ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴያቱ የመጀመሪያ ቃላት የሚጠሩ ቅዳሴያት እንዳሉን ማለት ነው:- ቅዳሴ ማርያም - “ኰሥዐ”፥ ቅዳሴ ፫ቱ፻ -“ግሩም”፥ ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ - “እምቅድመ ዓለም”፥ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ - “ተንሥኡ”። የቅዱስ ጴጥሮስ ሦስተኛ አኰቴተ ቊርባን (*ሻራር*)፥ ከዝማሬ ሱራፌል በኋላ ያሉት ጸሎታቱ በሙሉ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጸለዩ ናቸው።[204] ይህ አኰቴተ ቊርባን በውስጡ የያዘው ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ (*ኤፒክሌሲስ*) በቅዳሴ ታዴዎስ ወማሬስ

---

[200] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, 40.
[201] Wilson, “The Anaphora of the Apostles Addai and Mari,” p. 35.
[202] Maronite Church.
[203] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, 45.
[204] በአብዛኞቹ ጥንታውን ቅዳሴያት (Eucharistic prayers) ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው ጸሎታቱ በሙሉ የሚቀርቡት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለእግዚአብሔር አብ ነው። ለምሳሌ ከመጽሐፈ ሲኖዶስና ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰዱ ጥንታውያን ቅዳሴያት በመሆናቸው፥ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ሥርዓተ አምልኮ መሥራች ቅዳሴያት (foundational anaphoras) ተብለው ከሚታወቁት ከቅዳሴ ሐዋርያትና ቅዳሴ እግዚእ የተመረጡትን አጫጭር ጸሎታት ይመልከቱ:- “አቤቱ በተወደደ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ እናመሰግንሃለን”፥ “ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን፤ ከቅዱስ ምሥጢር በበረከት እንቀበል ዘንድ እንዲሰጠን”፥ “ቅዱስ አምላክ ሆይ እናመሰግንሃለን፥ ነፍሳችንን ፍጽምት የምታደርግ፥ ሕይወታችንን የምትሰጥ፥ የማይጠፋ መዝገብ፥ የአንድ ልጅህ የመድኃኒታችን አባት”፥ “[አቤቱ] የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፥ ፍጥረት ሁሉ ነፍስም የምትንቀጠቀጥልህና ፍርሃቱ አድሮባት የሚኖር፥ ይህ ምስጋና ለአንተ ይገባል . . . አዎን አቤቱ አምላካችን፥ ስለ ስምህ አንተን ደስ ከማያሰኝ አሳብ እንለይ ዘንድ መለየቱን ስጠን” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ “ቅዳሴ ሐዋርያት” ቊ. 4፣ ገጽ 101፤ ቊ. 58-59፣ ገጽ 111-112፤ “ቅዳሴ እግዚእ” ቊ. 18፣ ገጽ 146፤ ቊ. 49-51፣ ገጽ 151-152።

ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፥ በአንጻሩ ደግሞ በቅዳሴ ታዴዎስ ወማሬስ የማናገኘውና ግልጽ የሆነ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ አለው።[205]

## ቅዳሴ ማርቆስ ወንጌላዊ

በሐዋርያውና ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ ስም የተሰየመው አኰቴተ ቍርባን የእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ መደበኛ ቅዳሴ ነበር።[206] ይህ ቅዳሴ በየዘመናቱ የተለያዩ የአኰቴተ ቍርባን ክፍሎች እየተጨመሩበት መጨረሻ ላይ ያገኘውን ቅርጽ ከመያዙ በፊት፥ ጥንታዊ ይዘቱ በተለያዩ ብራናዎች ላይ ስለተገኘ ከጥንታውያን ቅዳሴያት መካከል ለጥናት እጅግ አመቺ ሆኗል። "PGr. 254" የተሰኘ የመለያ ኮድ የተሰጠው የ4ኛው ወይም 5ኛው ምእት ዓመት ፓፒረስ (ጥቅል)[207] እ.አ.አ. በ1928 ታትሟል።[208] የዚህ ጥንታዊ ሰነድ እድሜ በዚህ መልኩ ቢገመትም፥ በውስጡ የያዘው ጸሎተ ቅዳሴ ግን በ3ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ አካባቢ እንደነበሩ ከሚገመቱት ቅዳሴያት ጋር ይመደባል። ፓፒረሱ (ጥቅሉ) በውስጡ የያዘው ራሱን የቻለ ሙሉ አኰቴተ ቍርባን ሳይሆን፥ ክፍለ-አኰቴተ ቍርባን[209] ነው ሲሉ አስተያየት የሰጡ የሥርዓተ ቅዳሴ ምሁራን አሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ የጥቅሉ ጸሎተ ቅዳሴ ከተደረሰበት ዘመን አንጻር ሲታይ ሙሉ አኰቴተ ቍርባን ተብሎ ሊወሰድ እንደሚገባም ይታመናል።[210]

የቅዳሴ ማርቆስን ጥንታዊ ይዘት የሚያንጸባርቀው ፓፒረስ (ጥቅል)፥ በውስጡ የያዘው አኰቴተ ቍርባን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡- ምስጋና፥ አግብኦተ ግብር እና መስተብቍዕ/ የልመና ጸሎት። እነዚህ ክፍሎች በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ

---

205 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, pp. 48 & 50.
206 ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 52።
207 The Strasbourg Papyrus.
208 G. J. Cuming, "The Anaphora of St. Mark: A Study of Development," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Bradshaw, 58.
209 Paleo-anaphora.
210 የተለያዩ ሊቃውንትን ጥናታዊ ጽሑፎች በማነጻጸር የተደረጉ እነዚህን ጥናቶች ይመልከቱ፡- Mazza, "Chapter Five: The Alexandrian Anaphora," *Origin of the Eucharistic Prayer,* pp. 177-219; Cuming, "The Anaphora of St. Mark: A Study of Development," pp. 57-65.

የተመለከትናቸው መጻሕፍተ ሥርዓት (ዲዳኬ፥ ሐዋርያዊ ትውፊት) ከያዟቸው የቅዱስ ቍርባን ጸሎታት ጋር ስለሚመሳሰሉ የፓፒረሱን (የጥቅሉን) ይዘት ጥንታዊነት ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም በዲዳኬ፥ በቅዱስ ዮስጢኖስና ቅዱስ ሄሬኔዎስ መጻሕፍት የተጠቀሰው ትንቢተ ሚልክያስ 1፥11[211] በብራናው አኰቴተ ቍርባን ውስጥ መጠቀሱና የቅዳሴው አገልግሎት ደም አልባ አገልግሎት[212] መባሉ ለጸሎተ ቅዳሴው ጥንታዊነት ተጨማሪ ማረጋገጫዎች ናቸው።[213] የቅዳሴውን መሥዋዕት (ደም አልባ/ ዘእንበለ ደም) በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጸው በ177 ዓ.እ. አካባቢ የነበረውና አቴናጎራስ የተባለው የክርስትና እምነት ጠበቃ (ዐቃቤ እምነት) ነው።[214] አቴናጎራስ ይህን አገላለጽ የተጠቀመው የክርስቲያኖች መሥዋዕት አሕዛብ ለጣዖቶቻቸው ከሚያቀርቡት የእንስሳት ሥጋና ደም መሥዋዕት የተለየ እና ከአሕዛብ መሥዋዕት ጋር ምንም አይነት ኅብረት እንደሌለው ለማስገንዘብ ፈልጎ ነው።[215]

የቅዳሴ ማርቆስን መሠረታዊ ይዘት የሚያመለክተው ሌላው ጥንታዊ ሰነድ የተሰኘው አኰቴተ ቍርባን ዘባርሴሎና[216] የተሰኘው ብራና ነው። በጽርእ እና ቅብጥ (ኮፕቲክ) ቋንቋዎች የተዘጋጀው ይኸው አኰቴተ ቁርባን፥ ይዘቱ የሚከተለውን ይመስላል፡-

- አውሥኦ (ምልልስ)

---

211 "ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፥ ንጹሕም ቍርባን ያቀርባሉ፡ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።"

212 "Bloodless service." ከግሪክ ወደ ግእዝ የተተረጐመው "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ" የቅዳሴውን መሥዋዕት "ያለ ደም የሆነ እና የሚናገር" ሲል ይገልጸዋል፡- "ነአኵተከ ወናቄርብ ለከ ዛተ መሥዋዕተ ነባቢተ እንተ ይእቲ ዘእንበለ ደም" - *Missale Ethiopicum,* ገጽ 117 ይመልከቱ። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ፥ በቅዳሴ ሐዋርያት ሠራዒው ካህን፡- "ዝንቱ ደም ነባቢ ይኩን ሠራዬ ኃጢአትየ ለገብርከ - ይህ የሚናገር ደም የእኔን የባሪያህን ኃጢአት የሚያስተሠርይ ይሁን" በማለት ይጸልያል። "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 2000፣ ቍ. 106፣ ገጽ 123።

213 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 53.

214 "*Legatio* 13:3," Cuming, "The Anaphora of St. Mark: A Study of Development," p. 67.

215 Cuming, "The Anaphora of St. Mark: A Study of Development," p. 67.

216 The Barcelona Anaphora.

- መቅድም
- “ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ . . .” ለሚለው የመላእክት ዝማሬ መግቢያ
- ዝማሬ ሱራፌል
- አግብኦተ ግብር  እና ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ (የመጀመሪያ)
- ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ
- ዝከረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ
- ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ (ሁለተኛ).
- የማጠቃለያ ምስጋና፡፡[217]

በተጨማሪ የቅዳሴ ማርቆስን የተወሰነ ክፍል የያዙ የ6ኛው ምእት ዓመት ብራና እና የ8ኛው ምእት ዓመት ሥራ እንደሆነ የተገመተ የእንጨት ጽላት ተገኝተዋል።[218] እንዲሁም የተለያዩ የ13ኛው ምእት ዓመት ብራናዎች፥ ሙሉ ቅዳሴ ማርቆስን ባይሆንም፥ ከ5ኛው ምእት ዓመት በኋላ በቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ (+444 ዓ.እ.) መጠነኛ ማሻሻያ የተደረገለትን አኰቴተ ቍርባን የተወሰነ ክፍል ይዘው ይታያሉ።[219] የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ከምትጠቀምባቸው ሦስት ቅዳሴያት መካከል (የባስልዮስ፥ የቄርሎስ እና የጎርጎርዮስ ቅዳሴ) በቅዱስ ቄርሎስ ስም የተሰየመው፥ ጥንታዊው የቅብጡ (ኮፕቲክ) ቅዳሴ ማርቆስ ነው። ቅዳሴው በቅዱስ ቄርሎስ ስም የተሰየመው ይህ አባት ከቅዳሴ ባስልዮስና ከቅዳሴ ያዕቆብ አንዳንድ ጸሎታትን ወስዶ የቅዳሴውን ይዘት ስለቀየረው ነው። እዚህ ላይ፥ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቄርሎስ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ቅዳሴ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ባሳተመችው መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ “አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ቄርሎስ”[220] የሚል ርእስ ከተሰጠው ቅዳሴ ወይም እስካሁን ድረስ ካልታተመውና በብራና ከሚገኘው ቅዳሴ ቄርሎስ ካልእ (ሁለተኛ) ጋር ፈጽሞ እንደማይገናኝ ልብ ልንል ይገባል።

---

[217] Bryan D. Spinks, *Do This in Remembrance of Me: The Eucharist from the Early Church to the Present Day* (London: SCM Press, 2013) p. 101.

[218] ዝኒ ከማሁ፡ 115.

[219] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 53.

[220] መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 372።

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ያሻሻለውንና በስሙ የሚጠራውን ቅዳሴ ምሁራኑ ለጥናት የሚጠቀሙበት በወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ ስም ከተሰየሙ ቅዳሴያት ጋር በማነጻጸር ነው። የኮፕቲኩ ቅዳሴ ማርቆስ (ቅዱስ ቄርሎስ ካሻሻለው በኋላ በስሙ የተሰየመው) በግሪክ ቋንቋ ከሚገኘው ቅዳሴ ማርቆስ ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ ልዩነት ያሳያል፤ በግሪኩ የሚገኙ አንዳንድ ጸሎታት በኮፕቲኩ አይገኙም፥ የኮፕቲኩ ቅዳሴ ማርቆስ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ጸሎታት ደግሞ በግሪኩ የሉም።[221] ወደ ግእዝ የተተረጐመው ቅዳሴ ማርቆስ በተለያዩ ጊዜያት ጭማሬዎች እየተደረጉበት መጨረሻ የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰው የግሪኩ ቅዳሴ ማርቆስ ትርጉም እንደሆነ የሚጠቁም ጥናት አለ።[222] በ1945 እ.አ.አ. ሮም ውስጥ የታተመውና 17 ቅዳሴያትን የያዘው መጽሐፈ ቅዳሴ ከብራና የተወሰደውን የግእዙን ትርጉም፡- "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ" የሚል ርእስ ሰጥቶታል።[223]

የትርጒሙን ጠቅላላ ይዘት ስንመለከት፥ በእንግሊዝኛው ቅዳሴ ማርቆስ የሚገኙ ጸሎታትን ከመያዝ ባሻገር ልክ እንደ ቅዳሴ ሐዋርያት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተጨመሩ ክፍሎችን (ለምሳሌ፡- በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ፥ መሐሮሙ እግዚኦ፥ ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ወዘተ.) ያሳያል። እንዲሁም የቅዳሴው ተርጓሚዎች ግልጽ ያልሆኑላቸውን ምንባባት በራሳቸው ቃላት እየተኩ ተርጒመዋቸዋል። ለምሳሌ፥ የቅዳሴ ማርቆስ መለያ ባህርያት ከሆኑት መካከል፥ ከዝማሬ ሱራፌል  ጋር የተያያዘና መንፈስ ቅዱስ በመሥዋዕቱ ላይ እንዲወርድ የሚጠይቅ ጸሎት በውስጡ መገኘቱ ነው። ጸሎቱ፡- "አቤቱ እግዚአብሔር [ሆይ] ይህን መሥዋዕት በቅዱስ መንፈስህ መውረድ ከአንተ በሆነ በረከት ምላው" ይላል።[224] ቅዳሴ ማርቆስን ከግሪክ ወደ ግእዝ የመለሱ ተርጓሚዎች ግን፡- "ሀበነ እግዚኦ እምኀቤከ ዘንተ በረከተ፥ [ወ]ይኅድር መንፈስከ ቅዱስ ላዕሌነ"[225] ሲሉ ከምንጩ

---

[221] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 53.
[222] Cuming, "The Anaphora of St. Mark: A Study of Development," p. 58.
[223] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum,* ገጽ. 117።
[224] የእንግሊዝኛው ትርጒም፡- "fill, O God, this sacrifice also with the blessing from you through the descent of your Holy Spirit" ይላል። Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 64.
[225] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum,* ገጽ. 121።

ጋር አቻ ያልሆነ ትርጒም ሰጥተውታል፤ ይህም (አቤቱ ይህን በረከት ከአንተ ስጠን፥ መንፈስ ቅዱስም በእኛ ላይ ይደር) ማለት ነው። የግእዙ ተርጓሚዎች፥ የመሥዋዕቱ በበረከት መሞላት የሚለው አሳብ ስላልተመቻቸው፥ "ምላእ" የሚለውን ግስ ከመጠቀም ይልቅ "ሀበነ" በሚለው ግስ ተከተው "ከአንተ የሆነውን በረከት ስጠን" ብለው መተርጎምን መርጠዋል። ነገር ግን ይኸው የቅዳሴ ማርቆስ ጸሎት የግብፃዊው ጳጳስ ቅዱስ ሰራጵዮን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥም ስለሚገኝ፥ [226] "መሥዋዕቱን በበረከት ምላው" የሚለው ጸሎት የግብፅ ጥንታውያን ቅዳሴያት ዋነኛ መገለጫ ነው።

## ፫. የ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት

ታላቁ ቈስጠንጢኖስ በ4ኛው ምእት ዓመት የክርስትናን እምነት ከተቀበለ በኋላ፥ የስደት ዘመን አብቅቶ ቤተ ክርስቲያን አንጻራዊ ሰላም አግኝታ ነበር። በሰላሙ ዘመን የክርስቲያኖች ቍጥር እየጨመረ ሲመጣ፥ የአምልኮ ሥርዓታቸውን በነጻነት ለማካሄድ የሚያስችሏቸው ካቴድራሎች መታነጽ ጀመሩ። በተጨማሪም የሮማው ግዛት ጎረቤት ውስጥ ይከናወኑ የነበሩ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ክርስቲያናዊ ትርጒም እየተሰጣቸው ተቀባይነትን አገኙ።[227] በአምልኮ ጊዜ አንዳንድ ከሥርዓት ያፈነገጡ ባሕርያት በሚታዩበት ጊዜ፥ በዘመኑ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርታዊ ተግሣጽ ያስተላልፉ ነበር። ጣዖት አምልኮአቸውን ትተው የክርስትና እምነትን ለመቀበል በዝግጅት ላይ ላሉ ሰዎች ማስተማሪያና ማሠልጠኛ የሚሆኑ ጽሑፎችም (ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያን)[228] መዘጋጀት ጀመሩ። በዚህ ክፍለ ዘመን የታየው ዋነኛውና ታላቁ እድገት ግን ለሥርዓተ ቅዳሴ አገልግሎት የሚውሉና በዘመኑ ለተነሡ ኑፋቄያት መልስ የሚሰጡ ቅዳሴያት መደረሳቸው ነበር።[229]

የ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት ምንጭ የክርስትናው ዓለም ምሥራቃዊ ክፍል እንደነበር ታሪካዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህ ምዕራፍ ከላይ የተመለከትነው ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ የሚገኘው አኰቴተ ቍርባን ከሮም (ምዕራቡ ክፍል)

---

[226] Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p. 81.
[227] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 61.
[228] Mystagogical catecheses.
[229] Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p. 68።

እንደተገኘ በልምድ ቢታመንም፥ በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች የዚህ መጽሐፈ ሥርዓት መገኛ የምዕራብ ሶርያ ግዛት እንደሆነ አረጋግጠዋል።[230] ከምዕራቡ ዓለም የተገኘው ብቸኛው የሥርዓተ አምልኮ ምንጭ፥ ምሥጢራት[231] በሚል ርእስ ቅዱስ አምብሮስ ዘሚላን ያዘጋጀውና ስለ ምሥጢረ ቍርባን ማብራሪያ የሚሰጠው ድርሳን ነው።[232] የምሥራቁ ክፍል ቅዳሴያት ከይዘታቸው አንጻር፦ ዘእስክንድርያ፥ ዘምዕራብ ሶርያና ዘምሥራቅ ሶርያ[233] በሚሉ ሦስት መሠረታዊ ክፍሎች ይከፈላሉ። በመጀመሪያው ክፍል የሚመደቡ ቅዳሴያት፥ በመግቢያውና በዝማሬ ሱራፌል መካከል ተዝካረ ቅዱሳንን እና የልመና ጸሎታትን የማስገባት መገለጫ ባሕርይ አላቸው። የምሥራቅ እና ምዕራብ ሶርያ ማንኛውም ዓይነት አኰቴተ ቁርባን ደግሞ፥ “ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ምድር[234] ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች” (ት. ኢሳ. 6፥3) ከሚለው የሱራፌል ዝማሬ ጋር፦ “ሆሣዕና በአርያም፥ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው” የተሰኘውን ዝማሬ[235] በማካተት ይታወቃል።[236]

## የቅዱስ ሰራጵዮን መጽሐፈ ቅዳሴ [237]

ከ339-360 ዓ.እ. የዓባይን ወንዝ ተከትላ የተመሠረተችው ከተማ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ሰራጵዮን በ350 ዓ.እ. አካባቢ ለሥርዓተ አምልኮ የሚውል መጽሐፍ አዘጋጅቶ እንደነበር ይታመናል። ይህ የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ፦ አኰቴተ ቍርባን፥ ጸሎተ ፈትቶ፤ በዕለተ እሑድ፥ ስለሕዝብና ስለ መልካም ሰብል የሚጸለዩ፥ እንዲሁም ከስብከት በኋላ የሚጸለዩ ጸሎታትን ስለያዘ በአንዳንድ ሊቃውንት መጽሐፈ ቅዳሴ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል።[238] ቅዱስ ቍርባንን ለማክበር

---

[230] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ. 76።
[231] *De Sacramentis*.
[232] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 144-146።
[233] Alexandrian, West Syrian (Antiochene) and East Syrian.
[234] ቅዳሴያቱ “ሰማይና ምድር” ይላሉ።
[235] ይህ ዝማሬ በላቲን ቋንቋ *Benedictus* ይባላል፡፡
[236] ለምሳሌ፥ “The Liturgy of St. James” in Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist,* ገጽ 91 ይመልከቱ።
[237] The Euchology of St. Sarapion, Bishop of Thmuis.
[238] Spinks, *Do This in Remembrance of Me*, 94; Mazza, *The Origins of the Eucharistic Prayer,* 219.

የተዘጋጀውን ጸሎት ደግሞ ለይተው ጸሎተ ጵርስፎራ[239] ብለው ይጠሩታል።[240] የቅዱስ ሰራጵዮን አኰቴተ ቍርባን በኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ. አይታወቅም። ሆኖም፥ የቤተ ክርስቲያናችንን መጽሐፈ ቅዳሴ ያዘጋጁ ሊቃውንት አባቶቻችን ቅዳሴው መግቢያ ላይ በኅብስቱና ወይኑ ላይ ሠራዒው ካህን የሚጸልየውን ጸሎት "ጸሎተ እንፎራ - የኅብስት ጸሎት"[241] የሚል ርእስ ሰጥተውታል። "እንፎራ" የሚለው ቃል በግሪኩ *ኣናፎራ* ከሚለው የተወሰደ ይመስላል፤ እንዲሁም የግሪኩን *ፕሮስፎራ* የሚመስል "ጵርስፎራ"[242] የሚል ቃል በመጽሐፈ ቅዳሴ ስለምናገኝና እነዚህ ሁለት የግሪክ ቃላት ኅብስት ወይም አኰቴተ ቍርባን (የቍርባን ምስጋና) የሚሉ ትርጕሞችን ስለሚሰጡን፥ የቃላቱ ጥሬ ዘር በመጽሐፈ ቅዳሴ መገኘት ጥንታውያን አባቶቻችን በግሪክ ቋንቋ የተዘጋጀውን የቅዱስ ሰራጵዮን ጸሎተ ጵርስፎራ (አኰቴተ ቍርባን) የማየት እድሉ ነበራቸው ለማለት ያስችለናል።

በቅዱስ ሰራጵዮን ስም የሚጠራው አኰቴተ ቍርባን፥ የዚህ ቅዱስ *ሥራ* መሆኑን የተጠራጠሩ ምሁራን አሉ። ለዚህም ምክንያታቸው ወልድን እና መንፈስ ቅዱስን ከአብ የሚያሳንሱ የ4ኛው ምእት ዓመት ኑፋቄያት አመለካከት በውስጡ መንጸባረቁ ነው። ለምሳሌ ጸሎተ ቅዳሴው ውስጥ፥ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እና መንፈስ ቅዱስ በእኛ ይናገሩ፥ በእኛ ውስጥ አንተን ያመስግኑህ" የሚልና ወደ እግዚአብሔር አብ የተጸለየ ጸሎት ይገኛል።[243] ስለዚህ፥ እንደዚህ ዓይነቱን ጸሎት የታላቁ ኦርቶዶክሳዊ አባት የቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ጓደኛ የነበረው ቅዱስ ሰራጵዮን ሊያዘጋጅ አይችልም የሚል ሙግት ያቀርባሉ።[244] ነገር ግን፥ የመጽሐፈ ቅዳሴው አጠቃላይ ይዘት ቅዱስ አትናቴዎስ ለወዳጁ ቅዱስ ሰራጵዮን ከጻፈለት ደብዳቤዎች ጋር ስለሚመሳሰል የቅዳሴው ደራሲ ቅዱስ ሰራጵዮን መሆኑ ባያጠራጥርም፥ ጥያቄ

---

239 Prayer of offering (of Prosphora).

240 Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p. 80.

241 *መጽሐፈ ቅዳሴ*፤ ቍ. 46፣ ገጽ 46።

242 "ህበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ፥ ወፈውሰነ በዝንቱ ጵርስፎራ - የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን፥ በዚህም ጵርስፎር (በሥጋው በደሙ) አድነን" - *መጽሐፈ ቅዳሴ*፤ ቍ. 54፣ ገጽ 111።

243 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 76.

244 ዝኒ ከማሁ፡ 74፤ Mazza, *The Origins of the Eucharistic Prayer*, p. 221.

የሚፈጥሩ ምንባባትን አርዮሳውያን (የአርዮስ ኑፋቄ ተከታዮች) እንደጨመሯቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል።[245]

አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ሰራጵዮን ምንም እንኳን በ4ኛው ምእት ዓመት የተዘጋጀ ቢሆንም በዚህ ክፍለ ዘመን የምናገኛቸው ቅዳሴያት የደረሱበትን እድገት አያንጸባርቅም። ስለዚህ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘእስክንድርያ [246] በሚል ስያሜ የሚታወቀው የቅብጥ (ኮፕቲክ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ፥ እድገት ከማሳየቱ በፊት ለነበረበት ደረጃ እንደ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።[247] መግቢያው ላይ እንደ አብዛኞቹ የ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት "አንተን ማመስገን፥ ማወደስና ከፍ ከፍ ማድረግ በእውነት ይገባል"[248] በማለት ይጀምራል። ምስጋና የሚቀርብለትንም አምላክ "የማይመረመርና ሊነገር የማይችል"[249] ሲል ይገልጸዋል። ከዝማሬ ሱራፌል በፊትና በኋላ ያሉት የአኰቴተ ቍርባኑ ክፍሎች ከቅዳሴ ማርቆስ የተወሰዱ ይመስላሉ። ይህን ዝማሬ ተከትሎ በሚመጣው ክፍል፡- "የኃይላት ጌታ፥ ሰማይና ምድር ግሩም በሆነው ክብርህ የተሞሉ ናቸው" ካለ በኋላ፥ የቅዳሴ ማርቆስን አገላለጽ በመጠቀም "ይህንን መሥዋዕት በኃይልህ ሙላው . . . ለአንተ ይህን ሕያው መሥዋዕት እናቀርባለን" ይላል።[250] እንደ ቅዱስ ሰራጵዮን አገላለጽ፥ የቅዳሴው መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው ኅብስት "አርአያ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር" ሲሆን፥ ጽዋው (ወይኑ) ደግሞ "አርአያ ደሙ" ነው።[251] እንደዚህ ዓይነቱን አመለካከት የ2ኛውና የ3ኛው ምእት ዓመታት መጻሕፍተ ሥርዓት ውስጥ እንጂ፥

[245] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 74.
[246] Alexandrian rite.
[247] Mazza, *The Origins of the Eucharistic Prayer*, p. 239፤ Bradshaw and Johnson, p.106.
[248] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 76.
[249] ዝኒ ከማሁ።
[250] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 77።
[251] ዝኒ ከማሁ።

የ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት ውስጥ አናገኝም፤[252] ስለዚህ የሰራጵዮን ቅዳሴ በተደረሰበት ክፍለ ዘመን የነበረውን ትምህርተ ቍርባን አያመለክትም።

ቅዳሴ ሰራጵዮን ከተደረሰበት ክፍለ ዘመን አንጻር እጅግ ጥንታዊ አኰቴተ ቍርባን መሆኑን የሚያመለክቱ ተጨማሪ ነጥቦችም አሉት። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቍርባንን የመሠረተባቸውን ቃላት (ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ)፥ ወንጌላቱን አብነት በማድረግ "ኅብስቱን አነሣ፥ ቆረሰ፥ 'ይህ ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈተት ሥጋዬ ነው፥ ንሡ ብሉ' ብሎ ሰጣቸው" ካለ በኋላ፥ ጌታ ጽዋውን አንሥቶ የተናገራቸውን ቃላት ከመዘርዘሩ በፊት ከዲዳኬ 9፥2-4[253] በመጥቀስ የልመና ጸሎትን በመሃል ያስገባል። ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ በሚባለው የአኰቴተ ቍርባኑ ክፍል ደግሞ፥ በኅብስቱና በጽዋው ላይ እንዲወርድ የሚጠይቀው መንፈስ ቅዱስን ሳይሆን ቃለ እግዚአብሔር (ወልድን) ነው። ጸሎቱም፦ "የእውነት አምላክ ሆይ፥ ቅዱስ ቃልህ በዚህ ኅብስት ላይ ይምጣ፥ ኅብስቱ የቃል ሥጋ ይሆን ዘንድ፤ በዚህም ጽዋ ላይ፥ የእውነት ደም ይሆን ዘንድ"[254] ይላል። ቅዱስ አትናቴዎስ ለሰራጵዮን በጻፈለት ደብዳቤዎች ውስጥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሊለያይ የማይችል መለኮታዊ አንድነት እንዳላቸው ይገልጽለት ስለነበር፥ ሰራጵዮን በቅዳሴው በርደተ

---

[252] ለምሳሌ በ3ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ እንደተዘጋጀ የሚታመነው Apostolic Traditon እንደ ሰራጵዮን አኰቴተ ቍርባን ዓይነት አገላለጽ ይጠቀማል። "And then the offering shall be presented by the deacons to the bishop; and he shall give thanks over the bread for the representation, which the Greeks call 'antitype', of the body of Christ; and over the cup mixed with wine for the antitype, which the Greeks call 'likeness', of the blood which was shed for all who have believed in him . . ." Cuming, *Hippolytus,* p. 21. Alessandro Bausi የአርትኦት ሥራ ሠርቶ ወደ ጣሊያንኛ የተረጎመው የግእዙ Apostolic Traditon ውስጥ ተመሳሳይ ትርጕም እናገኛለን፦ "ያምጽኡ ተዝካረ [ዲያቆናት] ለኤጲስቆጶስ ወያእኵቶ ኅብስተ አርአያ ሥጋሁ ለክርስቶስ፥ [ወጽዋዐ] ወይን ቱሡሐ በእንተ አርአያ ደም [ዘተከዕወ] በእንተ እለ የአምኑ ቦቱ"። See Bausi, "*LA NUOVE VERSIONE ETIOPICA DELLA TRADITIO APOSTOLICA,*" *Studia Ephemeridis Augustinianum*, Vol. 125 (2011) p. 46.

[253] ከላይ የተጠቀሰው የዲዳኬ ጥቅስ ትርጕም፦ "ይህ ኅብስት [ኅብስቱ የተዘጋጀበት ስንዴ] በተራሮች ላይ ተበትኖ እንደነበር፥ ተሰብስቦም አንድ እንደሆነ፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ከሁሉም ነገድ፥ አገር፥ ከተማና መንደር ሰብስበህ አንዲት፥ ሕያዊት እና ኵላዊት ቤተ ክርስቲያን አድርጋት" የሚል ነው። Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 77.

[254] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 77-78።

መንፈስ ቅዱስ ቦታ የወልድን (ቃልን) መምጣት የጠየቀው በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል።[255] በተጨማሪም፥ የሰራጵዮን አኰቴተ ቍርባን የተጻፈው፥ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በካደው መቅዶንዮስ ምክንያት በ381 ዓ.እ. በቍስጥንጥንያ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ ተካሂዶ በአንቀጸ ሃይማኖት[256] የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚገልጹ ዐረፍተ ነገሮች ተጨምረው ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ ከመስፋፋቱ በፊት ስለሆነ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን የአካልና የግብር ልዩነት ያላገናዘበ መሆኑ ግልጽ ነው።[257]

## ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያን ዘቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም (+386 ዓ.እ.)

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ በ4ኛው ምእት ዓመት የደረሰበትን ደረጃ ከሚጠቁሙ ታሪካዊ መረጃዎች መካከል በኢየሩሳሌም ይካሄድ ስለነበረው ቅዳሴ ፍንጭ የሚሰጠን የቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያን ዋነኛው ነው። ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያን[258] የሚል ስያሜ የተሰጣቸው፥ ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ ላሉ ሰዎች (ንኡሰ ክርስቲያን) የተሰጡ የሥልጠና ትምህርቶች ናቸው። *ሚስታጎጊያ*[259] የሚለው የግሪክ ቃል፦ ማስተማርን፥ ለምሥጢራት ማዘጋጀትንና ስውር የሆነውን ነገር መግለጽን ያመለክታል።[260] ምንም እንኳ በአምስት ክፍሎች የተከፈሉ የእነዚህ ትምህርቶች ደራሲ ከ349 - 386 ዓ.እ. የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ ቄርሎስ ወይም እርሱን የተካው ሊቀ ጳጳሱ ዮሐንስ ዳግማዊ (387-417 ዓ.እ.) መሆኑ አከራካሪ ቢሆንም[261] ትምህርቶቹ ለትንሣኤ ዋዜማ ለተጠመቁ ክርስቲያኖች ጥምቀትንና ቅዱስ ቍርባንን አስመልክቶ

---

[255] Spinks, *Do This in Remembrance of Me*, 98.

[256] Creed.

[257] Robert Taft, "From logos to spirit: On the early history of the epiclesis," *GRATIAS AGAMUS: Studien zum eucharistischen Hochgebet,* Basel: Verlag Herder, 1992, p. 498.

[258] Mystagogical catecheses.

[259] Μυσταγωγία.

[260] Enrico Mazza, *Mystagogy: A Theology of Liturgy in the Patristic Age* (New York: Pueblo Publishing Company,1989) p. 1.

[261] በዚህ ጉዳይ ስለተደረጉ ጥናቶች፦ Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies*, p. 79, footnote 59 ይመልከቱ።

የተሰጡ መሆናቸው ይታመናል።[262] በ385 ዓ.እ. ኢየሩሳሌምን የጎበኘችው ኢጌሪያ የተባለች የስፔን መነኰሲት፥ ጳጳሱ መቅደሱ ፊት ለፊት ላይ ቆሞ በሥርዓተ አምልኮው የሚከናወኑትን ነገሮች በሙሉ እያብራራ ያስተምር እንደነበር ምስክርነት ሰጥታለች።[263]

በእኛም ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰደውና መግቢያው ላይ ባሉት ሁለት ቃላት "ትምህርተ ኅቡኣት" ተብሎ የተሰየመው ጥንታዊ ጽሑፍ፥ ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ ላሉ ሰዎች ስውር የሆነውን የጥምቀት ምሥጢር ለመግለጽ የተዘጋጀ የሥልጠና ትምህርት ነው።[264] ትምህርተ ኅቡኣት፥ የተዘጋጀበትን ምክንያት ግልጽ ሲያደርግ እንዲህ ይላል፦ "[ወ]በእንተዝ ይበል ኖላዊ መፍትው [እንከ] ነገረ ኅቡኣት ከመ ያእምሩ መነሂ [ይሳተፉ] በቅድሳት[265] ወለመኑ ይገብሩ ተዝካሮ በአኰቴት"[266] ይላል። ይህም ማለት፥ እረኛው (ቄሱ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ) ሥጋውን ደሙን በመቀበል ጊዜ ማንን እንደሚቀበሉ (ከማን ጋር እንደሚዛመዱ)[267] እና በጸሎተ ቅዳሴ የማንን መታሰቢያ እንደሚያደርጉ ያስተምራቸው ማለት ነው። ይህ ለጥምቀት የማዘጋጃ ትምህርት የሚሰጠውም ሁልጊዜ ሳይሆን እንደ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የክርስትናን እምነት የተቀበሉ ሰዎች በሚጠመቁበት በዘመነ ፋሲካ፥ በዓለ ኀምሳ ወይም በዕለተ እሑድ እና በዘመነ አስተርእዮ እንደሆነ የትምህርተ ኅቡኣት መጨረሻ ይናገራል፦ "አኮ እንከ ወትረ ኅቡኣተ ዘይት[ነ]ገር አላ በፋሲካ፥ ወበሰንበተ ክርስቲያን፥ ወኤጲፋንያ፥ ወበዓለ [ኀምሳ]"።[268] ከትምህርተ ኅቡኣት ጋር

262 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 82; Kenet J. Burreson, "The Anaphora of the Mystagogical Catecheses of Cyril of Jerusalem," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers*, ed. Bradshaw, p. 131.

263 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 82. የኢጌሪያን ጉብኝት ዝርዝር ለማንበብ፦ Egeria, *Peregrinatio* 27.6 ወይም የእንግሊዝኛውን ትርጉም፦ John Wilkinson, *Egeria's Travels,* 3rd ed., Oxford: Oxbow, Aris & Phillips, 1999, ገጽ 129 ይመልከቱ።

264 *Testamentum domini éthiopien*, ed. and trans. Beylot, 53.

265 "መነሃ ትሳተፉ ለቅድሳት" - "ትምህርተ ኅቡዓት [*sic*]" መጽሐፈ ቅዳሴ፥ ንባቡና ትርጓሜው፣ ቍ. 36፥ ገጽ. 21።

266 *Testamentum domini éthiopien*, ed. and trans. Beylot, 61.

267 "ትምህርተ ኅቡዓት [*sic*]" መጽሐፈ ቅዳሴ፥ ንባቡና ትርጓሜው፣ ቍ. 36፥ ገጽ. 21።

268 *Testamentum domini éthiopien*, ed. and trans. Beylot, 61. በያሬዳዊ ሥርዓተ ማኅሌት፥ ትምህርተ ኅቡኣት የሚቆመው ከጾመ ነቢያት ውስጥ ለስብከትና ለኖላዊ (ከልደት በፊት ካሉት ሦስት

ተመሳሳይ ይዘት ያለውና በግሪክኛ *ሚስታጎጊያ* የተሰኘውን ቃል መሠረት አድርጎ የዐረብኛውን አጠራር የተከተለ "እልመስጦአግያ" የተባለ ጽሑፍ ሃይማኖተ አበው ውስጥ ይገኛል። በቤተ ክርስቲያን ስላለው አገልግሎትም መግቢያው ላይ፡- "ያንብብዋ ምእመናን እምቅድመ ቅዳሴ ንጹሕ ለዛቲ ሃይማኖት እልመስጦአግያ - ይችህን [እልመስጦአግያ የተባለች የእምነት መግለጫ] ምእመናን ከቅዳሴ በፊት ያንብቧት"[269] ይላል።

የቅዱስ ቄርሎስ ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያን አምስተኛ ክፍል በ4ኛው ምእት ዓመት ይካሄድ ስለነበረው ሥርዓተ ቅዳሴ አጭርና ጠቅለል ያለ ገለጻን ይሰጠናል፡-

> ዲያቆናቱ የጳጳሱን እጅ ካስታጠቡ በኋላ[270] ዲያቆኑ በተቀደሰ ሰላምታ ሁሉም እጅ እንዲነሳሱ ያዛል። በመቀጠል፥ ጳጳሱ፡- "ልባችሁን (ልቡናችሁን)[271] ከፍ አድርጉ" ሲል፥ "ከእግዚአብሔር ጋር አሉ"[272] ብለው ይመልሱለታል፤ "እግዚአብሔርን እናመስግነው" ሲል ደግሞ፥ "እውነት ነው፥ ይገባል" ብለው ይመልሱለታል። ልዑል እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ፍጥረታት በመዘርዘር ምስጋና ካቀረብን በኋላ፥ የሱራፌልን ዝማሬ እንዘምራለን፤ በመቀጠልም፥ ኅብስቱን የጌታ ሥጋ ያደርገው ዘንድ፥ ወይኑን ደግሞ የጌታ ደም ወደመሆን ይለውጠው ዘንድ መንፈስ ቅዱስን አንዲልክልን እግዚአብሔር አብን በጸሎት እንጠይቃለን። ስለቤተ ክርስቲያን ሰላም፥ በሕመምና በክፉ አገዛዝ ስላሉት ሁሉ የምልጃ ጸሎት አቅርበን፥ ተዝካረ ቅዱሳንን እናስከትላለን፤ በሁለተኛው ክፍል በቅዱሳኑ ጸሎት ልመናችንን ይቀበል ዘንድ እግዚአብሔርን እንማጸነዋለን። እንዲሁም፥ "ስለ ኃጢአታችን የታረደውን ክርስቶስን" መሥዋዕት አድርገን በምናቀርብበት መንፈሳዊ አገልግሎት ከእኛ አስቀድመው ስላረፉ ወገኖቻችን እንጸልያለን። ከዚያም፥ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸውን ጸሎት ከጸለይን በኋላ፥ ጳጳሱ፡- "ቅድሳት ለቅዱሳን" (ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ለቅዱሳን ነው) የሚለውን ጥሪ ሲያውጅ፡- "ቅዱስ፥ አንዱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" ብለው ይመልሱለታል።

---

እሑዶች፡ በአንደኛውና በሦስተኛው) እና በበዓለ ጥምቀት ነው፡፡ ትምህርቱ በቅዳሴ ብቻ ሳይሆን በመደበኛው ዜማ ቤትም በቅዱስ ያሬድ ድርሰት ውስጥ "ምዕራፍ" የሚለው ክፍል ውስጥ ተካትቷል፡፡ ይህም ቅዱስ ያሬድ ጥንታውያን ድርሰቶችን በድርሰት ምንጭነት ይጠቀም አንደነበር ያስረዳናል፡፡

[269] "እልመስጦአግያ"፡ *ሃይማኖተ አበው*፡ ምእራፍ 2፡ ቊ. 2፣ ገጽ 21።

[270] ይህ የቅዳሴ ሥርዓት *lavabo* በሚል ስያሜ ይታወቃል - Jasper and Cuming, p. 85.

[271] እንግሊዝኛው ብዙ ቊጥርን ያመለክታል፡- "[Lift up your] hearts" - Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 85. ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነው የግእዙ ቅዳሴ ሐዋርያት አውሥኦም (Dialogue) በብዙ ቊጥር "አልዕሉ አልባቢክሙ" ይላል፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴ "ቅዳሴ ሐዋርያት" 1994 ቊ. 3፣ ገጽ 87፡፡

[272] "We have them with the Lord" - Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 85.

ወዲያው፥ ዘማሪው፡- "እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ፥ እዩም" የሚለውን የዳዊትን ዝማሬ (መዝ. 33/34 ፥ 8) እየዘመረ ምእመናን ቅዱስ ቍርባንን ይቀበሉ ዘንድ ይጋብዛል። በመጨረሻም፥ ለዚህ ታላቅ ምሥጢር የበቃን ያደረገንን አምላክ በኅብረት እናመሰግናለን።[273]

ይህን የቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌምን ገለጻ በመከተል በ4ኛው ምእት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የነበረው አኰቴተ ቍርባን የሚከተለው ቅደም ተከተል እንደነበረው እንረዳለን፡-

- ተሐፅቦተ እድ (የካህኑ ወይም ጳጳሱ እጅ መታጠብ )
- አምኃ ቅድሳት
- አልዕሉ አልባቢክሙ
- አእኵትዎ ለአምላክነ (አምላካችንን አመስግኑት)
- መቅድም
- ቅድመ ዝማሬ ሱራፌል
- ዝማሬ ሱራፌል
- ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ
- ጸሎት/መስተብቍዕ በእንተ ሕያዋን (በሕይወት ስላሉ ሰዎች የሚቀርብ የልመና ጸሎት)
- ተዝካረ ቅዱሳን
- ጸሎት በእንተ እለ ኖሙ (ስላረፉ ሰዎች የሚቀርብ የምልጃ ጸሎት)
- አቡነ ዘበሰማያት
- ቅድሳት ለቅዱሳን
- መዝሙረ ዳዊት 33 (34)፥ 8
- ተመጥዎ ቍርባን (ቅዱስ ቍርባን መቀበል)
- ቡራኬ።[274]

---

[273] "*Mystagogical Catechesis* 5: 2-23," quoted in Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 85-87 (ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ትርጉም፡ የእኔ)፡፡

[274] Kent J. Burreson, "The Anaphora of the Mystagogical Catecheses of Cyril of Jerusalem," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Bradshaw, p. 138-139.

## አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ባስልዮስ

ከታላላቆቹ ሦስት የቀጰዶቅያ አባቶች[275] አንዱ የሆነው የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያን (+379 ዓ.እ.)[276] ስም የያዙ ሁለት ጸሎታተ ቍርባን አሉ። ቅዳሴ ባስልዮስ ዘቅብጥ[277] የሚል ስያሜ የተሰጠውና በኮፕቲክ ቋንቋ ተጽፎ የተገኘው የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ቅዳሴ ነው። ሌላው ደግሞ ቅዳሴ ባስልዮስ ዘጽርእ[278] የተሰኘው ሲሆን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሚለው የጋራ ስም የሚጠሩ አብያተ ክርስቲያን ለሥርዓተ ቅዳሴ ይጠቀሙበታል። ሁለቱም ቅዳሴያት በቅዱስ ባስልዮስ ስም ቢጠሩም፥ በይዘት ተመሳሳይ አይደሉም። በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች የዚህ አኰቴተ ቍርባን ምንጭ ሶርያ እንደሆነች ሲያመላክቱ[279]፥ ቅዱስ ባስልዮስ በ357 ዓ.እ. ወደ ግብጽ ይዞት እንደመጣ ይታመናል።[280] የ4ኛው ምእት ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ላይ፥ የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት የሚክዱ መናፍቃን[281] ስለተነሡ፥ መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ባሕርይ ከአብና ከወልድ ጋር አንድ መሆኑን በማስረዳት በጥልቀት የጻፈው ቅዱስ ባስልዮስ[282] ከቀጰዶቅያ ይዞት በመጣው ቅዳሴ ላይም የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነትን የሚገልጹ ዐረፍተ ነገሮችን በመጨመር አሻሽሎታል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን የማዳን ሥራንም በዝርዝር በመግለጽ ለቅዳሴው ልዩ ሥነ

[275] Cappadocian Fathers.
[276] የተቀሩት ሁለቱ አባቶች፡- "Gregory the Theologian" (ታኦሎጎስ/ የነገረ መለኮት ሊቅ/ ነባቤ መለኮት) በመባል የሚታወቀው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ (St. Gregory of Nazianzus/ St. Gregory Nazianzene, + 390 ዓ.እ.) እና የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም፥ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (St. Gregory of Nyssa, +395 ዓ.እ.) ናቸው።
[277] Coptic Anaphora of St. Basil.
[278] Byzantine Anaphora of St. Basil.
[279] Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies*, p. 85.
[280] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 67.
[281] Pneumatomachians.
[282] Basil of Caesarea, "De Spiritu Sancto," *A Select Library of Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christian Church*, Vol. 8. Ed. Philip Schaff and Henry Wace. Michigan: Eerdmans Publishing Company, 1989.

ጽሑፋዊ ውበት ሰጥቶታል።[283] ለዚህም ነው ቅዱስ ባስልዮስ ያሻሻለውና በስሙ የሚጠራው የግሪኩ ቅዳሴ፥ ከኮፕቲኩ ቅዳሴ ጋር ሲነጻጸር ሁለት እጥፍ ያህል የሚረዝመው።[284]

በሐዋርያትና በቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም የሚጠሩ አብዛኞቹ ቅዳሴያት (ለምሳሌ፦ ቅዳሴ ማርቆስ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ [የጌታ ወንድም]፥ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ወዘተ.) ሌሎች ሰዎች ደርሰዋቸው እውቅና ለማግኘት ሲባል በቅዱሳኑ ስም የተሰየሙ ሲሆን፥ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ግን ጸሎታተ ቅዳሴን የማዘጋጀት ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው።[285] የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የሚገኘው ቅዳሴ ባስልዮስ በ14ኛው ምእት ዓመት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመ ነው፤ በአተረጓጐም ምክንያት አንዳንድ የቃላት ልዩነቶችን ቢያሳይም ቅዳሴ ባስልዮስ ዘቅብጥ ከተሰኘው የቅዱስ ባስልዮስ አኰቴተ ቍርባን ጋር አንድ ነው። በአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም የቅዳሴ ባስልዮስ ትርጒም የሆነ፥ ነገር ግን የአርመን ቤተ ክርስቲያን አባት በሆነው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን[286] ስም የሚጠራ ቅዳሴ አለ።[287] ቅዱስ ባስልዮስ የብዙ ጸሎታተ ቅዳሴ ደራሲ መሆኑን የሚጠቁሙ የተለያዩ ጸሎቶች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ይገኛሉ። ሠራዒው ካህን፥ በመቅደሱ ውስጠኛ መጋረጃ ፊት አንድ ጊዜ ሰግዶ ራሱን ለቅዳሴው እያዘጋጀ የሚጸልየው ጸሎት "የባስልዮስ ጸሎት" የሚል ርእስ ተሰጥቶታል።[288] "የሁሉን ልቡና የሚያውቅ፥ በቅዱሳንም የሚያድር ቅዱስ እግዚአብሔር ነው" በማለት የሚጀምረውና ሠራዒው ካህን ታቦቱን እያለበሰ የሚጸልየው ጸሎት ደግሞ ከኮፕቲኩ ቅዳሴ ባስልዮስ የዝግጅት ክፍል የተወሰደ

283 "Byzantine Anaphora of St. Basil" የሚለውን ክፍል Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* ገጽ 90 እና 91 ላይ ይመልከቱ።
284 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 114.
285 D. Rishard Stuckwish, "The Basilian Anaphoras," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers*, ed. Bradshaw, p. 109-110.
286 St. Gregory the Illuminator.
287 Stuckwish, "The Basilian Anaphoras," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers*, ed. Bradshaw, p. 111.
288 "ጸሎተ ባስልዮስ ላዕለ ሣዑናት እንዘ ያርኁ"፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ቍ. 23-28፥ ገጽ. 20-21።

ነው።[289] እንዲሁም፥ ሠራዒው ዲያቆን "ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን - የክርስቲያን ታናናሾች [ያልተጠመቃችሁ ሰዎች] ውጡ" ካለ በኋላ ካህኑ የሚጸልየው ጸሎት የቅዱስ ባስልዮስ እንደሆነ መጽሐፈ ቅዳሴው ይጠቁማል።[290] ይህም ከግብፅ ቅዳሴ ባስልዮስ የዝግጅት ክፍል የተወሰደ ነው።[291] በተጨማሪ፥ በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ፦ "ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ"[292]፥ "ጸሎተ ቡራኬ ዘባስልዮስ"[293]፥ "የሰባቱ ዕለታት የነግህ [የጠዋት] ሊጦን፥ ቅዱስ ባስልዮስ የተናገረው"[294] የሚል ርእሶች የተሰጣቸውን ጸሎታት መመልከት ይቻላል።

የቅዳሴ ባስልዮስን አኰቴተ ቍርባን ይዘት ስንመለከት፥ ቅዳሴያት ዘምዕራብ ሶርያ በሚለው የሥርዓተ ቅዳሴ ክፍል ከሚመደቡት መካከል እናገኘዋለን። ከላይ እንደተመለከትነው፥ አብዛኞቹ የግብፅ ቅዳሴያት ከዝማሬ ሱራፌል በኋላ "በእውነት ምስጋናህ በሰማይና በምድር ሞላ" ወይም "ይህን መሥዋዕት በበረከትህ ሙላ" የሚሉ የጸሎት መነሻ ሲኖራቸው፥ ቅዳሴ ባስልዮስ ግን እንደ ሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት "በእውነት እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ አንተ ቅዱስ ነህ" በማለት ይጀምራል።[295] በግሪክኛ *ዲፕቲክስ*[296] የሚባሉት (ላረፉና በሕይወት ላሉት

---

[289] "[ጸሎት] እንዘ ያለብስ ታቦተ ወያስተናብር"፣ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፣ ቍ. 53-56፥ ገጽ. 27-28፤ "The Prayer of Preparation – Liturgy of St. Basil," *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory, and Cyril* (Los Angeles: Coptic Orthodox Diocese of Southern United States, 2001) pp. 78-79.

[290] "[ጸሎት] ዘቅዱስ ባስልዮስ"፣ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 2000፣ ቍ. 2-3፥ ገጽ 87-88።

[291] "The Prayer of the Veil – Liturgy of St. Basil," *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory, and Cyril,* pp. 130-131.

[292] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 2000፣ ቍ. 53-55፥ ገጽ 98-99።

[293] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 10-21፥ ገጽ 103-105።

[294] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 460-474።

[295] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 70.

[296] *Diptychs* የሚለው ስያሜ የተገኘው *Diptichon* ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ መሃል ላይ የተያያዙና የሚታጠፉ ሁለት ሰሌዳዎች መጠሪያ ነው። በክርስትና የመካከለኛው ዘመን ጽሑፎች (Medieval Writings) ውስጥ *Diptychs* የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያረፉ ቅዱሳንና በሕይወት ያሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስሞችን የያዙ ሁለት ሰሌዳዎችን ነው፤ ዲያቆናት ቅዳሴ ላይ በሰሌዳዎቹ የተጻፉትን ስሞች በሙሉ ያነብቡ እንደነበር የሚዘግቡ መረጃዎች አሉ። የመጀመሪያው የአክሱም ኤጲስ ቆጶስ የሆነው የቅዱስ ፍሬምናጦስ ድርሳን ስሙ "ድብዲቆን" (*Diptichon*) ላይ ተጽፎ እንደተገኘ ይናገራል፦ "ዝንቱ ውእቱ ፍሬ፡ምናጦስ አቡነ ቀዳማይ ጳጳስ ለብሔረ አግዓዚ [. . .] ወበዝየኒ ውስተ ድብዲቆን ረከብናሁ ልኩዐ ከመ ቀዳማይ ውእቱ።" Getatchew Haile, "The Homily in Honour of St. Frumentius Bishop of Axum," *Analecta*

አማንያን የሚደረጉት የአኰቴተ ቍርባን የምልጃ ጸሎታት) ቅዳሴ ባስልዮስ ውስጥ የሚገኙት እንደ ሌሎቹ የግብፅ ቅዳሴያት በመቅድሙና በዝማሬ ሱራፌል መካከል ሳይሆን ከጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ነው።[297] እነዚህ የምልጃ ጸሎቶች በቅዳሴ ባስልዮስ በዝተው መታየታቸው በ4ኛው ምእት ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ላይ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተሰጣቸውን ሰፊ ቦታ ያመለክታል። ሌላው የአኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ባስልዮስ መለያ ባሕርይ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቍርባንን የመሠረተባቸውን ቃላት (ሡራዔ ቃል ዘእግዚእነ) ከመዘርዘሩ በፊት ከ1 ጢሞ. 3፥ 16 በመጥቀስ፦ "ይህን እግዚአብሔርን የመምሰል ታላቅ ምሥጢር [ክርስቶስ] ተወልን" ብሎ መጀመሩ ነው።[298] እንዲሁም፥ የቅዱሳን መታሰቢያ ጸሎት በሆነው የአኰቴተ ቍርባኑ ክፍል፥ በሌሎች ቅዳሴያት የማይገኝ ዐረፍተ ነገር አለ፦ "[አምላካችን ሆይ] የዝክረ ቅዱሳንህ ተካፋይ እንሆን ዘንድ የአንድ ልጅህ ትእዛዝ ነው"።[299]

## ቅዳሴ ቀሌምንጦስ ዘሮሜ[300]

ከ360-380 ዓ.እ. ባሉት ጊዜያት ውስጥ እንደተዘጋጀ የሚነገርለት የሥርዓተ አምልኮና የቀኖና መጽሐፍ (ሐዋርያዊ ሕግጋት)፥[301] ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን በመለኮቱ ፍጡር ነው በማለቱ በኒቅያ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ (325 ዓ.እ.) የተወገዘውን የአርዮስንና የተከታዮቹን ኑፋቄያት የሚያንጸባርቁ ገለጻዎች ይገኙበታል። ሐዋርያዊ ሕግጋት በስምንት መጻሕፍት ይከፈላል፤ እያንዳንዱ መጽሐፍም የተለያዩ ምዕራፎችን በውስጡ አካትቷል። ይህ የሥርዓተ አምልኮ መድበል በ364 ዓ.እ. አካባቢ የኪልቂያ ጳጳስ የነበረው ጁሊያን እንዳዘጋጀው

*Bolladiana: Revue Critique D'hagiographie,* Tome 97 (1979) pp. 315-316። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን *Diptychs* በተሰኘው ሰሌዳ ላይ የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ስም ጽፋ ስሙን በቅዳሴ መጥራት አለባት፤ የሊቀ ጳጳሱ ስም ከሰሌዳው የሚፋቀው ቤተ ክርስቲያኒቱ ከእርሱ ጋር ያላትን ኅብረት ማቆሟን ለመግለጽ ብቻ ነው።

[297] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 71።

[298] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 71።

[299] ዝኒ ከማሁ፥ገጽ 72።

[300] The Clementine Liturgy/ Liturgy of the Apostolic Constitutions.

[301] Apostolic Constitutions.

ጠቋሚ መረጃዎች ቢኖሩም፥[302] መጽሐፉ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት እንዲኖረው፥ አባቶቻችን ቅዱሳን ሐዋርያት አዘጋጅተውት የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ለነበረው ለቀሌምንጦስ ዘሮሜ (+99 ዓ.እ.) እንደሰጡት ይናገራል። ለዚህም ነው የሐዋርያዊ ሕግጋት ስምንተኛ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አኰቴተ ቊርባን በቅዱስ ቀሌምንጦስ ስም የተሰየመው። በተጨማሪም ሐዋርያት የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ትእዛዛትን ጽፈው ያስተላለፉ ለማስመሰል "እኛ ሐዋርያት ይህን ብለናል ፥ይህን አዘናል" የሚሉ ምንባባትን በየቦታው እናገኛለን። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊካሄድ ስለሚገባው የአምልኮ ሥርዓት ትእዛዛትን የሚሰጠው የሐዋርያዊ ሕግጋት ሁለተኛ መጽሐፍ፥ 57ኛ ምዕራፍ፥ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተወሰኑት ከተነበቡ በኋላ "የእኛ ሥራዎችም [የሐዋርያት ሥራ የተባለው መጽሐፍ] ይነበቡ . . . ዲያቆኑ ወይም ቄሱ ወንጌላውያኑ ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስና ዮሐንስ ለእናንተ ካስረከቡአችሁ ወንጌላት ያንብብ" ይላል።[303]

በቤተ ክርስቲያናችን "ዲድስቅልያ" ተብሎ የሚጠራው መጽሐፍ፥ በግሪኩ *ዲዳስካሊያ አፖስቶላረም*[304] የተሰኘውና በ3ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ላይ የተዘጋጀው መጽሐፈ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ቀጥተኛ ትርጒም አይደለም። ነገር ግን ሐዋርያዊ ሕግጋት ውስጥ ያሉትን የመጀመሪያዎቹን ስድስት መጻሕፍት ይዘት በመከተል የተዘጋጀው የሶርያው *ዲዳስካሊያ* ትርጒም እንደሆነ የጠቆሙ ምሁራን አሉ።[305] በሶርያው *ዲዳስካሊያ* የማይገኙ አንዳንድ ክፍሎች በግእዙ መገኘታቸውና የግእዙ ትርጒም ከዐረብኛው ጋር መስማማቱ፥ መጽሐፈ ዲድስቅልያ ከዐረብኛው *ዲዳስካሊያ* የተተረጐመ መሆኑን እንድንቀበል ያስገድደናል። በመጽሐፈ ዲድስቅልያ 33ኛው ምዕራፍ ውስጥ የሚገኘው የሐዋርያት አንቀጸ ሃይማኖት[306] የሐዋርያዊ ሕግጋት ስድስተኛ መጽሐፍ፥ ምዕራፍ 11 ውስጥ ይገኛል። የቤተ ክርስቲያናችን

[302] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 100.
[303] *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles): The Work Claiming to Be the Constitutions of the Holy Apostles including the Canons*, eds. Irah Chase and Otto Krabbe (D. Appleton and Company,1848) pp. 64-65.
[304] *Didascalia Apostolarum*.
[305] "Textual Tradition," *The Liturgical Portions of the Didascalia,* ed. Sebastian Brock and Michael Vasey (Bramcote: Grove Books, 1982) ገጽ 5 ይመልከቱ፡፡
[306] Apostolic Creed.

መሠረታውያን ቅዳሴያት[307] የሆኑት ቅዳሴ ሐዋርያትና ቅዳሴ እግዚእ በሚቀደሱበት ጊዜ ሊቃውንት አባቶቻችን የሐዋርያት አንቀጸ ሃይማኖት (አመክንዮ) እንዲነበብ ያደረጉበት ምክንያት ቅዳሴያቱና አንቀጸ ሃይማኖቱ የተዘጋጁባቸውን ተቀራራቢ ጊዜያት (4ኛው-5ኛው ምእት ዓመት) ከግንዛቤ በማስገባት ይመስላል።[308] መጽሐፈ ዲድስቅልያ ከስምንተኛው የሐዋርያዊ ሕግጋት መጽሐፍ የወሰደው ምንም ነገር ስለሌለ፥ እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውና በቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮሜ ስም የተሰየመው ቅዳሴ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አይታወቅም።

በ4ኛው ምእት ዓመት ስለነበረው አጠቃላይ ሥርዓተ አምልኮና የአኰቴተ ቍርባን ዓይነት ግንዛቤ የሚሰጡን የሐዋርያዊ ሕግጋት ክፍሎች፦ ሁለተኛው፥ ሰባተኛውና ስምንተኛው መጻሕፍት ናቸው። ሁለተኛው መጽሐፍ በአብዛኛው የ3ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ሥራ የሆነውን የግሪኩን ዲዳስካሊያ ይዘት ይዘረዝራል።[309] ሰባተኛው መጽሐፍ ደግሞ፥ የመጀመሪያው ምእት ዓመት መጽሐፈ ሥርዓተ አምልኮ የሆነው ዲዳኬን አስፋፍቶ ከማቅረብ ባሻገር አንዳንድ የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ ጸሎታትን ይዟል።[310] የዚህ መጽሐፍ 57ኛ ምዕራፍ፦ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲተከል የመቅደሱ አቅጣጫ በምሥራቅ በኩል መሆን እንዳለበት፥ ሕንጻው በመርከብ ቅርጽ መሠራት እንደሚገባውና በቅዳሴ ጊዜ ሊነበቡ ስለሚገባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ይነግረናል።[311]

ስምንተኛው መጽሐፍ በ4ኛው ምእት ዓመት የነበረውን ሥርዓተ ቅዳሴና በወቅቱ አገልግሎት ላይ ይውል የነበረውን ሙሉ አኰቴተ ቍርባን ያስነብበናል። የመጽሐፈ

---

307 "Foundational anaphoras" - Spinks, *Do This in Remembrance of Me,* p. 173.

308 በተጨማሪ ቅዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ በሚቀደሱበት ጊዜም የሐዋርያት አንቀጸ ሃይማኖት (Apostolic Creed) በገባሬ ሠናይ ዲያቆኑ አማካኝነት መነበብ እንዳለበት መጽሐፈ ቅዳሴ ያዛል። በ4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመታት በነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም የተደረሱት ቅዳሴያት በሚቀደሱበት ጊዜ፥ የተወሰነው ክፍል በኒቅያ ጉባኤ (325 ዓ.እ.) ተዘጋጅቶ በቍስጥንጥንያ ጉባኤ (381 ዓ.እ.) የተጠናቀቀውና ዓለም አቀፋዊው ጸሎተ ሃይማኖት/አንቀጸ ሃይማኖት (Niceo-Constantinopolitan Creed) በኅብረት ይጸለያል። መጽሐፈ ቅዳሴ፥ "ጸሎተ ሃይማኖት" ቍ. 1-10፣ ገጽ 219-220።

309 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 100.

310 ዝኒ ከማሁ።

311 *The Apostolic Constitutions,* pp. 64-65.

ቅዳሴው የመጀመሪያ ክፍል ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ ላሉ ክርስቲያኖች (ንኡሰ ክርስቲያን) የሚደረገውን ሥርዓተ ጸሎት ይዟል።[312] ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል የተዘጋጁ ምእመናን የሚሳተፉበት የአማንያን ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት ንኡሰ ክርስቲያንና በንስሐ ውስጥ ያሉ ሰዎች ይሰናበታሉ።[313] አኰቴተ ቍርባኑ በአብዛኞቹ የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ላይ እንደምናገኘው፡- "የእግዚአብሔር ጸጋ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት (አንድነት) ከሁላችሁ ጋር ይሁን" በሚለው የጳጳሱ ሰላምታ ይጀምራል።[314] መቅድሙ፥ "ከፍጥረታት በፊት የነበረውን ሕያው እግዚአብሔርን ማመስገን በእውነት ይገባል" በማለት ይጀምርና እጅግ ድንቅ በሆነ መልኩ በልዑል እግዚአብሔር የተፈጠሩ ፍጥረታት ገለጻን ያቀርባል።[315] በቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮሜ ስም የተሰየመው አኰቴተ ቍርባን የተቀሩት ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡- የዝማሬ ሱራፌል መግቢያና የመላእክቱ ዝማሬ፥ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ፥ ዝክረ ሞቱ ለእግዚእነ፥ አግብዖተ ግብር፥ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ፥ መስተብቍዓት/ የምልጃ ጸሎቶች ፥ ስባሔ/የማጠቃለያ ምስጋና (*ዶክሶሎጂ*) እና አሜን።

## ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም)

በአራተኛው ምእት ዓመት በኢየሩሳሌም ይካሄድ የነበረውን የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ከሚያሳዩን ምንጮች መካከል ቅዳሴ ያዕቆብ ዋነኛው ነው። ይህ ቅዳሴ "የጌታ ወንድም" እየተባለ በሚጠራውና በኢየሩሳሌም የተደረገው የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሊቀ መንበር (የሐዋ. 15፥13) በነበረው በሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስም መሰየሙ በጣም ጥንታዊ ቅዳሴ ተደርጎ እንዲወሰድ አድርጎታል። ነገር ግን የቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያንን እና ቅዳሴ ባስልዮስን መሠረት በማድረግ ቅዳሴ ያዕቆብን የማሻሻል ሥራ በ4ኛው

[312] "Mass of the Catechumens," *The Liturgy of the Eighth Book of 'The Apostolic Constitutions' Commonly Called the Clementine Liturgy,* trans. R. H. Cresswell, (London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1924) pp. 36-54.
[313] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 46።
[314] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 104.
[315] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 104-108።

ምእት ዓመት እንደተጠናቀቀ የጥንት ቅዳሴያት አጥኚዎች ያስረዳሉ።[316] ለዚህም ማስረጃው፥ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ በተሰኘው የአኰቴተ ቍርባኑ ክፍል የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት በግልጽ የሚያሳዩ ምንባባት መገኘታቸው ነው። እንደዚህ ዓይነት ምንባባት ቅዳሴው ውስጥ ሊጨመሩ የሚችሉት፥ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የካዱ ሰዎች ከተወገዙበት ዓለም አቀፋዊው የቍስጥንጥንያ ጉባኤ (381 ዓ.እ.) በኋላ እንደሆነ ግልጽ ነው።[317] ከቅዳሴ ማርቆስ ተወስደው ቅዳሴ ያዕቆብ ውስጥ የገቡ አንዳንድ ጸሎታት እንዳሉ ሁሉ፥ ቅዳሴ ማርቆስ በቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ አማካኝነት መጠነኛ ማሻሻል ሲደረግለት እንደ አብነት የተወሰደው ቅዳሴ ያዕቆብ ነበር። ከኢየሩሳሌም ውጪ ባሉት አብያተ ክርስቲያን የያዕቆብ ቅዳሴ እስከ 12ኛው ምእት ዓመት ድረስ አገልግሎት ላይ ይውል የነበረ ቢሆንም፥ ከዚያ በኋላ ግን በሌሎች ቅዳሴያት እየተተካ መጥቷል።[318]

ቅዳሴ ያዕቆብ ወደ ግእዝ ተተርጕመው በብራና ከሚገኙትና እስካሁን ድረስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ. ካላሳተመቻቸው ስድስት ቅዳሴያት[319] መካከል አንዱ ነው። የቫቲካን ማተሚያ ቤት በ1945 ዓ.እ. በቤተ ክርስቲያናችን ከታተሙት 14 ቅዳሴያት በተጨማሪ፦ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መዓዛ ቅዳሴን፥ ቅዳሴ ማርቆስንና ቅዳሴ ያዕቆብን (አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ በሚል ርእስ) አሳትሟል። እነዚህንና በብራና ያሉትን ተጨማሪ ሦስት ቅዳሴያት ቤተ ክርስቲያናችን አሳትማ አገልግሎት ላይ ቢውሉ መልካም ነው፤ እስካሁን ድረስ የኅትመት ብርሃንን ያላዩበት ምክንያት ግልጽ አይደለም። የግእዙ ቅዳሴ ያዕቆብ ከእንግሊዝኛው ጋር ሲነጻጸር፥ የግእዙ ተርጓሚዎች ለእነርሱ እንግዳና አስቸጋሪ የመሰሏቸውን ክፍሎች እንደዘለሏቸው በቀላሉ እንረዳለን። ለምሳሌ፥ የምሥራቅና ምዕራብ ሶርያ (አንጾኪያ) ቅዳሴያት መለያ ባሕርይ ከዝማሬ ሱራፌል ጋር "ሆሣዕና በአርያም፥ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው" የሚለውን መዝሙር

---

[316] Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p. 162.

[317] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 93.

[318] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 88.

[319] የተቀሩት አምስቱ፦ ቅዳሴ ማርቆስ ወንጌላዊ፥ መዓዛ ቅዳሴ፥ ቅዳሴ ቄርሎስ ካልእ፥ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ [ዘአርማንያ] እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ናቸው። በእነዚህ ቅዳሴያት ላይ አጭር ግንዛቤ ለማግኘት፦ Ernest Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras* (Stuttgart : Franz Steiner Verlan Wiesbaden GMBH, 1987) ገጽ 13-33 ይመልከቱ።

ማካተት ነው። ቅዳሴ ያዕቆብ የሚመደበው ከምዕራብ ሶርያ ሥርዓተ ቅዳሴ ወገን ስለሆነ ሁለቱንም ዝማሬያት አጣምሮ ይዟል።[320] የግእዙ ቅዳሴ ያዕቆብ ግን የተለመደውን ዝማሬ ሱራፌል፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ፥ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ" ብቻ ያስነብበናል።[321] የግብፅ ቅዳሴያት የመጀመሪያውን ዝማሬ ብቻ እንጂ ሁለቱን ዝማሬያት አጣምረው ስለማይዙና ኢትዮጵያውያን ተርጓሚዎቹ ደግሞ ይበልጥ የሚተዋወቁት ከግብፅ ቅዳሴያት ጋር ስለሆነ ሁለተኛውን ዝማሬ ሳይተረጉሙት አልፈውታል።

ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ከተሰኘው የአኰቴተ ቍርባን መሠረታዊ ክፍል ቀጥሎ ተዝከረ ቅዱሳንን እና የምልጃ ጸሎትን ማቅረብ በሶርያ ቅዳሴያት የተለመደ ቅደም ተከተል ነው። ቅዳሴ ያዕቆብም ይህን ቅደም ተከተል ይጠብቃል። የግእዙ ቅዳሴ ያዕቆብ ግን የተወሰኑትን የምልጃ ጸሎቶች ይተረጉምና አብዛኛዎቹን በመተው መሃል ላይ "በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ …" የሚለውን የምልጃ ጸሎት ከቅዳሴ ሐዋርያት አምጥቶ ያስገባል።[322] የግእዙ መተርጉማን በዚህ መልኩ የማይፈልጉትን ክፍል አውጥተው ለምን እንደተረጎሙ የቅዳሴ ያዕቆብን እንግሊዝኛ ትርጉም ስናነብ ግልጽ ይሆንልናል። የቅዳሴው ተዝካረ ቅዱሳን በምሥራቁም ሆነ በምዕራቡ ዓለም ተቀባይነት ያላቸውን የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ያነሣል፤ ከእነዚህ መካካል የሮሙ ፓፓ ልዮን[323] አንዱ ነው።

እንዲሁም የእኛን ቤተ ክርስቲያን ጨምሮ፥ የአርመን፥ የግብፅ፥ የኤርትራ፥ የሶርያ እና የማላንካራ (የሶርያ ቤ/ክ በሕንድ) አብያተ ክርስቲያን የሚቀበሏቸውን ሦስቱን ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት (ኒቅያ፥ 325 ዓ.እ.፤ ቍስጥንጥንያ፥ 381 ዓ.እ.፤ ኤፌሶን 431 ዓ.እ.) ብቻ ሳይሆን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን የሚቀበሏቸውን ተጨማሪ ሦስት ጉባኤያት ጠቅሶ፡- "ጌታ ሆይ፥ ስድስቱን ቅዱሳት እና ዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት አስብ"[324] ይላል። ኢትዮጵያውያኑ ተርጓሚዎች፥ የማይቀበሏቸውን ጉባኤያት በግእዙ ትርጉም ውስጥ መጥቀስ አልፈለጉም ማለት ነው። በሌላ በኩል

---

[320] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 91.

[321] "ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ," *Missale Ethiopicum,* p. 108.

[322] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 112።

[323] Pope Leo.

[324] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 91.

ደግሞ፥ የቅዳሴ ያዕቆብ ረጅም የልመና ጸሎት ስድስተኛው ጉባኤ ከተካሄደበት ዓመት (681 ዓ.እ.) በኋላ የተጨመረ ስለሆነ፥ የግእዙ መተርጉማን ለትርጉማቸው የተጠቀሙበት ምንጭ ጭማሬው የሌለበትን (ከስድስተኛው ጉባኤ በፊት የነበረውን) ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሁሉ ነጥቦች የግእዙ ቅዳሴ ማርቆስም ሆነ ቅዳሴ ያዕቆብ ብርቱ ጥናት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጥንታውያን ምንጮች እንደሆኑ በግልጽ ያመለክቱናል።

## ቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያ

የምዕራብ ሶርያ ሥርዓተ አምልኮ ክፍል ውስጥ ከሚመደቡት ቅዳሴያት መካከል አንዱ፥ በቅዱሳን ሐዋርያት አባቶቻችን ስም የተሰየመው ቅዳሴ ነው። ይህ ቅዳሴ፥ የቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊ አኰቴተ ቍርባን ከሆነው ቅዳሴ ሐዋርያት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። ቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያ መጀመሪያ የተጻፈው በግሪክ ነበር፤ በአሁኑ ጊዜ ግን የሚገኘው በሱርስት (ሶርያ) ቋንቋ ብቻ ነው።[325] ቅዳሴው በ350 ዓ.እ. አካባቢ እንደተደረሰ ይታመናል፤ ከቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ጋር ያለው ተቀራራቢነትም ሁለቱ ቅዳሴያት ከአንድ ምንጭ መቀዳታቸውን እንደሚያመለክት ምሁራኑ ይስማማሉ።[326] ከቅዳሴ ያዕቆብና ከቅዳሴ ባስልዮስ ተወስደው ቅዳሴ ሐዋርያት ውስጥ የገቡ አንዳንድ ጸሎታት እንዳሉ ጠቋሚ ምልክቶች በቅዳሴው ውስጥ ይታያሉ።

የቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያን ይዘት ስንመለከት፥ ከቅዳሴ ያዕቆብ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ፦ "የእግዚአብሔር አብ ፍቅር፥ የአንድያ ልጁ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን" በሚለው የሠራዒው ካህን ሰላምታ ይጀምራል። የመቅድሙ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ለቅድስት ሥላሴ የቀረበ ምስጋና ነው፦ "እውነተኛ አምላክ የሆንክ አንተን፥ አንድያ ልጅህን እና መንፈስ ቅዱስን እናመሰግንና እናመልክ ዘንድ በእውነት ይገባል"፡፡[327] ይህ ለሥሉስ ቅዱስ የቀረበና ዕሩይ የሆነ (የተካከለ) ምስጋና በ4ኛው

[325] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 124.
[326] ዝኒ ከማሁ፤ Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p. 98.
[327] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 125.

ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ የገባ እንደሆነ ግልጽ ነው።[328] ምክንያቱም፥ እንደዚህ ዓይነት ምስጋና በአኰቴተ ቍርባን ውስጥ በአብዛኛው የሚስተዋለው የወልድን እና የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ለካዱ መናፍቃን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ጉባዔያትን ጠርታ መልስ ከሰጠችበት ጊዜ (ከ381 ዓ.እ. በኋላ) ነውና።

ከመቅድሙ ቀጥሎ የተለመዱት የአኰቴተ ቍርባን ክፍሎች፦ ቅድመ ዝማሬ ሱራፌልና ዝማሬው፥ ድኅረ ዝማሬ ሱራፌል እና ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ ተራቸውን ጠብቀው ተቀምጠዋል። የቅዳሴ ሐዋርያት *አናምኔሲስ*[329] (ዝክረ ሞቱ ለእግዚእነ) ግን ከሌሎች ቅዳሴያት ለየት ባለ መልኩ የጌታን ሕማም፥ ሞትና ትንሣኤ እያሰብን የቅዳሴውን መሥዋዕት እንደምናቀርብ ግልጽ በሆነ መልኩ አያሳይም። ለምሳሌ ቅዳሴ ያዕቆብ፦ "ሕይወት ሰጭ የሆነውን መከራውን [የጌታን]፥ ሞቱን፥ በሦስተኛው ቀን ከሙታን መነሣቱን፥ ዕርገቱን፥ በአንተ በአባቱ ቀኝ መቀመጡን እና ግሩም የሆነ ዳግም ምጽአቱን እያሰብን አምላክ ሆይ ይህን መሥዋዕት እናቀርብልሃለን" ይላል።[330] ቅዳሴ ሐዋርያት ግን የጌታችንን የማዳን ሥራ (ሕማሙን፥ ስቅለቱን፥ ትንሣኤውን፥ ዕርገቱን፥ በአብ ቀኝ መቀመጡንና ዳግም ምጽአቱን) እያወጀ ይህን ሁሉ እንደምናስብ ቢጠቅስም "ይህን ሁሉ እያሰብን መሥዋዕት እናቀርብልሃለን" ግን አይልም።

በሌላ አገላለጽ፥ የጌታን የማዳን ሥራ ማሰብንና ማወጅን መሥዋዕት ከማቅረብ ጋር (አግብኦተ ግብር) አያገናኘውም። የቅዳሴው *አናምኔሲስ* የሚያመለክተው ምስጋና ማቅረብን ብቻ ነው፤ ይህንን ሁሉ እያሰብን "አንተን እናመሰግናለን፥ ስለሁሉም ነገርና ስለሰዎች በሙሉ አንተን እናውጃለን" ይላል።[331] ነገር ግን ቅዳሴው ጨርሶ መሥዋዕት ስለማቅረብ ምንም ነገር አይናገርም ማለት አይደለም። መሥዋዕቱ የጌታን ሕማምና ሞት ከማሰብ ጋር ተያይዞ የሚነገርበት ትክክለኛ ቦታ ላይ ባይጠቀስም፥ ከጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ (*ኤፒክሌሲስ*) ቀጥሎ፦ "ሁሉን ቻይ

[328] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 124.

[329] ከላይ ገጽ 55፥ ኅዳግ ቍጥር 20 ይመልከቱ፡፡

[330] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 92።

[331] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 126።

አምላክ ሆይ፥ ይህን መሥዋዕት እናቀርብልሃለን" የሚል ንባብ እናገኛለን።[332] መሥዋዕቱም የሚቀርበው ስለ አንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለካህናቱና ዲያቆናቱ እንዲሁም አማኞች ስለሆኑ ሰዎች (ምእመናን) መሆኑን ያስረዳል። በመጨረሻም የቅዳሴው ተዝካረ ቅዱሳን የሰማያዊቷ እና ድል አድራጊዋ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑትንና በዐጸደ ነፍስ ያሉትን ቅዱሳን ያነሣል።[333]

## ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ (+407 ዓ.እ.) የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት በነበረበት ጊዜ ይጠቀምበት የነበረውን ቅዳሴ (ቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያ) ይዞ በ398 ዓ.እ. ወደ ቍስጥንጥንያ እንደሄደ ምሁራኑ ባደረጓቸው ጥናቶች አረጋግጠዋል።[334] ዮሐንስ አፈ ወርቅ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ከሆነ በኋላ ሌላ ቅዳሴ መድረስ አላስፈለገውም፤ ይዞት የመጣው ቅዳሴ ላይ አንዳንድ ማሻሻያዎች አድርጎ ይጠቀምበት ነበር። ስለሆነም እርሱ ያሻሻለው ቅዳሴ በስሙ ተጠራ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያትን ምንጭና ደራስያን በምናጠናበት በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር እንደምንመለከተው፥ በሌሎች ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን የሚታወቀው ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ተመሳሳይ ስም ካለው የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ጋር ፈጽሞ አይገናኝም። እስከ 11ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ድረስ የቍስጥንጥንያ ዋነኛ ቅዳሴ የነበረው ቅዳሴ ባስልዮስ፥ በይዘት ከቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሁለት እጥፍ ይረዝማል።[335] አጠር በማለቱ ይመስላል፥ የዮሐንስ አፈ ወርቅ ቅዳሴ ከ1000 ዓ.እ. በኋላ የቅዳሴ ባስልዮስን ቦታ ተክቷል። በአሁኑ ሰዓት ሥርዓተ ቅዳሴ ዘጽርእ[336] የተሰኘውን ሥርዓተ አምልኮ በሚከተሉ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ

[332] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 127።
[333] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 128።
[334] Robert F. Taft, "St. John Chrysostom and the Byzantine Anaphora that Bears His Name," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Bradhshaw, 195; Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies*, 98.
[335] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 125.
[336] Byzantine Liturgical Rite.

ክርስቲያን ሁለቱም ቅዳሴያት አገልግሎት ላይ ይውላሉ፤ ነገር ግን፥ በዓመቱ አብዛኛዎቹ ቀናት የሚመረጠው ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው።[337]

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካላቸውና ከታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል አንዱ የሆነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ በስሙ በሚጠራው ቅዳሴ ውስጥ የእርሱ ድርሻ እንዳለበት የሚጠቁሙ ምልክቶች አሉ። በቅዳሴው የተጠቀሱት የትምህርተ ሥላሴ እና የነገረ ክርስቶስ ክፍሎች፥ ይህ ታላቅ አባት የጨመራቸው እንደሆኑ በግልጽ ያመላክታሉ።[338] ለምሳሌ፥ መግቢያው ላይ ምስጋና እና አምልኮ የሚቀርብለትንና በአንድነት እና በሦስትነት የሚመለከውን አምላክ “የማይመረመር፥ ሊረዱት የማይቻል፥ የማይታይና ከአእምሮ በላይ የሆነ” ሲል ይገልጸዋል።[339] በመለኮታዊ ባሕርዩ ሊታወቅ የማይችለውንና በፍጥረቱ በኩል ራሱን የገለጸውን አምላክ እነዚህን በመሰሉ አሉታዊ ቃላት የመግለጽን ነገረ መለኮታዊ መንገድ የሚከተለው የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን አስተምህሮ *አሉታዊ ነገረ መለኮት*[340] ይባላል። የዚህ አስተምህሮ ዋነኛ አሳብ፥ ልዑል እግዚአብሔር በፍጡራን ፈጽሞ ሊታወቅና ሊመረመር ስለማይችል እኛ ዘወትር በምንጠቀምባቸው አዎንታዊ ቃላት (መልካም፥ ቸር፥ መሐሪ ወዘተ.) ከመግለጽ ይልቅ፥ የአእምሮአችንን ውሱንነት በማሳየት ከላይ በተዘረዘሩት አሉታዊ ቃላት መግለጽ ይሻላል የሚል ነው። በተጨማሪም ይህ አስተምህሮ፥ አለማወቃችንን በማመንና ከማይመረመረው አምላክ ጋር ምሥጢራዊ ግንኙነት[341] በማድረግ እርሱን በተሻለ መልኩ የመረዳት ደረጃ ላይ እንደርሳለን የሚል አመለካከት አለው።[342] ኦርቶዶክሳውያን የነገረ መለኮት ምሁራን ለዚህ አስተምህሮ አብነት አድርገው ከሚጠቅሷቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል፥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይገኝበታል።

---

337 Stuckwisch, “The Basilian Anaphoras,” p. 109.
338 Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies*, 98.
339 እንግሊዝኛው የተጠቀመው፡- “ineffable, inconceivable, invisible, incomprehensible” የሚሉ ቃላትን ነው - Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 132.
340 Apophatic Theology.
341 Mystical union.
342 ይህን የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን አስተምህሮ ይበልጥ ለመረዳትና በአንጻሩ “Cataphatic theology” ከተሰኘው የምዕራባውያን ምልከታ ጋር ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ ይህን መጽሐፍ ይመልከቱ፡- Vladimir Lossky, *The Mystical Theology of the Eastern Church*, London: James Clarke and Co. Ltd., 1957.

በቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያ ላይ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ካደረጋቸው ማስተካከያዎች መካከል፥ ከላይ ያየነውን የቅዳሴውን *አናምኔሲስ* (ዝክረ ሞቱ ለእግዚእነ) መሥዋዕት ከማቅረብ ጋር ማገናኘት ነው። የመድኃኒታችንን የማዳን ሥራ ከዘረዘረ በኋላ፥ ይህንን እያሰብን "ከአንተ የሆነውን ለአንተ፥ ስለሁሉም እናቀርባለን" ይላል።[343] የቅዳሴ ሐዋርያት *ኤፒክሌሲስ* (ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ) መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና በጽዋው ላይ የሚወርድበትን ምክንያት በግልጽ አይናገርም። የዚህ ጸሎት የአማርኛ ትርጒም የሚከተለው ነው፦

> *ሁሉን ማድረግ የምትችል ጌታና የቅዱሳን ኃይላት አምላክ ሆይ…ቅዱስ መንፈስህን በፊትህ ባቀረብነው መሥዋዕት ላይ ትልክ ዘንድ እንለምንሃለን፤ ይህ ኅብስት ክቡር የሆነውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ፥ ጽዋው ደግሞ ክቡር ደሙን መሆኑን ያሳይ ዘንድ።*[344]

"ያሳይ ዘንድ" የሚለው ቃል ግልጽ አይደለም፤ እግዚአብሔር አብ መንፈስ ቅዱስን እንዲልክ የሚጠየቀው ኅብስቱን የጌታ ሥጋ፥ ወይኑን ደግሞ የጌታ ደም ያደርገው (ይለውጠው) ዘንድ ነው። ስለዚህ የተለመደው አገላለጽ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት "ይረስዮ - ያደርገው ዘንድ"[345] ወይም በአብዛኞቹ የውጪ ቅዳሴያት የእንግሊዝኛ ትርጒሞች እንደምናየው "ይለውጠው ዘንድ" የሚል ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ቅዳሴ ሐዋርያት ዘሶርያ *ኤፒክሌሲስ* ውስጥ ግልጽ ያልሆነውን ቃል በማሻሻል በዚህ መልኩ አስተካክሎታል፦ "መንፈስ ቅዱስን በእኛ ላይና በመሥዋዕቱ ላይ ትልክ ዘንድ እንለምንሃለን፤ ይህንን ኅብስት ለውጦ የመሢሕህን (የክርስቶስህን) ክቡር ሥጋ ያደርገው ዘንድ፥ በጽዋው ውስጥ ያለውንም (ወይኑን) ለውጦ የመሢሕህን (የክርስቶስህን) ክቡር ደም ያደርገው ዘንድ"።[346] ይህ ቅዱስ አባት ያደረገው ለውጥ፥ ጸሎቱን ግልጽ ከማድረግ በተጨማሪ፥ መንፈስ ቅዱስ እንዲላክ የሚጠየቀው መሥዋዕቱን ለማክበር በኅብስቱና በወይኑ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይቀደሱ ዘንድ በቅዳሴው ተሳታፊዎችም ላይ እንደሆነ ያስተምረናል።

---

343 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 133.

344 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 127።

345 በምእራፍ አንድ፥ ገጽ 15 እና 16 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

346 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 133.

## ፬. የ5ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው፥ የመጀመሪያው ምእት ዓመትን የቃላት ጸሎት ትውፊትና በ2ኛውና 3ኛው ምእት ዓመታት የነበሩ መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት በማድረግ ቅዳሴያት በብዛት የተደረሱት በ4ኛው ምእት ዓመት ነበር። ወደሚቀጥለው ምእት ዓመት ስንሻገር የምናገኘው፥ የቀድሞ ቅዳሴያትን አስፋፍቶ የማዘጋጀት ሥራ ብቻ ነው። በዋነኝነት ሐዋርያዊ ትውፊት የተሰኘው መጽሐፈ ሥርዓት ውስጥ ያለውን አኰቴተ ቍርባን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ሁለት ቅዳሴያትን እናገኛለን። አንደኛው፥ አስቀድሞ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈው ከጠፋ በኋላ በሶርያ ቋንቋ ብቻ የተገኘው መጽሐፈ ኪዳን[347] ውስጥ ያለው አኰቴተ ቍርባን ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ክፍለ-አኰቴተ ቍርባን[348] የሆነና በቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘሰላሚስ ስም የተሰየመ ነው።

### አኰቴተ ቍርባን ዘመጽሐፈ ኪዳን (ቅዳሴ እግዚእ)

መጽሐፈ ኪዳን በ5ኛው ምእት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ሶርያ ውስጥ እንደተዘጋጀ በእርሱ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይስማማሉ።[349] የመጀመሪያው ዝግጅት በግሪክ ቋንቋ ነበር፤ ግሪኩ ከጠፋ በኋላ የተገኘው ወደ ሱርስት (የሶርያ ቋንቋ) የተተረጐመው ነው።[350] መጽሐፈ ኪዳን፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ሐሳዊ መሢሕ እና ስለ መጨረሻው ዘመን የነገራቸውን የዳግም ምጽአቱን ምልክቶች፥ ስለ ሐዋርያት አገልግሎት፥ ስለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን (የጳጳሳት፥ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሢመት)፥ ስለ ሥርዓተ ጥምቀትና ቍርባን ዝርዝር መግለጫዎችን የሚሰጥና የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ጸሎታት ሰብስቦ የያዘ በጣም

347 *Testamentum Domini* (Testament of the Lord).
348 Paleo-anaphora.
349 Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 138.
350 የሶርያውን ቅጂ James Cooper እና Arthur Maclean ወደ እንግሊዝኛ ተርጕመውታል፡- *The Testament of Our Lord*: *Translated into English from the Syriac with Introduction and Notes*, trans. James Cooper and Arthur John Maclean, Edinburgh: T. & T. Clark, 1902.

ጠቃሚ የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ ነው።[351] በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ በዝርዝር እንዳየነው፥ በሂጶሊጦስ (አቡሉዲስ) ዘሮሜ ስም የተደረሰው ሐዋርያዊ ትውፊት በ3ኛውና 4ኛው ምእት ዓመታት የነበረውን ሥርዓተ አምልኮ ለማጥናት እንደሚረዳን ሁሉ፥ መጽሐፈ ኪዳን ደግሞ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያሉ ጸሎታትን አስፋፍቶ የያዘ ስለሆነ በቀጣዩ ምእት ዓመት (5ኛው ምእት ዓመት) የክርስትናው ሥርዓተ አምልኮ የደረሰበትን ደረጃ ለመረዳት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። እንደ መጽሐፈ ኪዳን፥ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ስለዳግም ምጽአቱ የነገራቸውን ምልክቶች በዝርዝር የያዘ ነገር ግን የሥርዓተ ጥምቀትና ቍርባን ጸሎታት የሌሉት "መጽሐፈ ኪዳን ዘገሊላ" የሚል ርእስ የተሰጠው ሌላ መጽሐፍ አለ።[352]

የ5ኛው ምእት ዓመት ሥራ የሆነው የመጽሐፈ ኪዳን አኰቴተ ቍርባን፥ በ4ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት ውስጥ የሚገኘው ዝማሬ ሱራፌል የለውም። መግቢያው ላይ "ነአኵተከ አምላከ ቅዱስ ፈጻሜ ነፍስነ ወሀቤ ሕይወትነ ዘኢይማስን መዝገብ"[353] ይልና እግዚአብሔር አብ፥ አንድ ልጁን ወደ ድንግል ማርያም ማኅፀን ልኮት፥ ወልደ እግዚአብሔር ያደረገውን የማዳን ሥራ ከዘረዘረ በኋላ፥ በሰማይ ስላለው የሱራፌል ዝማሬ ምንም ዓይነት ገለጻ ሳያቀርብና ዝማሬውንም ሳያካትት መድኃኒታችን ሥርዓተ ቍርባንን ወደ መሠረተባቸው ቃላት ዝርዝር (ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ) ይገባል።[354] አስተዋዮቹ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ቅዳሴ እግዚእን ሲያዘጋጁ ግን፥ የጎደለውን ክፍል (ዝማሬ ሱራፌል) – "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ"[355] – ሞልተው እንደሆነ ልብ እንበል።

[351] Robert Beylot በግእዝ እና በፈረንሳይኛ ያሳተመውን ይመልከቱ፦ *Testamentum domini éthiopien: Édition et traduction*, ed and trans. Robert Beylot, Louvain: Peeters, 1984.

[352] *Le Testament en Galilée de Notre-Seigneur Jésus Christ*, PO*,* Vol. 9, trans. L. Guerrier and S. Grébaut, (Paris: Firmin-Didot, 1913) pp. 177-232.

[353] የቅዳሴ እግዚእ አማርኛ ትርጉም፦ "ቅዱስ አምላክ ሆይ እናመሰግንሃለን፤ ነፍሳችንን ፍጽምት የምታደርግ፥ ሕይወታችንን የምትሰጥ፥ የማይጠፋ መዝገብ" ይላል። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 18፣ ገጽ 146።

[354] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 35-37.

[355] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ እግዚእ"፡ ቍ. 31 ገጽ 148 ይመልከቱ።

የግእዙ መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ ያለውን አኰቴተ ቍርባን በሌሎች ቋንቋዎች ከተተረጐሙት ጋር ስናነጻጽር መጠነኛ ልዩነቶች ይስተዋላሉ። የቅዳሴው አውሥኦ (ምልልስ) በጥንታውያን ቅዳሴያት የምናገኘውን ቅደም ተከተል ይጠብቃል[356]፡-

- ኤጲስ፡ ቆጶስ፡- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ (እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን)።[357]
- ሕዝብ፡- ምስለ መንፈስከ (ከመንፈስህ ጋር)።
- ኤጲስ፡ ቆጶስ፡- አልዕሉ አልባቢክሙ (ልቡናችሁን ከፍ አድርጉ)።
- ሕዝብ፡- ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ (በአምላካችን እግዚአብሔር ዘንድ አለን)[358]።
- ኤጲስ፡ ቆጶስ፡-[ነ]አኵቶ ለእግዚአብሔር (እግዚአብሔርን እናመስግነው)።
- ሕዝብ፡- ርቱዕ ወጽድቅ ይደሉ (እውነት በእውነት ይገባል)።[359]

እንደ እንግሊዝኛው ትርጉም ኤጲስ፡ቆጶሱ ቀጥሎ የሚለው "ቅድሳት ለቅዱሳን"[360] ነው። ሮበርት ባይሎ ያገኘው ብራና ላይ ግእዙ "ቅድሳት በቅዱሳን" ቢልም፥ አርታዒው ግን ኅዳጉ ላይ "ቅድሳት ለቅዱሳን" ብሎ አርሞታል።[361] ይህ ግን ምእመናን ቅዱስ ቍርባንን እንዲቀበሉ የሚጋብዝ ጥሪ ስለሆነ፥ የተለመደው ቦታው የአኰቴተ ቍርባኑ መጨረሻ ላይ ነው። ለዚህም ይመስላል የቅዳሴ እግዚእ አዘጋጆች "ቅዱስ በቅዱሳን"[362] ሲሉ የቀየሩት፤ እውነትም ቀጥሎ ከሚመጣው የሕዝቡ መልስ፡- "ወትረ በሰማይ ወበምድር" ጋር አብሮ ይሄዳል። አባቶቻችን መተርጕማን አብራርተው እንደጻፉልን፥ ፍጹምና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር

[356] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 35. ቅዳሴ እግዚእ ውስጥ ያለው Dialogue (አውሥኦ) ግን ይህን ተራ አይጠብቅም። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ እግዚእ"፡ ቍ. 14 ገጽ 145 ይመልከቱ።
[357] እንግሊዝኛው "Our Lord be with you" ይላል - Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, 139.
[358] እንግሊዝኛው "We have them with the Lord" ይላል - ዝኒ ከማሁ።
[359] እንግሊዝኛው "It is fitting and right" ይላል - ዝኒ ከማሁ።
[360] "Holy things for the holy people" - ዝኒ ከማሁ።
[361] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 35.
[362] "ቅዳሴ እግዚእ"፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 15፣ ገጽ 145።

አምላካችን “በልዑላንና በትሑታን (በመላእክት እና በደቂቀ አዳም) ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ተብሎ ዘወትር ይመሰገናል”።[363]

አኰቴተ ቍርባን ዘመጽሐፈ ኪዳን፥ መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና ወይኑ ላይ እንዲወርድ የሚጠየቅበት ጸሎት (*ኤፒክሌሲስ*) የለውም። በርናርድ ቦቴ ወደ ላቲን የተረጎመው መጽሐፈ ኪዳን[364] ውስጥ ግን ይህ ጸሎት እንዳለና፡- “አምላክ [ሆይ] መንፈስ ቅዱስህን በዚህ [ጽዋ] እና በዚህ የአንተ [ማዕድ] ላይ ላክ”[365] እንደሚል ተጠቁሟል። የእንግሊዝኛው መጽሐፈ ኪዳን ደግሞ፡- “ጌታ መንፈስ ቅዱስ [ሆይ] ከቅድስናህ የሆነውን ይህን [ጽዋ] እና ይህን [ማዕድ] አምጥተናል”[366] ይላል። የቅዳሴ እግዚእ አርታዕያን፥ በተራ ትርጉማቸው “መጠጥና መብል”[367] የሚሉት ቃላት የረበሿቸው ይመስላል። ስለሆነም ዐረፍተ ነገሩን፡- “አኮ መብልዐ ወመስቴ ዘአቅረብነ ለከ ለቅድሳቲከ”[368] (ለቅድሳትህ መብልንና መጠጥን ያቀረብንልህ አይደለም) ሲሉ ቀይረውታል። ሆኖም ግን፥ የጎደለውን ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ተገቢው ቦታ ላይ እንዲህ ሲሉ አስገብተውታል፡- “አቤቱ በዚህ ኅብስትና፥ በዚህ ጽዋ ላይ መንፈስ ቅዱስን ኃይልንም ትልክ ዘንድ እንለምንሃለን፥ እንማልድሃለን፤ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋውን* ደሙንም ያደርገው ዘንድ ለዘለዓለሙ”።[369] መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ ያለው የቅዱስ ቍርባን ምስጋና የአኰቴተ ቍርባኑን የማብቂያ ቦታ ይጠቁማል። ኤጲስ፡ቆጶሱ፡- “ህበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ…’’ (የአንተ በሚሆን መንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን) የሚለውን ሲጸልይ፥ ሕዝቡም የእርሱን ተቀብለው ይጸልያሉ። ከዚያም “ቡሩክ ስሙ

---

363 “ቅዳሴ እግዚእ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ንባቡና ትርጓሜው፣ ቍ. 19፣ ገጽ 169።
364 *Testamentum Domini*.
365 በእንግሊዝኛ ትርጉሙ፡- “Lord, send the Holy Spirit upon this drink and this holy food.” - Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 140.
366 “Lord Holy Spirit, we have brought this drink and this food of your holiness.” - Grant Sperry-White, “The Testamentum Domini: A Text for Students, with Introduction, Translation, and Notes,” *Alcuin Club Liturgical Studies,* no. 19 (1991) p. 17.
367 “Drink and food.”
368 *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 38.
369 “ቅዳሴ እግዚእ”፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 47-48፣ ገጽ 151።

ለእግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም" (የእግዚአብሔር ስሙ ለዘላለም የተባረከ ነው) የሚለው ዝማሬ "ማኅተመ አኰቴት"[370] (የአኰቴተ ቍርባኑ መደምደሚያ) እንደሆነ ይነግረናል።

## አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘሰላሚስ

በ5ኛው ምእት ዓመት የምናገኘው የመጨረሻው ጸሎተ ቍርባን የቆጵሮስ ደሴት ውስጥ በምትገኘው ሰላሚስ በተባለች ቦታ ጵጵስና ተሹሞ በነበረው ቅዱስ ኤጲፋንዮስ (+403 ዓ.እ.) ስም የሚጠራ ነው። አኰቴተ ቍርባኑ ከጉባኤ ኬልቄዶን (451 ዓ.እ.) በኋላ በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ ይታመናል። የመጀመሪያውን ሙሉ ቅጂ ማግኘት ስላልተቻለ በአርመንኛ የተገኙትን የቅዳሴውን የተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ምሁራኑ እ.አ.አ. በ1960 አሳትመዋቸዋል።[371] በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደ ምንመለከተው፥ በዝነኞቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም ቅዳሴያት እንደሚሰየሙ እውቀቱ ያላቸውና በወርቃማው የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ዘመናት (14ኛውና 15ኛው ምእት ዓመታት) የተነሡ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት፥ ለደረሷቸው ቅዳሴያት ከመረጧቸው ስሞች መካከል ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘደሴተ ቆጵሮስ ነው። ስለሆነም በዚህ አባት ስም "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘደሴተ ቆጵሮስ" ተብሎ የተሰየመ ቅዳሴ በቤተ ክርስቲያናችን አለ፤ ነገር ግን ከስም በስተቀር እዚህ ላይ በአጭሩ ከምንመለከተው የ5ኛው ዘመን ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ዘሰላሚስ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የለውም።

ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ዘሰላሚስ እንደ አብዛኞቹ የ4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመት ቅዳሴያት "አምላካችን ሆይ፡ ያለማቋረጥ አንተን ማመስገን በእውነት ይገባል" የሚል የምስጋና መግቢያ አለው።[372] ከሐዋርያዊ ትውፊት የተወሰደና "ቅዱስ ልጅህን ከሰማይ ላክህልን" የሚልንም ዐረፍተ ነገር ያስነብበናል። በአጭሩና በጥሩ ቃላት የተገለጸው ነገረ ክርስቶስም በዘመኑ ለነበሩ ኑፋቄያት መልስ በሚሰጥ መልኩ፥ ቃል ሥጋ ሲሆን መለኮታዊ ባሕርዩን ትቶ ሰው ወደ መሆን እንዳልተለወጠ፥ የእኛን

[370] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 40.
[371] Jasper and Cuming, *Prayers of the Eucharist*, p. 141.
[372] ዝኒ ከማሁ፡ 142።

ባሕርይ (ሥጋና ነፍስን) ወስዶ ከኃጢአት በስተቀር ሰው እንደሆነና፥ ሥግው ቃል (ክርስቶስ) ለሁለት ሊከፍሉት የማይቻል ፍጹም ሰው፥ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ያስረዳል። ከሌሎች ቅዳሴያት ለየት ባለ መልኩ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቍርባንን የመሠረተባቸውን ቃላት ከመዘርዘሩ በፊት፡- "ስለእኛ በፈቃዱ ሕይወት ሰጭ የሆነውን ሞትን ለመቀበል በመጣ ጊዜ፥ ቅዱሳትና ያለነውር በሆኑ እጆቹ ኅብስቱን አንሥቶ ለአንተ ለአባቱ አሳየህ" ይላል።[373]

## መደምደሚያ

በዚህ ምዕራፍ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ አምስት ምእት ዓመታት ትጠቀምባቸው የነበሩ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጁባቸውን ቋንቋዎችና ቦታዎች፥ እንዲሁም የመጻሕፍቱን ይዘት በአጭሩ ተመልክተናል። የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ባልተጻፉበት ወቅት ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚመራው ኤጲስ፡ቆጶስ ወይም ካህን የቻለውን ያህል በቃሉ ይጸልይ እንደነበርና በሂደትም ከአይሁድ መጻሕፍተ ጸሎት የተወሰዱትን ጸሎታት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ትጠቀም እንደነበር ለማሳየት ተሞክሯል። የአኰቴተ ቍርባንን ይዘት ያሟሉ ጸሎታተ ቍርባን መደረስ የጀመሩት በሦስተኛው ምእት ዓመት ሲሆን፥ ዝማሬ ሱራፌል ደግሞ በ4ኛው ምእት ዓመት የአኰቴተ ቍርባን ክፍል ሆኗል። በ3ኛውና 4ኛው ምዕት ዓመታት የተደረሱ ቅዳሴያትን ስዘረዝር፥ በእነዚህ ዘመናት የተደረሱ ቅዳሴያት በቤተ ክርስቲያናችን ያላቸውን ቦታ ጠቁሜአለሁ። እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ቅዳሴያት (ለምሳሌ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ቅዳሴ ቄርሎስ፥ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ) በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ስም ካላቸው ቅዳሴያት ጋር በይዘት እንደማይመሳሰሉ ለአንባብያን ግልጽ ለማድረግ ሞክሬአለሁ።

በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር እንደምንመለከተው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካሏት በርካታ ቅዳሴያት መካከል አብዛኛዎቹ የተደረሱት በ14ኛውና 15ኛው ምእት ዓመታት ሲሆን እነዚህ ቅዳሴያት በወቅቱ የተነሡ የትምህርተ ሃይማኖት ክርክሮች ውጤቶች ናቸው። ስለ ሰንበት አከባበር፥ ስለ ሰው ልጅ በሥላሴ አርአያና አምሳል መፈጠር፥ ስለ ማይታየውና የማይመረመረው የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚወያዩና በአቋም የተለያዩ ሁለት ወገኖች ስለነበሩ የራሳቸውን አቋም በማንጸባረቅ ቅዳሴያትን

[373] ዝኒ ከማሁ።

ይደርሱ ነበር። የነገረ መለኮት አቋማቸውን በቅዳሴያቱ ማስገባት የፈለጉትም የእነርሱ አስተምህሮ በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነትን እንዲያገኝ በማሰብ ነው። ከውጭ ከተቀበልናቸው ቅዳሴያት መካከል ደግሞ፥ የ3ኛው ምእት ዓመት ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያለው አኰቴተ ቍርባን በዘመነ አክሱም (4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመታት) ወደ ግእዝ ከተተረጐመ በኋላ ብዙ ማሻሻዎች ተደርገውበት "ቅዳሴ ሐዋርያት" የሚል ስያሜ አግኝቷል። በተመሳሳይ መልኩ የመጽሐፈ ኪዳን አኰቴተ ቍርባን በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ "ቅዳሴ እግዚእ - የጌታ ቅዳሴ" ተብሎ ተሰይሟል። ከእነዚህ ቅዳሴያት በተጨማሪ፦ ቅዳሴ ማርቆስ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታ ወንድም) እና ቅዳሴ ባስልዮስ ከግሪክና ዐረብኛ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተተረጐሙ ቅዳሴያት ናቸው። የተቀሩት ቅዳሴያት ግን የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሥራዎች እንደሆኑ ከበቂ በላይ ማስረጃዎች አሉ። በሚቀጥለው ምዕራፍ፥ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ሥርዓተ ቅዳሴን መሠረትና በየዘመናቱ ያሳየውን እድገት፥ እንዲሁም አብዛኞቹ ቅዳሴያት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ለመደረሳቸው የሚቀርቡ ታሪካዊ ማስረጃዎችንና በቅዳሴዎቹ ውስጥ የሚታዩ ጠቃሚ ምልክቶችን እንመለከታለን።

# ምዕራፍ ሦስት

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት እና ታሪካዊ እድገት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ መሠረት የእስክንድርያ ሥርዓተ ቅዳሴ[1] ተብሎ የሚታወቀው የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን በ4ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ላይ በቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ እጅ ተቀብቶ ከተላከላት ከመጀመሪያው ጳጳስ (አባ ሰላማ) ጀምሮ፥ የራሷ ፓትርያርክ ተሹሞላት ራሷን እስከቻለችበት 1951 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 1959) ድረስ በግብፃውያን ጳጳሳት ትመራ ስለነበር የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን በትርጉም መልኩ መቀበሏ አይገርምም። እንዲሁም፥ በተለያዩ ጊዜያት የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ አባቶች ድርሳናት ከሱርስት ቋንቋ ወይም ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ስለተተረጎሙ፥[2] በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ እድገት ላይ ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ይህ ማለት ግን የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ ከውጭ ቋንቋዎች ተሰብስበው የተተረጐሙ መጻሕፍት ውጤት ነው ማለት አይደለም። እንዲያውም በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ላይ ጥናት ያደረጉ ሊቃውንት እንደመሰከሩት፥ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከውጭ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ በሚተረጉሙበት ጊዜ የራሳቸውን አሳብ የመጨመርና የትርጉም ሥራ እስከማይመስል ድረስ ኢትዮጵያዊ (ብሔራዊ) ቅርጽና ይዘት ሰጥተው የመተርጐም ልምድ ነበራቸው።[3]

ለቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ ልዩ ውበት ከሰጡት ከቅዱስ ያሬድ (505-571 ዓ.ም.) የዜማ መጻሕፍት በተጨማሪ፥ በ14ኛውና 15ኛው ምእት ዓመታት የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፥ የተለያዩ የትምህርተ ሃይማኖት ድርሳናት እና

---

[1] Alexandrian Liturgical Rite.

[2] Tedros Abraha, O.F.M. Cap. "Jacob of Serug in the Ethiopic Tradition under Review and New Clues about the Background of the Ge'ez Anaphora Ascribed to Jacob of Serug," *OCA,* Vol. 298 (2015) p. 472.

[3] Lanfranco Ricci, "Ethiopian Christian Literature," *CE*, Vol. 3, ed. Aziz S. Atiya (New York: Macmillan Publishing Company, 1991) p. 977.

ቅዳሴያት የመድረስ ብቃት ነበራቸው። ድርሰቶቻቸውም ኢትዮጵያዊውን ትውፊት፥ ባህልና አስተምህሮ የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡[4] በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ በዝርዝር እንደምንመለከተው፥ በየዘመናቱ የተነሡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያንን መጻሕፍተ ሥርዓት በተለያዩ ጸሎታት አስፋፍተው የሥርዓተ ቅዳሴው ክፍል በማድረግ፤ ከግሪክ፥ ከሱርስትና ዐረብኛ ቋንቋዎች የተተረጐሙ የተለያዩ ጸሎታት እና ሊጦናትን በራሳቸው መረዳት በቅዳሴው ውስጥ ቦታ በመስጠትና "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ አትናቴዎስ፥ ቄርሎስ፥ ጎርጎርዮስ ወዘተ." በማለት የሰየሚቸውን ቅዳሴያት በመድረስ የራሱ የሆነ መለያ ባሕርያት ያሉት ኢትዮጵያዊ ሥርዓተ አምልኮ[5] ባለቤት አድርገውናል።[6]

## 3.1. አጭር ታሪካዊ ዳሰሳ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርቲስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ ጥናት ያደረጉ አንዳንድ ምሁራን፥ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘእስክንድርያ ብለው የሚጠሩት ሥርዓተ አምልኮ ክፍል እንደሆነ አድርገው ይቈጥሩታል።[7] ይህ ግን ቤተ ክርስቲያናችን ከግሪክና ከዐረብኛ

---

[4] Claude Sumner, "The Ethiopic Liturgy: An Analysis," *JES*, Vol. 1 (1963) p. 40.

[5] Ethiopian Liturgical Rite.

[6] Peter Jeffery ከዚህ እውነታ ጋር ይስማማል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጐሙ ጽሑፎችን ብትቀበልም፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓተ አምልኮ የትርጒም ሥራዎች ጥርቅም አለመሆኑን ያስረዳል። በአንጻሩ፥ የውጭ ምንጮችን ኢትዮጵያዊ ትርጒም ከመስጠት ጋር አገር በቀል ድርሰቶች በግልጥ እንደሚታዩበትና ራሱን የቻለ ኢትዮጵያዊ ሥርዓተ አምልኮ ተብሎ ሊጠራ እንደሚገባው በአጽንዖት ይናገራል። የእርሱን ቃላት ለመጠቀም ያህል፦ "[T]he Ethiopian liturgical tradition is much more than a mere patchwork of scraps imported from elsewhere. On the contrary, it exhibits much creativity and originality, both in its absorption and assimilation of diverse foreign elements and in the considerable bulk of indigenous material that emerged in Ethiopia itself. Thus it is undoubtedly correct that 'there exists a true Ethiopian rite'." Peter Jeffery, "The Liturgical Year in the Ethiopian Deggʷā" *ΕΥΛΟΓΗΜΑ: Studies in Honour of Robert Taft, S.J.*, eds. E. Carr, S. Parenti, A. Thiermeyer, E. Velkovska (Rome: Centro Studi S. Anselmo, 1993) p. 204.

[7] ለምሳሌ፥ Irénée-Henri Dalmais, *Eastern Liturgies* (New York: Hawtorn Publishers, 1960) ገጽ 56 ይመልከቱ። በተጨማሪም "Egyptian Rite," *Ancient Liturgies: Being Reprint of the Texts, Either Original or Translated, of the Most Representative Liturgies of the Church from Various Sources,* ed. C. E. Hammond and F. E. Brightman (New Jersey: Gorgias Press, 2006) ገጽ 769-824 ይመልከቱ።

ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የግብፅ ኦርቶዶክስ መጻሕፍትን ብትቀበልም፥ በተለያዩ ዘመናት እያደገ መጥቶ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ብሔራዊ ድርሰቶች የዳበረና ራሱን የቻለ ሥርዓተ አምልኮ መኖሩን ከግንዛቤ ያላስገባ አመለካከት ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ለ1600 ዓመታት ያህል በእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ሥር መቆየትዋ፥ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ኮፒ የተደረገ ሥርዓተ አምልኮ እንዳላት አያመለክትም። ሕንድ ውስጥ የምትገኘው የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት ቅዳሴ፥ ከሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ የተቀበለችው ስለሆነ ስያሜው ራሱ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘምዕራብ ሶርያ[8] ነው። ልዩነት አለ ከተባለ የማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ የሶርያ ቃላትን ከመጠበቅ ጋር በሕዝቧ ቋንቋ (*ማላያላም*) መቀደስዋ ነው። ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ግን ፈጽሞ ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። ቤተ ክርስተያናችን "ማርቆስ አባቴ፥ እስክንድርያ እናቴ" በምትልባቸው ዘመናት ከእናት ቤተ ክርስቲያን የተተረጐሙ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን ከኢትዮጵያዊ ትውፊት ጋር በማዛመድ ትጠቀምባቸው ነበር፤ በሂደትም የትርጒም ሥራዎቹ ላይ የተለያዩ አገር በቀል ጸሎታትን በመጨመር ብሔራዊ መልክ እንዲይዙ ተደርገዋል። እንዲሁም በግብፅ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የማይውሉ ጥንታውያን ቅዳሴያት (ቅዳሴ ሐዋርያት እና ቅዳሴ እግዚእ) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች ቅዳሴያት ከመሆናቸው ባሻገር፥ በግብፅ የማይታወቁ በርካት ቅዳሴያት በኢትዮጵያውን ሊቃውንት ተደርሰዋል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ቤተ ክርቲስቲያን ሥርዓተ አምልኮ፥ በየዘመናቱ ያሳየውን እድገትና ከሌሎች የሥርዓተ ቅዳሴ ትውፊቶች ጋር የማይጋራውን ባሕርያት በማገናዘብ ሊጠና ይገባዋል።

የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ሥርዓተ አምልኮ አራት ዋና ዋና የእድገት ሂደቶችን አልፎ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የመጀመሪያው በአክሱም[9] ዘመነ መንግሥት (ከ4ኛው-7ኛው ምእት ዓመታት) የነበረው የምሥረታ ጊዜ ሲሆን፥ በእነዚህ ክፍለ ዘመናት ከግሪክ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የሥርዓተ አምልኮ ጽሑፎችን እና የቅዱስ ያሬድን

---

[8] West Syrian Liturgical Rite.

[9]ታላቁ ሊቅ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በተለምዶ "አክሱም" ወይም "አኵስም" ብለን የምንጠራው ቃል መነሻ "አኵሽም" እንደሆነና ይህም የነገደ ኵሽ መዲና (አህጉረ ኵሽ) የሚል ትርጒም እንዳለው ጽፈዋል። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ*፣ ገጽ 219።

የዜማ መጻሕፍት እናገኛለን። ሁለተኛው የእድገት ጊዜ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው ደግሞ ከሰሎሞን ሥርወ መንግሥት መመለስ (1263 ዓ.ም.) እስከ 14ኛው ምእት ዓመት ድረስ ያለው ነው። ግብፅ በእስልምና ወራሪ ኃይሎች እጅ በ7ኛው ምእት ዓመት ከወደቀች በኋላ፥ ዐረብኛ የቅብጥ (ኮፕቲክ) ቋንቋን እየተካ መጥቶ በ12ኛው ምእት ዓመት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ መግለገያ ቋንቋ ለመሆን ቻለ፡፡[10] ስለዚህ ከ13ኛው ምእት ዓመት በኋላ በርካታ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል።

ከዚህ የሁለተኛ ትርጉም ሥራ ቀጥሎ የምናገኘው፥ በኢትዮጵያውን ሊቃውንት የተለያዩ የነገረ መለኮት ጽሑፎች[11] እና ጸሎታተ ቊርባን የተደረሱበትና የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ወርቃማ ክፍለ ዘመን ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለውን (ከ15ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ እስከ 16ኛው ሩብ ምእት ዓመት) ድረስ ያለውን ጊዜ ነው። በመጨረሻ፥ በ16ኛውና 17ኛው ምእት ዓመታት ኢትዮጵያን ሊቃውንት ከፖርቱጋል ከመጡ የካቶሊክ ካህናትና መልእክተኞች ጋር ባደረጓቸው የነገረ ክርስቶስ ክርክሮች አማካኝነት የቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ጽሑፍ እድገት ያሳየ ሲሆን፥ በዚሁ ዘመን የጎንደር ሊቃውንት የቅዱስ ያሬድን ድርሰቶች መሠረት በማድረግ ተጨማሪ የዜማ መጻሕፍት ደርሰዋል።[12] በእነዚህ አራት የእድገት ደረጃዎች ውስጥ የተከናወኑ ታሪካዊ ክሥተቶችን በዝርዝር እንይ ከተባለ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ይወጣዋል። የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ታሪካዊ ሂደትን በዚህ ምዕራፍ መመልከት ያስፈለገን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ እድገትን ለማሳየት ስለሆነ፥ ከአጭር ታሪካዊ ገለጻዎች ጋር የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን መጻሕፍት ይዘት ላይ መጠነኛ ትንታኔ አቀርባለሁ። እንዲሁም በወርቃማው ዘመን የተደረጉ የነገረ መለኮት ክርክሮች በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ለተደረሱት ቅዳሴያት መነሻ ምክንያቶች መሆናቸውን ለማሳየት እሞክራለሁ።

---

[10] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፥* ገጽ 123.

[11] Theological treatises.

[12] Getatchew Haile, "Ethiopic Literature," *African Zion*: *The Sacred Art of Ethiopia*, ed. Roderick Grierson (Milan: Amilcare Pizzi, 1993) p. 51; Ricci, "Ethiopian Christian Literature," *CE*, Vol. 3, p. 978; E. Cerulli, "Ethiopic Languages and Literature," *NCE,* Vol. 5, eds. Catholic University of America Editorial Staff (New York: McGraw-Hill, 1967) p. 592.

## ፮. ሥርዓተ ቅዳሴ ዘዘመነ አክሱም

የአክሱም መንግሥት በሮማ ግዛት ሥር ከነበሩ መንግሥታት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረው፤ መንግሥታዊ እድገቱም በዘመኑ ከነበረው የግሪክ ሥልጣኔ ጋር ሊፎካከር የሚችል እንደነበር ይታመናል።[13] የ4ኛው ምእት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ክርስትና የአክሱም መንግሥት ብሔራዊ ሃይማኖት ከመሆኑ በፊት ከደቡብ አረብ ፈልሰው የመጡ ሰዎች የጣዖት አምልኮ ልምዳቸውን ይዘው ስለመጡ በኅብረተሰቡ ላይ ግልጽ የሆነ ተጽእኖ አሳድረዋል።[14] የሃ ላይ በሳብኛ (ደቡብ ዐረብኛ) ቋንቋ "አልማቃህ" ተብሎ ለሚጠራው ጣዖት ቤተ መቅደስ ታንጾ እንደነበር ታሪካዊ መረጃዎች ያሳያሉ።[15] ንጉሥ ኢዛና ክርስትናን ከመቀበሉ በፊት፥ ለግዛቱ ስጋት የሆኑ ጠላቶቹን በጦርነት ድል ካደረገ በኋላ ድል አጎናጽፎኛል ብሎ ላሰበውና "ማሕረም" ለተባለው ጣዖት ምስጋና ያቀረበባቸው በድንጋይ ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ተገኝተዋል። ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ ደግሞ፥ ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረው ለእውነተኛው አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ያቀርብ እንደነበር በቁፋሮ የተገኙና ዓለት ላይ የተወቀሩ ጽሑፎቹ ይጠቁማሉ።[16]

ዋና ከተማውን አክሱም ላይ ያደረገው መንግሥት ቀይ ባሕር ላይ ባለው የአዱሊስ ወደብ አማካኝነት ከግሪክና ሶርያ ክርስቲያኖች ጋር የንግድ ልውውጥ ያደርግ ነበር። የእነዚህ ክርስቲያኖች ለንግድ ወደ አክሱም መምጣት ክርስትናን ለማስፋፋት ምን ያህል እንደጠቀመ በግልጽ ባይታወቅም፥ የተወሰነ አስተዋጽኦ ሳይኖረው አልቀረም። የሐዋርያት ሥራ 8 ፥26-41 ላይ እንደተጠቀሰው፥ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረው ጃንደረባ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ" ሲል እምነቱን ገልጾ በፊልጶስ እጅ እንደተጠመቀ ወንጌላዊው ሉቃስ ጽፎልናል። የጃንደረባው መጠመቅ የክርስትና ዘር በአገራችን ኢትዮጵያ እንዲዘራ ምክንያት እንደነበር ከታላቁ የቤተ ክርስቲያን

[13] Ewald Hien and Brigitte Kleidt, *Ethiopia – Christian Africa: Art*, *Churches and Culture*, trans. John M. Deasy (Retingen: Melina-Verlag, 1999) p. 17.

[14]ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ* ገጽ 79።

[15] Sergew Hable Sellassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270* (Addis Ababa: Haile Sellassie I University, 1972) p. 94.

[16]ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ* ገጽ 83።

ታሪክ ጸሐፊ ከቅዱስ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ዘገባ እንረዳለን፡- “[ጃንደረባው] በመገለጥ መለኮታዊ ቃልን ከፊልጶስ ለመቀበል የመጀመሪያው፤ እንዲሁም ወደ አገሩ ተመልሶ ወንጌልን ለመስበክ የመጀመሪያው ሰው ነበር።”[17] ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም፥ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገባ መጠነኛ ታሪካዊ ገለጻ ባቀረበበት የመጽሐፈ ምሥጢር “ምንባብ ዘልደት” ውስጥ “ወበዜና ዚአሁ አምኑ ሰብአ ኢትዮጵያ በወንጌለ ጸጋሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ” (በጃንደረባው የምሥራች ቃል የኢትዮጵያ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የጸጋ ወንጌል አመኑ) በማለት ዘግቦልናል። ነገር ግን፥ እንደ አባ ጊዮርጊስ ገለጻ፥ ጃንደረባው ካህን ስላልነበር ሊያጠምቃቸው አልቻለም።[18]

ጃንደረባው በመጀመሪያው ምእት ዓመት የክርስትናን ዘር ቢዘራም፥ የክርስትና እምነት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የሆነው ወንድማማቾቹ ነገሥታት (አብርሃና አጽብሐ)[19] ከተጠመቁ (ከ330 ዓ.እ.) በኋላ ነበር። ሩፊነስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ከፍሬምናጦስ ወንድም ከኤዴስዮስ ሰምቶ የዘገበልን ታሪክ እንደሚነግረን፥ ሁለቱ ወንድማማቾች ሜሮፒየስ ከሚባል ፈላስፋ ጋር ወደ ሕንድ በመርከብ ሲቀዝፉ ያልታወቁ ሰዎች መርከቢቷን መትተው ሜሮፒየስን ገደሉት፤ ሁለቱን ወጣቶች ግን ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ማርከው ወሰዷቸው። ንጉሡም ኤዴስዮስን ጽዋ ያዥ ሲያደርገው፥ የፍሬምናጦስን ንቃተ ሕሊና ስለተገነዘበ

[17] Eusebius of Caesarea, *Eusebius: The Church History, A New Translation with Commentary*, trans. Paul L. Maier (Baltimore: Kregel Publications, 1999) p. 59.

[18] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir,* ed. Yaqob Beyene, CSCO, Scriptores Aethiopici, Vol. 515. Tom. 89, ed. Yaqob Beyene (Louvain: Aedibus E. Peeters, 1990) ገጽ 119-120።

[19] በግእዝም ሆነ በአማርኛ የተጻፉ ታሪኮች አብርሃና አጽብሐ በእኩልነት እንደነገሡ ያሳያሉ፤ ለምሳሌ አባ ጊዮርጊስ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ የመጀመሪያው ጳጳስ አባ ሰላማ “በመንግሥተ አብርሃ ወአጽብሐ” ወደ ብሔረ አግአዚ (ኢትዮጵያ) እንደመጣ ጽፎልናል። *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir,* ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515. Tom. 89, ገጽ 121 ይመልከቱ። በቅዱስ አትናቴዎስ መንበር ተቀምጦ የነበረውን አርዮሳዊውን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ (Bishop George) የተቀበለው የሮማው ቄሣር (Constantius) ለሁለቱ ወንድማማች ነገሥታት በጻፈው ደብዳቤ ነገሥታቱን ኢዛኔስ እና ሳዛኔስ (Aezanes and Sazanes) በማለት ይጠራቸዋል - Athanasius, *Apologia ad Constantium,* Section 31 (http://www.newadvent.org/fathers/2813.htm, accessed on Novemer 10, 2019). ነገር ግን፥ ከ327-357 ዓ.እ. የነገሠው ኢዛና ብቻ እንደነበር የዘገቡም አልጠፉም - Bairu Tafla, “Ethiopian Orthodox Church,” *CE*, Vol. 3, ed. Aziz S. Atiya (New York: Macmillan Publishing Company, 1991) ገጽ 996 ይመልከቱ።

በመንግሥቱ ከፍተኛ ቦታ ሰጥቶ ሾመው። ንጉሡ ሲሞት፥ ኤዴስዮስና ፍሬምናጦስ ወደ አገራቸው ለመመለስ ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን የንጉሡ ልጆች አባታቸውን ለመተካት ያልደረሱ ሕፃናት ስለነበሩ የንጉሡ ሚስት በመንግሥቱ ሥራ እንዲረዷት ለመነቻቸው። ፍሬምናጦስ በዚህ አጋጣሚ ያገኘውን ሥልጣን ተጠቅሞ ከሮማ ግዛት የመጡ ክርስቲያኖችን በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ይረዳቸው ነበር። የንጉሡ ልጆች ለአቅመ አዳም ሲደርሱ ኤዴስዮስ ወደ አገሩ ጢሮስ[20] ተመለሰ። ፍሬምናጦስ ግን የክርስትና ዘርን በኢትዮጵያ ቢያይም ካህናት ባለመኖራቸውና ሥርዓተ ጥምቀት ላመኑ ሰዎች ባለመፈጸሙ ያሳሰበው ስለነበር፥ ይህን ጉዳይ በ328 ዓ.እ. በመንበረ ማርቆስ ላይ ለተሾመው ቅዱስ አትናቴዎስ ለማቅረብ ወደ እስክንድርያ ተጓዘ። የኢትዮጵያውያንን ጉዳይ ከፍሬምናጦስ የሰማው ቅዱስ አትናቴዎስ፦ "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት፥ ካንተ ሌላ ምን ዓይነት ሰው ማግኘት እንችላለን? አንተ ያደረግኸውንስ ማን ሊያደርግ ይችላል?" ሲል ፍሬምናጦስን ጳጳስ አድርጎ ሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ላከው።[21] አባ ጊዮርጊስ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ተመሳሳይ ታሪክ ዘግቦልናል፤ ነገር ግን የፍሬምናጦስን ወንድም ኤዴስዮስ ሳይሆን "ሲድራኮስ" ይለዋል። በተጨማሪም ፍሬምናጦስ በቅዱስ አትናቴዎስ ከተሾመ በኋላ ወደ "ብሔረ አግዓዚ" (ኢትዮጵያ) ተመልሶ ሕዝቡንና ነገሥታቱን እንዳጠመቀ፤ ኤጲስ ቆጶሳትን፥ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን እንደሾመ፤ በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትን እንዳተረፈና ስላመጣላቸው ሰላም "አባ ሰላማ"[22] ብለው እንደጠሩት ነግሮናል።[23]

የቅዱስ ፍሬምናጦስ ሹመት፥ ሢመተ ክህነትና ሥርዓተ ጥምቀት በኢትዮጵያ እንዲካሄዱ ምክንያት ከመሆኑ በተጨማሪ፥ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ወደ

---

[20] Tyre.

[21] *The Church History of Rufinus of Aquileia,* Books 10 and 11, trans. Philip R. Amidon, S.J. (Oxford: Oxford University Press, 1997) Book 10:9-10, pp. 18-20. EMML 1763 ላይ የሚገኘውና ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመው ያሳተሙት የቅዱስ ፍሬምናጦስ ድርሳን፥ የሩፊኖስን ትረካ የግእዝ ትርጉም የያዘ ሲሆን ስለታሪኩ ምንጭ፦ "ወዘንተ ኵሎ ዜነወ አሐዱ ዘስሙ ርፍኖስ በእንተ ፍሬ፡መንጦስ አቡነ ሰሚዖ እምአድስዮስ" (ሮፊኖስ የተባለ ሰው ከኤዴስዮስ ሰምቶ ይህንን ሁሉ ስለ አባታችን ፍሬምናጦስ ተናገረ) ይላል። Getatchew Haile, "The Homily in Honour of St. Frumentius Bishop of Axum," *Analecta Bolladiana: Revue Critique D'hagiographie,* Tome 97 (1979) p. 315.

[22] ከላይ (የኅዳግ ማስታወሻ ቍ 21) ላይ የተጠቀሰው የቅዱሰ ፍሬምናጦስ ድርሳን፥ የብራናው ላይኛው ኅዳግ ላይ ድርሳኑ የሚነበብበትን ጊዜ እየጠቆመ "ዘአባ ሰላማ" የሚል ርእስ ቢሰጠውም፥ "አባ ሰላማ" የሚለው ስም ድርሳኑ ውስጥ አይገኝም። Getatchew Haile, "The Homily in Honour of St. Frumentius Bishop of Axum," p. 311።

[23] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515. Tom. 89, ገጽ 120 እና 121 ይመልከቱ።

ኢትዮጵያ እንዲገቡ መንገድ ከፍቷል። ፍሬምናጦስ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሥርዓተ ቅዳሴ የምትጠቀምባቸውን ጸሎታት፥ ሐዋርያዊ ትውፊት የሚባለውን መጽሐፈ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንና[24] የእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ ዋነኛ ቅዳሴ የነበረውን (አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ማርቆስ) ይዞ እንደመጣ ይታመናል። በአክሱም ዘመነ መንግሥት ብሔራዊ ቋንቋ ከነበረው ከግእዝ በተጨማሪ፥ ግሪክኛ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ ያገለግል እንደነበር በቁፋሮ የተገኙ ታሪካዊ መዛግብት ያሳያሉ።[25] በዚሁ ዘመን (4ኛው ምእት ዓመት) የእስክንድርያው ሥርዓተ ቅዳሴ ቋንቋም ይኸው ግሪክኛ ስለነበር ቅዱስ ፍሬምናጦስ ያመጣቸው የተለያዩ የሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎታት[26]፥ የሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቍርባንና ቅዳሴ ማርቆስ ወደ ግእዝ እንደተተረጐሙ ይታመናል።[27] በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ላይ ብዙ ጥናቶችን ካደረጉት የአውሮፓ ምሁራን መካከል አንዱ የሆነው ኤንሪኮ ቼሩሊ በ4ኛው ምእት ዓመት መጽሐፍ ቅዱስ፥ አንዳንድ የሥርዓተ ምንኵስና እና የትምህርተ ሃይማኖት መጻሕፍት እንዲሁም ለቅዳሴ አገልግሎት የሚውሉ ጸሎታት

---

[24] Paulos Tzadua, *The Divine Liturgy According to the Rite of the Ethiopian Church* (Addis Ababa: Wien Ltd., 1973) p. 11.

[25] Getatchew Haile, "Ethiopic Literature," p. 47.

[26] የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ትርጉሞች የሆኑና የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ከምናገኛቸው ጸሎታት መካከል፦ "ጸሎተ ጎርጎርዮስ ቅድመ ግብአተ መንጦላዕት"፥ "[ጸሎት] እንዘ ያለብስ ታቦተ ወያስተናብር"፥ "[ጸሎት] እምድኅረ ፈጸመ አስተናብሮ ንዋየ ቅድሳት"፥ "[ጸሎት] እንዘ የዐውድ ምስለ አኰቴተ ቍርባን"፥ "ጸሎተ አኰቴት"፥ "ጸሎተ እንፎራ"፥ "ፍትሐት ዘወልድ ወጸሎት እምድኅረ ፍትሐት ዘወልድ [መዪጦ ገጾ] መንገለ ምሥዋዕ"፥ "አ አምላክ ዘለዓለም"፥ "ጸሎት በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን ፥በእንተ ማኅበር ወበእንተ አበዊነ"፥ "ጸሎተ ወንጌል"፥ "ጸሎተ ንስሐ" እና "*ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን . . . አአምን፥ አአምን፥ አአምን*" የሚሉትን እናገኛለን - መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 2000፣ ቍ. 17-22፣ ገጽ 18-19፤ ቍ. 53-56፣ ገጽ 27-28፤ ቍ. 57-60፣ ገጽ 28-29፤ ቍ. 5-7፣ ገጽ 36፤ ቍ. 31-39፣ ገጽ 42-44፤ ቍ. 46-50፣ ገጽ 46-47፤ ቍ. 56-65፣ ገጽ 48-51፤ ቍ. 108-110፣ ገጽ 59፤ ቍ. 111-114፣ ገጽ 60-61፤ ቍ. 179-183፣ ገጽ 76-77፤ ቍ. 72-88፣ ገጽ 114-118 እና ቍ. 98-103፣ ገጽ 120-122 ይመልከቱ። እነዚህ ጸሎታት አንዳንድ ቦታ ላይ መጠነኛ ለውጥ እየተደረገላቸው ነው የተተረጐሙት። ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመው የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ላይ የሚከተሉት ርእሶች ተሰጥቷቸዋል፦ "The Prayer of the Veil," "The Prayer of Preparation," "The Litany of Oblation," "The Prayer of Thanksgiving," "Prothesis of the Bread and Wine," "The Prayer of Absolution to the Son," "The Prayer of Incense," "Litany for Peace, for the congregation and Litany for the Fathers," "The Litany for the Gospel," "The Prayer of Absolution to the Father," and "Confession of Faith." See *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory and Cyril,* (Los Angeles: Coptic Orthodox Church Diocese of Southern USA, 2001) pp. 3, 28, 44-45, 59-61, 78, 80, 93-94, 99, 118-119, 193-196, 198-200 and 217.

[27] J. M. Harden (trans.) *The Anaphoras of the Ethiopic Liturgy*, Translations of Christian Literature, Vol. III: Liturgical Texts, (London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1928) p. 2. እንዲሁም Hammerschmidt, *Ethiopian Anaphoras*, ገጽ 41-42 ይመልከቱ።

ቍርባን ከግሪክ ወደ ግእዝ እንደተተረጐሙ ጽፏል፡፡[28] ኢትዮጵያዊው የታሪክና የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ምሁር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌም፥ የግእዙ ብሉይ ኪዳን (*መጽሐፈ ሄኖክ* እና *መጽሐፈ ኩፋሌን* ጨምሮ) ከሰብዓ ሊቃናት የግሪክ ትርጉም[29] የተመለሰ እንደሆነና ከተለያዩ የግሪኩ ቅጂዎች መካከል "*ሉሲያኒክ*"[30] የሚባለው የግእዙን ሐዲስ ኪዳን[31] ለመተርጐም እንደረዳ አስረድተዋል።[32] ባጠቃላይ የትርጉም ሥራዎች ከ4ኛው - 7ኛው ምእት ዓመታት ድረስ ይከናወኑ የነበሩት ከግሪክ ወደ ግእዝ ሲሆን፥ በዚህ ዘመን ከተተረጐሙት መካከል፡- የትምህርተ ሃይማኖት መድበል የሆነው "ቄርሎስ" እና የአባ ጳኵሚስ የምንኩስና ሥርዓትና ትእዛዝ (ሥርዓት ወትእዛዝ ዘአባ ጳኵሚስ) ይገኙበታል።[33]

የመጀመሪያው የሥርዓተ ቅዳሴ ትርጉም የተካሄደው ከግሪክ ቋንቋ መሆኑን የሚጠቁሙ አንዳንድ ቃላትን የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ እናገኛለን። ለምሳሌ፥ "ጸሎተ እንፎራ"[34] *አናፎራ* የሚለውን የግሪክ ቃል ያስታውሰናል፤ ይህም ቃል "ከፍ ማድረግ ወይም ማቅረብ" የሚል ትርጉም ካለው ግስ (*አናፌሮ*) የተገኘ ሲሆን የቍርባን ምስጋና (አኰቴተ ቍርባን) ማለት ነው። ስለዚህ "ጸሎተ እንፎራ" መሥዋዕት ሆኖ በቀረበው በኅብስቱ ላይ የሚጸለይ ጸሎት ነው። ከዚህ ቃል ጋር የሚቀራረብና በቀጥታ "ኅብስት" የሚል ትርጉም ያለው የግሪክ ቃል፡-*ፕሮስፎራ* መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ "ጵርስፎራ"[35] የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። እንዲሁም፥ ወደ ግእዝ ወይም ወደ አማርኛ ሳይተረጐም የቀረና የግሪክ ቃላትን የያዘ ዐረፍተ ነገር እናገኛለን፡- "አውሎግዮስ ኄርዮስ[36] [. . .]

---

[28] Enrico Cerulli, "Ethiopic Languages and Literature," 591.

[29] Septuagint version.

[30] Lucianic text.

[31] የግእዙ ሐዲስ ኪዳን ከዐረብኛ ትርጉሞች ጋር እየተነጻጸረ በአባ ሰላማ መተርጉም (እ.አ.አ.1348-1388) መሪነት አንዳንድ እርማቶች ተደርጎበታል።

[32] Getatchew Haile, "Ethiopic Literature," p. 47.

[33] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 48፤ Ricci, "Ethiopian Christian Literature," p. 976.

[34] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 2000፣ ቍ. 46፣ ገጽ 46።

[35] "ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ፥ ወፈውሰነ በዝንቱ ጵርስፎራ . . . " *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 2000፣ ቍ. 54፣ ገጽ 111።

[36] "ኄርዮስ" ተብሎ የተጠቀሰው "*Kyrios*" የሚለውን የግሪክ ቃል ለማመልከት ይመስላል፤ ይህም ጌታ ማለት ነው፡፡ ሁለቱ ቃላት (አውሎግዮስ ኪርዮስ) "ጌታ ሆይ ባርክ" የሚል ትርጉም ይሰጡናል፡፡ በሶርያ

አግዮስ፥ ማንጦን ፓንዋማንጦን አላቲኖን።"[37] ለቅዳሴ የምንጠቀምባቸው ንዋያተ ቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ምሳሌና ምሥጢራዊ ትርጉም ዘርዝረው የጻፉልን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የእነዚህን የግሪክ ቃላት ትርጉሞች ነግረውናል፡-[38]

- "አውሎግዮስ ብሂል ቡሩክ ወስቡሕ" (አውሎግዮስ ማለት የተባረከ፥ የተመሰገነ ማለት ነው)
- "ጌርዮስ ብሂል አረጋዊ ዘይደልዎ ክብር" (ክብር የሚገባው)
- "አግ[ዮ]ስ ማንጦስ ብሂል ቅዱስ እንበለ ኃጢአት" (ኃጢአት የሌለበት ቅዱስ)
- "ፓንዋማንጦስ[39] ብሂል ንጹሕ ኵለንታሁ" (ሁለመናው ንጹሕ የሆነ)
- "አላቲኖን[40] ብሂል ዘኢይሤወሮ ምንትኒ" (ምንም የማይሠወርበት/ሁሉን የሚያውቅ)።
- "አላትዮን ብሂል አምላክ አማልክት" (የአማልክት አምላክ ማለት ነው)።

የመጨረሻውን ቃል (አላትዮን) ሠራዒው ካህን ኅብስቱና ወይኑ ላይ የመጀመሪያውን ቡራኬ ከማድረጉ በፊት የሚጸልየው ጸሎት ላይ እናገኘዋለን፡- "ንጽሕ ወጣዕም ወበረከት ለእለ ይሰትዩ እምደምከ ክቡር አላትዮን በአማን፥ አሜን።" መጽሐፈ ቅዳሴን ወደ አማርኛ የተረጐሙልን ሊቃውንት አባቶቻችን፡- "በእውነት ሰው የሆንህ አምላክ ሆይ፣ ንጽሕ፥ ጣዕም፥ በረከትም ከክቡር ደምህ ለሚጠጡ ይህን፥ አሜን" ብለው ትርጉሙን ነግረውናል።[41]

---

ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የእነዚህ ቃላት አቻ *Barekmor* የሚል ነው - C. K. Varghese, *The Living Sacrifice: The Holy Qurbanakramam: Interpretation, Meaning of Songs, Biblical Quotations* (Kerala: Thuruthel Press and Book Depot [Seventh Edition], 2005) p. 15.

[37] መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 2000፣ ቍ. 10፣ ገጽ 37 ።

[38] Getatchew Haile, "An Amharic Study on the Liturgy and Symbolism of the Ethiopian Church," *Ethiopian Studies in Honour of Amha Asfaw* (New York: No publisher given, 2017) EMML 1157, f. 221 v, p. 93.

[39] ይህ ቃል *Pnevmatos* ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ይመስላል፤ ትርጉሙም መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው፡፡

[40] በግሪኩ "*Alethia*" እውነት ማለት ስለሆነ፤ አላቲኖን/አላትዮን = እውነተኛ ተብሎ ቢተረጐም ለግሪኩ ቀረብ ይላል፡፡

[41] መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 2000፣ ቍ. 19፣ ገጽ 37።

ሐዋርያዊ ትውፊት የተሰኘው መጽሐፈ ሥርዓት ከ4ኛው እስከ 5ኛው ምእት ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ ከግሪክ ወደ ግእዝ ከተተረጐመ በኋላ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶታል።[42] በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያገኘውን ቦታ ያህል በሌሎች አብያተ ክርስቲያን አላገኘም ብለን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን። ይህ መጽሐፈ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በ1848 እ.አ.አ. የኅትመትን ብርሃን ሲያይ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዘግብፅ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር[43]። ነገር ግን በውስጡ የሚገኙትን ጸሎታት (ስለቤተ ክርስቲያን ሰላም፥ ስለታመሙት፥ መንገድ ስለሄዱት፥ ስለዝናም፥ ስለምድር ፍሬ ወዘተ.) የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊጦናት[44] የሚል ስያሜ ሰጥታ ብትጠቀምባ-ቸውም፥ የሐዋርያዊ ትውፊት ክፍል የሆነው አኰቴተ ቍርባን ግን ቤተ ክርስቲያኒቷ ከምትጠቀምባቸው ቅዳሴያት መካከል አይደለም።[45] በሮማ ካቶሊክ ቤተ

---

[42] Alessandro Bausi በቅርቡ ባደረገው ጥናት በዘመነ አክሱም (4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመታት) በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአገልግሎት ይውሉ የነበሩ ጥንታውያን ምንጮችን (liturgical sources) አግኝቷል፤ ከግኝቶቹ መካከል ከሄጶሊጦስ ዘሮሜ ጋር ተያይዞ የሚነገርለት Apostolic Tradition ነው። Alessandro Bausi,"The Aksumite Background of the Ethiopic "Corpus Canonum"," *Aethiopistische Forschungen: Proceedings of the XVth International Conference of Ethiopian Studies, Hamburg July 20-25, 2003,* ed. Siegbert Uhlig, (Wiesbaden: Harrassowitz Verlag, 2006) p.533. በግእዙ Apostolic Tradition ላይ ያደረገውን ጥናትንም ይመልከቱ፦ Alessandro Bausi, "The 'so-called *Traditio apostolica'*: preliminary observation on the new Ethiopic evidence," *Volksglaube im antiken Christentum: Festschrift für Theofried,* eds. Heike Grieser and Andreas Merkt 2009) pp. 291-321); "LA NUOVA VERSIONE ETIOPICA DELLA *TRADITIO APOSTOLICA:* EDIZIONE E TRADUZIONE PRELIM INARE," *Studia Ephemeridis Augustinianum,* Vol. 125 (2011) pp. 19-69.

[43] "The Egyptian Church Order" - Cuming, *Hippolytus,* p. 3.

[44] Litanies.

[45] የግብፅ (Coptic) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለቅዳሴ አገልግሎት የምትጠቀምባቸው ቅዳሴያት ሦስት ብቻ ናቸው፦ ቅዳሴ ባስልዮስ፥ ቅዳሴ ቄርሎስ እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ። የመጀመሪያው ቅዳሴ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመ ስለሆነ በእኛ ቤተ ክርስቲያን "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ባስልዮስ" ተብሎ ከሚታወቀው ጋር አንድ ነው። የተቀሩት ሁለቱ ግን በእኛ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ስያሜ ከተሰጣቸው ቅዳሴያት ፍጹም የተለዩ ናቸው። ግብፆች "ቅዳሴ ቄርሎስ" የሚሉት በቅዱስ ማርቆስ ስም የተሰየመውንና ወደ ግእዝ ቢተረጎምም እስካሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያናችን ያላሳተመችውን ቅዳሴ ነው፤ "ቅዳሴ ቄርሎስ" የሚል ስያሜ የተሰጠው፥ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ በዘመነ ፓትርክናው በቅዳሴ ማርቆስ ላይ መጠነኛ ማሻሻያ ስላደረገበት ነው - *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory, and Cyril* (Los Angeles: Coptic Orthodox Church Diocese of Southern USA, 2001).

ክርስቲያን፥ ከዚህ መጽሐፈ ሥርዓት የተወሰደ የጸሎት ክፍል አኰቴተ ቍርባን ካልእ[46] በሚል ርእስ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፈ ቅዳሴ[47] ውስጥ ተካትቷል፤ ነገር ግን ሙሉ ቅዳሴው እስካሁን አገልግሎት ላይ አልዋለም።[48] ጥንታውያን የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮችን በጥንቃቄ ጠብቃ ለትውልድ በማቆየት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ያገኘችው የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ግን፥ በ215 ዓ.እ. የተደረሰውን የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት (ሐዋርያዊ ትውፊት) የሥርዓተ አምልኮዋ ማዕከል በማድረግ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጊዜ ጀምሮ ስትጠቀምበት ኖራለች።

የዚህ መጽሐፈ ሥርዓት የግእዝ ትርጉምን የምናገኘው "ትእዛዝ ሲኖዶስ" በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ነው። መጽሐፉ 72 ትእዛዛት አሉት፤ ከእነዚህ ውስጥ የሐዋርያዊ ትውፊት አቻ የሚሆኑት 27 ትእዛዛት (ከትእዛዝ 21-48) ያሉት ናቸው። ይህን የትእዛዝ ሲኖዶስ ክፍል ሁጎ ድዌንሲንግ በ1946 እ.አ.አ. ወደ ጀርመንኛ ተርጉሞ፥ አቡሊዲስ ዘሮሜ እንደደረሰው የሚነገርለት መጽሐፈ ሥርዓት የግእዝ ትርጉም መሆኑን በማስረዳት አሳትሞታል።[49] ይህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት (ሐዋርያዊ ትውፊት) መግቢያው ላይ፥ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ መመሪያ የሚሆኑ ትእዛዛትን እንደያዘ ይገልጽና በትውፊት እነዚህን ትእዛዛት የተቀበሉ አማንያን በተቀበሉት ላይ ምንም ነገር እንዳይጨምሩ ወይም እንዳያጎድሉ ይማፀናል፦ "ናስተበቍዓክሙ ከመ ትስምዑ ወትዕቀቡ ትእዛዛተ ወኢትወስኩ ላዕሌሆሙ፥ ወኢታንትጉ እምኔሆሙ።"[50] እንዲሁም፥ ይህ ሐዋርያዊ ትውፊት የተጻፈበትን ምክንያት መግቢያው ሲገልጽ፥ ከእውቀት ማነስ ምክንያት የስህተት ትምህርቶች ወደ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መግባት ስለጀመሩ፥ ንጹሐን ምንጮች

---

[46] Eucharistic Prayer II.
[47] Missal.
[48] Jasper and Cuming, *Eucharistic Prayers,* p. 34.
[49] Duensing ለግእዙ Apostolic Tradition መግቢያ ሊሆንለት የሚችለውን ትእዛዝ 21ን ትቶ፥ በHorner ትርጉም 22ኛ ትእዛዝ በሆነው፦ "በእንተ ሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ወሥርዓተ ቍርባን" ይጀምራል። ይህንንም ትእዛዝ 21ኛ ያደርገዋል። *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, p. 10 እና *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Hugo Duensing (Göttingen: Vandenhoeck and Ruprecht, 1946) p. 16 ይመልከቱ።
[50] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 10።

የሆኑት የጌታ ሐዋርያት  አስተምህሮ እንዲጠበቅ ለማድረግ እንደሆነ ያስረዳል።[51] የትእዛዝ ሲኖዶስ የመጀመሪያዎቹ 20 አንቀጾች ሐዋርያዊ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን[52] በሚል ስም ከሚታወቀው መጽሐፈ ሥርዓት ጋር ተቀራራቢ ይዘት አላቸው። ከእነዚህ አንቀጾች መካከል 14ቱ፡- ስለጠባቡና ሰፊው መንገድ፥[53] ስለወርቃማው ሕግ፥[54] ከዝሙትና ነፍስን ከመግደል ስለመራቅ[55] ወዘተ. የጌታ ደቀ መዛሙርት ተናግረውታል የተባሉትን አባባሎች "ይቤ ዮሐንስ፥ ይቤ ማቴዎስ፥ ይቤ ጴጥሮስ" በማለት ይዘግባሉ። ከግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት (ትእዛዝ 21-48) ቀጥለው የሚመጡት ቀሪዎቹ ትእዛዛት (49-72) ቀደም ብለው ባሉት ትእዛዛት ውስጥ የተጠቀሱና የተደጋገሙ የሥርዓተ ሢመትና ሥርዓተ ቍርባን ጸሎታትን ይዘዋል። በተጨማሪም፡- ስለ ዓሥራት (ትእዛዝ 60)፥ ሥርዓተ ጸሎት (ትእዛዝ 65)፥ ሁለቱ ሰናብት (ቅዳሜና እሑድ - ትእዛዝ 66)፥ ላረፉ ወዳጆቻችን ሊደረግ ስለሚገባው ተዝካር (የመታሰቢያ ጸሎት - ትእዛዝ 70) እና ስለ ሥርዓተ ክህነት (ትእዛዝ 72) አጫጭር መመሪያዎችን ይሰጣሉ።[56]

ሐዋርያዊ ትውፊት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ሰፊ ቦታ ለመረዳት፥ ቤተ ክርስቲያናችን ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ ያዘጋጀቻቸው መጻሕፍት ከዚህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት ጋር ያላቸውን ዝምድና በአጭሩ ማየት ያስፈልጋል። ኤጲስ፡ቆጶሳት ሲሾሙ የሚጸለየው የመጀመሪያው ጸሎተ ሢመት፥ በግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት "በእንተ ሢመተ ኤጲስ፡ቆጶሳት ወሥርዓተ

---

[51] Cuming, *Hippollytus,* Ch. 1, p. 8.

[52] "Apostolic Church Order" - J. P. Arendzen, *An Entire Syriac Text of the Apostolic Church Order,* JTS, Vol. 3 (1902) pp. 59-80.

[53] "ይቤ ዮሐንስ፡- 'እስመ ፪ቱ መካናት ፍሉጣት እማንቱ፤ አሐቲ ለሕይወት ወአሐቲ ለሞት' " ትእዛዝ ፪፣ ገጽ 2።

[54] "ይቤ ማቴዎስ፡- 'ኵሎ ዘኢትፈቅድ ይግበሩ ለከ አንተሂ ኢትግበር ለካልእከ፤ . . . ዘትጸልእ ለርእስከ ኢትግበር ለካልእከ'" ትእዛዝ ፪፣ ገጽ 2. ጌታ በተራራው ስብከት ካስተማረው የተወሰደ ይመስላል፡- "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" (ማቴ. 7፥ 12)።

[55] "ይቤ ጴጥሮስ፡- 'ኢትቅትል ነፍሰ ወኢትዘሙ፤ . . . ወኢትቅትል ፃእፃአ (do not abort a fetus) በውስተ ከርሥ እሙ' " ትእዛዝ ፬፣ ገጽ 2፤ "ይቤ ፊልጶስ፡- 'አ ወልድየ ኢትኩን ፈታዌ እስመ ፍትወትሰ ትስሕብ ኀበ ዝሙት ወእምድኅሬሁ ትሬስዮ ለብእሲ ሰሐቀ ወስላቀ ለኵሉ። እስመ ፍትወት ጋኔን መስሕት ይእቲ" ትእዛዝ ፮፣ ገጽ 3።

[56] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, p. 64-78.

ቍርባን" የተሰኘ ርእስ ካለው 22ኛ ትእዛዝ ተወስዶና ተሻሽሎ መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ፦ "ጸሎት በእንተ ሢመተ ጵጵስና" በሚል ርእስ የተቀመጠው ነው።[57] በተመሳሳይ መልኩ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ለቀሳውስት እና ዲያቆናት ሢመት (ሹመት) የምትጠቀምባቸው ጸሎታት ምንጫቸውና መሠረታቸው የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ነው።[58] የቤተ ክርስቲያናችን ማኅሌት አገልግሎት የሚጀምርበትና የልዑል እግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት የሚገልጸው የምስጋና ቀለም፦ "ሃሌ ሉያ ዘውእቱ ብሂል ንወድሶ ለዘሀሎ እግዚአብሔር ልዑል። ስቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኵሎ ዓለመ በአሐቲ ቃል" ከዚሁ የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት 37ኛ ትእዛዝ የተወሰደ ነው።[59]

ይኸው የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት፦ "በእንተ ሥርዓተ ጥምቀት ወምህሮ ሃይማኖት" እና "በእንተ ሥርዓተ ጥምቀት" በሚል ርእስ የሚጀምሩ ንኡሰ ክርስቲያንን (ከአረማዊነት ወደ ክርስትና እምነት የመጡትን) የማጥመቂያ ሥርዓት ይዟል። ከትእዛዝ 30 የሚጀምረው ሥርዓተ ጥምቀት፥ ንኡሰ ክርስቲያን ለሦስት ዓመታት ያህል ትምህርተ ሃይማኖትን መማር እንዳለባቸው ይጠቁምና "በጊዜ ይነቁ ዶርሆ - ዶሮ በሚጮህበት ጊዜ/ሰዓት" የሚጸለዩ ጸሎታትን ያካትታል። በተጨማሪም፥ ለመጠመቅ የተዘጋጀው ሰው በጸሎተ ሃይማኖት የተጠቀሱትን መሠረታዊ የእምነት አንቀጾች መቀበሉን ለማረጋገጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎችንም ይዟል።[60] "በእንተ ሥርዓተ ሀብት ዘሐዋርያት" የሚል ርእስ ያለው የትእዛዝ 39 ክፍል የሆነውና ሁለተኛው "ሥርዓተ ጥምቀት" ደግሞ፦ "ጸሎት በእንተ እለ ወሀቡ አስማቲሆሙ - [ለመጠመቅ] ስማቸውን ስለሰጡ [የሚጸለይ] ጸሎት"፥ "ጸሎተ ርቅየተ ማይ - ጸበል የመርጨት ጸሎት"፥ "ጸሎት [ላዕለ] ቅብዐተ በለሳን ለእለ

---

[57] የሚከተሉትን ጸሎታት በማነጻጸር ይመልከቱ፦ *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ.10፤ *Testamentum domini éthiopien,* ed. and trans. Beylot፣ ምዕ. 12፣ ገጽ. 24፤ *መጽሐፈ ሥርዓት ዘሢመተ ክህነት* (Washington D.C: The Legitimate and Exiled Holy Synod, 2007) ገጽ. 9-10።

[58] *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፳፬፡ በእንተ ሢመተ ቀሳውስት" እና "ትእዛዝ ፳፫፡ በእንተ ሢመተ ዲያቆናት"፣ ገጽ 30-34 ይመልከቱ።

[59] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፴፯፣ ገጽ 28፤ *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, p. 76.

[60] *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፴-፴፬፣ ገጽ. 46-64።

ይጠመቁ - የሚጠመቁ ሰዎች የሚቀቡት ቅብዐ ቅዱስ ላይ የሚጸለይ ጸሎት" እና "አንብሮተ እድ ላዕለ ንኡሰ ክርስቲያን - በንኡሰ ክርስቲያን ላይ እጅ መጫን"[61] የሚሉ ክፍሎችን ያካትታል። ሁለቱም የጥምቀት ሥርዓቶች ከተከናወኑ በኋላ ፍጻሜ የሚያገኙት በቅዱስ ቍርባን አገልግሎት እንደሆነ መጽሐፈ ሥርዓቱ ያሳያል። ቤተ ክርስቲያናችን ከሁለቱም ሥርዓተ ጥምቀት የተውጣጡ ጸሎታትን ወስዳ "መጽሐፈ ክርስትና" የተባለ መጽሐፍ አዘጋጅታለች። ነገር ግን ጥንታውያኑ ጸሎቶች የተዘጋጁት ከአረማዊ እምነት ተመልሰው ወደ ክርስትና እምነት ለገቡት (ንኡሰ ክርስቲያን) እንጂ ከክርስቲያን ቤተሰብ ለተወለዱ ሕፃናት አለመሆኑ ከግንዛቤ ስላልገባ፥ እስካሁን ድረስ ሕፃናትን ለማጥመቅ የምንጠቀመው ለንኡሰ ክርስቲያን የተዘጋጀውን ጥንታዊ ጸሎት ነው።[62]

## አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ሄጶሊጦስ/አቡሊዲስ ዘሮሜ ወይስ ቅዳሴ ሐዋርያት?

በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው፥ ሐዋርያዊ ትውፊት ለረጅም ጊዜ የቅዱስ ሄጶሊጦስ ወይም አቡሊዲስ ዘሮሜ ድርሰት እንደሆነ ይታመን ነበር። ከዚህ መጽሐፈ ሥርዓት የተወሰዱ አንዳንድ ክፍሎች የሚገኙባቸው 38ቱ "ቀኖናተ አቡሊዲስ"[63] በጥንታውያን አባቶቻችን ዘንድ የታወቁ ስለሆኑ፥ ከዚህ ጥንታዊ መጽሐፈ ሥርዓት የተወሰደውን ቅዳሴ፡- "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ሄጶሊጦስ ወይም ዘቅዱስ አቡሊዲስ ዘሮሜ" በማለት ሊሰይሙት ይችሉ ነበር። ነገር ግን፥ የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት የሚገኝበት ትእዛዝ ሲኖዶስ መግቢያው ላይ፡- "ዝንቱ ሲኖዶስ ዘአበው ሐዋርያት ዘሠርው ለአርትዖ ቤተ ክርስቲያን[64] - ይህ [መጽሐፈ] ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያንን ለማቅናት [መመሪያ ይሆን ዘንድ] አባቶች ሐዋርያት የሠሩት ነው" ስለሚል፥ አስተዋዮቹ አባቶቻችን ቅዳሴውን በአቡሊዲስ ዘሮሜ ስም ከመሰየም

---

[61] ዝኒ ከማሁ፡ ትእዛዝ ፴፱፣ ገጽ 78-126።

[62] "ጸሎት በእንተ ይትረቀዩ ንዑሰ [*sic*] ክርስቲያን" እና "ጸሎት በእንተ እለ ወሀቡ አስማቲሆሙ"፥ *መጽሐፈ ክርስትና* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ 1994፣) ገጽ 15-17፣ 20-28 ይመልከቱ።

[63] Bausi, "Hippolytus," *EA*, Vol 3, p.36፤ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፥ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት* (አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1963 ዓ.ም.) ገጽ 226.

[64] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ገጽ 1።

ይልቅ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ብለው ጠሩት። በተመሳሳይ መልኩ፥ ከመጽሐፈ ኪዳን[65] የተወሰደውን አኰቴተ ቍርባን "ቅዳሴ እግዚእ - የጌታ ቅዳሴ" ብለው እንደሰየሙት ማለት ነው።

ከግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ተወስዶና አንዳንድ ጸሎታትና ዝማሬያት (ለምሳሌ፡- ዲያቆኑ "በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ" ብሎ በዜማ የሚጀምረውና በንባብ የሚጨርሰው፥ ጸሎተ ቡራኬ፥ ጸሎተ ፈትቶ ወዘተ.) ተጨምረውበት "አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት" የሚል መጠሪያ የተሰጠው ቅዳሴ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ቅዳሴ [66] ሆኗል። [67] እነዚህ ክፍሎች በየትኞቹ ዘመናት እየተጨመሩ እንደገቡ ሊያስረዱን የሚችሉ በቂ ታሪካዊ ፍንጮች የሉም፤ እጅግ ጥንታዊ የሚባሉና በታወቁ ቤተ መጻሕፍት የሚገኙት የብራና መጻሕፍተ ቅዳሴ ከ17ኛው ምእት ዓመት በኋላ የተጻፉ ናቸው። [68] ለግንዛቤ እንዲረዳን፥ የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ የሚገኘው አኰቴተ ቍርባን ላይ የተደረገውን ለውጥ እና የተጨመሩ ክፍሎችን በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡-

| ሥርዓተ ጥምቀት እና የአኰቴተ ቍርባኑ ይዘት | የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቍርባን | አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት |
|---|---|---|
| አምኃ ቅድሳት (የተቀደሰ | "ወእምድኅረ ፈጸሙ ጸልዮ ይትዋሀቡ ሰላመ | ይበል ዲያቆን፡- "ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት ወፍቅር ተአምኁ |

[65] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, pp. 35-44.
[66] Principal anaphora.
[67] "The Anaphora of the Ethiopic Church Ordinaces" የሚለውን ርእስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይመልከቱ፡- *Ancient Liturgies: Being Reprint of the Texts, either Original or Translated, of the Most Representative Liturgies of the Church from Various Sources*, eds. C. E. Hammond and F. E. Brightman (New Jersey: Gorgias Press, 2006) p. 769.
[68] Alessandro Bausi ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ይጠቅሳል፡- BritLib Orient. 545 (1670/75 ዓ.እ.); BN d'Abbadie 13 and 72 (17ኛው ምእት ዓመት); EMML 1434 (1680 ዓ.እ.); EMML 4190 (1671/93 ዓ.እ.); EMML 2811 (1671/75 ዓ.እ.); EMML 2021, 3084, 3553, 3649, 3945, 4742 (17ኛው እና 18ኛው ምእት ዓመታት); VatLib Comboni B 30 (1660/65 ዓ.እ.) – Bausi, "Qəddase: Mäṣḥafä Qəddase," *EA,* Vol. IV, p. 280.

| | | |
|---|---|---|
| ሰላምታ) | በበይናቲሆሙ በአፉሆሙ"[69] | በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት"[70] |
| አውሥኦ<br>(ምልልስ) | -ኤጲስ ቆጶስ፡- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ<br>-ሕዝብ፡- ምስለ መንፈስከ<br>-ኤጲስ ቆጶስ፡-አልዕሉ አልባቢክሙ<br>-ሕዝብ፡- ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ<br>-ኤጲስ ቆጶስ፡-ነአኵቶ ለእግዚአብሔር<br>-ሕዝብ፡-ርቱዕ ይደሉ ወጽድቅ።[71] | -ይበል ካህን፡- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ<br>-ይበሉ ሕዝብ፡- ምስለ መንፈስከ<br>-ይበል ካህን፡- አእኵትዎ ለአምላክነ<br>-ይበሉ ሕዝብ፡-ርቱዕ ይደሉ<br>-ይበል ካህን፡- አልዕሉ አልባቢክሙ<br>-ይበሉ ሕዝብ፡- ብነ ኀበ እግዚአብሔር<br>አምላክነ።[72] |

[69] "ጸሎት ከፈጸሙ በኋላ እርስ በእርሳቸው በአፋቸው ሰላምታ ይሰጣጡ" የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው የተጠመቁ አዲስ አማንያን ወደ ክርስቲያኖች ኅብረት ሲቀላቀሉ የሚደረገውን የተቀደሰ ሰላምታ (holy kiss) ነው። የጥምቀቱ ሥርዓት እንዳለቀ፥ ሰላምታ ተለዋውጠው ሥርዓተ ቅዳሴው ይቀጥላል። *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፴፩፣ ገጽ 60።

[70] ይህ የዲያቆኑ ትእዛዝ የቅዳሴ ሐዋርያት (Anaphra of the Apostles) ክፍል ሳይሆን፥ "Liturgy of the Word" በመባል የሚታወቀው የቅዳሴው ሁለተኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ስለሚገኝ ወደ ሶስተኛውና ዋናው የቅዳሴ ክፍል (ፍሬ ቅዳሴ) ከመግባታችን በፊት ከክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር የሰላምና የፍቅር ሰላምታን በመለዋወጥ መዘጋጀት እንዳለብን ያመለክታል። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ሥርዓተ ቅዳሴ" ቍ. 58፣ ገጽ 100 ይመልከቱ። የግእዙ Apostolic Tradition በእንግሊዝኛው ትርጉም በማይገኘውና "ጸሎት ቀዳሚት በእንተ ጥምቀት ዲበ ማይ" የሚል ርእስ በተሰጠው ክፍል ውስጥ፥ "ይብል ዲያቆን ለሕዝብ ተአምኁ በበይናቲክሙ - ዲያቆን ሕዝቡን እርስ በእርሳችሁ እጅ ተነሣሡ ይላል" የሚል ትእዛዝ (rubric) አለው። *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ገጽ 88 እና 120 ይመልከቱ።

[71] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፷፪፣ ገጽ 11። ይህ አውሥኦ (Dialogue) በቅደም ተከተል ደረጃ በሌሎች ጥንታውያን ቅዳሴያት ውስጥ ካለው Dialogue ጋር አንድ ነው። ለምሳሌ፥ የቅዳሴ ማርቆስ Dialogue ልክ እንደዚህ፥ ካህኑ "እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ" ካለ በኋላ፥ በመቀጠል የሚለው "አልዕሉ

| | | |
|---|---|---|
| መቅድም | "ነአኵተከ እግዚኦ[73] በፍቁር ወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘበደኃሪ መዋዕል ፈነውከ[74] ለነ ወልደከ መድኀነ ወመቤዝወ መልአከ ምክርከ። ዝ ቃል እንተ እምኀቤከ[75] ውእቱ ዘቦቱ ኵሎ ገበርከ ፈቂደከ።"[76] | "ነአኵተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ዘበደኃሪ መዋዕል ፈኖከ ለነ ወልደከ መድኀነ ወመቤዝወ መልአከ ምክርከ፤ ዝ ቃል እንተ እምኔከ ውእቱ ፥ ወቦቱ ኵሎ ገበርከ በፈቃድከ።"[77] |
| ተዝካረ ቅዱሳን ወጸሎት በእንተ እለ ኖሙ(ስላረፉ ሰዎች የሚደረግ | - | "በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳስት አባ _______________ ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ አባ __________________ እንዘ የአኵቱከ በጸሎቶሙ |

አልባቢክሙ" እንደሆነ ያመለክታል፤ ከዚያም "አእኵትዎ ለአምላክነ" የሚለው ይከተላል። "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ"*Missale Ethiopicum,* ገጽ 117 ይመልከቱ። Hammond እና Brightman ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውና "The Anaphora of the Ethiopic Church Ordinaces" የሚል ርእስ የተሰጠው ቅዳሴ ሐዋርያት ይህን ቅደም ተከተል የሚጠብቅ Dialogue አለው - *Ancient Liturgies,* ገጽ 808 ይመልከቱ። ነገር ግን፥ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችን ባሳተመችው መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የምናገኘው "ቅዳሴ ሐዋርያት" ይህንን structure የማይጠብቅ Dialogue ይዟል፤ ካህኑ "እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ" ካለ በኋላ "አልዕሉ አልባቢክሙ" ማለት ሲገባው፥ መጽሐፈ ቅዳሴው፦ "አእኵትዎ ለአምላክነ" ይበል ይላል - መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 2፣ ገጽ 101 ይመልከቱ። ከቅዳሴ ባስልዮስ በስተቀር ቤተ ክርስቲያናችን ያሳተመቻቸው ሁሉም ቅዳሴያት የቅዳሴ ሐዋርያትን Dialogue ይከተላሉ። መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የሚገኘው ቅዳሴ ባስልዮስ "The Egyptian Anaphora of St. Basil" በሚል ስም የሚታወቀው የዐረብኛው ቅዳሴ ባስልዮስ ትርጉም ስለሆነ የጥንቱን structure (እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ፥ አልዕሉ አልባቢክሙ፥ አእኵትዎ ለአምላክነ) ይጠብቃል- መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ባስልዮስ፡ ቍ. 5፣ ገጽ 278 ይመልከቱ።

72 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" 2000፣ ቍ. 2፣ ገጽ 101።

73 የDuensing ትርጒም "ነአኵተከ እግዚአብሔር በፍቁር ወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ" ይላል። *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 20።

74 "ፈኖከ" – Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 20።

75 "እንተ እምኔከ" - ዝኒ ከማሁ።

76 *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11።

77 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" 2000፣ ቍ. 4-5፣ ገጽ 101።

| | | |
|---|---|---|
| የምልጃ ጸሎት) | | ወበስእለቶሙ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት፥ ዘካርያስ ካህን ወዮሐንስ መጥምቅ፤ ወበእንተ ኲሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት እለ አዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት . . .”[78] |
| ጸሎተ ቡራኬ | - | “ኦ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ባርክ ዲበ ሕዝብከ ፍቁራን ክርስቶሳውያን . . .”[79] |
| የምልጃ ጸሎት ላረፉ ሰዎች (ከላይኛው የቀጠለ) | - | - ንፍቅ ዲያቆን፡- “መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት፥ ጳጳሳት፥ ኤጲስቆጶሳት፥ ቀሳውስት ወዲያቆናት፥ ወኲሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን”[80]<br>- ይበል ካህን፡- “ለእሉኒ ወለኲሎሙ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣሃሎሙ”[81] |

[78] ሠራዒው ዲያቆን፥ በዚህ ክፍል ከ4ቱ ወንጌላውያን ጀምሮ፥ የወላዲተ አምላክ ማርያምንና የጌታ ደቀመዛሙርትን ስሞች፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስንና ከእርሱ ጋር በወንጌል አገልግሎት የደከሙትን ሲላስና በርናባስን፤ የጳውሎስ የመንፈስ ልጆችን፡- ቲቶንና ጢሞቴዎስን፤ እንዲሁም ፊልሞናንና ቀሌምንጦስን ያነሣል። በመጨረሻም፡- “የሁሉም ጸሎት ትድረሰን፥ ከእነርሱም ጋራ እኛን ጎብኝ። ከሁሉ በላይ የምትሆን የሐዋርያትንም ቤተ ክርስቲያን አስብ፥ በፍቅርዋ በክርስቶስም በተደረገው በከበረ ደም፤ በእምነት የቃልን መንገድ የሚያቀኑ ሊቃነ ጳጳሳቱን፥ ጳጳሳቱን፥ ኤጲስቆጶሳቱን፥ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱንም ሁሉ አስብ” ይላል። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ “ቅዳሴ ሐዋርያት” ቍ. 7-9፣ ገጽ 102-103። ይህ ተዝካረ ቅዱሳን ወጸሎት በእንተ እለ ኖሙ (Diptychs) ሐዋርያዊ ትውፊት (Apostolic Tradition) ውስጥ ስለማይገኝ፥ ከሌላ ምንጭ ተወስዶ የአኰቴተ ቍርባኑን መግቢያ (Preface) አቋርጦ መሃል ላይ እንዲገባ መደረጉ ግልጽ ነው። የዚህ ጸሎት ምንጭና ከመቼ ጀምሮ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ውስጥ እንደገባ ለማወቅ ሰፊ ጥናት ያስፈልጋል።

[79] “ጸሎተ ቡራኬ ዘባስልዮስ” የሚል ርእስ ስለተሰጠው፥ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለሥርዓተ ቅዳሴ የሚውሉ ጸሎታትን በመድረስ የሚታወቀው ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ካዘጋጃቸው ጸሎታትና ቡራኬያት ተወስዶ እዚህ ላይ እንደገባ መረዳት እንችላለን። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ቍ. 10፣ ገጽ 103።

[80] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ “ቅዳሴ ሐዋርያት” ቍ. 22፣ ገጽ 105።

[81] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 23፣ ገጽ 105። “ለእሉኒ ወለኲሎሙ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣሃሎሙ - የእነዚህን የሁሉንም ነፍሳቸውን አሳርፍ ይቅርም በላቸው” የሚለው የሠራዒው ካህን ጸሎት፥ ሠራዒው ዲያቆንና

| | | |
|---|---|---|
| መቅድም (ከላይኛው የቀጠለ) | "ወፈነውከ እምሰማይ ወልደከ ውስተ ማኅፀነ ድንግል[82]። ዘሥጋ ኮነ ወተጸውረ ውስተ በከርሥ፤ ወወልድከ ተዐውቀ እመንፈስ ቅዱስ"[83] | -<u>ይበል ካህን</u>፡- "ዘፈኖከ እምሰማይ ወልደከ ውስተ ማኅፀነ ድንግል፥ ተፀውረ በከርሥ፥ ሥጋ ኮነ፥ ወወልድከ (ወልደቱ) ተዐውቀ እመንፈስ ቅዱስ"[84] |
| የዝማሬ ሱራፌል መግቢያ እና ዝማሬው | - | -<u>ይበል ካህን</u>፡- "ለከ ለዘይቀውሙ ቅድሜከ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት ቅዱሳን መላእክት ወሊቃነ መላእክት . . ." <br> -<u>ይበል ካህን</u>፡- "በ፪ኤ ክነፊሆሙ ይከድኑ ገጾሙ . . ." <br> -<u>ይበል ካህን</u>፡- "ወዘልፈ እንከ ኵሎሙ ከመ ኪያከ ይቄድሱ ወይዌድሱ፥ ወምስለ ኵሎሙ እለ ይቄድሱከ ወይዌድሱከ ዓዲ ተወከፍ ዘዚአነሂ ቅዳሴ እለ ዘንብለከ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም . . ." <br> -<u>ይበሉ ሕዝብ</u>፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ |

ንፍቁ ዲያቆን ለሚሉት *Diptychs* ማጠቃለያ ነው። ይህ ዓረፍተ ነገረ የApostolic Tradition አኰቴተ ቍርባን (eucharistic prayer) ውስጥ አይገኝም።

[82] የDeunsing ትርጉም፡- "ወፈኖከ እምሰማይ ውስተ ማሕፀነ [*sic*] ድንግል" ይላል፤ Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 20።

[83] Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11።

[84] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 23፣ ገጽ 105-106። ቅዳሴ ሐዋርያት ከግእዙ Apostolic Tradition የተወሰደውን የቍርባን ምስጋና (eucharistic prayer) መቅድም እዚህ ላይ በድጋሚ ያቋርጥና Pre-Sanctus እና Sanctus የተባሉ ክፍሎችን ያስገባል።

| | | |
|---|---|---|
| | | ቅድሳተ ስብሐቲከ"<br>-ይበል ካህን፡- "አማን መልዐ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ በእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ"[85] |
| መቅድም (ከላይኛው የቀጠለ) | "እምድንግል ተወሊዶ[86] ከመ ይፈጽም ፈቃደከ ወሕዝበ ለከ ይግበር።"[87] | "ቅዱስ ወልድከ መጽአ፥ ወእምድንግል ተወልደ ከመ ፈቃደከ ይፈጽም፥ ወሕዝበ ለከ ይግበር"[88] |
| ተዘከረነ + አዕርጎተ ዕጣን | - | -ይበሉ ሕዝብ፡- "ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ፤ ተዘከረነ እግዚኦ ኦ ሊቅነ . . ."[89]<br>-ትእዛዝ፡- "ወእምዝ ንፍቅ ካህን ይውግር ዕጣነ ወያቅርብ ሎቱ ማዕጠንተ ወይዕጥን እዴሁ ወያዕርግ በበ፫ቱ ጊዜ ላዕለ ኅብስት ወጽዋዕ"[90] |
| ነገረ ድኅነት[91] | "ሰፍሐ እደዊሁ ለሕማም | -ይበል ካህን፡- "ሰፍሐ እደዊሁ |

[85] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 25፥27፥29፥30፥32፥ 33፣ ገጽ 106-107።
[86] "እምድንግል ተወሊዶ" የሚለው በDuensing ትርጕም አይገኝም - Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 20። የCuming ትርጕም፡- "he was made flesh and was manifestd as your son, being born of the [H]oly Spirit and the Virgin" ይላል። Cuming, *Hippollytus,* Ch. 4, p. 10.
[87] Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11።
[88] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 33፣ ገጽ 107። "ቅዱስ ወልድከ መጽአ - ቅዱስ ልጅህ መጣ" የሚለው የገባው መቅድሙ ተቋርጦ ስለነበር ከሚቀጥለው ዓረፍተ ነገር ጋር ለማያያዝ እንዲመች ነው።
[89] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 34፣ ገጽ 107።
[90] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 35፤ ገጽ 107።
[91] Salvation history.

| | | |
|---|---|---|
| | ከመ ሕሙማነ ይፍታሕ ለእለ ተወከሉ በላዕሌከ[92]። ዘተውህበ በፈቃዱ<br><br>ለሕማም ከመ ሞተ ይሥዓር፥ ወማእሠረ ሰይጣን ይብትክ፥ ወይኪድ ሲኦለ፥ ወቅዱሳነ ይምራሕ፥ ሥርዓተ ይትክል፥ ወትንሣኤሁ ያዕቅ[93] [*sic*]::"[94] | ለሕማም፤ (ሐሚሞ) ከመ ሕሙማነ ያድኅን እለ ተወከሉ በላዕሌሁ።<br><br>ዘተውህበ በፈቃዱ ለሕማም ከመ ሞተ ይሥዓር፥ ወማእሠረ ሰይጣን ይብትክ፥ ወይኪድ ሲኦለ፥ ቅዱሳነ ይምራሕ፥ ሥርዓተ ይትክል፥ ወትንሣኤሁ ያዑቅ።"[95] |
| *ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ* | "ነሢኦ እንከ ኅብስተ[96] አእኰተ፥ ወይቤ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ ዘበእንቲአከሙ ይትፈተት [*sic*]። [97] ወከማሁ ጽዋዐኒ ይቤ[98] ዝ ውእቱ ደምየ | -<u>ይበል ዲያቆን</u>፡- "አንሥኡ እደዊከሙ ቀሳውስት"[99]<br><br>-<u>ይበል ካህን</u>፡- "በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብዕዎ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት |

[92] "ሰፍሐ እደዊሁ ሐሚሞ ከመ ለሕሙማን ይፍታሕ ለእለ ተወከሉ ላዕሌከ ፥" - Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 20።
[93] የDuensing ትርጉም "ወትንሣኤ ያዕቅ" ይላል - Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 20። ቅዳሴ ሐዋርያት ላይ ግን የፊደል ግድፈቱ ታርሞ፡- "ወትንሣኤሁ ያዑቅ - ትንሣኤውንም ይገልፅ ዘንድ" ተብሏል። መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 37፣ ገጽ. 108።
[94] Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11-12።
[95] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" 2000፣ ቍ. 37፣ ገጽ 107-108።
[96] የHorner ትርጉም፡- "በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ" ይላል - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12። Horner ትርጉም ውስጥ የተጨመረው፡- "በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ" የCuming እንግሊዝኛ ትርጉም ውስጥም አይገኝም። ልክ እንደ Duensing ትርጉም "he took bread" ብሎ ይጀምራል። Cuming, *Hippollytus,* Ch. 4, p.11.
[97] "ወይቤሎሙ ንሥኡ ወብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ ዘበእንቲአከሙ ይትፌተት ለኅድገተ ኃጢአት" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "shall be broken for you" - Cuming, *Hippollytus,* Ch. 4, p.11.
[98] "ወከማሁ ጽዋዓኒ አእኲቶ ይቤ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "Likewise also the cup, saying, . . ." Cuming, Ch. 4, p.11.
[99] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 38፣ ገጽ 108።

| | | |
|---|---|---|
| | ዘበእንቲአከሙ ይትከዐው፤ ሶበ ትገብርዎ ለዝ ተዝካረ ዚአየ ትገብሩ።" | በብፁዓት እለ እንበለ ነውር"[100]<br><br>-ይበሉ ሕዝብ፡- "ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን"[101]<br><br>-ይበል ካህን፡- "አንቃዕደወ ሰማየ ኀቤከ ኀበ አቡሁ፤ አእኰተ፥ ባረከ፥ ወፈተተ . . . ወወሀቦሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ<br><br>ለዘበእንቲአከሙ ይትፌተት ለኀድገተ<br><br>ኃጢአት"[102]<br><br>-ይበሉ ሕዝብ፡- "አሜን፥ አሜን፥ አሜን ነአምን ወንትአመን . . ."[103]<br><br>-ይበሉ ሕዝብ፡- "ወከማሁ ጽዋዓኒ እእኩቶ፥ ባሪኮ፥ ወቀዲሶ መጠዎሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአከሙ ይትከዐው (ለቤዛ ብዙኃን) ለሥርየተ ኃጢአት"[104] |

[100] ዝኒ ከማሁ፡ ቊ. 39፣ ገጽ 108።
[101] ዝኒ ከማሁ፡ ቊ. 40፣ ገጽ 108።
[102] ዝኒ ከማሁ፡ ቊ. 41-42፣ ገጽ 108።
[103] ዝኒ ከማሁ፡ ቊ. 43፣ ገጽ 108።
[104] ዝኒ ከማሁ፡ ቊ. 44፣ ገጽ 108-9።

| | | |
|---|---|---|
| | | -<u>ይበሉ ሕዝብ፡-</u> "አሜን፥ አሜን፥ አሜን ነአምን ወንትአመን . . ."[105]<br>-<u>ይበል ካህን</u>፡- "ወሶበ ትገብርዎ ለዝንቱ ተዝካረ ዚአየ ትገብሩ"[106]<br>-<u>ይበሉ ሕዝብ፡-</u> "ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ፥ ወትንሣኤከ ቅድስት . . ."[107] |
| ዝከረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ | "እንዘ ንዜከር እንከ ሞቶ ወትንሣኤሁ[108] ናቄርብ ለከ ዘንተ ኅብስተ ወጽዋዐ[109] እንዘ ናአኵተከ ዘቦቱ ረሰይከነ ተድላነ[110] ከመ ንቁም ቅድሜከ፥ ወለከ ንትከሀን።"[111] | - <u>ይበል ካህን</u>፡- "ይእዜኒ እግዚኦ እንዘ ንዜከር ሞተከ ወትንሣኤከ ንትአመነከ ወናቄርብ ለከ ዘንተ ኅብስተ፥ ወዘንተ ጽዋዐ እንዘ ናአኵተከ ወቦቱ ረሰይከ ለነ ለተድላ ንቁም ቅድሜከ ወለከ ንትከሀን።"[112] |
| ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ | "ወናስተበቍዐከ[113] ከመ ትፌኑ መንፈሰከ ቅዱሰ ዲበ ቍርባን[114] ዘቤተ- | "ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፌኑ መንፈሰ ቅዱሰ ወኃይለ፥ ዲበ ዝንቱ ኅብስት |

105 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 45፣ ገጽ 109።
106 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 46፣ ገጽ 109።
107 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 47፣ ገጽ 109።
108 "እንዘ ንዜከር እንከ ሞተከ ወትንሣኤከ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "Remembering therefore his death and resurrection" Cuming, Ch. 4, p.11.
109 "ወዘንተ ጽዋዓ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12።
110 "ረሰይከነ ለተድላ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "you have held us worthy to stand before you and minister to you" - Cuming, Ch. 4, p.11.
111 Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 22።
112 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 48፣ ገጽ 109።
113 "ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዓከ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12።
114 "ዲበ ዝ ቍርባን" - ዝኒ ከማሁ።

| | | |
|---|---|---|
| | ክርስቲያን፤ ደሚረከ ተሀብ ለኵሉ ለእለ ይነሥኡ ቅድሳተ[115]፥ ወለምልዐተ መንፈስ ቅዱስ ወለአጽንዖ ሃይማኖት፥ በአማን" | ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ ይረስዮ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ወአምላክነ (ወመድኃኒነ) ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም"[116]<br>-ይበሉ ሕዝብ፡- አሜን እግዚኦ መሐረነ፥ እግዚኦ መሐከነ፥ እግዚኦ ተሣሃለነ[117]<br>-ይበል ዲያቆን፡- "በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ . . ."[118]<br>-ይበሉ ሕዝብ፡- "በከመ ሀሎ ሕልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም"[119]<br>-ይበል ካህን፡- "ደሚረከ ተሀቦሙ ለኵሎሙ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ ይኩኖሙ ለቅድሳት ወለምልዐተ መንፈስ ቅዱስ ወለአጽንዖ ሃይማኖት ዘበአማን" |
| | "ከመ ኪያከ ይሴብሑ ወይዌድሱ[120]" በወልድከ | "ከመ ኪያከ ይቄድሱ ወይዌድሱ ወለወልድከ ፍቁርከ ኢየሱስ |

[115] "ደሚረከ ተሀቦሙ ለኵሎሙ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ ይኩኖሙ ለቅድሳት" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "And we ask that you would send your [H]oly Spirit upon the offering of our holy church; that, gathering (her) into one, you would grant to all who partake of the holy things" - Cuming, Ch. 4, p.11.
[116] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 49፣ ገጽ 110።
[117] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 50፣ ገጽ 110።
[118] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 51፣ ገጽ 110።
[119] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 52፣ ገጽ 110። በግእዙ Apostolic Tradition ይህ የሕዝብ ዝማሬ የተጠቀሰው አኰቴተ ቍርባኑ ካለቀ (ከDoxology) በኋላ ነው። የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ካህኑ ከሚጠይቅበት (*Epiclesis*) ጋር አብረው የተጠቀሱ የልመና ጸሎቶችን አቋርጦ ለምን እንደገባ ግልጽ አይደለም። Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12 እና Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 24 ይመልከቱ።
[120] "ይሰብሑ ወይወድሱ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "that we may praise and glorify you" - Cuming, Ch. 4, p.11.

| | | |
|---|---|---|
| የማጠቃለያ ምስጋና እና አሜን | ኢየሱስ ክርስቶስ፤[121] ዘቦቱ ለከ ስብሐት ወኃይል በቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[122] | ክርስቶስ (ዘምስለ መንፈስ ቅዱስ) ለዓለመ ዓለም።[123]<br><br>ይበሉ ሕዝብ፡- አሜን።[124] |
| ጸሎተ ፈትቶ | -ኤጲስቆጶስ ይበል፡-<br>"ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ የሀበነ በበረከት ንንሣእ ዘቅዱስ ምሥጢር[125]፤ ወኢመነሂ እምውስቴትነ | -ይበል ካህን፡- ጸሎተ ፈትቶ፡-<br>"ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ የሀበነ በበረከት ንንሣዕ ዘእምቅዱስ ምሥጢር፤ ጽንዓተ ለነ የሀበነ፥ ወኢመነሂ |

121 "በወልድከ መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ "thourgh your child Jesus Christ" - Cuming, Ch. 4, p.11.

122 *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፳፭፣ ገጽ 22 እና 24። በእንግሊዝኛው ትርጕም፥ ኤጲስቆጶሱ የሚጸልየው አኰቴተ ቍርባን (Eucharistic prayer):- "we [. . .] praise and glorify you through your child Jesus Christ, through whom be glory and honour to you with the Holy Spirit, in your holy Church, both now and to the ages of ages. Amen" ብሎ ካበቃ በኋላ የሚጨምረው ነገር የለም፤ የሚቀጥለው ክፍል "Of the Offering of Oil" የሚል ርእስ ተሰጥቶታል። Cuming, *Hippollytus,* Ch. 5, p. 11 ይመልከቱ። የግእዙ Apostolic Tradition ግን፥ ከአኰቴተ ቍርባኑ ፍጻሜ በኋላ "በእንተ ቍርባን" በሚል ርእስ ሥር የሚገኙ፥ በእንግሊዝኛው ትርጕም የሌሉና ቅዳሴ ሐዋርያት ውስጥ፡- "ጸሎተ ፈትቶ፥ ሐዳፌ ነፍስ፥ አንብሮ እድ ወዘተ." የተሰኙ ርእሶች የተሰጣቸውን ጸሎታት ይጨምራል። *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12-14፤ *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፳፭፣ ገጽ 24፥26፥28 እና 30 ይመልከቱ። ይህ የሚያሳየው፥ Apostolic Tradition ወደ ግእዝ ከተተረጐመ በኋላ እነዚህ ክፍሎች ከሌሎች ምንጮች (liturgical sources) ተወስደው የተጨመሩ መሆናቸውን ነው፤ ምክንያቱም Apostolic Tradition በተደረሰበት በ3ኛው ምእት ዓመት እነዚህን ሁሉ ክፍሎች ያሟላ ቅዳሴ ማግኘት አይቻልምና።

123 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 53፣ ገጽ 110።

124 ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 111።

125 "ምሥጢረ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12::

| | | |
|---|---|---|
| | ኢያርስሕ አላ ለኵሉ ተድላሆሙ ይረሲ ለእለ ይትሜጠዉ ንሥአተ ቅዱስ ምሥጢር[126] ዘሥጋ[127] ወደሙ ለክርስቶስ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ።"[128]<br><br>-ዲያቆን ይብል[129]፡- ጸልዩ | እምውስቴትነ ኢያርስሕ አላ ለኵሎሙ ተድላሆሙ ይረሲ ለእለ ይትሜጠዉ ንሥአተ ቅዱስ ምሥጢር ዘሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ።"[130] |
| አቡነ ዘበሰማያት | - | -ይበል ዲያቆን፡- ጸልዩ<br><br>-ይበሉ ሕዝብ፡- "አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ . . ."[131] |
| ጸሎተ ፈትቶ (ከላይኛው የቀጠለ) | [132]"እግዚአብሔር ዘኵሎ ትእኅዝ ንሥአተ ዘቅዱስ ምሥጢር[133] ጽንዐተ ለነ ሀበነ። ወኢመነሂ እምውስቴትነ ኢታርስሕ፤ አላ ኵሎ ባርክ በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ | -ይበል ካህን፡- "እግዚአብሔር አምላክነ ዘኵሎ ትእኅዝ ንሥአተ ዘቅዱስ ምሥጢር ጽንዐተ ለነ ተሀበነ። ወኢመነሂ እምውስቴትነ ኢታርስሕ፤ አላ ኵሎ ባርክ በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ |

126 "ዘቅዱስ ምሥጢር" - ዝኒ ከማሁ።

127 "ሥጋሁ" - ዝኒ ከማሁ።

128 Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 24 እና 26።

129 "ይበል ዲያቆን" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 13።

130 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 58-59፣ ገጽ 111-112።

131 ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 60፣ ገጽ 112።

132 የHorner ትርጉም ከጸሎቱ በፊት "ወይበል ኢጲስ፡ቆጶስ" የሚል ትእዛዝ (rubric) ይጨምራል - ዝኒ ከማሁ።

133 "ምሥጢርከ" - ዝኒ ከማሁ።

| | | |
|---|---|---|
| | ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ወለዝሉፉ[134] ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[135] | ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[136] |
| ሥራዊተ መላእክቲሁ + አርኅዉ | - | -ይበሉ ሕዝብ፡- በከመ ምሕረትከ አምላክነ፥ ወአኮ በከመ አበሳነ (፫ተ ጊዜ)[137] -ወእምዝ በተባርዮ ኵሎሙ ይብሉ፡- "ሥራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ዬ ዬ ዬ ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም . . ."[138] -ይበል ንፍቅ ዲያቆን፡- አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት።[139] |
| ጸሎት እምድኅረ "እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ" | -ዲያቆን ይብል፡- እንዘ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ።[140] "[141]እግዚአብሔር ዘለዓለም ማእምር ዘኅቡእ[142] ለከ አትሐቱ ርእሶሙ ሕዝብከ ወለከ አግረሩ ቀፈተ ልብ ወሥጋ፥ ርኢ እምድልው ማኅደርከ፥ | -ይበል ዲያቆን፡- እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ። "እግዚአብሔር ዘለዓለም ማእምር ዘኅቡእ ወዘገሃድ፥ ቅድሜከ አትሐቱ ርእሶሙ ሕዝብከ ወለከ አግረሩ ቀፈተ ልብ ዘሥጋ፥ ርኢ ዘእምድልው ማኅደርከ፥ ባርክ ኪያሆሙ ወኪያሆን፥ አጽምዕ ሎሙ እዝነከ፤ ወስምዖሙ ጸሎቶሙ፥ ወአጽንዕ በኃይለ |

[134] "ይእዜኒ ወዘልፈኒ" - ዝኒ ከማሁ።
[135] Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 26።
[136] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 61፣ ገጽ 112-113።
[137] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 62፣ ገጽ 113።
[138] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 63፣ ገጽ 113።
[139] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 66፣ ገጽ 113።
[140] Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 26።
[141] የHorner ትርጉም ከጸሎቱ በፊት "ይበል ኤጲስ፡ቆጶስ" የሚል ትእዛዝ (rubric) ይጨምራል - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 13።
[142] "ዘኅቡእ ወዘገሃድ" - ዝኒ ከማሁ::

| | | |
|---|---|---|
| | ወባርክ ኪያሆሙ ወኪያሆን፥ አጽምእ ሎሙ እዝነከ። ወስምዖሙ ጸሎቶሙ፥ አጽንዕ[143] በኃይለ የማንከ ወክድን እምሕማም[144] እኩይ፥ ዐቃቤ[145] ሎሙ ኩን ለሥጋ ወለነፍስ[146]፤ ወስከ ሎሙሂ ወለነሂ[147] ሃይማኖተ ወፈሪሆተ[148] በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ለዝሉፉ[149] ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[150] | የማንከ፥ ክድን ወርዳእ እምሕመሜ እኩይ፥ ዐቃቤ ሎሙ ኩን ለሥጋነሂ ወለነፍስነሂ፤ ወስከ ሎሙሂ ወሎንሂ ሃይማኖተከ ወፈሪሆተ ስምከ በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[151] |
| ጸሎተ ንስሐ | - | -ይበል ካህን፡- "እግዚእ እግዚኦ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም፥ አንተ ውእቱ ዘትፌውስ ቍስለ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ . . ."[152] |
| | -ዲያቆን ይበል፡- ንነጽር<br>-ኤጲስቆጶስ፡- ቅድሳት | - ይበል ዲያቆን፡- ነጽር<br>-ይበል ካህን፡- ቅድሳት ለቅዱሳን |

[143] "ወአጽንዕ"- ዝኒ ከማሁ::
[144] "እምሕመሜ" - ዝኒ ከማሁ::
[145] "ዓቃቤ" - ዝኒ ከማሁ::
[146] "ወለነፍስነ" - ዝኒ ከማሁ።
[147] "ሎሙ ወለነኒ" - ዝኒ ከማሁ።
[148] "ሃይማኖተከ ወፈሪሆተከ" - ዝኒ ከማሁ።
[149] "ይእዜኒ ወዘልፈኒ" - ዝኒ ከማሁ።
[150] Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 26።
[151] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 68፣ ገጽ 114።
[152] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 72-88፣ ገጽ 114-118።

| | | |
|---|---|---|
| ቅድሳት ለቅዱሳን | ለቅዱሳን<br>-ሕዝብ፡- አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።[153] | -ይበሉ ሕዝብ፡- አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ። |
| እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ +<br>ካህኑ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ የሚጸልየው ጸሎት | - | -እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ (ካህን ምስለ ሕዝብ በተባርዮ ፵፩ ጊዜያተ)<br>-ይበል ካህን፡- "እግዚአብሔር አምላክነ ነጽር ዲበ ሕዝብከ እለ ውስተ ንስሓ ሀለዉ፥ ወተሣሃሎሙ . . ."[154] |
| የእምነት መግለጫ (በቅዱስ ቍርባን ላይ) | - | -ይበል ካህን፡- "ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን . . ."<br>- "ደም ክቡር ዘበዘማን . . ."<br>- "አአምን አአምን አአምን ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ . . ."<br>-"አአምን አአምን አአምን ወእትአመን ከመ ኢተፈልጠ መለኮቱ እምትስብእቱ . . ."<br>-"አአምን አአምን አአምን ወእትአመን ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ . . ." |
| ጸሎተ እምቅድመ | | -ይበል ካህን፡- "እግዚአብሔር አምላኪየ ናሁ ሥጋ ወልድከ |

[153] Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 26።

[154] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 93-96፣ ገጽ 118-120።

| | | |
|---|---|---|
| ተመጥዎ ቍርባን (ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በፊት የሚጸለይ ጸሎት) | - | መሥዋዕት ዘያሠምረከ . . ." -እምቅድመ ተመጥዎ ቍርባን ይበሉ ኵሎሙ፡- "ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አኮ ዘይደልወኒ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ ርኵስት . . . " |
| ትእዛዛት በእንተ መጥዎ ወተመጥዎ ቍርባን (ቅዱስ ቍርባንን ስለማቀበል እና መቀበል የሚመለከቱ ትእዛዞች)[155] | -ኤጲስቆጶስ፡- "ዝንቱ ኅብስት ሰማያዊ ሥጋሁ ለክርስቶስ"[156] -ትእዛዝ፡- "ዘይትሜጦ ይብል አሜን" - ትእዛዝ፡- "ወለእመ ኢሀለዉ ቀሳውስት ዘየአክሉ የአኀዙ ዲያቆናት ጽዋዓተ ወይቁሙ በሥርዓት"[157] -ትእዛዝ፡- "ወይበል ዘይሜጡ ጽዋዐ፡- ዝ ውእቱ ደሙ ለእግዚእነ | -ይበል ካህን፡- "ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ቅዱስ ሥጋሁ ለክርስቶስ -ትእዛዝ፡- "ዘይቀርብሂ ይበል አሜን"[158] -ትእዛዝ፡- ይበል ዲያቆን እንዘ ይትሜጦ ጽዋዐ፡- "ጽዋዐ ሕይወት እትሜጦ ወስመ እግዚአብሔር እጼውዕ።" - ወይበል ዘንተ፡- "ጸልዩ በእንቲአነ ወበእንተ ኵሎሙ ክርስቲያን እለ ይቤሉነ ግበሩ ተዝካሮሙ በሰላም ወበፍቅረ |

[155] Communion Formula and Administering the Holy Eucharist.

[156] "ዝንቱ ኅብስት ሰማያዊ ሥጋሁ ለእግዚእነ ለክርስቶስ" - Horner, ትእዛዝ ፴፩፣ ገጽ. 24።

[157] በቂ ቀሳውስት ከሌሉ ዲያቆናት ጽዋውን እንዲይዙ የሚያዝዘው ትእዛዝ "Baptismal Eucharistic Liturgy" ተብሎ በሚታወቀው የእንግሊዝኛው Apostolic Tradition ውስጥም ይገኛል፡- "And if there are not enough presbyters, the deacons also shall hold the cups, and stand by in good order and reverence." See Cuming, *Hippollytus,* Ch. 21, p. 21. ይህን ጥንታዊ ሥርዓት በመከተል፥ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ፥ ዲያቆናት ጽዋውን ይዘው ለምእመናን ደሙን ያቀብላሉ። የቅዳሴ ሐዋርያት ትእዛዝም እንዲህ ይላል፡- "ይመጡ ለሕዝብ [ሠራዒ] ካህን ሥጋ፥ ወዲያቆን ደመ - ካህኑ ለሕዝቡ ሥጋውን፥ ዲያቆኑም ደሙን ያቀብል"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 128፣ ገጽ 128።

[158] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 115፣ ገጽ 125።

| | | |
|---|---|---|
| | ኢየሱስ ክርስቶስ<br>-ትእዛዝ፡- ወዘይትሜጠው ይበል፡- አሜን፥ ወአሜን። | ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብሑ ወዘምሩ"[159]<br>-ትእዛዝ፡- ይበል ንፍቅ ቀሲስ እንዘ ይሜጡ ደመ፡- "ዝንቱ ጽዋዐ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ክቡር ደሙ ለክርስቶስ"<br>-ትእዛዝ፡- ወዘይትሜጦ ይበል አሜን ወአሜን።[160]<br>-ትእዛዝ፡- ወእምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን እንዘ ሀሎ በአፉሁ ይበል ኵሉ ለለ፩ዱ ፩ዱ፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር . . ."[161]<br>- ጸሎት ዘባስልዮስ [እምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን]፡- "አ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ ናሁ ተመጠውኩ ሥጋከ ንጹሐ ወደመከ ክቡረ፥ ይኩነኒ ለሥርየተ ኃጢአትየ ወለኀድገተ አበሳየ . . . ስብሐት ለከ አ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወሀብከኒ ዕሩየ በእደ ዚአሁ ለገብርከ ______ . . ."[162] |
| ጸሎት እንዘ ይወጽዕ እመቅደስ ለመጥዎ ቍርባን<br>(ካህኑ | - | - ትእዛዝ፡- እንዘ ይወጽእ [እም፡ መቅደስ ይበል ዘንተ]፡- "እለ ጸዋዕከ እግዚኦ ወእለ ቀደስከ፤ ክፍል በጽዋዔከ፥ ወአጽንዕ በኃይልከ፥ ወዕቀብ በፍቅርከ፥ ወደምር ውስተ ዘለዓለም |

159 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 125፣ ገጽ 128.

160 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 120፣ ገጽ 127።

161 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 117፣ ገጽ 126። ይህ ዝማሬ የተወሰደው ከመጽሐፈ ኪዳን ነው፤ "ጸሎት ዘይጼልዩ ምእመናን" (ምእመናን የሚጸልዩት ጸሎት) የተሰኘ ርእስ አለው - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 42 ይመልከቱ።

162 ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 121-124፣ ገጽ 127።

| | | |
|---|---|---|
| ለማቀበል ሲወጣ የሚጸልየው ጸሎት) | | መንግሥትከ በክርስቶስ፥ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[163]<br><br>- <u>ትእዛዝ፡-</u> ወይዕትብ እንዘ ይወጽእ ዲበ ፃሕል ፩ደ ጊዜ።[164] |
| ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በኋላ የሚጸለይ ጸሎት | -<u>"ጸሎት እምድኅረ ተመጠዉ"፡-</u><br>"እግዚአብሔር ዘኲሎ ትእኅዝ አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ናአኵተከ[165] እስመ ከፈልከነ ንንሣእ እምቅዱስ ምሥጢር[166]። ኢይኩን ለርስሐት ወኢለኵነኔ አላ ለሐድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ። በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ለዝሉፉ[167] ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[168] | -<u>ትእዛዝ</u>፡- <u>እምድኅረ ተመጠዉ ሕዝብ ይበል ካህን</u>፡-<br>"እግዚአብሔር ዘለዓለም ብርሃነ ሕይወት ዘወሀብከነ እግዚኦ ለአግብርቲከ ጽንዐተ ወዕቅበተ . . ."[169]<br><br>- <u>ይበል ዲያቆን</u>፡- "ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ . . ."<br><br>- "ተመጦነ እም ሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ"<br><br>- "ወናእኵቶ ይደልወነ ከመ ንሳተፍ ምሥጢረ ክብርተ ወቅድስተ"[170]<br><br>- <u>ይበል ካህን</u>፡- "ኀዳፌ ነፍስ፤ |

[163] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 127፣ ገጽ 128።
[164] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 128፣ ገጽ 128።
[165] "ነአኵተከ"- Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 13::
[166] "ምሥጢር" - ዝኒ ከማሁ።
[167] "ይእዜኒ ወዘልፈኒ" - ዝኒ ከማሁ።
[168] Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 28።
[169] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 129፣ ገጽ 129።
[170] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 130፣ 132፣ 134፤ ገጽ129-130።

| | | |
|---|---|---|
| | | ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኲሎ ይእኀዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ነአኵተከ እስመ ከፈልከነ ንንሣእ ዘእምቅዱስ ምሥጢርከ። ኢይኩን ለርስሐት ወኢለኲነኔ አላ ለሐድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ። በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።”[171] |
| ጸሎተ እምድኅረ ተፈጸመ አስተናጽሖ | - | - <u>ይበል ካህን</u>፡- “መልዐተ እግዚኦ ምሥጢርከ ቅድስት እንተ ኢትማስን ዘወሀብከነ ለነ ኃይለ [ወመድኃኒተ] ተዝካረ ሞትከ ዘሀልው ምስሌከ . . .”[172] |
| ጸሎተ እምድኅረ ማየ መቍረር | - | - <u>ትእዛዝ፡- ጸሎተ እምድኅረ ማየ መቍረር ኀቡረ ይበሉ፣ ዘኲሎሙ ውእቱ፡-</u> “ እጼሊ ኀቤከ ወእስእለከ እግዚእየ ወአምላኪየ፥ ኖላዊ ኄር ዘአፍቀርከ መርዔተከ . . .”[173] |
| በእንተ አኰቴትነ | - | - <u>ይበል ዲያቆን</u>፡- “በእንተ አኰቴትነ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር በመጽሐፈ ሕይወት ይጽሐፍ ስእለተነ . . .”[174] |

[171] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 139-140፣ ገጽ 131።
[172] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 143-144፣ ገጽ 132-133።
[173] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 145-147፣ ገጽ 133-134።
[174] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 148-149፣ ገጽ 134።

| | | |
|---|---|---|
| አንብሮ እድ | -ትእዛዝ[175]፡- ቀሲስ ይብል፡- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ<br><br>-አንብሮ እድ እምድኅረ ነሥኡ[176]፡-<br><br>"እግዚአብሔር ዘለዓለም ዘኵሎ ትእኅዝ አብ ለእግዚእ ወመድኅኒነ[177] ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ባርክ አግብርቲከ ወአእማቲከ፤ ክድን፥ ወርዳእ፥ ወሠርሖ በኀይለ መላእክቲከ[178]፤ ዕቀብ፥ ወአጽንዕ ላዕለ ፍርሀትከ[179] በዘዚአከ ዕበይ አሰርጕ፥ ዘዚአከ የኀልዩ[180] ወዘዚአከ ይእመኑ ጸጉ፤ ወዘዚአከ ይፍቅዱ[181] ሱላሜ ዘእንበለ አበሳ ወመዐት ጸጉ። በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[182] | - ይበል ካህን (አንብሮ እድ)፡- ፡- "እግዚአብሔር ዘለዓለም ብርሃነ ሕይወት ዘኢይጠፍዕ ነጽሮሙ ለአግብርቲከ ወለአእማቲከ ወዝራዕ ውስተ ልቦሙ ፈሪሆተ ስምከ ይፍረዩ በበረከት፥ ወኈልቆሙ ምስለ እለ ተውህቦሙ ሥጋከ ወደምከ ወይኩን እዴከ ዘየኀድር ላዕሌሆሙ ዲበ እለ አትሐቱ አርእስቲሆሙ ቅድሜከ እድ ወአንስት፥ አዕሩግ ወሕፃናት፥ ደናግል ወመነኮሳት-፤ ዕቤራት ወዕጓለ ማውታ፤ ወኪያነሂ ደምር ህየ ወክድን ወርዳእ ወአጽንዕ በኃይለ ሊቃነ መላእክቲከ፤ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አግኅሠነ ወውስተ ኵሉ ምግባረ ሠናይ ደምረነ፤ በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።"[183] |

175 "ወቀሲስ ይብል አንብሮ እድ እምድኅረ ነሥኡ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 13።

176 Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 28።

177 "ወመድኃኒነ" - Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 14።

178 "በኃይለ ሊቃነ መላእክቲከ" - ዝኒ ከማሁ።

179 "ላዕሌሆሙ ፍርሃተከ"- ዝኒ ከማሁ።

180 "ወዘዚአከ የሐልዩ" - ዝኒ ከማሁ።

181 "ወዘዚአከ ይዕመኑ፥ ወዘዚአከ ይፍቅዱ ጸጉ ሎሙ" - ዝኒ ከማሁ።

182 Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 28 እና 30።

183 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 150፣ ገጽ 134-135።

| | | |
|---|---|---|
| ወዕቀቦሙ | - | - ይበል ንፍቅ ካህን፡- "ወዕቀቦሙ በርትዕት ሃይማኖት በስብሐት ወክብር በኵሉ መዋዕለ ሕይወቶሙ፥ ወረስዮሙ ውስተ ፍቅር ወሰላም እንተ ትትሌዓል . . ."[184] |
| አ ንጉሠ ሰላም | - | -ይበሉ ሕዝብ፡- "አ ንጉሠ ሰላም ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመከ ሀበነ ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ፥ ወሥረይ ለነ ኃጣውኢነ ወረስየነ ድልዋነ ከመ ንሑር ወንእቱ ውስተ አብያቲነ በሰላም"[185] |
| ቡራኬ እና ሥርሖተ ሕዝብ | - ኤጲስቆጶስ፡- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ። <br> - ሕዝብ፡- ምስለ መንፈስከ። <br> - ዲያቆን፡- "እትዉ በሰላም።"[186] | - ይበል ዲያቆን፡- "አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርክሙ።"[187] <br> - ይበል ካህን፡- "አ እግዚአ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ . . ."[188] <br> - ይበል ካህን፡- እግዚአብሔር የሃሉ ምስለ ኵልክሙ።[189] <br> - ይበሉ ሕዝብ፡- "ምስለ መንፈስከ፤ አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ለአግብርቲሁ በሰላም፤ ሥርየተ ይኩነነ ዘተመጦነ ሥጋከ |

[184] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 154- 157፣ ገጽ 135-137።
[185] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 158፣ ገጽ 138።
[186] Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 30።
[187] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ "ቅዳሴ ሐዋርያት" ቍ. 159፣ ገጽ 138።
[188] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 160-161፣ ገጽ 138-139።
[189] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 163፣ ገጽ 140።

| | | |
|---|---|---|
| | | ወደመከ፥ አብሐነ በመንፈስ ንኪድ ኵሎ ኃይሎ ለጸላዒ . . .”[190] - <u>ዲያቆን</u>፡- “ዕትዉ [*sic*] በሰላም።”[191] |

ይህ ሰንጠረዥ በዝርዝር እንደሚያመለክተው፥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት ውስጥ የሚገኘው አኰቴተ ቍርባን፥ በኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ውስጥ ለአገልግሎት የዋለው ብዙ ጸሎቶችና ትእዛዞች ተጨምረውበት እንደሆነ ግልጽ ነው። ከላይ የኅዳግ ማስታወሻ ቍጥር 122፥ ገጽ 153 ላይ እንደተገለጸው፥ የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ትርጉም ከአኰቴተ ቍርባኑ ፍጻሜ በኋላ በሌሎች ቋንቋዎች ትርጉሞች የማይገኙ የተለያዩ ጸሎቶችን ይዟል። እነዚህ ጸሎቶች በቤተ ክርስቲያናችን በሐዋርያት ስም የተሰየመው ቅዳሴ ውስጥ ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በኋላ ላለው የምስጋና ጸሎት ማሟያ ሆነው እንደገቡ ተመልክተናል፤ ከሌሎች ምንጮች ተወስደው የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ “በእንተ ቍርባን”[192] በሚል ርእስ ተቀላቅለው እንደገቡም ግልጽ ነው። የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ሐዋርያት፥ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ በሚገኘው አኰቴተ ቍርባን ላይ ተመሥርቶና በተለያዩ ጸሎቶች ተስፋፍቶ የተዘጋጀ ቅዳሴ እንደሆነ ከላይ ያለው ሰንጠረዥ በግልጽ ያሳያል።

ከላይ የተጠቀሱት ጸሎታት ከመጨመራቸው በፊት በዘመነ አክሱም የነበረው ሥርዓተ ቅዳሴ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያለውን አኰቴተ ቍርባን (ከላይ ባለው ሰንጠረዥ በግራ በኩል የተዘረዘረውን) የአገልግሎቱ ማእከል ያደረገ ነበር ማለት ይቻላል። በዚያ ዘመን የነበረውን የቅዳሴ አገልግሎት ሙሉ ይዘት በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም፥ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያለውን አኰቴተ ቍርባንና የመግቢያ ጸሎቶቹን የያዘ፥ እንዲሁም ከሌሎች ቅዳሴያት ተጨማሪ ዝማሬያትን (ለምሳሌ ዝማሬ ሱራፌል) ያካተተ ሊሆን ይችላል። ይህን አሳብ ለማጠናከር የሚረዳን አንድ

[190] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 164-165፣ ገጽ 140።
[191] ዝኒ ከማሁ፡ ቍ. 165፣ ገጽ 140።
[192] Duensing, ገጽ 24።

ጥንታዊ ብራና ውስጥ የሚገኝ አጭር ትምህርተ ቍርባን አለ፡፡ [193] ትምህርቱ የተዘጋጀው በጥምቀት የቤተ ክርስቲያን አባላት ለሆኑ ሐዲሳን አማንያን ሲሆን፥ የአማንያን ቅዳሴ (ፍሬ ቅዳሴ) የሚባለውን ክፍል በሚሳተፉበት ጊዜ ሊያደርጉት የሚገባውን ነገር እየጠቆመ የቅዳሴውን ዝርዝር በመጠኑ ይነግረናል፡-[194]

> እያንዳንዱ መዝሙር ተፈጽሞ ካህኑ ‘ምስጋና ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን’ ሲል እናንተም እንደርሱ በሉ። [. . .] ከጳውሎስና ከሐዋርያት መልእክታት፥ ከግብረ ሐዋርያት (የሐዋርያት ሥራ) በሚያነቡበት ጊዜ፥ ስለበጎ ምግባር ያስተማሩትን ትጠብቁ ዘንድ በማስተዋል አዳምጡ። ከወንጌል በፊት[195] ሲነበብ፥ ያለመታከት መልስ ስጡ። ለመዝሙሩ በሚሰጠው መልስም፥ ሃሌ ሉያ ሲባልም እንዲሁ፤ በዚህ ጊዜ ታላቅ ምስጋና [ይደረጋልና]። ወንጌል ሲነበብም፥ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምስጋናውን ቅዱስ ወንጌል ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ትሰሙ ዘንድ በማስተዋል አዳምጡ። ንኡሰ ክርስቲያን ተሰናብተውና ሕዝበ ክርስቲያኑ (ምእመናን) ቀርተው የመላእክት ሠራዊት ከተነበበ በኋላ፥[196] ለእርሱም በደስታ መልስ ስጡ፤ ቆመው የክርስቶስን ምሥጢር ከሚያመሰግኑና ከሚያገለግሉ የመላእክት ሠራዊት ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ። ወደ እርሱ በበጎ ምግባርና በቀና ሃይማኖት የሚቀርቡ ሁሉ ኃጢአታቸው ይሠረይ ዘንድ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበውን የክርስቶስን ቅዱስ ቍርባን ካህናት በሚያቀርቡበት ጊዜና፥ ‘እርስ በእርሳችሁ በተቀደሰ ሰላምታ እጅ ተነሳሱ’ በሚሉበት ጊዜ በባልንጀራችሁ ላይ ተጣልታችሁ የያዛችሁትን በደል ሁሉ

193 “ትምህርተ ቍርባን” ያልኩት Robert Beylot የሰጠውን ስያሜ በመከተል ነው፡- “Sermon éthiopien anonyme sur l’Eucharistie,”*Abbay,* 12 (1983-1984) pp. 113-116. Emmanuel Fritsch ደግሞ፥ መግቢያው ላይ ያሉ ሁለት ቃላትን “ሥርዓተ ምሥጢር” ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ “Order of the Mystery” የሚል ርእስ ሰጥቶታል፤ በጥምቀት ክርስትናን ለተቀበሉ ሰዎች የተዘጋጀ ትምህርት መሆኑን ለማመልከትም “catechesis” ይለዋል - Emmanuel Fritsch, “The ‘Order of the Mystery’: An Ancient Catechesis Preserved in BnF Ethiopic ms. d’Abbadie 66-66bis (Fifteenth Century) with a Liturgical Commentary,” *Studies in Oriental Liturgy* (Leuven : Peeters, 2019) pp. 195 and 198.

194 Le synaxaire éthiopien, ed. Gérard Colin, PO*,* Tome 45 (1990) pp. 218, 220, 224, 226 (ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ)።

195 ግእዙ “ቅድመ ወንጌል” ነው የሚለው፤ ግብረ ሕማማት ውስጥ “ቅድመ ወንጌል” የሚለው ቃል አሁን በቤተ ክርስቲያናችን “ምስባክ” የምንለውን ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰዱ የሦስት መሥመር ዝማሬን ነው የሚያመለክተው። Fritsch, “The ‘Order of the Mystery’፥ ኅዳግ ቍጥር 30፣ ገጽ 13።

196 ግእዙ “ወተነበ ሠራዊተ መላእክት” ይላል - Colin, “Le synaxaire éthiopien”፥ ገጽ 220፤ “ሠራዊተ መላእክቲሁ” ብሎ የሚጀምረውን ዝማሬ ይሁን ወይም የመላእክትን አገልግሎት የሚያመለክት ንባብ ግልጽ አይደለም። አባ አማኑኤል በፍልስጥኤምና በኢየሩሳሌም፡- “መድኃኒታችን ሆይ የቅዱሳን መላእክት ሠራዊት በፊትህ ይቆማሉ፥ ያመሰግኑህማል” የሚል ዝማሬን ጠቅሶ “ሠራዊተ መላእክት” የተባለው ይህን ዝማሬ ሊያመለክት ይችላል ብለዋል። የዚህ ዝማሬ ስም ትምህርተ ቍርባኑ ውስጥ መጠቀሱ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ሠራዒው ካህን የጸሎተ ፈትቶን የመጨረሻ ክፍል እየደገመ እያለ ለሚዘመረው ዝማሬ፡- “ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም . . . ” መነሻ ሊሆን እንደሚችልም ጠቁመዋል - Fritsch, “Order of the Mystery”፣ ገጽ 20።

> ትታችሁ በንጹሕ ልብ እጅ ተነሳሱ። [. . .] ‘ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ’ በማለትም የዚህ ዓለም አሳብ ወስዷችሁ ከሆነ [እንድትነቁ] ያስታውሷችኋል። [. . .] ያን ጊዜ “ከቡራን እንስሶችህ፥ ክንፎቻቸው ስድስት የሚሆኑ ሱራፌልና ኪሩቤል ላንተ (በፊትህ) ይቆማሉ፤ በሁለት ክንፎቻቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፥ በሁለት ክንፎቻቸው እግሮቻቸውን ይሸፍናሉ፥ በሁለት ክንፎቻቸው ይበራሉ፤[197] አንተን ከሚያመሰግኑህ ጋር፦ ‘ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ሥሉስ እግዚአብሔር ጸባኦት (የሠራዊት ጌታ) ፍጹም፥ የጌትነትህ ምስጋና ሰማይንና ምድርን መላ’[198] የምንልህን የእኛንም ምስጋና [ተቀበል]” የሚለውን ትሰሙ ዘንድ [ያመለክቷችኋል]። ወዲያው ከፍ ባለ ጽምጽ፦ ‘ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ሥሉስ እግዚአብሔር ጸባኦት (የሠራዊት ጌታ) ፍጹም፥ የጌትነትህ ምስጋና ሰማይንና ምድርን መላ’ እያላችሁ መልስ ስጡ።

ይህ ትምህርተ ቍርባን የሚገኘው ፓሪስ፥ ፈረንሳይ ውስጥ BnF Ethiopic Ms. d’Abbadie 66-66bis (15th C.) የሚል መለያ ቍጥር የተሰጠው ብራና ውስጥ ነው። ብራናው የጥር 28 ስንክሳር ንባብ አድርጎ ያቀርበዋል፤ ነገር ግን በሌሎች መጻሕፍተ ስንክሳር ውስጥ እንደዚህ አይነት ትምህርተ ቍርባን አናገኝም። ብራናው የ15ኛው ምእት ዓመት እንደሆነ ቢገለጽም፥ በውስጡ የምናገኘው የሥርዓተ ቅዳሴ ይዘት ጸሎተ ሃይማኖትንና ጌታ ያስተማረውን ጸሎት (አቡነ ዘበሰማያት) ስለማያካትት በ5ኛው ምእት ዓመት ይካሄድ የነበረውን አገልግሎት እንደ ሚያመለክት ታምኖበታል።[199] ትምህርተ ቍርባኑ የሚያሳየው በ5ኛው ምእት ዓመት እስክንድርያ ውስጥ የነበረውን ሥርዓተ ቅዳሴ ቢሆንም፥ በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን ትከተል የነበረው ይህንኑ የእስክንድርያ ቅዳሴ ስለነበር[200] ተመሳሳይ የቅዳሴ አገልግሎት በኢትዮጵያ ይካሄድ ነበር ለማለት ያስችለናል።[201] ትምህርተ ቍርባኑ ውስጥ የምናገኘው አውሥኦ (ምልልስ) የሚባለው የአኰቴተ ቍርባን የመግቢያ ሰላምታ ልውውጥም፥ ከላይ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ የምናገኘውን የሐዋርያዊ ትውፊት አውሥኦ ቅደም ተከተልን ይጠብቃል፦

---

197 “ራ” ይጠብቃል።

198 ግእዙ በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ካለው ዝማሬ ሱራፌል መጠነኛ ለውጥ አለው።

199 Heinzgerd Brakmann, “Le déroulement de la Messe copte: Structure et histoire,” *LeEucharistie: Célébrations, rites, piétés* (BEL.S 79), eds. Achille M. Triacca and Alessandro Pistoia, Rome 1995, p. 109.

200 Fritsch, “The ‘Order of the Mystery’,” p. 24.

201 Emmanuel Fritsch, “Qəddase,” *EA,* Vol. IV, p. 272.

- ኤጲስ፥ ቆጶስ ወይም ቀሲስ፦ እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ
- ሕዝብ፦ ምስለ መንፈስከ
- ኤጲስ፥ ቆጶስ ወይም ቀሲስ፦አልዕሉ አልባቢክሙ
- ሕዝብ፦ ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ
- ኤጲስ፥ ቆጶስ ወይም ቀሲስ፦ናአኵቶ ለእግዚአብሔር
- ሕዝብ፦ርቱዕ ውእቱ፥ ወጽድቅ ይደሉ።[202]

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰውን የትምህርተ ቍርባኑን ገለጻና ቀሪ ክፍሎቹን መሠረት በማድረግ፥ በዘመነ አክሱም (በ5ኛው ምእት ዓመት) የነበረው ሥርዓተ ቅዳሴ ይዘት ይህን ይመስል ነበር ማለት እንችላለን፦

- መዝሙረ ዳዊት (የተወሰኑ መዝሙራት)
- ንባባት ከመጽሐፍ ቅዱስ (ከጳውሎስ እና ከሌሎች ሐዋርያት መልእክታት፥ ግብረ ሐዋርያት)
- ቅድመ ወንጌል (ምስባክ)
- ሃሌ ሉያ
- ወንጌል
- ንኡሰ ክርስቲያንን ማሰናበት
- አግብኦተ ግብር
- አምኃ ቅድሳት
- አኰቴተ ቍርባን (ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያለውና ይዘቱ ከላይ የተዘረዘረው)፦
- አውሥኦ (ምልልስ )[203]
- ቅድመ-ዝማሬ ሱራፌል እና ዝማሬ ሱራፌል[204]

[202] Colin, *Le synaxaire éthiopien*, ቍ. 15፣ ገጽ 222 እና ቍ. 5፣ ገጽ 224።
[203] ዝኒ ከማሁ።
[204] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 30፣ ገጽ 224 እና ቍ. 35፣ ገጽ 226። እነዚህ ክፍሎች በዘመነ አክሱም በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እውቅና ካገኙት ቅዳሴያት (ቅዳሴ ማርቆስ ወይም የጌታችን ወንድም የያዕቆብ ቅዳሴ) የተወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ከላይ እንደተመለከትነው የApostolic Tradition አኰቴተ ቍርባን ዝማሬ ሱራፌል (*Sanctus*) የለውም።

- ጸሎት በእንተ እለ ኖሙ (ያረፉ ሰዎች ስማቸው እየተጠራ የሚደረግ ጸሎት)[205]
- ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኅብስት ወወይን [206]
- የማጠቃለያ ምስጋና (*ዶክሶሎጂ*)፡፡[207]
- ቅድሳት ለቅዱሳን[208]
- ተመጥዎ ቍርባን (ቅዱስ ቍርባን መቀበል)[209]
- ቡራኬ[210]
- ሠርሖተ ሕዝብ (ሕዝቡን ማሰናበት)፡፡[211]

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ነጥብ አለ፤ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለመሥዋዕትነት የተዘጋጀው ኅብስትና ጽዋ የሚቀርበው የአማንያን ቅዳሴ የሚጀመርበት ቦታ ላይ (ንኡሰ ክርስቲያን ከተሰናበቱ በኋላ) ነበር። እስከዚያ ድረስ ካህናቱ የተለየ ክፍል ውስጥ ሆነው በኅብስቱና ጽዋው ላይ የዝግጅት ጸሎት[212] ያደርሳሉ። ከ10ኛው ምእት ዓመት በኋላ ግን ኅብስቱና ጽዋው የሚቀርቡበት (አግብኦተ ግብር) ወደ ቅዳሴው መጀመሪያ ክፍል ተዛውሮ በኢትዮጵያም ሆነ በግብፅ ካህናቱ የዝግጅቱን ጸሎት የሚጸልዩት መንበሩ ላይ ሆኗል።[213] ጀራርድ ኮሊን ከብራና አግኝቶ ያሳተመው፥ ከላይ የተጠቀሰው ትምህርተ ቍርባን ይህን

[205] Colin, *Le synaxaire éthiopien*, ፥ ቍ. 10፣ ገጽ 226።
[206] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 15፣ ገጽ 226። ትምህርተ ቍርባኑን የጻፈው ሰው፥ ጌታችን ሥርዓተ ቍርባንን የመሠረተባቸውን ቃላት (ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ - Instituion Narrative) እና የጌታችን ሕማም፥ መከራና ትንሣኤ የሚታሰብበትን (Anamnesis) ክፍሎች ያለፋቸው ይመስላል። ምክንያቱም፥ በላይኛው ሰንጠረዥ እንደተመለከትነው የApostolic Tradition አኰቴተ ቍርባን የግእዙ ትርጒም ውስጥም ሆነ የእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ ዋነኛ ቅዳሴ በነበረው ቅዳሴ ማርቆስ ውስጥ እነዚህ ሁለት ክፍሎች ይገኛሉና።
[207] Colin, *Le synaxaire éthiopien*፥ ቍ. 25፣ ገጽ 226።
[208] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 5፣ ገጽ 228።
[209] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 25፣ ገጽ 228።
[210] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 5፣ ገጽ 230።
[211] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 5፣ ገጽ 230።
[212] Preparation rites/ *prosthesis*.
[213] Fritsch, "Order of the Mystery, " p. 16።

የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ስለሚያንጸባርቅ ለጥንታዊነቱ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው።

በዚህ መልኩ ከዘመነ አክሱም ጀምሮ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው የሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቁርባን በተለያዩ ጸሎታትና ዝማሬያት ተስፋፍቶ "ቅዳሴ ሐዋርያት" የሚል ስያሜ እንዴት እንዳገኘ የሚያመለክቱ ጥናቶች አሉ።[214] ይህ ሥራ የተሠራበትን ዘመን በተሳሳተ መልኩ ያቀረቡም አልጠፉም። ለምሳሌ፥ ሬናርድ ሜሽነር እና ማርቲን ላንግ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ሐዋርያት በቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ስም ከተሰየመው ከቅብጥ (ኮፕቲክ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ እና የነጩ ገዳም መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ከሚገኘው የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ አኰቴተ ቍርባን በተወሰዱ የተለያዩ ጸሎታት ተስፋፍቶ የተዘጋጀ እንደሆነ ጠቁመዋል። የቅዳሴ ሐዋርያት ዝግጅትም የተጠናቀቀው በ14ኛው ምእት ዓመት እንደሆነ ገልጸዋል።[215] ይህን ለማለት የቻሉትም የቅዳሴ ሐዋርያት መነሻ ምንጭ የሆነው የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ትርጒም የሚገኘው መጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ ስለሆነና መጽሐፈ ሲኖዶስ ደግሞ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመው በ13ኛው ወይም 14ኛው ምእት ዓመት ነው ከሚለው አመለካከት ተነሥተው ነው። ኢሬኒ ዳልሜ ይህንን አመለካከት ይጋራል።[216]

ነገር ግን፥ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የተለያዩ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን አሰባስቦ "መጽሐፈ ሲኖዶስ" የሚል ስያሜ የመስጠቱ ሥራ በ14ኛው ምእት ዓመት ቢሠራም፥ እዚያው መጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ

---

[214] በቅዳሴ ሐዋርያት ላይ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል ይህን ይመልከቱ፡- José L. Bandrés, "The Ethiopian Anaphora of the Apostles: Historical Considerations," *Proche-Orient Chretien,* 34 (1986) pp. 3-13.

[215] Reinard Meßner and Martin Lang, "Ethiopian Anaphoras Status and Tasks in Current Research via an Edition of the Ethiopian Anaphora of the Apostles," *Jewish and Christian Liturgy and Worship: New Insights into Its History and Interaction,* eds, Albert Gerhards and Clemens Leonhard (Leiden: Brill, 2007) p. 194.

[216] Irénée-Henri Dalmais, "The Eastern Liturgical Families," *The Church at Prayer: Principles of the Liturgy*, I, eds. Irénée-Henri Dalmais, Pierre Marie Gy, Pierre Jounel, and Aimé Geoges Martimort, (Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1987) p. 43.

ጽሑፎች በአክሱም ዘመነ መንግሥት ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ ናቸው። ከእነዚህ ጥንታውያን የሥርዓት መጻሕፍት መካከል የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ይገኝበታል። በእነዚህ የግእዝ ጥንታውያን ጽሑፎች ላይ ጥናት በማድረግ የሚታወቀውና ዓለም አቀፋዊ እውቅናን ያገኘው አሌሳንድሮ ባውሲ፥ በ4ኛው እና 5ኛው ምእት ዓመታት ከግሪክ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጽሑፎችን አክሱማዊ መድበል[217] በሚል ርእስ ለማሳተም በዝግጅት ላይ እንደሆነ አሳውቋል።[218] በዝግጅት ላይ ያለውን መድበል በባውሲ ፈቃድ ለመመልከት እድል ያገኙት አባ አማኑኤል ደግሞ፥ የጥንቱን ቅዳሴ ሐዋርያት እና ቅዳሴ ማርቆስን የመሰለ ይዘት ያለውን ጽሑፍ ለይተው ለማወቅ መቻላቸውን ነግረውናል።[219]

ስለሆነም፥ እነዚህን መረጃዎች መሠረት አድርገን የሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቍርባን ከአክሱም ዘመነ መንግሥት (ከ4-5ኛው ምእት ዓመት) ጀምሮ በኢትዮጵያ ይታወቅ እንደነበርና በየዘመናቱ አዳዲስ ጸሎቶች እየተጨመሩበት "አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት" የሚል ስያሜን እንዳገኘ እንረዳለን። ሬናርድ ሜቨነር እና ማርቲን ላንግ እንዳሉት ግን ቅዳሴ ሐዋርያት የ14ኛው ምእት ዓመት ትርጉም ከሆነ፥ ይህ ቅዳሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረታዊ ቅዳሴ እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያናችን እስከ 14ኛው ምእት ዓመት ድረስ ቅዱስ ቍርባንን ለማክበር የምትጠቀምበት ጸሎት (አኰቴተ ቍርባን) አልነበራትም ማለት ነው። ይህ ግምታዊ አስተሳሰብ፥ በ4ኛው ምእት ዓመት የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ እንዲታወጅ ታላቅ አስተዋጽኦ ለነበራት ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የሚመጥን አይደለም። ስለዚህ ቅዳሴ ሐዋርያት ከ4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናችን እውቅና እንደነበረው መካድ አይቻልም።

---

217 Aksumite collection.

218 Alessandro Bausi, "The Aksumite Background of the Ethiopic "Corpus Canonum"," *Proceedings of the XVth International Conference of Ethiopian Studies,* ed. Siegbert Uhlig, 65 (2006) p. 533.

219 Emmanuel Fritsch, "The Anaphoras of the Ge'ez Churches: A Challenging Orthodoxy," *The Anaphoral Genesis of the Institution Narrative in Light of the Anaphora of Addai and Mari: Acts of the International Liturgy Congress,* OCA, 295 (2013) p. 275.

ከላይ እንደ ተመለከትነው ቅዳሴ ሐዋርያት ከተዘጋጀበት መጽሐፈ ሥርዓት (ትእዛዝ ሲኖዶስ) ጋር በ4ኛውና በ5ኛው ምእት ዓመታት ከግሪክ ወደ ግእዝ እንደተተረጐመ የሚነገርለት ቅዳሴ ማርቆስ ነው። እነዚህ ሁለት ቅዳሴያት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እውቅናን ካገኙ ጥንታውያን ጸሎታተ ቍርባን መካከል ዋነኞቹ ናቸው።[220] ስለዚህ እነዚህ ቅዳሴያት ተቀራራቢነት ባለው የአክሱም ዘመነ መንግሥት ወደ ግእዝ ቋንቋ ከተተረጐሙ፥ በቀጣይ ዘመናት ቅዳሴ ሐዋርያት ባሳየው እድገት ላይ የቅዳሴ ማርቆስ ተጽእኖ እንደነበር መገመት እንችላለን። በዚህ ምዕራፍ ከገጽ 143-164 ባለው ሰንጠረዥ የግእዙ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ በሚገኘው አኰቴተ ቍርባን እና ቤተ ክርስቲያናችን ባሳተመችው ቅዳሴ ሐዋርያት መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ለማሳየት ሞክሬአለሁ። በሰንጠረዡ ግራ ረድፍ በኩል የምንመለከተው አኰቴተ ቍርባን "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ . . ." የሚለው የመላእክት ዝማሬ እና የዝማሬው መግቢያ የለውም። በአንጻሩ ደግሞ በቀኝ ረድፍ የተዘረዘረው ቅዳሴ ሐዋርያት ሁለቱንም ይዟል። እነዚህ ክፍሎች ደግሞ ከዲያቆኑ ትእዛዛት [221] (የተቀመጣችሁ ተነሡ፥ ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ፥ እናስተውል፥ ተሰጥዎውን መልሱ) ጋር ቅዳሴ ማርቆስ ውስጥ ይገኛሉ።[222] ስለዚህ ከቅዳሴ ማርቆስ ተወስደው፥ ቅዳሴ ሐዋርያት ውስጥ ለማሟያነት የገቡ ይመስላል።

በተጨማሪ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘእስክንድርያ በሚለው ክፍል የሚካተቱ ቅዳሴያት፥ ከአኰቴተ ቍርባኑ መግቢያ በኋላ (ከዝማሬ ሱራፌል በፊት) የተዝካረ ቅዱሳን እና የልመና ጸሎትን በመያዝ ይታወቃሉ።[223] ቅዳሴ ማርቆስም ሆነ ቅዳሴ ሐዋርያት ይህንን የአኰቴተ ቍርባን ቅደም ተከተል ይጠብቃሉ። ይህ ማለት ግን የሐዋርያዊ ትውፊትን አኰቴተ ቍርባን መሠረት በማድረግና በእርሱ ላይ የተለያዩ ጸሎታትን በመጨመር በቤተ ክርስቲያናችን "አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት" የሚል ስያሜ የተሰጠውን ቅዳሴ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሲያዘጋጁ ለዚህ ሥራ የተጠቀሙት ቅዳሴ ማርቆስን ብቻ ነበር ማለት አይደለም። እንዲያውም በቅዳሴ

[220] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ*፡ ገጽ 89።

[221] ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን በየቦታው ለቅዳሴ የተገኙትን ምእመናን ለማንቃት በንባብና በዜማ የሚያስተላልፋቸው ትእዛዛት በእንግሊዝኛ "diaconal exclamations" ይባላሉ።

[222] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum,* ገጽ. 120።

[223] Mazza, *The Origins of the Eucharistic Prayer,* 177; Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* 159.

ሐዋርያት አንዳንድ ክፍሎች ላይ የተደረጉ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች፥ የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት መገለጫ ባሕርያት በቅዳሴ ሐዋርያት ላይ እንደሚንጸባረቅ አረጋግጠዋል።[224] ስለዚህ ቅዳሴ ሐዋርያት የመጨረሻው ይዘት ላይ እስኪደርስ ድረስ ትጉዎቹ አባቶቻችን በጥንታዊው መጽሐፈ ሥርዓት (ሐዋርያዊ ትውፊት) ላይ አዳዲስ ጸሎታትን በመጨመር፥ እንዲሁም የግብፅ እና ሶርያ ቅዳሴያትን አብነት በማድረግ ዘመን ተሻጋሪ ድንቅ ሥራ ሠርተዋል። ይህ የአባቶቻችን አኩሪ ተግባር ራሱን የቻለ ጥልቅ ጥናት ያስፈልገዋል ብዬ አምናለሁ።

## "ጻድቃን ዘመጥራ" እና ተስዐቱ ቅዱሳን

ከሶርያና ከአንዳንድ የሮም ግዛት ክፍሎች በ5ኛው ምእት ዓመት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ቅዱሳን በዚያ ዘመን ለነበረው የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ እድገት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ይታመናል። የመጀመሪያዎቹ በአገራችን ሰሜናዊ ክፍል መጥራ በሚባለው ቦታ ስብከተ ወንጌልንና ሥርዓተ ምንኵስናን በማስፋፋት የኖሩ ናቸው።[225] ጥቅምት 19 ቀን የሚነበበው ስንክሳር፥ "ጻድቃን ዘመጥራ" ብሎ ይዘክራቸውና በሰማዕትነት እንዳረፉ ይነግረናል።[226] የሰማዕትነታቸው ምክንያት ደግሞ፥ ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ እንደጠቆሙት፥ ጻድቃኑ ባረፉበት ቦታ ገና ክርስትናን ያልተቀበሉ አሕዛብ (አረማውያን) ይኖሩ ስለነበር ከእነርሱ በደረሰባቸው ተቃውሞ ነው።[227] እነዚህ ጻድቃን ለጸሎት የተሰጠ ሕይወት ያላቸው ገዳማውያን እንደመሆናቸው መጠን፥ የመጡበት የጥንቱ ሮም ግዛት (ከአውሮፓ እስከ መካከለኛው ምሥራቅ) ውስጥ ይካሄድ የነበረውን ሥርዓተ ጸሎት ኢትዮጵያ ውስጥ ያከናውኑ እንደነበር ለመገመት አያስቸግርም። ስማቸው ካልተጠቀሰው "ጻድቃን ዘመጥራ" ጋር ተመሳሳይ ሕይወት የነበራቸው አባ ሊባኖስ (አባ መጣዕ) የማኅበር የምንኵስና ሥርዓትን[228] ከመሠረቱት ከአባ ጳኵሚስ አስኬማ-ምንኩስናን የተቀበሉና

---

[224] የእነዚህ ጥናቶችን ምንጮች ለማግኘት Bradshaw and Johnson, *Eucharistic Liturgies,* p.159, footnote no. 49 ይመልከቱ።

[225] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ* ገጽ 92.

[226] *መጽሐፈ ስንክሳር፡ ከመስከረም እስከ የካቲት* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፥ 1994፤) ገጽ 218።

[227] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ* ገጽ 92.

[228] Cenobitic monasticism.

በግላቸው ገዳማዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ጥረት ያደረጉ ናቸው። የማቴዎስ ወንጌልን እንደተረጐሙ የሚነገር ትውፊት ስላለና በዕብራይስጥ ማቴዎስ የሚለው ስም አቻ “መጣዕ” ስለሆነ፥ “አባ ሊባኖስ” ከሚለው በተጨማሪ “አባ መጣዕ” በሚለውም ስም ይታወቃሉ።[229] ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ አባ መጣዕ እና አባ ሊባኖስ የአንድ ጻድቅ ስም መሆኑን የሚያስረዳውን ድርሳን፥ የአርትዖት ሥራ ሠርተው ከግእዝ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመውታል።[230] ለትርጉሙ ባዘጋጁት መቅድም አባ መጣዕ (ሊባኖስ) ከተስዐቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን አንዱ እንደሆኑ አድርገው የሚያቀርቡ ምንጮች እንዳሉ ጠቁመው፥ አባ መጣዕ (ሊባኖስ) ከዘጠኙ ቅዱሳን ቀድመው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ መነኮስ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስረድተዋል።[231]

በ5ኛው ምእት ዓመት መጨረሻ እና 6ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከጥንታዊቷ የሮም ምሥራቃዊ ግዛት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ተስዐቱ ቅዱሳን፥ ክርስትናን እና ሥርዓተ ምንኩስናን በማስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። አገልግሎታቸው ከአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (ብርሃን ገላጭ) ቀጥሎ የተካሄደ ሁለተኛው ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ ተደርጎ ተወስዷል። ተስዐቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን ተብለው የተጠሩ መነኮሳት ከተጻፉላቸው ገድላት አንጻር ስሞቻቸውና የዕረፍቶቻቸው ቀናት የሚከተሉት ናቸው፡-

- አባ አሌፍ (መጋቢት 11)
- አባ አፍጼ (ግንቦት 29)
- አባ አረጋዊ/ ዘሚካኤል (ጥቅምት 14)
- አባ ገሪማ/ ይስሐቅ (ሰኔ 17)
- አባ ጉባ (ግንቦት 29)
- አባ ሊቃኖስ (ኅዳር 28)
- አባ ጰንጠሌዎን (ጥቅምት 6)

[229] *ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ* ገጽ 93።
[230] Getatchew Haile, “The Homily of Abba Eləyas, Bishop of Aksum on Mäṭṭa,” *Analecta Bolladiana*, Vol. 108/1-2 (1990) pp. 29-47 - “ድርሳን ዘብፁዕ ኤጲስ ቆጶስ አባ ኤልያስ ዘደረሰ በእንተ ብፁዕ መነኮስ አባ መጣዕ ዘውእቱ ሊባኖስ ብእሴ እግዚአብሔር” - ድርሳኑ ለጥናት የተወሰደው ከሁለት የተለያዩ የብራና ቅጂዎች (EMML 1763 እና EMML 7602) ነው።
[231] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 33-34።

- አባ ጽሕማ (ጥር 16)
- አባ ይምአታ (ጥቅምት 18)።[232]

ስለ ተስዐቱ ቅዱሳን የሚነግሩን ገድላትና ድርሳናት የተጻፉት ከ14ኛው ምእት ዓመት በኋላ ስለሆነ ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ዋነኛ ምክንያትና በዘመናቸው የሠሯቸው *ሥራዎች* በዝርዝር አልተገለጹም። ሆኖም ግን በ451 ዓ.እ. የተካሄደውን የኬልቄዶን ጉባኤ ስላልተቀበሉ በእምነት ወደሚመስሏቸው ኢትዮጵያውያን እንደመጡ ይታመናል።[233] ከሮማ ግዛት እንደመጡ ለማሳየት ሲሉ እነዚህን ቅዱሳን "ቅዱሳነ ሮም" በማለት የሚጠሯቸው ጸሐፍያን አሉ።[234] ነገር ግን የሮም ግዛት በወቅቱ በጣም ሰፊ ስለነበር ከተለያዩ አገሮች እንደመጡ ይታመናል፡- አባ አረጋዊ፥ አባ ገሪማና አባ ጰንጠሌዎን ከሮም፤ አባ አፍጼ ከእስያ፤ አባ ሊቃኖስ ከቍስጥንጥንያ፤ አባ ጉባ ከኪልቅያ፤ አባ ጽሕማ ከአንጾኪያ፤ አባ ይምአታ ግብፅ ውስጥ ከሚገኝ ቆስያ ከተባለ ቦታ፤ አባ አሌፍ ከቂሣርያ።[235] ይህ የሚያመለክተው እነዚህ ቅዱሳን በም*ሥራ*ቃዊው የሮማ ግዛት ክፍል ይከናወኑ የነበሩ የተለያዩ የ*ሥ*ርዓተ ቅዳሴ ዓይነቶችን ወደ ኢትዮጵያ ይዘው እንደመጡ ነው።

ቅዱሳኑ የመጡበትና ከላይ የተዘረዘሩት የሮም ም*ሥራ*ቃዊ ክፍሎች የሶርያ *ሥ*ርዓተ ቅዳሴን የሚከተሉ ቦታዎች ስለሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ምንጫቸው ሶርያዊ የሆኑ የ*ሥ*ርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን አግኝታለች። ከእነዚህም መካከል በ3ኛውና 4ኛው ምእት ዓመታት ከነበሩ መጻሕፍተ *ሥ*ርዓት ጋር በይዘት የሚመሳሰለውና በ5ኛው ምእት ዓመት ፍጻሜ ያገኘው መጽሐፈ ኪዳን[236]፥ እንዲሁም ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም)[237] ዋነኞቹ ናቸው። መጽሐፈ ኪዳን

---

[232] Antonella Brita, "Nine Saints," *EA,* Vol. III, p. 1188.
[233] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 1189።
[234] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፡* ገጽ 94።
[235] Antonella Brita, "Nine Saints," *EA,* Vol. III, p. 1189.
[236] Miguel Arranz, "The Functions of the Christian Assembly in the Testament of the Lord," *Roles in the Liturgical Assembly: The Twenty-third Liturgical Conference, Saint Serge,* trans. Matthew J. O'Connell (New York: Pueblo Publishing Company, 1976) 31.
[237] Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras,* p. 44; Paulos Tzadua, *The Divine Liturgy According to the Rite of the Ethiopian Church,* pp 12 and 14.

በኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ትልቅ ቦታ እንደተሰጠው ለመረዳት ከመጽሐፉ ተወስደው የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የገቡ ጸሎታትን መመልከቱ ብቻ በቂ ነው። ከሥር የተዘረዘሩት "ሰባቱ ኪዳናት"[238] እና የቅዳሴ እግዚእ ጎዳፌ ነፍስ[239] የተወሰዱት ከመጽሐፈ ኪዳን ነው፡-

- በእንተ ቅድሳት[240]
- በሰማይ የሀሉ ልብክሙ[241]
- ቅዳሴ እግዚእ[242]
- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር[243]
- ኪዳን (የመንፈቀ ሌሊት ሦስት፥ የነግህ ሦስት፥ የሠርክ ሦስት)[244]
- ትምህርተ ኅቡኣት[245]

---

[238] "ቅዳሴ እግዚእ"፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 164.

[239] "ጸሎት እምድኅረ ተመጠዉ አኰቴተ" (ቍርባን ከተቀበሉ በኋላ የሚጸለይ ጸሎት) የሚል ርእስ ተሰጥቶታል - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 43። በተጨማሪ መጽሐፈ ቅዳሴ (2000፣) ቍ. 81-82፣ ገጽ 157-158 ይመልከቱ።

[240] በመጽሐፈ ኪዳን "በእንተ ሥርዓተ ቅኔ ቤተ ክርስቲያን" (ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሥርዓት) የሚል ርእስ ተሰጥቶታል - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 78። በተጨማሪ መጽሐፈ ቅዳሴ (2000፣) ቍ. 66-98፣ ገጽ 51-56 ይመልከቱ።

[241] "በእንተ ሥርዓተ ቍርባን" የሚለው ክፍል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፥ ንኡሰ ክርስቲያን ከተሰናበቱ በኋላ ዲያቆኑ የሚያነበው ትእዛዝ እንደሆነ ተመልክቷል - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 78። በተጨማሪ መጽሐፈ ቅዳሴ (2000፣) ቍ. 2-13፣ ገጽ 143-145 ይመልከቱ፡፡

[242] አኰቴተ ቍርባኑ "በእንተ ሥርዓተ ቍርባን" የሚለው ክፍል ውስጥ ይገኛል - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 35-40። በተጨማሪ መጽሐፈ ቅዳሴ (2000፣) ቍ. 17-60፣ ገጽ 145-154 ይመልከቱ።

[243] "ጸሎት ዘይጼልዩ ምእመናን" (ምእመናን የሚጸልዩት ጸሎት) የተሰኘ ርእስ ተሰጥቶታል - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 42። በተጨማሪ መጽሐፈ ቅዳሴ (2000፣) ቍ. 117-118፣ ገጽ 126 ይመልከቱ።

[244] በሌሊት የሚደርሱት ሦስቱ የኪዳን ጸሎታት (ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኵሉ፥ አምላከ ብርሃን፥ ንሤልስ ለከ ዘንተ ስብሐተ) "በእንተ ስብሐተ ማኅበር" የሚለው ርእስ ሥር ይገኛሉ፤ የነግህ ኪዳን (እግዚአብሔር አብ፥ እግዚኦ ኢየሱስ፥ ንሤልስ ለከ ዘንተ ቅዱሰ ስብሐተ) ደግሞ "ቅኔ ጽባሕ - የጠዋት አገልግሎት" የሚል ርእስ ተሰጥቶታል፤ መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ "ኪዳን ዘሠርክ" የተባሉት ጸሎታት (ለከ ለአብ፥ ንዌድሰከ፥ ለከ ዘእምልብነ)፥ "ስብሐት ዘወትር በቤተ ክርስቲያን" የቤተ ክርስቲያን የዘወትር ምስጋናዎች እንደሆኑ መጽሐፈ ኪዳን ያመለክታል። *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 45-48፤ 50-53፤ 70-74። በተጨማሪ መጽሐፈ ቅዳሴ (2000፣) ገጽ 447-459 ይመልከቱ።

- እግዚአብሔር ዘብርሃናት።[246]

የሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቍርባንን ከቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ሐዋርያት ጋር በዝርዝር እያነጻጸርን ባጠናንበት ክፍል፥ አኰቴተ ቍርባኑ ከተለያዩ ምንጮች በተወሰዱ ጸሎታትና ዝማሬያት ተስፋፍቶ ቅዳሴ ሐዋርያት እንደተባለ ተመልክተናል። በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ "ቅዳሴ እግዚእ" ተብሎ የተጠራው የመጽሐፈ ኪዳን አኰቴተ ቍርባን ሲሆን፥ እንደ ቅዳሴ ሐዋርያት ተመሳሳይ ማሻሻያና ጭማሬዎች ተደርገውበታል። ሐዋርያዊ ትውፊት እና መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ጸሎታተ ቍርባን ብናነጻጽር እንኳን የመጽሐፈ ኪዳኑ አኰቴተ ቍርባን የፊተኛውን መሠረት አድርጎና ተስፋፍቶ የተዘጋጀ መሆኑን በቀላሉ እንረዳለን።

ቅዳሴ ሐዋርያትና ቅዳሴ እግዚእ ከጥንታውያን የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት መካከል ዋነኞቹ እንደሆኑ በቅዳሴያቱ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይስማማሉ።[247] ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት እነዚህ ሁለት ቅዳሴያት በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት መስጠት በጀመሩባቸው ዘመናት (4ኛውና 5ኛው ምእት ዓመታት) ቅዳሴ ማርቆስና ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም) ኢትዮጵያ ውስጥ እውቅና አግኝተው ነበር። አባ ተክለማርያም ሰመሃራይ ሰሊም (+1942 እ.አ.አ.) ባደረጉት ጥናት፥ ቅዳሴ ማርቆስን አባ ዜና ማርቆስ ገዳም ውስጥ በሚገኝ ጥንታዊ ብራና ላይ ማየታቸውንና ይህ ቅዳሴ በዚሁ ገዳም ይቀደስ እንደነበር ዘግበውልናል።[248] ነገር ግን በዘመነ አክሱም ወደ ግእዝ የተተረጐሙት ጥንታውያኑ

---

245 ለጥምቀት የተዘጋጁ ሰዎች በጥምቀት ስለሚያገኙት ሰማያዊ ጸጋ እና በቅዱስ ቍርባን አማካኝነት ስለሚያደርጉት ሱታፌ የሚማሩት ትምህርት - *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 53-61፤ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 1-23።

246 "ርቅየተ ንኡሰ ክርስቲያን ከመ ይትዓወቁ እለ ቦሙ መንፈሰ ነኪረ" በሚለው ርእስ ውስጥ ይገኛል። ርእሱ ባዕድ ወይም ክፉ መንፈስ ያለባቸውና ያልተጠመቁ ሰዎች ክፉው መንፈስ እንዲለቃቸው የሚጸለይ መሆኑን ስለሚገልጽ አጋንንትን ለማስወጣት (exorcism) የሚደረግ ጸሎት ነው። *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, ገጽ 117-121፤ መዝሙር ዘዳዊት (አዲስ አበባ፡ አክሱም ማተሚያ ቤት፡ 2000 ዓ.ም.) 6ኛ እትም፣ ገጽ 535-537።

247 ለምሳሌ Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras,* ገጽ 42 ይመልከቱ።

248 A. T. M. Semharay Selim, *Ephemerides Liturgicae* 42 (1928) pp. 440-441, የሃመርሽሚት መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰ፡- Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras,* ገጽ 43 ይመልከቱ።

ቅዳሴያት (አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ማርቆስና ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ) ለምን ከአገልግሎት ውጪ እንደሆኑና ቤተ ክርስቲያናችን ካሳተመቻቸው ቅዳሴያት ጋር እንዳልተካተቱ በግልጽ አይታወቅም። የእነዚህ ቅዳያሴት ለኅትመት መብቃት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴን ጥንታዊነት ከሚያሳዩ ነጥቦች መካከል አንዱ ስለሆነ፥ በብራና ብቻ ተወስነው ከቀሩት ሌሎች ቅዳሴያት ጋር ቤተ ክርስቲያናችን በሊቃውንቷ አስጠንታ ልታሳትማቸው ይገባል።[249]

## የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት

ከላይ እንደተመለከትነው የትርጒም ሥራዎች በዋነኝነት ከግሪክ ወደ ግእዝ ይካሄዱበት በነበረው በአክሱም ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅና ከሶርያ የተቀበለቻቸው የተለያዩ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ቢኖሩም፥ ለግእዝ ሥነ ጽሑፍ ፈር ቀዳጅ የሆነ ታላቅ ሥራ በ6ኛው ምእት ዓመት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ብቅ አለ። ታላቁ የቅኔ እና የነገረ መለኮት ሊቅ ቅዱስ ያሬድ፥ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጠው ጸጋ የደረሳቸው የዜማ መጻሕፍት ፍጹም ኢትዮጵያዊ ድርሰቶች ከመሆናቸው በተጨማሪ የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ በቅዱስ ያሬድ ሥራዎች ውስጥ ልዑል እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለው መግቦት፥ ክብረ ቅዱሳን እና የቤተ ክርስቲያን (ማኅበረ ምእመናን) ውበት ጣዕም ባለው አገላለጽ በተደጋጋሚ ተገልጸው እናገኛለን።

“ድግዱገ ጽሕፈት” ወይም ቀጥኖና ተጠቅጥቆ የተጻፈ የሚል ትርጒም የሚሰጠን “ድጓ” የተባለው የቅዱስ ያሬድ መጽሐፍ ከቅዱሳት መጻሕፍት፥ ከታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ድርሳናትና ከገድለ ቅዱሳን የተለያዩ አሳቦችን በመውሰድ የተጻፈ ምዕላድ (መድበል) ነው።[250] የድጓ አራት ክፍሎች፡- ዮሐንስ፥ አስተምሕሮ፥ ጾመ ድጓ እና ፋሲካ የቤተ ክርስቲያናችን ዓመታዊ የሥርዓተ አምልኮ ቀመር፡- ዘመነ ዮሐንስ፥ ዘመነ አስተምሕሮ፥ ዘመነ ጾም እና ዘመነ ፋሲካ ተብሎ እንዲከፈል

---

[249] ቅዳሴ ማርቆስና ቅዳሴ ያዕቆብ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ካሳተመቻቸው 14 ቅዳሴያት እና የአባ ጊዮርጊስ መዓዛ ቅዳሴ ጋር (ባጠቃላይ 17 ቅዳሴያት) ሮም ውስጥ በ1945 ዓ.እ. ታትመዋል። “አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ” እና “አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ” *Missale Ethiopicum,* ገጽ 107-117፤ 118-126 ይመልከቱ።

[250] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ*፡ ገጽ 338።

መሠረት (ምክንያት) ሆኗል።[251] እንዲሁም በውስጡ ያሉት ዝማሬያት የተዘጋጁት “እም ዮሐንስ እስከ ዮሐንስ” (ከዓመት እስከ ዓመት) አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ስለሆነ፡- መጸው፥ በጋ፥ ጸደይና ክረምት በተባሉት አራቱ የአገራችን ወቅቶች ለሚከበሩት የጌታና ቅዱሳን በዓላት በሙሉ የሚሆኑ መዝሙራትን ይዟል። መጽሐፈ ድጓ ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሡ ቅዱሳንን ስም ስለሚጠቅስ ያሬዳውያን ደቀ መዛሙርት የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ የጨመሯቸው የተወሰኑ ክፍሎች እንዳሉ እንረዳለን።[252] በተጨማሪ በሦስት የዜማ ስልት (ግእዝ፥ ዕዝል፥ አራራይ) ለሚዜመው ዜማ ምልክት ያዘጋጁ የቅዱስ ያሬድ የመንፈስ ልጆች እንዳሉ ሁሉ፥[253] ከድጓ ውስጥ ለጾም የተዘጋጀውን ለይቶ በማውጣትና “ጾመ ድጓ” ብሎ በመሰየም ደግሞ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (+1417 ዓ.ም.) ይጠቀሳሉ።[254]

ሁለተኛው የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጽሐፍ ምዕራፍ ሲሆን፥ ከዳዊት መዝሙራትና ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ዝማሬያት ተውጣጥቶ የተዘጋጀ ነው።[255] በየመዝሙራቱ መሐል ሃሌታና ድጓ እያስገባ ለመዝሙራቱ ማረፊያ ስለሚሰጥ “ምዕራፍ” ተብሏል። መጽሐፉ የዘወትርና የጾም ምዕራፍ ተብሎ ይከፈላል፤ የመጀመሪያው በዓመቱ ውስጥ ባሉት ቀናትና በዓላት፥ ሁለተኛው ደግሞ በዐቢይ ጾም አገልግሎት ላይ

[251] Habtemichael Kidane, “Ethiopian (or Gəʿəz) Worship,” *The New Westminster Dictionary of Liturgy and Worship,* ed. Paul Bradshaw (London: Westminster John Knox Press, 2002) p. 171. ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ፡ በተለምዶ ሁለተኛው ዘመን “ዘመነ አስተምህሮ = የትምህርት ዘመን” ቢባልም፡ ይህ ወቅት በዋነኝነት የእግዚአብሔር ምሕረት የሚለመንበት ወቅት ስለሆነ “ዘመነ አስተምሕሮ (ምህላ)- [Season of Supplication]” ተብሎ ሊጠራ እንደሚገባው ከላይ በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሑፋቸው ጠቁመዋል፡፡ በዚሁ ወቅት ከኅዳር 6-19 ባሉት ቀናት ውስጥ በሚውለው እሑድ የሚዘመረው መዝሙርም፡- “ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ኢኀደገነ ፍጹመ ንማስን ኄር እግዚአብሔር - ቸሩ እግዚአብሔር በደላችንን ሳያስብ ፈጽመን እንጠፋ ዘንድ አልተወነም” እያለ የአምላካችንን ምሕረት (መሐሪነት) ያደንቃል፡፡ “መዝሙር ዘአስተምህሮ” : *መጽሐፈ ዚቅ ወመዝሙር፡* 1987 ዓ.ም.፣ ገጽ 13፡፡

[252] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣* ገጽ 338፤ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት፣* ገጽ 74፤ ሀብተሚካኤል ኪዳነ፡ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፣* ገጽ 108።

[253] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣* ገጽ 339።

[254] ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት፣* ገጽ 85።

[255] Bernard Velat ወደ ፈረንሳይኛ በመተርጐም በጾመ ድጓ እና ምዕራፍ ላይ ያደረጋቸውን ጥናቶች ይመልከቱ፡- *Ṣoma Deggua*, PO, Vol. 32 (Paris: Firmin-Didot, 1966) and *Études sur le Me'erāf: commun de L'office Divin Éthiopien: Traduction et commentaire*, PO, Vol. 33 (Paris: Firmin-Didot, 1966).

ይውላል።[256] ሦስተኛውና "ዝማሬ" ተብሎ የሚጠራው የቅዱስ ያሬድ መጽሐፍ በቅዳሴ ሰዓት ምእመናን ቅዱስ ቍርባን በሚቀበሉበት ጊዜ የሚዘመርና በምሥጢረ ቍርባን ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ነው፤ በውስጡም፦ ኅብስት፥ ጽዋዕ፥ መንፈስ፥ አኰቴትና ምሥጢር የተባሉ ክፍሎችን ይዟል።[257] አራተኛውና የመጨረሻው መጽሐፍ (መዋሥዕት)፥ የመጽሐፉ ስያሜ እንደሚያመለክተው በግራና በቀኝ እየተመላለሰ የሚዜም መጽሐፍ ነው።[258] መዋሥዕት ዐረፍተ ዘመናቸው በሞት ተገትቶ ላረፉ ሰዎች በሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት አገልግሎት ላይ ይውላል።

ቅዱስ ያሬድ በነበረበት በ6ኛው ምእት ዓመት ስለ ክርስትና እምነት መስፋፋት ታሪካዊ መግለጫዎችን አናገኝም። ሆኖም በዚሁ ክፍለ ዘመን ኮስማስ ኢንዲኮፕሌዎስ[259] የተባለ ነጋዴ ወደ አዱሊስ መጥቶ የታዘበውን ከትቦልናል። ክርስቲያናዊ የቦታ ጥናት[260] የሚል ትርጕም ባለው መጽሐፉ፥ በ525 ዓ.እ. አካባቢ ወደ አዱሊስ እንደመጣ፥ በአንድ ሐውልት ላይና ስሙ ባልተጠቀሰ አክሱማዊ ንጉሥ ዙፋን ላይ የተቀረጹ ጽሑፎችን እንዳገኘ ዘግቦልናል። እነዚህ ድንጋይ ላይ የተቀረጹ ጽሑፎች በዘመኑ ኃያል የነበረው የአክሱም መንግሥት በቀይ ባሕር አካባቢ ከዐረቦች ጋር የነበረውን ጦርነት የሚያወሱ ናቸው።[261] በተጨማሪም እንደዚህ ጸሐፊ አገላለጽ፥ አክሱማዊው መንግሥት ክርስትና በስፋት ከተስፋፋባቸው፥ በየቦታው አብያተ ክርስቲያን ከታነጹባቸውና ጳጳሳትና መነኮሳት ካላቸው አገሮች ጋር የሚቈጠር ነበር።[262] ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ ይህ አገላለጽ ትንሽ የተጋነነ መስሎ

---

[256] ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ጸዋትወ ዜማ"፥ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም (2000)*፥ (አዲስ አበባ፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡ 2000) ገጽ 110።

[257] ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፡ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፣ ገጽ 103።

[258] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ*፣ ገጽ 339፤ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ጸዋትወ ዜማ"፣ ገጽ 111።

[259] "Indicopleustes" የሚለው የግሪክ ቃል "የሕንድ መንገደኛ" ማለት ነው፤ ነገር ግን ወደ ሕንድ መሄዱን የሚጠቁሙ መረጃዎች ስለሌሉ አንዳንድ ጸሐፍያን ይህን ስያሜ እውነተኛ አድርገው አይቀበሉትም። Alexander Sima, "Cosmas Indicopleustes," *EA,* Vol. I, p. 806.

[260] Christian Topography.

[261] Sima, "Cosmas Indicopleustes," *EA,* Vol. I, p. 806.

[262] Taddesse Tamirat, *Church and State in Ethiopia 1270-1527* (Oxford: Clarendon Press, 1972) p. 25.

ታይቷቸዋል። [263] ምናልባት ኮስማስ ኢንዲኮፕሌዎስ በአዱሊስ እና አክሱም አካባቢዎች ያየው የክርስትና እንቅስቃሴ በተመሳሳይ መልኩ በመላው ኢትዮጵያ የተስፋፋ መስሎት ሊሆን ይችላል።[264] ሆኖም የጸሐፊው አገላለጽ ቢያንስ ክርስትና በተመሠረተባት በታላቋ የአክሱም ከተማ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ እድገት ላይ እንደነበር መጠነኛ ፍንጭ ይሰጠናል።

## ከአክሱም መንግሥት ውድቀት በኋላ

በ619 ዓ.እ. የፋርስ መንግሥት በዐረቡ ዓለም ላይ ኃይልን መጎናጸፍ ሲጀምር ቀይ ባሕርን ተሻግሮ ይገዛ የነበረውን የአክሱምን መንግሥት አዳከመው።[265] በ7ኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ የእስልምናን መነሣት ተከትሎ የሙስሊም ኃይሎች ቀይ ባሕርን መቈጣጠር ሲጀምሩ፥ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ላይ ከነበረው መካከለኛ ምሥራቅ መገለል ደረሰባት። [266] ሆኖም የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያው ፓትርያርክ ተሹመው የሚላኩ ጳጳሳትን ወደ ኢትዮጵያ መላክዋን ስለቀጠለች በሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት አልተቋረጠም። ነገር ግን በዚሁ ምእት ዓመት ግብፅ በእስላማዊ ኃይሎች እጅ በመውደቋ፥ የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን በእድገት ላይ ከነበረችው ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላት ግንኙነት በመጠኑም ቢሆን ተዳክሞ ነበር።

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እናት የነበረችው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በእስላማዊ ኃይሎች በተወረረች ጊዜ፥ እስልምና የኢትዮጵያ ፈተና አልነበረም። እንዲያውም የአክሱም ነገሥታት በስደት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የነበሩትን የመጀመሪያዎቹን ሙስሊሞች (የመሐመድ ተከታዮች) ጥገኝነት ሰጥተው በመቀበላቸው አገሪቱ ለተወሰኑ ዓመታት ከእስላማዊ ወረራ ተርፋ ነበር። [267] የአክሱምን መንግሥት በእጅጉ የተፈታተኑትና ያጠቁት የኲሽ ነገዶች የሆኑ አገዎች

---

[263] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ*፡ ገጽ 85።
[264] Taddesse Tamirat, *Church and State in Ethiopia,* 1972, p. 25.
[265] Hien and Kleidt, *Ethiopia – Christian Africa,* p. 18.
[266] Robert Hess, *Ethiopia* (Illinois: Northwestern University, 1970) p. 32.
[267] J. S. Trimingham, *Islam in Ethiopia* (London: Oxford University Press, 1952) p. 44.

ነበሩ።[268] ቀይ ባሕር ላይ የነበረው የንግድ ሂደት መቋረጥና ከውስጥ ይደርሱ የነበሩ ጥቃቶች መጨመር የአክሱምን መንግሥት ለረጅም ዓመታት አዳከሙት፤ በዚህም ምክንያት ከሌላው ክፍለ ዓለም ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ። በ9ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ላይ ከፈላሻ (ቤተ እስራኤላውያን) ወገን የነበረችው ዮዲት ጉዲት (እሳቶ) በአክሱማዊው ንጉሥ ድግናዣን ምትክ የነገሠው ሕፃን ልጁን (አንበሳ ውድም) እና ወገኖቹን ለስደት ዳርጋ፥ ለ40 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ የጥፋት ዘመቻ አካሄደች።[269] በንግሥናዋ ዘመን ለቍጥር የሚያዳግቱ አብያተ ክርስቲያንን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የተለያዩ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን አቃጠለች።

ስለዚህ ከአክሱም መንግሥት መዳከምና ውድቀት በኋላ ያሉት ዘመናት (ከ7ኛው - 9ኛው ምእት ዓመታት) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ምን ይመስል እንደነበር ምንም ዓይነት ታሪካዊ መረጃዎች አይሰጡንም፡፡ ይህ ማለት ግን በእነዚህ የቃጠሎና የእልቂት ዘመናት ክርስትና ከምድረ ኢትዮጵያ ጠፍቶ ነበር ማለት አይደለም። ነገር ግን የክርስትናው እድገት ስለተገታ፥ እንዲሁም በየዘመናቱ እያደገ የነበረውን ሥርዓተ አምልኮ የሚያበለጽጉ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የሚሠሩበት አጋጣሚ ስላልነበር ዘመናቱ አሳዛኝና አስከፊ ሁነው አልፈዋል። በእነዚህ አሳዛኝ ዘመናት ስለተተረጐሙ ወይም ስለተጻፉ መጻሕፍት ምንም ዓይነት ፍንጭ አናገኝም። እጅግ ጥንታዊ ከሚባሉ የብራና ስብስቦች መካካል እንኳን ማግኘት የምንችለው ከ11ኛው ምእት ዓመት በኋላ የተጻፉትን ነው።[270]

ከጥፋቱ ዘመን በኋላ ለ330 ዓመታት ያህል (ከ933-1263) የነገሡት የዛግዌ ነገሥታት[271] በዋነኝነት ዝነኛ የሆኑትንና ከአንድ ዓለት የተወቀሩ አብያተ ክርስቲያንን

---

[268] Hien and Kleidt, *Ethiopia – Christian Africa,* p. 19.
[269] አባ ጎርጎርዮስ፡ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1991 ዓ.ም.) ገጽ 30።
[270] ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ እነዚህን የብራና መጻሕፍት ቅጂዎች በምሳሌነት ይጠቅሳሉ፡- EMML 6913 (11ኛ እና 12ኛው ምእት ዓመታት)፥ EMML 8509 (11ኛ እና 12ኛው ምእት ዓመታት)፥ EMML 6940 (12ኛው ምእት ዓመት)፥ EMML 2080 (12ኛው እና 13ኛው ምእት ዓመታት)፥ EMML 6919 (13ኛው ምእት ዓመት) - ሀብተሚካኤል ኪዳነ፡ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ*፡ ገጽ 113።
[271] ጌታቸው ኃይሌ፡ *ባሕረ ሐሳብ: የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር* (ኮሌጅቪል፡ ሚኒሶታ፡ 1993 ዓ.ም.) ገጽ 232።

በማሳነጽ ይታወቃሉ። ከነገሥታቱ መካከል ይምርሐነ ክርስቶስና ሐርቤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ አገዛዝ ነጻ እንድትወጣ ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ። የንጉሥ ላሊበላ (+1173 ዓ.ም.) ብርቅዬ የውቅር አብያተ ክርስቲያናት ከታነጹበት ሥነ-ሕንጻ አንጻር የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ ያሳየውን እድገት ለማጥናት ያገለግላሉ።[272] ይህ ጥናት ብዙ ጊዜ የሚካሄደው በመጥራ፥ አዱሊስና አክሱም የታነጹትን አብያተ ክርስቲያን ከላሊበላ አብያተ መቅደስ ጋር በማነጻጸርና በታየው የሥነ ሕንጻ ለውጥ አማካኝነት በሥርዓተ ቅዳሴው ላይ ያመጣውን ለውጥ በመመርመር ነው። ነገር ግን፥ በዮዲት ጉዲት ቃጠሎ የጠፉትን መጻሕፍት የመተካት ወይም ለሥርዓተ አምልኮው አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ አዳዲስ መጻሕፍትን የመተርጎም ሥራ በዛግዌ ነገሥታት የንግሥና ዘመናት አልተሠራም። በአንጻሩ በዛግዌ ነገሥታት ተወስዳ የነበረችውን ሰሎሞናዊ መንግሥት ያስመለሰው የአፄ ይኵኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት (1263 – 1277 ዓ.ም.) የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ከውድቀቱ እንዲያንሰራራ እድል ከፈተ።

## ፪. ሁለተኛው የትርጉም ሥራ፡- ከዐረብኛ ወደ ግእዝ

በዘመነ አክሱም (ከ4ኛው-7ኛው ምእት ዓመታት) የትርጉም ሥራዎች ይከናወኑ የነበሩት ከግሪክ ወደ ግእዝ እንደነበር ተመልክተናል። ግብፅ በእስላማዊ ኃይሎች ከተወረረች በኋላ ዐረብኛ የሕዝቡ መግባቢያ ቋንቋ ሆነ። ይህን ከግምት በማስገባት የመንበረ ማርቆስ 70ኛ ፓትርያርክ ገብርኤል ዳግማዊ ኢብን ቱርያቅ/የቱርያቅ ልጅ (1131-1145 እ.አ.አ.) ዐረብኛ የሥነ ጽሑፍና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መገልገያ ቋንቋ እንዲሆን አወጁ።[273] ስለዚህ ከ13ኛው ምእት ዓመት በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የገቡ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ ናቸው። ለዚህ ሥራ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት ከ1341-1381 ዓ.ም. ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አባ ሰላማ ካልእ

[272] Emmanuel Fritsch, “Ethiopian Liturgy and Church Architecture,” *Ethiopian Review of Cultures,* Vol. 14 (2011) pp. 90-91.
[273] *The Canons of Gabriel Ibn Turaik, LXX Patriarch of Alexandria,* trans. O. H. E. Burmester, OCP*,* Vol. 1 (1935) p. 19፤ ሀብተሚካኤል ኪዳነ፡ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፡* ገጽ 123።

(ሁለተኛ)[274] ናቸው። ብዙ መጻሕፍት ማስተርጐማቸውን ለመግለጽ "አባ ሰላማ መተርጉም" በሚል መጠሪያ ስም ይታወቃሉ።[275] ከትርጉም ሥራ ውጭ በአባ ሰላማ ካልእ ዘመነ ጵጵስና፥ በዘመነ አክሱም ከግሪክ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ከዐረብኛ ትርጉሞች ጋር በማነጻጸር ተጨማሪ ጥናት ተደርጓል።[276]

የትርጉም ሥራው በ12ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ እስከ 16ኛው ምእት ዓመት ድረስ ይካሄድ ነበር። በእነዚህ ረጅም ዘመናት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐሙትን መጻሕፍት በሙሉ መዘርዘር ባይቻልም ለቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ እድገት ታላቅ ሚና የተጫወቱትን መጻሕፍት እንመለከታለን። ከ12ኛው - 13ኛው ምእት ዓመት ባሉት ጊዜያት መጽሐፈ ሲኖዶስ ላይ ተጨማሪ ሥራ የተሠራ ሲሆን መጽሐፈ ዲድስቅልያ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሟል። እዚህ ላይ ስለ መጽሐፈ ሲኖዶስ ሥራ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ፤ የመጽሐፈ ሲኖዶስ ክፍል የሆነውና የግእዙን ሐዋርያዊ ትውፊት የያዘው "ትእዛዝ ሲኖዶስ" በዘመነ አክሱም (4ኛው-5ኛው ምእት ዓመት) ከግሪክ ወደ ግእዝ ከተተረጐሙ ጥንታውያን መጻሕፍት መካከል ነው።[277] የተቀሩት የመጽሐፈ ሲኖዶስ ክፍሎች (ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ፥ ግጽው ሲኖዶስ፥ አብጥሊስ ሲኖዶስ፥ ጦማረ ጴጥሮስ ኀበ ቀሌምንጦስ እና የተለያዩ ጉባኤያት ቀኖናዎች)[278] ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ (12ኛው - 13ኛው ምእት ዓመት)

[274] የመጀመሪያው አባ ሰላማ (ቅዱስ ፍሬምናጦስ) በቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ እጅ ተቀብቶ በ4ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ላይ ጵጵስና የተሾመው ነው።

[275] ጌታቸው ኃይሌ፡ *ባሕረ ሐሳብ፣* ገጽ 232።

[276] Edward Ullendorff, *Ethiopia and the Bible* (London: Oxford University Press, 1968) p. 35.

[277] Alessandro Bausi, "The Aksumite Background of the Ethiopic "Corpus Canonum"," p. 533፤ እንዲሁም በግእዙ Apostolic Tradition ትርጉም ላይ የአርትዖት ሥራ ሠርቶ ወደ ጣሊያንኛ የተረጎመውን ይመልከቱ፦ Alessandro Bausi, " LA NUOVA VERSIONE ETIOPICA DELLA *TRADITIO APOSTOLICA*: EDIZIONE E TRADUXIONE PRELIMINARE," *Studia Ephemeridis Augustinianum,* Vol. 125 (2011) pp. 19-69.

[278] *Il Senodos Etiopico Canoni pseudoapostolici: Canoni dopo l'Ascensione, Canoni di Simone Cananeo, Canoni Apostolici, Lettera di Pietro,* CSCO*,* Vol. 552, Tom. 101. Scriptores Aethiopici, ed. Alessandro Bausi. Louvain: Aedibus Peeters, 1995.

ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ሲተረጐሙ እነዚህን ሁሉ መጻሕፍተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የያዘው መድበል "መጽሐፈ ሲኖዶስ" የሚል ስያሜ አገኘ። ስለዚህ መጽሐፈ ሲኖዶስ ከ12ኛው ምእት ዓመት በኋላ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ከተተረጐሙ መጻሕፍት መካከል ቢቈጠርም፥ በውስጡ በዘመነ አክሱም የተተረጐመ መጽሐፈ ሥርዓት (ሐዋርያዊ ትውፊት) እንደያዘ ልንገነዘብ ይገባል።

በ14ኛው ምእት ዓመት ከተተረጐሙት መጻሕፍት መካከል የሚከተሉትን መጻሕፍት እናገኛለን፡- መጽሐፈ ግብረ ሕማማት፥[279] መጽሐፈ ሰዓታት ዘግብፅ፥[280] መጽሐፈ ግንዘት፥ ውዳሴ ማርያም፥ ላሐ ማርያም[281]፥ መጽሐፈ ስንክሳር እና መጽሐፈ ግጻዌ።[282] መጽሐፈ ግጻዌ ይህን ስያሜ ከማግኘቱ በፊት "ግብፃዌ" (ግብፃዊ) ተብሎ የተጠራበት አንድ ጥንታዊ ብራና እናገኛለን።[283] ይህ አጠራር የመጽሐፉ ምንጭ ግብፅ እንደሆነ፥ በቆይታ ግን "ገጸወ = ገለጸ፥ ለየ" ከሚለው የግእዝ ግስ ተወስዶ "ግጻዌ"፥ ማለትም በቅዳሴና በማኅሌት ከቅዱሳት መጻሕፍት የሚነበቡ ምንባባት ማውጫ (መግለጫ፥ መለያ) የሚል ትርጕም እንደተሰጠው ዶ\ር ሀብተሚካኤል ያስረዳሉ።[284] ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ

---

[279] ይህ መጽሐፍ በሰሙነ ሕማማት የሚነበቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባትንና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ድርሳናትን የያዘ ሲሆን ከተተረጐመ በኋላ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የተለያዩ ድርሳናተ አበውንና ኢትዮጵያዊ ዝማሬያትን በመጨመር በእጅጉ አበልጽገውታል። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሰሙነ ሕማማት አገልግሎት በምትጠቀምበት መጽሐፍ (በዐረብኛ፡ *al-Basha*) እና በእኛ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ግብረ ሕማማት መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። Ugo Zanetti, "Is the Ethiopian Holy Week Service Translated from Sahidic? Towards a Study of the Gebra Ḥemamat," *Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies,* Vol. I (1994) pp. 774-775.

[280] በሂደት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በደረሱት መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት ተተክቷል - Getatchew Haile, "Ethiopic Literature," ገጽ 49:: የሰዓታት ዘግብፅ የግእዙ ትርጕም በ1944 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 1952) ሮም ውስጥ ታትሟል፡፡

[281] እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ውድ ልጇ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ቤዛ ሆኖ መከራ መስቀልን በሚቀበልበት ሰዓት፥ በቅርበት ሕማሙን እና መንገላታቱን እያየች ስላለቀሰችው ለቅሶና ስለተሰማት ከባድ ኀዘን ልብን በሚማርክ መልኩ ገለጻ የሚያቀርብ መጽሐፍ ነው።

[282] Ricci, "Ethiopian Christian Literature," 976፤ ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዙ* ገጽ 127።

[283] "EMML 1832" ፤ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ*፥ ገጽ 124 ላይ የተጠቀሰ።

[284] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 125።

አገልግሎት እየሰጠ ያለው መጽሐፈ ግጻዌ EMML 1832 የሚል መለያ ቍጥር በተሰጠው የብራና ቅጂ ላይ የሚገኘው (መጽሐፈ ግብፃዌ) ትርጉም ነው ማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም መጽሐፈ ግጻዌ ውስጥ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱና በአገራችን ኢትዮጵያ ያሉትን አራቱን ወቅቶች (መጸው፥ በጋ፥ ጸደይ እና ክረምት) ተከትለው የልዑል እግዚአብሔርን መለኮታዊ መግቦት የሚያስረዱ የዕለተ እሑድ መዝሙራት ተጠቅሰው እናገኛለን። እነዚህ መዝሙራት በኋላ የተጨመሩ ናቸው ቢባል እንኳን፥ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለነግህ፥ ለሠርክ ጸሎትና ለቅዳሴ የምትጠቀምበትን የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ማውጫን ከእኛ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ግጻዌ ጋር ማመሳከር ያስፈልጋል። የጥንታውያን አባቶቻችን የትርጉም ሥራ ዓይነተኛ ባሕርይ ከኢትዮጵያዊ ትውፊት ጋር እንዲስማማ አድርጎ መተርጎምና የራስን አስተዋጽኦ መጨመር ስለሆነ፥ "ግብፃዌ" በሚል ስም የተጠራውን መሠረት አድርገው በዓመቱ ውስጥ ባሉት ቀናት በሙሉ የሚነበቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባትን (ከመልእክታተ ጳውሎስ፥ ከሌሎች ሐዋርያት መልእክታት [አልፎ አልፎ ከዮሐንስ ራእይ]፥ ከግብረ ሐዋርያት እና ከአራቱ ወንጌላት) በማዘጋጀት የራሳቸውን ድርሻ ተወጥተዋል ብዬ አምናለሁ። በተጨማሪም፥ በዓመቱ ውስጥ ላሉ ሰናብት (እሑዶች) በሙሉ መዝሙራትን በማዘጋጀት ብሔራዊ መጽሐፈ ግጻዌ አዘጋጅ ተውልናል።

ተአምረ ማርያም፥ መጽሐፈ ክርስትና፥ መጽሐፈ ጥምቀት[285] እና ፍትሐ ነገሥት በ14ኛው እና 15ኛው ምእት ዓመታት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ መጻሕፍት ናቸው።[286] ፍትሐ ነገሥት በ13ኛው ምእት ዓመት "የአል-አሳል ልጅ የአሳድ

[285] በበዓለ ጥምቀት (በዓለ ኤጲፋንያ/ አስተርእዮ (መገለጥ) ጥር 11 ቀን የሚነበብ መጽሐፍ።

[286] በእነዚህ ዘመናት ከሥርዓተ አምልኮ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖራቸውም፥ ለመንፈሳዊ ሕይወት በጣም ጠቃሚ የሆኑ "ዜና አበው ቅዱሳን" እና "ፊልክስዩስ" ተተርጉመዋል - Ricci, "Ethiopian Christian Literature," 977፤ ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፥* ገጽ 128። ከሦስቱ መጻሕፍተ መነኮሳት አንዱ የሆነውንና "ፊልክስዩስ" የተሰኘውን መጽሐፍ፥ "መንበግ" ተብላ በምትታወቀው ቦታ ጳጳስና ተሹሞ የነበረው ፊልክስዩስ ሶርያዊ እንደጻፈው የመጽሐፉ መቅድም ይናገራል። መቅድሙ ወደ ግሪኩ ትርጉም ቀረብ ባለ መልኩ "ፊልክስዩስ" ማለት "መፍቀሬ አጋው (የወንድሞች ወዳጅ)" ማለትም እንደሆነ ይነግረናል - "ፊልክስዩስ፡ መቅድም" *መጻሕፍተ መነኮሳት፡ ማር ይስሐቅ፤ ፊልክስዩስ (ገብረ ክርስቶስ)፤ አረጋዊ መንፈሳዊ* (አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1988 ዓ.ም.) ገጽ 9 ይመልከቱ። በመቅድሙ የተጠቀሰው የምዕራብ ሶርያ አባት Philoxenus of Mabbug

ቀኖናዎች"[287] በሚል ርእስ በዐረብኛ ለግብፅ ክርስቲያኖች የተዘጋጀው የሕገ-ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ትርጉም ነው።[288] በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ ከጉባኤ ኬልቄዶን (451 ዓ.እ.) በፊት የነበሩ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፏቸውን ጽሑፎች ሰብስቦ የያዘው "ሃይማኖተ አበው"፥ በዐረብኛ *ኢቲራፍ አል-አባ* የተሰኘው መጽሐፍ ትርጉም ነው። የትርጉም *ሥራው* በ16ኛው ምእት ዓመት እንደተከናወነ ይታመናል።[289]

በርካታ የትርጉም *ሥራዎች* ከዐረብኛ ወደ ግእዝ መከናወናቸው አገር በቀል ለሆኑ *ሥራዎች* በር ከፍቷል። በ13ኛውና 14ኛው ምእት ዓመታት የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን መንፈሳዊ ሕይወትና ተጋድሎን የሚዘክሩ ገድላት በግእዝ ቋንቋ መጻፍ ጀመሩ።[290] ከገድላቱ ጋር "መልክዕ" የሚል ርእስ የተሰጠውና መልክዑ የተደረሰለት ቅዱስ (የተደረሰላት ቅድስት) የሰውነት ክፍሎችን እየዘረዘረ የቅዱሳኑን ውብ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያወድስ *ሥራ* የግእዝ *ሥነ-ጽሑፍ* አካል ሆነ። "መልክዐ

---

(A.D. 450 – 523) ሲሆን፥ የኬልቄዶንን ጉባኤ የተቀበሉ ወገኖችን በመቃወምና የቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያን ነገረ ክርስቶስ አብራርቶ በመጻፍ የታወቀ አባት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በመንፈሳዊ ሕይወት ዙሪያ የጻፋቸው ድርሳናት ሲኖሩት እነዚህ ድርሳናት እስካሁን ድረስ ወደ ግእዝ አልተተረጎሙም - *The Discourses of Philoxenus of Mabbug,* trans. Robert A. Kitchen (Collegeville, MN: Cistercian Publications, 2013)። የተለያዩ ሊቃውንት በጥናቶቻቸው እንዳረጋገጡት፥ በእኛ ቤተ ክርስቲያን "ፊልክስዩስ" በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ፥ ዳዲሾ ዘኳታር (Dadisho Qataray) የተባለና በ7ኛው ምእት ዓመት የነበረ የምሥራቅ ሶርያ (East Syrian/ Assyrian) መነኮስ፥ "ኢናንሾ" ወደ ሶርያ ቋንቋ በተረጐመው "ገነተ መነኮሳት" ላይ ያዘጋጀው አንድምታ ነው - *Dadisho Qaṭraya's Compendious Commentary on the Paradise of the Egyptian Fathers in Garshuni,* eds. and trans. Mario Kozah, Abdulrahim Abu-Husayn and Suleiman Mourad (New Jersey: Gorgias Press, 2016) ይመልከቱ። ነገር ግን በምሥራቅና በምዕራብ ሶርያ አብያተ ክርስቲያን መካከል በአንዳንድ አስተምህሮዎች ላይ አለመግባባት ስላለ፥ የምዕራብ ሶርያ ወገኖች የምሥራቅ ሶርያ አባት የሆነውን የዳዲሾን ስም ከመጽሐፉ ርእስ በማስወገድ በራሳቸው አባት (በፊልክስዩስ ዘመንበግ - Philoxenus of Mabbug) ተክተውታል። ለዚህ ነው በእኛም ቤተ ክርስቲያን የዳዲሾ ዘኳታር አንድምታ "ፊልክስዩስ" በመባል የሚታወቀው። Witold Witakowski, "Filekseyus, the Ethiopic Version of the Syriac Dadisho Qatraya's Commentary on the Paradise of the Fathers," *Rocznik Orientalistyczny* 95/1 (2006) p. 286.

[287] *Majmuʿ al-Qawanin al-Asʿad Ibn Al-Assal*.

[288] Ricci, "Ethiopian Christian Literature," p. 977.

[289] ዝኒ ከማሁ፤ ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ፡* ገጽ 124።

[290] Ricci, "Ethiopian Christian Literature," p. 977.

ቊርባን” ተብሎ የሚጠራና ከሌሎቹ መልክዐት (መልካ መልኮች) በተለየ ሁኔታ በምሥጢረ ቊርባን ላይ የሚያተኩር ድንቅ ድርሰት ከላይ የተጠቀሱት ዓመታት ሥራ (ውጤት) ነው።[291] በተጨማሪም እንደ ገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥ መጀመሪያ በግእዝ ተጽፎ ወደ ዐረብኛ የተተረጐመውን ክብረ ነገሥት[292]፥ መጽሐፈ ሥላሴ፥ ዜና ሥላሴ፥ አንቀጸ አሚን እና መዝሙረ ክርስቶስን አናገኛለን።[293] እነዚህ አገር በቀል ሥራዎች በወርቃማው የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ዘመናት ለተነሡት ደራስያንና አስደናቂ ድርሰቶቻቸው መንገድ ጠራጊዎች ነበሩ።

## ፫. የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ወርቃማ ዘመናት

ከ15ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ እስከ 16ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ድረስ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ እድገት ታላቅ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡ በጊዜው የተነሡ የተለያዩ የትምህርተ ሃይማኖት ክርክሮች የበርካታ ድርሳናት መገኛ ምክንያቶች ሲሆኑ አብዛኞቹ ደራስያን የሚጽፉት ለትሕትና ስማቸውን ሳይገልጹ ወይም በብእር ስም ስለነበር የሁሉም ድርሳናት ትክክለኛ ደራስያን አይታወቁም፡፡ በስም የሚታወቁት ሁለቱ ዝነኛ ደራስያን፡- አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (1357-1417 ዓ.ም.) እና ከ1426-1460 የነገሠው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ናቸው፡፡ “ርቱዓ ሃይማኖት” የሚል ብእር ስም ይጠቀም የነበረው ምሁር ደግሞ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታላላቅ በዓላትን አስመልክቶ በጻፈው ድርሳን ይታወቃል፡፡[294] ከላይ በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ

---

[291] አባ አማኑኤል በመልክዐ ቊርባን ላይ ያደረጉትን ጥናት ይመልከቱ፡- Emmanuel Fritsch, “Une hymne eucharistique éthiopinne: le Malk’a Qʷerban ou ‘Portrait de l'Eucharistie’” *Irénikon,* no. 2-3 (2002) pp. 195-229.

[292] Ricci, “Ethiopian Christian Literature,” p. 977.

[293] ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ* ገጽ 134፡፡

[294] EMML 2375 እና 7028 ይመልከቱ፡፡ ድርሳን የተደረሰላቸው የጌታ ዐበይት (ታላላቅ) በዓላት የሚከተሉት ናቸው፡- ብሥራት፥ ልደት፥ ጥምቀት፥ ሆሣዕና፥ ስቅለት፥ ዕርገት፥ በዓለ ኀምሳ እና ደብረ ታቦር። በተጨማሪ መጽሐፉ ለዐቢይ ጾም ቅበላ፥ በጾሙ ውስጥ ለሚውሉ ሰናብት (እሑዶች)፤ በበዓለ ፍልሰታ ለማርያም፥ በበዓለ ጴጥሮስ ወጳውሎስ እና በበዓለ መላእክት የሚነበቡ ድርሳናትንም ይዟል። የርቱዓ ሃይማኖት “ድርሳን ዘበዓላት ዐበይት” (Project Number 2375) ላይ የተሰጡትን ገለጻዎች Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis*

የትምህርተ ሃይማኖት ክርክሮች (አለመግባባቶች) በተነሡ ቁጥር፥ የአባ ጊዮርጊስን አስተምህሮ በመከተል ይጽፍ የነበረው አፄ ዘርአ ያዕቆብ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሠረታዊ አቋም በማሳየት ይከራከር ነበር፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ንጉሥ ስለሆንኩ ይሰገድልኝ[295] የሚለውን ትእዛዝና በተሳሳተ ግንዛቤ የሚያቀርባቸውን የነገረ መለኮት አሳቦች[296] ዝም ብለው ያልተቀበሉትና በጽኑ የሞገቱ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ መካከል፡- አባ እስጢፋኖስ ዘጕንዳጕንዲ (+1443 ዓ.ም.)[297]፤ እንዲሁም በዘርአ ያዕቆብ መጻሕፍት ውስጥ የምናውቃቸው፡- ዘሚካኤል፥ ገማልያል፥ ፍሬ ማኅበር እና አጽቃ ይገኙባቸዋል፡፡ በዘመኑ የተነሡት የትምህርተ መለኮት ክርክሮች ለበርካታ አገራዊ ጸሎታተ ቍርባን (ቅዳሴያት) እና መስተብቍዓት (የምልጃ ጸሎቶች) መገኛ ምክንያቶች ስለሆኑ በዚህ ክፍል በአጭሩ እንመለከታቸዋለን፡፡

## በእንተ ስግደት ለሥዕል ወለመስቀል

ለሥዕልና ለመስቀል የመስገድ ጉዳይ ሲነሣ በቀጥታ ወደ አእምሮአችን የሚመጡት አባ እስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቶቻቸው (ደቂቀ እስጢፋኖስ) ናቸው፡፡ ነገር ግን ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፥ ኮንቲ ሮሲኒ የአርትዖት ሥራ ሠርቶ የተረጎመውን ገድለ መርቆሬዎስን ጠቅሰው እንደነገሩን፥ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ "ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም" የሚለው የተቃውሞ አሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰማው ደቂቀ እስጢፋኖስ ከመነሣታቸው በፊት በአፄ ያግብአ ጽዮን ዘመነ መንግሥት (1278-1286 ዓ.ም.) ነበር፡፡[298] ትግራይ ውስጥ "ሥዕል ሰሌዳ ነው፤ መስቀልም የጎልጎታ እንጨት ነው" የሚሉ ሰዎች ተነሥተው የተቃውሞ እንቅስቃሴ

*Ababa and the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. VI, Project Numbers 2001-2500 (*Collegeville, MN: HMML, 1982) pp 451-457 ላይ ይመልከቱ፡፡

[295] ጌታቸው ኃይሌ (ትርጕም)፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ* (ኮሌጅቪል፡ ሚኒሶታ፥ 1996) ገጽ 102፥ 106 እና 109፡፡ በወቅቱ የነበረውን የስግደት ትእዛዝ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ሲያብራሩ፡- "የንጉሡ ስም በተጠራ ቍጥር ወይም 'ንጉሡ' የሚል ቃል በተሰማ ቍጥር 'ለክብረ መንግሥቱ ይደሉ ሰጊድ' (ለመንግሥቱ ክብር መስገድ ይገባል) ብሎ ለጥ ብሎ እጅ መንሣት" ከሕዝቡ ይጠበቅ እንደነበር አስረድተዋል፡፡ ጌታቸው ኃይሌ፡ *ስለ ግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የተሰበሰቡ አንዳንድ ማስታወሻዎች* (ኒው ዮርክ፡ 2010 ዓ.ም.) ገጽ 51.

[296] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ*፥ ገጽ 28፡፡

[297] ጌታቸው ኃይሌ፡ *ስለ ግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የተሰበሰቡ አንዳንድ ማስታወሻዎች*፥ ገጽ 51፡፡

[298] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ*፥ ገጽ 24፡፡

ሲጀምሩ፥ አፄ ያግብአ ጽዮን እንቅስቃሴውን ለማስቆም፡- እመቤታችን ተገልጻ "ለሥዕሌና ለልጄ መስቀል መስገድ ይገባል" ብላኛላችና የማይሰግድ ሰው ቢኖር "አንገቱ ለገመድ፥ ያከማቸው ንብረት ለሠራዊቴ፥ ቤቱ ከጠመንጃዬ አፎት ለምትወጣ እሳት ይዳረጋል" ሲል አወጀ፡፡ ይህን አዋጅ የሰሙ ሰዎች በሙሉ ለንጉሡ የጠመንጃ አፎት እንዳይዳረጉ ስለፈሩ፡- "ንጉሡ ያዘዘንን ሁሉ እናደርጋለን፤ ለመስቀልና ለሥዕል እንሰግዳለን" በማለታቸው እንቅስቃሴው በቀላሉ በቁጥጥር ሥር ሊውል ችሏል፡፡[299]

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በ1996 ዓ.ም. የአባ እስጢፋኖስንና የመንፈስ ልጆቻቸውን ገድላት (ገድለ አባ እስጢፋኖስ፥ ገድለ አበው ወአኃው፥ ገድለ አባ አበክረዙን እና ገድለ አባ ዕዝራ) ከግእዝ ወደ አማርኛ ከመተርጐማቸው በፊት ብዙዎቻችን ስለደቂቀ እስጢፋኖስ የምናውቀው፥ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ተአምረ ማርያም ውስጥ ስለእነርሱ ያጻፈውን በመስማት ብቻ ነበር፡፡ በእርሱ ዘመን "ለእግዝእትነ ማርያምና ለልጇ መስቀል አንሰግድም የሚሉ ደቂቀ እስጢፋ" እንደ ተነሡና በዚህም ምክንያት በድንጋይ ተወግረው እንደተገደሉ ነግሮናል፡፡[300] ሚዛናዊ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ግን፥ አፄ ዘርአ ያዕቆብ በአሰቃቂ መከራና በሞት ስለቀጣቸው ስለአባ እስጢፋኖስና የመንፈስ ልጆቻቸው ያጻፈውን ብቻ ሳይሆን ከላይ የተዘረዘሩትን ገድላትንም ማንበብ ይጠበቅበታል፤ ገድላቱ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ደቂቀ እስጢፋኖስ የነበራቸውን አቋም በግልጽ ያስረዱናል፡፡

በ19 ዓመቱ አስኬማ መላእክትን ከአባ ሳሙኤል ዘቈየጻ እጅ ተቀብሎ የመነኰሰው አባ እስጢፋኖስ፥ የመላእክትን አስኬማ ከለበሰበት ጊዜ ጀምሮ የሥጋውን መሻት ለነፍሱ ፈቃድ እያስገዛ በልዩ ትኅርምት (ሥጋን በመኀሰም) ይኖር ነበር፡፡ ከገዳሙ ሥርዓት ውጪ የራሳቸውን ምግብ የሚያዘጋጁ መነኮሳት ሕይወት ግራ ስላጋባው፥ የምንኵስናን ጻማ (ድካም) የተሸከመ አንድ አረጋዊ መነኵሴን፡- "የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደማያቸው ሰዎች መንገድ ነው ወይስ የቤተ ክርስቲያን

299 ዝኒ ከማሁ፡፡

300 ተአምረ ማርያም፥ 1961፥ ገጽ 73፡፡

መጻሕፍት እንደሚሉት?" ሲል ጠየቀው፡፡[301] አረጋዊው መነኩስም አባ እስጢፋኖስ የታዘባቸው መነኮሳት የምንኵስናን ሕይወት መታገሥ አቅቷቸው በገዛ ፈቃዳቸው እንደሚሄዱ አስረዳው፡፡ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር አይተባበርም ነበር፡፡ ብዙዎች በመንፈሳዊ ሕይወቱ ተማርከው ወደ እርሱ መጡ፤ ይህ ግን በአባ እስጢፋኖስ ላይ የመጀመሪያውን ተቃውሞ አስነሣበት፡፡ ከማኅበሩ ልማድ እንደሚያፈነግጥ አድርገው በመክሰስ ከገዳማቸው አባረሩት፡፡ አብረውት የተሰደዱ ደቀ መዛሙርቱ በደብረ ገርዜን (ገሪዛን) የራሳቸውን ማኅበር መሠረቱ፡፡[302]

ይህ ያልበቃቸው መነኰሳት፥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብዙዎችን ወደ ቅድስና ሕይወት መሳቡ ስላስቀናቸው፥ "በመተት የሰውን ልብ ይማርካል" ሲሉ አፄ ይስሐቅ (1406-1421 ዓ.ም.) ዘንድ ከሰሱት፡፡ ነገር ግን በምንኵስና ስም የሚጠሩና እንደ ዓለማውያን ቤታቸው ውስጥ የሚኖሩ መኳንንትና መሳፍንት ስለነበሩ፥ በአፄ ይስሐቅ ችሎት ፊት የአባ እስጢፋኖስን ተግሣጽ ተቀብለዋል፡፡ ለምሳሌ አባ እስጢፋኖስን ለመክሰስ ወደ ችሎቱ የመጣ አባ ሲኖዳ የተባለ የስም መነኵሴ፥ ለዓለም ሞቻለሁ ብሎ ከመነኰሰ በኋላ ሀብት ንብረት ማከማቸት እንደሌለበት አባ እስጢፋኖስ ሲነግረው፦ "ይኽን የምትለውን ሁሉ ለኛ ለመነኵሴዎች ማን ከለከለን?" ሲል በሚያሳፍርና ከአንድ መነኵሴ በማይጠበቅ መልኩ መልሷል፡፡[303] በአባ እስጢፋኖስ ትምህርትና መንፈሳዊነት የተማረከው አፄ ይስሐቅም የትምህርቱን ትክክለኛነት በአደባባይ መሰከረለት፡፡[304]

እንግዲህ አባ እስጢፋኖስ የመጀመሪያው ክስ እና መንገላታት የደረሰበት በዘመኑ የነበሩ መነኰሳት ዓለማዊ ሕይወታቸውን ትተው ወደ ትክክለኛው የምንኵስና ሥርዓት እንዲመለሱ በድፍረት በመናገሩ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ተከሶ[305] ሲቆም፥ ንጉሡ ለምን ከሌሎቹ መነኮሳት ጋር እንደማይተባበር ሲጠይቀው፦ "ለእነዚህ መነኮሳት እንደ ቅዱሳን ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ልጅ ለመከተል ወንጌልን በመሸከም የምትገኝ የሥርዓት ብርሃን

[301] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 64-65፡፡

[302] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 75፡፡

[303] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 88፡፡

[304] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 90፡፡

[305] "ሶ" ጠበቅ ብሎ ይነበብ፡፡

ተሰጣቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ኪዳናቸውን ትተው ወደ ዓለም ተመልሰዋል" የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡[306] አባ እስጢፋኖስ አጥብቆ የሚከተለው የአበው መጽሐፍም፡- "ለመነኮሴ ሞትንና ስቅላትን ተስፋ ከማድረግ የሚበልጥበት [ነገር] የለም"[307] ስለሚል፥ ላመነበት ነገር አንገቱ እስኪቆረጥ ድረስ በአምላኩ ኃይል እንደሚተማመን በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ችሎት ፊት ግልጽ አድርጓል፡፡

አባ እስጢፋኖስን ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ጋር በዋነኝነት ያጋጨው በዘመኑ የነበሩ ሰዎች እንደሚያደርጉት ለንጉሡ የአክብሮት ስግደት አለመስገዱ ነበር፡፡ ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስለሚገባው የጸጋ ስግደትም ተጠይቆ አቋሙን የገለጸበት ሁኔታ አልተዘገበም፡፡ በንጉሡ ፊት በቆመ ቍጥር በእግዚአብሔር ስም ሰላምታ ይሰጠዋል እንጂ በፍጹም ራሱን በስግደት ዝቅ አያደርግም፡፡ እምነቱን ሲመሰክርም፡- "ሃይማኖቴ ይህ ነው፤ አብ የወለደ፥ ወልድ የተወለደ፥ መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ መንፈስ ነው፡፡ ለዚህ (ሥላሴ) እሰግዳለሁ፤ አመልካለሁም . . ." ይል ነበር፡፡[308] ይህን ሁሉ የታዘበው አፄ ዘርአ ያዕቆብም ለእርሱ እንዲሰግድለት፡- "ለምንድን ነው በስግደት ራስክን ዝቅ የማታደርገው?" ብሎ ሲጠይቀው፥ አባ እስጢፋኖስ የማያዳግም መልስ ሰጥቶታል፡- "ሕጉ የሚያዘን[309] ለእግዚአብሔር እንድንሰግድ እንጂ በውስጡ አንተ እንደምትለው እንድንሰግድ ትእዛዝ የለበትም፡፡ ለማንኛውም ከኛ ስግደት አትፈልግ፤ ጸሎትና ቡራኬ ይበቃሃል"፡፡[310] የንጉሡን ጥያቄ በአዎንታ አለመመለሱ አባ እስጢፋኖስን ከባድ ዋጋ አስከፍሎታል፡፡ በንጉሡ ትእዛዝ ወታደሮቹ ሁለንተናው ደም በደም እስኪሆንና ዓይኑ የጠፋ እስኪመስል ድረስ ደበደቡት፡፡ በድብደባው ምክንያት አቋሙን የሚለውጥ የመሰለው አንድ የንጉሡ መልእክተኛ "ለንጉሡ ስገድ" ሲለው፡- "እኔ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ለሌላ አልሰግድም" በማለት መልሶለታል፡፡[311] በተጨማሪም ለንጉሡ ወሬ ከሚያቀብሉ ሰዎች መካከል አንዱ፡- "ለንጉሡ ለምን አትሰግድም?" በማለት

---

[306] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 93፡፡

[307] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 102፡፡

[308] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 101፡፡

[309] "ዘ" ጠብቆ ይነበብ፡፡

[310] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 102፡፡

[311] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 105፡፡

ሲጠይቀው፥ ምክንያቱን፡- "ራሴን ለቅድስት ሥላሴ ስላስገዛሁ ርባዔ [አራተኛ] አላደርግም" ሲል አስረድቶታል።[312] ስለዚህ እንደ አባ እስጢፋኖስ እምነት፥ ሌላው ቀርቶ በአድንኖ (ራስን ዘንበል በማድረግ) ምድራዊ ንጉሥን ማክበር እንኳ እንደ ባዕድ አምልኮ ይቆጠራል፡፡ ይህ አቋም ግትርነትን የተሞላና ለልዑል እግዚአብሔር ብቻ በሚቀርበው የአምልኮ ስግደትና በዘመኑ ለነገሥታቱ ይሰጥ በነበረው የአክብሮት አድንኖ መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ያላገናዘበ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰውና "እኔ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ለሌላ አልሰግድም" የሚለው የአባ እስጢፋኖስ መልስ ውስጥ፥ "ለሌላ" እና "አልሰግድም" የሚሉት ቃላት "ለሥላሴ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ (ለፍጡራን) የአምልኮ ስግደት አልሰግድም" ወይም "ለቅዱሳን የጸጋ ስግደት አልሰግድም (አያስፈልግም)" ማለቱ እንደሆነ ምንም የሚነግሩን ነገር የለም፡፡ በአጭሩ የአባ እስጢፋኖስ አቋም ለእግዚአብሔር ብቻ በሚሰጠው የአምልኮ ስግደትና ቤተ ክርስቲያናችን ለቅዱሳን እንደሚገባ በምታስተምረው የጸጋ ስግደት መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ አያሳይም፡፡ ደቀ መዛሙርቱም እንደ መምህራቸው መከራ እስከመቀበል ድረስ ደርሰው ለንጉሡ መስገድን እምቢ ያሉ ሲሆን፥ ለእመቤታችን የማይሰግዱበትን ምክንያትም ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ትእዛዝ ግርፋትና ድብደባ የደረሰባቸው የአባ እስጢፋኖስ ደቀ መዛሙርት "ለንጉሡ ስገዱ እንጂ" ለሚለው የንጉሡ ወታደሮች ጥያቄ ሲመልሱ፡- "በምን ምክንያት ሆነና ነው በሕይወታችን ዘመን ሁሉ የምንገረፈው፥ የምንሰደደው? በዚህ ምክንያት አይደለምን? እኛ ለእግዚአብሔር ካልሆነ ለማንም አንሰግድም"[313] የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ በዘመኑ የነበሩት ግብፃዊ ጳጳስ አባ ገብርኤል የአባ እስጢፋኖስ ደቀ መዛሙርትን እምነት ከመረመሩ በኋላ "ሃይማኖታችሁ ጥሩ ነው፤ ግን ለምንድን ነው ለማርያም የማትሰግዱት?" የሚል ጥያቄ ሲጠይቋቸው፡- "ካሁን በፊት ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ ሲባል እንጂ ለማርያም እሰግዳለሁ ሲባል አላገኘንም" በማለት መልሰዋል፡፡[314]

---

[312] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 107፡፡

[313] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 136፡፡

[314] ጌታቸው ኃይሌ፡ *ስለ ግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የተሰበሰቡ አንዳንድ ማስታወሻዎች*፥ ገጽ 52፡፡

ነገር ግን ይህ መልሳቸው ለእመቤታችን ምንም አይነት ክብር እንዳልነበራቸው አያሳይም፡፡ ምክንያቱም ተአምረ ማርያምን ለምን እጅ እንደማይነሱ በራሱ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ሲጠየቁ ከደቂቀ እስጢፋኖስ መካከል አንዱ ክሱን በሚገባ አስተባብሏል፡-

> እኛ እጅ አንነሣም አላልንም፤ ብቻ አንድ ተላላኪ ከወንጌል ንባብ በኋላ እንዲነበብ አንድ መጽሐፍ አመጣልኝ፤ ይኼ ምንድን ነው? አልኩት። *መጽሐፈ ተአምረ ማርያም* ነው አለኝ። የሐዋርያት ሥርዓት እኮ እንደዚህ አይደለም። ከኦሪት፥ ከነቢያት፥ ከሐዋርያት ዜና መጻሕፍት [የሐዋርያት ሥራ] ሁሉ (ተነብቦ) ከዚያም ቀጥሎ ወንጌል ይነበባል፤ ከጸሎት ፍጻሜ በኋላ ወንጌልና መስቀል እጅ ይነሣል[315] አልኩት። የቃሌን መጨረሻ ሰምቶ መጽሐፉን ይዞ ሄደ። ከዚያ በኋላ ያንን መጽሐፍ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፥ ሰጠኝ፤ አንብቤ እጅ ነሣሁት።[316]

ይህ መልስ ደቂቀ እስጢፋኖስ በደብረ ገርዜን በነበራቸው ሥርዓተ ጸሎት፥ ከወንጌል እኩል መስቀልን እጅ ይነሡ እንደነበርና ጌታ ለተሰቀለበት መስቀል ክብር እንደነበራቸው ያስረዳል። በወቅቱ በገዳማቸው የማይታወቀውን መጽሐፈ ተአምረ ማርያምን እንኳ መልእክተኛው ከደቂቀ እስጢፋኖስ አንዱ ለሆነው መነኮስ ከሰጠው በኋላ አንብቦ እጅ መንሣቱ ለእመቤታችን ያለውን ክብርና ፍቅር ያሳያል።

በእርግጥ በዱላና በግርፋት የታጀበው የአፄ ዘርአ ያዕቆብ "ስገዱ" ትእዛዝ ደቂቀ እስጢፋኖስን ከንጉሡ ጋር እልህ ውስጥ ከቷቸው እንደነበር መካድ አይቻልም። በአንድ ወቅት የንጉሡ ወታደሮች ከንጉሡ ፊት አቁመው፡- "ለንጉሡ ስገዱ" ሲሏቸው፥ "ለእግዚአብሔር በቀር ለሰው አንሰግድም" የሚል መልስ ከሰጡ በኋላ፥ "በሉ ለማርያም ስገዱ" ሲባሉ፥ "ማርያምንማ ለልጇ ስንሰግድ እዚያ እናገኛ-ታለን"[317] በማለት ቅንነት በጎደለውና በእልኸኝነት ስሜት መልሰዋል። ነገር ግን በዚህ መልስ ምክንያት ደማቸው እንደ ውኃ እስኪወርድ ድረስ ከተገረፉ በኋላ ግብፃዊው ጳጳስ አባ ገብርኤል፥ ለድንግል ማርያም ባለመስገዳቸው "ማርያምን ከሐዲዎች" ከመባል ውጪ ምንም ነገር እንደማያተርፍላቸው መክረው "የሞታችሁ

[315] "ነ" እና "ሣ" ጠብቀው ይነበቡ፡፡

[316] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ*፥ ገጽ 128፡፡

[317] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 147፡፡

ምክንያት ለማርያም ስለ መስገድ አይሁን፤ [ . . . ] አሁንም ኑ አብረን እንስገድ"[318] ሲሏቸው፥ ከውዳሴ ማርያም በመጥቀስ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፦

> አንተ አባታችን ነህ፤ በመንፈስ ስትነግረን መልካም ነው። አባ ሆይ፥ በፊትም ለማርያም አንሰግድም ያልነው አቃልለን አይደለም። እኛኮ ሕይወታችን በማርያም ነው። የትምክሕታችን አክሊል፥ የመድኃኒታችን መጀመሪያ፥ የንጽሕናችን መሠረት የተገኘው ስለ ድኅነታችን ሰው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በወለደች በድንግል ማርያም ነው።[319]

ይህንን ካሉ በኋላ ከጳጳሱ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ለእመቤታችን አብረው ሰገዱ።[320] "ለማርያም አንሰግድም ያልነው" የሚለው አገላለጽ ለወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የጸጋ ስግደት ለመስገድ ፈቃደኛ ያልነበሩበት ጊዜ እንደነበር ያመለክታል፡፡ በጳጳሱ ምክር መስገዳቸውም፥ አቋማቸውን ለማስተካከል የነበራቸውን ዝግጁነትና ለጳጳሱ የሰጧቸውን ትልቅ ቦታ (ክብር) ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ፥ ደቂቀ እስጢፋኖስ፥ አፄ ዘርአ ያዕቆብና መልእክተኞቹ በቃልም በመጽሐፍም እንዳንጸባረቁት የጥላቻ አዋጅ[321] ጸረ ማርያም ሳይሆኑ፥ ውዳሴ ማርያም የሚደግሙና ክብረ ድንግል ማርያምን የሚያውቁ መነኰሳት ነበሩ። እንዲያውም በገዳማቸው ጕንዳ ጕንዲ (ደብረ ገርዜን) ውስጥ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን በድንግል ማርያም ስም (ጕንዳጕንዲ ማርያም)[322] የተሰየመች ናት።

ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል የጸጋ ስግደት መስገድን አስመልክቶ በአባ ዕዝራ ዘመን የነበሩ ደቂቀ እስጢፋኖስ፥ ከፊተኞቹ የአባ እስጢፋኖስ ልጆች የተለየ አቋም እንዳንጸባረቁ የአባ ዕዝራ ገድል ያስረዳናል። ደቂቀ እስጢፋኖስ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ

---

[318] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 149።

[319] ዝኒ ከማሁ።

[320] ዝኒ ከማሁ።

[321] ለምሳሌ አፄ ዘርአ ያዕቆብ "መጽሐፈ ብርሃን" ሲል በሰየመው መጽሐፉ የጻፈውን ይመልከቱ፦ "እነዚህ ደቂቀ እስጢፋ በእርግጥ በሁለት መንገድ ድንግል ለሆነች ለማርያምና ለአንድ ልጁ መስቀል ለመስገድ እምቢ ያሉ አይሁድ ናቸው። የሚገባቸው ቅጣት ሞት ነው። [...] ለእስጢፋ ሰላምታ ሲሰጥ የተገኘ ሰውም ቅጣቱ ደቂቀ እስጢፋን እንደተቀበሏቸው ይሁን"። *Il libro della duce del negus Zar'a Yā'qob (Maṣḥafa Berhān),* CSCO, Vol. 261, Tom. 51(Scriptores Aethiopici) eds. Conti Rossini and L. Ricci (Louvain: 1965) p. 48.

[322] Robert Beylot, "Gundä Gunde," *EA,* Vol. II, ed. Siegbert Uhlig (Wiesbaden, Harrassowitz Verlag, 2005) p. 917.

በሚያደርጉበት ጊዜ ስለ እነርሱ የሚወራውን ወሬ የሰሙ ሌሎች መነኰሳት ማርያ የምትባል ቦታ ወደተሾመ ሹም ሄደው "ለማርያምና [ለአንድ] ልጁ መስቀል የማይሰግዱ ፈላሻዎች"[323] ሲሉ ከሰሷቸው። ደቂቀ እስጢፋኖስም "ለማርያምና ለአንድ ልጁ መስቀል እንሰግዳለን" ካሉ በኋላ፥ በዚህ ብቻ ሳይሆን፥ እንደከሰሷቸው መነኰሳት ሥጋ ስለማይበሉ፤ ወይን፥ ጠላና ወተትም ስለማይጠጡ ከሳሾቻቸው እንደሚቃወሟቸው አስረዱ። ሹሙም "የእግዚአብሔር ሰዎች" ሲል ስለ ደቂቀ እስጢፋኖስ በተረዳው መንገድ ምስክርነት ሰጠ።[324] ኢየሩሳሌም ከደረሱ በኋላ በዚያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኰሳት ከሊቀ ጳጳሳቱ አባ ዮሐንስ ዘንድ፦ "እነሆ፥ አይሁድም፥ አረማውያንም ያልሆኑ መነኮሳት ወደዚህ መጥተዋል። በሥላሴ ኣያምኑም፤ ለማርያም፥ ለመስቀል አይሰግዱም። ታቦትም የላቸውም፤ ቍርባንም አይቆርቡም፤ ሲጸልዩም አቡነ ዘበሰማያትና ጸሎተ ሃይማኖት አይደግሙም። የኢትዮጵያ ንጉሥ ይገድላቸዋል፥ ጳጳሱም ያወግዛቸዋል፤ ሕጋቸው እንደ ሕጋችን አይደለም"[325] ሲሉ ስማቸውን ለማጥፋት ሞክረው ነበር፡፡ አባ ዕዝራ በክሱ ለተጠቀሱት ነጥቦች አጥጋቢ መልስ የሰጠ ሲሆን "ለማርያምና ለመስቀል አይሰግዱም" የሚለውን ክስ ሲያስተባብል እንዲህ ነበር ያለው፦

> ለመለኮት እሳት ልብሱ ለሆነች፥ የዚህ ዓለም ቆሻሻ ላልነካት ለማርያም እንሰግዳለን። ለመስቀልም የሥቃዩ አልጋ ስለሆነ እንሰግዳለን። ነቢዩ [ስለእርሱ]፦ "በመስዕ አቅጣጫ የተተከለ የተመሰገነ እንጨት አየሁ፤ ከፍሬው ለምርጦች ይሰጣል" ይላል። ይህ ስለመስቀል ነው። ሰሎሞንም፦ "ከጥላው ስር አምሮኝ ተቀመጥኩ፤ ፍሬውም ለጕሮሮ ይጣፍጣል" ይላል። የመስቀል ፍሬ ይህ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። [የእርሱ] "ምርጦች" ስለስሙ የሞቱ ሰማዕታት ናቸው።[326]

ይህንን ውብ የሆነ አገላለጽ የሰሙ ሁሉ ስለደቂቀ እስጢፋኖስ፦ "ምን ትሏቸዋላችሁ (እነዚህ) በእውነት የሙሽራው ልጆች፥ የክርስቶስ ወንጌል ተሸካሚዎች፥ እንደ ሐዋርያት ሰባኪዎች ናቸው" አሉ። ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ዮሐንስም የዲቁና ሹመት ሾሞ አሰናበታቸው።[327] የኋለኞቹ የአባ እስጢፋኖስ ልጆች (በአባ

[323] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 286።

[324] ዝኒ ከማሁ።

[325] ዝኒ ከማሁ፥ 289።

[326] ዝኒ ከማሁ።

[327] ዝኒ ከማሁ፥ 290።

ዕዝራ ዘመን የነበሩት) የቀድሞውን አቋም አስተካክለው ስግደትን አስመልክቶ ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ መቀበላቸው የሚያስመሰግናቸው ነው፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብም፥ እስጢፋኖሳውያን ላይ የሚዘገንኑ መከራዎችን በማድረስ ለማሳመን ከመሞከር ይልቅ፥ በሰንበት አከባበር ምክንያት የተነሳውን ውዝግብ ለመፍታት የተጠቀመበትን አይነት ጥበብ[328] ተጠቅሞ ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋር የነበረውን ውዝግብ ለመፍታት ቢሞክር ኖሮ በታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ይድን ነበር፡፡

## ውዝግቡ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ላይ ያስከተለው ለውጥ

በአፄ ዘርአ ያዕቆብና በደቂቀ እስጢፋኖስ መካከል የተፈጠረውና እስጢፋኖሳውያኑን ለእልቂት የዳረገው ውዝግብ ከመነሣቱ በፊት የተደረሱት የቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት፥ ስግደትን አስመልክቶ ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይኸውም የአምልኮ ስግደት[329] የሚቀርበው በአንድነት በሦስትነት ለሚመለከው ሁሉን ቻይ አምላክ ብቻ ሲሆን፤ ለቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፥ ለሌሎቹ ቅዱሳንና በደመ ክርስቶስ ለከበረው ቅዱስ መስቀል ያለንን ፍቅርና ክብር[330] በቅዱሳት ሥዕላቱ ፊት የጸጋ ስግደት በመስገድ እናሳያለን የሚል ነው፡፡[331] ለምሳሌ፥ ከቅዱስ ያሬድ ጾመ ድጓ ዘስቅለት ተወስዶ ግብረ ሕማማት ውስጥ የገባው ዝማሬ፡- "ለመስቀልከ ንሰግድ ኦ ሊቅነ፥ ወለትንሣኤከ ቅድስት ንሴብሕ ኵልነ"[332] (መምህራችን ሆይ፡ ለመስቀልህ እንሰግዳለን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም ሁላችን እናመሰግናለን) ይላል፡፡ በተጨማሪ ደቂቀ እስጢፋኖስ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ አደባባይ ከመቆማቸው ጥቂት ዓመታት በፊት

---

[328] ከሥር ገጽ 210-211 ይመልከቱ፡፡

[329] *Latriea* ወይም worship.

[330] *Dulia* ወይም veneration.

[331] *Apologia of St. John of Damascus Against Those who Decry Holy Images,* (Accessed on April 18, 2019: http://www.ccel.org/ccel/damascus/icons.html) p.7-10.

[332] መምህር ጥዑመ ልሳን ኪ/ማርያም፡ *ሥርዓተ ሰሙነ ሕማማት ወሰላምታ ከነምልክቱ* (አዲስ አበባ፡ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ፡ 1996 ዓ.ም.) ገጽ 84፡፡

ያረፈው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት[333] እንዲህ ይላል፡- "ንሰግድ ለኪ ኦ ንግሥት፥ ወናንቀዐዱ ኀበ ወልድኪ አኃዜ ዓለም፡፡ ስፍሒ እዴኪ ወባርኪ ላዕሌነ ለለ አሐዱ፡ አሐዱ ለአግብርትኪ"[334] (ንግሥት ሆይ፡ እንሰግድልሻለን፥ ዓለምን ወደያዘ ልጅሽም እናንጋጥጣለን፡፡ እጆችሽን ዘርጊ፥ እያንዳንዱን አገልጋይሽንም ባርኪ)፡፡ ከደቂቀ እስጢፋኖስ መነሣት በኋላ የተደረሱና ሥርዓተ አምልኮው ውስጥ የገቡ አንዳንድ መኃልያት (የዜማ ድርሳናት) ግን፥ የጸጋ ስግደት ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል እንደሚገባ የሚገልጹ ብቻ ሳይሆኑ የማይሰግዱትን የሚያወግዙም ናቸው፡፡

## መጽሐፈ ሥርዓት ዘወጽአ እመንበረ ማርቆስ፡ መቅድመ ተአምረ ማርያም

የመጽሐፈ ተአምረ ማርያም ምንጩ፥ እመቤታችን በ12ኛው ምእት ዓመት ፈረንሳይ ውስጥ ያደረገቻቸው ተአምራት እንደሆኑ የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ፡፡[335] አዳዲስ ተአምራት እየተጨመሩ የካቶሊክን እምነት በተቀበሉ የአውሮፓ አገሮች ውስጥ እውቅናን እያገኘ ከመጣ በኋላ፥ በ13ኛው ምእት ዓመት የመጽሐፉ ዝና በሶርያ፥ በምድረ ፍልስጥኤምና ግብፅ ደርሶ ወደ ዐረብኛ ተተረጐመ፡፡ ተአምረ ማርያም የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ በገባበት ጊዜ መጽሐፉ 74 ተአምራትን ብቻ ይዞ ነበር፡፡ መጽሐፉ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመው በአፄ ዳዊት ዳግማዊ (14ኛው ምእት ዓመት) ሲሆን ለንጉሡ የተዘጋጀውና በግሸን ማርያም ዕቃ ቤት ውስጥ የሚገኘው የብራና ተአምረ ማርያም

333 EMML 204, f.39a. አባ ጊዮርጊስ ይህን ድንቅ የምስጋና መጽሐፍ፡- "ስብሐተ መኃልይ" እና "መጽሐፈ ብርሃን" በሚሉ ሁለት ስያሜዎች ይጠራዋል፡፡ ከሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በማይክሮፊልም ኮፒ የተደረገው የአባ ጊዮርጊስ ገድል መግለጫ (EMML 1838) ደግሞ፥ በገድሉ ውስጥ ከተጠቀሱት የሊቁ ሥራዎች መካከል፡- "መጽሐፈ ስብሐት ዘመዓልት ወዘሌሊት" አንደሆነ ይነግረናል፤ በዚህ ስም የተጠራው መጽሐፍ አባ ጊዮርጊስ "መጽሐፈ ብርሃን" ብሎ የጠራው መጽሐፉ እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡ Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. V: Project Numbers 1501-2000* (Collegeville, MN: HMML, 1981) p. 340.

334 EMML 204, f.14b.

335 Ewa Balicka-Witakowska, "Täʾammərä Maryam," *EA,* Vol. IV, p. 789.

75 ተአምራትን ይዟል፡፡[336] አፄ ዘርአ ያዕቆብ የስእለት ልጅ ስለነበረና በልጅነቱ ለእመቤታችን ብፅዐት ተሰጥቶ ስላደገ ለድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር ነበረው፤ ስለዚህ በአፄ ዳዊት ዘመን የተተረጐሙ ተአምራትን ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ የተሠሩትን ተአምራተ ማርያምን ጨምሮ መጽሐፉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ክፍል ይሆን ዘንድ ወደ ተለያዩ ገዳማት ላከው፡፡[337] ነገር ግን በሁሉም ገዳማት ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም፤ ደፍረው የተቃወሙም አበ ምኔቶች ነበሩ፡፡ [338] "ዝንቱ መጽሐፈ ሥርዓት ዘወጽአ እመንበረ ማርቆስ ሐዋርያ እመካነ መዓልቃ ዘምስር"[339] የሚለው የመጽሐፉ መቅድም፥ *የሙዐሊቃ* ቀኖና[340] የተሰኘውንና ከመንበረ ማርቆስ ተገኘ የተባለውን ቀኖና (ሥርዓት) የሚያመለክት ቢሆንም፥ በቅብጥ (ኮፕቲክ) ወይም በዐረብኛ የዚህ መጽሐፈ ሥርዓት አቻ አልተገኘም፡፡[341] ስለዚህ የተአምረ ማርያም መቅድም ደራሲ አፄ ዘርአ ያዕቆብ እንደነበር መገመት አያዳግትም፡፡

በዕለተ እሑድ እንዲነበብ የተዘጋጀው የተአምረ ማርያም መቅድም፥ የእመቤታችን ተአምር በዕለተ እሑድና በ33ቱ በዓላተ ማርያም መነበብ እንዳለበት ያዛል፤ ንባቡም እንዳይታጎል በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን የነበሩት ሁለቱ ግብፃውያን ጳጳሳት (አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል) እንዳወገዙ ይነግረናል፡፡[342] የመጽሐፈ ተአምረ ማርያም

---

[336] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 790።

[337] *ጌታቸው ኃይሌ፥ ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* 25፡፡

[338] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 26፡፡

[339] *ተአምረ ማርያም* (አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ 1988) ገጽ 35፡፡

[340] "*Canon of al-Muᶜallaqah*" - ይህ ስያሜ "*Al-Kanisah al-Muᶜallaqah* - አል፡ከኒሳ አል፡ሙዐለቃ" - (The Hanging Church) ተብላ የምትታወቀውና አሮጌው ካይሮ ውስጥ የምትገኘውን ዝነኛ ቤተ ክርስቲያን ያመለክታል - Ewa Balicka-Witakowska, "Täᵓammərä Maryam," *EA,* Vol. IV, p. 790. ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለመግባት 29 ደረጃዎችን መውጣት የሚያስፈልግ ሲሆን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ከደረጃዎቹ በላይ ተንጠልጥሎ የታነጸ ነው፤ ለዚህም ነው በእንግሊዝኛ ቤተ ክርስቲያኒቱ The Hanging Church ተብላ የምትጠራው፡፡ በ12ኛው ምእት ዓመት ኢጋማሽ መንበረ ማርቆስ ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ ሲዛወር መንበሩ ለተወሰኑ ዓመታት በዚህች ዝነኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቆይቶ ነበር፡፡ በተአምረ ማርያም መቅድም "ዝንቱ መጽሐፈ ሥርዓት ዘወጽአ እመንበረ ማርቆስ ሐዋርያ እመካነ መዓልቃ ዘምስር" የሚለው አገላለጽ፥ ትእዛዙ የተገኘው *Al-Kanisah al-Muᶜallaqah* በምትባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንበሩን ካደረገው ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ነው ለማለት ይመስላል፡፡ በዐረብኛ፥ ግብፅ "ምስር ወይም አል-ምስር" ተብላ ትጠራለች፡፡

[341] Ewa Balicka-Witakowska, "Täᵓammərä Maryam," *EA,* Vol. IV, p. 790.

[342] *ተአምረ ማርያም*፥1988 ዓ.ም. ፥ ገጽ 36፡፡

የዘወትር መቅድም ደግሞ ለእመቤታችን የጸጋ ስግደት እንደሚገባ ይገልጽና፡- “በሥዕሏም ፊት ስገዱ፤ ለሥዕሏ ያልሰገደ ግን ከቆመበት ቦታ ይጥፋ ስም አጠራሩም አይታወቅ”[343] ይላል፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር ፥ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ፡- “ለእግዝእትነ ማርያምና ለልጇ መስቀል አንሰግድም የሚሉ”[344] ተብለው የተገለጹትን ደቂቀ እስጢፋኖስን የሚያመለክት ሲሆን፥ አፄ ዘርአ ያዕቆብን እንደዚህ ዓይነት የግዝት ቃል በተአምረ ማርያም መቅድም ውስጥ እንዲጽፍ ያስገደደው ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋር የነበረው አስከፊና አሰቃቂ ጸብ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዘመነ ዘርአ ያዕቆብም ሆነ ከእርሱ በኋላ በተደረሱት የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ውስጥ፥ ለሥዕለ ድንግል ማርያም የማይሰግዱ ሰዎችን፥ የንጉሡን ፈለግ በመከተል የሚያወግዙ ኃይለ ቃላት እናገኛለን፡፡

## መልክዐ ሥዕል ወማኅሌተ ጽጌ

የተለያዩ ይዘቶች ያሏቸውና *“ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ”*[345] ወይም *“መጽሐፈ ሰዓታት ወኵሉ ፀዋትዊሁ ምስለ ባሕረ ሐሳብ”*[346] በሚል ርእስ የታተሙት መጻሕፍት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ለ24 ሰዓታት አገልግሎት ካዘጋጀው መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት ውስጥ ከመንፈቀ ሌሊት እስከ ሌሊቱ አሥር ሰዓት ድረስ ያለውን ክፍል ብቻ የያዙ ናቸው፡፡ በታተሙት መጻሕፍት ውስጥ የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች፡- “ሃሌ፡ ሃሌ፡ ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ፡ ሃሌ ሉያ፤ አአትብ ወእትነሣእ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ …” ከሚለው ጀምሮ፥ “ሰአሊ ለነ ማርያም ማኅቶተ ዓለም…”[347] እስከሚለው ክፍል መጨረሻ ያለው ብቻ ነው፡፡[348] በታተሙት መጻሕፍት ውስጥ “ሰአሊ ለነ ማርያም ማኅቶተ ዓለም . . .” ከሚለው ክፍል ቀጥለው የሚገኙት የተለያዩ ዝማሬያት (ለምሳሌ፡- ወትቤ ማርያም፥ ለኖኅ

---

[343] ዝኒ ከማሁ፥ 29፡፡
[344] ተአምረ ማርያም፥ 1961ዓ.ም. ፥ ገጽ 73፡፡
[345] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ* (አዲስ አባባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1989 ዓ.ም).
[346] *መጽሐፈ ሰዓታት ወኵሉ ፀዋትዊሁ ምስለ ባሕረ ሐሳብ* (አስመራ፡ ኮከበ ጽባህ ማተሚያ ቤት፡ 1959 ዓ.ም).
[347] ልብን በሚማርክ ዜማ የሚዜመው ይህ ውብ ድርሰት የሚጠቃለለው ከሉቃ. 1፥ 46-55 በተወሰደው ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም (ተአብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር . . .) ነው፡፡
[348] EMML 204, f.11a-f.26a እና *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ፥* ገጽ 6-132ን በማነጻጸር ይመልከቱ፡፡

ሐመሩ፥ ስብሐተ ፍቁር፥ አ ርጎርጎተ ሕሊና፥ መልክዐ *ሥዕል*፥ ተፈ*ሥ*ሒ ማርያም ወዘተ.) የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች አይደሉም፡፡ ስማቸው የማይታወቅ የተለያዩ ሊቃውንት የደረሷቸው እነዚህ ዝማሬያት ከአባ ጊዮርጊስ ከፊል *ሥራዎች* ጋር "*ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ*" በሚል ርእስ እንደታተሙ ልብ እንበል፡፡

እስካሁን ድረስ ያልታተመው የአባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት "ሰአሊ ለነ ማርያም ማኅቶተ ዓለም …" ከሚለው ዝማሬ ቀጥሎ የሊቁን በጣም የምትወደድ ድርሰት፥ "እሴብሕ ጸጋኪ ኦ ምልዕተ ጸጋ …" ያስከትልና ከሌሊቱ 10፡00 እንዲደርስ የተዘጋጀውን የአገልግሎት ክፍል "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ"፥ "ባርከነ እግዚኦ አምላክነ"፥ "ጸሎተ ሃይማኖት" በተሰኙ ጸሎታት ይደመድማል፡፡[349] የአባ ጊዮርጊስን "እሴብሕ ጸጋኪ ኦ ምልዕተ ጸጋ …" አብነት በማድረግ ከእርሱ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት "እሴብሕ ጸጋኪ ዘቀኍስቋም"[350]፥ "እሴብሕ ጸጋኪ ዘዘወትር/ዘመላእክት"[351]፥ "እሴብሕ ጸጋኪ ዘዘመነ ጽጌ"[352]፥ "እሴብሕ ጸጋኪ ዘደብረ ዘይት ወዘጰጕሜን (ዘሐዋርያት)"[353] እና "እሴብሕ ጸጋከ ዘመድኃኔ ዓለም"[354] የተባሉ ዝማሬያትን እንደደረሱ ሁሉ፥ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ላይ እንዲዘመር ያዘጋጀውን "በእንተ ቅኔ ሠራዊተ መላእክት"[355] መሠረት በማድረግ ደግሞ፡- "ኵሎሙ ዘእግዝእትነ ማርያም"[356]፥ "ኵሎሙ ዘኪዳነ ምሕረት

[349] EMML 204, f. 26a-26b.
[350] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ*፥ ገጽ 250፡፡
[351] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 375፡፡
[352] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 376፡፡
[353] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 377፡፡
[354] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 378፡፡
[355] EMML 4493, f. 48b. በማይክሮ፡ፊልም ኮፒ በተደረገው በዚህ የብራና መጽሐፍ ላይ የተሰጠውን ገለጻ Getatchew Haile, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Minuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. X: Project Numbers 4001-5000* (Collegeville, MN: HMML, 1993) ገጽ 181-187 ላይ ይመልከቱ፡፡ ተስፋ ገብረ *ሥ*ላሴ (ዘብሔረ ቡልጋ) ያሳተመው *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ*፥ "ኵሎሙ ዘዘወትር" የሚል ርእስ ሰጥቶታል፡፡ *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ*፥ ገጽ 99፡፡
[356] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ*፥ ገጽ 104፡፡

ወፍልሰታ"[357]፥ "ኵሎሙ ዘቀኍስቋም"[358]፥ "ኵሎሙ ዘመላእክት"[359]፥ "ኵሎሙ ዘቅድስት ሥላሴ"[360] እና "ኵሎሙ ዘበዓለ እግዚአብሔር"[361] የተሰኙ ዝማሬያትን አዘጋጅተዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የአባ ጊዮርጊስ ዝማሬያት ከእርሱ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት ከደረሷቸው መዝሙራት ጋር ስናነጻጽር በሁሉም ሥራዎች ላይ ፍቅረ ድንግል ማርያም በግልጽ የሚነበቡ ቢሆንም፥ የኋለኞቹ ሥራዎች በዚህ ንኡስ ክፍል የተመለከትነውን ውዝግብ (ለሥዕለ ድንግል ማርያም መስገድ) የሚያንጸባርቁ ዓረፍተ ነገሮች ይገኙባቸዋል፡፡[362] ለምሳሌ የታተመው መጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የምናገኘው (በሌሎች ሊቃውንት የተደረሰው) "ኵሎሙ ዘእግዝእትነ ማርያም" ውስጥ "ዘኢሰገደ ለንግሥኪ ውሳጤ ልቡ አትሒቶ፤ ንጽሐ ድንግልናኪ አስቲቶ፤ ለዓለመ ዓለም ያስቆቁ በከርሠ ገሃነም ተዐጊቶ"[363] የሚል ንባብ እናገኛለን፡፡ ይህም፥ የድንግልናሽን ንጽሕና በማቃለል ልቡን ዝቅ አድርጎ [በትሕትና] ለንግሥናሽ ያልሰገደ [ሰው] በገሃነም ሆድ ውስጥ ተይዞ ለዘላለም ያልቅስ ማለት ነው፡፡

ሥዕለ ማርያም ፊት ለእመቤታችን ያለንን ፍቅርና ክብር በመግለጽ ለድንግል ማርያም የጸጋ ስግደት መስገድ እንደሚገባ በግልጽ የሚያመለክቱና የማይሰግዱትን ደግሞ የሚያወግዙ ንባባትን "መልክዐ ሥዕል" እና "ተፈሥሒ ማርያም" በተባሉ ድርሰቶች ውስጥም እናገኛለን፡፡ ለመልክዐ ሥዕል መቅድም ሆኖ የተዘጋጀው ዝማሬ፡

[357] ዝኒ ከማሁ፥ 108፡፡

[358] ዝኒ ከማሁ፥ 112፡፡

[359] ዝኒ ከማሁ፥ 117፡፡

[360] ዝኒ ከማሁ፥ 119፡፡

[361] ዝኒ ከማሁ፡፡

[362] በአባ ጊዮርጊስ ዘመን ውዝግቡ የቤተ ክርስቲያኒቷን አንድነት እስከመፈታተን ድረስ ስላልደረሰ በሊቁ ድርሰቶች ውስጥ ለሥዕለ እግዝእትነ ማርያምና ለቅዱስ መስቀል አልሰግድም የሚሉ ሰዎችን የሚያወግዙ ምንባባት አናገኝም፡፡ በመጽሐፈ ምሥጢር እንደምናነበው፥ አባ ጊዮርጊስ በአጽንዖት የሚያወግዘው ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ሥጋዌን የተመለከቱ ዓለም አቀፍ ኑፋቄያትን፥ እንዲሁም በእርሱ ዘመን የተነሡ አንዳንድ የትምህርተ ሃይማኖት አለመግባባቶችን (ለምሳሌ፥ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት "ቢቱ" የተባለ ሰው ያስተማረውን ትምህርት የገሠጸበትን) ነው፡፡ "ምንባብ ዘደብረ ዘይት" *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, ገጽ 183-209 ተመልከት፡፡

[363] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግሁ፡* ገጽ 107-108.

- "ምልዕተ ጸጋ ተፈሥሒ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ሰላማዊት ሰላም ለኪ፤ መንፈሳዊት ርግብ ወንሰግድ ለኪ" [364] (ጸጋን የተመላሽ [ሆይ] ደስ ይበልሽ፡ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፤ ሰላማዊትና መንፈሳዊት ርግብ [ሆይ] ሰላም ላንቺ ይሁን [እያልን] እንሰግድልሻለን) ይላል፡፡ ደራሲው የድንግል ማርያምን ሥዕል በደስታና በሐሤት እጅ መንሳት እንዳለብን ሲገልጽ ደግሞ እንዲህ በማለት ይዘምራል፡- "መጽአት ነዋ ኅቡረ ምስለ ወልዳ፤ ናንፈርዕፅ ቅድመ ሥዕላ እንዘ ንሁብ ጋዳ፤ ለለጌሠሙ ትመስል እንግዳ"[365] (እነሆ ከልጅዋ ጋር መጣች፤ እጅ መንሻን እየሰጠን በሥዕሏ ፊት እንዝለል፤ በየቀኑ (በየነጋው) እንግዳ[366] ትመስላለች)፡፡ ተመሳሳይ አገላለጽ "ማኅሌተ ጽጌ" በተሰኘው ዝማሬ ውስጥም እናገኛለን፡- "ከመ ይትፌሣሕ ሕፃን ሶበ ይሬኢ እሞ፤ እትፌሣሕ አንሰ ሥዕለኪ በርእይ ወተሣልሞ"[367] (ሕፃን ልጅ እናቱን ሲያይ ደስ እንደሚለው፥ እኔም ሥዕልሽን በማየትና በመሳለም ደስ ይለኛል)፡፡ የመልክዐ ሥዕል ደራሲ "ሰጊድ ወአምኃ ይደሉ ለሥዕልኪ፤ ወለሥዕለ ክርስቶስ ወልድኪ"[368] (ለሥዕልሽና ለልጅሽ ለክርስቶስ ሥዕል ስግደትና እጅ መንሳት/ እጅ መንሻ ይገባል) ካለ በኋላ ለሥዕለ ማርያምና ለልጇ ሥዕል እንደሚሰግድ በግልጽ ይነግረናል፡- "ቅድመ ሥዕልኪ እሰግድ ወለሥዕለ ወልድኪ እገኒ፤ ማርያም ድንግል ማርያም እመ አዶኒ"[369] (የአዶናይ እናት ማርያም [ሆይ] ከሥዕልሽ ፊት እሰግዳለሁ፤ ለልጅሽ ሥዕልም እገዛለሁ)፡፡

ከመልክዐ ሥዕል ጋር ዘወትር በነግህ የሚደርሰው "ተፈሥሒ ማርያም" የተሰኘው ዜማ የሚያወሳው ለእመቤታችን የጸጋ ስግደት እንደሚገባ ብቻ ሳይሆን፥ ለክብሯ የማይሰግዱትንም በአጽንዖት ያወግዛል፡- "ሰላም ለማርያም ዐጽፈ ወልድ ዋሕድ፤ ወመንበረ ሕያው ነድ፤ ለድንግልናሃ ይደሉ ሰጊድ፤ ለማርያም ዘይቤ

[364]ዝኒ ከማሁ፥ 228፡፡

[365] ዝኒ ከማሁ፥ 229፡፡

[366] ደራሲው "በየቀኑ የማትጠገብና አዲስ ናት" ብሎ ለእመቤታችን ያለውን ፍቅር ለመግለጽ ፈልጎ ነው፡፡

[367] "ማኅሌተ ጽጌ" *መዝሙረ ዳዊት፡ ማኅሌተ ጽጌ፥ ሰቆቃወ ድንግል በልሳነ ግዕዝ* (አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1987) ገጽ 5፡፡

[368] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ፥* 232፡፡

[369] ዝኒ ከማሁ፥ 231፡፡

ኢይሰግድ፤ ሞጻፌ መብረቅ በሊኅ በርእሱ ለይረድ፡፡"[370] ይህም፡- የአንዱ ልጅ [የክርስቶስ] መኅናጸፊያና የሕያው እሳት[371] መንበር ለሆነች ለማርያም ሰላም ይሁን፤ ለድንግልናዋ ስግደት ይገባል፥ ለማርያም አልሰግድም በሚል ሰው ራስ ላይ እሳታዊ መብረቅ ይውረድ ማለት ነው፡፡ በበዓለ ኀምሳ በሚደርሰው "ተፈሥሒ ማርያም" ውስጥም ተመሳሳይ ተግሣጽ እናነባለን[372]፡- "እሰግድ ቅድመ ማርያም ለዝክረ ስምኪ በጽዋዔ፤ ወእሰግድ ካዕበ ለድንግልናኪ ክልኤ፤ ወእሰግድ ሠልሰ ለሥዕልኪ ቅድመ ጉባኤ፤ ዘኢሰገደ ለሥዕልኪ አስሪጾ ምማዔ፤ በሥጋሁ ወበነፍሱ ኢይርከብ ትንሣኤ" [373] (የስምሽን መታሰቢያ በመጥራት [በፊትሽ] እሰግዳለሁ፤ በድጋሚ በሁለት ወገን[374] ለሆነ ድንግልናሽም እሰግዳለሁ፤ ሦስተኛም በጉባኤ ፊት ለሥዕልሽ እሰግዳለሁ፤ ለሥዕልሽ [በፍርሃትና በትሕትና ሆኖ] ያልሰገደ ሰው፥ በሥጋውና በነፍሱ ትንሣኤን አያግኝ)፡፡

ለሥዕለ ማርያምና ለቅዱስ መስቀል መስገድን አስመልክቶ ከተነሣው ውዝግብ በኋላ ከተደረሱት ዝማሬያት መካከል ማኅሌተ ጽጌ ይገኝበታል፡፡ አባ ጽጌ ድንግል[375] የተባለ መነኮስ እንደደረሰው የሚነገርለት ይህ ዝማሬ ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ያለው ሲሆን፥ የእመቤታችንን ንጽሕና እና ድንግልና፥ በእርሷ የተደረጉትን ተአምራት (ጌታን ከመውለዷ ጀምሮ ያለውን)፥ ዕረፍቷንና ዕርገቷን አስመልክቶ በግጥም የተዘጋጀ ነው፡፡ ደራሲው የቅኔ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትና የነገረ መለኮት ምሁር

---

370 "*ተፈሥሒ ማርያም ዘዘወትር*"፥ *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግሁ፡* ገጽ 155፡፡

371 እመቤታችን በማኅፀንዋ የተሸከመችውን የወልደ እግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ (በመለኮቱ የሚያቃጥል እሳት መሆኑን) ለማመልከት ነው፡፡

372"ባ" ጠበቅ ብሎ ይነበብ፡፡

373 "*ተፈሥሒ ማርያም ዘበዓለ ሃምሳ*"፥ *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግሁ፡* ገጽ 248፡፡

374 የእመቤታችን ድንግልና በክልኤ (በሁለት ወገን) ነው የሚባለው የሥጋ ድንግልና ብቻ ሳይሆን የሐሳብም ድንግልና ስለተሰጣት (ከተሰጣት ጸጋ እግዚአብሔር የተነሣ በሥጋና በሕሊና ፍጽምትና ንጽሕት ስለሆነች) ነው፡፡

375 ዶ/ር ሀብሚካኤል ኪዳነ የማኅሌተ ጽጌን ሥነ ጽሑፋዊ ውበትና በውስጡ የተጠቀሱትን አስደናቂ የነገረ መለኮት አሳቦች በመመልከት ደራሲው የ15ኛው ምእት ዓመት ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ሊሆን እደሚችል ጠቁመዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ፥ ማሕሌተ ጽጌ የተደረሰው በአፄ ዘርአ ያዕቆብ የንግሥና ዘመን መጨረሻና የአፄ ልብነ ድንግል ንግሥና መጀመሪያ ላይ እንደሆነና ማኅሌቱ በተለያዩ ሰዎች እንደተደረሰ የገመቱ ሊቃውንት እንዳሉም ነግረውናል፡፡ Habtemichael Kidane "Maḫletä Ṣəge," *EA*, Vol. 3, p.661.

እንደነበር ድርሰቱ ይመሰክርለታል፡፡ ማኅሌተ ጽጌ፡- "ማርያም ጽጌ ዘዕብሬትኪ መፀው"፥[376] "ጽጌ ደንጐላ ዘቈላ ወአኮ ዘደደክ፤ ዘጸገይኪ ጽጌ በማዕከለ አይሁድ አሥዋክ"[377] እያለ ድንግል ማርያምን፤ "በጌጋየ አዳም ወሔዋን ሱራፌ ዘአፀዋ፤ እንበለ ጽጌኪ መኑ ለአንቀጸ ገነት ዘአርኃዋ?[378]፥ "እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ ጽጌ ጸዐዳ ወቀይሕ"[379] በማለት ደግሞ ውድ ልጇን በአበባ እየመሰለ ይዘምራል፡፡ እንዲሁም የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትሕትና እና መለኮታዊ ክብሩ የተገለጸባቸውን ሁነቶች እያነጻጸረ እንደሚከተለው ያደንቃል፡-

ስፍነ ድንግል ለጽጌኪ ተአምራቲሁ እዜኑ፡፡
ወትሕትናሁ እሔሊ ሶበ ረፈቀ ለስምዖን በውስተ ሐፅኑ፡፡
ከመ ቆመኑ ቅድመ ዮሐንስ ድኑኑ፡፡
ወሚመ ከመ በረቀ በደብረ ታቦር ብርሃኑ፡፡
ወከደነ ሰማያተ ሥኑ፡፡[380]

የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ የደቂቀ እስጢፋኖስን እንቅስቃሴ እንደሚያውቅ፥ እንዲሁም አባ እስጢፋኖስና የመንፈስ ልጆቻቸው "ጸረ ማርያም" እንደነበሩ ከሚያምኑ ወገኖች መካከል እንደሆነ በማኅሌቱ ውስጥ አሳይቶናል፡፡ ደራሲው፥ አባ እስጢፋኖስ በምንኵስና ተጋድሎው የሚመካ (የሚመጻደቅ) መነኵሴ እንደነበር ሲገልጽ፡- "ብፁዓን ኃጥአን እለ ተአምረኪ ተወከሉ፡፡ እምጻድቅ እስጢፋ ዘይትሜካህ በጻማ ገድሉ"[381] ይላል፡፡ ይህም፥ ጻድቅ እንደሆነ አስቦ በገድሉ ድካም [በምንኵስና ሕይወቱ] ከሚመካው [አባ እስጢፋኖስ] ይልቅ፥ ተአምርሽን የታመኑ ኃጥአን የተሰመገኑ ናቸው ማለት ነው፡፡ እንዲሁም፥ ማርያምን እወዳታለሁ እያለ

---

376 "ማኅሌተ ጽጌ" *መዝሙረ ዳዊት*፥ ገጽ 5፡፡

377 ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 36፡፡ መኃ. መኃ. ዘሰሎሞን 2፥2 ላይ "በእሾህ መካከል እንዳለ የሱፍ አበባ፡ እንዲሁ ወዳጄ በቆነጃጅት መካከል ናት" የሚለውን አሳብ በመውሰድ፥ ደራሲው ድንግል ማርያምን በእሾህ በተመሰሉት አይሁድ መካከል አብባ (ጌታን ወልዳ) የተገኘች የሱፍ አበባ እንደሆነች ድንቅ በሆነ መልኩ በምሳሌ እነዚህን ስንኞች ቋጥሯል፡፡

378 "ማኅሌተ ጽጌ" *መዝሙረ ዳዊት*፥ ገጽ 7፡፡ በአዳምና በሔዋን በደል ምክንያት የተዘጋችው ገነት ከእመቤታችን በተገኘው አበባ (በጌታ) መከፈቱን የሚያመለክት ዝማሬ ነው፡፡

379 "ማኅሌተ ጽጌ" *መዝሙረ ዳዊት*፥ ገጽ 21፡፡

380 ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 24 - ደራሲው የጌታን ትሕትና (በአረጋዊው ስምዖን መታቀፉ፥ ራሱን ዘንበል አድርጎ በዮሐንስ እጅ መጠመቁ) በታቦር ተራራ ብርሃነ መለኮቱን ከመግለጹ ጋር ያነጻጽርና የቱን እንደሚያደንቅ ይጠይቃል፡፡

381 "ማኅሌተ ጽጌ" *መዝሙረ ዳዊት*፥ ገጽ 10፡፡

ተአምረ ማርያምን የማይወድ ሰው ሁሉ ከአባ እስጢፋኖስ ጋር ኅብረት ያለውና ክርስቲያን ሊባል የማይገባው (አይሁዳዊ) መሆኑን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡-

ዘሰ ይብል አፈቅረኪ ወኢያፈቅር ተአምረኪ ክርስቲያናዊ፡፡
ኢክርስቱን ውእቱ አይሁዳዊ፡ ወሠርፀ እስጢፋ ሐሳዊ፡፡
አንሰ እቤ በማኅሌተ ሰሎሞን ወልደ ሰንቃዊ፡፡
አፈቅሮ ለፍግዕኪ ወለተ ይሁዳ ወሌዊ፡፡
ከመ መርዓቶ ያፈቅር ጽጌኪ መርዓዊ፡፡[382]

ማኅሌተ ጽጌ ከደቂቀ እስጢፋኖስ እንቅስቃሴ በኋላ እንደተጻፈ የምንረዳው ለድንግል ማርያምና ለመስቀለ ክርስቶስ ስግደት እንደሚገባ የሚያስረዳውን ክፍል ስናነብ ነው፡፡ በተለመደው ማራኪ ሥነ ጽሑፋዊ አገላለጽ ደራሲው እንዲህ ሲል ስንኞቹን ቋጥሯል፡-

ቡሩካን አርጋብ እለ በታሕቴኪ ያጸልሉ፡፡
ወይሴስዩ ፍሬኪ እንዘ በደሙ ያጠልሉ፡፡
ዕፀ መዓዛ ማርያም ለመስቀል ትእምርተ አምሳሉ፡፡
እስመ ጽጌኪ ጽጌሁ ወአስካልኪ አስካሉ፡፡
ለክልኤክሙ ሰጊድ ይደሉ፡፡[383]

እንደ ደራሲው (አባ ጽጌ) አገላላጽ፥ የቅድስት ድንግል ማርያምን ተአምር የሚያቃልሉ ሰዎች መርገምን የማይፈሩ ደፋሮች ናቸው፡- “ዘያስተሐቅር ተአምረኪ ወኢይፈርህ መርገመ፤ ሰይጣን ወልዶ መስተቃርነ አቀመ፡፡”[384] ለክብረ ድንግል ማርያምና ለመስቀል የጸጋ ስግደት እንደሚገባ ከመግለጽ ባሻገር፥ ለሁለቱ የምንሰግድባቸውን ምክንያቶች የሚያስረዱ መስብቍዓት (የምልጃ ጸሎታት) ተደርሰው የሥርዓተ አምልኮው ክፍል ሆኑ፡፡

---

[382] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 13፡፡
[383] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 39፡፡
[384] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 32፡፡

## መስተብቍዕ ዘማርያም ወዘመስቀል

ወሎ ውስጥ የሚገኘው የደደቢት ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነው የብራና መጽሐፈ ቅዳሴ፥[385] የታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ከምናገኘው የተለየ "መስተብቍዕ ዘማርያም" ይዟል፡፡ "ወካዕበ ናስብቍዓ ለነቅዓ ሕይወት ለቅድስት ደብተራ፤ ዘወለደት ወአግመረት ጽርሰፎራ" ("የሕይወት ምንጭ፥ ቅድስት ድንኳንንም እንለምናታለን፤ ጽርሰፎራን (መሥዋዕትን) የወለደችና የቻለች ናትና"[386]) ብሎ ይጀምርና፥ "ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት፤ ዘምስለ ወልዳ አምልኮ ወስግደት፥ በምድር ወበሰማያት፥ በባሕር ወበቀላያት፥ ለዓለመ ዓለም፡ አሜን"[387] ("[ለእርሷ] ክብርና [ምስጋና] ይገባል፤ ከልጇም ጋር አምልኮና ስግደት፤ በምድርም በሰማዮችም፥ በባሕርም በውቅያኖስም፥ [ለዘላለሙ] አሜን"[388]) ብሎ ይጨርሳል፡፡ ይህ መስተብቍዕ ከደቂቀ እስጢፋኖስ እንቅስቃሴ መነሣት በኋላ የተደረሰ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡[389] ከተደረሰበት ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ገብቶ የሥርዓተ አምልኮው ክፍል ሆኖ ለረጅም ዓመታት ከቆየ በኋላ በ1870 ዓ.ም. በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን የምሥጢረ ሥጋዌ ክርክሮች አስመልክቶ ቦሩ ሜዳ ላይ የተካሄደው ጉባኤ፥ ከላይ የተጠቀሰው መስተብቍዕ ውስጥ፡- "ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት፤ *ዘምስለ ወልዳ* አምልኮ ወስግደት" – "[ለእርሷ] ክብርና [ምስጋና] ይገባታል፤ *ከልጇም ጋር* አምልኮና ስግደት" የሚለውን ዓረፍተ ነገር መርምሮ፥ እመቤታችን ከልጇ ጋር መመለክ እንደሚገባት የሚገልጽና በፍጡርና ፈጣሪ መካከል ያለውን ልዩነት ያላገናዘበ መሆኑን ተረድቶ፡- "ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት፤ **ወለወልዳ** አምልኮ ወስግደት" (ለእርሷ ክብርና ምስጋና ይገባል፤

[385] ስለዚህ መጽሐፈ ቅዳሴ (EMML 2969) የተሰጠውን አጭር መግለጫ፡- Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. VII: Project Numbers 2501-3000* (Collegeville, MN: HMML, 1983) pp. 282-284 ይመልከቱ፡፡

[386] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 37፡፡

[387] EMML 2969, ff.14b-15a; *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 36-37 ላይ የተጠቀሰ፡፡

[388] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፥* ገጽ 38፡፡

[389] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 36፡፡

**ለልጇም** አምልኮና ስግደት) ሲል አርሞታል፡፡ የታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የሚገኘው፥ ይኸው የታረመው ንባብ ነው፡፡[390]

በተመሳሳይ ወቅት (ከደቂቀ እስጢፋኖስ መነሣት በኋላ) የተደረሰው "መስተብቍዕ ዘመስቀል" የቅዱስ ወንጌል መምህራን ለድንግል ማርያምና ለመስቀል እንድንሰግድ እንዳዘዙን ይናገራል፡- "በእንተ ዝንቱ አዘዙነ መምህራነ ቅዱስ ወንጌል … ንስግድ ለመስቀል ወለማርያም ድንግል"፡፡ [391] እንዲሁም፥ ለክርስቶስ መስቀል የምንሰ ግድበት ምክንያት፥ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተቀደሰ ስለሆነ፤ ለድንግል ማርያም የምንሰግደው ደግሞ፥ መድኃኒት የሆነው ጌታ ክርስቶስ ከእርሷ በመወለዱ መሆኑን ያስረዳል፡፡ [392] በዚህ መስተብቍዕ መጨረሻ ላይ ድንግል ማርያምና የክርስቶስ መስቀል በክብር የተካከሉ መሆናቸውን የሚገልጽ ሐረግ (እስመ ተአረዩ በክብሮሙ) እናገኛለን፡፡ ይህ ሐረግ የገባበት ምክንያት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፈ ምሥጢር እንደጠቆመን፥ የተወሰኑ ወገኖች "ከዕፀ መስቀሉ [ጌታን] የወለደችው ማርያም ትበልጣለች" ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ "በሕማሙ ደም የተጠመቀው መስቀል ይበልጣል"[393] በማለት ይከራከሩ ስለነበር ለዚህ መልስ ለመስጠት ይመስላል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ክርክሩ ያስደሰተው አይመስልም፤ ቀጥተኛ መልስ ሳይሰጥ "ወቦ ዘሮጸ ዜና ውስተ እዘኒነ" (በጆሮአችን የተሰማ ዜና አለ) ሲል የገለጸውን ጉዳይ በአጭሩ ይዘጋዋል፡- "ንሕነሰ ንብል ነአምን በማርያ[ም] ከመ ወላዲተ እግዚአብሔር ይእቲ፤ ወነአምን በመስቀሉ ከመ ማዕተበ ብርሃን ውእቱ ዘተቀደሰ በደመ ትስብእተ መለኮቱ" [394] (እኛ ግን ማርያም እግዚአብሔርን እንደወለደች እናምናለን እንላለን፤ መለኮት [በተዋሐደው] በሥጋ ደም በተቀደሰውና የብርሃን ምልክት በሆነው በመስቀሉም እናምናለን)፡፡

---

[390] "መስተብቍዕ ማርያም"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 1994፣ ገጽ 434፡፡

[391] ጌታቸው ኃይሌ፥ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ፡* ገጽ 39፡፡

[392] ዝኒ ከማሁ፡፡

[393] "ምንባብ ዘስብከተ ጌና" *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, p. 8.

[394] ዝኒ ከማሁ፡፡

## በእንተ አክብሮ ሰንበታት

በአቡነ ኤዎስጣቴዎስ (1265-1344 ዓ.ም.) የተመራውና "ሁለቱን ሰንበታት (ሰንበተ አይሁድንና ሰንበተ ክርስቲያንን) እኩል ማክበር ይገባል" የሚለው እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለሁለት ለመክፈል የደረሰ ነበር፡፡ በቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት፥ በመጽሐፈ ሲኖዶስ 66ኛው ትእዛዝ እና በመጽሐፈ ዲድስቅልያ 38ኛው ምዕራፍ የሁለቱ ሰንበታት ክብር በሰፊው ስለተጻፈ፥ በአዋጅ ባይጸድቅም፥ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለቱንም ሰንበታት የማክበር የቆየ ባህል እንደነበር ይታወቃል፡፡ እ.አ.አ. በ1238 የተሰበሰቡት የኢብን አል-አሳል ቀኖናዎች፥ ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር አይሁዳዊ ባህል ስለሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለውና[395] ክርስቲያኖች ሊያከብሩት የሚገባው "የጌታ ቀን" (ራእ. 1፥10) የተባለውንና ጌታ ሞትን ድል አድርጎ የተነሳበትን ቀን (ዕለተ እሑድ) ብቻ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ቀኖናዊ ውሳኔ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የግብፅ ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያናቸውን አቋም ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈጸም ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት አለመግባባት ሲፈጠር፥ በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት (1263-1277 ዓ.ም.) ሕይወት ብነ በጽዮን የተባለ ካህን፥ ነባሩ ባህል ተጠብቆ፥ የአይሁድ ሰንበት (ቅዳሜ) እና ሰንበተ ክርስቲያን (እሑድ) በእኩል ደረጃ የዕረፍት ቀናት ሆነው መከበር እንዳለባቸው መሟገት ጀመረ፡፡[396] አባ ዳንኤል ዘገረዓልታ የሕይወት ብነ በጽዮንን አስተምህሮ ለማራመድ የሞከሩ ሲሆን፥ ከአጎታቸው አባ ዳንኤል ዘገረዓልታ እጅ ምንኵስናን የተቀበሉት አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፥ ሁለቱም ሰንበታት እኩል ይከበሩ የሚለው ትምህርት ወራሽ ሆኑ፡፡[397]

አባ ኤዎስጣቴዎስ (ማዕቀበ እግዚእ) ገረዓልታን ለቅቀው ሰራዬ በምትባል ቦታ የራሳቸውን ማኅበር መሠረቱ፤ ደቀ መዛሙርትንም አፈሩ፡፡ ሰንበተ አይሁድ የክርስቲያኖች ሰንበት ከሆነችው ዕለተ እሑድ ጋር እኩል መከበር እንዳለባት

---

[395] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia,* p. 209.
[396] Zemene Abuhay, *Brief Introduction to the History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church* (San Jose, CA: Mekane Rama Qidus Gabriel Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, 2005) p. 92.
[397] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia,* p. 206.

በአጽንዖት ያስተምሩ ነበር፡፡ ይህን አቋማቸውን ለአፄ አምደ ጽዮን (1306-1336 ዓ.ም.) ለማስረዳት ወደ ንጉሡ ሲሄዱ በቅርቡ (1330 ዓ.ም. አካባቢ) ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን ግብፃዊ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብን አግኝተው በዚህ ጉዳይ ያላቸውን አቋም ጠየቋቸው፡፡[398] ከላይ እንደተገለጸው የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት፥ ክርስቲያኖች ሊያከብሩት የሚገባቸው እሑድን ብቻ ነው የሚል ስለሆነ ግብፃዊው ጳጳስ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስን ትምህርት ሊደግፉ የሚችሉበት ምክንያት አልነበረም፡፡ ንጉሡም በይፋ ይደግፍ የነበረው "ልትከበር የሚገባት የክርስቲያኖች ሰንበት (እሑድ) ብቻ ናት" የሚለውን አቋም ነበር፡፡[399] ስለሆነም አባ ኤዎስጣቴዎስ የመሠረቱትን ማኅበር ለአባ አብሳዲ አደራ ሰጥተው አቤቱታቸውን ለፓትርያርክ ብንያሚን (እ.አ.አ. 1327-1339) ለማቅረብ ወደ ግብፅ ሄዱ፡፡[400]

አባ ኤዎስጣቴዎስን አገር ለቅቆ እስከመሄድ ድረስ ያደረሳቸው ጉዳይ ፓትርያርኩን ቢያሳዝናቸውም "ከወገኖችህ ጋር ተስማማ" ከማለት በስተቀር ምንም ዓይነት መፍትሔ ሊሰጧቸው አልቻሉም፡፡[401] አባ ኤዎስጣቴዎስ በአስቄጥስ ገዳም የተወሰኑ ዓመታትን አሳለፉ፡፡ በዚህም ገዳም የሐዋርያት ቀኖና ይከበር በማለቱ ተሰድዶ የነበረውን የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ ያዕቆብ ዳግማዊን አገኙ፡፡ [402] እርሳቸውም ከአገራቸው የተሰደዱት በመጽሐፈ ሲኖዶስ እንደተገለጸው ሰንበተ አይሁድ ከዕለተ እሑድ ጋር እኩል ትከበር በማለታቸው ስለሆነ ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ከመንበሩ የተሰደደው አርመናዊ ፓትርያርክ የመጽናኛቸው ምክንያት ሆነ፡፡ በ1343 እ.አ.አ. ከደቀ መዛሙርቶቻቸው (በኪሞስ፡ ገብረ ኢየሱስና መርቆሬዎስ ጋር) ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ቤተልሔምን፥ ናዝሬትንና ጎልጎታን ከጎበኙ በኋላ ዐጽፋቸውን [403] እንደ መርከብ በመጠቀም ከደቀ መዛሙርቶቻቸው በኪሞስና ቆዝሞስ ጋር የሜዲትራኒያንን ባሕር አቋርጠው ወደ ደሴተ ቆጵሮስ ተጓዙ፡፡ ከዚያም

---

[398] ዝኒ ከማሁ ፥ ገጽ 207፡፡

[399] Getatchew Haile, "Ethiopian Heresies and Theological Controversies," *The Coptic Encyclopedia,* Vol. 3, ed. Aziz S. Atiya (New York: Macmillan Publishing Company, 1991) p. 985.

[400] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia,* p. 208.

[401] Gianfranco Fiaccadori, "Ewosṭatewos," *EA,* Vol. II, p. 470.

[402] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 471፡፡

[403] ከላይ የሚደረብ ልብስ ፥ መጎናጸፊያ፡፡

የአፄ አምደ ጽዮን ዜና ዕረፍት በተሰማበት ዓመት (1336 ዓ.ም.) አርማንያ ደረሱ፡፡ [404] በአስቄጥስ ገዳም ያገኙት የአርመን ፓትርያርክ አቋማቸውን ስለተረዳላቸው የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትደግፋቸው ቢመስላቸውም በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሮማ ካቶሊክን ትምህርት በመቀበል ጉዳይ ለሁለት ጎራዎች ተከፍላ ስለነበር የአባ ኤዎስጣቴዎስን ጉዳይ ቦታ የሰጠው አልነበረም፡፡ ሆኖም በዚያው በምድረ አርማንያ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ዕረፍት ሲሰማ ቅድስናቸው በአርመናውያንም ዘንድ የታወቀ ስለነበር በአርመኑ ፓትርያርክ መሪነት ጸሎተ ፍትሐት ተፈጽሞላቸው ቅዱስ ቤህናም የተባለው የአርመን ቤተ ክርስቲያን ሰማዕት መቃብር አጠገብ ተቀብረዋል፡፡[405]

በአባ አብሳዲ መሪነት ኢትዮጵያ ውስጥ "ሁለቱም ሰንበታት ይከበሩ" የሚለውን አስተምህሮ ያንጸባርቁ የነበሩት የአባ ኤዎስጣቴዎስ ተከታዮች ከማኅበረ ምእመናን የመገለል ፈተና ገጥሞአቸው ነበር፡፡ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ኢትዮጵያ በነበሩበት ጊዜ ከአባ አኖሬዎስ ዘሸዋ ጋር በሰንበት ጉዳይ ከፍተኛ ሙግት በገጠሙበት ጊዜ ይህን የሰማው አፄ አምደ ጽዮን "በሃይማኖታዊ ሙግታችሁ መንግሥቴን ልትከፍሉ ነውን?" በሚል አባ አኖሬዎስን አስገርፏቸው እንደነበር ተዘግቧል፡፡[406] እየቆየ ግን የንጉሡ ጥርጣሬ እውን ሆነ፤ በሰንበት አከባበር የተነሣው አለመግባባት አገሪቱንና ቤተ ክርስቲያኒቷን ለሁለት የመከፈል ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ የአባ ኤዎስጣቴዎስ የመንፈስ ልጆች፥ ግብፃውያን ጳጳሳት ቀዳሚት ሰንበትን ስለማያከብሩ በእነርሱ እጅ ክህነት አንቀበልም ማለት ጀመሩ፡፡[407] ኢትዮጵያ ውስጥ እ.አ.አ. ከ1399-1436 የኖሩት ግብፃዊው ጳጳስ አባ በርተሎሜዎስ ጉዳዩ አሳስቧቸው ለማግባባተ ቢሞክሩም አልተሳ ካላቸውም፡፡ እርሳቸውን ተክተው ወደ ኢትዮጵያ በመጡት አባ ገብርኤልና አባ ሚካኤል ዘመነ ጵጵስና ግን አፄ ዘርአ ያዕቆብ ጉዳዩን በጥበብ ስለያዘው ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመከፈል ያንዣብብ የነበረው አደጋ ተወገደ፡፡ በኢየሩሳሌም ለነበሩት የኢትዮጵያ መነኰሳት፡- "ስለቀዳሚት ሰንበትና ስለሰንበተ ክርስቲያን ከእርሱ አንብባችሁ ትረዱ ዘንድ ይህን መጽሐፈ ሲኖዶስ

[404] Gianfranco Fiaccadori, "Ewosṭatewos," *EA,* Vol. II, p. 471.
[405] ዝኒ ከማሁ፡፡
[406] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia,* p. 208.
[407] ዝኒ ከማሁ ፥ ገጽ 211፡፡

ልኬላችኋለሁ''[408] ሲል አስቀድሞ የማግባባት ሥራ ከሠራ በኋላ፥ በ1443 ዓ.ም. ሸዋ ውስጥ ባሠራው ደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱ ግብፃውያን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ጉባኤ አደረገ፡፡ የጉባኤው ዓላማ ከደቂቀ ኤዎስጣቴዎስ ጋር እርቅ መፈጸም ስለነበር አፄ ዘርአ ያዕቆብ የሠራውን የማግባባት ሥራ የተረዱ ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት ሁለቱም ሰንበታት (ቅዳሜና እሑድ) ኢትዮጵያ ውስጥ እኩል እንዲከበሩ አወጁ፤ ደቂቀ ኤዎስጣቴ ዎስም ከሊቃነ ጳጳሳቱ እጅ ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኑ፡፡[409]

የአባ ኤዎስጣቴዎስና የልጆቻቸው አስተምህሮ በዚህ መልኩ ተቀባይነትን አግኝቶ ቢቋጭም እንቅስቃሴው የቤተ ክርስቲያኒቱን የቀድሞ አቋም የሚያንጸባርቅ አኰቴተ ቊርባን አበርክቶልናል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተማረበት የደብረ ሐይቅ ገዳም እስከ 1396 ዓ.ም. ድረስ የአይሁድ ቀዳሚት ሰንበት፥ ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሣባት ዕለተ እሑድ ልትከበር አይገባትም የሚለውን የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተቀበሉ ወገኖች ዋነኛ ማዕከል ነበር፡፡[410] ስለሆነም፡ "ንዑ ናዕብያ፥ ንዑ ንወድሳ፥ ንዑ ናክብራ፥ ንዑ ናብዕላ ለበኲረ በዓላት እንተ ይእቲ ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት''[411] (የበዓላትን በኲር ኑ ከፍ ከፍ እናድርጋት፥ ኑ እናክብራት፥ ኑ በዓል እናድርግላት፤ ይህችውም ቅድስት ሰንበተ ክርስቲያን ናት)[412] የሚልና የኦሪትን ሥርዓት መተው እንዳለብን[413] በግልፅ የሚያስረዳው፥ በቅዱስ አትናቴዎስ ስም የተሰየመው አኰቴተ ቊርባን የሰንበተ ክርስቲያን መከበርን ብቻ በሚደግፉ ወገኖች

---

[408] ዝኒ ከማሁ ፥ ገጽ 229፡፡

[409] ዝኒ ከማሁ ፥ ገጽ 230፡፡

[410] ዝኒ ከማሁ ፥ ገጽ 224፡፡

[411] "ቅዳሴ አትናቴዎስ"፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ* (1994፣) ገጽ 223፣ ቍ. 55፡፡

[412] በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጥናት ያደረገው ጀርመናዊ ምሁር Ernst Hammerschmidt በቅዳሴ አትናቴዎስ ውስጥ ለክርስቲያኖች ሰንበት የተሰጠውን ከፍተኛ ክብር ሰንበተ-አይሁድን የእስራኤል ሙሽሪት አድርጎ ከሚያሞግሳት የSolomon Ben Moses Halevi Alkabez ጋር በማነጻጸር የቅዳሴ አትናቴዎስ ደራሲ፥ መነሻ የሚሆነውን አሳብ ከኢትዮጵያውያን አይሁድ (ፈላሾች) የአምልኮ መጻሕፍት ወስዶ ሊሆን ይችላል የሚል አመለካከት አቅርቧል፡፡ Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras,* p. 81-82.

[413] "ወንጌልን በእውነት እንያዝ፥ በውስጡ ትሕትናና ፍቅር ያለበትን፡፡ ኦሪትን ግን እንተው፥ በውስጡ ስለ ነፍስ የነፍስ ቤዛ የሚሆን የሞት ፍርድ ያለበትን፡፡ "ቅዳሴ አትናቴዎስ"፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ* (1994፣) ገጽ 224፣ ቍ. 58፡፡

እንደተደረሰ መገመት አያዳግትም፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በአባ ጊዮርጊስ መጻሕፍት ውስጥ የሚታየው የአጻጻፍ ዘዴ (የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር በጀመረበት ሐረግ ተከታታይ መሥመሮችን መቀጠል) በቅዳሴ አትናቴዎስም ውስጥ ስለሚታይ[414] የዚህ ቅዳሴ ደራሲ ከታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሌላ ሊሆን እንደማይችል አስረድተዋል፡፡ [415] ወደፊት እንደምንመለከተው በ14ኛውና 15ኛው ምእት ዓመታት የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ቅዳሴያት እየደረሱ በታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች (ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ወዘተ.) ስም የሰየሙት ቅዳሴያቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነት እንዲያገኙ ሲሆን፥ የሰንበተ ክርስቲያንን ክብር አምልቶና አስፍቶ ለሚናገረው አኰቴተ ቍርባን ስያሜ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ “ጦማር ዘወረደት እምሰማያት ላዕለ እደ አትናቴዎስ በዕለተ እሑድ”[416] የሚለው ድርሳን ኢትዮጵያ ውስጥ ይታወቅ ስለነበር ነው፡፡

አባ ጊዮርጊስ በደረሰው መጽሐፈ ምሥጢር ውስጥ የአይሁድ ሰንበት እንዳል ተሻረችና በሰንበተ ክርስቲያን እንደከበረች የሚያትቱ ገለጻዎች ስላሉ ከላይ የተጠቀሰውን አሳብ የሚሞግቱ ጥያቄዎች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ ለምሳሌ “ምንባብ ዘስብከተ ጌና” የሚል ርእስ የተሰጠው የመጽሐፈ ምሥጢር ምዕራፍ ውስጥ የሚከተለውን ንባብ እናገኛለን፡-

> ወቦ እለ ይቤሉ ከመ ተፀርዓት ኦሪት በምጽአተ ወንጌል፥ ወበጠለ ትንቢተ ነቢያት በስብከተ ሐዋርያት፥ ወተሥዕረት ሰንበት [በእሑደ ትንሣኤ]፡፡ ንሕነሰ ንብል ከብረት ኦሪት በስብከተ ወንጌል፥ ተለዐሉ ነቢያት በትምህርተ ሐዋርያት፥ ተከለለት ሰንበተ አዕርፎ ዘእምፍጥረተ ዓለም በሰንበተ ትንሣኤ ዘመድኅነ ዓለም፡፡[417]

---

[414] ለምሳሌ፡- “ወኢመኑሂ ኢየሀሉ” በሚለው ሐረግ የሚጀምሩና ይህንኑ ሐረግ የሚደጋግሙ ዓረፍተ ነገሮችን (“ቅዳሴ አትናቴዎስ”፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ ገጽ 215፣ ቍ. 5-7)፤ “ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ” በሚለው ሐረግ የሚጀምሩትንና በተመሳሳይ መልኩ የጀመሩበትን ሐረግ የሚደጋግሙትንም (“ቅዳሴ አትናቴዎስ”፥ *መጽሐፍ ቅዳሴ*፥ ገጽ 217፣ ቍ. 20-22) ላይ ይመልከቱ፡፡

[415] Getatchew Haile, “On the Authorship of Ethiopian Anaphoras,” *Ethiopian Studies in Honour of Amha Asfaw* (New York, 2017) pp. 20-23.

[416] Getatchew Haile, “Religious Controversies,” p. 131.

[417] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, p. 7-8.

የዚህም የአማርኛ ትርጉም የሚከተለው ነው፦

> ኦሪት በወንጌል መምጣት እንደ ተተወች፥ የነቢያት ትንቢት በሐዋርያት ስብከት እንደጠፋ፥ [የአይሁድ] ሰንበት ደግሞ [ጌታ በተነሣባት] እሑድ እንደተሻረች የሚናገሩ አሉ፡፡ እኛ ግን ኦሪት በወንጌል ስብከት ከበረች፥ ነቢያት በሐዋርያት ትምህርት ከፍ ከፍ አሉ፥ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ የነበረችው ሰንበት፥ የዓለም መድኅን በተነሣባት ሰንበት ከበረች እንላለን፡፡[418]

ነገር ግን ታላቁ የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት በመጽሐፋቸው እንዳስረዱን፥ እስከ 1396 ዓ.ም. ድረስ አባ ጊዮርጊስ የተማረበት ደብረ ሐይቅ ጻረ ሰንበተ አይሁድ አቋም ስለነበረው፥ አባ ጊዮርጊስም የተማረበትን ገዳም አስተምህሮ ይደግፍ ነበር፡፡ ሆኖም በገዳሙ የአስተምህሮ ለውጥ ከተደረገበት ከ1396 ዓ.ም. ጀምሮ አባ ጊዮርጊስ እስካረፈበት 1417 ዓ.ም. ድረስ የነበሩትን 20 ዓመታት አባ ጊዮርጊስ ያሳለፈው የአይሁድ ቀዳሚት ሰንበት መከበር አለባት የሚለውን አመለካከት በማስተጋባት ነበር፡፡[419] ስለዚህ ቅዳሴ አትናቴዎስን የደረሰው ሰንበተ ክርስቲያን ብቻ ትከበር የሚለውን (የተማረበት ገዳም አስተምህሮን) በተቀበለበት ጊዜ ሲሆን፥ መጽሐፈ ምሥጢርን የጻፈው ደግሞ የቀዳሚት ሰንበትን ክብር አስመልክቶ የአቋም ለውጥ ካደረገ በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡

## በእንተ ምሳሐ ደብረ ጽዮን

የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት በ15ኛው ምእት ዓመት ሊቃውንቱን ያከራከሩ ከነበሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጉዳዮች አንዱ በራእይ 20፡4 ላይ የተጠቀሰው ለአውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱ ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት የሺህ ዓመት ንግሥና[420] ነው፡፡ አባ ጊዮርጊስና አፄ ዘርአ ያዕቆብ የዚህ አስተምህሮ ደጋፊዎች ነበሩ፡፡ አባ ጊዮርጊስ "መንግሥተ ደብረ ጽዮን" ወይም "ምሳሐ ደብረ ጽዮን"[421] በማለት ሲጠራው፥ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ደግሞ "መንግሥተ ቅዱሳን" ወይም

---

[418] ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ፡፡

[419] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia,* p. 208.

[420] Millenarianism.

[421] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, p. 203.

“መርዓ ቅዱሳን”[422] የሚሉ ስያሜዎችን ሰጥቶታል፡፡ የሺህ ዓመት ንግሥናው የሐሳዊ መሢሕን መምጣት ተከትሎ የሚከናወን ሲሆን የንግሥናው ዋነኛ መገለጫ በደብረ ጽዮን ተራራ ላይ ለተመረጡት የሚደረገው የምሳ ግብዣ (ምሳሐ ደብረ ጽዮን) ነው፡፡[423] ቅዱስ ሄሬኔዎስ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ እግዚአብሔር ዓለማትን ፈጥሮ ባረፈባት በሰባተኛዋ ቀን (በሰንበት) በመንግሥቱ ለጻድቃኑ (ለእውነተኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች) ማዕድ እንደሚያዘጋጅላቸው ጽፏል፡፡[424] በትንቢተ ኢሳይያስ 25፥ 6 ላይ፡- “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ በዚህ [በጽዮን]ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ፥ ያረጀ የወይን ጠጅ፥ ቅልጥም የሞላባቸው የሰቡ ነገሮች፥ የጥሩና ያረጀ የወይን ጠጅ ግብዣ ያደርጋል” የሚለው አገላለጽ ምሳሐ ደብረ ጽዮን የሚለውን አስተምህሮ የሚደግፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የምሳ ግብዣው የሚዘጋጀው “በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ” (1 ተሰ. 4፥16) ለተባለላቸው ቅዱሳን ሲሆን፥ ለምሳው ብቁ ያልሆኑ ኃጥአን ግን ግብዣው በሚካሄድባቸው አንድ ሺህ ዓመታት ያህል ከሞት

[422] *Das Maṣḥafa Milad (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis)* ed. Kurt Wendt, CSCO*,* Scriptores Aethiopici, Vol. 235, Tom 43, (Louvain: 1963) pp. 32 and 35.

[423] አፄ ዘርአ ያዕቆብ የሺህ ዓመት የምሳ ግብዣው የሚከናወንበትን ቦታ አስመልክቶ ከአባ ጊዮርጊስ የተለየ አሳብ አለው፡፡ አባ ጊዮርጊስ፥ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የሚገለጥበትም ሆነ የምሳ ግብዣ የሚያደርግበትን ቦታ “ደብረ ጽዮን፥ ደብረ ምርፋቆሙ ለቅዱሳን” ሲል ይጠራዋል - *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, ገጽ 203፡፡ እንደ ዘርአ ያዕቆብ አመለካከት ግን፥ የሺህ ዓመቱ የምሳ ግብዣው የሚካሄደው ለጊዜው ከሰው ልጆች አሁን በተሰወረችው ከተማ ውስጥ ነው፤ ይህን አሳብ ለመደገፍም አሁን ከምድር የተሰወረችው ከተማ ወደፊት የምትገለጥበት ጊዜ እንደሚመጣ የሚያስረዳ ጥቅስ ከመጽሐፈ ዕዝራ ካልእ 7፥ 26-28 ይጠቅሳል፡፡ ከተማዪቱ የተዘጋጀችው ከክርስቶስ ጋር ለሚነግሡት ቅዱሳን ነው፤ ዲያብሎስና ሠራዊቱ ሊቀርቧት አይችሉም፡፡ አሁን ያለንባት ምድር ስታልፍ፥ የተሰወረችው ከተማ ግን አታልፍም (በክብር ትገለጻለች)፡፡ *Das Maṣḥafa Milad (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis)* ed. Kurt Wendt, CSCO*,* Vol. 235, Tom 43, ገጽ 34-38 ይመልከቱ፡፡

[424] Irenaeus of Lyons, “Against Heresies, Book V, XXXIII” *The Ante-Nicene Fathers*: *Translations of the Writings of the Fathers Down to A.D. 325*, eds. Alexander Roberts and James Donaldson (Michigan: W.M.B. Eerdmans Publishing Company, 1993) p. 562.

አይነሡም፡፡[425] አባ ጊዮርጊስና አፄ ዘርአ ያዕቆብ በዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው የጻፉት እንደ ቅዱስ ሄሬኔዎስ ይህን አስተምህሮ የሚደግፉ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አበው መጻሕፍትን ስላነበቡ ሊሆን ይችላል፡፡[426]

በደብረ ጽዮን ተራራ ይከናወናል ተብሎ የሚገመተው የክርስቶስ (ከቅዱሳኑ ጋር) ሺህ ዓመት ንግሥና እና የምሳ ግብዣው ከዚህ ዓለም ፍጻሜ በኋላ ስለሆነ ይህን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበትንም ጊዜ መገመት ነበረባቸው፡፡ አይሁድ በሙሴ የመጀመሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን፥ ፍጥረት የተፈጠረባቸውን ሰባት ቀናት እያንዳንዳቸው የአንድ ሺህ ዓመታት ጊዜ እንደነበራቸው አድርገው ነው የሚረዱት፡፡ በመዝሙር 89(90)፥4፡- "ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፥ እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና" ተብሎ እንደተጻፈ፥ ይህ ዓለም የተፈጠረባቸው ሰባት ቀናት በውስጡ 7000 ዓመታትን የያዘ አንድ ሳምንት እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚታሰበው፡፡[427] ይህን አሳብ የሚጋሩ የ15ኛው ምእት ዓመት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የዓለሙ ፍጻሜ በእነርሱ ዘመን (በ8ኛው ሺህ መግቢያ ላይ) እንደሚሆን ገምተው ነበር፡፡ *መጽሐፈ ኪዳን ዘገሊላ* በሚል ስያሜ የሚታወቀውና ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ስለዳግም ምጽአቱ ያስተማራቸውን ትምህርት ይዟል ተብሎ በሚታመንበት መጽሐፍ ውስጥ ጌታችን ከ150 ዓመታት በኋላ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደሚመጣ እንደነገራቸው ተዘግቧል፡፡[428] እነዚህ 150 ዓመታት 1500 ዓመታት ተደርገው ስለታሰቡ፥ ዓለም ከተፈጠረበት እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ያሉትን 5500 ዓመታት ስንደምር 7000

---

425 *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, p. 203.

426 በተለይ ለአፄ ዘርአ ያዕቆብ ይህ አስተምህሮ የተለየ ትርጉም ነበረው፤ ምክንያቱም እርሱ ራሱ የሚያውቀው ትውፊት ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ንጉሥ የሰማያዊው ንጉሥ (የክርስቶስ) እንደራሴ አድርጎ ይቀበል ነበር - Gianfrancesco Lusini, "Eschatology," *EA,* Vol. 2 (2003) p. 380፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ከቅዱሳኑ ጋር ለሺህ ዓመት ይነግሣል፥ የምሳ ግብዣም ያደርጋል የሚለው አመለካከት፥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ራሱን በቀጥታ የሚመለከተው አድርጎ እንዲጽፍ ግድ ብሎታል፡፡

427 Willy Rordorf, "Sunday: The Fullness of Christian Liturgical Time," *Studia Liturgica,* 14/1 (1980/1981) 91.

428 L Guerrier and S. Grébaut (trans.), "Le Testament en Galilée de Notre-Seigneur Jésus Christ," *Patrologia Orientalis,* 9 (Paris: Firmin-Didot, 1913) p. 199.

ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህ ዓለም ከተፈጠረ ከ7000 ዓመታት በኋላ ወይም የ8ኛው ሺህ መጀመሪያ ላይ ያልፋል የሚል ግምት ነበር፡፡ የዓለሙ ፍጻሜ ይሆናል ተብሎ የተገመተበት ዓመት (7000 ዓመተ ዓለም ወይም 7000-5500 = 1500 ዓ.ም.) ስለሆነ፥ ከዘመናቸው አንጻር አባ ጊዮርጊስ (+1417 ዓ.ም.) እና አፄ ዘርአ ያዕቆብ (+1460 ዓ.ም.) የእነርሱ ትውልድ የዓለምን ፍጻሜ እንደሚያይ እያሰቡ የጻፉ ይመስላል፡፡

ነገር ግን በ15ኛው ምእት ዓመት ይህ አስተምህሮ ያለምንም ተቃውሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ትምህርቱን የማይቀበሉ ሰዎች እንደነበሩ የሚጠቁም ጥቅስ ለበዓለ ደብረ ዘይት እንዲነበብ የተዘጋጀው የመጽሐፈ ምሥጢር ክፍል ውስጥ እናገኛለን፡- “ለእለሰ ይብሉ አልቦ ምሳሐ ደብረ ጽዮን መሐልኩ እዴሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከመ አልቦሙ መክፈልተ እምሳሕ ዘ፲፻ ዓመት፤ በከመ ይቤ በመዝሙር ዘአበያ ለበረከት ትርሕቅ እምኔሁ”[429] (“የደብረ ጽዮን ምሳ የለም” ስለሚሉት፥ በመዝሙር “በረከትን እምቢ ያላት ከእርሱ ትርቃለች” [መዝ. 108(109)፥17] እንዳለ በአንድ ሺህ ዓመቱ ምሳ ተሳትፎ እንደሌላቸው የኢየሱስ ክርስቶስን እጅ [መትቼ] ምያለሁ)፡፡ ደቂቀ እስጢፋኖስም “ክርስቶስ በዚህ ምድር ለሺህ ዓመት ከቅዱሳኑ ጋር ይነግሣል፥ በደብረ ጽዮን ተራራም የምሳ ግብዣ ያደርጋል” የሚለውን አስተምህሮ በመቃወም ለቅዱሳን የሚደረግ የምሳ ግብዣ[430] ካለም አሁን ባለንበት በዘመነ ድኅነት ለሚያምኑ ሁሉ የሚታደል ነው (በክርስቶስ ያመኑ እውነተኞች የሚያገኙት ጸጋ ነው) የሚል አመለካከት ነበራቸው፡፡[431] በተለይ ዘሚካኤላውያን በሚል የጋራ ስም ይጠሩ የነበሩ ወገኖች፥ አሳማኝ የሆነና ቤተ ክርስቲያናችን በኋላ የተቀበለችውን አሳብ ጠቅሰው የሺህ ዓመቱን ንግሥና እና የደብረ ጽዮንን ማዕድ ይቃወሙ ነበር፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብ በመጽሐፉ እንደነገረን የዘሚካኤላውያኑ አስተምህሮ ይህ ነበር፡- “አሁን ካለንበት ከዘመነ ሥጋዌ በስተቀር

[429] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO*,* Vol. 515, Tom. 89, p. 203-204.
[430] Banquet.
[431] Getatchew Haile, “The Cause of the Ǝsṭifanosites: A Fundamental Sect in the Church of Ethiopia,” *Paideuma,* 29 (1983) p. 109.

የቅዱሳን የሺህ ዓመት ንግሥና የለም፤ ማዕዱም የክርስቶስ *ሥጋና ደም* ነው"፡፡[432] እንዲሁም፥ ደብረ ጽዮን ተብላ ልትጠራ የሚገባት የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ (*ሥጋሁ ወደሙ*) የሚሠዋባት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡[433]

የዮሐንስ ራእይ 20፡4-6 ላይ የተጠቀሰውን የሺህ ዓመት ንግሥና አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜ ከላይ ከተጠቀሰው የዘሚካኤላውያን አሳብ ጋር አንድ ዓይነት ቢሆንም "ምሳሐ ደብረ ጽዮን" የሚለውን የ15ኛው ምእት ዓመት አስተም-ህሮ የሚያንጸባርቁ ምንባባትን በሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ውስጥ እናገኛለን፡፡ የታተመው መጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የተአምረ ኢየሱስ መርገፍ ሆነው ከሚዜሙት ዝማሬያት መካከል አንዱ እንዲህ ይላል፡-

> *ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአጽልዕቲሁ ምስሌሁ፤ ወመስቀለ ሞቱ ቅድሜሁ፡፡*
> *ዐዘቅተ ወይን ገቦሁ፤ ቊርባነ አምልኮ ሥጋሁ፡፡*
> *ያብአነ ቤተ መርዓሁ ውስተ ደብተራሁ፡፡*
> *አመ ይትጋብኡ ለምሳሕ ሥርግዋን ሐራሁ፡፡*[434]

ይህ ወደ አማርኛ ሲመለስ፡- "ኢየሱስ ክርስቶስ ቁስሎቹ ከእርሱ ጋር፥ የሞቱ መስቀል በፊቱ ነው፤ ጎኑ የወይን ጉድጓድ፥ *ሥጋው* የአምልኮ ቊርባን ነው፡፡ ያጌጡ ጭፍሮቹ ለምሳ በሚሰባሰቡበት ጊዜ ወደ ሠርጉ ቤት ድንኳን ያስገባን" የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህ ንባብ እንደሚያመለክተው፥ "ያጌጡ ጭፍሮች" የተባሉት ለሰማያዊው ሠርግ የታደሙ ቅዱሳን ሲሆኑ፥ የሠርጉ ማዕድም "ምሳሐ ደብረ ጽዮን" እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከዚሁ ከመጽሐፈ ሰዓታት ሳንወጣ ባለራእዩና ወንጌላዊው ዮሐንስ፡- "በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር" (ራእ. 14፥1) ሲል የገለጸው የእግዚአብሔር በግ ከሰማያዊ ሠርጉ እንዳይለየን የሚማፀን ጸሎት እናገኛለን፡- "አ በግዕ ዘአርያም በርእሰ ደብረ ጽዮን ዘቆምከ ኢትፍልጠነ እምከብካበ ቅዱስ መርዓከ፡፡"[435]

[432] *Das Maṣḥafa Milad (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis),* ed. Kurt Wendt, CSCO*,* Vol. 235, Tom 43, p. 40.

[433] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 43፡፡

[434] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግሁ፥* ገጽ 240፡፡

[435] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 134፡፡

የመዝሙሩ ደራሲ[436] ሰማያዊውን ሠርግ በደብረ ጽዮን ከቆመው በግ ጋር ማገናኘቱ "ምሳሐ ደብረ ጽዮንን" እያሰበ እንደጻፈው ሊያመለክት ይችላል፡፡ በዚሁ መንፈስ የተጻፈ ተጨማሪ ንባብ ቅዳሴ ማርያም ውስጥም ይገኛል፡- "እናንት የክርስቲያን ወገኖች ሆይ፥ በዚህች ቀን እንደተሰበሰባችሁ እንደዚሁ ክብርት በምትሆን በደብረ ጽዮን … ይሰብስባችሁ"፡፡[437] ተስፋ ገብረ ሥላሴ በ1984 ዓ.ም. ባሳተመው ተአምረ ማርያም ውስጥም 29ኛው ተአምር "በእንተ እለ ያሰትቱ ደብረ ጽዮን" (ደብረ ጽዮንን ስለሚንቁ/ ስለሚያቃልሉ [ሰዎች] የሚል ርእስ ተሰጥቶታል፡፡[438]

እንደተጠበቀው በ8ኛው ሺህ መግቢያ ላይ (1500 ዓ.ም.) የዚህ ዓለም ፍጻሜ ስላልሆነ፥ በተጠቀሰው ጊዜ በደብረ ጽዮን ተራራ የሺህ ዓመት ንግሥና እና ማዕድ እንደሚከናወን ይሰጥ የነበረው ትምህርት እየቀረ መጣ፡፡ ስለሆነም የቤተ ክርስቲ ያናችን መተርጒማን አባቶች በራእይ 20፥4-6 የተጠቀሰውን የሺህ ዓመት ንግሥና ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ አሁን ያለንበት ጊዜን (ዘመነ ሥጋዌ) ያመለክታል ብለው ይተረጒሙታል፡፡ [439] "ሺህ ዓመት" የሚለው በቍጥር የተወሰነ ጊዜን ስለማያመለክት ከክርስቶስ ቀዳማዊ ምጽአት እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ያለውን ጊዜ ለመግለጽ የገባ ቃል ነው፡፡[440] የቀደመው እባብ (ዲያብሎስ) ሰንሰለት በያዘ መልአክ መታሰሩም (ራእ. 20፥ 1-2) በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ በሰው ዘር ጠላት ዲያብሎስ፥ በሞትና በኃጢአት ላይ ያገኘነውን ድል

[436] ይህ ዝማሬ መጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ ቢገባም የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት ግን አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው "ሰዓታት ዘመዓልት ወዘነግህ" በሚል ርእስ የታተመው መጽሐፍ፥ አባ ጊዮርጊስ "መጽሐፈ ብርሃን" ብሎ ከሰየመው የ24 ሰዓታት አገልግሎት (መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት) ከእኩለ ሌሊት እስከ ሊሌቱ 10፡00 ድረስ ያለውን ክፍል ብቻ የያዘ ነው፡፡ በታተመው መጽሐፍ የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት ያልሆኑ የተለያዩ ዝማሬያት ተጨማረዋል፤ ከእነዚህ ዝማሬያት መካከል ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የሚገኝበትና "ተዘከር ካዕበ አግብርቲከ ወአእማቲከ" በማለት የሚጀምረው አንዱ ነው፡፡

[437] "ኅዳፄ ነፍስ ዘቅዳሴ ማርያም"፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 1994፣ ገጽ 186፣ ቍ. 156፡፡

[438] *ተአምረ ማርያም ግዕዝ እና አማርኛ* (አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1984 ዓ.ም.) ገጽ 132፡፡

[439] ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ፥ *መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ* (አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ 1951 ዓ.ም.) ገጽ 465፡፡

[440] ስቡሕ ዳምጤ፥ *ሺህ ዓመትና ሐሳዊ መሲሕ* (አዲስ አበባ፡ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት፡ 1997 ዓ.ም.) ገጽ 15፡፡

ያመለክታል፡፡[441] ሠራዒው ካህን በቅዳሴው የዝግጅት ክፍል በፃሕሉ ላይ የሚጸል የው ጸሎት፡- "በዕፀ መስቀል ላይ ቅዱሳት የሚሆኑ እጆችህን የዘረጋህ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፥ በጎ ነገርን በተመላች በዚች ፃሕል ላይ ክቡር እጅህን ዘርጋ፡፡ ቅዱስ ስምህን የሚወዱ ሰዎች የሺህ ዘመን ምግብን በላይዋ የሚያዘጋጁባት ናት"[442] ይላል፡፡ ነገር ግን "የሺህ ዘመን ምግብ" የተባለው ከሺህ ዓመት ንግሥና ጋር ይካሄዳል ተብሎ ይታሰብ የነበረው "ምሳሐ ደብረ ጽዮን" ሳይሆን ለአማንያን የሚሰጠው የጌታ ሥጋና ደም ነው፡፡ በዚህ ምድር የምንቀበለው ቅዱስ ቊርባን፥ የምትገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕድ መሆኑን ለማጠየቅ ሲሉ አበው "የሺህ ዘመን ምግብ" ብለውታል፡፡[443]

## አልቦቱ ለእግዚአብሔር መልክዐ ከመ መልክዐ ሰብእ

በ15ኛው ምእት ዓመት ለበርካታ አገር በቀል ቅዳሴያት መደረስ ምክንያት የሆኑ የትምህርተ ሃይማኖት ክርክሮች፡- "እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን፣ እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" (ዘፍ. 1፥26) እና "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም" (ዮሐ. 1፥18) በሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ እነዚህን ጥቅሶች በተለያየ መልኩ በመተርጐምና ሊስማሙ የማይችሉ አቋሞችን በማንጸባረቅ ይከራከሩ የነበሩት አፄ ዘርአ ያዕቆብና በመሪያቸው ዘሚካኤል "ዘሚካኤላውያን" ተብለው የተጠሩት ወገኖች ሲሆኑ፥ ሁለቱም ወገኖች ከእነርሱ በፊት የተነሡ ዝነኛ ደራስያንን ጽሑፎች ይጠቅሱ ነበር፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብ፥ ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ስለሆነ፥ እግዚአብሔር የሰውን መልክ የሚመስል (ዓይን፥ አፍንጫ፥ ጆሮ ወዘተ. ያለው) መልክ አለው ብሎ ያምን ነበር፡፡ ለዮሐንስ ወንጌላዊ ክብር በደረሰው ጦማር እንደገለጸው፡- "[እግዚአብሔር] አብ ከሰው መልክ የተለየ ሌላ መልክ የለውም[444]፥ ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ

[441] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 24፡፡

[442] "ጸሎት ላዕለ ፃሕል"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 1994፣ ገጽ 14፣ ቍ. 43፡፡

[443] *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው*፥ ገጽ 30፡፡

[444] በሰው ዓይን ሊታይ የማይችል መለኮታዊ አካል ያለውና መለኮታዊ ባሕርዩ በሰው ሕሊና ፈጽሞ ሊመረመር የማይችለው እግዚአብሔር፡ "የሰው ልጅን መልክ የመሰለ መልክ አለው" የሚለው አስተምህሮ anthropomorphism የተሰኘ የኑፋቄ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብና የእርሱ ጸሐፍያን የነበሩ

ፈጥሮታልና፡፡ የወልድም መልክ እንደ አባቱ መልክ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስም መልክ እንደ አብ እና ወልድ መልክ ነው፡፡"[445] ምንም እንኳ እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ባሕርዩ ያየው ማንም ባይኖርም፥ የሚታየውና የሚዳሰሰው የሰው ልጅ መልክ (አካል) የተፈጠረው በማይታየውና በማይዳሰሰው በእግዚአብሔር መልክ አምሳል ነው፡፡[446] አፄ ዘርአ ያዕቆብ በጦማሩ እንደነገረን የእርሱ አስተምህሮ ተቃዋሚዎች የነበሩት ዘሚካኤል፥ ገማልያል እና ዓጽቃ ከዚህ የተለየ አመለካከት ነበራቸው፡፡ በአጭሩ የተገለጸው ትምህርታቸው ወደ አማርኛ ሲተረጐም ይህን ይመስላል፡-

> እግዚአብሔር የሰውን መልክ የሚመስል መልክ የለውም፤ የሚታየውንና የሚዳሰሰውን የአዳምን የሥጋ መልክ (አካል) በአርአያውና በአምሳሉ አልፈጠረውም፡፡ የእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በአዳም ፊት ላይ እፍ የተባለውና የማይታየው መንፈስ ነው፡፡ ዮሐንስ በወንጌሉ፡- "እግዚአብሔርን ፈጽሞ ያየው ማንም የለም" እንዳለ፥ እግዚአብሔር አይታይም፤ ሰው የሚያውቀው መልክም የለውም፥ እርሱ ራሱ መልኩን ያውቃል [እንጂ]፤ ነፍስም ሰው ሊያውቀው የሚችለው መልክ (ቅርጽ) የላትም፤ የእግዚአብሔር አምሳል ናትና አትታይም፡፡[447]

አፄ ዘርአ ያዕቆብ የዘገበልን የዘሚካኤላውያኑ አቋም የሚያመለክተው በኦሪት ዘፍ. 1፥26 ላይ ያለውን ጥቅስ ቃል በቃል ወስደን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚመስል (የሚታይና የሚዳሰስ) መልክ (አካል) እንዳለው አድርገን ማሰብ እንደሌለብን ነው፡፡ አዳም በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ተፈጠረ የተባለው በነፍስ ባሕርይ (ሕያውነት፥ ነባቢነት/መናገር መቻል፥ ረቂቅነት/አለመታየት ወዘተ.) እግዚአብሔርን ስለሚመስለው እንጂ፥ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" (ዮሐ. 4፥24) ተብሎ የተነገረለት አምላክ እንደ ሰው የሚታይና የሚዳሰስ መልክ (አካል) ስላለው አይደለም፡፡

---

ካህናተ ደብተራ ይህን አስተምህሮ ያንጸባርቁ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡ Getatchew Haile, "Religious Controversies," ገጽ 108 ይመልከቱ፡፡

445 Getatchew Haile, trans. [from Ge'ez to English], "The Homily of Zär'a Ya'əqob in Honour of St. John the Evangelist," *OC,* 67 (1983) "ምንባብ [አመ ረቡዑ] ለጥር" ገጽ 152 (ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጕም የእኔ)፡፡

446 ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 154፡፡

447 ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 149 (ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጕም የእኔ)፡፡

አፄ ዘርአ ያዕቆብና ዘሚካኤላውያን የተከተሏቸው የተለያዩ ትምህርቶች ንጉሡ ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊት በጣም አወዛጋቢ ባልሆነ መልኩ ተገልጠው እንደነበር በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና በብዕር ስም ይጽፍ በነበረው በርቱዓ ሃይማኖት ሥራዎች ውስጥ እንመለከታለን፡፡ ስለዚህ ዘርአ ያዕቆብ የአባ ጊዮርጊስን አስተምህሮ ሲከተል፥ ዘሚካኤላውያን ደግሞ የርቱዓ ሃይማኖትን አሳብ ያንጸባርቁ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ "አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል (ገጽ) ናቸው" የሚለውን የሰባልዮስን ኑፋቄ ባወገዘበት የመጽሐፈ ምሥጢር ክፍል (ምንባብ ዘስብከተ ጌና) እግዚአብሔር "ሰውን በመልካችን፥ እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" አለ እንጂ "በመልኬ ወይም በአምሳሌ ልፍጠር" አለማለቱ እግዚአብሔር አንድ አካል (ገጽ) ብቻ አለመሆኑን እንደሚያመለክት ይገልጽና "የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያ (መልክ) እንደተሣለ እወቅ"[448] ይላል፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር በሦስት ሰዎች አምሳል ለአብርሃም እንደተገለጸለት (ዘፍ. 18፥ 1-5)፥ ያዕቆብም "እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ" ብሎ መናገሩን (ዘፍ. 32፥30)፥ ዳዊትም፡- "አቤቱ ፊትህን እሻለሁ… ፊትህን ከእኔ አትሰውር" (መዝ. 26/27፥8)፥ "እግዚአብሔር ጌታዬን… በቀኜ ተቀመጥ አለው" (መዝ. 109/110፥1) ብሎ መዘመሩን ከቅዱሳት መጻሕፍት ይጠቅስና የመጻሕፍቱ ምስክርነት እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ የሰው ልጅ መልክ (እንደ ሰው ልጅ ፍጹም መልክ) እንዳለው ያስረዳል በማለት ይጽፋል፡፡[449] በተጨማሪም ከኢሳይያስ ትንቢት፡- "እጄም ምድርን መሠርታለች፥ ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች" (ት. ኢሳ. 48፥13) የሚለውን ይጠቅስና፥ "እመኑኬ ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር አእዳው፥ ወመዝራዕተ፥ [ወአጻብዕ]"[450] (እንግዲህ እግዚአብሔር እጆች፥ ክንድና ጣቶች እንዳሉት እመኑ) ይላል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰበት ዋነኛ ምክንያት የእግዚአብሔርን የአካል ሦስትነት (ሥላሴ) የሚክዱ

[448] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, p. 9.

[449] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 15-25፡፡ አሳቡን ያጠቃለለበትና ገጽ 25 ላይ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር፡- "ናሁኬ አብጻሕነ ለከ ስምዓ እመጻሕፍት ከመ ቦቱ ለእግዚአብሔር ፍጹመ መልክዐ እጓለ እመሕያው" ይላል፡፡

[450] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 23፡፡

የሰባልዮስንና የተከታዮቹን ኑፋቄ ለማረም ብሎ እንደሆነ መልስ የሰጠበትን ድርሳን (ምንባብ ዘስብከተ ጌና) ሙሉ ክፍል ስናነብ እንረዳለን፡፡[451]

አባ ጊዮርጊስ በነበረበት ዘመን (በ14ኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ) ይጽፍ እንደነበር የሚታመነው ርቱዓ ሃይማኖት "ድርሳናት ዘበዓላት ዐበይት" በሚባለው ሥራው የሚታወቅ ሲሆን፥ እነዚሁ ድርሳናት ርቱዓ ሃይማኖት ከአባ ጊዮርጊስ የተለየ አስተምህሮ እንደነበረው በግልጽ ያሳዩናል፡፡ ለምሳሌ፥ ለበዓለ ዕርገት የጻፈው ድርሳን ውስጥ፡- "ለመለኮት ቀኝና ግራ፥ ፊትና ኋላ የለውም" ይልና የማይታየውን (ረቂቅ የሆነውን) አካለ መለኮት ግዙፍ (በቦታ የተወሰነ) ከሆነው ከፍጡር አካል ጋር ማመሳሰል እንደማይገባ ይነግረናል፡፡[452] አባ ጊዮርጊስ ግን እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የሚመስሉ እጆችና ጣቶች አሉት ብሎ እንደሚያምን ከላይ ተመልክተናል፡፡ ሁለቱ ምሁራን የማይከፈል መለኮታዊ ባሕርይ ያለው አምላክ በአካል እንዴት ሦስት እንደሚሆን ለማስረዳት በመረጧቸው ምሳሌያት[453] ላይም ልዩነት ነበራቸው፡፡ ለምሳሌ ፀሐይን ለምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ አድርገው የተጠቀሙበት መንገድ የተለያየ ነው፡፡ ርቱዓ ሃይማኖት ከመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ጠቅሶ፡- "ጌታችን 'አባቴ ፀሐይ ነው፥ እኔ ብርሃኑ፥ መንፈስ ቅዱስ ሙቀቱ' ያለውን አድምጥ"[454] በማለት ይጽፋል፡፡ በዚህ ምሳሌ መሠረት አብ በፀሐይ (በሰሌዳው)፥ ወልድ በፀሐይ ብርሃን፥ መንፈስ ቅዱስ በሙቀቱ እንደተመሰሉ ልብ እንበል፡፡ አባ ጊዮርጊስ ግን ለእያንዳንዱ የሥላሴ አካል ሙሉውን ፀሐይ በምሳሌነት ይጠቀማል፡- "አብ ዘወትር የሚያበራ ፀሐይ እንደሆነ፥ ወልድም በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራ ፀሐይ ነው፤ ወልድ በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራ ፀሐይ እንደሆነ፥ መንፈስ ቅዱስም ቤተ ክርስቲያንን

[451] የምንባቡ መጨረሻ ላይ የሰባልዮስ ኑፋቄ ተከታይ የሆነ ሁሉ ከክህደቱ ተመልሶ በመለኮታዊ ባሕርዩ አንድ የሆነው እግዚአብሔር የአካል ሦስትነት (ሥላሴ/ ግጻዌ መለኮት) እንዳለው ማመን እንዳለበት ሲያጠይቅ እንዲህ ይላል፡- "ሕድግ እንከሰ አ ንፉቅ ዕልወተ ዘላዕሌከ፤ እመን በሥላሴ፡ ወተጋነይ ለግጻዌ መለኮት" - *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO*,* Vol. 515, Tom. 89, p. 25-26.

[452] ድርሳን ዘበዓለ ዕርገት፥ EMML 2375, f. 91a.

[453] Analogies.

[454] ድርሳን ዘበዓለ ጥምቀት፥ EMML 2375, f. 26a.

የሚያስጌጣት ፀሐይ ነው፡፡"[455] እንዲያውም የርቱዓ ሃይማኖትን ምሳሌ የሚጠቀሙትን ሰዎች ያወግዛል፡- "አብ ፀሐይ፥ ወልድ ብርሃን [የፀሐይ ብርሃን]፥ መንፈስ ቅዱስ ሙቀቱ ነው ብሎ የሚናገር ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን"፡፡[456]

እነዚህ ምሳሌያት በውግዘት የታጀበ ልዩነት የፈጠሩትና የሁለቱን ደራስያን የተለያዩ አስተምህሮዎች በተከተሉ ክፍሎች (በዘርአ ያዕቆባውያንና ዘሚካኤላውያን) መካከል በጣም አከራካሪ የሆኑት፥ የተሳሳተውን ምሳሌ መከተል በምሥጢረ ሥላሴ ላይ መዛባትን ይፈጥራል የሚል ስጋት ስለነበራቸው ነው፡፡ የርቱዓ ሃይማኖትን ምሳሌ የመረጡ ወገኖች ምሳሌው የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ለማስረዳት በቂ እንደሆነ ሲያስቡ፥ የአባ ጊዮርጊስ ምሳሌ ግን የሦስቱን አካላት የህልውና አንድነት ያላገናዘበ መስሎ ታይቷቸዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የአባ ጊዮርጊስን ምሳሌ የተከተሉ ወገኖች፥ የርቱዓ ሃይማኖት ምሳሌ "አሐዱ ገጸ እግዚአብሔር" (የእግዚአብሔር ገጽ/አካል አንድ ነው) የሚለውን የሰባልዮስን ኑፋቄ የሚከተል ስለመሰላቸው ለመቀበል ተቸግረዋል፡፡ ለምሳሌ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ለሥላሴ አካላት ሦስት ፀሐዮችን እንደ ምሳሌነት የሚያቀርበውን የአባ ጊዮርጊስን አስተምህሮ ሲደግፍ፥ ዘሚካኤላውያን ግን ይህ ምሳሌ "ሦስት አማልክት" የማለት ያህል መስሎ ስላልታያቸው አልተቀበሉትም፡፡ እነርሱ የመረጡት አንዲቱን ፀሐይንና ያሏትን ባሕርያት (ብርሃንና ሙቀት) ለሥላሴ ምሳሌ አድርጎ የሚያቀርበውን የርቱዓ ሃይማኖትን ትምህርት ነው፡- "የፀሐይ ሰሌዳ የአብ ምሳሌ ሲሆን፥ ብርሃኗ በወልድ፥ ሙቀቷ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ" ይመሰላሉ፡፡[457] በአንጻሩ ደግሞ ለዘርአ ያዕቆብ ይህ ምሳሌ የአካል ሦስትነትን የካደ መስሎ ታይቶታል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው አፄ ዘርአ ያዕቆብ "አልቦቱ ለእግዚአብሔር መልክዐ ከመ መልክዐ ሰብእ"[458] (እግዚአብሔር የሰውን መልክ የሚመስል መልክ የለውም)

---

[455] *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO*,* Vol. 515, Tom. 89, p. 31.
[456] Getatchew Haile, "Religious Controversies," ገጽ 114 ላይ የተጠቀሰ፤ ጥቅሱ የተወሰደው ከEMML 6456, f.29r ነው፡፡
[457] Getatchew Haile, "Religious Controversies," p. 108.
[458] Getatchew Haile, trans., "The Homily of Zär'a Yaʿəqob in Honour of St. John the Evangelist," (ምንባብ እምረቡዑ ለጥር) *OC,* 67 (1983) p. 150.

የሚለውን የዘሚካኤልን አሳብ የተቃወመው የእግዚአብሔርን የአካል ሦስትነት የሚቃረን ስለመሰለው ነው፡፡ ነገር ግን የዘሚካኤላውያኑ አስተምህሮ የአካል ሦስትነትን የሚክድ ሳይሆን በዋነኝነት የእግዚአብሔር መለኮታዊ አካል በፍጡራን ሊታወቅ (ሊመረመር) አለመቻሉ ላይ የሚያተኩር እንደሆነ ከሰጡት መልስ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ አፄ ዘርአ ያዕቆብ፥ ገማልያል የተባለውን የዘሚካኤል ጓደኛ ከላይ በተጠቀሰው የዘሚካኤል አመለካከት የሚስማማ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ሲጠይቀው የሰጠው መልስ፡- "ከዘሚካኤል ጋር አበርኩ፥ ወንጌል 'እግዚአብሔርን ፈጽሞ ያየው ማንም የለም' እንዲል፤ ፈጽሞ ያየው ከሌለ ማንን ይመስላል እላለሁ?"[459] የሚል ነበር፡፡በተጨማሪም አፄ ዘርአ ያዕቆብ ስለዘሚካኤላውያኑ የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ ይዘት እንደነገረን፥ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ…" የሚለውን ዝማሬ ከዘመሩ በኋላ በአንድነት፥ በሦስትነት የሚመለከውን አምላክ ሲገልጹት "[በአርአያ] ፍጥረታት [ኢይትሜሰል]"[460] (በፍጡራን አርአያ [መልክ][461] ሊመሰል የማይችል) ይሉ ነበር፡፡

ዘሚካኤላውያን "ፍካሬ መለኮት" በተሰኘው የነገረ መለኮት ድርሳናቸው ውስጥ እንደምናነበው "በአካል ሦስት፥ በመለኮታዊ ባሕርይ አንድ" በሆኑት በአብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ (በአንድ አምላክ) እንደሚያምኑ በግልጽ አስረድተዋል፡፡[462] ከዘርአ ያዕቆብ ጋር ሊያስማማቸው የሚችለውን ይህን ቃለ ተአምኖ ከገለጹ በኋላ፥ ትምህርታቸውን በዝርዝር ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል፡- "ነገር ግን፡ አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ብለን ስንናገር ወይም ተናጋሪ እንስሳ እንደ ሆነውና ዕድሜው እንደተወሰነው እንደ ሰው ስምና አካላት አሏቸው ስንል [ሥላሴን] ፍጡራን

---

[459] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 151፡፡

[460] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 155፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብ "መጽሐፈ ብርሃን" በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥም ይህንን የዘሚካኤላውያን ዝማሬ ዘግቦታል፡- *Il Libro Della Luce Del Negus Zar'a Yāʿqob: Maṣḥafa Berhān*, CSCO, Vol. 261, Tom. 51, Scriptores Aethiopici, ed. Conti Rossini and L. Ricci (Louvain: 1965) p. 124.

[461] Image.

[462] "ፍካሬ መለኮት" *Scritti teologici etiopici dei secoli XVI-XVII*: *Tre opuscoli dei Mikaeliti,* Vol. 1, ed. Enrico Cerulli (Vatican: Biblioteca Apostolica Vaticana, 1958) p. 3.

ማድረጋችን አይደለም"፡፡ [463] እንዲሁም አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከዘሚካኤላውያን ጋር በነበረው ክርክር ሥላሴ የሰውን ልጅ የሚመስል መልክ ወይም አካል (ፊት፥ ዓይኖች፥ ጆሮዎች፥ እጆች ወዘተ.) እንዳሏቸው የሚያመለክቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን በብዛት የጠቀሰ ሲሆን [464] ዘሚካኤላውያኑ በበኩላቸው ለተጠቀሱት ጥቅሶች የራሳቸውን መልስ ሰጥተዋል፡፡ እንደ እነርሱ አስተምህሮ፡- እግዚአብሔር ዓይኖች፥ ጆሮዎች፥ እጆች ወዘተ. እንዳሉት የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የሚመስል አካል እንዳለው እንድናስብ ሊያደርጉን ይችላሉ፡፡ [465] ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች ምሳሌያዊ አገላለጾች ናቸው፡፡ [466] እግዚአብሔር በሥላሴሁ (በሦስትነቱ) የሚታወቅበት አካላት ቢኖሩትም እነዚህ መለኮታዊ አካላት በፍጡር አእምሮ ሊመረመሩ የማይችሉ ናቸው፤ "ዘላለማዊ ምሥጢራቸውን መቅረብ ባይቻለንም፥ ስለእነዚህ [መለኮታዊ] አካላት በሕሊናችን እናስባለን፤ ሊዳሰሱ የማይችሉና ከፍጡር ሕሊና በላይ ናቸውና"፡፡[467]

ዘሚካኤላውያን የነገረ መለኮት ትምህርታቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነት እንዲያገኝና መሠረታዊ አስተምህሮ ሆኖ እንዲቀር ስለፈለጉ የእነርሱን አቋም የሚያንጸባርቁ ቅዳሴያት ይደርሱ ነበር፡፡ አፄ ዘርአ ያዕቆብ "መጽሐፈ ብርሃን" ሲል በሰየመው መጽሐፉ ይህን ሥራቸውን ተቃውሟል፡-

> ወቅዳሴ ቍርባንሂ አቀሙ በፈቃደ ርእሶሙ ኀዲጎሙ ቅዳሴ እግዚእነ ዘተጽሕፈ በኪዳን ወቅዳሴ ሐዋርያት ዘተጽሕፈ በሲኖዶስ፡፡[468]
>
> በመጽሐፈ ኪዳን የተጻፈውን ቅዳሴ እግዚእን እና በመጽሐፈ ሲኖዶስ የተጻፈውን ቅዳሴ ሐዋርያትን ትተው በራሳቸው ፈቃድ አኰቴተ ቍርባን መሠረቱ (አዘጋጁ)፡፡[469]

---

[463] ዝኒ ከማሁ (ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ)፡፡
[464] *Il Libro Della Luce: Maṣḥafa Berhān*, ed. Conti Rossini and L. Ricci, CSCO, Vol. 261, Tom. 51, ገጽ 127-128፡፡
[465] "ፍካሬ መለኮት" *Scritti teologici etiopici*, p. 15.
[466] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 47፡፡
[467] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 58፡፡
[468] *Il Libro Della Luce: Maṣḥafa Berhān*, ed. Conti Rossini and L. Ricci, CSCO, Vol. 261, Tom. 51, p. 41.
[469] ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ፡፡

ይህ የዘርአ ያዕቆብ ቅሬታ፥ እርሱ እስከ ነበረበት (15ኛው ምእት ዓመት) ድረስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚታወቁት ቅዳሴያት ሁለት ብቻ (ቅዳሴ እግዚእ እና ቅዳሴ ሐዋርያት) እንደነበሩ ያስረዳናል፡፡ ከቅዳሴ ሐዋርያት እኩል በዘመነ አክሱም (4ኛው-5ኛው ምእት ዓመት) ወደ አገራችን እንደገባ የሚነገርለት ቅዳሴ ማርቆስና በተሰዐቱ (ዘጠኙ) በኩል የደረሰን ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም) በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ለምን አገልግሎት ላይ እንዳልዋሉ ወይም አገልግሎታቸው ለምን እንደተቋረጠ ግልጽ ባይሆንም፥ ንጉሡ እውቅና የሰጠው ከላይ ለተጠቀሱት ሁለት ቅዳሴያት ብቻ ነው፡፡

ከሥር በዝርዝር የምንመለከተው ቢሆንም ከግሪክ፥ ሱርስት እና ዐረብኛ ቋንቋዎች በተለያዩ ዘመናት ወደ ግእዝ ከተተረጎሙት ቅዳሴያት (ቅዳሴ ሐዋርያት፥ ቅዳሴ ማርቆስ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ፥ ቅዳሴ እግዚእ እና ቅዳሴ ባስልዮስ)[470] በስተቀር የተቀሩት ቅዳሴያት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እንደ ተደረሱ የሚጠቁሙ በቂ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ከላይ በአጭሩ የተዘረዘሩት የነገረ

[470] ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግም ወደ ግእዝ ከተተረጐሙት ቅዳሴያት ጋር እንደሚመመደብ የጠቆሙ ምሁራን አሉ፤ ለምሳሌ Getatchew Haile, "On the Authorship of Ethiopian Anaphoras," pp. 25 & 27 እና S. Euringer, "die äthipischen Anaphoren des HI. Evangelisten Johannes des Donnersohnes und des HI. Jacobus von Sarug," *OCa,* 33/1 (1934) p. 82 ይመልከቱ፡፡ ይህ አስተያየት የተሰነዘረው የቅዳሴው ይዘትና በውስጡ የሚገኙት አንዳንድ ክፍሎች (ለምሳሌ ሜሎስ የሚለውን ቃል ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ በኅብስቱና ወይኑ ላይ እንዲወርድ የሚጠይቀው ጸሎት - *epiclesis*) በዚሁ ቅዱስ ስም የተሰየመውን የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ባሕርይ ስለሚያሳይ ሊሆን ይችላል - Habtemichael Kidane, "A Note on the Aspects of the Epiclesis of the Gə'əz Anaphora of St. James of Sərug," *Rites and Rituals of the Christian East,* eds. Bert Groen, Daniel Galadza, Nina Glibetick and Gabriel Radle, Eastern Christian Studies*,* Vol. 22 (Leuven: Peeters, 2014) pp. 154-155፡፡ ነገር ግን በሁለቱ ቅዳሴያት መካከል ያለው ግንኙነት ግልጽ ቢሆንም የግእዙ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ፥ በዚሁ ስም የተሰየመው የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ትርጉም ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ያለ አይመስልም፡፡ አባ ቴዎድሮስ አብርሃ የግእዙን ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ የደረሱ ሊቃውንት፥ ከሶርያዊው አባት ድርሳናት (homilies) ብዙ ጥቅሶችን እንደወሰዱና እነዚህን ድርሳናት የቅዳሴያቸው መሠረት አድርገው እንደተጠቀሙባቸው በጥናታቸው አረጋግጠዋል - Tadros Abraha, "Jacob of Serug in the Ethiopic Tradition under Review and New Clues about the Background of the Gəʿəz Anaphora Ascribed to Jacob of Serug," *OCA,* Vol. 298 (2015) pp. 473-477 ይመልከቱ፡፡

መለኮት አስተምህሮዎችንና የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌያትን የያዙ ቅዳሴያት (ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፥ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፥ ቅዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ) በቤተ ክርስቲያናችን ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ቅዳሴያት በ14ኛውና 15ኛው ምእት ዓመታት አገራችን ውስጥ ይካሄዱ የነበሩ የነገረ መለኮት ክርክሮች[471] ውጤቶች ናቸው ማለት ነው፡፡ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ዋነኛ መገለጫ፥ ደራስያኑ ካላቸው ትሕትና የተነሣ በሥራዎቻቸው ውስጥ ስማቸውን አለመጥቀሳቸው ሲሆን የደረሷቸውን ቅዳሴያት "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ አትናቴዎስ፥ ዘቅዱስ ቄርሎስ፥ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ፥ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ፥ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ" ወዘተ. በማለት የሰየሟቸው፥ ድርሰቶቻቸው በቀላሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነት እንዲያገኙ በማሰብ ነበር፡፡

ከላይ ወደተነሣሁበት ነጥብ ልመለስና፥ ርቱዓ ሃይማኖትና ዘሚካኤላውያን ምሥጢረ ሥላሴን ለመግለጽ ይጠቀሙበት የነበረው ምሳሌ በ318ቱ የኒቅያ ጉባኤ አባቶች ስም በተሰየመው ቅዳሴ ውስጥ ይገኛል፡፡ ጌታችን ስለአባቱና ቅዱስ መንፈሱ ህልውና ለደቀ መዛሙርቱ እንደነገራቸው የሚያትተው የቅዳሴው ክፍል፡- "አባቴ፥ እኔ [እና] መንፈስ ቅዱስ፡- ፀሓይ፥ ብርሃን [እና] ዋዕይ ነን፡፡ አባቴ፥ እኔ [እና] መንፈስ ቅዱስ፡- እሳት፥ ነበልባል [እና] ፍሕም ነን"[472] ይላል፡፡ እዚህ ላይ አብ በፀሐይ፥ ወልድ በፀሐይ ብርሃን፥ መንፈስ ቅዱስ በዋዕይ (ሙቀት) እንደተመሰሉ ልብ እንበል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እሳት የአብ፥ ነበልባሉ (የእሳቱ ብርሃን) በወልድ፥ ፍሙ (የተዳፈነ እሳት) ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌያት ሆነው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ምሳሌያት በቅዳሴ ማርያም ከተጠቀሱት የሥላሴ ምሳሌያት ግልጽ የሆነ ልዩነት አላቸው፤ የሠለስቱ ምእት ቅዳሴ ደራሲ የፀሐይን ወይም የእሳትን አካልና መገለጫ ባሕርያትን በምሳሌነት ሲጠቀም፥ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ ግን የአባ ጊዮርጊስን አስተምህሮ ይከተላል፡-

[471] Theological controversies.

[472] "ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 1994፣ ገጽ 197-198፣ ቍ. 47-48፡፡

አብ ፀሓይ ነው፤ ወልድ ፀሓይ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ፀሓይ ነው፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን አንድ የእውነት ፀሓይ ነው፡፡ አብ እሳት ነው፤ ወልድ እሳት ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እሳት ነው፤ በልዕልና ያለ አንድ የሕይወት እሳት ነው፡፡[473]

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ Vatican MS 15, f. 186rv እና Vatican MS 18, ff. 72v-73r በተሰኙ የመለያ ቍጥሮች የተመዘገቡ ጥንታዊ ብራናዎችን ጠቅሰው፥ በቤተ ክርስቲያናችን የታተመው ቅዳሴ ማርያም ውስጥ ያለው ምሳሌ ማስተካከያ ተደርጎበት እንጂ የቀድሞ ይዘቱ ከዚህ የተለየ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡[474] ፕሮፌሰሩ ብራናዎችን ምንጭ አድርገው የጠቀሱት ምሳሌ እ.አ.አ. በ1945 ቫቲካን ውስጥ የታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ይገኛል፡- **"አብ ፀሓይ፥ ወወልድ ብርሃን፥ ወመንፈስ ቅዱስ [ዋዕይ]፡ አሐዱ ውእቱ ፀሓየ ጽድቅ ዘያበርህ ለኵሉ**"፡፡[475] በተጨማሪ "ለመለኮት ወርድና ቁመት፥ ላይና ታች፥ ቀኝና ግራ ያለው አይደለም፤ በሁሉ የመላ ነው እንጂ፡፡ ለመለኮት የሚዘረጋበትና የሚሰበሰብበት ያለው አይደለም፤ ግዛቱ ባገር ሁሉ ነው እንጂ"[476] የሚለው የቅዳሴ ማርያም አገላለጽ ከላይ ከርቱዓ ሃይማኖት ድርሳን ከጠቀስኩት[477] ጥቅስ ጋር የሚስማማ ሲሆን የቅዳሴውን አገራዊ ምንጭ ያመላክታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከላይ የተጠቀሰውን የዘሚካኤላውያንን አስተምህሮ የሚደግፍ ጥቅስ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ውስጥ ይገኛል፡- "የሚያውቅህ የለም፡፡ አንተን ማየት የሚችል የለም፤ ራስህን አንተ ታውቃለህ"[478]፡፡ በወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ፥ በ318ቱ የኒቂያ ጉባኤ አባቶችና በአባ ሕርያቆስ ዘብህንሳ ስም የተሰየሙ ሦስቱ ቅዳሴያት ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መካከል በማን (በእነማን) እንደተደረሱ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም፥ የቅዳሴያቱ አጠቃላይ ይዘትና ከላይ የተጠቀሱት የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌያት ቅዳሴያቱ በ15ኛው ምእት ዓመት አገራችን ውስጥ የነበሩ ሊቃውንት ድርሰቶች መሆናቸውን የሚጠቁሙ ምልክቶች ናቸው፡፡

---

473 "ቅዳሴ ማርያም"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፥1994፣ ገጽ 174፣ ቍ. 74-75፡፡

474 Getatchew Haile, "Religious Controversies" p. 108.

475 "አኰቴተ ቍርባን ዘእግዝእትነ ማርያም,'' *Missale Ethiopicum* [Ethiopian Missal] (Rome: Vatican Printing Press, 1945) p. 79.

476 "ቅዳሴ ማርያም"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 1994፣ ገጽ 171፣ ቍ. 49-50፡፡

477 ገጽ 222 ይመልከቱ፡፡

478 "ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ"፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 1994፣ ገጽ 139፣ ቍ. 5፡፡

በሌላ መልኩ የአባ ጊዮርጊስን አመለካከት የሚደግፍና በቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስም የተሰየመ ቅዳሴ እናገኛለን፡፡ "ዓለምን ሁሉ የያዙ ሠለስቱ ዕደው (ሦስት ሰዎች) ከእኛ ዘንድ አሉ"[479] የሚለው የዚህ ቅዳሴ አገላለጽ ኢጋዕዝተ ዓለም ሥላሴን በሦስት ሰዎች መስሎ ስለሚያቀርብ፥ እግዚአብሔር እንደ ሰው ዓይነት መልክ (ቅርጽ) አለው[480] የሚለውን የአባ ጊዮርጊስን አስተምህሮ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለዚህ አባ ጊዮርጊስ ይህን ቅዳሴ ከደረሰ በኋላ የራሱን ስም ሳይጠቅስ "አኰቴተ ቍርባን ዘጎርጎርዮስ ኤጲስ፡ቆጶስ ዘኑሲስ እኁሁ ለባስልዮስ"[481] የሚል ርእስ ሰጥቶት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ማድረጉም ቅዳሴው በቤተ ክርስቲያኒቱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት በአባ ጊዮርጊስ ዘመን የነበሩት ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ አባ በርተሎሜዎስ (1390-1428 ዓ.ም.) ጸሎታተ ቅዳሴ እንዲደርስ ለአባ ጊዮርጊስ ሥልጣን ከሰጡት[482] በኋላ እንኳን "መዓዛ ቅዳሴ" በማለት የሚጀምረውን አኰቴተ ቍርባን እርሱ አንደደረሰው ስለታወቀ በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ ነው፡፡[483] ለዚህም ይመስላል በአገራችን ሊቃውንት የተደረሱና ኢትዮጵያዊ የአጻጻፍ ዘዬን በግልጽ የሚያሳዩት አገር በቀል ቅዳሴያት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ባገኙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም የተሰየሙት፡፡

"ርቱዓ ሃይማኖት" በተሰኘ የብእር ስም መጻፍ የመረጠው ኢትዮጵያዊ ምሁርም እንደ አባ ጊዮርጊስ ቅዳሴያት በመድረስ ተሳታፊ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ በመጽሐፈ ምሥጢር ውስጥ የሚገኘውን የጸሎተ ኀሙስ ምንባብ ከዚህ ሊቅ ሥራ ወስዶ

---

479 "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ"፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 1994፣ ገጽ 272፣ ቍ. 24፡፡

480 ገጽ 221 ይመልከቱ፡፡

481 "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ"፥ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 1994፣ ገጽ 269፣ ቍ. 2.

482 ገድለ አባ ጊዮርጊስ አንድ አይሁዳዊ ላነሣው ጥያቄ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ድንቅ መልስ ሰጥቶ ስላሳፈረው ጳጳሱ አባ በርተሎሜዎስ በመልሱ ደስ ተሰኝተው ቅዳሴያት ይደርስ ዘንድ እንደፈቀዱለት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡- "ወእምብዝኀ ፍሥሓ አምኖ ጳጳስ ወባረኮ ወአብኖ ከመ ይድርስ ቅዳሴያተ፥ ወእምአሜሃ አኀዘ ይድርስ ቅዳሴያተ" - *Vie de Georges de Saglā* [ገድለ አባ ጊዮርጊስ], CSCO, Vol. 492*,* Tom, 81, Scriptores Aethiopici, ed. Gérard Colin (Louvain: Aedibus E. Peeters, 1987) p. 25.

483 መዓዛ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያናችን ያሳተመቻቸው 14 ቅዳሴያት ዝርዝር ውስጥ አይገኝም፡፡

"ድርሳን ዘደረሰ አሐዱ ርቱዓ ሃይማኖት ዘብሔረ ኢትዮጵያ"[484] ሲል እውቅና እንደሰጠው ሁሉ፥ እዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የርቱዓ ሃይማኖትን ቅዳሴ ይጠቅሳል፡፡ "አኰቴተ ቍርባን ዘርቱዓ ሃይማኖት" የሚል ርእስ ከተሰጠው ፍሬ ቅዳሴ የተወሰደ ጥቅስ ይህን ይመስላል፡- "ህልው አብ ምስለ ወልዱ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ እምቅድመ ሰዓት ወዕለት እምቅድመ አዝማን ወዕለታት (ዓመታት)፤"[485] ይኸው ዓረፍተ ነገር ቅዳሴ ቄርሎስ ውስጥ ይገኛል፡፡ [486] ስለዚህ በቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ (+444 ዓ.እ.) ስም የሚታወቀው ቅዳሴ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በ1375 ዓ.ም. አካባቢ "ርቱዓ ሃይማኖት" በሚል ብእር ስም ይጽፍ የነበረ ሊቅ ድርሰት መሆኑን ፍንጭ አግኝተናል ማለት ነው፡፡ በመቀጠል አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት በ14ኛው እና 15ኛው ምእት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ሊቃውንት ድርሰቶች መሆናቸውን አሳማኝ በሆነ መልኩ የሚያስረዱ ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ማስረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

## 3.2. ቅዳሴያቱ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መደረሳቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎች

ቤተ ክርስቲያናችን ከግሪክ፥ ሱርስት እና ዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐሙ በርካታ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ባለቤት እንደሆነች በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ተመልክተናል፡፡ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ሲተረጉሙ ቃል በቃል ከመተርጐም ይልቅ ከኢትዮጵያዊው ባህልና አስተምህሮ ጋር እንደሚስማማ አድርገው የመተርጐም ልምድ ስላላቸውና በትርጉም ሥራቸው ውስጥም የራሳቸውን አስተዋጽኦ ስለሚጨምሩባቸው፥ ትርጉሞቹ መሠረት ከሆኗቸው (ከተተረጐሙባቸው) መጻሕፍት የተለየ ይዘት ያሳያሉ፡፡ ከትርጉም ሥራዎች በተጨማሪ ደግሞ በአገራችን የተነሡ የነገረ መለኮት ክርክሮችን መነሻ በማድረግ ሊቃውንቱ የተለያዩ ቅዳሴያትን ደርሰዋል፡፡ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱ

---

484 *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir*, ed. Yaqob Beyene, CSCO, Vol. 515, Tom. 89, p. 235.

485 EMML 6456 f. 35r, Getatchew Haile, "Religious Controversies" ገጽ 123, የኀዳግ ማስታወሻ ቍ፣ 79.

486 "ቅዳሴ ቄርሎስ"፥ መጽሐፈ ቅዳሴ፥ 1994፣ ገጽ 337፣ ቍ. 92፡- "አብ ከልጁ ጋር፥ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ከሰዓትና ከዕለት፥ [ከዘመናትና] ከዓመታት አስቀድሞ የነበረ ነው"፡፡

ቅዳሴያት የተለያዩ የነገረ መለኮት አስተምህሮዎች ውጤት ስለሆኑ ከአኰቴተ ቍርባን መገለጫ ባሕርያት ይልቅ የትምህርተ ሃይማኖት ድርሳናትን[487] የሚመስሉ ባሕርያት ይታይባቸዋል፡፡ ይህ የአብዛኞቹ አገር በቀል ቅዳሴያት አይነተኛ መገለጫ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ያሳተመቻቸው 14 ቅዳሴያት[488] አሏት፡፡ እስካሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያናችን እውቅና ተሰጥቷቸው ያልታተሙና በብራና የሚገኙ ተጨማሪ 6 ቅዳሴያት አሉ፤ እነርሱም[489]፡-

- መዓዛ ቅዳሴ ዘአባ ጊዮርጊስ ("መዓዛ ቅዳሴ ውኩፍ ዘምስለ ስብሐት ወግናይ ናቄርብ ለስምኪ ማርያም" በማለት ይጀምራል)፤
- ቅዳሴ ማርቆስ ወንጌላዊ ("እግዚአብሔር አምላክነ አብ አኃዜ ኵሉ ለከ ንሴብሐከ፡ ለከ ንዌድሰከ" በማለት ይጀምራል)፤
- ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ[490] [የጌታ ወንድም]("ርቱዕ ወጽድቅ ይደሉ ኪያከ ንሴብሕ፡ ኪያከ ንባርክ" በማለት ይጀምራል)፤
- ቅዳሴ ማርያም ዘጎርጎርዮስ [ዘእንዚናዙ] ("ነአኵተከ አምላክ በወልድከ ዋሕድ ወመንፈስከ ቅዱስ፡ እንበለ ተፈልጦ ዘትሤለስ" በማለት ይጀምራል)፤
- ቅዳሴ ማርያም ዘጎርጎርዮስ [ዘአርማንያ፤ ከሣቴ ብርሃን][491] ("ነአኵተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቍርባን ንጹሐ ዘያሠምሮ ለኂሩትከ"[492] በማለት ይጀምራል)፤

---

[487] Theological treatises.

[488] በታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ ላይ እንደምንመለከተው የእነዚህ ቅዳሴያት ዝርዝር የሚከተለው ነው፡- ቅዳሴ ሐዋርያት፥ ቅዳሴ እግዚእ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ፥ ቅዳሴ ማርያም፥ ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት (318ቱ የኒቂያ ጉባኤ ሊቃውንት)፥ ቅዳሴ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ፥ ቅዳሴ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፥ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (የባስልዮስ ወንድም፤ የሆሣዕና ቅዳሴ)፥ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ዘደሴተ ቆጵሮስ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ቅዳሴ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ፥ ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ [ዘቀጸዶቅያ/ ገባሬ መንክራት] (የልደት ቅዳሴ) ናቸው፡፡

[489] Habtemichael Kidane, "Anaphoras," *EA,* Vol. 1, p. 252.

[490] ከ14ቱ ቅዳሴያት በተጨማሪ፡- መዐዛ ቅዳሴ፥ ቅዳሴ ማርቆስና ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ በ1945 እ.አ.አ. ሮም በሚገኘው ቫቲካን ማተሚያ ቤት ታትመዋል - *Missale Ethiopicum*, Rome: Vaticano Printing Press, 1945 ይመልከቱ፡፡

- ቅዳሴ ቄርሎስ ካልዕ (“ነአኵተከ ወናሌዕለከ፡ ንባርከከ ወንሴብሐከ” በማለት ይጀምራል)፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ካሏት 20 ቅዳሴያት መካከል አብዛኞቹ (ወደ ዐሥራ አምስት የሚጠጉት) በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተደርሰው በቤተ ክርቲያኒቱ ተቀባይነት ያገኙ ዘንድ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ አባቶች የተሰየሙ ናቸው፡፡ የአባቶቻችንን ታላላቅ ሥራዎች ለግብፃውያን የመስጠት ጥናት የጎደለው ልማድ ስላለ አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ካህናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያሳተመቻቸውን 14 ቅዳሴያት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን እንደተቀበለቻቸው አድርገው ያስባሉ፡፡ ይህን የየዋህነት አመለካከት የተረዳውና 14ቱን ቅዳሴያት በብላታ መርስዔ ኀዘን እርዳታ ከግእዝ ወደ እንግሊዝኛ እና ዐረብኛ የተረጐመው ግብጻዊው ቄስ ማርቆስ ዳውድ የትርጉም ሥራው መቅድም ላይ በድፍረት የሚከተለውን እውነታ የሌለው ዐረፍተ ነገር አስነብቦናል፡-

> 14ቱን ቅዳሴያት ከግብፅ (ኮፕቲክ) ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቀበሉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይነገራል፤ የግብፅ ቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ ታረጋግጣለች፡፡ ነገር ግን ከ14ቱ መካካል አብዛኞቹ ጠፍተውባታል፡፡[493]

ፕሮፌሰር ጌታቸው እንዳሉት፥ ማርቆስ ዳውድ ቤተ ክርስቲያናችን ያሏት ቅዳሴያት 14 ብቻ ሳይሆን፥ 20 መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጠፍተውባታል የሚለውን የቅዳሴያት ቍጥር ከፍ ያደርገው ነበር፡፡[494] ወይም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀያውንም ቅዳሴያት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላላች

---

[491] ይህ አባት፡- “St. Gregory the Illuminator (the Armenian)” በሚል ስያሜ ይታወቃል - See Mebratu Kiros, “Anaphoras of the Ethiopian Church: A Historical Introduction,” *Ephrem's Theological Journal,* Vol 5 (October 2001) p. 204፡፡

[492] በዚህ ዐረፍተ ነገር የሚጀምርና “ጸሎተ አኰቴት ዘእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል በክልኤ፡ ዘደረሰ ላቲ ናትናኤል ሐዋርያ ዘሀገረ ሰማርያ” የሚል ርእስ የተሰጠው አኰቴተ ቍርባን በብራና ይገኛል፡፡ ነገር ግን ከመዐዛ ቅዳሴ ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ራሱን የቻለ አኰቴተ ቍርባን ነው ማለት አይቻልም፡፡ Stefan Strelcyn, “L'action de grâce de n.de. Marie et l'anaphore de n.d. Marie dite Mä'aza Qəddase dans la liturgie éthiopienne,” *JSS,* Vol. 24/2 (1979) ገጽ 241 እና 246 ይመልከቱ፡፡

[493] “Foreword,” *The Liturgy of the Ethiopian Church,* trans. Marcos Daoud (London: Kegan Paul, 2005).

[494] Getatchew Haile, “On the Authorship of Ethiopian Anaphoras,” p. 9.

ሊለን ይችል ነበር፡፡ እውነታው ግን የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ያሏት ቅዳሴያት ሦስት ብቻ (ዘቅዱስ ባስልዮስ፥ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙና ዘቅዱስ ቄርሎስ)[495] ሲሆን ከእነዚህ መካከል በእኛ ቤተ ክርስቲያን የሚታወቀው *አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ባስልዮስ* የዐረብኛው ቅዳሴ ባስልዮስ ትርጉም ነው፡፡ የተቀሩት ሁለቱ ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተመሳሳይ ስም ከሚገኙት ቅዳሴያት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም፡፡ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን *ቅዳሴ ቄርሎስ* በሚል ስያሜ የሚታወቀው ቅዳሴ፥ በቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ስም የሚጠራው፥ ይህ አባት በጥንቱ ቅዳሴ ማርቆስ ላይ መጠነኛ ማሻሻዎች ስላደረገበት እንጂ እርሱ ስለደረሰው አይደለም፡፡ በቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ስም የሚታወቀውም የኮፕቲክ ቅዳሴ የዚህ አባት *ሥራ* እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ የሚያስረዳን ቅዳሴያት እየደረሱ በታወቁት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም መሰየም በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ ልምድ መሆኑን ነው፡፡ የእኛም አገር ሊቃውንት ይህንን ተከትለው የደረሷቸውን ቅዳሴያት በዝነኞቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስም ሰይመዋቸዋል፡፡ ሆኖም ግን የቅዳሴያቱ ይዘት ኢትዮጵያዊ ድርሰት መሆናቸውን ይመሰክራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ምሁራን በተደረጉት ጥናቶች መሠረት፥ አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት በ14ኛውና 15ኛው ምእት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ የአገራችን ሊቃውንት ስለመደረሳቸው የሚቀርቡ ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

## ፩. ቅዳሴያቱ በተሰየሙባቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሥራዎች ውስጥ አለመገኘታቸው

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሕይወትና *ሥነ* ጽሑፋዊ *ሥራዎች* በሚጠናበት የትምህርት ዘርፍ[496] እነዚህ አባቶች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የተነሡ የነገረ መለኮት ውይይቶችንና ጥንታውያን ብራናዎችን በማጥናት የድርሰቶቻቸውን ይዘት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከታላላቆቹ ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል አኰቴተ ቍርባን እንደ ደረሰና የተለያዩ ጸሎታተ ቅዳሴን እንደ ጻፈ የሚነገርለት አባት ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ነው፡፡ የእኛም ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ በ14ኛው ምእት

[495] See Antonios Rofail, “The Eucharistic Liturgy in the Coptic Orthodox Church,” *The Logos*, 9/2 (1996) 6-11.

[496] Patrology.

ዓመት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ከተተረጐመው ቅዳሴ ባስልዮስ በተጨማሪ "ጸሎተ ባስልዮስ"[497]፥ "ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ"[498]፥ "ሊጦን ዘነግህ ዘሰብዓቱ ዕለታት ዘተናገሮ ቅዱስ ባስልዮስ"[499] የተሰኙ ጸሎታትን ይዟል፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ቅዳሴ ማርቆስን፥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ደግሞ ተሹሞ ወደ ቍስጥንጥንያ ሲሄድ ከአንጾኪያ ይዞት የመጣውን ቅዳሴ እንዳስፋፉትና እንዳሻሻሉት ቢታመንም የቅዳሴያቱ ደራስያን እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ በእኛ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የተጠቀሱት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች (ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ፥ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፥ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፥ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘደሴተ ቆጵሮስ ወዘተ.) የተለያዩ የነገረ ሃይማኖት ድርሳናትን፥ ለመንፈሳዊነት የሚጠቅሙ ጽሑፋትን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜያትን በመድረስ የሚታወቁ አባቶች ናቸው፤ ነገር ግን የጽሑፎቻቸው ዝርዝር ውስጥ ጸሎታተ ቅዳሴን አናገኝም፡፡ ስለዚህ ከላይ እንደተጠቀሰው በ14ኛው እና 15ኛው ምእት ዓመታት የተነሡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ቅዳሴያት እየደረሱ በእነዚህ ቅዱሳን አባቶች ስም የሰየሙበት ምክንያት ቅዱሳኑ በቤተ ክርስቲያናችን ያላቸውን ትልቅ ቦታ ከግምት በማስገባት የደረሷቸው ቅዳሴያት በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማሰብ ነው፡፡ ስማቸውን ያልገለጹበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ትሕትና ነው፡፡

## ፪. በተለምዶ ከግብፅ መጡ የሚባሉት ቅዳሴያት በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አለመታወቃቸው

አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን የአብነት መምህራንና ቅዳሴያቱን የሚቀድሱት ካህናት በታላላቆቹ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ፓትርያርኮች (አትናቴዎስ፥ ቄርሎስ እና ዲዮስቆሮስ) የሚጠሩት የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት ከግብፅ እንደመጡ ወይም ከኮፕቲክ/ዐረብኛ ወደ ግእዝ እንደተተረጐሙ ያምናሉ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ይህን ኢትዮጵያዊ የልምድ አስተሳሰብ የሚያውቀውና ኢትዮጵያ ውስጥ በመምህርነት ይኖር የነበረው ግብጻዊ ቄስ ማርቆስ ዳውድ ምንም ዓይነት

[497] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፥ 1994፣ ገጽ 9፡፡
[498] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 53፣ ገጽ 84።
[499] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 394-404፡፡

ማስረጃ ሳያቀርብ ቤተ ክርስቲያናችን ያሳተመቻቸውን 14 ቅዳሴያት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን እንደተቀበለችና አብዛኞቹ አሁን በግብፅ እንደማይገኙ (እንደጠፉ) ጽፏል፡፡ ነገር ግን እውነታው ይህ አይደለም፤ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከምትገለገልባቸው ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት ቅዳሴያት ውጪ ሌሎች ቅዳሴያት እንደነበሯት የሚያስረዳ ጥናታዊ ጽሑፍ የለም፡፡ በ1131 (እ.አ.አ.) የተሾሙት 70ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ አባ ገብርኤል ወልደ ቱርያክ[500] በዘመነ ፕትርክናቸው የሚታዩ አንዳንድ ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያፈነገጡ ድርጊቶችን ለማረም ካወጇቸው 32 ቀኖናት መካከል 26ኛው ቀኖና ላይ ሳኢድ በምትባለው ግዛት ውስጥ የግብፅ ቤተ ክርስቲያኒን ከምታውቃቸው ሦስት ቅዳሴያት (ዘባስልዮስ፥ ዘቄርሎስ እና ዘጎርጎርዮስ) ጋር የማይስማሙ ቅዳሴያትን የሚቀድሱ ሰዎች መኖራቸውን እንደሰሙና ይህን ድርጊት እንደሚያወግዙ ገልጸዋል፡፡[501] እንግዲህ በ4ኛው እና 5ኛው ምእት ዓመታት የነበሩት ቅዱሳን ፓትርያርኮች አትናቴዎስና ዲዮስቆሮስ ቅዳሴያት ቢደርሱ ኖሮ፥ ፓትርያርክ ገብርኤል ወልደ ቱርያክ ከጠቀሷቸውና ቤተ ክርስቲያኒቱ እውቅና ከሰጠቻቸው ቅዳሴያት ዝርዝር ውስጥ ይገኙ ነበር፡፡ ስለዚህ እስካሁን ድረስ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸው ቅዳሴያት ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ ብቻ ስለሆኑ፥ አትናቴዎስና ዲዮስቆሮስ የደረሷቸው ወይም በሌሎች ሊቃውንት ተደርሰው በእነዚህ ቅዱሳን አባቶች ስም የተሰየሙ ቅዳሴያት ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሉም ማለት ነው፡፡

## ፫. የአፄ ዘርአ ያዕቆብ አዋጅ

ከላይ እንደተጠቀሰው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከእርሱ ጋር በትምህርተ መለኮት ጉዳይ ይከራከሩ የነበሩ ዘሚካኤላውያን ትምህርታቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይነትን እንዲያገኝ አስበው የተለያዩ ቅዳሴያትን ሲደርሱ ተቃውሞውን መግለጹን ተመልክተናል፡፡ “ወቅዳሴ ቊርባንሂ አቀሙ በፈቃደ ርእሶሙ ኀዲጎሙ ቅዳሴ እግዚእነ ዘተጽሕፈ በኪዳን ወቅዳሴ ሐዋርያት ዘተጽሕፈ በሲኖዶስ”[502] (በመጽሐፈ

[500] Gabriel Ibn Turaik.
[501] O. H. E. Burmester (trans.), “The Canons of Gabriel Ibn Turaik, LXX Patriarch of Alexandria,” *OCP,* Vol. 1 (1935) p. 41.
[502] *Il Libro Della Luce: Maṣḥafa Berhān*, ed. Conti Rossini and L. Ricci, CSCO, Vol. 261, Tom. 51, p. 41.

ኪዳን የተጻፈውን ቅዳሴ እግዚእን እና በመጽሐፈ ሲኖዶስ የተጻፈውን ቅዳሴ ሐዋርያትን ትተው በራሳቸው ፈቃድ አኰቴተ ቊርባን መሠረቱ/አዘጋጁ) የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው እስከ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (15ኛው ምእት ዓመት) ድረስ ቤተ ክርስቲያናችን እውቅና የሰጠቻቸው ቅዳሴያት ሁለት ብቻ (ቅዳሴ ሐዋርያት እና ቅዳሴ እግዚእ) እንደነበሩ ነው፡፡ "ቅዳሴ ማርያም" በሚል ርእስ የሚጠራ ቅዳሴ በዘመነ ዘርአ ያዕቆብ ቢኖር ኖሮ፥ ንጉሡ ለእመቤታችን ከነበረው ልዩ ፍቅር የተነሣ ይህ ቅዳሴ የተለየ ቦታ ተሰጥቶት እንዲቀደስ ያደርግ ነበር፤ ወይም በየድርሰቶቹ ቅዳሴውን ሲጠቅስ እናነብ ነበር፡፡ ነገር ግን ቅዳሴ ማርያም በዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በቤተ ክርስቲያናችን ስለማይታወቅ ይህ ሊሆን አልቻለም፡፡ ስለዚህ ከቅዳሴ ሐዋርያትና ከቅዳሴ እግዚእ በስተቀር፥ ቅዳሴ ማርያምም ሆነ ሌሎች በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱ ቅዳሴያት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውቅናን ያገኙት ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በኋላ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው የንጉሡ አዋጅ በግልጽ ያስረዳናል፡፡

## ፩. በቅዳሴያቱ ውስጥ ያሉ ጠቋሚ ምልክቶች

አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መደረሳቸውን የሚያመለክቱ ግልጽ ምልክቶች መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ወንድም በሆነው በቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስም የተሰየመውና በበዓለ ሆሣዕና ሳምንት የሚቀደሰው ቅዳሴ፡- "የአምላክን የፊቱን መጸፋት [በጥፊ መመታት] ባየች ጊዜ ባሕር ተንቀጠቀጠች፥ ማየ ተከዚም ሸሸች" ይላል፡፡[503] እንግዲህ ይህ ቅዳሴ በቅዱስ ጎርጎርዮስ የተደረሰ ቢሆን ኖሮ ቅዱሱ ይኖርበት በነበረው በቀጰዶቅያ ከሚገኙት ወንዞች መካከል አንዱን ይጠቅስ ነበር እንጂ የማያውቀውንና ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የተከዜን ወንዝ (ማየ ተከዚ) ሊጠቅስ አይችልም፡፡ ነገር ግን የቅዳሴው ደራሲ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ የሚያውቀውን የተከዜ ወንዝ በምሳሌነት ጠቀሰ፡፡

ሌላው ቅዳሴ ማርያም ውስጥ፡- "ባለማወቃቸው የእግዚአብሔርን ገጽና አካል አንድ ነው የሚሉ በደለኞቹን የይስማኤል [*sic*] ወገኖችን እነሆ እንሰማቸዋለን፤

[503] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 43፣ ገጽ 275።

ልቡናቸውን ያሳወሩ ናቸው"[504] የሚል ንባብ እናገኛለን፡፡ ግብፅ ከ640 ዓ.እ. ጀምሮ በእስልምና ኃይሎች መውደቋን ታሪክ ይነግረናል፡፡ እነዚህ ኃይሎች የበላይነት ባገኙበት በምድረ ግብፅ ማንኛውም ግብፃዊ መነኮስ የእስማኤል ወገኖችን (እስላሞችን) እምነት የሚነቅፍ ዐረፍተ ነገር ሊጽፍ አይችልም፤ ምክንያቱም የሚከተለውን የበቀል እርምጃ ያውቃልና፡፡[505] ነገር ግን ክርስትና ከ4ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ የአገራችን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ከመሆኑም ባሻገር አገሪቱ በክርስቲያን ነገሥታት ትመራ ስለነበር የቅዳሴው ደራሲ ከላይ የተጠቀሰውን ዐረፍተ ነገር ለመጻፍ የደፈረው ከእነዚህ የታሪክ እውነታዎች በመነሣት ነው ብለን፥ ዐረፍተ ነገሩን ቅዳሴው ኢትዮጵያ ውስጥ ለመደረሱ ጠቋሚ ምልክት አድርገን መውሰድ እንችላለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ፥ ቅዳሴ ማርያምን እንደደረሰ የሚነገርለት አባ ሕርያቆስ ዘብህንሳ[506] ይኖር የነበረው በ4ኛው ምእት ዓመት (ከእስልምና መነሣት በፊት) ስለነበር[507]፥ እስልምና ከተነሣበት (ከ7ኛው ምእት ዓመት) 300 ዓመታት ቀድሞ "የይስማኤል ወገኖች" ሲል የጠራቸውን የእስልምና እምነት ተከታዮችን ጠቅሶ ሊጽፍ አይችልም፡፡ ስለዚህ ይህ ዐረፍተ ነገር በራሱ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ አባ

---

504 "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 70፣ ገጽ 174።

505 Getatchew Haile, "On the Identity of Silondis and the Composition of the anaphora of Mary Ascribed to Hərəyaqos of Bəhənsa,' *OCP,* Vol. 49 (1983) p. 383.

506 "Cyriacus of al-Bahnasā/Oxyrhynchus"- Renē-Georges Coquin, "Cyriacus," *CE,* Vol. 3 (1991) p. 669. በጥንቱ *Behnesa* ፥ አሁን ደግሞ *Benswif* ትባላለች (ከግብጻዊው ካህን አባ አንጌሎስ ጋር በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መጋቢት 23፣ 2019 ዓ.ም. የነበረኝ ውይይት)፡፡

507 በእርግጥ አባ ሕርያቆስ የነበረበትን ዘመን ለማወቅ አስቸጋሪ እንደሆነ በእርሱ ላይ ጥናት ያደረጉ ሊቃውንት ጠቁመዋል፡፡ ስለእመቤታችን የጻፋቸው ድርሳናት (መጽሐፈ ዕርገታ ለማርያም፥ ላሐ ማርያም) እና ሌሎች ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቹ (የሕፃኑ ኢየሱስ ከእናቱ ጋር መሰደድ፥ ስምዐ ጲላጦስ፥ መጽሐፈ ዶርሆ) ወዘተ. በዐረብኛ ስለሚገኙ፥ አባ ሕርያቆስ የኖረበት ዘመን ዐረብኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮ ቋንቋ ከሆነበት ከ12ኛው ምእት ዓመት በኋላ ነው የሚል አስተያየት የሰጡ ምሁራን አሉ፤ አንዳንዶችም ዘመኑን ወደ 14ኛው-15ኛው ምእት ዓመት ከፍ አድርገውታል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ጽሑፎቹ ውስጥ በዘመነ ቅዱስ አትናቴዎስ (4ኛው ምእት ዓመት) እንደኖረ ስለተናገረና *Sahidic* በተሰኘው የኮፕቲክ ቋንቋ የተጻፉ ጽሑፎቹ ስለተገኙ አባ ሕርያቆስ የኖረው በ4ኛው ምእት ዓመት ወይም Conti Rossini በመጽሐፈ አክሱም እንደነገረን በ6ኛው ምእት ዓመት ነበር ወደሚል ድምዳሜ ተደርሷል፡፡ Alin Suciu, *The Berlin-Stasbourg Apocryphon: A Coptic Apostolic Memoir* (No Place Given: Mohr Siebeck, 2017) pp. 85-86; Conti Rossini, *Book of Aksum,* CSCO, Tom. 54 (1909) p. 5.

ሕርያቆስ እንዳልሆነ ያስረዳናል ማለት ነው፡፡ የቅዳሴው ደራሲ ለቅዳሴው መጠሪያ አባ ሕርያቆስን ለምን እንደመረጠ በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ (ገጽ 243) ላይ እንመለከታለን፡፡

## ፫. አንድ አይነት የጸሎት ክፍሎች እና ዐረፍተ ነገሮች በቅዳሴያቱ ውስጥ መገኘታቸው

መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ የምናገኛቸውን ቅዳሴያት ስናነብ፥ ምንም እንኳን ቅዳሴያቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ባገኙ አባቶች ስም የተሰየሙ ቢሆኑም በቅዳሴያቱ ውስጥ ተመሳሳይ አገላለጾችን እናገኛለን፡፡ አልፎ አልፎም አንድ አይነት ጸሎቶችና ዐረፍተ ነገሮች ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስና ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ "አይቴ ብሔራ ለጥበብ - የጥበብ አገሯ ወዴት ነው?" በማለት የሚጀምር አንድ አይነትና ረጅም ጸሎተ ፈትቶ አላቸው፡፡[508] እነዚሁ ቅዳሴያት ምንም አይነት የቃላት ለውጥ የሌላቸውና "ኅዳፌ ነፍስ" በሚል ርእስ የሚታወቁ ጸሎታትንም ያስነብቡናል፡፡[509] ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ውስጥ፡- "ፍቅር ሰሐቦ ለወልደ አምላክ እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት"[510] (ፍቅር የአምላክን ልጅ ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው) የሚለው ዐረፍተ ነገር ፥ በአንድ ቃል ልዩነት ብቻ "ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት" ሲል ቅዳሴ ማርያም ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ መድኃኒታችን ለእኛ ቤዛነት የተቀበለውን የመስቀል መከራ ውብ በሆኑ ቃላት እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡-[511]

- አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፡፡
- በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ፡፡
- በአዳም ፊት የሕይወት መንፈስን እፍ ያለ አፍ ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ፥ የኮመጠጠ መጻጻን ጠጣ፡፡

---

508 "ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 76፣ ገጽ 298፤ "ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ" ቍ. 48፣ 365 ይመልከቱ።

509 "ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 108-144፣ ገጽ 303-304፤ "ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ" ቍ. 61-67፣ ገጽ 367-368 ይመልከቱ።

510 "ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 53፣ ገጽ 313፤ "ቅዳሴ ማርያም" ቍ. 127፣ ገጽ 182 ይመልከቱ።

511 "ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 54-55፣ ገጽ 313-314፡፡

እነዚሁ ዐረፍተ ነገሮች ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት ውስጥ ይገኛሉ፤ ብቸኛው ልዩነት የሠለስቱ ምእት ቅዳሴ "ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ [መጻጻንና] ከርቤን ጠጣ"[512] ማለቱ ነው፡፡ ከዚሁ ከቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሳንወጣ፥ "የማይሞተው ሞተ፥ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ፤ ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ"[513] የሚለው አገላለጽ፥ ቃል በቃል ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ውስጥ ይገኛል፡፡[514] እንግዲህ በተለምዶ እንደ ሚባለው እነዚህ ቅዳሴያት ከላይ ስማቸው በጠቀሱት አባቶች ከተደረሱ፥ እንዴት እነዚህ ሁሉ አንድ አይነት የጸሎት ክፍሎችና ዐረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ሊገኙ ቻሉ? ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች የሚያመለክቱት ቅዳሴያቱ በተለያዩ አገሮችና በተራራቁ ዘመናት በነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መደረሳቸውን ሳይሆን፥ የአንድ ምሁር ወይም በአንድ አገር የሚኖሩና ተመሳሳይ ጽሑፎችን ያነበቡ ሊቃውንት ሥራዎች መሆናቸውን ነው፡፡ የኋለኛውን አሳብ የሚያጠናክር ነጥብ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

## ፮. ኢትዮጵያዊ የአጻጻፍ ዘዴ

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት አይነተኛ መገለጫቸው በውስጣቸው የያዙት አስደናቂና ጥልቅ የነገረ መለኮት ትምህርት ሲሆን ለየት ያለ የአጻጻፍ ዘዴም ይታይባቸዋል፡፡ በግጥም መልክ ከተጻፈውና "ቅዳሴ ማርያም ዘቅዱስ ኅርኅርዮስ"[515] ከተሰኘው አኰቴተ ቍርባን በተጨማሪ፥ በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የምናገኘው የአጻጻፍ አይነት የሚታይባቸው በርካታ ቅዳሴያት አሉ፡፡ የቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ደራሲ በግጥም የቋጠራቸውን ስንኞች እንደሚከተለው ያስነብበናል፡-

በኀለ እንስሳ ተወድየ
አምኃ ንግሡ ተወፈየ
በከመ ሕፃናት በከየ
እንዘ ይስእል እምአጥባተ እሙ ሲሳየ፡፡
. . . በውስተ ገዳም ኀደረ

[512] "ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 95-96፣ ገጽ 205፡፡
[513] "ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 58፣ ገጽ 314፡፡
[514] "ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 35፣ ገጽ 363፡፡
[515] Osvaldo Rainery, "L'anafora etiopica inedita di Maria," *Miscellanae Bibliothecae Apostolicae Vaticanae,* Vol. VII (2000) p. 338.

እምኀበ ዲያብሎስ ተመከረ
በኃይለ መለኮቱ መኳንንተ ጽልመት ሠዐረ፡፡[516]

እንግዲህ ቅዳሴው እንደስያሜው በቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ ከተደረሰ፥ ይህ ቅዱስ ይጽፍ የነበረው በግሪክ ቋንቋ ስለሆነ ወደ ግእዝ የተተረጐመው ንባብ እንዴት ሊገጥም (ቤት ሊመታ) ቻለ? እንደሚታወቀው ንጉሥ ዳዊት መዝሙራቱን በዕብራይስጥ ቋንቋ የጻፈው በግጥም ነበር፤ ነገር ግን የመዝሙረ ዳዊት የግሪኩም ሆነ ከግሪክ ወደ ግእዝ የተመለሱት መዝሙራት ግጥምነታቸውን አጥተዋል፡፡ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ" በሚል ስያሜ የሚታወቀው ቅዳሴ፥ ትርጉም ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ድርሰት ነው ለማለት እንገደዳለን፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰቶች አራት መገለጫ ባሕርያት የሚታይባቸው ቅዳሴያት የዚህ ቅዱስ ሥራዎች እንደሆኑ ዝርዝር ማስረጃዎች ጠቅሰው አስረድተውናል፡፡ እንደ ፕሮፌሰሩ አገላለጽ፥ የአባ ጊዮርጊስ የጽሑፍ ሥራዎች መለያ ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው፡-

- የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር  በጀመረባቸው ቃላት (ሐረግ) ተከታታይ ዐረፍተ ነገሮችን መጀመር
- ተቃራኒ ሁነቶችን እያነጻጸሩ ልዩነታቸውን ማሳየት
- የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን መጥቀስ
- አዳዲስ ቃላትን መፍጠር፡፡[517]

ፕሮፌሰር ጌታቸው አርጋኖን፥ ውዳሴ መስቀል፥ እንዚራ ስብሐት እና ኆኅተ ብርሃን ከተሰኙት የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች አራቱን የአጻጻፍ ዘዴዎችን የሚያሳዩ ጥቅሶች እየጠቀሱ ይኸው የአጻጻፍ ዘዴ የሚታይባቸውን የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ለምሳሌ አባ ጊዮርጊስ በጀመረበት ቃል ተከታታይ ዐረፍተ ነገሮችን ሲጽፍ አርጋኖን በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፡-

- መኑ እምከፈለኒ ከመ እኩን ህልወ ኀበ ውእቱ ማኅበር?

---

[516] "ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 17-20፣ ገጽ 360-361፡፡ ቤት የማይመታው የአማርኛ ትርጉም፡- "በእንስሳት በረት ተጨመረ፤ የንግሥኑም እጅ መንሻ ተቀበለ፤ ከእናቱ ጡቶች ምግብን እየለመነ እንደ ሕፃናት አለቀሰ፡፡ . . . በገዳም አደረ፤ ከዲያብሎስ ዘንድ ተፈተነ፤ የጨለማን መኳንንት በአምላክነቱ ኃይል ሻረ" ይላል፡፡
[517] Getatchew Haile, "On the Authoriship of Ethiopian Anaphoras," p. 12-13.

- መኑ እምከፈለኒ አአምኀ ኀለ ኀበ ሰከበ ሕይወተ ምውታን?
- መኑ እምከፈለኒ ከመ እስዐም ምድረ ኀበ ኬደ ነሶሳወ እግራ ለወለተ መድኀኒት?
- መኑ እምከፈለኒ ከመ ይልክፈኒ ጽላሎታ ለወለተ ሣህል?[518]

ተቃራኒ ሁነቶችን ደግሞ እንደሚከተለው ያነጻጽራል፡-

- ኢሀሎኩ በሥጋ፡ ሀሎኩ በመንፈስ፤
- ኢሀሎኩ በህላዌ፡ ሀሎኩ በአሚን፤
- ኢሀሎኩ በግጻዌ፡ ሀሎኩ በሃይማኖት፤[519]

እነዚህ እና የተቀሩት የአጻጻፍ ዘዴዎች በተለያዩ ቅዳሴያት ውስጥ ስለሚገኙ፥ ቅዳሴያቱ የአባ ጊዮርጊስ ሥራዎች ለመሆናቸው በቂ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ቅዳሴ አትናቴዎስ ውስጥ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር  በጀመረበት ቃል የሚቀጥሉ ተከታታይ ዐረፍተ ነገሮችን እናገኛለን፡-

- ወኢመኑሂ ኢየሀሉ ዝየ በመዓት ምስለ እኁሁ፤
- ወኢመኑሂ ኢየሀሉ ዝየ በተቃርኖ፤
- ወኢመኑሂ ኢየሀሉ ዝየ በተጓሕልዎ፤[520]

ሁለተኛውን የአጻጻፍ መንገድ በቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ እንደሚከተለው እናነባለን፡-

- ወፈነውኮ ለወልድከ ኀቤነ፡፡ መጽአ እንዘ ኢይወፅእ እምኀቤከ፤ ነገደ እንዘ ኢይትሐወስ እምኔከ፤
- ነበረ ኵለንታሁ ኀቤከ፤ ወፈነውኮ ኀቤነ እንዘ ኢይትፈለጥ እምኀቤከ…፤
- ነበረ ሰማያተ ኀበ አቡሁ፡ እንዘ ሀሎ ምድረ ምስለ ወላዲሁ፤
- ወረደ እንዘ ኢየሐጽጽ እምላዕሉ፡ ወኢይትዌሰክ በታሕቱ፡፡[521]

ኆኅተ ብርሃን በተባለው መጽሐፉ አባ ጊዮርጊስ እመቤታችንን፡- “አ መድኀኒቱ ለአዳም፥ ወምውካፈ መሥዋዕቱ ለአቤል፥ ወመስተባዝኂተ አዝርእቲሁ ለሴት፥ ሕይወተ ነፍሱ ለሄኖክ፥ ወኑኀ መዋዕሊሁ ለማቱሳላ፥ ዕረፍቱ ለላሜሕ፥ ታቦት አንተ

[518] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 14፡፡
[519] ዝኒ ከማሁ፡፡
[520] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 21፤ “ቅዳሴ አትናቴዎስ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 5-7፣ ገጽ 215፡፡
[521] Getatchew Haile, “On the Authoriship of Ethiopian Anaphoras,” p. 25፤ “ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 30-31፣ ገጽ 144፡፡

ኖኅ፥ ሀብተ ጺጋሁ ለሴም፥ ወሀብተ ቡራኬሁ ለያፌት”[522] በማለት እንደጠራት፥ ይህን የሚመስል ምሳሌያዊ አገላለጽ በቅዳሴ ማርያም ይገኛል፡- “አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም . . . ፥ የውሃቱ ለአቤል ዘተቀትለ በዓመፃ፥ ኂሩቱ ለሴት ወምግባራቲሁ ለሄኖክ፥ ታቦት እንተ ኖኅ . . . ፥ ቡራኬሁ ለሴም . . . ፡፡”[523] አዳዲስ ቃላትን በመፍጠር የሚታወቀው የኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ድርሰት ስለመሆኑ ከላይ ማስረጃ ያገኘንለትና በወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ስም የተሰየመው ቅዳሴ (ዘወልደ ነጎድጓድ) “መጽለብት”(መስቀል) እና “ምሕጽና”[524] (አደራ) የሚሉ ቃላትን ያስነብበናል፡፡ ስለዚህ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ጥናታቸውን ሲያጠቃልሉ፥ ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ቅዳሴያት (ቅዳሴ አትናቴዎስ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፥ ቅዳሴ ማርያም) እና የአባ ጊዮርጊስን የአጻጻፍ ዘዴ በግልጽ የሚያንጸባርቁት ተጨማሪ ቅዳሴያት (ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት እና ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ) የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡[525] በአባ ጊዮርጊስ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ግብፃዊ ጳጳስ አባ በርተሎሜዎስ፥ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ለአንድ አይሁዳዊ በሰጠው መልስ ደስ ተሰኝቶ ቅዳሴያትን እንዲደርስ እንደ ፈቀደለትና ሊቁም የተለያዩ ጸሎታተ ቅዳሴን እንደደረሰ በገድለ አባ ጊዮርጊስ መጠቀሱ[526] ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የደረሱበትን ድምዳሜ ያጠናክራል፡፡

## 3.3. የቅዳሴያቱ ስያሜያት እንዴት ተመረጡ?

በሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቻቸው የምንኮራባቸውና በወርቃማው ዘመን (14ኛው-15ኛው ምእት ዓመት) የነበሩ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የተለያዩ ቅዳሴያትን ከደረሱ በኋላ ድርሰቶቻቸው ውስጥ ስማቸውን ያልጠቀሱበት ምክንያት ይህን ቢያደርጉ ተቀባይነትን እንደማያገኙ ስለገባቸው ነው፡፡ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

---

522 Getatchew Haile, “On the Authoriship of Ethiopian Anaphoras,” p. 18-19፡

523 “ቅዳሴ ማርያም” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 31፣ ገጽ 168፡፡

524 Getatchew Haile, “On the Authoriship of Ethiopian Anaphoras,” p. 25፤ “ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 52 እና 57፣ ገጽ 148-149፡፡

525 Getatchew Haile, “On the Authoriship of Ethiopian Anaphoras,” p. 31-36፡፡

526 *Vie de Georges de Saglā* [ገድለ አባ ጊዮርጊስ], CSCO, Vol. 492*,* Tom, 81, Scriptores Aethiopici, ed. Gérard Colin (Louvain: Aedibus E. Peeters, 1987) p. 25.

መጽሐፈ ሰዓታት እንኳን መጀመሪያ ላይ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በማይክሮ ፊልም ኮፒ ተደርጎ ይህ የመለያ ቊጥር (EMML 2275, ff. 233v-240v) የተሰጠውን የብራና ተአምረ ማርያም ለኅትመት አብቅተው እንዳስነበቡን፥ የአባ ጊዮርጊስን ሰዓታት ከመጥላቱ የተነሣ ወደ ገዳሙ እንዳይገባ ያደርግ የነበረ አንድ አበ ምኔት መጽሐፈ ሰዓታትን የተቀበለው በራእይ ተነጥቆ ወደ ሰማያት ከተወሰደ፥ አባ ጊዮርጊስ በአርጋኖነ ውዳሴ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ሲያመሰግን ከሰማ እና በሰማያት ለአባ ጊዮርጊስ የተሰጠውን የክብር ቦታ ካየ በኋላ ነው፡፡ [527] ስለዚህ አባ ጊዮርጊስም ሆነ በስም የማይታወቁት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የደረሷቸውን ቅዳሴያት ቤተ ክርስቲያኒቱ እውቅና በሰጠቻቸው አባቶች ስም ለመሰየም ተገደዱ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሊቅ ለደረሰው አኰቴተ ቊርባን መጠሪያ የሚሆን የቤተ ክርስቲያን አባት ስም ሲመርጥ እንዲሁ በዘፈቀደ ሳይሆን ከቅዳሴው ይዘት ጋር የሚመሳሰል ድርሳን [528] ያለው አባት በጥንቃቄ እየተፈለገ እንደነበር የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች አሉ፡፡

ለምሳሌ ቅዳሴ ማርያም ለአባ ሕርያቆስ የተሰጠበት ምክንያት ወይም የቅዳሴው ደራሲ አባ ሕርያቆስን የመረጠበት ምክንያት የብህንሳው ኤጲስቆጶስ ስለእመቤታችን የተለያዩ ድርሳናትን በመድረስ ስለሚታወቅ ነው፡፡ “መጽሐፈ ዕርገታ ለማርያም” የተሰኘው መጽሐፍ እና በአባ ሰላማ መተርጉም አማካኝነት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጒሞ መጽሐፈ ግብረ ሕማማት ውስጥ የገባው “ላሐ ማርያም” (የማርያም ለቅሶ) የተባለው ድርሳን የአባ ሕርያቆስ ዘብህንሳ ሥራዎች እንደሆኑ ይታመናል፡፡[529] ከመጀመሪያው መጽሐፍ ጋር ተመሳሳይነት ያለው “ድርሳን ዘይነግር ዘከመ ተረክበ ዜናሃ ለቅድስት ማርያም”[530] ደራሲም አባ ሕርያቆስ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ስለዚህ የአባ ሕርያቆስን ድርሳናት የሚያውቀው የቅዳሴ ማርያም ደራሲ፥ ስለትሕትና የራሱን ስም ሳይነግረን ቅዳሴው በአባ ሕርያቆስ ስም እንዲጠራ መረጠ ማለት ነው፡፡

---

[527] Getatchew Haile, “On the Wrtings of Abba Giyorgis Säglawi from Two Unedited Miracles of Mary,” *OCP* (1982) pp. 65-91.

[528] Homily/ theological treatise.

[529] Verena Böll, “Ǝrgäta lämaryam,” *EA,* Vol, 2, p. 354.

[530] Basil Lourié, “Cyriacus of Jerusalem,” *EA,* Vol, 1, p. 843-844.

እዚህ ላይ የቅዳሴው ደራሲ ማንነት በተሻለ ማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ የተለያዩ ግምቶች እንደ ነበሩ መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ እ.አ.አ. በ1983 በጻፉት ጥናታዊ ጽሑፍ በቅዳሴ ማርያምና ውዳሴ ማርያም መካከል ያሉ ተመሳሳይ ዐረፍተ ነገሮችን መርጠው ካወጡና የቅዳሴው ደራሲ ውዳሴ ማርያምን በየዕለቱ በግእዝ ቋንቋ የሚደግም ኢትዮጵያዊ ሊቅ ሊሆን እንደሚችል ከጠቆሙ በኋላ[531] የደራሲውን ማንነት ለመገመት የሚከተለውን የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ታሪክ መነሻ በማድረግ ተጠቅመዋል፡-[532]

> ["ከባሕር ወዲህስ ማን አምጥቶልናል?"] ቢሉ፥ ቅዱስ ያሬድ ማይ ኪራህ መደበይ ታብር በሚባል ቦታ ይኖር ነበር፡፡ እመቤታችን ኤፍሬምን ከሶርያ፥ አባ ሕርያቆስን ከብህንሳ በደመና ጠቅሳ ያሬድ ካለበት አድርሳ፥ ["አንተ ውዳሴዬን፥ አንተ ቅዳሴዬን ነግራችሁት በዜማ ያድረስ"] ብላ፥ ነግረውት በዜማ አድርሶታል፡፡[533] ከዚህ አያይዞ ዐሥራ ሦስቱን [ቅዳሴያት] ሁሉ በዜማ ደርሷል፤ ይህም ሊታወቅ ሥረይ በቅዳሴ ማርያም ይበዛል፡፡
>
> ["ከተከዜስ ወዲህ ማን አምጥቶልናል?"] ቢሉ፥ ሳሙኤል ትውልደ ጌዴዎን ዘገበዘ አክሱም ይለዋል፥ እሱ አምጥቶልናል፡፡ እሱም ይኸን እየደገመ ሲሄድ ክንድ ከስንዝር ከመሬት መጥቆ ይሄድ ነበር፡፡ [ከዕለታት አንድ ቀን] ይኸን ደግሞ ውኃውን ቢባርከው ኅብስት ሁኖለት ተመግቦ ምእመናንን መግቧቸዋል፡፡ "ሶበ አተቦ ለማይ በቅዳሴኪ እንዘ ይጼሊ፡፡ ረሰዮ ኅብስተ ጽጌ ሃይማኖት ሳሙኤል ዘሐቅለ ዋሊ፡፡ ምሕረተ ወፍትሐ ለተአምርኪ እኅሊ፡፡ ሥረዩ ኃጢአትየ ወዕፀብየ አቅልሊ፡፡ እስመ ኵሎ ገቢረ ማርያም ትክሊ" እንዳለ ደራሲ፡፡[534]

"ከተከዜ ወዲህ ቅዳሴ ማርያምን አምጥተውልናል" የተባሉት አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ጸሎተ ቅዳሴውን ሲደግሙ ከተደረጉላቸው ተአምራት በተጨማሪ፥

---

[531] Getatchew Haile, "On the Identity of Silondis," pp. 379-382.

[532] *ቅዳሴ ማርያም አባ ሕርያቆስ የደረሰው፡ ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደ ተረጎሙት* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፡ 1983 ዓ.ም.) ገጽ 8፡፡

[533] አረጋዊው ሊቀ ጳጳስና የበርካታ መጻሕፍት ደራሲ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በታሪኩ የተጠቀሱት ሦስቱ ቅዱሳን የነበሩበትን የተለያዩ ዘመናት ጠቅሰው "ቅዱሳኑ የተገናኙት በአካለ ነፍስ ነው ቢባል የተሻለ ነው" የሚል አሳብ ያነሣሉ፡፡ ቋንቋቸውም የተለያየ ስለነበር የተግባቡበትም ቋንቋ ጥያቄ እንደሚፈጥር ጠቁመዋል፡፡ በትውፊት፥ ግብጻዊው አባ ሕርያቆስ ደረሰው የተባለው ቅዳሴ በግብጻውያን ዘንድ ስለማይታወቅና አጠቃላይ ይዘቱ ትርጒም ስለማይመስል የተለያዩ ምሁራን እንዳረጋገጡት "ፍጹም ኢትዮጵያዊ ድርሰት ነው" የሚል አመለካከትም አላቸው፡፡ አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ፥ *የቅዳሴያችን ይዘት* (ቶሮንቶ፡ ጣና ማተሚያ ቤት፡ 2003 ዓ.ም.) ገጽ 46-47፡፡

[534] "እንዳለ ደራሲ" ያለው ጥቅሱ የተወሰደበት የማኅሌተ ጽጌን ደራሲ (አባ ጽጌ ድንግልን) ነው፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾላቸው በቅድስት ድንግል እናቱ ስም አኰቴተ ቍርባን ያከብሩ ዘንድ እንደነገራቸው በተአምረ ማርያም ተዘግቧል፡፡ [535] እመቤታችንም ለአባ ሳሙኤል ተገልጻላቸው፥ እርሳቸውም ሆኑ የመንፈስ ልጆቻቸው ቅዳሴዋን መድገም እንዳያቋርጡና በዚህ ቅዳሴ የሚጠራትን ሰው በጣም እንደምትወደው መናገሯን የሚዘግብም ተጨማሪ ተአምር አለ፡፡ [536] ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ከላይ የተጠቀሱ ነጥቦችን መሠረት በማድረግ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አሳብ አቅርበው ነበር፡፡[537] ነገር ግን ፕሮፌሰሩ በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፍ፥ አባ ሳሙኤል በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ስለማይታወቁ፥ እንዲሁም የቅዳሴ ማርያም የአጻጻፍ ዘዴና በውስጡ የያዘው ትምህርተ መለኮት የቅዳሴው ደራሲ በሚደነቁ የትምህርተ ሃይማኖት ድርሰቶቹ የሚታወቀው አባ ጊዮርጊስ ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል፡፡[538] ይህም በመረጃ ተደግፎ የሚቀርብ ጥናታዊ ጽሑፍን የሚቀበል ሰው ሁሉ ሊስማማበት የሚችል አመለካከት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ቅዳሴ ማርያም በ14ኛው እና 15ኛው ምእት ዓመታት አገራችን ውስጥ ተነሥተው የነበሩ የነገረ መለኮት ክርክሮችን ይዘት እንደሚያሳይ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ደራሲው፥ ሊቃውንቱ ይወዛገቡባቸው ከነበሩት የነገረ መለኮት አስተምህሮዎች በተጨማሪ ከሌሎች ምንጮች ያገኛቸውን አሳቦችንም የቅዳሴው አካል አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ፥ ቅዳሴ ማርያም ውስጥ "አንደ ንብ ያለ ሩካቤ ከቃል ድምፅ የተገኘ ፅንስ" [539] የሚለው አሳብና በእመቤታችን ማኅፀን ለተከናወነው የሥጋዌ ምሥጢር (የትስብእትና የመለኮት ተዋሕዶ) ምሳሌ ሆኖ የቀረበው ድርና ማግ የሚዋሐዱበት የሸማኔ ጕድጓድ [540] ከቅዱስ ኤራቅሊስ

[535] EMML 22, f. 141r, Getatchew Haile, "On the Identity of Silondis," ገጽ 386 ላይ የተጠቀሰ፡፡
[536] EMML 2999, f. 243v, Getatchew Haile, "On the Identity of Silondis," ገጽ 388 ላይ የተጠቀሰ፡፡
[537] Getatchew Haile, "On the Identity of Silondis," p. 387-389.
[538] Getatchew Haile, "On the Authoriship of Ethiopian Anaphoras," p. 28.
[539] "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 83፣ ገጽ 175፡፡
[540] ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ፡ 1983፣ ገጽ 64፡፡

ዘቍስጥንጥንያ (+446 ዓ.እ.) ድርሳን የተወሰደ ነው፡፡[541] ቅዱስ ኤራቅሊስ፥ ሔዋን የእባብን ድምፅ በጆሮዋ ሰምታና ዕፀ በለስን በልታ የሞት ምክንያት መሆኗን፥ ድንግል ማርያም የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራትን በጆሮዋ ሰምታና "እነሆኝ የጌታ ባሪያ፥ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" (ሉቃ. 1፥38) ብላ በመታዘዝ የድኅነት ምክንያት ከመሆኗ ጋር ሲያነጻጽር፡- "ቀድሞ የሞት በር የነበረው፥ የድኅነት ደጅ ሆነ፡፡ ባልታዘዙ ጆሮዎች እባቡ መርዙን ረጨ፤ ሕያው ቤተ መቅደስን ለመሥራት ቃለ እግዚአብሔር በታዘዙ ጆሮዎች ውስጥ ገባ"[542] ብሏል፡፡ ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው እመቤታችን የመልአኩን ብሥራት በተቀበለችበት ቅጽበት በመለኮታዊ ጥበብ ቃለ እግዚአብሔር (ወልድ) በጆሮዋ ገብቶ በማኅፀንዋ ማደሩን ስለሆነ፥ ኢትዮጵያዊው የቅዳሴ ማርያም ደራሲ "ከቃል ድምፅ የተገኘ ፅንስ"[543] የሚለውን አሳብ ያገኘው ከድርሳነ ኤራቅሊስ እንደሆነ ያስዳናል፡፡

የቅዳሴ ማርያም ደራሲ የቅዱስ ኤራቅሊስን ድርሳን ያውቅ እንደነበር እርግጠኛ የምንሆነው ከድርሳኑ ተወስዶ ቅዳሴው ውስጥ የገባውን የምሥጢረ ሥጋዌ ምሳሌ ስንመለከት ነው፡፡ ይኸው ምሳሌ በቅዳሴ ማርያም እንዲህ ይላል፡-

> አማኑኤል የማይተረጐም የሥጋን ልብስነት ከአንቺ የለበሳት መሥሪያ ነሽ፡፡ ዝሐውን ከአዳም ጥንተ ሥጋ አደረገ፡፡ ማጉም ያንቺ ሥጋ ነው፡፡ መወርወሪያውም ቃል እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ መሕኑም ከልዕልና የወረደ የልዑል እግዚአብሔር አምሳል ነው፡፡ ሠሪውም መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡[544]

የዚህ ምሳሌ ምንጭ የሆነው የቅዱስ ኤራቅሊስ ድርሳን የእንግሊዝኛ ትርጒም ደግሞ ይህን ይመስላል፡-

> She […] is the Holy Mary; […] the workshop for the union of natures; the awesome loom of the divine economy upon which the

[541] Aloys Grillmeier, SJ., *Christ in Christian Tradition*: *The Church of Alexandria with Nubia and Ethiopia after 451,*Vol. 2, Part 4, trans. O. C. Dean Jr. (London: Mowbray, 1996) p. 353.

[542] *Proclus of Constantinople and the Cult of the Virgin in Late Antiquity, Homilies 1-5, Texts and Translations*, ed. Nicholas Constas (Leiden, Boston: Brill, 2003) Homily I, Part II, No. 35, p. 139.

[543] "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 83፣ ገጽ 175፡፡

[544] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 29፣ ገጽ 168፡፡

> robe of union was ineffably woven. The loom-worker was the Holy Spirit; the wool-worker the overshadowing power from on high. The wool was the ancient fleece of Adam; the interlocking thread the spotless flesh of the Virgin. The weaver's shuttle was propelled by the immeasurable grace of him who wore the robe; the artisan was the Word who entered in through her sense of hearing. [545]

ሁለቱን ጥቅሶች ስናወዳድር፥ የቅዳሴው ደራሲ የምሳሌውን ዋነኛ አሳቦች ብቻ እንደወሰደና የተወሰኑ ዐረፍተ ነገሮችን አንደተዋቸው እንረዳለን፡፡ የቅዱስ ኤራቅሊስ ድርሳን የተወሰነ ክፍል፥ በዘመነ አክሱም (5ኛው/6ኛው ምእት ዓመት)[546] ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግእዝ እንደተተረጐመ የሚነገርለት ድርሳነ ቄርሎስ ውስጥ ስለሚገኝ[547] ኢትዮጵያዊው የቅዳሴ ማርያም ደራሲ፥ ድርሳነ ኤራቅሊስን የመመልከት ዕድል ነበረው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡

ወደ ሌሎቹ አገር በቀል ቅዳሴያት ስያሜ ስናመራ፥ ከላይ እንደተገለጸው የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰት የሆነውና የሰንበተ ክርስቲያንን ክብር አምልቶና አስፍቶ የሚናገረው ቅዳሴ በቅዱስ አትናቴዎስ ስም የተሰየመው "ጠማር ዘወረደት እምሰማያት ላዕለ እደ አትናቴዎስ በዕለተ እሑድ"[548] የሚለውን ድርሳን ደራሲው ያውቅ ስለነበር መሆኑን ገልጫለሁ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ "ኀዳፌ ነፍስ" በተሰኘው የቅዳሴ ክፍል ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት በዝርዝር የሚያትተው *አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ* በዚህ ቅዱስ ስም የተሰየመው ያዕቆብ ዘሥሩግ ስለሙታን ትንሣኤ በሶርያ ቋንቋ ድርሳን ስለጻፈ ሲሆን፥ [549] የቅዳሴው ደራሲ ምናልባት የድርሳኑን ግእዝ ትርጕም ስላገኘው ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም የቅዳሴው ደራሲ

[545] *Proclus of Constantinople*, Homily I, Part I, No. 15, 25-20, p. 137.

[546] Getatchew Haile, "Ethiopic Literature," p. 47፤ Ricci, "Ethiopian Christian Literature," p. 976.

[547] ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ (አዘጋጅና አሳታሚ)፥ "ተረፈ ቄርሎስ ምዕራፍ ፲፰፡ ድርሳን ዘጵርቅሎስ [ኤራቅሊስ] ዘሀገረ ቂዝቆስ ዘደረሰ በቈስጠንጢኑ [በቊስጥንጥንያ]"፥ *ድርሳነ ቄርሎስ ወጸላድዮስ ምስለ ተረፈ ቄርሎስ፡ ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲነበብና ሲተረጐም የመጣው ንባቡና ትርጓሜው በአንድምታ* (ጎንደር፡ [ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ]፡ 2008 ዓ.ም.) ገጽ 735-745፡፡

[548] Getatchew Haile, "Religious Controversies," p. 131.

[549] *Jacob of Sarug's Homily on the Creation of Adam and the Resurrection of the Dead,* trans. Edward G. Mathews (Piscataway, NJ: Gorgias Press, 2014).

“ድርሳን ዘአባ ያዕቆብ በስብከተ ጌና ዘበእንተ ማርያም ወኤልሳቤጥ”[550] በሚል ርእስ ወደ ግእዝ የተተረጐመውን የቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግን ድርሳን ለቅዳሴው ድርሰት እንደተጠቀመበት የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ፡፡ አባ ቴድሮስ አብርሃ በጥናታዊ ጽሑፋቸው እንደገለጹት የቅዳሴው ደራሲ የሚከተለውን ክፍል የወሰደው ከቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ድርሳን ነው፡-[551]

> ከአብ የማይለይ ረጅም ፈትል፥ ሰማይንና ምድርን የፈጠርህ፥ በፈቃድህ ከሰማይ ወረድህ፤ የድንግል ማኅፀን ወሰነህ፥ የድሆች ልጅ ትንሽ ብላቴና ገሊላዊት አቀፈችህ፤ ነፍስዋን አከበርህ፥ *ሥጋዋንም* አነጻህ፡፡ አጸናሃት፥ ባንተ አልደነገጠችም፡፡[552]

ስለሆነም ደራሲው የቅዳሴውን መጠሪያ ለቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ለመስጠት በቂ ምክንያት ነበረው ማለት ነው፡፡[553]

በኦሪት ዘፍጥረት 1፥1 እስከ 2፥4 ያለውን የስድስቱን ቀናት ሥነ ፍጥረት መሠረት በማድረግ የሚጻፍ ጽሑፍ *ሄክሳሜሮን*[554] በሚል ስያሜ ይታወቃል፤ ስያሜው የተገኘው *ሔክሲ* (ስድስት) እና *ሂሜራ* (ቀናት) ከሚሉ ሁለት የግሪክ ቃላት ነው፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን “አክሲማሮስ”[555] የተሰኘውና የስድስቱን ቀናት ፍጥረታት የሚተርከው መጽሐፍ ተመሳሳይ የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ከሚያትቱ የሥነ ጽሑፍ *ሥራዎች*[556] የሚመደብ ነው፡፡ በትውፊት አክሲማሮስን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘደሴተ ቆጵሮስ እንደጻፈው ቢነገርም፥ ሊቃውንቱ ግን ስሙ ባልታወቀ ሰው ተደርሶ በዚህ ቅዱስ ስም እንደተሰየመ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡[557] በተመሳሳይ መልኩ፥

---

[550] EMML 1763, ff. 80b-82a, Tedros Abraha, O.F.M. Cap., “Jacob of Serug in the Ethiopiac Tradition,” ገጽ 472 ላይ የተጠቀሰ፡፡

[551] Tedros Abraha, O.F.M. Cap., “Jacob of Serug in the Ethiopiac Tradition,” p. 473፡፡

[552] “ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 21፣ ገጽ 343፡፡

[553] Tedros Abraha, O.F.M. Cap., “Jacob of Serug in the Ethiopiac Tradition,” p. 474.

[554] Hexaemeron.

[555] ይህ ቃል hexaemeron ከሚለው የግሪክ ቃል ጋር ያለውን ተመሳሳይነት ልብ ይሏል፡፡

[556] Hexaemeral literature.

[557] Roger W. Cowley, *Ethiopian Biblical Interpretation: A Study in Exegetical Tradition and Hermeneutics* (Cambridge: Cambridge University Press, 1988) pp. 123-124; August Haffner, “Das Hexaëmeros des Pseudo-Epiphanius,” *Oriens*

ስሙን ሳይነግረን፡- “ከጨለማ ለይቶ ብርሃንን ፈጠረ፤ ደመናውን መለየት ያውቃል. . . ምድርን ፈጠራት፥ መጠንዋንም አዘጋጀ… ባሕርን ከእናትዋ ሆድ በወጣች ጊዜ በበሮች አጠራት፡፡ ልብሷንም ደመና አደረገላት፥ በጉም ጠቀለላት፥ ወሰን አደረገላት፥ በውስጥዋም መዝጊያዎችንና ቊልፎችን አደረገላት …”[558] እያለ ፈጣሬ ዓለማት ልዑል እግዚአብሔር ፍጥረቱን እጅግ ውብ በሆነ መልኩ መፍጠሩን የሚተርከውን ቅዳሴ የደረሰው ኢትዮጵያዊ ሊቅ፥ ቅዳሴውን በቅዱስ ኤጲፋንዮስ ስም የሰየመው ይመስላል፡፡ ይህን ቅዱስ የመረጠበት ምክንያት ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው በትውፊት እንደሚነገረው አክሲማሮስ የቅዱስ ኤጲፋንዮስ ድርሰት መሆኑን ስለሚያውቅ ነው፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያም *ሄክሳሜሮን* የተሰኘ እና ከሥነ ፍጥረት ጋር የተያያዙ የነገረ መለኮት ጉዳዮችን የሚያትት ድንቅ መጽሐፍ ጽፏል፡፡[559] ነገር ግን ኢትዮጵያዊው ሊቅ የደረሰው ቅዳሴ ከቅዱስ ባስልዮስ ይልቅ በቅዱስ ኤጲፋንዮስ ስም እንዲጠራ የመረጠበት ምክንያት ምናልባት የባስልዮስ *ሄክሳሜሮን* ወደ ግእዝ ስላልተረጐመ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ኢትዮጵያዊው ደራሲ የቅዱስ ባስልዮስን *ሄክሳሜሮን* የሚያውቅበት አጋጣሚ ቢኖር እንኳን፥ ቅዱስ ባስልዮስ የደረሰው ቅዳሴ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ስለተተረጐመ ሁለት ቅዳሴያት በአንድ የቤተ ክርስቲያን አባት ስም ከሚጠሩ ይልቅ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ለቅዳሴው መጠሪያ ቅዱስ ኤጲፋንዮስን የመረጠ ይመስላል፡፡

በመጨረሻም፥ “የሚያውቅህ የለም፤ አንተን ማየት የሚችል የለም፡፡… የወለድኸው ልጅህ የአንተን ነገር ነገረን”[560] በሚለው አገላለጽ፥ በፍጡር ሕሊና ሊመረመር የማይችለው አምላክ ራሱን በውድ ልጁ በኩል መግለጹን የሚያስረዳው ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፥ ለምን በዚህ ወንጌላዊ ስም እንደተሰየመ ለማወቅ አያዳግትም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ለዚህ ቅዳሴ መደረስ ምክንያት የነበረው አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በ15ኛው ምእት ዓመት “መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን

---

*Christianus: Halbjahrshefte für die Kunde des Christlichen Oreints*, ed. A. Baumstark (Leipzig: Otto Harrassowitz, 1923) pp. 91-145.

[558] “ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 17-19፣ ገጽ 290፡፡

[559] Basil of Caesarea, *Hexaemeron,* A Select Library of Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christian Church, Vol. 8, ed. Philip Schaff and Henry Wace (Michigan: Eerdmans Publishing Company 1989).

[560] “ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 5 እና 9፣ ገጽ 139 እና 140፡፡

ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው" (ዮሐ. 1፥18) የሚለውን የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌልን መሠረት ያደረገ የነገረ መለኮት ክርክር ነበር፡፡ ስለሆነም የቅዳሴው ደራሲ ለድርሰቱ ስያሜ የወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስን ስም መረጠ፡፡ "ወልደ ነጐድጓድ/ የነጐድጓድ ልጅ" የሚለው አጠራርም የተወሰደው፥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘብዴዎስ ልጆች የሆኑትን ያዕቆብንና ዮሐንስን "ቦአኔርጌስ - የነጐድጓድ ልጆች" ብሎ እንደሰየማቸው ከሚገልጸው የማርቆስ ወንጌል ነው (ማር. 3፥17)፡፡

## መደምደሚያ

በዚህ ምዕራፍ ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ከሆነበት ከ4ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ በየዘመናቱ ያሳየውን እድገት ተመልክተናል፡፡ ከግብፅ እና ሶርያ አብያተ ክርስቲያን የተቀበልናቸው የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ቢኖሩም ሊቃውንቱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የአገራችንን ባህል ከግንዛቤ በማስገባት ከማንም በደፈናው ኮፒ ያልተደረገ ኢትዮጵያዊ ሥርዓተ አምልኮን ሠርተውልን አልፈዋል፡፡ ለዚህ የአባቶቻችን ሥራ እውቅና መስጠትና አገር በቀል የሆኑ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን ከውጭ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ከተተረጐሙት መለየት የእኛ ድርሻ ነው፡፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን፥ እናት ቤተ ክርስቲያናችንን ለ1600 ዓመታት ያህል ስላስተዳደረች ብቻ ሁሉም የቤተ ክርስቲያናችን የአምልኮ መጻሕፍት ከግብፅ እንደመጡ ማሰብ አላዋቂነት ብቻ ሳይሆን፥ ቅዳሴያት በመድረስና ጥልቅ የነገረ መለኮት ድርሳናትን በመጻፍ ከ14-15ኛው ምእት ዓመታት የነበሩ ሊቃውንት አባቶቻችን ለግእዝ ሥነ ጽሑፍ እድገት ያበረከቱትን ታላቅ አስተዋጽኦ ማቃለል ይሆናል፡፡

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ካሳተመቻቸው 14 ቅዳሴያት በተጨማሪ እስካሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያኒቱ እውቅና ተሰጥቷቸው ያልታተሙ ስድስት ቅዳሴያት እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ ባጠቃላይ ከአምስቱ ቅዳሴያት (ቅዳሴ ሐዋርያት፥ ቅዳሴ እግዚእ፥ ቅዳሴ ማርቆስ፥ ቅዳሴ ያእቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም) እና ቅዳሴ ባስልዮስ በስተቀር) የተቀሩት 15ቱ ቅዳሴያት በኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የተደረሱ ናቸው፡፡ የአብዛኞቹ ቅዳሴያት ደራሲም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መሆኑን የሚያመለክቱ ከበቂ በላይ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግም ወደ

ግእዝ ከተተረጐሙት ቅዳሴያት መካከል እንደሆነ የገመቱ ሊቃውንት ቢኖሩም፥ ከዚህ ይልቅ ቅዳሴውን የደረሰው ኢትዮጵያዊ ምሁር በዚሁ ቅዱስ ስም ከተሰየመው የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ[561] ብዙ አሳቦችን ወሰደ እንጂ ድርሰቱ ኢትዮጵያዊ ነው የሚለው የተሻለ ተቀባይነት ያለው ይመስላል፡፡ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱ ቅዳሴያት ከ14-15ኛው ምእት ዓመት አገራችን ውስጥ የነበሩ የነገረ መለኮት ክርክሮች ውጤት ስለሆኑ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ለየት ባለ መልኩ ጥልቅ የሆነ የነገረ መለኮት አስተምህሮን ይዘዋል፡፡ ሌላው የኢትዮጵያ ቅዳሴያትን ለየት የሚያደርጋቸው ነጥብ፥ ከ15ቱ አገር በቀል ቅዳሴያት መካከል አራቱ (ቅዳሴ ማርያም ዘሕርያቆስ፥ መዓዛ ቅዳሴ ዘአባ ጊዮርጊስ፥ ቅዳሴ ማርያም ዘጎርጎርዮስ [ዘእንዚናዙ] እና ቅዳሴ ማርያም ዘጎርጎርዮስ [ዘአርማንያ፤ ከሣቴ ብርሃን]) በእመቤታችን ስም መሰየማቸው ነው፡፡ ይህም የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክንን በዓለም ልዩ ያደርጋታል፡፡ አራተኛና የዚህ መጽሐፍ መጨረሻ በሆነው በሚቀጥለው ምዕራፍ፥ በየዘመናቱ የተነሡ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከተለያዩ መጻሕፍት የተወሰዱ ዝማሬያትን በመጨመርና የሥርዓተ ቅዳሴውን ቅደም ተከተል[562] መልክ በማስያዝ ያሳዩትን ብቃትና የቅዳሴውን አጠቃላይ ይዘት እንመለከታለን፡፡

[561] Habtemichael Kidane, “A Note on the Aspects of the Epiclesis of the Gəʼəz Anaphora of St. James of Sərug,” *Rites and Rituals of the Christian East,* eds. Bert Groen, Daniel Galadza, Nina Glibetick and Gabriel Radle, Eastern Christian Studies, Vol. 22 (Leuven: Peeters, 2014) p. 154.

[562] Liturgical structure.

# ምዕራፍ አራት

## የቅዳሴ አጠቃላይ ይዘት

በምዕራፍ ሦስት ለመግለጽ እንደሞከርኩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግሪክ፥ ከሶርያና ከዐረብኛ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተተረጐሙ የተለያዩ የቅዳሴ መጻሕፍትንና ድርሳናትን ተቀብላለች፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ለቤተ ክርስቲያናችን የሾመልን የመጀመሪያው ጳጳስ አባ ሰላማ (ከሣቴ ብርሃን)፥ በላቲኑ *ኦርዶ ኮሚዩኒስ*[1] (*ሥርዓተ ቅዳሴ*) በሚል ስያሜ የሚታወቀውን የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ክፍልን እንዳመጣልን ይታመናል፡፡ ነገር ግን ሊቃውንቱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከግብፅ የተቀበሉትን (*ሥርዓተ ቅዳሴ* እንደወረደ ወደ ግእዝ ተርጕመው አላስቀመጡትም፡፡ ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት አንዳንድ ዝማሬያትን እያስገቡ፥ እንዲሁም ከመጽሐፈ ሲኖዶስና ከመጽሐፈ ኪዳን የተለያዩ ትእዛዛት፥ ሊጦናት እና ጸሎታተ ቅዳሴ አውጣጥተው በተገቢው ቦታ እያስቀመጡ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን *ሥርዓተ ቅዳሴ* የተለየ ብሔራዊ (ኢትዮጵያዊ) *ሥርዓተ ቅዳሴ*ን አስረክበውን አልፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ከግብፅ ይላኩ የነበሩት ሊቃነ ጳጳሳት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መካከል አንድ ዓይነት ዶግማና *ሥርዓተ አምልኮ* እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት ነበራቸው፡፡ ነገር ግን የትምህርተ ሃይማኖት ልዩነት ባይኖርም ሊቃነ ጳጳሳቱ የግእዝን ቋንቋ ስለማይረዱ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቱ በ*ሥርዓተ አምልኮ*ው ላይ ያደረጉትን ለውጥ ማስቆም አልቻሉም፡፡[2] በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ቅዱሳን መካናትን ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ በኢየሩሳሌም ያሉ የተለያዩ *ሥርዓተ አምልኮ* ዓይነቶችን የመመልከት እድል ስለነበራቸው፥ ከዚያ የወሰዷቸውን አንዳንድ *ሥርዓቶች* ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በማስገባት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ልዩ ውበት ሰጥተውታል፡፡ ነገር ግን

---

[1] *Ordo communis* - Bausi, "Qəddase: Mäṣḥafä qədasse," *EA,* Vol. 4, p. 280.

[2] Habtemichael Kidane, "Does the Ethiopian Pre-Anaphora Maintain the Egyptian Preparatory Service? Towards a Study of the Sərə'ata Qəddase," *Proceedings of the First International Conference on Ethiopian Texts,* eds. Daniel Assefa and Hiruy Abdu (Addis Ababa: CFRRC Press, 2016) p. 76.

እነዚህ ሁሉ ለውጦች መቼ እንደተካሄዱ በእርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም፤ እኛ የተረከብነው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ በየዘመናቱ ያሳያቸውን እድገቶች በዝርዝር የሚያስረዳ ጥናትም እስካሁን አልተካሄደም፡፡ [3] በዚህ ምዕራፍ ለሥራዎቻቸው እውቅና ሰጥተን ልናደንቃቸውና ልንኮራባቸው የሚገቡ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የሥርዓተ ቅዳሴውን አጠቃላይ ይዘት አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ያደረጉትን ጥረትና ጥናታዊ ገለጻ የሚያስፈልጋቸውን የቅዳሴውን ዋና ዋና ክፍሎች እንመለከታለን፡፡

## 4.1. ሦስቱ የቅዳሴ ክፍሎች

የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ "ሥርዓተ ቅዳሴ" እና ፍሬ ቅዳሴ (አኰቴተ ቍርባን) የሚሉ ርእሶች የተሰጣቸው ሁለት ዋና ዋና ክፍሎችን ያሳየናል፡፡ የአብነት መምህራን ደግሞ ቅዳሴውን እንደሚከተለው በሦስት ክፍሎች ይከፍሉታል፡-[4]

- የዝግጅት ክፍል ("ሥርዓተ አበዊነ ግብፃውያን" ከሚለው እስከ "ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት")[5]
- ሥርዓተ ቅዳሴ (ከ"ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት" እስከ "ወንትመጦ እንበለ ኵነኔ")[6]
- ፍሬ ቅዳሴ (አኰቴተ ቍርባን)፡፡[7]

ነገር ግን ከላይ ባለው አከፋፈል "ሥርዓተ ቅዳሴ" ውስጥ የተካተተውና "ጸሎተ እንፎራ" [8] የሚል ርእስ የተሰጠው ጸሎት፥ በመካከለኛው ዘመን [9] ቅዳሴው

[3] Alessandro Bausi, "Qəddase: Mäṣḥafä qədasse," *EA,* Vol. 4, p. 279.
[4] Emmanuel Fritsch, "Qəddase," *EA*, Vol.4, p. 273.
[5] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 4-23፡፡
[6] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 23-86፡፡
[7] ለምሳሌ "አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት" (ቅዳሴ ሐዋርያትን) እና "ወእምድኅረ ተመጠዉ ሕዝብ" (Post-communion service) መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 87-124 ይመልከቱ፡፡
[8] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 46-49፣ ገጽ 34-35፡፡ ጸሎቱ ይህን ስያሜ ያገኘው "Anaphora" ከሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ ስለዚህ አባ አማኑኤል እንደተረጎሙት "Prayer of the Anaphora or of the offering" የሚል አቻ ስያሜ ሊሰጠው ይችላል - Emmanuel Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," *Rites and Rituals of the Christian East: Proceedings of the Fourth International Congress of the Society of Oriental Liturgy, Beirut, Lebanon, 10-15*

ከመጀመሩ በፊት በኅብስቱና በጽዋው ላይ የሚጸለይ የዝግጅት ጸሎት ስለነበርና[10] አሁንም የጸሎቱ አገልግሎት ይኸው ስለሆነ የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ መካተት አለበት፡፡ ስለዚህ በዓለም አቀፋዊ የሥርዓተ አምልኮ ትምህርት ዘርፍ[11] መሠረት የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ እንደሚከተለው ለሦስት ይከፈላል፡-[12]

- 1) የዝግጅት ክፍል:-[13] ዲያቆናቱ በቤተልሔም፥ ሠራዒው ካህን መንበሩ ላይ ከሚያደርጉት ዝግጅት ጀምሮ ሠራዒው ካህን  በአራቱ ማዕዘናት "ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ" እያለ እስከሚያጥንበት ድረስ ያለው፡፡
- 2) የትምህርት ክፍል:- [14] የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት በሠራዒው ዲያቆን ከሚነበብበት ጀምሮ እስከ ንባበ ወንጌል፡፡[15]
- 3) ፍሬ ቅዳሴ (ቅድመ አኰቴተ ቍርባን እና አኰቴተ ቍርባን):-[16] ሠራዒው ዲያቆን "ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን" ብሎ ያልተጠመቁ ሰዎችን ከሚያሰናብትበት ጀምሮ "ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት" በማለት ካህናቱና ምእመናኑ የተቀደሰች ሰላምታ እንዲለዋወጡ እስከሚያዝበት ድረስ ያለው (ቅድመ-አኰቴተ ቍርባን) እና ለዕለቱ የተመረጠው አኰቴተ ቍርባን፡፡

---

*July, 2012*, eds. Bert Groen, Daniel Galadza, Nina Glibetić and Gabriel Radle, Eastern Christian Studies, 22 (Leuven: Peeters Publishing House, 2014) p.175. ነገር ግን እዚህ ላይ "Anaphora" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በተለመደው ትርጉሙ "eucharistic prayer" (አኰቴተ ቍርባንን) ሳይሆን የቅዳሴውን መሥዋዕት ነው፡፡

[9] Medieval period.

[10] Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 177.

[11] Liturgiology.

[12] Fritsch, "Qəddase," *EA*, Vol.4, pp. 273-274.

[13] Preparatory Service/ Introduction to the Liturgy.

[14] Lections/ Liturgy of the Word.

[15] Homily (ትምህርተ ወንጌል) የቅዳሴው ክፍል ስለሆነ ሠራዒው ካህን ወንጌሉን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ በእርሱ ወይም በሌላ መምህር የወንጌል ትምህርት መሰጠት አለበት፡፡

[16] Pre-anaphora and anaphora/ Liturgy of the Eucharist.

# ፩. ሥርዓተ ቅዳሴ

## የዝግጅት ክፍል

የዕለቱ ቀዳሾች ልኡካን (ሦስት ዲያቆናትና ሁለት ካህናት) እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ከታጠቡ በኋላ ዲያቆናት "ቤተ ልሔም"[17] በተሰኘችውና ከመቅደሱ ፊት ለፊት በስተ ምሥራቅ በኩል በተሰራችው ትንሽ ቤት ኅብስቱንና ወይኑን ያዘጋጃሉ፡፡ ለጸሎት ከመዘጋጀታችን በፊት እጃችንን መታጠብ እንደሚገባን የሚጠቁሙ ጥንታውያን መጻሕፍተ ሥርዓት አሉ፡፡ ለምሳሌ ከቀኖናተ አቡሊዲስ (ሂጶሊጦስ) ተወስዶ መጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የገባው ዝማሬ በመንፈቀ ሌሊት ፍጥረታት በሙሉ አምላካቸውን እንደሚያመሰግኑ ይገልጽና ለጸሎት እኩለ ሌሊት ላይ የተነሣውን አማኝ "ተሐጺበከ በማይ ጸሊ- በውኃ ታጥበህ ጸልይ"[18] ይለዋል፡፡ አስተናጽሖ[19] በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ እንደነበርና አማንያን ለአምልኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባታቸው በፊት እንዲታጠቡ በር ላይ ውኃ ይዘጋጅ እንደነበር ዓለም አቀፍ እውቅናን ያገኘው የሥርዓተ አምልኮ ምሁር ሮበርት ታፍት ጽፏል፡፡[20]

ቅዳሴውን የሚመራው ሠራዒ ካህን ራሱን እያዘጋጀ የሚጸልያቸው የተለያዩ ጸሎታት፡- "ሥርዓተ አበዊነ ግብፃውያን" የሚል ርእስ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን ጸሎታቱ ለእርሱ ብቻ ሳይሆኑ አብረውት ለሚያገለግሉ ካህናትና የቅዳሴው ተሳታፊ ለሆኑ ምእመናንም ጭምር ስለሆነ የሚከተለውን ትእዛዝ እናነባለን፡-

---

[17] "በይት" እና "ልኼም" ከተባሉ ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት የተገኘ ሲሆን ቤተ ኅብስት ወይም የእንጀራ ቤት ማለት ነው፡፡ አባ አማኑኤል ይህ ስያሜ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን እንደሚታወቅ ገልጸው ኅብስቱ የሚዘጋጅበት ፅዕዱት/ምጣድ (oven) በዚሁ ስፍራ እንደሚገኝ ነግረውናል፤ ተመሳሳይ ሥርዓትም በሶርያ ቤተ ክርስቲያን አለ - Emmanuel Fritsch, "The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 170.

[18] *ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግሀ* (አዲስ አባባ፡ ተስፋ ማተሚያ ቤት፡ 1989 ዓ.ም) ገጽ 1፡፡ ፍጥረታት በሙሉ በመንፈቀ ሌሊት ልዑል እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ የሚገልጸውን ዝማሬ:-*The Apostolic Tradition of Hippolytus*, trans. Burton S. Easton (Cambridge: Cambridge University Press, 1934) ገጽ 56 ላይ ይመልከቱ፡፡

[19] Ablution.

[20] Robert Taft, *The Great Entrance: A History of the Transfer of Gifts and other Pre-anaphoral Rites of the Liturgy of St. John Chrysostom,* OCA, Vol. 200 (1978) p. 202, no. 77.

> ለቄስና ለዲያቆን ለሕዝብም ሁሉ የሚገባ፥ በየጊዜውም ሁሉ ሊሠሩት የሚገባ የቅዳሴ ሥርዓት ይህ ነው፤ እንደ አባቶቻችን እንደ ግብፃውያን ሥርዓት፡፡ ቄስም ቢሆን ዲያቆንም ቢሆን በቅዳሴ ጊዜ መጀመሪያ ይህን ቃል በግድ ያንብብ፥ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉም ሁሉ በማስተዋል ይህን ይስሙ፡፡[21]

ሥርዓቱ ይህን ትእዛዝ ቢያስተላልፍም ሠራዒው ካህን ለምእመናን አሰምቶ ስለማያነበው፥ ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል የተዘጋጁ ምእመናን ይህን የመስማት እድል የላቸውም፡፡ "*ሥርዓተ አበዊነ ግብፃውያን*" ስለተባለ ብቻ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የያዘው የዝግጅት ክፍል ጸሎት፥ ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ አይነት እንደሆነ ልናስብ እንችላለን፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ዝግጅት ክፍል ውስጥ ካህኑ የሚጸልያቸው አንዳንድ ጸሎታት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን የተወሰዱ ቢሆኑም፥ ሁለቱ ሥርዓተ ቅዳሴያት በይዘት አንድ አይነት አይደሉም፡፡ ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከውጪ በትርጉም የሚመጡ ጽሑፎች ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ በመጨመር የተለየ መልክ እንደሚሰጧቸው ነው፡፡

ከሠራዒው ካህን የዝግጅት ጸሎታት መካከል፡-"ጸሎት ዘጎርጎርዮስ ቅድመ ግብአተ መንጦላዕት"[22] የሚል ርእስ የተሰጠው *ጸሎተ መንጦላዕት*[23] የተሰኘውና ኮፕቲክ ቅዳሴ ውስጥ የሚገኘው ጸሎት ትርጉም ነው፡፡ እዚሁ ክፍል ውስጥ "[ጸሎት] እንዘ ያለብስ ታቦተ ወያስተናብር" እና "[ጸሎት] እምድኅረ ፈጸመ አስተናብሮ"[24] በሚል ርእሶች የሚታወቁት ጸሎታት፥ *የዝግጅት ጸሎት*[25] የሚል ርእስ የተሰጣቸው የኮፕቲክ ቅዳሴ ጸሎታት ትርጉሞች ናቸው፡፡ ሠራዒው ካህን ወደ መቅደሱ ውስጣዊ መጋረጃ ከመግባቱ በፊት የሚጸልያቸውን ጸሎታት ከጨረሰ

---

[21] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቊ. 1፣ ገጽ 4፡፡

[22] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 8፡፡

[23] "The Prayer of the Veil" - *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory and Cyril* (Los Angeles: Coptic Orthodox Church Diocese of Southern USA, 2001) p. 3.

[24] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ገጽ 17 እና 18፡፡

[25] "The Prayer of Preparation" – ይህ ርእስ የተሰጠውን ክፍል፡- *The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory and Cyril,* 2001, ገጽ 28 ላይ ይመልከቱ፡፡

በኋላ፥ ወደ መቅደሱ ገብቶ "ጸሎተ ባስልዮስን"[26] ይጸልይና ሦስት ጊዜ ሰግዶ "ጸሎተ ዮሐንስ"[27] የሚል ርእስ የተሰጠውን ጸሎት ይደግማል፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴው ይህ ጸሎት፥ "ዮሐንስ" በሚል ስም ከሚታወቁት ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል በየትኛው ዮሐንስ እንደተሰየመ አይናገርም፡፡ ምናልባት "ቅዱስ ለሚሆን ለዚህም ምሥጢር የበቃን አድርገን፡፡ ክፉውንም ሕሊና ሁሉ ከእኛ አርቅ፤ ነፍሳችንን የምትዋጋት ፍትወትንም አርቅልን"[28] የሚለው የጸሎቱ *ክፍል የአባ ዮሐንስ ዘቦስትራ የማስታረቅ ጸሎት*[29] ከተሰኘው ጸሎት ጋር ስለሚመሳሰል በ6ኛው ምእት ዓመት ሶርያ ውስጥ ቦስትራ በምትባል ቦታ ጳጳስ የነበረ አባ ዮሐንስ ድርሰት ሊሆን ይችላል፡፡ ከእነዚህ ጸሎታት በተጨማሪ የሠራዒው ካህን የዝግጅት ጸሎት፡- ጸሎተ ንስሓ፥ መዝሙራት ዘዳዊት (መዝ. 24፣ 60፣ 101፣ 102፣129 እና 130) እና በቅዱሳት ንዋያቱ (በማኅፈዳቱ፥ በፃሕሉ፥ በጽዋው፥ በዕርፈ መስቀሉ ወዘተ.)[30] ላይ የሚጸለዩ ጸሎታትን ያካትታል፡፡[31] በአንጻሩ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የቅድመ-ቅዳሴ የዝግጅት ጸሎት *አዕርጎተ ዕጣን* የሚል ርእስ የተሰጠው የምስጋና እና የልመና ጸሎታትን (መስተብቍዓት) ብቻ የያዘ ነው፡፡[32] ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ የዝግጅት ጸሎት "ሥርዓተ አበዊነ ግብፃውያን" የሚል ርእስ ቢሰጠውም በአሁኑ ሰዓት በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ለዝግጅት ከሚያገለግለው የጸሎት ሥርዓት ግልጽ የሆነ ልዩነት አለው፡፡

---

[26] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 9፡፡ ይህ ጸሎት የኮፕቲክ (ግብፅ) ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ አይገኝም፡፡

[27] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 10-12፡፡

[28] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 11፡፡

[29] "Prayer of Reconciliation by the Thrice Blessed John [Bishop of Bostra]" - *Holy Euchologion*, (Kitchener: St, Mary's Coptic Orthodox Church, 2004) (Third Edition) p 121; Fr. Athanasius Iskander, *Understanding the Liturgy* (Kitchener: St. Mary's Coptic Orthodox Church, 1997) p. 62.

[30] በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳቱ እነዚህ ንዋያት ቅዱሳት ላይ ጸሎት የሚያደርጉት ለአገልግሎት በሚቀደሱበት ጊዜ ብቻ ነው፤ አንድ ጊዜ በጸሎቱ ንዋያቱ ከተቀደሱ በኋላ በየጊዜው ካህናቱ ለቅዳሴ በገቡ ቍጥር ጸሎቱን አይደግሙም፡፡ William Macomber, "Ethiopian Liturgy," *CE,* Vol. 3, ed. Aziz S. Atiya (New York: Macmillan Publishing Company, 1991) p. 987.

[31] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 12-20፡፡

[32] "The Offering of Incense" - *Holy Euchologion*, pp. 1-29

## የመግቢያ ዝማሬያት[33]

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ መለያ ባሕርያት ከሆኑት መካከል አንዱ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱ ዝማሬያት በቅዳሴው የተለያዩ ክፍል ውስጥ መገኘታቸው ነው፡፡ ቅዳሴው መጀመሩን የሚያበስረው ደወል ሲሰማ ካህናቱ፥ ዲያቆናቱና የቅዳሴው ተሳታፊ የሆኑት ምእመናን ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት የተወሰዱ ዝማሬያትን ይዘምራሉ፡፡ እነዚህ የመግቢያ ዝማሬያት በተወሰነላቸው የሳምንቱ ቀናት መሠረት ይዜማሉ፡-[34]

- "እምነ በሓ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን..." (እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ላንቺ ይሁን) በማለት የሚጀምረው ዝማሬ፡- ሰኞ፥ ማክሰኞና ኀሙስ፤
- "መስቀል አብርሃ፡ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ..." (መስቀል አበራ፥ ሰማይን በከዋክብት አስጌጠ) በማለት የሚጀምረው ዝማሬ፡- ረቡዕ፥ ዓርብና ቅዳሜ፤
- "ኵሉ ዘገብራ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ..."[35] (እውነትን የሚያደርጋት ሁሉ፥ ሰንበትንም የሚያከብር እውነተኛ ነው) በማለት የሚጀምረው ዝማሬ፡- እሑድ፡፡

ከእነዚህ ዝማሬያት አንዱ ተመርጦ ከተዜመ በኋላ የሚቀጥለው ዝማሬ፡- "ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ እምእመናን..." በማለት የሚጀምር ሲሆን "ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ" (ሐዋርያት [አብጥሊስ በተባለው የመጽሐፈ ሲኖዶስ ክፍል] እንዲህ አስተማሩን) ብሎ ስለሚጨርስ ዝማሬው የተገኘበትን ምንጭ ጠቁሞናል፡፡[36]

የመጀመሪያው የመግቢያ ዝማሬ፡- እምነ በሓ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፥ *ሥርጉት* አረፋቲሃ በዕንቈ ጳዝዮን (እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን [ሆይ] ሰላም ላንቺ

---

[33] "Entrance Antiphons" - Fritsch, "The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 174.

[34] *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ* (ሎስ አንጀለስ፡ ፊደል ማተሚያ ቤት፡ 1995 ዓ.ም.) ገጽ 2፡፡

[35] ለምሳሌ ይህ ዝማሬ የተወሰደበትን የጾመ ድጓ ክፍል ይመልከቱ፡- *ጾመ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1994 ዓ.ም.) ገጽ 10፡፡

[36] በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 1፣ ገጽ 48፡ የኅዳግ ማስታወሻ ቍ. 157 ላይ የተጠቀሰውን ይመልከቱ፡፡

ይሁን፤ ግድግዳዎቿ ጳዝዮን በተባለ ዕንቍ ያጌጡ ናቸው) እያለ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ውበት ያደንቃል፡፡ ይህ ዝማሬ ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊት ኢየሩሳሌም (ለሙሽራው የተሸለመችው ቅድስቲቱ ከተማ - ራእ. 21፥ 1-3) ምሳሌ ስለሆነች፥ [37] በቅዳሴ ሰዓት ሕሊናችንን ወደ ሰማያት ከፍ አድርገን ተስፋ የምናደርጋትን ቅድስቲቷን ከተማ እንድናስብ ያደርገናል፡- "[የከተማይቱ] ቅጥር ከኢያሰጲድ የተሠራ ነበረ፥ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች፡፡ … ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም" (ራእ. 21፥ 18 እና 27)፡፡

## ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት

ሠራዒው ካህን "ሚ መጠን ግርምት ዛቲ ዕለት …" የሚለውን ጸሎት አሰምቶ እየጸለየ የቅዳሴውን መጀመር ያበሥራል፡፡ የዚህ ጸሎት ሙሉ የአማርኛ ትርጉም የሚከተለው ነው፡-

> ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት [!] ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት [!] መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድባት፤ ይህን መሥዋዕቱን የሚሰውርባትና የሚያከብርባት፡፡ በጽሙናና በመፍራት ቁሙ፤ የእግዚአብሔር ሰላም ከእኔና ከእናንተ ጋር ይሆን ዘንድ ጸልዩ፡፡[38]

ይህ ጸሎት የቤተ ክርስቲያናችንን ቅዳሴ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ጸሎቱ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ውስጥ አይገኝም፤ የተወሰደው ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን አረጋግጠዋል፡፡[39] በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ከላይ የተጠቀሰውን ጸሎት በትእዛዝ መልኩ የሚለው ዲያቆን ሲሆን፥ ቦታውም ካህኑ የመንፈስ ቅዱስን

[37] "ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም" እንዲል፡፡

[38] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 1፣ ገጽ 23፡፡

[39] Peter Fink, "Liturgical Traditions in the East," *The New Dictionary of Sacramental Worship*, ed, Peter Fink (Collegeville, MN: The Liturgical Press, 1990) p. 1270; Macomber, "Ethiopian Liturgy," p. 988; Habtemichael Kidane, "Does the Ethiopian Pre-Anaphora Maintain the Egyptian Preparatory Service? Towards a Study of the Sərə'ata Qəddase," p. 105.

መውረድ ከሚጠይቅበት ጸሎት (ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ) አስቀድሞ ነው፡፡ ለምሳሌ በቅዱስ ያዕቆብ ወልደ-ሳሊቢ አኰቴተ ቍርባን [40] ዲያቆኑ በሶርያ ቋንቋ የሚያስተላልፈው ትእዛዝ የእንግሊዝኛ ትርጉም ይህን ይመስላል፡-

> How solemn is this hour, and how awesome this time, my beloved, wherein the Holy Spirit, from the topmost heights of heaven, takes wing, descends, hovers and rests upon this Eucharist and sanctifies it. Be calm and in awe, while standing and praying, pray![41]

ይህን ጸሎት ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የወሰዱት አባቶቻችን፥ ጸሎቱ በዚያች ቤተ ክርስቲያን እንደሚሰጠው አገልግሎት ከኢትዮጵያውያን ቅዳሴያት መካከል አንዱ አኰቴተ ቍርባን ውስጥ ሊያስገቡት ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን አስተዋዮቹ አባቶቻችን ጸሎቱን የቅዳሴው መጀመሪያ ላይ ለማስቀመጥ የመረጡበት በቂ ምክንያት ነበራቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይኸውም የጸሎቱን ይዘት በማስተዋል ከምድራዊውና ከተለመደው ሰዓት[42] በተለየ መልኩ፥ በቅዳሴ ጊዜ ዘላለማዊው ሰዓት[43] ወደ እኛ እንደሚመጣ ለማስገንዘብ እንደሚጠቅም ስላሰቡ ነው፡፡

## አግብኦተ ግብር

ሠራዒው ካህን ኅብስቱን በእጁ ይዞ መንበሩን እየዞረ፡- “አቤቱ ይህን ቍርባን ያቀረቡልህን አስብ . . .” በማለት የሚጀምረውን ጸሎት ይጸልያል፡፡ በዚህ ምድር የአምላካቸውን ቅዱስ ስም አስበው ቍርባኑን ያመጡ ሰዎችን በሰማያዊ መንግሥቱ እንዲያስባቸው ይለምናል፡፡[44] ይህ ጸሎት የሚያመለክተው በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለቍርባን የሚሆነውን መባእ (ኅብስት) ምእምናን ያመጡ እንደነበር ነው፡፡ ዲያቆናትም ከምእመናን የተቀበሉትን መባአ ቍርባን የአማንያን ቅዳሴ የሚጀመ ርበት ቦታ ላይ (ያልተጠመቁ ሰዎች ከተሰናበቱ በኋላ) መሥዋዕቱ ከሚዘጋጅበት

[40] Anaphora of Saint Jacob Bar Salibi.
[41] *Holy Qurbono: The Divine Liturgy of Saint Jacob Bar Ṣalibi According to the Rite of the Syriac Orthodox Church of Antioch,* eds. His Eminence Mor Cyril Aphrem Karim and et al (New Jersey, Beth Antioch Press and Gorgias Press, 2009) p. 30.
[42] Chronos.
[43] Kairos.
[44] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፤ ቍ. 5-7፤ ገጽ 24-25፡፡

ክፍል[45] ወደ መንበሩ ያመጡት ነበር፡፡ እስከ 12ኛው ምእት ዓመት ድረስ አገራችን ውስጥ ይኸው ሥርዓት ይከናወን ነበር፡፡[46] በአሁኑ ሰዓት በግብፅም ሆነ በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያን ኅብስቱንና ወይኑን የማቅረብ ሥርዓት (አግብኦተ ግብር) የሚከናወነው የቅዳሴው መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ጸሎት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን *ጸሎተ መባእ*[47] የተወሰደ ሲሆን መጠነኛ የቃላት ልዩነት ያሳያል፡፡[48]

## አሐዱ አብ ቅዱስ . . .

እንደ መጽሐፈ ቅዳሴው ትእዛዝ፥ ቅዳሴውን የሚመራው ሠራዒ ካህን (ገባሬ ሠናዩ ካህን) ሁለት እጆቹን ዘርግቶ፥ ቀጥ ብሎ በመቆምና ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ በአንድነት፥ በሦስትነት የሚመለከውን አምላክ ፍጹምነትና ቅድስና እያወጀ በታላቅ ድምጽ ፡- "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በማለት ያዜማል፡፡[49] አንዱ አብ ቅዱስ ነው፥ አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው፥ አንዱ መንፈስም ቅዱስ ነው ለሚለውና ካህኑ ለሥሉስ ቅዱስ ላቀረበው ምስጋና[50] በእውነት እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ልዩ እና ፍጹም የሆነ የባሕርይ ቅድስና እንዳለው (ልዩ፥ ንጹሕና ቅዱስ እንደሆነ) በመመስከር፡- "በአማን አብ ቅዱስ፥ በአማን ወልድ ቅዱስ፥ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በማለት መልስ ይሰጣሉ፡፡[51]

በግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይህን የሥሉስ ቅዱስ ምስጋና፥ ንባብ በሚመስል ዜማ የሚያዜመው ቀዳሹ ካህን ሳይሆን፥ ካህኑን የሚራዳው ዲያቆን

[45] Postophorion.
[46] Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 191.
[47] "Prayer of Oblation"-*The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory and Cyril,* 2001, pp. 44-45.
[48] የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለቅዳሴ መሥዋዕት የተመረጠውን ኅብስት lamb (በግ/በግዕ) ብላ ትጠራዋለች፤ ስለዚህ መሥዋዕቱን የማቅረቡ ሥርዓተ ዑደት፡- "The Procession of the Lamb"[48] ይባላል - *Holy Euchologion*, 2004, p. 67፡፡ በሶርያ ቋንቋ *Lahamo* የሚለው ቃል ኅብስት (leavened bread) የሚል ትርጉም ይሰጠናል - Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 25.
[49] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 26፣ ገጽ 29-30፡፡
[50] Doxology.
[51] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 27፣ ገጽ 30፡፡

ነው፡፡ [52] ምእመናኑም ለምስጋናው የሚሰጡት ምንም ዓይነት መልስ የለም፡፡ እንግዲህ ሊቃውንቱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን የተቀበሉትን የምስጋና ዝማሬ፥ የተለየ ሥርዓት ሠርተውለት የዝማሬው ምንጭ በሆነው አገር እንኳን የማይታወቅና የተለየ ኢትዮጵያዊ ትርጒም እንደሰጡት ልብ እንበል፡፡

## ጸሎተ አኰቴት፤ ጸሎተ መባእ ዘሐዋርያት

"[ለእኛ] በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን" በማለት የሚጀምረው ጸሎተ አኰቴት (የምስጋና ጸሎት) ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የተወሰደ ቀጥተኛ ትርጒም ነው፡፡ [53] የግእዙ መጽሐፈ ቅዳሴ፡- "ጸሎተ አኰቴት ዘቅዱስ ባስልዮስ" የሚል ርእስ ስለሰጠው ጸሎታተ ቅዳሴ በመድረስ የሚታወቀው ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ የደረሰው የምስጋና ጸሎት እንደሆነ ጠቁሞናል፡፡ ከዚህ የምስጋና ጸሎት በኋላ በኮፕቲክ ቅዳሴ ካህኑ (በዕለቱ የተገኘው ሊቀ ጳጳስ) ፍትሐት ዘወልድን[54] ነው የሚደግመው፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ግን ከጸሎተ አኰቴት ቀጥሎ የሚመጣው ከመጽሐፈ ሲኖዶስ የተወሰደው "ጸሎተ መባእ" ነው፡፡[55] ጸሎቱ ሐዋርያዊ ትውፊት እንዳለው ለማመልከት በመጽሐፈ ቅዳሴ፡ - "ጸሎተ መባእ ዘሐዋርያት" (የሐዋርያት የመባ ጸሎት) የሚል ርእስ ተሰጥቶታል፡፡[56]

---

[52] *Holy Euchologion*, 2004, p. 69.

[53] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 43 እና 72፤ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 56-65፣ ገጽ 37-40፡፡

[54] የእንግሊዝኛው ትርጒም "The Absolution of the Son" ይላል፡፡ ከቅዳሴው በፊት አዕርጎተ ዕጣን (The Offering of Incense) በተባለው ክፍል ካህኑ ፍትሐት ዘወልድን ስለሚደግም ቅዳሴ ላይ "አግብርቲከ እለ ተልዕኩ በዛቲ ዕለት ቀሲስ ወዲያቆን . . ." ከሚለው ጀምሮ ያለውን ብቻ ይጸልያል፡፡ *Holy Euchologion*, 2004, pp. 70-71; መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 31-39፣ ገጽ 31-32፡፡

[55] ይህ ጸሎት "ትእዛዝ ሲኖዶስ" መጨረሻ ላይ ከሚገኙት 13 መስተብቊዓት (የልመና ጸሎቶች) መካከል አንዱ ነው፡፡ ጸሎታቱ፥ በመጽሐፉ እንደተሰጣቸው ቅደም ተከተል፥ የሚከተሉት ናቸው፡- ጸሎተ ነግህ ቀዳሚት፥ በእንተ ዱያን፥ በእንተ እለ ይነግዱ፥ በእንተ ዝናማት፥ በእንተ ፍሬ ምድር፥ በእንተ ማያተ አፍላግ፣ በእንተ ንጉሥ፥ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ፥ በእንተ ንኡሰ ክርስቲያን፥ በእንተ እለ ኖሙ፥ በእንተ ሰላም፥ በእንተ ማኅበር እና በእንተ ጳጳስ፡፡ *The Statutes of the Apostles or Canones Ecclesiastici*, trans. G. Horner (London: Williams and Norgate, 1904) p.79-87. (https://ia902606.us.archive.org/6/items/statutesapostle00unkngoog/statutesapostle00unkngoog.pdf - accessed on October 13/2019).

[56] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 41፣ ገጽ 33፡፡

## ጸሎተ እንፎራ[57]

የታተመው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ "ጸሎተ እንፎራ" ሲል ለሰጠው ርእስ "የኅብስት ጸሎት" የሚል ትርጒም አስቀምጧል፡፡[58] "እንፎራ" የሚለው ቃል "*አናፎራ*" ለሚለው የግሪክ ቃል ይቀርባል፤ የግሪኩ ቃል የግእዝ አቻ "አኰቴተ ቍርባን" ቢሆንም፥ "ጸሎተ እንፎራ" የሚል ስያሜ የተሰጠው "ኅብስት" የሚለውን የግእዝ ቃል ለማመልከት ነው፡፡ ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰደውና ሠራዒው ካህን ሥርዓተ ፈትቶን እያከናወነ የሚያዜመው ጸሎት፡- "ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ፥ ወፈውሰነ በዝንቱ ጵርስፎራ . . . "[59] ይላል፡፡ ጵርስፎራ ተብሎ በግእዙ የተወሰደው የግሪኩ ቃል *ፕሮስፎራ፥ መሥዋዕት* ሆኖ የቀረበ ኅብስትን[60] ያመለክታል፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴውም ጵርስፎራ ለሚለው ቃል *ሥጋሁ ወደሙ* (የጌታ *ሥጋና ደም*) የሚል ትርጒም ይሰጣል፡፡[61]

ኅብስቱን የመባረኪና የማዘጋጃ ጸሎት (ጸሎተ እንፎራ) በምሥራቁ የክርስትና ዓለም ቅዳሴያት ከሚታወቁት ጥንታውያን ጸሎታት አንዱ እንደሆነ የሚያስረዱ ጥናቶች አሉ፡፡[62] የግብፅ ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ድረስ በቅዳሴዋ የምትጠቀምበት ጸሎት ሲሆን[63] ከግሪክ ወደ ግእዝ ከተተረጐሙ ጥንታውያን ጸሎታት መካከል አንዱ

---

[57] Prayer of the *Prothesis*.

[58] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 46፣ ገጽ 34፡፡

[59] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 40፤ በተጨማሪ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 54፣ ገጽ 96 ይመልከቱ፡፡

[60] Oblation ወይም offering.

[61] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 54፣ ገጽ 96፡፡

[62] አባ አማኑኤል በ8ኛው ምእት ዓመት በተጻፈ ብራና ላይ ያገኙትን የግሪኩን የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ቅዳሴ ጸሎተ እንፎራ (Prayer of the Prothesis) ወደ እንግሊዝኛ ተርጒመው በእኛ ቤተ ክርስቲያን ከሚታወቀው ጸሎት ጋር ያለውን ተመሳሳይነት አሳይተውናል፤ የእንግሊዝኛ ትርጒማቸው የሚከተለው ነው፡- "Lord our God, who have offered yourself as an immaculate lamb for the life of the world, turn your face upon this bread and upon this cup, and make them your pure body and your precious blood in view to the communion of souls and bodies. For hallowed and glorified is [your name] . . ." ለግእዙ ጸሎተ እንፎራ በጣም የቀረበ ጸሎት የግሪኩ ቅዳሴ ማርቆስ ውስጥ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡ Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," pp. 175-176.

[63] Iskander, *Understanding the Liturgy*, p. 8.

ነው፡፡ ጸሎተ እንፎራ "ይህን ኅብስት ባርከው፤ ይህን ጽዋ አክብረው" ስለሚል፥ ካህኑ ኅብስቱንና ጽዋውን እየባረከ መንፈስ ቅዱስ በሁለቱም ላይ እንዲወርድና የጌታ ሥጋና ደም ወደመሆን እንዲለውጣቸው ለሚጸልየው ጸሎት (ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ) የማዘጋጃ ጸሎት[64] ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## በእንተ ቅድሳት

የእኛ ቤተ ክርስቲያን እናት ከነበረችው ከግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካልተቀበልናቸውና በአባቶቻችን የማስተዋል ጥበብ ቅዳሴያችን ውስጥ ከገቡት ጸሎታት መካከል "በእንተ ቅድሳት ሰላማዊት ሰላመ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ያስተሳልመነ በሣህለ ዚአሁ" በማለት የሚጀምረው ጸሎት ይገኝበታል፡፡[65] ይህም "አንድ ስለምታደርግ ሥጋውና ደሙ እግዚአብሔር አንድ ያደርገን ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን" ተብሎ የተተረጐመ ሲሆን፥ በየአንቀጹ የተዘረዘሩት ጸሎታት የእግዚአብሔር ጥባቆትና መግቦት ለፍጥረቱ ሁሉ እንዲደረግ የሚማፀኑ ናቸው፡፡[66] ዲያቆኑ እያንዳንዱን የልመና ጸሎት እያሳረፈ ሲያነብ ምእመናን "አሜን ኪርያላይሶን"[67] ወይም "አሜን ጌታ ሆይ ይቅር በለን"[68] ይላሉ፡፡ "በእንተ ቅድሳት" የተወሰደው ከመጽሐፈ ኪዳን ነው፤ የመጽሐፉ 33ኛ ምዕራፍ ለዚህ የምልጃና የልመና ጸሎት "በእንተ ሥርዓተ ቅኔ ቤተ ክርስቲያን" (ስለ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ሥርዓት) የሚል ርእስ ሰጥቶታል፡፡[69] መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያው አንቀጽ ግን እንደ ቅዳሴው "በእንተ **ቅድሳት ሰላማዊት** ሰላመ

---

[64] Pre-epiclesis - ዝኒ ከማሁ፡፡

[65] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 66፣ ገጽ 40፡፡

[66] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 68-98፣ ገጽ 40-45 ይመልከቱ፡፡

[67] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 67፣ ገጽ 40፡፡ በግሪክ ቋንቋ Κύριος (ኪሪዮስ) "ጌታ" ማለት ሲሆን፥ Κύριε ἐλέησόν (ኪሪኤ ኤሌኢሶን) "ጌታ ሆይ ማረኝ/ ማረን" ማለት ነው፡፡ የእነዚህ ቃላት መገኛ ከነናዊቷ ሴት "ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረኝ" (ማቴ. 15፥22) እና ጌታ በኢያሪኮ ያነኛቸው ሁለቱ ዕውሮች፡- "ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረን" (ማቴ. 20፥30) በማለት ያቀረቡት ልመና ነው፡፡

[68] ምእመናን በግእዙ "አሜን እግዚኦ ተሣሀለነ" ወይም በአማርኛ "አሜን አቤቱ ይቅር በለን" ማለት ሲገባቸው፥ ግሪኩንና ግእዙን አንድ ላይ አድርገው "አሜን ኪርያላይሶን፥ እግዚኦ ተሣሀለነ" ሲሉ እንሰማቸውለን፤ የሁለቱ ቃላት ትርጒም አንድ መሆኑን ካለመረዳት የመጣ የልምድ አባባል ይመስላል፡፡

[69] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 78.

ናስተበቍዕ…” ሳይሆን “በእንተ **ቅድስት ሰማያዊት** ሰላመ ናስተበቍዕ …”[70] ይላል፡፡ የግእዙ መጽሐፈ ኪዳን ትርጉም ከላቲኑ ትርጉም ጋር እንደሚስማማ ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ አረጋግጠዋል፡፡[71] ከላይ የተጠቀሰው የግእዙ መጽሐፈ ቅዳሴ ትርጉም እንደሚያመለከተው “ቅድሳት” የተባለው የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ መጽሐፈ ኪዳን ውስጥ ያለው ንባብ ግን “ቅድሳት” የሚለውን ቃል ስለማይጠቀም ሥጋውና ደሙን አያስተረጉምም፡፡ ስለዚህ ቅድስትና ሰማያዊት (ከሰማይ) ስለሆነች ሰላም፥ እግዚአብሔር በይቅርታው አንድ ያደርገን ዘንድ እንማልዳለን የሚል ትርጉም ይሰጠናል፡፡[72] የትርጉም ለውጥ ያመጡት የተወሰኑ ፊደላት ልዩነት እንደሆነ ልብ እንበል፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ምናልባት የታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ የተወሰደበት የብራና ቅዳሴ ጸሐፊ የፊደላት ግድፈት ስለፈጸመ ሊሆን ይችላል፡፡

መጽሐፈ ቅዳሴውን ያዘጋጁልን አባቶቻችን በእንተ ቅድሳትን ከመጽሐፈ ኪዳን ወስደው የቅዳሴው መጀመሪያ ቦታ ላይ[73] ለማስቀመጥ ለምን እንደመረጡ ለመረዳት ሥርዓተ ቅዳሴ ዘጽርእ[74] በሚል ስም የሚታወቀውን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ቅዳሴ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የግሪክ፥ ራሽያ፥ ሮማንያ፥ ሰርቢያ፥ ቡልጋሪያ፥ ቆጵሮስ ወዘተ. አብያተ ክርስቲያን የሚከተሉት ሥርዓተ ቅዳሴ የእግዚአብሔር መንግሥት ቡሩክ (የተባረከ) መሆኑን በማወጅ ይጀምርና በእንተ ቅድሳት ላይ እንዳሉት የልመና ጸሎቶች፥ ዲያቆኑ ለፍጥረቱ ሁሉ (ስለ ዓለም ሰላም፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ ሥልጣን ስላላቸው ሰዎች፥ ስለ ምድር ፍሬ፥ በባሕርና በየብስ ስለሚጓዙ ሰዎች፥ ስላረፉ የቤተ ክርስቲያን አባላት) የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት እና መግቦት እንዲደረግ የምልጃ ጸሎታትን[75]

---

[70] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 79፡፡
[71] Habtemichael Kidane, “Does the Ethiopian Pre-Anaphora Maintain the Egyptian Preparatory Service? Towards a Study of the Sərə’ata Qəddase,” p. 101.
[72] ዝኒ ከማሁ፡፡
[73] *Enarxis*.
[74] Byzantine Liturgy.
[75] Litanies.

ያቀርባል፡፡[76] ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱ አባቶቻችን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ ቅዳሴ ለመመልከት እድል ስለነበራቸው ከመጽሐፈ ኪዳን የወሰዱትን በእንተ ቅድሳት የትኛው ቦታ ማስገባት እንዳለባቸው ፍንጭ አግኝተዋል ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡

## ማዕጠንት ዘወርቅ

ሠራዒው ካህን "አንቲ ውእቱ" (አንቺ ነሽ) እያለ ሲያዜም ምእመናን "ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት . . ." (የእሳትን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ጥና [ጽንሐሕ] . . ." በማለት የሚጀምረውን ዝማሬ እያዜሙ መልስ ይሰጣሉ፡፡[77] ይህ ዝማሬ የተወሰደው ከኮፕቲክ ቅዳሴ ሲሆን የመዝሙሩ የእንግሊዝኛ ትርጉም *መዝሙረ ማዕጠንት ዘወርቅ*[78] የተሰኘ ርእስ ሰጥቶታል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ከዚህ ዝማሬ በፊት ካህኑና ምእመናኑ እየተቀባበሉ የሚያዜሟቸው (ንስግድ፡- ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ሠለስቱ አሐዱ፤ ሰላም ለኪ፡- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ መለኮት፤ ሰአሊ ለነ፡- ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ)[79] በኮፕቲክ ቅዳሴ ውስጥ አይገኙም፡፡ ስለሆነም ሊቃውንቱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከተለያዩ ምንጮች ወስደው የጨመሯቸው ናቸው፡፡

"ማዕጠንት ዘወርቅ" የሚለው ዝማሬ ምሥጢረ ሥጋዌን (የአምላክ ሰው መሆንን ምሥጢር - ዮሐ. 1፥14፤ 1 ጢሞ. 3፥16) ድንቅ በሆነ ምሳሌ የሚያስተምር መዝሙር ነው፡፡ በመለኮታዊ ባሕርዩ የሚያቃጥል እሳት የሆነው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለማደሪያነት በመረጣት በቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ድንግል ማርያም ማኅፀን አድሯልና የዝማሬው ደራሲ፥ ጌታን በእሳቱ ፍሕም፥ እመቤታችንን ደግሞ ፍሕሙን በሚሸከመው ጥና (ጽንሐሕ)[80] መስሎ ያስተምረናል፡፡ እዚሁ ዝማሬ ላይ ከወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል የተወለደው

---

[76] *The Divine Liturgy of Our Fathers Among the Saints John Chrysostom* (No Place given: Ad Usum Privatum, 2015) pp. 23-26.

[77] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቊ. 122፣ ገጽ 51፡፡

[78] The Hymn of the [Golden] Censer - *Holy Euchologion*, 2004, p. 72-73.

[79] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቊ. 119-121፣ ገጽ 50-51፡፡

[80] Censer.

ጌታ "ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል" እና መልካም መዓዛ እንዳለው ዕጣን "ራሱን ለአባቱ ያማረ መሥዋዕት አድርጎ ያሳረገ"[81] በሚሉ ቃላት ተገልጿል፡፡

## የትምህርት ክፍል

ቅዳሴ ለአምልኮ የሚረዱ ጸሎታትን ብቻ ሳይሆን የውስጥ ዓይኖቻችንን ብሩሃን የሚያደርገውን የእግዚአብሔርን ቃል ያካትታል፡፡ ስለዚህ በቅዳሴ ሰዓት የቅዱሳን ሐዋርያት መልእክታት ይነበባሉ፤ ሠራዒው ካህን ወንጌል ካነበበ በኋላም ትምህርተ ወንጌል [82] ይሰጣል፡፡ የምንሰማውን የወንጌል ቃል በማስተዋል እንድንሰማና የመንፈስ ፍሬያትን እንድናፈራ ይረዳን ዘንድ ቀዳሹ ካህን መፍቀሬ ሰብእ (ሰው ወዳጅ) ወደሆነው አምላክ እንዲህ በማለት ይጸልያል፡-

> አምላካችንና መድኃኒታችን ሰውንም የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ፥ ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና አገልጋዮችህን ንጹሐን ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሁሉ ዳርቻ የሰደድሃቸው አንተ ነህ፡፡ የመንግሥትህን ወንጌል ይሰብኩና ያስተምሩ ዘንድ፤ በሕዝብህ ውስጥ ያለውን ደዌውን ሁሉ፥ በሽታውንም ሁሉ ያድኑ ዘንድ፤ ከዓለም አስቀድሞ የነበረውንና የተሰወረውን ምሥጢርህንም ያስተምሩ ዘንድ፡፡
>
> አሁንም ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክልን፤ የአሳባችንና የልቡናችንን ዓይኖች አብራልን፡፡ የከበረ የወንጌልህን ቃል በመጨከን እንሰማ ዘንድ የበቃን አድርገን፡፡ የምንሰማ ብቻ አይደለም፤ እንደሰማን ልንሠራም ነው እንጂ፡፡ ስለአንዱ ፈንታ ሠላሳና ስልሳ፥ መቶም ያማረ ፍሬ [ማቴ 13፥ 23] በላያችን ያፈራ ዘንድ፥ የወገኖችህን ኃጢአት ታስተሠርይ ዘንድ፥ ለመንግሥተ ሰማያትም የበቃን ታደርገን ዘንድ፡፡[83]

## መልእክታተ ሐዋርያት

በምሥራቁም ሆነ በምዕራቡ ዓለም ባሉ የሥርዓተ ቅዳሴ አይነቶች በሁለተኛው የቅዳሴ ክፍል የቅዱሳን ሐዋርያት መልእክታት ይነበባሉ፡፡ እንደሚታወቀው በቤተክርስያናችን ቅዳሴ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት፥ ከሌሎቹም ሐዋርያት መልእክታት እና ከግብረ ሐዋርያት የተውጣጡ መልእክታት መጽሐፈ ግጻዌ[84] በሚያዘው መሠረት ይነበባሉ፡፡ በኮፕቲክ ቅዳሴ የሐዋርያት ሥራ ከተነበበ በኋላ

[81] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 122፣ ገጽ 51፡፡
[82] Homily.
[83] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 186-187፣ ገጽ 66፡፡
[84] Lectionary.

ከመጽሐፈ ስንክሳር በአጭሩ ይነበባል፡፡[85] ሠራዒው ዲያቆን ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት መካከል ለዕለቱ የተመረጠውን ከማንበቡ በፊት የሚከተለውን ይላል፡-

> ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው፥ የመንፈስ ቅዱስ [ማደሪያና] በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከቅድስት ማርያም መወለዱን የማያምን ሰው ሁሉ እንግዳ እስከሚሆን [የጌታ ምጽአት] ድረስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ የተለየ (የተወገዘ) ይሁን፡፡[86]

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን" ብሎ ስለጻፈ (1 ቆሮ. 16፥22) የዚህ አዋጅ መሠረቱ ይኸው የሐዋርያው ቃል ነው፡፡[87] ንባቡንም ከጨረሰ በኋላ የሐዋርያውን ቃለ በረከት (2 ቆሮ. 13፥14) ያሰማል፡- "ቅድስት በምትሆን በጽርሐ ጽዮን[88] በሐዋርያት ላይ የወረደው የአብ በረከት፥ የወልድ ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት (ኅብረት) [በእኔም በእናንተም ላይ] ይውረድ ዕጥፍ ድርብም ይሁን"፡፡[89] እነዚህ የዲያቆኑ ንባባትም ሆኑ የምእመናኑ መልስ (ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሠናየ መልእክት . . .)[90] የኮፕቲክ ቅዳሴ ውስጥ አይገኙም፤ የሌሎቹ ሐዋርያት መልእክታት ከተነበቡ በኋላ የእኛ ምእመናን በዜማ የሚያሰሟቸውንም መልሶች የግብፆች መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ አናገኛቸውም፡፡[91]

---

[85] *Holy Euchologion*, 2004, p. 78.

[86] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 136፣ ገጽ 55፡፡

[87] በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ዲያቆኑ ከመልእክተ ጳውሎስ አንብቦ ሲጨርስ ምእመናኑ "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" (ገላ. 1፥8) የሚለውን የሐዋርያውን መልእክት ጠቅሰው እንዲህ በማለት ያዜማሉ፡- "Paul the Blessed Saint, the Lord's Apostle said:- If one [comes] to preach to you other doctrine than we knew, be he man or angel bright, cursed be he in church's sights; doctrine all diverse arise, shooting up with many lies; [blessed] is he who first and last trusts God's truth and holds it fast." Varghese, *The Living Sacrifice*, 2005, p. 191.

[88] ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በእሳት አምሳል የተቀበሉበት ቦታ (የሐ. ሥራ 2፥ 1-4)፡፡

[89] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 136፣ ገጽ 55፡፡

[90] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 137፣ ገጽ 55፡፡

[91] *Holy Euchologion*, 2004, p. 75-78፤ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 143 እና 150፣ ገጽ 57 እና 59 ይመልከቱ፡፡

ነገር ግን መልእክታቱ ከተነበቡ በኋላ ሠራዒው ካህን የሚጸልያቸው ጸሎቶች ከኮፕቲክ ቅዳሴ የተወሰዱ ናቸው፡፡[92]

## ተፈሥሒ ኦ ዘንስእለኪ ዳኅና

"ደኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተመላሽ ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ . . ."[93] በማለት የሚጀምረው ጸሎት የተወሰደው ከመጽሐፈ ሰዓታት ዘግብፅ ነው፡፡ መጽሐፉ ለሰባቱ የጸሎት ሰዓታት[94] የተዘጋጁ የተለያዩ ጸሎቶችን የያዘ ሲሆን ከላይ የተጠቀሰው ጸሎት የሚገኘው "ጸሎት ዘነግህ" (የጠዋት/ማለዳ ጸሎት) የሚለው ክፍል ውስጥ ነው፡፡[95] ይህ ጸሎት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ[96] ውስጥ አይገኝም፡፡ ነገር ግን *አግቤያ* (ሰዓታት) የተሰኘውና በኮፕቲክ፥ ዐረብኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ የጸሎት መጽሐፍ ስላለ ካህናቱና ዲያቆናቱ ከቅዳሴ በፊት፥ ምእመናን ደግሞ ለግል ጸሎት ይጠቀሙበታል፡፡ ተፈሥሒ (ደስ ይበልሽ) ተብሎ ወደ ግእዝ የተተረጐመው የጸሎቱ የመጀመሪያ ቃል፥ መጽሐፈ ሰዓታት ዘግብፅ ላይ በዐረብኛ "*አል-ሰላሙ ለኪ*" (ሰላም ለኪ/ ሰላም ላንቺ ይሁን) ይላል፡፡[97]

## ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት

ሠራዒው ካህን ከላይ የተጠቀሰውን ጸሎት አንብቦ ከጨረሰ በኋላ ካህናቱና ዲያቆናቱ ከቅድስተ ቅዱሳን (መቅደስ) ወጥተው ቅድስት ላይ በመቆም "ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት፥ ወዝ ውእቱ ጊዜ ዕጣን ኅሩይ ..." (የማመስገን ጊዜ ይህ ነው፤ የተመረጠ የዕጣን ጊዜም ይህ ነው...)" በማለት የሚጀምረውን ጸሎት እስከ

---

92 Macomber, "Ethiopian Liturgy," p. 988; *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 132-155፣ ገጽ 54-55; ቍ. 139-141፣ ገጽ 56-57 ይመልከቱ፡፡

93 *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 155፣ ገጽ 60፡፡

94 The Seven Canonical Hours፡- ነግህ (ጠዋት/ማለዳ)፥ ሦስት ሰዓት፥ ስድስት ሰዓት፥ ዘጠኝ ሰዓት፥ ሠርክ (አሥራ አንድ ሰዓት)፥ ንዋም (የእንቅልፍ ሰዓት) እና መንፈቀ ሌሊት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ "ጸሎት በንቅወተ ዶርሆ" የተሰኘና ዶሮ በሚጮህበት ሰዓት (ከሌሊቱ አሥር ሰዓት) የሚጸለይ ጸሎት ይዟል፡፡

95 *መጽሐፈ ሰዓታት* [*ዘግብፅ*] (ሮም፡ ቫቲካን ማተሚያ ቤት፡ 1944 ዓ.ም (እ.አ.አ. 1952) ገጽ 48-49.

96 Holy Euchologion.

97 እንግሊዝኛው "Hail to you" ይላል፡፡ *The Coptic Orthodox Horologion: The Book of the Seven Nocturnal and Daylight Canonical Prayers,* trans. Fayek M. Ishak (Toronto: Coptologia Spiritual Publications, 1992) ገጽ 93 ይመልከቱ፡፡

መጨረሻው ድረስ ከምእመናን ጋር እየተቀባበሉ በዜማ ያደርሱታል፡፡ ዩጎ ዛኔቲ የተባለ የካቶሊክ መነኩሴ በዚህ ዝማሬ ላይ ያደረገውን ጥናት ከማሳወቁ በፊት የዚህ ዝማሬ ምንጭ አይታወቅም ነበር፡፡ የአገራችን የአብነት መምህራን ይህን ዝማሬ ቅዱስ ያሬድ እንደደረሰው ይናገራሉ፡፡[98] ነገር ግን እንደ ዩጎ ዛኔቲ አስደናቂ ጥናት፥ የዚህ ጸሎት ምንጭና መገኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ዩጎ ዛኔቲ በኮፕቲክ ቋንቋ በብራና ያገኘውን ንባብ ከግእዙ ጋር እያነጻጸረ ይህ የቡራኬ ዝማሬ በአንድ ወቅት የኮፕቲክ ቅዳሴ አካል እንደነበርና አሁን ግን እንደቀረ በዝርዝር ያስረዳናል፡፡[99] በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ግን እስካሁን ድረስ ይዘመራል፤ ይህ የሚያሳየው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴዋ ላይ ለውጥ በምታደርግበት ጊዜ እንኳን የእኛ አባቶች ግብፆችን በደፈናው በመከተል ሳይሆን በራሳቸው መንገድ ይጓዙ እንደነበር ነው፡፡ ከላይ ያየናቸው የተለያዩ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ክፍሎች የአገራችንን ሥርዓተ ቅዳሴ፥ መሠረቱ ከሆነው ከግብፁ ሥርዓተ ቅዳሴ፥ ፈጽሞ የተለየ በማድረግ (የተለያዩ ጸሎታትን ከመጽሐፈ ሲኖዶስና ከመጽሐፈ ኪዳን በመጨመር) ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ያበረከቱትን ታላቅ አስተዋጽኦ በግልጽ ያሳየናል፡፡

## ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት (ሠለስቱ ቅዳስያት)

ሱራፌል የተሰኙት ነገደ መላእክት፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች" (ት. ኢሳ. 6፥3) እያሉ ያለዕረፍት ለሥሉስ ቅዱስ በሰማያት ምስጋና ያቀርባሉ (ራእ. 4፥8)፡፡ ምድራዊቷም ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ የሥሉስ ቅዱስ ምስጋና (ሠለስቱ ቅዳስያት)[100] ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ታቀርባለች፡፡ ይህ ዝማሬ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሲዘመር

[98] Habtemichael Kidane, "Does the Ethiopian Pre-Anaphora Maintain the Egyptian Preparatory Service? Towards a Study of the Sərə'ata Qəddase," p. 90.

[99] Ugo Zanetti, "Voici le temps de la bénédiction . . .": Origine copte d'une hymme liturgique éthiopienne" *OCP*, Vol. 1 (2009) pp. 27-30.

[100] ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "ሠለስቱ ቅዳስያት" የሚለው ስያሜ በግሪኩ 'Trisagion' ለተሰኘው ዝማሬ አቻ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመውኛል፡፡ ዝማሬው 'Trisagion' የተባለው በተደጋጋሚ ሦስት ጊዜ ቅዱስ (thrice holy/ *agios*) የሚል ሐረግ በውስጡ ስለያዘ ነው፡፡

የነበረ ምስጋና ሲሆን ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ በነገረ ክርስቶስ ላይ አለመግባባት ተፈጥሮ አንዲቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ስትከፈል የመዝሙሩም ይዘት ተቀየረ፡፡ ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት[101] የሚለው ዝማሬ ለእያንዳንዱ የሥላሴ አካል የሚቀርብ ውዳሴ እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ለዚህም ነው ዝማሬው ስብሐት ለአብ፥ ስብሐት ለወልድ፥ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ (ዛሬም ዘወትርም) ወለዓለመ ዓለም[102] በማለት የሚጨርሰው፡፡ አባ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያ[103] (+488 ዓ.እ.) ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው የሚለው ዝማሬ ላይ "ስለእኛ የተሰቀለ፤ [አቤቱ] ይቅር በለን"[104] የሚል ዐረፍተ ነገር ስለጨመረበትና ከሦስቱ አካላት በተለየ አካሉ ሰው ሆኖ ቤዛ ይሆነን ዘንድ ስለ እኛ የተሰቀለው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ፥ ዝማሬው ለክርስቶስ የቀረበ ምስጋና[105] ሆነ ማለት ነው፡፡[106] የሶርያ ቤተ ክርስቲያን፥ በቅዳሴዋ ይህንን ዝማሬ (ሠለስቱ ቅዳስያት) በዚህ መልኩ ትዘምረዋለች፡-

Holy are thou, O God.
Holy are thou, Almighty
Holy are thou, Immortal.
Crucified for us,
Have mercy on us.[107]

ይህ ዝማሬ በኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያን[108] ቅዳሴያት ውስጥ ተቀባይነት ያገኘው በነገረ ክርስቶስ ላይ የኬልቄዶንን ጉባኤ ከተቀበሉት አብያተ ክርስቲያን ጋር

---

[101] "Holy God, Holy Almighty, Holy Immortal" - ግእዙ Immortal ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ ሁለት ቃላትን ነው የሚጠቀመው፡- ሕያው ዘኢይመውት (የማይሞት እና ሕያው)፡፡

[102] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 384፡፡

[103] Peter the Fuller.

[104] "Crucified for us; have mercy on us."

[105] Christological hymn.

[106] በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ (Divine Liturgy) ይህ ዝማሬ አሁንም የሚቀርበው ለሥሉስ ቅዱስ (ለአብ፥ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ) ነው፡፡

[107] Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 189.

[108] የኢትዮጵያ፥ የኤርትራ፥ የግብፅ፥ የአርመን፥ የሶርያና የማላንካራ (ሕንድ ውስጥ የምትገኘ የሶርያ ቤተ ክርስቲያን)፡፡

የአስተምህሮ ልዩነት ስላላቸው ብቻ ሳይሆን የዝማሬውን ተቀባይነት የሚያጠናክር ትውፊት ስላለም ጭምር ነው፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርቶስን ዝም ብለው ሲገንዙት (ዮሐ. 19፥ 38-40) በመለኮታዊ ባሕርዩ ሕያው የሆነው ጌታ ዓይኑን ገለጥ አድርጎ፡- "ለምን ዝም ብላችሁ ትገንዙኛላችሁ? ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት (የማይሞት) . . ." እያላችሁ ገንዙኝ እንዳላቸው የሚነገር ትውፊት አለ፡፡[109] የሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት እሳታዊው አግናጥዮስ[110] የተባለው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ስላየው ራእይ ተመሳሳይ ነገር ይነግረናል፡፡ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን በሚገንዙበት ሰዓት ሱራፌል የተባሉ ነገደ መላእክት ተገልጸው ግማሾቹ፡- "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል" ሲሉ፥ የተቀሩት ደግሞ "ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት" በማለት ዘመሩ፡፡ ይህንን የሰሙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ፡- "ስለእኛ የተሰቀልክ ሆይ፤ [አቤቱ] ይቅር በለን" ሲሉ መልስ ሰጡ፡፡[111]

መጽሐፈ ቅዳሴ ላይ የምናገኘው ዝማሬ (ሠለስቱ ቅዳስያት) ከኮፕቲኩ ዝማሬ የሚጨምራቸው ሐረጋት ስላሉ መጠነኛ ልዩነት ያሳያል፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴው ውስጥ የተጨመሩትን ሐረጋት አውጥተን የኮፕቲኩን ሠለስቱ ቅዳስያት ብንመለከት ይህንን እናገኛለን፡-

- ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተወልደ እምድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ፡፡
- ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተሰቅለ በእንቲአነ ተሣሃለነ እግዚኦ፡፡
- ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተንሥአ እሙታን፡ ወዐርገ ውስተ ሰማያት ተሣሃለነ እግዚኦ፡፡

---

[109] "ኪዳን ዘነግህ" *መጽሐፈ ቅዳሴ ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ 1991 ዓ.ም.) ገጽ 24፡፡
[110] Ignatius Noorono the fiery one.
[111] Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 188.

- ስብሐት ለአብ፥ ስብሐት ለወልድ፥ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፡ አሜን፡፡ አ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ (3)፡፡[112]

የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ያለው ሠለስቱ ቅዳስያት የሚከተሉትን ሐረጋትና ዐረፍተ ነገሮችን ይጨምራል፡-

- እማርያም እምቅድስት
- ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ[113] ዲበ ዕፀ መስቀል
- . . . አመ ሣልስት ዕለት . . . በስብሐት . . . ወነበረ በየማነ አቡሁ፡፡ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ
- ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ሕያው ተሣሃለነ፡፡[114]

የግእዙ ሠለስቱ ቅዳስያት በዝማሬው የተጠቀሱትን የክርስቶስ የማዳን ሥራዎች ሲጠቅስ፥ መሠረቱ የሆነውን (የተተረጐመበትን) የኮፕቲኩን እንዳለ ከመከተል ይልቅ በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮች ይጨምራል፡፡ ይህን ለመረዳት ከላይ "የተጨመሩ ሐረጋትና ዐረፍተ ነገሮች" ተብለው የተጠቀሱትን ከግእዙ ጸሎተ ሃይማኖት የተወሰነ ክፍል ጋር ማነጻጸር ይቻላል፡-

- (ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ) ወእማርያም እምቅድስት ድንግል
- ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት … ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ፡፡ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ . . .፡፡[115]

ይህ ዝማሬ በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ውስጥ የተሰጠው ቦታ፥ የኮፕቲኩ ሠለስቱ ቅዳስያት የሚዘመርበት ቦታ ላይ (ከወንጌል በፊት) ነው፡፡[116] ነገር ግን ከቅዳሴው በፊት ባለው አገልግሎት፥ ዝማሬው የኪዳን መቅድም ሆኖ ስለሚያገለግል፥[117]

---

[112] *The Coptic Orthodox Horologion,* 1992, 91 & 93; *Holy Euchologion*, 2004, p. 78.

[113] የኮፕቲኩ Trisagion ልክ እንደ ሶርያው ዝማሬ "crucified for us" ይላል፤ ግእዙ ይህን ተከትሎ "ዘተሰቅለ በእንቲአነ" (ስለእኛ የተሰቀለ) ማለት ሲገባው "ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል" ይላል፡፡

[114] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 384፡፡

[115] "ጸሎተ ሃይማኖት"፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 5-7፣ ገጽ 190-191፡፡

[116] በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ Trisagion የሚዘመረው ልክ ቅዳሴው እንደተጀመረ ነው - "Public Celebration of the Holy Qurbana," Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 189.

[117] የማንኛውም ክብረ በዓል ዋዜማ ሲቆምም በዚሁ ዝማሬ (ቅዱስ ተብሎ) ነው የሚጀምረው፡፡ ምዕራፍ የተሰኘው የቅዱስ ያሬድ ድርሰትም የሚጀምረው በዚህ ዝማሬ ነው፡፡

ቅዳሴው ላይም በዝማሬውና በጸሎተ ወንጌል መካከል ጸሎተ ኪዳን ይገባል፡፡[118] የተለመደውን አካሄድ ለመድገም ካልሆነ በስተቀር "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው . . ." የሚለውን ዝማሬ (ሠለስቱ ቅዳስያት) ተከትሎ ሊመጣ የሚገባው ከግብፅ ቅዳሴ የተወሰደውና[119] "አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ" በማለት የሚጀምረው የወንጌል ጸሎት ነው፡፡[120]

## ጸሎት በእንተ ኵሉ ዓለም[121]

ወንጌል ከመነበቡ በፊት ወይም በኋላ ንፍቁ ካህን (የሠራዒው ካህን ረዳት) የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት በፍጥረቱ ላይ ሁሉ እንዲደረግ የሚለምን ጥንታዊ ጸሎትን ይደግማል፡፡ ይህ ጸሎት እርስ በእርሳቸው የተሳሰሩ ልመናዎችን እያከታተለ ስለሚያቀርብ *ሲናፕቲ*[122] ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ስያሜ አግኝቷል፡፡[123] ጸሎቱ "*መዓትህ የራቀ፥ ምሕረትህ የበዛ እና እውነተኛ*"[124] በሚሉ ቅጽሎች ለተገለጸው አምላክ የሚቀርብ ምልጃና ልመና ሲሆን፦

- የታመሙ ወገኖችንና መንገድ የሄዱትን (በሌላ አገር እንግዶች የሆኑትን)፥
- ቍርባኑንና ዕጣኑን ያቀረቡትን፥
- የተማረኩ ወገኖችን፥
- በመሪር ኀዘን የተጨነቁትንና ድኆችን በይቅርታውና በምሕረቱ እንዲያስባቸው፤
- ንኡሰ ክርስቲያንን (ያልተጠመቁ ሰዎችን) አዲስ ልደት ለምታሰጠው ጥምቀት እንዲያበቃቸውና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንዲያደርጋቸው፤
- የዓየሩን ጠል፥ ዘሩንና መከሩን፥ የምድሩን ፍሬ፥
- በየዓመቱ የሚዘንበውን ዝናብና የወንዝ ውኆችን ያለ ጥፋት እንዲጠብቅ፤

---

118 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 175፣ ገጽ 63፡፡
119 "The Prayer of the Gospel," *Holy Euchologion*, 2004, p. 79.
120 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 179፣ ገጽ 64፡፡
121 *Oratio universalis*.
122 Συναπτή.
123 "Litnaic Synapte" ይባላል፡፡ Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 178.
124 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 194፣ ገጽ 68፡፡

- የሰው ዘርንና የእንስሳውን ደኅንነት እንዲጠብቅ፤ በመጨረሻም
- እግዚአብሔርን የምትወድ አገራችንን ኢትዮጵያን ለዘላለሙ በደኅንነትና በሰላም እንዲጠብቃት ይማፀናል፡፡[125]

## ቅድመ አኰቴተ ቍርባን

ሁለተኛው የቅዳሴ ክፍል ወንጌል ተነቦና ትምህርት ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ፥ ወደ ሦስተኛው ክፍል (አኰቴተ ቍርባን) ከማምራታችን በፊት የሚከናወኑ ሥርዓቶችና ጸሎቶች አሉ፡፡ በዚህ ክፍል የእነዚህን ጸሎታት ጥንታዊ መሠረት በአጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

### ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን [126]

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን (በ4ኛው ምእት ዓመት) በጥምቀት ልጅነትን አግኝተው የአንዲቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት መሆን የሚፈልጉ ሰዎች[127] የተለያዩ ትምህርቶችን እየወሰዱ ለሦስት ዓመታት ያህል ሥልጠና ይሰጣቸው ነበር፡፡[128] በእነዚህ የሥልጠና ጊዜያት ከተጠመቁ አማንያን ጋር የሥርዓተ ቅዳሴ ተሳታፊ ለመሆን ወደ ምእመናን ማኅበር (ቤተ ክርስቲያን) ሲመጡ አገልግሎቱን የሚሳተፉት የአማንያን ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት እስካለው ድረስ ነበር፡፡ ላልተጠመቁ ሰዎች የሚደረገው ሥርዓተ ቅዳሴ (የንኡሰ ክርስቲያን ቅዳሴ)[129] እንዳበቃ ኤጲስቆጶሱ ወይም ቅዳሴውን የሚመራው ካህን ለእነርሱ የተዘጋጀውን ጸሎት ከጸለየላቸው በኋላ ዲያቆኑ ያሰናብታቸዋል፡፡ ከእነርሱም ጋር በዕለቱ ለቅዱስ ቍርባን ያልተዘጋጁ ምእመናንም አብረው ይወጡ ነበር፡፡[130] ጥንታውያን ከሚባሉ የሥርዓተ ቅዳሴ አይነቶች አንዱ የሆነው የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ይህንን የዲያቆኑን ትእዛዝ

---

[125] ዝኒ ከማሁ፥ 1994፣ ቍ. 195-207፣ ገጽ 69-70፡፡
[126] Dismissal of the Catechumens.
[127] Catechumens.
[128] Fr. Lawrence Farley*, Let Us Attend: A Journey through the Orthodox Divine Liturgy,* (Cherserton, Indiana: Conciliar Press, 2007) p. 47; *The Statutes of the Apostles or Canones Ecclesiastici*, trans. G. Horner, 1904, p. 176, no. 20.
[129] Liturgy of the catechumens.
[130] Farley*, Let Us Attend*, p. 48; *The Statutes of the Apostles or Canones Ecclesiastici*, trans. G. Horner, 1904, p. 176, no. 25.

እስካሁን ድረስ እንደያዘ ይገኛል፡- "ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን - የክርስቲያን ታናናሾች [ያልተጠመቃችሁ ሰዎች] ውጡ"፡፡[131] ነገር ግን ትእዛዙ የሚመለከታቸው ሰዎች በቅዳሴው ስለማይገኙና ድንገት ቢገኙም የትእዛዙን መልእክት ስለማይረዱት ተፈጻሚ ሲሆን አይታይም፡፡ ምናልባት ቤተ ክርስቲያናችን ኢአማንያንን ወደ ክርስትና ለማምጣት በምታደርገው አገልግሎት የጥንቱን የንኡሰ ክርስቲያን ሥልጠና[132] እና ቅዳሴው ላይ በዲያቆኑ በኩል የሚደረገው የንኡሰ ክርስቲያንን ስንብት ተግባራዊ ልታደርገው ትችላለች፡፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ንኡሰ ክርስቲያንን የማሰናበቱ ትእዛዝ ተፈጻሚነት ስለሌለው ከቅዳሴዋ አውጥታዋለች፡፡ ይህ ማለት ግን ጥንታዊው ትእዛዝ በኮፕቲክ ቅዳሴ ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ተካትቶ ስለማይታይና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ውስጥ ግን ስለሚገኝ፥ ዊሊያም ማኮምበር በስህተት ድምዳሜ ላይ እንደ ደረሰው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ከኮፕቲክ ቅዳሴ ቅድምና አለው ማለት አይደለም፡፡[133]

## ጸሎት እንዘ ይቀርብ ኀበ ታቦት[134]

ሠራዒው ካህን ቅዳሴው ከመጀመሩ በፊት ወደ መጋረጃው ሳይገባ በሚያደርገው ጸሎት (ጸሎት ቅድመ ግብአተ መንጦላዕት) "ያንተ በሚሆን በዚህ ቅዱስ ቦታ አገለግል ዘንድ ሳይገባኝ ጠርተኸኛል" በማለት በራሱ ብቃት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ለተቀደሰው አገልግሎት እንደተመረጠ ይጸልያል፡፡ በተጨማሪም፥ "በቤተ መቅደስህም እቆም ዘንድ ኃጢአቴንና በደሌን ለማስተሥረይም በቅን ልቡና ንጹሕ መሥዋዕትን አቀርብልህ ዘንድ የበቃሁ አድርገኝ" በማለት በፍርሃትና በትሕትና ልመናን ያቀርባል፡፡[135] ንኡሰ ክርስቲያን ከተሰናበቱ በኋላ ደግሞ፥ የቀረበውን ኅብስትና ወይን የጌታ ሥጋና ደም ወደመሆን ይለውጠው ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ወደሚጠይቅበትና ሥጋ ወልደ እግዚአብሔርን ወደሚፈትትበት የቅዳሴው ዋነኛ ክፍል (ፍሬ ቅዳሴ) ከመግባቱ በፊት ለራሱና የቅዳሴው ተሳታፊ ለሆኑት በሙሉ የምልጃ ጸሎትን ያቀርባል፡፡ እንደ መጽሐፈ ቅዳሴው ትእዛዝ ይህን ጸሎት የሚያቀርበው በለኆሳስ (ዝግ ባለ ድምጽ/ ቀስ ብሎ)

---

[131] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ምዕራፍ 4፡ ቍ. 1፣ ገጽ 74፡፡
[132] Catechumenate.
[133] Macomber, "Ethiopian Liturgy," p. 988.
[134] Prayer of *accessus ad altare*.
[135] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 17 እና 20፣ ገጽ 8፡፡

እና "በዊአ ኀበ ታቦት" (ወደ ታቦቱ ቀረብ ብሎ/ መንበሩ ፊት ለፊት ሆኖ) ነው፡፡ ይህም ድፍረት እንዳይሆንበት፡- "መምህራችን ሆይ . . . ወደዚህ ወደሚያስፈራ ቍርባን በቀረብን ጊዜ ወደ ኋላ እንዳትመልሰን ወዳንተ እንማልዳለን፡፡ ይህችን ባሕርያችንን የወደድሃት ሆይ፥ በሥራችን የምንታመን አይደለንም፤ በምሕረትህ ነው እንጂ" ይላል፡፡[136] ይህ ጸሎት በምዕራብ ሶርያ ቅዳሴ *ጸሎተ መንጦላዕት*[137] በሚል ስም ከሚታወቀው ጋር ተመሳሳይነት እንዳለውና ከአንጾኪያ በግብፅ በኩል ወደ አገራችን እንደገባ ይታመናል፡፡[138]

## ጸሎት በእንተ ቤተ ክርስቲያን፥ በእንተ ጳጳስ ወበእንተ ማኅበር

በሦስተኛው ምእት ዓመት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ትጠቀምበት የነበረው *መጽሐፈ ሥርዓት* (ሐዋርያዊ ትውፊት) ከንኡስ ክርስቲያን ስንብት በኋላ ስለሦስት ነገሮች ጸሎት ሊደረግ እንደሚገባ ይነግረናል፡- ስለሰላም፥ ስለማኅበርና ስለሊቀ ጳጳሱ፡፡ [139] እነዚህ ጸሎታት በግብፅ እና በኢትዮጵያ ቅዳሴያት እስካሁን ድረስ ቦታቸውን ጠብቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያገኛሉ፡፡[140] በመጀመሪያው ጸሎት ካህኑ፡- "አቤቱ ሐዋርያት የሰበሰቡዋት አንዲት የምትሆን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን[141] ሰላም አስብ" ካለ በኋላ "ከሰማይ የሚገኝ ሰላምን ሁሉ በሁላችን ልቡና አሳድርብን" ሲል ይማፀናል፡፡[142] በመቀጠል፥ ሁሉን ያያዘ (አኃዜ ኵሉ)[143] የኢየሱስ ክርስቶስ አባት (እግዚአብሔር አብ)፥ ጺጋውን አብዝቶ የመንጋውን ጠባቂ

---

[136] ዝኒ ከማሁ፥ 1994፣ ቍ. 2-3፣ ገጽ 74-75፡፡

[137] The Prayer of Veil.

[138] Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 179.

[139] *The Statutes of the Apostles or Canones Ecclesiastici*, trans. G. Horner, 1904, p. 176, no. 20.

[140] "The Three Long Prayers," *Holy Euchologion*, 2004, p. 82-85፤ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 6-27፣ ገጽ 75-79፡፡

[141] የኮፕቲክ ቅዳሴ እንግሊዝኛ ትርጉም፡- "remember, O Lord, the peace of Thine One, […] Holy, Catholic and Apostolic Church" ይላል - *Holy Euchologion*, 2004, p. 82. አራቱ የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት (አሐቲ፥ ቅድስት፥ ሰፋኒት (በሁሉ ያለች) እና ሐዋርያዊት) በዚህ ጸሎት ውስጥ ስለተጠቀሱ የአማርኛው ትርጉም "ሐዋርያት የሰበሰቡዋት" ከማለት ይልቅ "ሐዋርያዊት እና ሰፋኒት" በማለት አራቱን የቤተ ክርስቲያን መገለጫ ባሕርያት በግልጽ ማሳየት ነበረበት፡፡

[142] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 6 እና 9፣ ገጽ 75-76፡፡

[143] *Pantocrator*.

(ሊቀ ጳጳሱን) ለብዙ ዘመናት በሰላም ይጠብቀው ዘንድ[144] እና ማኅበረ ምእመናኑም ቅድስትና ብፅዕት የሆነች ፈቃዱን እያደረጉ የእርሱ ወገኖች ይሆኑ ዘንድ፤ እንዲሁም የጸሎት፥ የንጽሕና እና የበረከት ቤት ሆነው ይሠሩ[145] ዘንድ (1 ጴጥ. 2፥5)[146] እንዲረዳቸው የምልጃ ጸሎትን ያቀርባል፡፡[147] እነዚህን ሦስት ጸሎታት ሠራዒው ዲያቆን በእንተ ቅድሳትን በሚደግምበት ሰዓትና[148] ሠራዒው ካህን "የአባታችን የአብርሃምን መሥዋዕት የተቀበልህ" በማለት የሚጀምረውን ጸሎት ከደገመ በኋላ[149] ካህኑ ይጸልያቸዋል፡፡ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ግን እነዚህ ጸሎታት በቅዳሴው የመጀመሪያ የዝግጅት ክፍል ውስጥ አይገኙም፤ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ለምን ተደጋጋሚ ቦታ እንደተሰጣቸው ግልጽ አይደለም፡፡

## ጸሎተ ሃይማኖት[150]

ይህ የክርስትና እምነት መግለጫ (ጸሎተ ሃይማኖት)[151] "በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን" እስከሚለው ድረስ በኒቂያው ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ (325 ዓ.እ.) የተዘጋጀ ሲሆን፥ ቀሪው ክፍል የተጨመረው በቊስጥንጥንያው ዓለም አቀፋዊ ጉባኤ (381 ዓ.እ.) ነበር፡፡[152] ጸሎተ ሃይማኖት የቅዳሴ አካል ሆኖ የገባው በ5ኛው ምእት ዓመት፥ ጴጥሮስ በተባለው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ (+488 ዓ.እ.)[153] አማካኝነት

---

[144] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 16፣ ገጽ 77፡፡

[145] "ሠ" ጠብቆ ይነበብ፡፡

[146] "መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ"፡፡

[147] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 27፣ ገጽ 79፡፡

[148] ዝኒ ከማሁ፥ 1994፣ ቊ. 111-115፣ ገጽ 48-50፡፡

[149] ዝኒ ከማሁ፥ 1994፣ ቊ. 154፣ ገጽ 60፡፡ እዚህ ላይ ጸሎታቱን መጽሐፈ ቅዳሴው አይጽፋቸውም፤ "ከመ ቀዳሚ - አንደ ቀደመው" የሚል ትእዛዝ (rubric) ያስቀምጥና የመጀመሪያውን ጸሎት መነሻ ብቻ ይጠቅሳል፡፡ ካህኑ አስቀድሞ (ዲያቆኑ በእንተ ቅድሳትን በሚደግምበት ሰዓት) እንደጸለየው እዚህ ላይም እንደዚያው ያደርጋል ማለት ነው፡፡

[150] Creed.

[151] ጸሎት ሳይሆን የእምነት መግለጫ ስለሆነ "አንቀጸ ሃይማኖት" ተብሎም ሊጠራ ይችላል፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ይህ ርእስ የተመረጠው ምናልባት ሊቃውንቱ በጸሎት (lex orandi) እና በእምነት (lex credendi) መካከል ያለውን የተሰናሰለ ግንኙነት ስለተረዱ ይሆናል፤ ዝነኛው የምሁራኑ አባባል *lex orandi est lex credendi* (የምንጸልየው የምናምነውን ነው፤ የምናምነውን እንጸልየዋለን) እንዲል፡፡

[152] የሁለቱ ግባኤያት ውጤት መሆኑን ለማመልከት Niceo-Constantinopolitan Creed በመባል ይታወቃል፡፡

[153] Peter the Fuller.

እንደሆነ ይታመናል፡፡ በቊስጥንጥንያም በ6ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ በቅዳሴው መሃል ላይ ይጸለይ ጀመር፡፡[154] በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ቅዳሴያት፥ ጸሎተ ሃይማኖት በዲያቆኑ መሪነት ከምእመናኑ ጋር በኅብረት የሚጸለየው የቅዳሴው ተሳታፊዎች የተቀደሰ ሰላምታን ከመለዋወጣቸው በፊት ነው፡፡[155]

የቤተ ክርስቲያናችንም መጽሐፈ ቅዳሴ ከላይ የተጠቀሰው ቦታ ላይ ዲያቆኑ፡- "በእግዚአብሔር ጥበብ ሁነን ሁላችን የሃይማኖትን ጸሎት እንበል" የሚል ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡[156] ነገር ግን ለዕለቱ በተመረጠው ቅዳሴ መሠረት ዓለም አቀፋዊው ጸሎተ ሃይማኖት ወይም "አመክንዮ ዘሐዋርያት"[157] በኅብረት (በዲያቆኑ መሪነት) ይጸለያል፡፡ "አመክንዮ ዘሐዋርያት" የሚል ስያሜ የተሰጠው የእምነት መግለጫ ሐዋርያዊ ሕግጋት በተሰኘው መጽሐፈ ሥርዓት ስድስተኛው መጽሐፍ፥ ምዕራፍ 11 ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፥[158] ከዚህ መጽሐፈ ሥርዓት ተወስዶ የመጽሐፈ ዲድስቅልያ 33ኛ ምዕራፍ ውስጥም ተካትቷል፡፡ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት "አመክንዮ ዘሐዋርያት" ሲሉ የሰየሙት የእምነት መግለጫ (የሐዋርያት አንቀጸ ሃይማኖት)[159] የቅዱሳን ሐዋርያት ድርሰት ነው ብለው ስላሰቡ፥ ቅዳሴ ሐዋርያትና በዘመነ ሐዋርያት እንደተደረሱ የገመቷቸው ቅዳሴያት (ቅዳሴ እግዚእ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድና ቅዳሴ ማርያም) በሚቀደሱበት ጊዜ "አመክንዮ ዘሐዋርያት"፥ በሌሎቹ ቅዳሴያት ደግሞ "ጸሎተ ሃይማኖት"[160] እንዲጸለይ ሥርዓት ሠርተዋል፡፡

---

[154] Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 190.

[155] ዝኒ ከማሁ፤ *Holy Euchologion*, 2004, p. 86; Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 200.

[156] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 32፣ ገጽ 80፡፡

[157] ዝኒ ከማሁ፥ 1994፣ ቊ. 33-45፣ ገጽ 80-82፡፡

[158] *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles): The Work Claiming to Be the Constitutions of the Holy Apostles including the Canons*, eds. Irah Chase and Otto Krabbe (D. Appleton and Company,1848) pp. 117-118.

[159] Apostolic Creed.

[160] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 1-10፣ ገጽ 190-191፡፡

## ተሐፅቦተ እድ[161]

ሠራዒው ካህን "ንጹሕ የሆነ ከቍርባን ይቀበል፤ ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል . . ."[162] የሚለውን እያወጀ እጁን የሚታጠብበት ምክንያት በጲላጦስ አምሳል እንደሆነ መጽሐፈ ቅዳሴ ይነግረናል፡፡ [163] የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች በባሕርዩ ጻድቅ (እውነተኛ) እና ንጹሕ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን ጲላጦስ ፊት ለፍርድ እየከሰሱ ባቀረቡት ጊዜ ጲላጦስ እጅግ እስኪደነቅ ድረስ ጌታ አንዲትም ቃል አልመለሰም ነበር፡፡ "ስቀለው" የሚለው የሕዝቡ ጩኸት ሲበረታም ጲላጦስ፥ "ውኃ አንሥቶ፡- ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ" (ማቴ. 27፥24)፡፡ በዚህ አምሳል ካህኑ፡- "እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ፥ እንደዚሁ ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ፤ ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከእርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም"[164] እያለ አምላካቸውን ስላሳዘኑበት ኃጢአት ከልብ ተጸጽተው ንስሐ ሳይገቡ በድፍረት የጌታን ሥጋና ደም ቢቀበሉ ፍርድ እንዳለባቸው ያስጠነቅቃቸዋል (1 ቆሮ. 11፥27-29)፡፡ ከዚህ አዋጅ ቀጥሎ፥ ምንም እንኳን ተግባራዊ ባይሆንም፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ ሕዝቡን ማስተማርና መምከር እንዳለበት የሚገልጽ ትእዛዝ መጽሐፈ ቅዳሴው ይዟል፡፡[165]

በቅዳሴው ዋነኛ ክፍል ካህኑ የሚያከናውነው እጅ የመታጠብ ሥርዓት ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ (348 ዓ.እ. አካባቢ) የሚታወቅ ሲሆን፥ የካህኑን መንፈሳዊ ዝግጅት ያመለክታል፡፡[166] ከላይ እንደተገለጸው፥ ካህኑ ወደ መንበሩ ቀረብ ብሎ ለራሱና ለሕዝቡ እንደሚጸልይ ተመልክተናል፤ እጁን

[161] *Lavabo*.
[162] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 46-47፣ ገጽ 83፡፡
[163] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 51፣ ገጽ 84፡፡
[164] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 547፣ ገጽ 83፡
[165] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 51፣ ገጽ 84፡፡
[166] Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 190.

ከታጠበ በኋላ ደግሞ ኃጢአተኛነቱን እያሰበ *ወደ መንበሩ የመቅረብ ጸሎት*[167] ይጸልያል፡-

> አቤቱ ጌታዬና አምላኬ ሆይ፥ ሥርዓትን የሠራህ፥ ሰላምንና ፍቅርን የምትሰጥ፤ ክፉውን ሕሊና ሁሉ፥ ቂምን፥ ቅንዓትንና ሥጋዊ ፈቃድን ሁሉ ከእኔ አርቅልኝ፡፡ በበጎ ሕይወታቸው በሰላምና በፍቅር ወራት ካገለገሉህ ከክቡራን ባሮችህ ጋር አንድ እንድሆን አድለኝ፡፡ ከሰማይ የወረድህ፥ ከሰማያውያንና ከምድራውያን ጋር ሰላምን ያደረግህ፥ አንተንም ያመሰግኑ ዘንድ ወገኖችህን ሁሉ የሰበሰብሃቸው አንተ ነህና፤ ምስጋና የሚገባህ ስለሆነ ለዘላለሙ፡ አሜን፡፡[168]

## አምኃ ቅድሳት[169]

ከላይ ከተጠቀሰው ጸሎት ቀጥሎ የሚመጣው ከኮፕቲክ ቅዳሴ የተወሰደውና "ለዘላለሙ ገናና የምትሆን እግዚብሔር ሆይ፥ ያለጥፋት ሰውን የፈጠርኸው" በማለት የሚጀምረው "ጸሎተ አምኃ" ነው፡፡ የኮፕቲኩ መጽሐፈ ቅዳሴ *የዕርቅ ጸሎት* በማለት ይጠራዋል፤ መጽሐፉ የተለያዩ የዕርቅ ጸሎት ዓይነቶች የያዘ ሲሆን፥ የኮፕቲክ ካህናት ይህን ጸሎት የሚጸለዩት ቅዳሴ ባስልዮስን ሲቀድሱ ነው፡፡[170] የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ የጸሎቱን ምንጭ ሲጠቁም፡- "ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ" የሚል ርእስ ሰጥቶታል፡፡ [171] ካህኑ፡- "ከሰማይ የተገኘች ሰላምን በምድር ሁሉ መላህ . . . [አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደፈቃድህ ልባችንን በሰላምህ ሙላ]…"[172] በማለት ሲጸልይ፥ ዲያቆኑ "ፍጽምት ስለምትሆን ሰላምና ፍቅር ጸልዩ፤ እርስ በርሳችሁ በተለየች እማኄ (እጅ መንሣት) እጅ ተነሣሡ"[173] የሚለውን ትእዛዝ በዜማ ያሰማል፡፡ ዲያቆኑ ይህን ሲል ከምእመናኑ የሚጠበቀው

---

[167] Prayer of *accessus ad altare*.

[168] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 49-50፣ ገጽ 83-84፡፡

[169] Holy Kiss/ Kiss of Peace.

[170] The Prayer of Reconciliation - *Holy Euchologion*, 2004, p. 86.

[171] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 53፣ ገጽ 84፡፡

[172] ግእዙ፡- " እግዚአ በሥምረትከ ምላዕ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ" የሚለውን፡ አማርኛው፡- "አቤቱ ፈቃድህን በሁላችን ልቡና ሙላ" ይላል፡፡ የኮፕቲክ ቅዳሴ የእንግሊዝኛ ትርጒም "According to [Your] good will, O God, fill our hearts with [Your] peace" ስለሚል የተሻለው ትርጒም (አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደፈቃድህ ልባችንን በሰላምህ ሙላ) መሆን አለበት፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 55-56፣ ገጽ 85፤ *Holy Euchologion*, 2004, p. 87.

[173] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 58፣ ገጽ 85፡፡

በመካከላቸው ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል የሚከለክል ምንም ነገር እንደሌለና ሰላማውያን መሆናቸውን ለማመልከት እርስ በእርስ የተቀደሰውን ሰላምታ[174] መለዋወጥ ነው፡፡ ለዚህም መሠረቱ “መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ” የሚለው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የፍቅር ትእዛዝ ነው (ማቴ. 5፥ 23-24)፡፡

ስለዚህ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የሰላምታው ልውውጥ መሥዋዕቱ ከሚቀርብበት ሰዓት ቀደም ብሎ እንዲፈጸም ተደረገ፤ ከላይ የተጠቀሰውን የወንጌል ቃል የሚያጠናክር ተጨማሪ ትእዛዝም መጽሐፈ ዲዳኬ ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፦ “ከወዳጁ ጋር ጸብ ያለበት ሰው ቢኖር መሥዋዕታችሁ እንዳይረከስ ከመታረቁ በፊት ወደ [ተጋብኦተ ቍርባን] መምጣት የለበትም”፡፡[175] ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሁለት ጊዜ “በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ” የሚል መልእክት ልኮላቸዋል (1 ቆሮ. 16፥20፤ 2 ቆሮ. 13፥12)፡፡ ይህን ጥንታዊ ሥርዓት በመጠበቅ የግብፅ፥ የሶርያ እና ሕንድ ኦርቶዶክስ አማንያን የዲያቆኑን ትእዛዝ ሲሰሙ እርስ በርሳቸው ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡[176] የእኛ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ግን በዚህ ርእስ በቂ ትምህርት ስላልተሰጣቸው፥ ወይም ዲያቆኑ በግእዝ ያስተላለፈውን ትእዛዝ ስላልተረዱት፥ አጠገባቸው ካለው ሰው ጋር የተቀደሰውን ሰላምታ ከመለዋወጥ ይልቅ በአራቱ ማዕዘናት አንገታቸውን ዘንበል አድርገው እጅ ሲነሡ እናያለን፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴው ግን ግልጽ በሆነ መልኩ፦

[174] ይህ መንፈሳዊ ሰላምታ የተቀደሰና በሥጋ ስሜት በየመንገዱ ወጣቶች ከሚያደርጉት መሳሳም (ስዒም) የተለየ መሆኑን ሲያጠይቅ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም እንዲህ ብሏል፦ “You must not suppose that this kiss is the kiss ordinarily exchanged in the streets by ordinary friends. This kiss is different, for it effects a [co-mingling] of souls, and pledges complete forgiveness. The kiss then is a sign of a true union of hearts, and of banishing any grudge . . . . The kiss then is a reconciliation and is therefore holy.” *Mystagogical Catechesis* 5, quoted in Iskander, *Understanding the Liturgy,* p. 27.

[175] Didache 14:2 in *The Complete Works of the Church Fatehrs,* ed. Phil Schaff (Toronto: 2016) Kindle edition.

[176] Iskander, *Understanding the Liturgy,* p. 27; Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 200.

"በዚህ ጊዜ ቀሳውስት ከቀሳውስት ጋር፥ ዲያቆናትም ከዲያቆናት ጋር፥ [ወንዶችም ከወንዶች ጋር]፥ ሴቶችም ከሴቶች ጋር እጅ ይነሳሱ" ይላል፡፡[177]

## ፪. ፍሬ ቅዳሴ፡ ቅዳሴያት ዘኢትዮጵያ

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኑ ያመጡትን ቍርባን፥ ዲያቆናቱ ከማዘጋጃው ክፍል[178] ወደ መንበሩ የሚያመጡት ንኡሰ ክርስቲያን ከተሰናበቱና ምእመናኑ የተቀደሰውን ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ነበር፡፡[179] በቆይታ ብዛት ግን ኅብስቱንና ወይኑን የማቅረቡ ሥርዓት (አግብኦተ ግብር) ቅዳሴው መጀመሪያ ላይ (የዝግጅት ክፍል) እንዲከናወን ሆኖ፥ ከላይ እንደተመለከትነው ሁለተኛው (የትምህርት ክፍል) በተለያዩ ጸሎታትና እና ዝማሬያት ይዘቱ እያደገ መጣ፡፡ አግብኦተ ግብር የሚከናወነው በቅዳሴው የመጀመሪያ ክፍል ቢሆንም፥ የቀረበው ኅብስትና ጽዋ ላይ መንፈስ ቅዱስ ከሰማያት ወርዶ የጌታ ሥጋና ደም ያደርገው ዘንድ ሠራዒው ካህን የሚጸልየው ጸሎት (*ኤፒክሌሲስ*)[180] እና ሥርዓተ ፈትቶ[181] የሚከናወኑት የቅዳሴው ሦስተኛ ክፍል ውስጥ ስለሆነ በውስጡ የሚከናወነውን ምሥጢር ታላቅነት ለማመልከት ፍሬ ቅዳሴ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ፍሬ ቅዳሴው ውስጥ ያለው የቍርባን ምስጋና (አኰቴተ ቍርባን) በዚህ ስያሜ ለመጠራት የሚያስችሉትን ጸሎታት ማካተት ይኖርበታል፡፡ [182] የቤተ ክርስቲያናችን መሥራች ቅዳሴያት ከሚባሉት አንዱ የሆነው ቅዳሴ ሐዋርያትን እና የእርሱ መገኛ የሆነውን የሐዋርያዊ ትውፊት አኰቴተ ቍርባን በይዘት በማነጻጸር ዝርዝር መግለጫ በምዕራፍ 3፡ ገጽ 143-164 ቀርቧል፡፡ የእያንዳንዱን አኰቴተ ቍርባን ይዘት እናጥና ከተባለ ራሱን የቻለ ትልቅ መጽሐፍ ይወጣዋል፤ በዚህ ክፍል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ውስጥ የሚንጸባረቁ መለያ ባሕርያትን ብቻ በመጠኑ እንመለከታለን፡፡

---

[177] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 59፣ ገጽ 85፡፡

[178] Postophorion.

[179] Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 191.

[180] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 48-49፣ ገጽ 95፡፡

[181] Fraction.

[182] የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጸሎታተ ቍርባን (anaphoras) በ3ኛውና በ4ኛው ምእት ዓመታት የነበራቸውን ይዘት የሚያስረዳውን (የዚህን መጽሐፍ ሁለተኛ ምዕራፍ) ይመልከቱ፡፡

የፍሬ ቅዳሴው መግቢያ ላይ ሠራዒው ካህን ለዕለቱ የመረጠውን የአኰቴተ ቍርባን አይነት ያሳውቃል፤ ቅዳሴውን የሚመርጠውም በዕለቱ ከሚከበረው በዓል (ከሚታሰበው ቅዱስ) አንጻር መጽሐፈ ግጻዌን በመከተል ነው፡፡ እንደ ግጻዌው ትእዛዝ በተዝካረ ቅዱሳንና ዐበይት በዓላት የሚመረጡት ቅዳሴያት የሚከተሉት ናቸው[183]፡-

1) በጌታ ዐበይት በዓላት - በልደት በዓል፡- ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ፤[184]
   - በዘመነ አስተርእዮ (በሰሙነ ልደት ወጥምቀት)፥ ዘመነ ፋሲካ፥ በዓለ ዕርገት እና በዓለ ጰራቅሊጦስ፤ መስከረም 7 ቀን (የቅዱስ ዲዮስቆሮስ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ፤[185]
   - የኒቆዲሞስ ረቡዕ ጀምሮ እስከ ሆሣዕና እሑድ እና ጥር 21 ቀን (የቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፤[186]
   - በበዓለ ብሥራት/ትስብእት እና በዓለ ደብረ ታቦር፡- ቅዳሴ ማርያም፡፡[187]
2) በበዓለ መድኃኔ ዓለም፥ በበዓለ መስቀል እና ግንቦት 12 ቀን (የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤[188]

---

183 አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ፥ *የቅዳሴያችን ይዘት* (ቶሮንቶ፡ ጣና ማተሚያ ቤት፡ 2003 ዓ.ም.) ገጽ 40-62፡፡

184 "በደመናት መጋረጃ ተሠወረ፥ ከቅድስት ድንግል መድኅን ተወለደ፥ ጌታ ተገኘ፥ እውነተኛ ፀሓየ ጽድቅ ወጣ" የሚል ነክ ስላለው፤ ሠራዊቱም፡ "ነአምን ልደቶ ለክርስቶስ፥ ልደቶ ለክርስቶስ ነአምን" ስለሚል - "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 12፣ ገጽ 371 እና ቍ. 55፣ ገጽ 377 ይመልከቱ ፡፡

185 የጌታን የማዳን ሥራ በሰፊው ስለሚያወሳ፡- "በአባቱ ፈቃድ ወረደ፥ በማርያም ዘንድ እንግዳ ሆነ፥ እግዚአብሔር በንጹሕ ድንግልናዋ ተወለደ . . . በግልጥ ተመላለሰ፥ እንደ ሰውም ታየ፥ በየጥቂቱ አደገ፥ በሠላሳ ዘመን በዮርዳኖስ ተጠመቀ . . . በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ፥ የተሰበሰቡ ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበትም ገባ፥ በጽርሐ ጽዮንም ታያቸው፤ በአርባኛውም ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ . . . [በአምሳኛውም] ቀን በእሳተ አምሳል መንፈስ ቅዱስን ሰደደላቸው፥ በአገሩም ሁሉ ቋንቋ ተናገሩ . . ." - "ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 15-39፣ ገጽ 360-363፡፡

186 "የሆሣዕናን ዑደት ለደቀ መዛሙርቱ አሳየ . . . ሆሣዕና በአርያም፥ ሆሣዕና በአርያም፥ ሆሣዕና በአርያም . . ." የሚል ነክ ስላለው - "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 47፣ ገጽ 277፡፡

187 የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት የሚያመለክት ነክ፡- "እርሱ ቅሉ እግዚብሔር አብ ንጽሕናሽን ባየ ጊዜ ስሙ ገብርኤል የሚባል ብርሃናዊ መልአኩን ወደ አንቺ ላከ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ይመጣል፥ የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል አለሽ" በቅዳሴ ማርያም ስለሚገኝ፡፡ በደብረ ታቦር የተገለጸውን ብርሃን መለኮት ስለሚመለከት በበዓለ ደብረ ታቦር ከቅዳሴ ማርያም የሚከተለው ይዜማል፡- "አብ ጎሕ፥ ወልድ ጎሕ፥ መንፈስ ቅዱስ ጎሕ፤ አሐዱ ውእቱ ጎሐ ጽባሕ ዘበፀዳለ ብርሃኑ ሰሰለ ጽልመት" - "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 45፣ ገጽ 170 እና ቍ. 75፣ ገጽ 174 ፡፡

3) በዘመነ አስተምሕሮ[189] (ከበዓለ ልደት በፊት ባሉት እሑዶች፡- ስብከት፥ ብርሃን፥ ኖላዊ)፥ በበዓለ ቊስቋም እና ነሐሴ 16 ቀን፡- ቅዳሴ እግዚእ፤
4) በእመቤታችን በዓላት (ልደታ፥ በኣታ ውስተ ቤተ መቅደስ ወበዓለ ዕረፍታ፥ በጾመ ፍልሰታ)፡- ቅዳሴ ማርያም፤
5) በበዓለ ሐዋርያት፡- ቅዳሴ ሐዋርያት፤
6)ኅዳር 8 ቀን (በበዓለ አርባዕቱ እንስሳ)፥ ኅዳር 24 (በበዓለ ካህናተ ሰማይ)፥ በበዓለ ጻድቃን (ጥር 3፡- የጻድቃን ሁሉ መታሰቢያ በሚደረግበት ቀን) እና 318ቱ የኒቂያ ጉባኤ ሊቃውንት ተሰብስበውበታል ተብሎ በሚታመንበት ቀን (መስከረም 21)፡- ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፤[190]
7) በበዓለ ሰማዕታት[191] እና በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዓል (ጥር 4)፡- ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፤
8) በበዓለ መላእክት፥ በዕለታተ ጳጉሜ እና ሰኔ 27 ቀን (የቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ፤[192]

---

[188] "ሁሉን የያዘውን ያዙት፥ ሁሉን የሚገዛውን አሠሩት፥ በቀኚጣ ጎተቱት፡ በፍቅር ተከተላቸው . . . አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ . . ." እያለ ጌታ ስለእኛ የተቀበለውን ሕማም አምልቶና አስፍቶ ስለሚናገር -"ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 46 እና 54፣ ገጽ 212 እና 213።

[189] ስለዚህ ዘመን ከላይ ገጽ 178፡ ኅዳግ ቊ. 251 ላይ የተሰጠውን አጭር ማብራሪያ ይመልከቱ።

[190] "የጻድቃን ነፍሶቻቸው በዚያ ይኖራሉ፥ በዚያም ይጠበቃሉ . . . ጻድቃን በክብር፥ የዋሃን በክብር፥ የተመረጡትም በክብር ከዚያ ይኖራሉ" የሚል ነክ ስላለው፤ ሠራዊቱም መጨረሻ ላይ፡- "ጻድቃን ስለእርሱ ተጋደሉ" ይላል፤ በሐዳፌ ነፍሱም፡- "የተቀበልነው እኛ 318ቱ ነን፤ ሃይማኖትን ያቀናን ሙሽራዋ አምላካችን እግዚአብሔር የሆነ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሠራን" ስለሚል - "ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 64፣ ገጽ 200፤ ቊ. 71፣ ገጽ 201፤ ቊ. 132፣ ገጽ 211 እና ቊ. 134፣ ገጽ 213 ይመልከቱ።

[191] ሠራዊቱ፡- "እርሱን በማመን ሰማዕታት ስለእርሱ ደማቸውን አፈሰሱ" በማለት ስለሚጨርስ - "ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 115፣ ገጽ 159።

[192] "ለእርሱ ለወዳጅህ መላእክትና ሊቃነ መላእክት ይሰግዱለታል። የአለቆች አለቆች፥ ከሰማይና ከምድር በታች የሚጠራም ስም ሁሉ። የሚካኤል ሠራዊት በየነገዳቸው፥ የገብርኤልም ሠራዊት በየማኅበራቸው፥ ኪሩቤልም በግርማቸው፥ ሱራፌልም በቅዳሴያቸው፥ የመላእክትም ሠራዊት ሁሉ በየወገናቸው በቅዱሳን ምስጋና የሚመሰገን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል" ስለሚል፤ ጳጉሜ የዓመቱ መጨረሻ እንደሆነች በእነዚህ 5 ወይም 6 ቀናት የዓለሙ ፍጻሜ ይታሰባል። ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ "ሐዳፌ ነፍስ" በተባለው ክፍል የዚህ ዓለምን ፍጻሜና ነገረ ምጽአትን በሰፊው ስለሚያነሳ በዕለታተ ጳጉሜ ይቀደሳል - "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 15-16፣ ገጽ 342-343 እና ቊ. 87-101፣ ገጽ 354-357 ይመልከቱ።

9) በበዓለ ደብረ ዘይት እና ነገረ ምጽአት (የጌታ ዳግም መምጣት) በሚወሳባቸው እሑዶች፥ እንዲሁም ግንቦት 7 ቀን (የቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ አትናቴዎስ፤[193]

10) በዘመነ ክረምት፥ "ቅድስት" በተባለችው የዐቢይ ጾም እሑድ፥ በምሴተ ኀሙስ እና ግንቦት 17 ቀን (የቅዱስ ኤጲፋንዮስ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፤[194]

11) ዝክረ አበው፥ የነቢያት መታሰቢያ በሚደረግባቸው ቀናት እና ሐምሌ ሦስት ቀን (የቅዱስ ቄርሎስ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ቄርሎስ፡፡

12) በኤጲስቆጶሳት ሢመት (ሹመት)፥ በዝክረ ጳጳሳት (በጳጳሳት መታሰቢያ) እና ጥር ስድስት ቀን (የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ በዓለ ዕረፍት)፡- ቅዳሴ ባስልዮስ፡፡[195]

አባዛኞቹ ካህናት የግጻዌውን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ አይከተሉም፤ ግጻዌው ረጃጅም ቅዳሴያትን (ለምሳሴ፡- ቅዳሴ አትናቴዎስ፥ ዘሠለስቱ ምእት፥ ዘኤጲፋንዮስ ወዘተ.)

---

[193] ከሌሎች ቅዳሴያት ለየት ባለ መልኩ የሰንበተ ክርስቲያንን ክብር እና ነገረ ምጽአትን በሰፊው ያወሳል፡፡ መጽሐፈ ግጻዌ ዓመቱን ለሦስት ከፍሎ፥ በአራት ወር አንድ ጊዜ፥ በሦስት እሑዶች (በአስተምህሮ፥ በደብረ ዘይት/ ዐቢይ ጾም እና በክረምት) ቅዳሴ አትናቴዎስ እንዲቀደስ ያዛል - *መጽሐፈ ግጻዌ ከነምልክቱ ዘይትነበብ እምዓመት እስከ ዓመት ወዘሰናብት ዘየኀብር ምስለ መዝሙራት፡* አሳታሚ፡- መምህር አባ ጥዑመ ልሳን ኪዳነ ማርያም (አዲስ አበባ፡ አክሱም ማተሚያ ቤት፡ 1994 ዓ.ም.) ገጽ 167፥ 173 እና 183 ይመልከቱ ፡፡ ቅዳሴ አትናቴዎስና ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ነገረ ምጽአትን በሰፊው ስለሚያትቱ ከሁለቱ አንዱን እንደ አማራጭ ወስዶ በበዓለ ደብረ ዘይትና የጌታ ምጽአት በሚታሰብባቸው ሰናብት (እሑዶች) መቀደስ ይቻላል፡፡

[194] በክረምት የሚታየውን የእግዚአብሔርን መግቦት፡- "ከምድር ዳርቻ ደመናውን ያወጣል፥ መብረቅንም በዝናብ ጊዜ አደረገ፤ ዝናብንም እንደ መሸረብ ነጠብጣብ ያፈሳል፤ ጉምን እንደ አመድ ይበትነዋል፤ በረዶንም እያጠቃቀነ ያወርዳል፤ ለእንስሳም ሣሩን ያለመልማል" እያለ ስለሚያነሳ፤ ስለእግዚአብሔር ፍጹም ቅድስና፡-እግዚአብሔር በገናንነቱ ገናና ነው፥ በቅድስናው የተቀደሰ ነው፥ በምስጋናው የተመሰገነ ነው፥ በክብሩም የከበረ ነው" ስለሚል፤ እንዲሁም ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካ ያደረገበትን ቤት አስመልክቶ፡- "በዚያች ሌሊት ለዐርብ አጥቢያ ኀሙስ ማታ በወዳጁ በአልዓዛር ቤት በተቀመጠ ጊዜ . . ." የሚል ነክ ስላለው - "ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 35፣ ገጽ 292፤ ቍ. 3፣ ገጽ 287 እና ቍ. 58፣ ገጽ 295 ይመልከቱ፡፡

[195] የግእዙ ቅዳሴ ባስልዮስ (ከዐረብኛ የተተረጐመው) ዐረፍተ ዘመን የገታቸውን የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳትን ስለሚያነሳ - "ቅዳሴ ባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 81-84፣ ገጽ 255-260 ይመልከቱ፡፡

በሚያዝበት ጊዜ ሰዓት ለመቆጠብ በሚል ሰበብ አጭሩን ቅዳሴ (አኰቴተ ቊርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት) መርጠው ይቀድሳሉ፡፡ ነገር ግን ይህን በማድረጋቸው ከ10 እና 15 ደቂቃዎች በላይ አይቆጥቡም፤ ደግሞስ እንደ መላእክት ለቅዳሴ አገልግሎት የተጠሩ ካህናት ከተፈጠሩበት ዓላማ (ከስብሐተ እግዚአብሔር) የሚበልጥ ምን ጉዳይ አላቸው? አንዳንዴም "ምእመናን ይቸኩላሉ" የሚል ምክንያት ይሰጣሉ፤ ነገር ግን ምእመናን፥ ሰምተዋቸው የማያውቁት ረጃጅም ቅዳሴያት ሲቀደሱና ካህኑ ረጋ ብሎ በአማርኛ የሚያነበው ከሆነ፥ በቅዳሴያቱ ጥልቅ የነገረ መለኮት ትምህርት ተነክተው በተመስጦ ያዳምጣሉ እንጂ በፍጹም ቅዳሴ ረዘመ ብለው አያማርሩም፡፡ ስለዚህ የቅዳሴያቱን ውብ እና ድንቅ አስተምህሮ ለምእመናኑ የምናሳውቅበት አንዱ መንገድ፥ እንደ ግጻዌው ትእዛዝ የዕለቱን አኰቴተ ቊርባን መርጦ መቀደስ መሆኑን የቤተ ክርስቲያናችን ካህናት ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

## አውሥኦ (ምልልስ)

እንደሌሎቹ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ማንኛውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የሚጀምረው ካህኑ ከምእመናን ጋር በሚያደርገው አውሥኦ (ምልልስ) ነው፡፡ [196] የሶርያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች ቅዳሴ የሆነው አኰቴተ ቊርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታ ወንድም) እንደሚከተለው ይጀምራል፡-[197]

- ካህን፡- የእግዚአብሔር አብ ፍቅር፥ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን (2 ቆሮ. 13 14)፡፡
- ሕዝብ፡- ከመንፈስህ ጋር፡፡

[196] ከአውሥኦ በፊት በቅዳሴ እግዚእ ዲያቆኑ፡- "በሰማይ የሃሉ ልብክሙ"፤ በቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ደግሞ፡- "ጸልዩ በእንተ አበዊነ ጳጳሳት . . ." ይላል - "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 2፣ ገጽ 125፤ "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ" ቊ. 1፣ ገጽ 269፡፡ ነገር ግን ቅዳሴያቱ የሚጀምሩት የምልሱ (Dialogue) መነሻ በሆነው የካህኑ ቡራኬ፡- "እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ" እንጂ በዲያቆኑ የማነቃቂያ ትእዛዝ (acclamation) አይደለም፡፡ መጽሐፈ ኪዳን ላይ ቅዳሴው የሚጀምረው ከዲያቆኑ ትእዛዝ በኋላ መሆኑን ሲያመለክት፡- "ዲያቆን ከመዝ ይበል ቅድመ አኰቴት፡- በሰማይ የሃሉ ልብክሙ" ([ከአኰቴተ ቊርባን] በፊት ዲያቆን "ልባችሁ በሰማይ ይሁን" ይበል) ይላል፡፡ *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 34.

[197] "አኰቴተ ቊርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ," *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 107.

- ካህን፡- ሕሊናችሁ፥ አሳባችሁና ልባችሁ በሰማይ ይሁን፡፡
- ሕዝብ፡- በእግዚአብሔር ዘንድ አለን፡፡[198]
- ካህን፡- እግዚአብሔርን እናመስግነው፡፡
- ሕዝብ፡- እውነት በእውነት ይገባል፡፡[199]

የእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ቅዳሴ በመባል የሚታወቀው አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ አውሥኦ (ምልልስ) አለው፡-[200]

- 1) ካህን፡- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ (እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን)
- ሕዝብ፡- ምስለ መንፈስከ (ከመንፈስህ ጋር)፡፡
- 2) ካህን፡- አልዕሉ አልባቢክሙ (ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ)፡፡
- ሕዝብ፡- ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ (በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን)፡፡
- 3) ካህን፡- አእኵትዎ ለአምላክነ (አምላካችንን አመስግኑት)፡፡
- ሕዝብ፡- ርቱዕ ወጽድቅ ይደልዎ (እውነት በእውነት ይገባዋል)፡፡

ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ ያለው አኰቴተ ቍርባን ከዚህ ጋር አንድ አይነት አውሥኦ (ምልልስ) ይዟል፡፡ [201] ይህን አኰቴተ ቍርባን መሠረት አድርጎና ተስፋፍቶ የተዘጋጀው ቅዳሴ ሐዋርያት ግን ከላይ የተጠቀሱትን ተራ ቍጥር 2 እና 3ን ያቀያይራቸዋል፤[202] "አእኵትዎ ለአምላክነ" ለሚለው ሕዝቡ የሚሰጠው መልስ "ርቱዕ ይደሉ" የሚል ብቻ ነው፡፡

በኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የተደረሱ ቅዳሴያት በሙሉ የቅዳሴ ሐዋርያትን አውሥኦ ይከተላሉ፡፡ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመው የቅዳሴ ባስልዮስ

---

[198] የእንግሊዝኛው ትርጉም፡- "With the Lord God are our minds, out intellect and our hearts" ይላል - Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 209.

[199] በሌሎቹ ቅዳሴያት "ርቱዕ ይደሉ" የሚለውን፥ እዚህ ቅዳሴ ላይ አንድ ቃል ጨምሮ፡- "ርቱዕ ወጽድቅ ይደሉ" ይላል፡፡

[200] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 117.

[201] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11።

[202] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 3፣ ገጽ 87፡፡

አውሥኦ ግን ከላይ የተጠቀሰውን የቅዳሴ ማርቆስን ቅደም ተከተል ይዟል፡፡[203] በ318ቱ የኒቂያ ጉባኤ ሊቃውንት የተሰየመው ቅዳሴ፥ ሁለት አይነት ምልልሶችን ያስነብበናል፡፡ ቅዳሴው እንደሌሎቹ ቅዳሴያት፥ በቅዳሴ ሐዋርያት አውሥኦ ይጀምርና[204] የክርስቶስን የማዳን ሥራ ዘርዝሮ ከጨረሰ በኋላ "በዚያም (በመቃብር) ሳለ ወደ ባርያው ወደ አዳም፥ ወደ ልጆቹም [እንዲህ ብሎ] ጮኸ" ከሚለው ማብራሪያ ጋር የሚከተለውን አውሥኦ ያስነብበናል፡-[205]

- ካህን፡- እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡
- ሕዝብ፡- ከመንፈስህ ጋር፡፡
- ካህን፡- አምላካችንን አመስግኑት፡፡
- ሕዝብ፡- እውነት ነው ይገባል፡፡
- ካህን፡- ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ፡፡
- ሕዝብ፡- በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን፤ የሰማይ አባታችን ሆይ (ሦስት ጊዜ) ጌታችንና አምላካችን አንተ ነህ፡፡

ይህ አውሥኦ የአኰቴተ ቍርባኑ መጀመሪያ ላይ ከተባለ በኋላ እዚህ ቦታ ላይ የተደገመው፥ ጌታችን ክርስቶስ አዳምንና ልጆቹን ለማዳን በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ከወረደ በኋላ ምንም ተስፋ በሌለበት በዚያ የጨለማና የእስር ሥፍራ የሰጣቸውን ሰላም ለማመልከት ይመስላል፡፡ እነርሱም በሲኦል እየተሰቃዩ ነጻ የሚያወጣቸውን መድኃኒት ሲጠባበቁ ነበርና ድምፁን ሲሰሙ "ጌታችንና አምላካችን አንተ ነህ" አሉት፡፡

## ተዝካረ ቅዱሳን ወጸሎት በእንተ እለ ኖሙ

የአኰቴተ ቍርባን አንዱ ክፍል በሕይወት ያሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ፓትርያርክ እና ሊቃነ ጳጳሳት የሚጠሩበት፥ ወደ ጌታ ደስታ የገቡ ቅዱሳን የሚዘከሩበት (ማቴ. 25፥21 እና 23) እና በዚህ ምድርና በዐጸደ ነፍስ ላሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚቀርብ የምልጃ ጸሎት ነው፡፡ በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ይህ የምልጃ

---

[203] "ቅዳሴ ባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 5-6፣ ገጽ 243፡፡
[204] "ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 12፣ ገጽ 192፡፡
[205] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 99-100፣ ገጽ 206፡፡

ጸሎት የሚቀርበው ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ከተሰኘው የአኰቴተ ቍርባኑ ጸሎት በኋላ ነው፡፡ ለምሳሌ አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ እና መሠረቱ ሶርያ ውስጥ እንደሆነ የሚነገርለት ቅዳሴ ባስልዮስ ይህን ቅደም ተከተል ይጠብቃሉ፡፡[206]

በእንጻሩ ደግሞ የግብፅ ቅዳሴያት በአኰቴተ ቍርባኑ መቅድም እና ዝማሬ ሱራፌል መሃል በሚገቡ የምልጃ ጸሎታት ይታወቃሉ፡፡[207] አብዛኞቹ የአገራችን ቅዳሴያት ይህን ይዘት ይከተላሉ፤ በቅዳሴ ሐዋርያት፥ በቅዳሴ እግዚእ፥ በቅዳሴ ማርያም፥ በቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ በቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ እና በቅዳሴ ዲዮስቆሮስ መቅድሙን አቋርጦ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት. . ." ከሚለው ዝማሬ በፊት "በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ" በማለት የሚጀምር የምልጃ ጸሎት ይገባል፡፡ [208] ካህኑ ይህን ጸሎት ሲያጠናቅቅ በቅዳሴ ሐዋርያት፡- "የእኒህንም የሁሉንም ነፍሳቸውን አሳርፍ፡ ይቅርም በላቸው"[209] ፥ በቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ደግሞ፡- "እኒህንና ሁሉንም ስማቸው የተጠራውንና ስማቸው ያልተጠራውን፥ ይህ በጎ መታሰቢያ በፊትህ የተደረገላቸውንም ነፍሳቸውን አሳርፍ፡ ይቅርም በላቸው" ይላል፡፡[210] በሌሎቹ አገር በቀል ቅዳሴያት ግን የምልጃ ጸሎቱ የአኰቴተ ቍርባኑን መቅድም ሳያቋርጥ በዝማሬ ሱራፌል እና በሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ መካከል ይገኛል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ቅዳሴያት፡- ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፥ ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፥ ቅዳሴ አትናቴዎስ፥ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፥ ቅዳሴ ቄርሎስና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ ናቸው፡፡[211]

---

[206] "አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ," *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 110-112፤ "ቅዳሴ ባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 40-42፣ ገጽ 248-249 እና ቍ. 87፣ ገጽ 260፡፡
[207] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 118.
[208] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 87፥ 128፥ 164፥ 309፥ 341 እና 360 ይመልከቱ፡፡
[209] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 23፣ ገጽ 91፡፡
[210] "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 8፣ ገጽ 342፡፡
[211] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 75፣ ገጽ 151፤ ቍ. 74፣ ገጽ 202፤ ቍ. 105፣ ገጽ 230፤ ቍ. 44፣ ገጽ 294፤ ቍ. 74፣ ገጽ 330 እና ቍ. 23፣ ገጽ 372 ይመልከቱ፡፡

## ጸሎተ ቡራኬ

ሌላው የአገራችን ጸሎታተ ቍርባን መለያ ባሕርይ (ጠባይ) ከላይ የተጠቀሰውን የምልጃ ጸሎት ተከትሎ የሚመጣ "ጸሎተ ቡራኬ" ማስገባታቸው ነው፡፡[212] ጸሎቱ ለሥሉስ ቅዱስ የሚቀርብ ሲሆን በዋነኝነት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንዲበዛልን፤ የሰማዩ ነፋስ፥ በየጊዜው የሚዘንበው ዝናብና የምድሩ ፍሬ እንዲባረክ ልመናን ያቀርባል፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴ የዚህ ጸሎት ደራሲ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ እንደሆነ ለጸሎቱ በሰጠው ርእስ ጠቁሞናል:- "ጸሎተ ቡራኬ ዘባስልዮስ"፡፡[213] ተስፋ ጽዮን እ.አ.አ. በ1548 ሮም ላይ ላሳተሙት የግእዝ ሐዲስ ኪዳን አባሪ አድርገው ያስገቡት ሥርዓተ ቅዳሴ፥ ጸሎተ ቡራኬን "ወዕቀቦሙ በሃይማኖት" በማለት ከሚጀምረው ጸሎት ጋር ያቀርበዋል፡፡[214] "ወዕቀቦሙ … በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ በቀናች ሃይማኖት በጌትነትና በክብር ጠብቃቸው" በማለት የሚጀምረው ጸሎት፥ ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በኋላ የሚጸለዩ ጸሎታት እንዳበቁ ንፍቁ ካህን እንዲጸልየው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ይገኛል፡፡[215] ይህ ጸሎት (ወዕቀቦሙ) ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ከተተረጐመው ግብረ ሕማማት የተወሰደ ስለሆነና ሁለቱ ጸሎታት (ጸሎተ ቡራኬ እና ወዕቀቦሙ) ተያያዥነት ስላላቸው የጸሎተ ቡራኬም መገኛ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ልትሆን ትችላለች፡፡

ሁሉም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት አንድ አይነት ጸሎተ ቡራኬ የላቸውም፡፡ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (ዘሆሣዕና) እና ቅዳሴ ባስልዮስ ዘቂሣርያ በሚቀደሱበት ጊዜ፥ በተለመደው ጸሎተ ቡራኬ ምትክ የሰማይና የምድር ፍጥረታት

---

[212] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 10-21፣ ገጽ 89-91፡፡
[213] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 10፣ ገጽ 89.
[214] Tasfā-Ṣəyon (ed.) *Testamentum Novum […] Missale cum benediction incensi, cerae […] quae omnia Fr. Petrus Ethyops asuxilio piorum sedente Paulo III pont. Max. et Claudio illius regni imperatore imprimis curvit [Romae] anno sal.* MDXLVIII [1548] fols. 158-67.
[215] "ወዕቀቦሙ በርትዕት ሃይማኖት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 154-161፣ ገጽ 119-122፡፡

በሙሉ እንዲባረኩ የሚማልድ በጣም አስደናቂ ጸሎተ ቡራኬ እንዲጸለይ መጽሐፈ ቅዳሴው ያዛል፡-[216]

> ልዩ ሦስት አቤቱ ዓለሙን ሁሉ የያዝህ፥ በቃልህ ሥልጣን ደገኛና ድንቅ ሥራን የሠራህ፤ ምሥራቁንና ምዕራቡን፥ ሰሜኑንና ደቡቡን፥ መስዑንና አዜቡን[217] ባርክ፤ ሰማይንና ምድርን፥ ባሕሩንና ወንዞቹን፥ የውኃውንም ፈሳሾችና የውኃውንም ምንጭ ሁሉ ባርክ፡፡
>
> የሰማይን ነፋስ፥ ዝናሙንም ባርክ፡፡ ፀሓይንና ጨረቃን፥ ከዋክብትንም ባርክ፡፡ ተራራውንና ኮረብታውንም፥ ዕንጨቱንና ሰብሉን፥ የምድርንም ፍሬ ባርክ፡፡ ከሰማይ በታች ያሉትን፥ ከምድርም በታች ያሉትን ባርክ፡፡ አምላካችን ክርስቶስ ሆይ፥ በልቡናቸው ስምህን መፍራትን ምላ፤ [ሕይወታቸውንም] እስከ ዘላለሙ አከናውን፡፡

## ዝማሬ ሱራፌል

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ፥ ሱራፌል የተሰኙት ነገደ መላእክት፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች" (ት. ኢሳ. 6፥3) እያሉ ያለዕረፍት ለሥሉስ ቅዱስ በሰማያት ምስጋናን ሲያቀርቡ ተመልክቷል፡፡ ይኸው ራእይ ለወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ የተገለጸ ሲሆን እርሱም ያየውን ጽፎልናል (ራእ. 4፥8)፡፡ በቅዳሴ ሰዓት ይህን የማያቋርጥ የነገደ ሱራፌል ምስጋና በምድር ሆነን ስንዘምረው ከቅዱሳን መላእክት ጋር የአምልኮ ኅብረት ይኖረናል፡፡ ዝማሬ ሱራፌል የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጸሎታተ ቅዳሴ ውስጥ መግባት የጀመረው በ4ኛው ምእት ዓመት ስለሆነ ከዚያ በፊት የተደረሱ ቅዳሴያት ውስጥ አናገኘውም፡፡ በምዕራፍ ሦስት እንደተመለከትነው ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ የሚገኘው አኰቴተ ቊርባን፥ እግዚአብሔር አብ በአንድያ ልጁ ያደረገውን የማዳን ሥራ ሲገልጽ "ወፈነውከ እምሰማይ ወልደከ ውስተ ማኅፀነ ድንግል። ዘሥጋ ኮነ ወተጸውረ ውስተ በከርሥ፤ ወወልድከ ተዐውቀ እመንፈስ ቅዱስ" ካለ በኋላ "እምድንግል ተወሊዶ ከመ ይፈጽም ፈቃደከ ወሕዝበ ለከ ይግበር"[218] በማለት

---

[216] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 56-59፣ ገጽ 278 እና "ቅዳሴ ባስልዮስ" ቊ. 88፣ ገጽ 260 ይመልከቱ፡፡

[217] መስዕ በሰሜንና በምሥራቅ በኩል ያለ አቅጣጫ ነው፤ ሰሜን ምሥራቅ ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡ አዜብ ደግሞ በመስዕ ትይዩ በደቡብ በኩል ያለ (ደቡብ ምዕራብ) ነው፡፡ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ*፡ ገጽ 614፡፡

[218] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 11። በግእዝ የተጠቀሰው ጥቅስ፥ በታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ የሚከተለው የአማርኛ ትርጉም ተሰጥቶታል፡- "ልጅህን ከሰማይ ወደ

ይቀጥላል፡፡ ይህ አኰቴተ ቍርባን አንዳንድ ጸሎታት ተጨምረውለት ቅዳሴ ሐዋርያት እንደተባለ በምዕራፍ ሦስት ተመልክተናል፡፡ በቅዳሴ ሐዋርያት፥ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ጥቅሶች መካከል ለመላእክቱ ዝማሬ መግቢያ የሚሆን መጠነኛ ገለጻ[219] እና የመላእክቱ ዝማሬ ተጨምሮበታል፡-

> አእላፈ አእላፋትና ትእልፊተ አእላፋት[220] የሚሆኑ ቅዱሳን መላእክት፥ የመላእክትም አለቆች፥ ክንፋቸው ስድስት የሚሆን ክቡራን አርባዕቱ እንስሳም[221] ከፊትህ ለሚቆሙልህ ለአንተ. . . በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤ በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍናሉ፤ በሁለት ክንፋቸው ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ይወጣሉ . . . ሁሉም ዘወትር አንተን ከሚቀድሱህና ከሚያመሰግኑህ ሁሉ ጋር እንዲቀድሱና እንዲያመሰግኑ፤ ዳግመኛ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ፍጹም [የሠራዊት ጌታ][222] እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው፡፡[223]

ስለቅዱሳን መላእክቱ የተሰጠውን ተመሳሳይ አገላለጽ በቅዳሴ ማርቆስ እናገኛለን፡፡ ቅዳሴ ሐዋርያት "ክቡራን አርባዕቱ እንስሳ" እና "ክንፋቸው ስድስት የሚሆን" በማለት የሚገልጻቸውን ነገደ መላእክት፥ ቅዳሴ ማርቆስ፡- "ኪሩቤል እለ ብዙኃት አእይንቲሆሙ" (ዓይኖቻቸው ብዙ የሆኑ ኪሩቤል - ራእ. 4፥8)፥ "ወሱራፌል እለ ስድስቱ ክነፊሆሙ" (ክንፎቻቸው ስድስት የሆኑ ሱራፌል - ራእ. 4፥8) በማለት ይጠራቸዋል፡፡[224] ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ደግሞ "ኪሩቤል እሳታውያን፥ ወሱራፌል ልቡሳነ ብርሃን" (እሳታውያን የሚሆኑ ኪሩቤል፥ ብርሃን የለበሱ ሱራፌል) የሚል

---

ድንግል ማኅፀን [ሰደድህ]፤ በማኅፀን ተወሰነ፥ ሥጋም ሆነ፥ ልጅህም በመንፈስ ቅዱስ ታወቀ፡፡ . . . ከድንግል ተወልዶ ፈቃድህን ይፈጽም ዘንድ፥ ሕዝቡንም ላንተ ያደርግ ዘንድ" - "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 23 እና 33፣ ገጽ 91 እና 92፡፡

[219] Pre-sanctus.

[220] በግእዝ "እልፍ" 10,000 ሲሆን፥ "አእላፍ" የሚለው ደግሞ የ100,000 አቻ ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ*፣ ገጽ 95)፡፡ የመላእክት ብዛት ሊቆጠር ስለማይችል "አእላፈ አእላፋትና ትእልፊተ አእላፋት" በሚል መልኩ ተገልጸዋል፤ በእንግሊዝኛ thousands of thousands and myriads of myriads እንደማለት ነው፡፡

[221] ግእዙ "ሱራፌል ወኪሩቤል" የሚሉ ቃላትን ይጨምራል፡፡

[222] "ጸባዖት" (*Shabaot*) የሚለው የዕብራይስጥ ቃል "የሠራዊት ጌታ" ማለት ነው፤ የኮፕቲክ ቅዳሴ እንግሊዝኛ ትርጉም፡- "Lord of Hosts" ይላል - *Holy Euchologion*, 2004, p. 92፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ ግን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ "አሸናፊ" የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

[223] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 10-21፣ ገጽ 89-91፡፡

[224] "አኰቴተ ቍርባን ዘአቡነ ማርቆስ ወንጌላዊ," *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 120.

ግሩም አገላለጽ ይጠቀማል፡፡ [225] ባለራእዩ ዮሐንስ "በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ" ሲል ጽፎልናል (ራእ. 8፥2)፡፡ በጌታችን በዓለ ልደት የሚቀደሰው የቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ (ሁለተኛ) ደራሲ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ክብር የሚቀርቡ ግሩማን (አስፈሪዎች) መላእክት ቍጥር ስምንት እንደሆነ ይነግረናል፡- "ወደ አንተ የሚቀርቡ ስምንቱ ግሩማን ናቸው፤ ከእሳት ማዕበልም የተነሣ ወደ አንተ እንዳይቀርቡ ይሸሻሉ፤ ከአፍህ ከሚወጣው ፍሕመ እሳት የተነሣ ይፈራሉ ይደነግጣሉ፡፡"[226]

ዝማሬ ሱራፌልን ቀድሞ የሚመጣው የአኰቴተ ቍርባን ክፍል፥ ግሩማን ስለሆኑ መላእክት ወይም ስለነገዳቸው ብዛት ገላጻ ከማቅረብ በተጨማሪ ከእነርሱ ጋር የአምልኮ ኅብረት እንዲሰጠን ለልዑል እግዚአብሔር ልመና ያቀርበል፡፡ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ የመላእክትን ሠራዊትና ነገድ ከዘረዘረ በኋላ "በአንድነት የጌትነትህን ምስጋና ያሳርጉልሃል፤ ከእነርሱ ጋር . . . እኛንም አስተካክለን" ይላል፡፡ [227] ተመሳሳይ ልመና በቅዳሴ አትናቴዎስ እናገኛለን፡- "በምስጋና ቃል እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት መላእክት እንሁን፡፡" [228] ይኸው ቅዳሴ ያለዕረፍት በሰማያት ቅዱሳን መላእክት የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያመሰግኑት መጠነኛ ገለጻ ይሰጠናል፡-

> [በየመዓርጋቸውና] በየማኅበራቸው፥ በየነገዳቸውና በየሠራዊታቸው፥ በየስማቸውና በየቍጥራቸው የሚጋርዱ አሉ፤ የሚከቡም አሉ፡፡ በዜማ የሚያመሰግኑ አሉ፤ የሚዘምሩም አሉ፡፡ በልብ የሚያመሰግኑ አሉ፤ በቃልም የሚያመሰግኑ አሉ፡፡ ክንፎቻቸው ስድስት [የሆኑም አሉ] . . . ፡፡[229]

ተጨማሪና አስደናቂ ገለጻዎችን ቅዳሴ ቄርሎስና ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ውስጥ እናገኛለን፡-

> የሚያቃጥል እሳት እንዳያቃጥላቸው በሁለቱ የእሳት ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፡፡ ግሩም የሚሆን ብርሃኑ (ነበልባሉ) እንዳይመታቸው በሁለት የብርሃን ክንፋቸው

[225] "ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 27፣ ገጽ 291፡፡

[226] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 6፣ ገጽ 370፡፡

[227] "ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 19፣ ገጽ 142፡፡

[228] "ቅዳሴ አትናቴዎስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 53፣ ገጽ 223፡፡

[229] ዝኒ ከማሁ፡፡

> እግራቸውን ይሸፍናሉ፡፡ … ሱራፌል በአለቆቻቸው፥ ኪሩቤል በምስጋናቸው፥ መላእክት በየሥርዓታቸው፥ ትጉሃንም በየሠራዊታቸው፡፡ የትጉሃን አለቆች በየወገናቸው፤ እሳትነት ያላቸው መላእክት በብርሃናቸው፤ መንፈሳውያን [በባሕርያቸው] ግሩም በሚሆን ቃል ያመሰግናሉ፥ ይቀድሳሉ፤ ከፍ ባለና በታላቅ ቃልም ይጮኻሉ፡፡[230]
>
> ለእርሱ ለወዳጅህ (ለአንድ ልጅህ) መላእክትና ሊቃነ መላእክት ይሰግዱለታል፡፡ የአለቆች አለቆችና ከሰማይና ከምድር በታች የሚጠራም ስም ሁሉ [ይሰግድለታል]፡፡ የሚካኤል ሠራዊት በየነገዳቸው፥ የገብርኤልም ሠራዊት በየማኅበራቸው፥ ኪሩቤል በግርማቸው፥ ሱራፌልም በቅዳሴያቸው፥ የመላእክት ሠራዊት ሁሉ በየወገናቸው በቅዱሳን ምስጋና የሚመሰገን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፡፡[231]

እንደነዚህ አይነት ድንቅ ገላጻዎችን በመስጠት ወደ ዝማሬ መላእክት የሚያሸጋግሩን ቅዳሴያት እንዳሉን ሁሉ፥ ለዝማሬው ምንም አይነት መግቢያ ሳይሰጡ ወደ ዝማሬው የሚገቡ ቅዳሴያትም አሉን፡፡ ለምሳሌ ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰደው ቅዳሴ እግዚእ "ከድንግል ተወልዶ ፈቃድህን ይፈጽም ዘንድ፥ ሕዝቡንም ንጹሕ አድርጎ ያከናውንልህ ዘንድ" ካለ በኋላ "አውሥኡ - ተሰጥዎውን መልሱ" የሚለውን የዲያቆኑን ትእዛዝ አስገብቶ ወደ ዝማሬ ሱራፌል ያመራል፡፡ ከዛም "እጀቹን ለሕማም ዘረጋ …" የሚለውን የአኰቴተ ቍርባኑን መቅድም ይቀጥላል፡፡[232] እዚህ ላይ ስለሰማያዊው የመላእክት ዝማሬ የተሰጠ ምንም አይነት ገለጻ ወይም መግቢያ አናነብም፡፡ መጽሐፈ ኪዳን ላይ ካለው አኰቴተ ቍርባን የሚጨምረው ነገር ቢኖር ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ጥቅሶች መካከል የሱራፌልን ዝማሬ ማስገባቱ ነው፡፡[233] እንደ ቅዳሴ እግዚእ፥ ለመላእክቱ ዝማሬ መግቢያ የሚሆን መጠነኛ ገለጻ ሳያደርጉ ወደ መላእክቱ ዝማሬ በቀጥታ የሚገቡ ቅዳሴያት፡- ቅዳሴ ማርያም፥ ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት፥ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እና ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ናቸው፡፡[234]

## ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ቍርባንን በሠራበት የአይሁድ ፋሲካ፥ ለደቀ ቀመዛሙርቱ "እንጀራን [አንሥቶ፥ ባርኮና ቆርሶ] እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ

[230] "ቅዳሴ ቄርሎስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 7-8፣ ገጽ 324፡፡

[231] "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 15-16፣ ገጽ 342-343፡፡

[232] "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 30-32፣ ገጽ 129-130፡፡

[233] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 36-37.

[234] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 167፥ 193፥ 271 እና 310 ይመልከቱ፡፡

ነው . . . ጽዋውንም አንሥቶ፥ አመስግኖም . . . ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ብሎ እንደሰጣቸው በቅዱስ ወንጌል እናነባለን (ማቴ. 26፥ 26-28)፡፡ እዚህ ላይ ሦስት ነገሮችን እናያለን፡- መባረክ (ማመስገን)፥ መቁረስና መስጠት፡፡ በቅዳሴም ካህኑ እነዚህን ሦስት ነገሮች ያከናውናል፡- ኅብስቱንና ወይኑን ይባርካል (ምስጋና ያቀርባል)፥[235] ይፈትታል (ይቆርሳል) ከዚያም "ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ቅዱስ ሥጋሁ ለክርስቶስ - ከሰማይ የወረደ የሕይወት ኅብስት የሚሆን የክርስቶስ ክቡር ሥጋ"[236] እያለ የጌታን ሥጋ ያቀብላል፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ጌታ ትእዛዝ ሕማሙን፥ ሞቱንና ትንሣኤውን እያሰበች (ሉቃ. 22፥ 19፤ 1 ቆሮ. 11፥26) የምታቀርበው አኰቴተ ቊርባን ከሚያካትታቸው ጸሎታት መካከል፥ ከላይ ከቅዱስ ወንጌል የተጠቀሱትና ጌታችን ሥርዓተ ቊርባንን የመሠረተባቸው ቃላት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ (ጌታ ቅዱስ ቊርባንን የመሠረተበት ቃል) የሚለው ስያሜ የሚያመለክተው ካህኑ እነዚህን ቃላት የሚጠቅስበትን የአኰቴተ ቊርባኑን ክፍል ነው፡፡

ከዝማሬ ሱራፌል ወደ ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ ለመሸጋገር አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት መድኃኒታችን ስለእኛ ኃጢአት ተላልፎ ከተሰጠባት ሌሊት ይጀምራሉ፡-

> እርሱን በያዙባት በዚያች ሌሊት ነውር በሌለባቸው ንዑዳት፥ ክቡራት፥ ብፁዓትም በሚሆኑ እጆቹ ኅብስቱን አንሥቶ ያዘ፡፡ . . . ወደ አንተ ወደ አባቱ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ አመሰገነ፥ ባረከ፥ ቈረሰ፡፡[237]

"ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እለ እንበለ ነውር" የሚለው ዐረፍተ ነገር ቃል በቃል ቅዳሴ እግዚእ[238] እና ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ[239] ውስጥ

---

[235] ቅዳሴ ምስጋና ማለት ነው፤ የግሪኩ አቻ *evcharistia* ሲሆን ይህም (thanksgiving) የሚል ትርጒም ይሰጠናል፡፡ ቤተ ክርቲያናችን መሥዋዕት አድርጋ የምታቀርበው ኅብስትና ጽዋ የሚባረክበትን ጸሎት "አኰቴተ ቊርባን - የቊርባን ምስጋና (eucharistic thanksgiving)" ብላ መጥራቷ ተገቢ ነው፤ ስያሜውም ትክክለኛ ነው፡፡

[236] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 115፣ ገጽ 110፡፡

[237] ዝኒ ከማሁ፥ 1994፣ ቊ. 39 እና 41፣ ገጽ 93-94፡፡

[238] "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 38፣ ገጽ 130፡፡

[239] "አኰቴተ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ" *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 108.

ተጠቅሷል፡፡ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፥ ልብን በሚነካ አገላለጽ፡- “አባታችንን አዳምን በፈጠረባቸውና በተቸነከሩ እጆቹ ኅብስቱን ያዘ” ይላል፡፡[240] ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ደግሞ ጌታ ኅብስቱን በእጆቹ አንሥቶ መያዙን ብቻ ሳይሆን የያዘውን ኅብስት ምሥጢራዊ ትርጕም እንዲህ ያስነብበናል፡- “ቅዱሳት ብፁዓት በሚሆኑ እጆቹ ኅብስቱን ያዘ፤ ለሙሽራህ [ለቤተ ክርስቲያን] ማጫዋ፥ ለተውካት [ለፈታሃት] ምኵራብም መፋቻዋ (መፍቻዋ) የሚሆን፡፡”[241]

ከዚህ ገለጻ ቀጥሎ ካህኑ በወንጌላት የተጠቀሱትን የጌታን ቃላት እንዲህ በማለት ይደግማል፡-

> ለወገኖቹ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፡፡ “ንሡ ብሉ ይህ ኅብስት ለኃጢአት ማስተሥረያ ሊሆን ስለእናንተ የሚፈተት ሥጋዬ ነው” አላቸው፡፡ እንዲሁም ጽዋውን አመስግኖ፥ ባርኮ፥ አክብሮ ለወገኖቹ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፡፡ “ንሡ ጠጡ ይህ ጽዋ ለብዙ ሰዎች ቤዛ ሊሆን ስለ እናንተ የሚፈስ ደሜ ነው” አላቸው . . . ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የእኔን መታሰቢያ አድርጉ፡፡[242]

በዚህ ጊዜ ምእመናን “አሜን፥ አሜን፥ አሜን እናምናለን፤ እንታመናለን”[243] በማለት እምነታቸውን ይገልጻሉ፡፡ አብዛኞቹ ቅዳሴያት በሦስቱ ወንጌላት (ማቴ. 26፥26-28፤ ማር. 14፥22-24፤ ሉቃ. 22፥19-20) የምናገኛቸውንና ሥርዓተ ቍርባን የተመሠረተባቸውን የጌታን ቃላት ሲጠቅሱ፥ የቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ሠራዔ ቃል ግን በዮሐንስ ወንጌል ጌታ ኢየሱስ “ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ . . . ሥጋዬ እውነተኛ መብል፥ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና” (ዮሐ. 6፥54-55) ሲል የተናገራቸውን ቃላት ይጠቀማል፡-

> “ይህ ኅብስት ለዓለም ሁሉ ደኅንነትን የሚሰጥ እውነተኛ የጽድቅ መብል ሥጋዬ ነው ንሡ ብሉ” ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፡፡ የበላውም እስከ ዘላለሙ ይድናል፡፡ . . . ይህ “ጽዋ እውነተኛ የሕይወት መጠጥ የሚሆን ደሜ ነውና ንሡ ጠጡ” ብሎ ለወገኖች

[240] “ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 31፣ ገጽ 273፡፡
[241] “ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 83፣ ገጽ 153፡፡
[242] “ቅዳሴ ሐዋርያት” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 42፥ 44 እና 46፣ ገጽ 94፡፡
[243] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 43 እና 45፣ ገጽ 94፡፡

> ለሐዋርያት ሰጣቸው፡፡ [ከእርሱ] የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡ ለሕይወትና ለመድኃኒት ይሆናችሁ ዘንድ ሁላችሁ ንሡ ጠጡ፡፡[244]

በአብዛኞቹ የአገራችን ቅዳሴያት የምናገኛቸው ሠራዔ ቃላት በሌሎቹ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ቅዳሴያት ውስጥ እንደተለመደው "ኅብስቱን አንሥቶ፥ ባርኮ፥ ቆርሶ ሰጣቸው" እንዲሁም "ጽዋውን አመስግኖ፥ ባርኮ፥ አክብሮ ሰጣቸው" የሚል አንድ አይነት የቃላትና የ3ኛ መደብ አነጋገርን ያሳያሉ፡፡ ሁለተኛው የጎርጎርዮስ ቅዳሴ ግን ገለጻ ጨምሮና መደቡንም 2ኛ መደብ አድርጎ (አቅርቦ) "ይህ ኅብስት [ለኃጢአት ሥርየት/ ይቅርታ] ለዘላለም ሕይወት ስለናንተ ተፈትቶ (ተቆርሶ) የሚሰጥ ሥጋዬ ነው፤ ንሡ ብሉ ብለህ ለደቀ መዛሙርትህ የሰጠሃቸው አንተ ነህ" ይላል፡፡ እንዲሁም፡- "በጽዋው ላይ ነገርሃቸው፤ "ይህ ጽዋ [ለኃጢአት ሥርየት/ ይቅርታ] ለዘላለም ሕይወት ስለእናንተ የሚፈስ የሚሰጥም ደሜ ነው፤ ንሡ ጠጡ ብለህ"[245] ሰጠሃቸው የሚል ለየት ያለ ንባብ ይዟል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ የተለየ ሠራዔ ቃል በቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ እናነባለን፡-

> ቅዱሳት በሚሆኑ በእጆችህ ኅብስትን ያዝጎ፡፡ ለንጹሐን ደቀ መዛሙርትህ ትሰጣቸው ዘንድ፡፡ …ከበረከት ጋር ያን ጊዜ እንደ ባረክህ አሁንም ይህን ኅብስት ባርከው፤ ያን ጊዜ ከማመስገን ጋር የቈረስህ፡ አሁንም ይህን ኅብስት ቍረሰው፡፡ … ዳግመኛም የወይኑን ጽዋ ከውኃ ጋር ቀላቅለህ ለንጹሐን [ሐዋርያትህ] ትሰጣቸው ዘንድ፤ ያን ጊዜ ያከበርህ አሁንም ይህን ጽዋ አክብረው፤ ያን ጊዜ የሰጠህ አሁንም ይህን ጽዋ ስጠው፡፡[246]

እዚህ ጥቅስ ውስጥ ከላይ ያየነውና በወንጌላቱ የተጠቀሰው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃላት ስለማይገኙ ይህ ቅዳሴ፥ ሠራዔ ቃል የለውም በማለት አኰቴተ ቍርባን የመሆን ብቃቱን ጥያቄ ውስጥ ያስገቡ ምሁራን ነበሩ፡፡ ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ምንም እንኳን የጌታን ቃላት ባይዝም፥ በምሴተ ኀሙስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀምጦ ኅብስቱንና ጽዋውን ባርኮ የሰጣቸውን ጌታ አሁንም ይህንኑ እንዲያደርግ ስለሚጠይቅና ሠራዔ ቃሉን

---

[244] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 33 እና 35፣ ገጽ 273-274፡፡

[245] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 34 እና 36፣ ገጽ 374፡፡ ቅዳሴ አትናቴዎስም፡- "ሥጋዬ ነው ንሡ ብሉ . . . ደሜ ነው ንሡ ጠጡ ብለህ ሰጠሃቸው" ይላል - መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 130 እና 132፣ ገጽ 234፡፡

[246] "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 42-43 እና 45-46፣ ገጽ 346-347፡፡

በመተረክ መልኩ ባይሆንም፥ ቁልፍ ወይም ገዥ የሆኑት ሠራዕያን ቃላትን (መባረክ፥ መቁረስ፥ መስጠት) ስለያዘ ሠራዔ ቃል ተብሎ ሊጠራ እንደሚገባው አሳማኝ በሆነ መልኩ ሞግተዋል፡፡[247]

## ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ

ከላይ የተመለከትነው ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ የተሰኘው የአኰቴተ ቍርባን ክፍል "ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የእኔን መታሰቢያ አድርጉ"[248] በማለት ይጨርሳል፡፡ ስለሆነም እንደ ጌታ ትእዛዝ በግሪኩ *ሓናምኔሲስ* (ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ) በተባለው የቅዳሴው ክፍል ካህኑ፡- "አሁንም አቤቱ ሞትህንና ትንሣኤህን እናስባለን፥ እናምንሃለን፤ እያመሰገንህ ይህን ኅብስት፥ ይህንንም ጽዋ እናቀርብልሃለን" ይላል፡፡[249] የቅዳሴ አትናቴዎስ ሠራዔ ቃል:- "ይህን ኅብስት በምትበሉበት፥ ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት [ጊዜ ሞቴንና ትንሣኤዬን] ንገሩ፤ ወደ ሰማይ ማረጌንም እመኑ፤ ዳግመኛ በክብር መምጣቴን ተስፋ እያደረጋችሁ"[250] ይላል፡፡ ስለዚህ በቅዳሴ ጊዜ የምናስበው የጌታን ሞት ብቻ ሳይሆን ትንሣኤውን፥ ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱንም[251] ነው፡- "አቤቱ ሞትህን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም እንናገራለን፡፡ ዕርገትህን፥ ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን፤ [እናመሰግንሃለን] እናምንሃለንም፡፡ ጌታችንና አምላካችን ሆይ፡ እንለምንሃለን፤ እንማልድሃለንም"፡፡[252] የተወሰኑት ቅዳሴያት "አሁንም አቤቱ ሞትህንና ትንሣኤህን እናስባለን" በማለት የሚጀምረው የካህኑ ጸሎት ባይኖራቸውም፥ ከላይ የተጠቀሰው የምእመናን ዝማሬ (አቤቱ ሞትህን፥ ቅድስት ትንሣኤህንም እንናገራለን...) በሁሉም ቅዳሴያት ውስጥ ስለሚገኝ፥ ሁሉም

---

[247] Habtemichael Kidane, "The Institution Narrative-Anamnesis in the Ethiopian Anaphora of James of Sərug," *'Faire mémoire': l'anamnése dans la liturgie,* eds. André Lossky and Manlio Sodi," Menumenta Studiea Instrumenta Liturgical, Vol. 63 (Vatican City: 2011) pp. 132-134.

[248] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 46፣ ገጽ 94፡፡

[249] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 48፣ ገጽ 95፡፡

[250] "ቅዳሴ አትናቴዎስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 133፣ ገጽ 235፡፡

[251] የቅዳሴው ሰዓት ተራ ጠብቆ ከሚጓዘው ከዚህ ዓለም ጊዜ/ሰዓት (chronos) የተለየና የእግዚአብሔርን መንግሥት ጊዜ የምንለማመድበት ሰዓት (kairos) ስለሆነ ወደ ፊት የሚከናወነው የጌታ ምጽአት አሁን እንደተደረገ አድርገን እናስባለን፡፡

[252] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 47፣ ገጽ 95፡፡

ጸሎታተ ቍርባን *ኣናምኔሲስ* የተሰኘውን የአኰቴተ ቍርባን ክፍል ይዘዋል ማለት ይቻላል፡፡

## ሠለስቱ ቅዳስያት ዘአኰቴተ ቍርባን

በቅዳሴው ሁለተኛ ክፍል ውስጥ የሚዘመረው "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት . . ." የሚለው ዝማሬ (ሠለስቱ ቅዳስያት)[253] ሁለት ጸሎታተ ቍርባን ውስጥ በንባብ ይባላል፡፡ ቅዳሴ ማርያም በምሥጢረ ሥላሴ ላይ ያለውን አስተምህሮ ሲጨርስ "እንዲህ እናምናለን አንዲህም እንታመናለን የሃይማኖትን ጸሎት እንበል"[254] በማለት በቅዳሴው የቀረበውን ትምህርተ ሥላሴ ለመቀበላቸው ማረጋገጫ ምእመናኑ ጸሎተ ሃይማኖትን እንዲደግሙ ያዛል፡፡ በእመቤታችን ማኅፀን የተከናወነውን ምሥጢረ ሥጋዌ (የአምላክ ሰው የመሆን ምሥጢር) አድንቆ ሲጨርስ ደግሞ፥ ሰው የሆነውን አምላክ "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት . . ." እያልን እናመስግነው ይላል፡፡[255] ይህ ዝማሬ እዚህ ቦታ ላይ የገባው በመለኮታዊ ባሕርዩ በቦታ የማይወሰነው፥ ሕማምና ሞት የሌለበት ወልደ እግዚአብሔር፥ በሥጋ በድንግል ማኅፀን ተወስኖ ከእርሷ ተወለደ፥ ከእመቤታችን በነሣው ሥጋ ታመመ፥ ሞተ የሚለውን ትምህርተ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ለማስገንዘብ ነው፡፡

ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ (*ኣናምኔሲስ*) በተሰኘው የአኰቴተ ቍርባኑ ክፍል፡- "የተሰበሰብን እኛም የማይታመም የእርሱን ሕማሙን እንናገራለን፤ የማይሞት የእርሱን ሞቱን እንናገራለን" ይላል፡፡[256] ለእኛ ቤዛነት የተደረገውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማሙንና ሞቱን ልብን በሚነካ መልኩ ከገለጸው በኋላ፡- "ጻድቃን ከዕንጨት አወረዱት፥ ሥጋውንም ለመገነዝ ከርቤ የሚባል የጣፈጠ ሽቱንና ንጹሕ በፍታን አመጡ" ይልና "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት . . ." የሚለውን ዝማሬ

---

[253] Trisagion.
[254] "ቅዳሴ ማርያም" *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 78፣ ገጽ 175፡፡
[255] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 88-89፣ ገጽ 176-177፡፡
[256] "ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 45፣ ገጽ 312፡፡

ያስገባል፡፡[257] ይህ ዝማሬ እዚህ ቦታ ላይ እንዲገባ የተደረገበት ምክንያት የቅዳሴው *አናምኔሲስ* ላይ የተጠቀሰውን አስተምህሮ (በመለኮታዊ ባሕርዩ ሞት የሌለበት አምላክ በሥጋ ሞተ የሚለውን) ለማጠናከር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡[258]

## ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ

ቅዳሴውን የሚመራው ሠራዒ ካህን (ኤጲስቆጶስ ወይም ጳጳስ) ወደ እግዚአብሔር አብ በሚያደርገው ጸሎት፥ መንፈስ ቅዱስን ወደ ኅብስቱና ጽዋው እንዲልክና የተላከውም ቅዱስ መንፈስ በሕሊናችን ልንረዳው የማንችለውን ምሥጢር እንዲያከናውን ይለምናል፡፡ ይህ ወሳኝ የአኰቴተ ቍርባን ክፍል ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ (በግሪኩ *ኤፒክሌሲስ*) ይባላል፡፡ ካህኑ መንፈስ ቅዱስ እንዲላክ የሚጠይቀው በቀረበው መሥዋዕት ላይ ብቻ ሳይሆን ለቅዳሴው አገልግሎት በተሰበሰቡ ልኡካን እና ምእመናን ላይም ጭምር ነው፡- "እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ፈኑ ላዕሌነ ወላዕለ ዝንቱ ቍርባን ዘአቅረብነ መንፈሰከ ቅዱሰ - ሁሉን የያዝህ እግዚአብሔር አብ፡ ቅዱስ መንፈስህን በእኛ ላይና ባቀረብነው በዚህ ቍርባን ላይ ላክ"፡፡[259] የቅዳሴ ሐዋርያት ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል[260]፡-

> ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፈኑ መንፈሰ ቅዱሰ ወኃይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ ይረስዮ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም፡፡
>
> በዚህ ኅብስት [እና በዚህም ጽዋ] ላይ [መንፈስ ቅዱስንና ኃይልን ትልክ ዘንድ] እንለምንሃለን፡ እንማልድሃለንም፤ የጌታችን፥ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ያደርገው ዘንድ ለዘለዓለሙ፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ጸሎት ውስጥ የተሰመረበት ግስ (ይረስዮ) ያላቸውና የሌላቸው ቅዳሴያትን መጽሐፈ ቅዳሴ በዝርዝር ያሳየናል፡፡ "ይረስዮ" የሌላቸው

---

257 ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 63-64፣ ገጽ 314-315፡፡

258 Habtemichael Kidane, "Does the Ethiopian Pre-Anaphora Maintain the Egyptian Preparatory Service? Towards a Study of the Sərə'ata Qəddase," p. 92.

259 "አኰቴተ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ," *Missale Ethiopicum,* 1945, p. 108. የቅዳሴ ባስልዮስ *Epiclesis* ላይም ተመሳሳይ ጸሎት እናገኛለን፡- "አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ . . . በፊትህ ወደ ተሠራው ወደዚህ ቍርባን በአባትህ ፈቃድ መንፈስ ቅዱስን ትልክ ዘንድ፥ ታነጻው ዘንድ፥ እኛንም በቅድሳትህ ታከብረን ዘንድ፡፡" "ቅዳሴ ባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 40፣ ገጽ 248፡፡

260 "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 48-49፣ ገጽ 95፡፡

ቅዳሴያት፡- ቅዳሴ ማርያም፥ ቅዳሴ ፫ቱ፻፥ ቅዳሴ አትናቴዎስ፥ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (የባስልዮስ ወንድም) ፥ ቅዳሴ ቄርሎስ፥ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ ሲሆኑ፤ ያላቸው ደግሞ፡- ቅዳሴ ሐዋርያት፥ ቅዳሴ እግዚእ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፥ ቅዳሴ ባስልዮስ፥ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፥ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅና ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ናቸው፡፡[261] የኋለኛው ዝርዝር ውስጥ፥ ካልታተሙት የቤተ ክርስያናችን ቅዳሴያት መካከል፡- መዓዛ ቅዳሴን (ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ)፥ ቅዳሴ ማርቆስንና ቅዳሴ ያዕቆብ እኅሁ ለእግዚእነን መጨመር ይቻላል፡፡[262] ይህ አከፋፈል ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ያላቸውንና የሌላቸውን የሚለይ ይመስላል፤ ነገር ግን ይረስዮ (ያደርገው ዘንድ) የሚለውን ግስ ሳይዙ ግልጽ የሆነ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው ቅዳሴያት (አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ቄርሎስ፥ ዘቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እና ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ)[263] ስላሉና አከፋፈሉ ማእከል ያደረገው "ይረስዮ" የሚለውን ግስ ብቻ ስለሆነ በቀጥታ ወሳኝ ከሆነው የአኰቴተ ቍርባን ክፍል (*ኤፒክሌሲስ*)[264] ጋር ይያያዛል ማለት አይደለም፡፡ ወይም ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ያላቸውና የሌላቸው የሚል ትርጉምን አያሰጥም፡፡[265] በዚህ ግንዛቤ መሠረት ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ቅዳሴያት የሚከተሉት ናቸው፡- ቅዳሴ ማርያም፥ ቅዳሴ ፫ቱ፻፥ ቅዳሴ አትናቴዎስ እና ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ፡፡

ቅዳሴ ቄርሎስና ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ "ሜሎስ ሰይፈ እሳት" የሚሉ ቃላትን በመጠቀም ቅዱሱ መንፈስ በኅብስቱና በጽዋው ላይ እንዲወርድ የሚጠይቅ ጸሎት አላቸው፡-

> የሚነድ የእሳት ሰይፍ ሜሎስ ይገለጽ፥ ሰማየ ሰማያትም በቸርነትህ ይከፈት፥ በፈቃድህም ሕያውና ቅዱስ መንፈስህ ይላክ፥ ይውረድ፥ ይምጣም፡፡ በዚህም ኅብስትና ጽዋ ላይ ይረፍ፡፡ ይባርከው፥ ይቀድሰውም፤ ከአንድ ልጅህ ከጌታችንና ከአምላካችን ከመድኃኒታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ጋር አንድ ይሆን ዘንድ፡፡[266]

---

[261] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 383፡፡

[262] Habtemichael Kidane, "A Note on the Aspects of the Epiclesis of the Gə'əz Anaphora of St. James of Sərug," *Rites and Rituals of the Christian East,* eds. Bert Groen, Daniel Galadza, Nina Glibetick and Gabriel Radle, Eastern Christian Studies*,* Vol. 22 (Leuven: Peeters, 2014) p. 153.

[263] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 21፣ ገጽ 272፤ ቍ. 70፣ ገጽ 333፤ ቍ. 53፣ ገጽ 348 ይመልከቱ፡፡

[264] Epiclesis (invocation of the Holy Spirit) - ጽዋኤ መንፈስ ቅዱስ፡፡

[265] Habtemichael Kidane, "A Note on the Aspects of the Epiclesis of the Gə'əz Anaphora of St. James of Sərug," p. 153.

[266] "ቅዳሴ ቄርሎስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 70፣ ገጽ 333፡፡

በዚህ ጸሎት ውስጥ ያለው የመጨረሻው ዐረፍተ ነገር ፥ "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?" የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ያስታውሰናል (1 ቆሮ. 10፥16)። የቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ "የእግዚአብሔር በግ እነሆ ይውረድ በእኔ በባሪያህ ፊት በተዘጋጀ በዚህ በክህነት ማዕድ ላይ ይቀመጥ። የሚያስደነግጥ የእሳት ሰይፍ ሜሎስ ይላክ፤ በዚህ ኅብስትና ጽዋ ላይም ይገለጥ፤ ይህን አኰቴት ፍጹም ያደርግ ዘንድ" የሚሉ ሁለት ልመናዎችን ያቀርባል።[267] ይህ ጸሎት እንደሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያን፥ የእግዚብሔር በግ የተባለውና (ዮሐ. 1፥ 36) ለኃጢአታችን ቤዛ ይሆን ዘንድ የተሠዋው ኢየሱስ ክርስቶስ በመንበሩ ላይ ተገልጦ ከቀረበው መሥዋዕት ጋር ይዋሐድ ዘንድ (አንድ ይሆን ዘንድ) ያላትን ፍላጎት እንረዳለን። በኅብስቱና በወይኑ ላይ ወርዶ የማይመረመረውን ምሥጢር ያከናውን ዘንድ የተጠየቀው ግን "የእሳት ሰይፍ ሜሎስ" የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው።[268]

ከላይ እንደተመለከተነው ሠራዒው ካህን በቀረበው ኅብስትና ወይን ላይ መንፈስ ቅዱስን እንዲልክ የሚጸልየው ወደ እግዚአብሔር አብ ነው። የተወሰኑ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት ግን ይህንን ጸሎት ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያቀርባሉ። ለምሳሌ ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፦ "እኛም ጌታችንና አምላካችን እንለምንሃለን፥ እንማልድሃለንም። ሰውን የምትወድ ሆይ ከቸርነትህ እንሻለን፤ ወደዚህ ኅብስት ወደዚህም ጽዋ መንፈስ ቅዱስን ኃይልንም ትሰድ ዘንድ" ይላል።[269] ምንም እንኳን ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ (ኤፒክሌሲስ) የተሰኘው ጸሎት ትክክለኛ ቦታው ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ እና ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ ከተባሉት ጸሎታት በኋላ ቢሆንም፥ እነዚህን ሁሉ ቀድሞ የሚመጣው የቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

---

[267] "ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 53፣ ገጽ 348።
[268] Habtemichael Kidane, "A Note on the Aspects of the Epiclesis of the Gəʻəz Anaphora of St. James of Sərug," p. 158.
[269] "ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 68፣ ገጽ 296።

> አቤቱ ጌታዬ ሊቅ፥ ከቀዳማዊና ከደኃራዊ ጋር አንድ የምትሆን[270] ከሰማይ የወረድህ የሕይወት ኅብስት አንተ ነህ፡፡ በዚህ ኅብስት ላይና በዚህ ጽዋ ላይ መንፈስ ቅዱስን ኃይልንም ላክ፡፡[271]

\

ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጸለዩ የጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ተጨማሪ ጸሎታትን በቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ[272] እና በቅዳሴ ዲዮስቆሮስ[273] እናገኛለን፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፥ ቅዳሴ ማርያም የሚመደበው ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ከሌላቸው ቅዳሴያት መካከል ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጸሎት በሚጸለይበት የአኰቴተ ቍርባን ቦታ ላይ የሚከተለውን የቡራኬ ጥያቄ ያቀርባል፡- "ኦ እግዚኦ በከመ አሜሃ ዘንተ ኅብስተ ባርክ፥ ወፈትት ወሀብ ... ኦ እግዚኦ በከመ አሜሃ ዘንተ ጽዋዐ እተብ፥ ወቀድስ ወመጡ - አቤቱ እንደዚያን ጊዜ ይህን ኅብስት ባርከህ፥ ቈርሰህ ስጥ ... አቤቱ እንደዚያን ጊዜ ይህን ጽዋ ባርከህ፥ አክብረህ ስጥ"፡፡[274] የመጽሐፈ ቅዳሴ አንድምታ "በይረስዮ ፋንታ የገባ"[275] ይለዋል፤ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ በተሰኘው ጸሎት ምትክ የገባ ብለን ልንወስደው እንችላለን፡፡

## ጸሎተ ፈትቶ፥ ኅዳፌ ነፍስ ወአንብሮ እድ

በሦስተኛው ምእት ዓመት አንደተደረሱ የሚነገርላቸው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጸሎታተ ቍርባን ፍጻሜ፥ ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስን ተከትሎ የሚመጣው የማጠቃለያ ምስጋና ነበር፡፡ ለምሳሌ ሐዋርያዊ ትውፊት ውስጥ የሚገኘው አኰቴተ ቍርባን የመደምደሚያ ጸሎት እንዲህ ይላል፡-

> [ናስተበቍዐከ] ከመ ትፈኑ መንፈሰከ ቅዱሰ ዲበ ቍርባን ዘቤተ ክርስቲያን፤ ደሚረከ ተሀብ ለኵሉ ለእለ ይነሥኡ ቅድሳተ፥ ወለምልዐተ መንፈስ ቅዱስ ወለአጽንዖ ሃይማኖት፥ በአማን ከመ ኪያከ [ይሰብሑ ወይወድሱ] በወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ዘቦቱ ለከ ስብሐት ወኃይል በቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፥ አሜን።[276]

---

[270]አልፋና *ዖሜጋ* (ፊተኛውና መጨረሻው አንተ ነህ) ለማለት ነው - ራእ. 2፥8፡፡

[271] "ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 21፣ ገጽ 271-271፡፡

[272] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 70፣ ገጽ 316፡፡

[273] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 39፣ ገጽ 363-364፡፡

[274] "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 112-113፣ ገጽ 179-180፡፡

[275] "ቅዳሴ ማርያም" *መጽሐፈ ቅዳሴ አንድምታ*፡ 1991፣ ምዕራፍ 6፡ ቍ. 40፣ ገጽ 257፡፡

[276] *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 22 እና 24.

ቅዱስ መንፈስህን በቤተ ክርስቲያን ቊርባን ላይ ትልክ ዘንድ እንማልድሃለን፤ ቅዱስ ቊርባንን ለሚቀበሉ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ለመመላትና እውነተኛውንም እምነት ለማጽናት አንድ አድርገህ ትሰጥ ዘንድ፡፡ አንተን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ፈጽመው ያመሰግኑ ዘንድ፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእርሱ ያለህ ምስጋና እና ኃይል ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡[277]

ይህን ጸሎትና የማጠቃለያ ምስጋና ተከትሎ ጥንታዊው የምእመናን ዝማሬ ይዘመር ነበር፡- "በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም"[278] (በፊት እንደነበረ ለዘላለሙ ለልጅ ልጅ ይኖራል)፡፡ የመጽሐፈ ኪዳን አኰቴተ ቊርባን ከዚህ ዝማሬ በኋላ "ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ" (የአንተ በሚሆን መንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን) በማለት የሚጀምረውን ጸሎት ኤጲስቆጶሱ ሲጸልይ ምእመናንም እንደርሱ ጸልየው "ማኅተመ አኰቴት"[279] (የአኰቴተ ቊርባን ፍጻሜ) እንደሚሆን ይጠቁማል፡፡ በ4ኛው ምእት ዓመት የተጻፈው የቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም ትምህርተ ንኡሰ ክርስቲያን እንደ ሚያመለክተው፥ ከጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ተዝካረ ቅዱሳን እና ላረፉ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚደረገው የልመና ጸሎት ተጨምሮ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸው ጸሎት (አቡነ ዘበሰማያት - ማቴ. 6፥ 9-13) የአኰቴተ ቊርባኑ ፍጻሜ ሆነ፡፡[280] ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እዚህ ቦታ ላይ የሚጸለየውና ጌታ ያስተማረው ጸሎት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን ቅዳሴያት (ጸሎታተ ቊርባን) መቋጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡[281]

---

[277] ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ፡፡

[278] *The Statutes of the Apostles,* trans. Horner, ትእዛዝ ፳፪፣ ገጽ 12፤ *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 24 ። የዚህ ጥንታዊ መዝሙር የኮፕቲክ ቅዳሴ የእንግሊዝኛ ትርጉም፡- "As it was, and shall be, from generation to generation, and unto all ages of ages. Amen" ይላል - *Holy Euchologion*, 2004, p. 106. መጠነኛ ልዩነት የሚያሳየው የሶርያ ቅዳሴ እንግሊዝኛ ትርጉም ደግሞ እንዲህ ይላል፡- "Amen. As it was, and is and shall be, from generation to generation, for all generations and for ever and ever. Amen" - Varghese, *The Living Sacrifice,* p. 221.

[279] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 40.

[280] Kent J. Burreson, "The Anaphora of the Mystagogical Catecheses of Cyril of Jerusalem," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Bradshaw, p. 138-139.

[281] Iskander, *Understanding the Liturgy*, p. 70.

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት፥ ጸሎተ ፈትቶ (የመፈተት ጸሎት)[282] መሃል ጌታ ያስተማረውን ጸሎት በማስገባት ከላይ የተጠቀሰውን ጥንታዊ ትውፊት ይከተላሉ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያናችን አኰቴተ ቊርባን የራሱ የሆነ "ጸሎተ ፈትቶ"፥ "ኅዳፌ ነፍስ" እና "አንብሮ እድ" የተሰኙና ከሌላው ቅዳሴ ለየት ያሉ ጸሎታትን ይዟል፡፡[283] የመጀመሪያው ጸሎት ካህኑ "ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ"[284] (የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን) በማለት የሚጀምረውን ዝማሬ እያዜመ ሥርዓተ ፈትቶውን ካከናወነ በኋላ የሚጸልየው ነው፡፡ ሁለተኛው ጸሎት "ኅዳፌ ነፍስ" (ነፍስን የምታሻግር) የሚል ስያሜ ያገኘው፥ ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰደውና[285] ምእመናን የጌታን ሥጋና ደም ከተቀበሉ በኋላ በቅዳሴ እግዚእ ካህኑ የሚጸልየው የምስጋና ጸሎት በእነዚህ ሁለት ቃላት ስለሚጀምር ነው፡- "ኅዳፌ ነፍስ፥ ለጻድቃን መርሕ ወለቅዱሳን ምክሕ፤ ሀበነ እግዚኦ አዕይንተ አእምሮ ወትረ ኪያከ ይርአያ፥ ወአእዛንነሂ ቃለ ዘባሕቲትከ ይስምዓ . . ." (ነፍስን የምታሻግር፥ ለጻድቃን መሪ፥ ለቅዱሳን መመኪያ፤ አቤቱ የዕውቀት ዓይኖችን ስጠን፡፡ ዘወትር አንተን ያዩ ዘንድ፤ ጆሮቻችንም ያንተን ብቻ ቃል ይሰሙ ዘንድ . . .)"[286] በሌሎቹ ቅዳሴያት "አንብሮ እድ" (እጅ መጫን) የተሰኘው ጸሎት ሠራዒው ካህን የጌታን ሥጋ ለምእመናን አቀብሎ ወደ መቅደስ

---

[282] Prayer of Fraction.

[283] ከእነዚህ ጸሎታት በተጨማሪ "ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም - የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮች የሚሆኑ የመላእክት ሠራዊት" በማለት የሚጀምረው የቅዱስ ያሬድ ዝማሬ በይዘት አንዳንድ ቅዳሴያት ላይ ለውጥ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ የቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ሠራዊት፡- "ወይኬልልዎ መላእክት ዘእሳት መንጦላዕቱ ለመድኃኔ ዓለም፤ በእንተ ሥጋሁ ቅዱስ፡ ወበእንተ ደሙ ክቡር፡፡ ወንብጸሕ ቅድመ ገጹ ከመ ንባእ ውስተ ጽርሐ ቅድሳቱ ለመድኃኔ ዓለም፤ አሚነነ ኪያሁ ተወኪለነ ቦቱ ነሐዩ" ይላል - የአማርኛ ትርጉሙን፡- መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 69፣ ገጽ 351 ላይ ይመልከቱ፡፡ ስለዚህ ዝማሬ፥ አባቶቻችን በቅዳሴው ውስጥ ስላሉት ምሳሌያት ትርጒም በጻፉት ጽሑፍ፡- "ሠራዊተ መላእክቲሁ የያሬድ ነው" ብለዋል፡፡ Getatchew Haile, "An Amharic Study on the Liturgy and Symbolism of the Ethiopian Church," *Ethiopian Studies in Honour of Amha Asfaw* (New York: No publisher given, 2017) EMML 1157, f. 222v, p.94.

[284] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 54፣ ገጽ 96፡፡

[285] *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 43.

[286] "ቅዳሴ እግዚእ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 81፣ ገጽ 137-138፡፡

ከተመለሰ በኋላ የሚጸልየው ሲሆን፥ በቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ግን በዜማ እያሰማ ምእመናንን የሚባርክበትና የሚያሰናብትበት[287] ነው፡-

> ሠናይ ለክሙ (በጎ ነገር ተደረገላችሁ - ሦስት ጊዜ)፡፡ የክርስቶስ የበጎቹ መንጋዎች ሆይ፥ በልታችሁ ጠገባችሁ፥ ጠጥታችሁ ረካችሁ፡፡ በሰላም ወደ ቤታችሁ ግቡ፤ እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይኑር፡፡[288]

## ፫. ቅዱስ ቊርባንን ከመቀበል በፊት እና በኋላ

ገባሬ ሠናዩ ዲያቆኑ፡- "የቆማችሁ ሰዎች ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ"[289] በማለት ሠራዒው ካህን ስለእነርሱ ለሚጸልየው ጸሎት (ጸሎተ አድንኖ)[290] ምእመናንን ያዘጋጃቸዋል፡፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያናችን አኰቴተ ቊርባን የራሱ የሆነ ጸሎተ አድንኖ ያለው ሲሆን፥ በቅዳሴ ሐዋርያት ካህኑ ራሳቸውን በትሕትና ዝቅ ስላደረጉ ሰዎች ከመጽሐፈ ሲኖዶስ[291] በተወሰደው ጸሎት እንዲህ በማለት ይጸልያል፡-

> የተሰወረውንና የተገለጸውን የምታውቅ ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር ሆይ፥ ወገኖችህ በፊትህ ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ አደረጉ፡፡ የሥጋ ልቡናቸውንም አስገዙ፤ ከተዘጋጀ ማደሪያህ ሁነህ እይ፡፡ ወንዶችንም ሴቶችንም ባርክ፡፡ ጆሮህን [ወደ እነርሱ አዘንብል]፤ ጸሎታቸውንም ስማቸው፡፡[292]

ከዚህ ቀጥሎ ካህኑ "ጸሎተ ንስሓ"[293] የተሰኘውን ረጅም ጸሎት ይጸልያል፡፡ ይህ ጸሎት ከኮፕቲክ ቅዳሴ በትርጒም የተገኘ ነው፤[294] ጸሎቱን ሠራዒው ካህን ቅዳሴ

---

[287] በሌሎቹ ቅዳሴያት "እትዉ በሰላም - በሰላም ግቡ" በማለት ምእመናንን የሚያሰናብተው ዲያቆኑ ነው - "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 165፣ ገጽ 123፡፡

[288] "ቅዳሴ ዮሐንስ አፈ ወርቅ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 107፣ ገጽ 322፡፡

[289] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 67፣ ገጽ 99፡፡

[290] Prayer of inclination - Fritsch, "Qəddase," *EA*, Vol.4, p. 274.

[291] *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt,* trans. Duensing, ትእዛዝ ፳፩፣ ገጽ 26።

[292] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 68፣ ገጽ 99፡፡

[293] ዝኒ ከማሁ፥ ቊ. 72-88፣ ገጽ 99-103፡፡

[294] የግብፁ መጽሐፈ ቅዳሴ የእንግሊዝኛ ትርጒም *The Absolution of the Father* የሚል ርእስ ሰጥቶታል፡፡ *Holy Euchologion*, 2004, p. 110.

ከመጀመሩ በፊት ይጸልየዋል፡፡እዚህ ቦታ ላይ ደግሞ የሚጸልየው ቅዳሴው ከመጀመሩ በፊት በሰዓቱ ላልተገኙ ሰዎች ነው፡፡[295]

## ቅድሳት ለቅዱሳን

ገባሬ ሠናዩ ዲያቆን "ነጽር" (ተመልከት፥ አስተውል)[296] ወይም በአንዳንድ የብራና መጻሕፍት ላይ እንደተጠቀሰው "ንነጽር" (እንመልከት፥ እናስተውል)[297] በማለት የጌታን ሥጋና ደም ለመቀበል እንድንዘጋጅ ያዘናል፡፡ ይህን ተከትሎ፥ ካህኑ "ቅድሳት ለቅዱሳን" የሚለውንና ምእመናንን ወደ ጌታችን ሥጋና ደም የሚጠራ በትን ጥሪ ያሰማል፡፡ "ቅድሳት ለቅዱሳን"[298] የሚሉት ቃላት ከ4ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ የአኰቴተ ቊርባን ክፍል እንደነበሩ የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ፡፡[299] "ቅድሳት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የክርስቶስን ሥጋና ደም ሲሆን፥ የካህኑ ጥሪ "እነዚህ ምሥጢራት የሚሰጡት ለተቀደሱ ሰዎች (ለቅዱሳን) ነው" የሚል መልእክት አለው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም የእነዚህን ሁለት ቃላት ትርጉም ሲያብራራ፥ በመሥዋዕቱ ላይ መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ የተቀደሰ እንደሚሆንና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የተቀበሉ አማንያንም ቅዱሳን እንደሆኑ ጽፏል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥሪ ቅዱስ ቊርባንን ከቅዱሳን ጋር ያገናኛል ማለት ነው፡፡[300]

---

[295] ከንፈ ገብርኤል አልታዬ (ሊቀ ካህናት)፡ *ሥርዓተ ቤተክርስቲያን* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡ 1983 ዓ.ም.) ገጽ 63፡፡

[296] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 89፣ ገጽ 103፡፡

[297] አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ፥ *የቅዳሴያችን ይዘት*፣ ገጽ 135፡፡ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት መጻሕፍተ ሥርዓት መካከል አንዱ የሆነው Apostolic Constitutions (ሐዋርያዊ ሕግጋት) ምእመናንን ለቅዱስ ቊርባን የሚያዘጋጀው የዲያቆኑን ትእዛዝ፡- Let us attend" (እንመልከት/ እንሳተፍ) የሚል እንደነበር ዘግቦልናል፡፡ *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles),* Book VIII, Ch. 13, 1848, p. 181.

[298] በላቲኑ *Sancta sanctis* ወይም በእንግሊዝኛ፡- Holy things for the holy ones.

[299] *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles),* Book VIII, Ch. 13, 1848, p. 181፤ Kent J. Burreson, "The Anaphora of the Mystagogical Catecheses of Cyril of Jerusalem," *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers,* ed. Bradshaw, p. 138-139.

[300] St. Cyril of Jerusalem, *Mystagogical Catechesis*, quoted in Iskander, *Understanding the Liturgy*, p. 70.

በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ካህኑ "ቅድሳት ለቅዱሳን"[301] የሚለው ኅብስቱ የተቀመጠበትን ፃሕል እና ጽዋውን ከፍ በማድረግ[302] ነው፤ ይህም የጌታ ዕርገት ምሳሌ የሚል ትርጒም ተሰጥቶታል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ግን ካህኑ ኅብስቱን ከፍ እንዲያደርግ "ያንሥእ ካህን ኅብስተ ፍጹመ" የሚለውን ትእዛዝ የሚጠቁመን፥ ካህኑ በልዑል ዜማ ሦስት ጊዜ እና በንኡስ ዜማ 15 ጊዜ "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" እያለ በሚያዜምበት ጊዜ እንጂ "ቅድሳት ለቅዱሳን" ሲል አይደለም፡፡[303] በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ካህኑ "ቅድሳት ለቅዱሳን" ሲል፥ ምእመናኑ "ቅዱስ የሆነ አንድ አለ፤ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ለዘላለሙ የተባረከ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ" [304] የሚል መልስ ይሰጡ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት በኮፕቲክ ቅዳሴ ካህኑ "ቅድሳት ለቅዱሳን" ከሚለው አዋጅ ጋር አብሮ "ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ቡሩክ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ ቀድሷቸዋል" ይላል፡፡ [305] የምእመናኑ መልስ በእኛም ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ እንደተጠቀሰው፡- "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" የሚል ነው፡፡ [306] ቀዳሹ ካህን "ቅድሳት ለቅዱሳን" (የተቀደሱት ምሥጢራት ለቅዱሳን ናቸው) ሲል፥ ምእመናን፡- "ቅዱስ አብ አንድ ነው፤ ቅዱስ ወልድም አንድ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አንድ ነው" የሚል መልስ ለምን ይሰጣሉ? የሚል ጥያቄ ቢነሣ፥ በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ምእመናኑ ለካህኑ ጥሪ የሚሰጡት መልስ ጥያቄውን ይመልሰዋል፡- "ከአንዱ ቅዱስ አብ፥ ከአንዱ ቅዱስ ወልድ እና ከአንዱ ቅዱስ መንፈስ በስተቀር ማንም ቅዱስ የለም፤ አሜን"[307]፡፡ ስለዚህ የምእመናኑ መልስ፥ ፍጹምና የባሕርይ ቅድስና የሥሉስ ቅዱስ ገንዘብ ብቻ እንደሆነና አማንያን የሚቀደሱት (ቅዱሳን የሚሆኑት) ከእግዚአብሔር በሚያገኙት የቅድስና ጸጋ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

---

[301] "Holy mysteries, for the holy."

[302] Elevation of the Holy Mysteries - Varghese, *The Living Sacrifice*, p. 232.

[303] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 92፣ ገጽ 103፡፡

[304] እንግሊዝኛው፡- "There is One that is holy; there is one Lord, Jesus Christ, blessed forever, to the glory of God the Father" ይላል፡፡ *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles),* Book VIII, Ch. 13, 1848, p. 181.

[305] *Holy Euchologion*, 2004, p. 110.

[306] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 112፤ "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 90፣ ገጽ 103፡፡

[307] የእንግሊዝኛው ትርጒም፡- "None is holy, save the One holy Father, the One holy Son, and the One Holy Spirit. Amen" ይላል፡፡ Varghese, *The Living Sacrifice*, p. 232.

## ጸሎት እምቅድመ ተመጥዎ ቍርባን

ገባሬ ሠናዩ (ቀዳሹ) ካህን የጌታን *ሥጋ*ና ደም ራሱ ተቀብሎ ለሌሎች ከማቀበሉ በፊት "*ሥጋ* ቅዱስ ዘበአማን . . . ደም ክቡር ዘበአማን . . ."[308] እያለ በቅዱስ ቍርባን ላይ ያለውን እምነት ይገልጻል፡፡ ይህ የእምነት መግለጫ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የተወሰደ ነው፡፡[309] ካህኑ በቅዱስ ቍርባን ላይ ያለውን እምነት ለምእመናን አሰምቶ ካነበበ በኋላ "ዓስበ ዲያቆን" የሚል ስያሜ በተሰጠውና የመስቀል ምልክት ባለበት የ*ሥጋ*ው መካከለኛ ክፍል ደሙን አስነክቶ *ሥጋ*ውን "አአምን፥ አአምን፥ አአምን . . ." ፥ ደሙን ደግሞ "ቡሩክ እግዚብሔር አብ አኃዜ ኵሉ አምላክነ . . ." እያለ ይባርክና ዓስበ ዲያቆኑን ጽዋው ውስጥ ይጨምረዋል፡፡[310] ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ በግሪኩ *ዴስፖቲኮን*[311] የሚለው ቃል በኮፕቲክ ቋንቋ "ስፑዲኮን"፥ በዐረብኛ ትርጕሞች ደግሞ "ኢስባዲያቆን" የሚል ስያሜዎችን እንዳገኘና ቃሉ ወደ ግእዝ ሲተረጐም "ዓስበ ዲያቆን" ተብሎ "ለዲያቆን የሚገባ ወይም የሚሰጥ" የሚል የተሳሳተ ትርጕም እንደያዘ ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን የግሪኩ *ዴስፖቲኮን* ትክክለኛ ትርጕም "*ሥጋሁ ለእግዚእ - የጌታ ሥጋ*" የሚል ነው፡፡[312]

*መጽሐፈ* ቅዳሴው ሠራዒው ካህን ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበሉ በፊት የሚጸልየውን ጸሎትና ቅዱስ ቍርባንን የሚቀበሉ ሁሉ (በመቅደስ ውስጥ ያሉ ካህናት፥ ዲያቆናትና ምእመናን) ሊጸልዩት የሚገባውን ጸሎት በግልጽ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ካህኑ "አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ ደስ የሚያሰኝህ *መሥዋዕት* የልጅህ *ሥጋ* እነሆ"[313] በማለት የሚጀምረውን የራሱን ጸሎት ጨርሶ ምእመናን ሊጸልዩት የሚገባውን አብሮ ስለሚደግመው፥ ምእመናን ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበላቸው በፊት እንዲጸልዩት የተዘጋጀውን ጸሎት ሳይጸልዩት ይቆርባሉ፡፡ ስለዚህ ይህን ጸሎት

---

[308] "ቅዳሴ ሐዋርያት" *መጽሐፈ* ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 98-99፣ ገጽ 105፡፡
[309] *Holy Euchologion*, 2004, pp. 113-114.
[310] "ቅዳሴ ሐዋርያት" *መጽሐፈ* ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 104፣ ገጽ 107፡፡
[311] *Despotikon*.
[312]ሀብተሚካኤል ኪዳነ፥ *ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ*፡ ገጽ 215-216፡፡
[313] "ቅዳሴ ሐዋርያት" *መጽሐፈ* ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 105-109፣ ገጽ 107-108፡፡

ካህናቱና ዲያቆናቱ ለምእመናኑ አሰምተው በማንበብ ምእመናን እንዲያውቁት የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የመጽሐፈ ቅዳሴው ትእዛዝ እንዲህ ይላል፡-

**ቍርባኑን ከመቀበል አስቀድሞ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉ ሁሉ እንዲህ ይበሉ፡-**

> አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ርኵስት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለም [ማቴ. 8፥8]፡፡ እኔ አሳዝኜሃለሁና፤ በፊትህም ክፉ ሥራ ሠርቻለሁና፤ በአርኣያህና በአምሳልህ የፈጠርኸው ሥጋዬንና ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌአለሁና፤ ሥራም ምንም ምን የለኝምና፡፡
>
> ነገር ግን [እኔን] ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለ መሆንህ፥ ስለ ክቡር መስቀልህም፥ ማሕየዊት[314] ስለ ምትሆን ስለ ሞትህ፤ በሦስተኛው ቀን ስለ መነሣትህም፤ ጌታዬ ሆይ፥ ከበደልና ከመርገም ሁሉ፤ ከኃጢአትና ከርኵሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፥ እማልድሃለሁም፡፡
>
> የቅድስናህንም ምሥጢር በተቀበልሁት ጊዜ ለወቀሳ፥ ለመፈራረጃ አይሁንብኝ፤ ማረኝ፥ ይቅርም በለኝ እንጂ፡፡ የዓለም ሕይወት ሆይ፥ በእርሱ[315] የኃጢአቴን ሥርየት፥ የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ፡፡ በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ማርያም፥ በመጥምቁ በዮሐንስም አማላጅነት፥ ክቡራን በሚሆኑ በመላእክትም፥ በሰማዕታትና ለበጎ ነገር በሚጋደሉ በጻድቃንም ሁሉ ጸሎት እስከ ዘላለሙ ድረስ፡ አሜን፡፡[316]

## ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር

ካህናቱና ዲያቆናቱ የጌታን ሥጋና ደም ለማቀበል በኅብረት ከመቅደስ (ቅድስተ ቅዱሳን) ወደ ቅድስት በሚወጡበት ሰዓት[317] ለሥጋሁ ወደሙ ክብር ምእመናን ይሰግዳሉ፡፡ ይህም የጌታን ሥጋ ሽቱ ለመቀባት ወደ መቃብር የሄዱት ቅዱሳት አንስት (ሴቶች) ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን ጌታ ባዩት ጊዜ እግሩን ይዘው የመስገዳቸው ምሳሌ ነው (ማቴ. 28፥9)፡፡ በዚህ ጊዜ በኅብረት ከመጽሐፈ ኪዳን የተወሰደውን ዝማሬ እንዘምራለን፡፡ ይህ መዝሙር ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በኋላ

---

[314] ድኅነትን የምትሰጥ (የምታድን)፡፡

[315] "የቅድስና ምሥጢር" በተባለው በጌታ ሥጋና ደም፡፡

[316] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 110-112፣ ገጽ 108-109፡፡

[317] ይህ ሁነት "ድርገት" ይባላል፤ ደረገ = አንድ ሆነ (ኅብረተ ፈጠረ) ከሚለው ግስ የተገኘ ቃል ነው፡፡ "ካህናቱ ድርገት ወረዱ" የሚለው የተለምዶ አነጋገር የጌታን ሥጋና ደም ለምእመናን ለማቀበል ከመቅደስ ወደ ቅድስት መውጣታቸውን (መውረዳቸውን) ለመግለጽ ነው፡፡

የሚዘመር እንደሆነ መጽሐፈ ኪዳን ይናገራል፡፡ "[ይጸሊ] ከመዝ እምድኅረ ነሥአ አኰቴተ"[318] - ቊርባንን ከተቀበለ በኋላ እንዲህ ይጸልይ፡-

> የማይነገር ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሦስት የምትሆን ይህን ሥጋና ደም ሕይወት ሊሆነኝ፥ ሳይፈረድብኝ እቀበል ዘንድ ስጠኝ፡፡ በጌትነትህ እንድገለጽ[319] ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ እሠራ ዘንድ ስጠኝ፤ የአንተንም ፈቃድ እየሠራሁ እኖርልህ ዘንድ ስጠኝ፡፡ በማመን አባት ብዬ እጠራሃለሁ፥ መንግሥትህንም እጠራለሁ፡፡ አቤቱ ስምህ በእኛ ላይ ይመስገን፤ ምስጉን፥ ክቡር የምትሆን ኃያል አንተ ነህና፤ ለአንተ ክብር ይገባሃል፡ ለዘላለሙ፡፡[320]

## እምድኅረ ተመጥዎ ቊርባን[321]

መጽሐፈ ኪዳን፥ ሕዝቡ (ምእመናን) ቅዱስ ቊርባንን ከተቀበሉ በኋላ ዲያቆን እንዲህ ብሎ ያመስግን ይላል፡- "ነአኵቶ ለእግዚብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ፤ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውሰ፡፡ ዘተመጦነ ንስእል ወንትመሐፀን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላክነ፡፡"[322] ይህም መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ እንዲህ ተተርጕሟል፡ - "*ሥጋውን ደሙን ተቀብለን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፤ ለነፍሳችን [ሕይወት] መድኃኒት ይሆን አንድ [የተቀበልን] እኛ አምላካችንን እግዚአብሔርን [እያመሰገንን] እንለምናለን፤ አደራም እንላለን፡፡*"[323] በዕለቱ የተመረጠውን ቅዳሴ የምስጋና ጸሎት (ኅዳፌ ነፍስ) ካህኑ ጸልዮ ሲጨርስ ካህናቱና ዲያቆናቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን (መቅደስ) ይመለሳሉ፡፡ ከ12ኛው ምእት ዓመት በፊት አገራችን ውስጥ በነበረው ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ አባ አማኑኤል ያደረጉት ጥናት እንዲሚያመለክተው፥ ካህናቱና ዲያቆናቱ ተረፈ መሥዋዕቱን (የተመለሰውን የጌታን ሥጋና ደም) የሚወስዱት *ፓስቶፎሪዮን*[324] ወደ ተባለውና ከመቅደሱ ጋር አብሮ ወደተሠራ ኅብስቱንና

---

318 *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 42.

319 መጽሐፈ ኪዳን ላይ "ከመ አስተርኢ በሥምረትከ" (በፈቃድህ/ አንተን ደስ በሚያሰኝህ እገለጽ ዘንድ) የሚለውን፥ መጽሐፈ ቅዳሴው "ከመ አስተርኢ በስብሐቲከ" (በምስጋናህ/በጌትነትህ እገለጽ ዘንድ) ይላል፡፡

320 "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 117-118፣ ገጽ 110-111፡፡

321 Post-Communion Rites.

322 *Testamentum domini éthiopien*, ed and trans. Beylot, p. 43.

323 "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቊ. 130፣ ገጽ 113፡፡

324 Pastophorion (sacristy).

ወይኑን የማዘጋጃ ክፍል ነበር፡፡[325] ሐዋርያዊ ሕግጋት የተባለውም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት ይህንኑ እንዲያደርጉ ያዛል፡፡[326] አሁን ግን ካህናቱ ተረፈ መሥዋዕቱን መንበሩ ላይ አድርገው በመጽሐፈ ቅዳሴ የታዘዘውን ሥርዓት[327] እና አስተናጽሖ[328] ይፈጽማሉ፡፡

በመጨረሻም ዲያቆኑ ምእመናንን ለማሰናበት ለቡራኬ እያዘጋጃቸው፡- "በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ፤ አገልጋዩ በሚሆን በካህኑ እጅ ይባርካችሁ ዘንድ"[329] የሚለውን በዜማ ከማሰማቱ በፊት፥ እንደ መጽሐፈ ቅዳሴው ትእዛዝ፥ ምእመናን የሚከተለውን ይላሉ፡-

> የፍቅር ባለቤት፥[330] የሰላም ንጉሥ፥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡ ሰላምህን ስጠን፤ ሰላምህንም አጽናልን፡፡ ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፡፡ በሰላም ወደ ቤታችን [. . .] እንገባ ዘንድ የበቃን አድርገን፡፡[331]

ሠራዒው ካህን ምእመናን ባርኮ[332] ሲጨርስ "እግዚአብሔር የሀሉ ምስለ ኵልክሙ" (እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይኑር) ይላቸዋል፡፡ ምእመናንም "ምስለ መንፈስከ" (ከመንፈስህ ጋር/ከአንተም ጋር ይሁን) ካሉት በኋላ፥ የሚከተለውን ጸሎት በኅብረት ይጸልያሉ፡-

> አሜን እግዚአብሔር እኛን ባሮቹን በሰላም ይባርከን፡፡ የተቀበልነው ሥጋህና ደምህ ለሥርየት ይሁነን፡፡ የጠላትን ኃይል ሁሉ በመንፈስ እንረግጥ ዘንድ አሠልጥነን፡፡

---

[325] Emmanule Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 192.

[326] "And when all, both men and women, have communicated, let the deacons take what remains and carry it into the sacristy." *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles),* Book VIII, Ch. 13, 1848, p. 183.

[327] "ወለእመ ተርፈ ሥጋ ወደም ይመጥዎሙ ካህን ለካህናት ወለዲያቆናት . . ." – "ትእዛዝ ዘባስልዮስ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 141፣ ገጽ 115-116፡፡

[328] ፃሕሉንና ጽዋውን በጥንቃቄ የማጠብ ሥርዓት ሲሆን ከላቲኑ የተወሰደው የእንግሊዝኛ ስያሜ ablution ይባላል፡፡

[329] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 159፣ ገጽ 121፡፡

[330] ግእዙ "አ ንጉሠ ሰላም" (የሰላም ንጉሥ ሆይ) በማለት ይጀምራል፡፡

[331] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 158፣ ገጽ 121፡፡

[332] ቡራኬው "አቤቱ ሕዝብህን አድን፡ ርስትህንም ባርክ" በማለት ይጀምራል - "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 160፣ ገጽ 121፡፡ የኮፕቲክ ቅዳሴ በእነዚህ ቃላት የሚጀምር የካህኑ የማጠቃለያ ቡራኬን ይዟል፤ ነገር ግን ከዚህ ዐረፍተ ነገር በስተቀር በይዘት የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ካለው ቡራኬ ጋር አንድ አይደለም፡፡ *Holy Euchologion*, 2004, p. 118.

ምሕረትን የተመላች ክብርት የምትሆን የእጅህን በረከት ሁላችን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ከክፉ ሥራ ሁሉ አርቀን፥ በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን፡፡

ቅዱስ ሥጋውን፥ ክቡር ደሙንም የሰጠን ቡሩክ ነው፡፡ ጸጋን ተቀበልን፤ ደኅንነትንም በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል አገኘን፡፡ አቤቱ ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ ጸጋን ተቀብለን አንተን እናመሰግናለን፡፡[333]

ዲያቆኑ "እትዉ በሰላም" (በሰላም ግቡ)[334] በማለት ምእመናንን ያሰናብታል፡፡ ሠራዒው ካህን ጣቶቹን አመሳቅሎ፡- "ልዑል እግዚብሔር ይባርክህ/ሽ፤ ፊቱንም ይግለጽልህ/ሽ"[335] (ዘኍ. 6፥24-26) እያለ ይባርካቸዋል፡፡ መቅደስ ውስጥ፥ ረዳቱ ካህን መጽሐፈ ቅዳሴ ላይ ያለውን ጸሎት[336] ጸልዮና አውሎግያውን (የበረከት ኅብስት) ፈትቶ (ቆርሶ) ለካህናቱና ዲያቆናቱ ያድላል፡፡ ይህ "አውሎግያ"[337] ወይም አኰቴት[338] የጌታ ሥጋ ወደ መሆን ስላልተለወጠ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ካህናቱ ለበረከት ለምእመናን ያድሉታል፡፡

## 4.2. የሥርዓተ ቅዳሴ ምሳሌዎች እና ትምህርታዊ መልእክቶቻቸው

የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የሰው ልጅን፥ ግዑዛን ፍጥረታትንና መላእክትን የሚያስተባብር በምድር ላይ የሚከናወን ሰማያዊ አምልኮ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ሰዓት በመሥዋዕትነት የምታቀርበው ኅብስትና ወይን የምድር ምርቶች ስለሆኑ፥ ልዑል እግዚአብሔር ውብ አድርጎ የፈጠረውን የዚህ ዓለም

---

[333] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 164-165፣ ገጽ 123፡፡

[334] በግብፅ ቤተ ክርስያን ቅዳሴ "Go in peace. The Lord be with you all" (በሰላም ሂዱ፤ እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን) በማለት የሚያሰናብተው ካህኑ ነው - *Holy Euchologion*, 2004, p. 118. Apostolic Constitutions ላይ ግን "depart in peace" (በሰላም ሂዱ) በማለት ዲያቆኑ ምእመናንን እንደሚያሰናብት ተጽፏል - *The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles),* Book VIII, Ch. 13, 1848, p. 184. እዚህ ላይ ከኮፕቲክ ቅዳሴ ይልቅ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንደጠበቀ እንረዳለን፡፡

[335] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 162፣ ገጽ 122-123፡፡

[336] "ይበል ንፍቅ ካህን እንዘ ይሜጡ አውሎግያ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 167-170፣ ገጽ 124፡፡

[337] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 167፣ ገጽ 124፡፡ ከግሪኩ *evlogia* የተወሰደ ሲሆን የተባረከ ኅብስት (blessed bread) ማለት ነው፡፡

[338] በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን *apporgē* (first-fruit) የሚለው ስያሜ እየተለመደ እንደመጣ አባ አማኑኤል ጠቁመዋል፡፡ በሮማኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን *"anaphora"* ይሉታል፡፡ ይህም thanksgiving (ምስጋና) ማለት ስለሆነ "አኰቴት" ከሚለው የቤተ ክርስቲያናችን ስያሜ ጋር አንድ አይነት ትርጉም አለው፡፡ Emmanule Fritsch,"The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D.," p. 193.

ፍጥረት ወክለው የቅዳሴው ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡[339] ለዚህም ነው አንድ ሊቅ፥ ካህኑ በቅዳሴ ሰዓት ኅብስቱን በእጁ በሚይዝበት ሰዓት ዓለምን ሁሉ እንደያዘ ሊያስብ ይገባል ያለው፡፡ [340] የቅዳሴው መሥዋዕት (ኅብስቱና ወይኑ) በመንፈስ ቅዱስ አሠራር የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም ስለሚሆን፥ በመለኮታዊ ባሕርዩ ምሉዕ በኲለሄ[341] የሆነው አምላካችን ክርስቶስ ባለበት ቦታ ሁሉ በእርሱ ሕያዋን የሆኑ ነፍሳትና አገልጋዮቹ ቅዱሳን መላእክት እንደሚገኙ እሙን ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጆች፥ በዓይን የሚታየው የዚህ ዓለም ፍጥረታትና የድል አድራጊዋ (ሰማያዊቷ) ቤተ ክርስቲያን አባላት (ቅዱሳን መላእክትና በአጸደ ነፍስ ያሉ ጻድቃን/ውሉደ ብርሃን) በምድር የሚከናወነው ቅዳሴ ተሳታፊዎች ይሆናሉ፡፡ ይህ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ የምድራዊቷን ቤተ ክርስቲያን አምልኮ፥ ፍጥረት በሙሉ የሚሳተፍበት ቅዳሴ[342] የሚል ስያሜ አሰጥቶታል፡፡ [343] ስለዚህ የቅዳሴው ሰዓት ምድርና ሰማይ የሚገናኙበት፥ በዚህ ዓለም የምናውቀው የጊዜና የቦታ ልዩነት ተወግዶ ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን ከሰማያዊቷ ቤተ ክርስቲያን ጋር በአምልኮ አንድ የምትሆንበት ጊዜ ነው፡፡ [344] ለዚህ ሥርዓተ አምልኮ የተለየውና የተቀደሰው ኦርቶዶክሳዊ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለ ሰማይ[345] ሲሆን፥ አባቶቻችን "ሥርዓተ ሰማይ ተሠርዓ በዲበ ምድር" [346] እንዲሉ፥ በውስጡ የሚከናወነው

[339] Elizabeth Theokritoff, "Embodied Word and New Creation: Some Modern Orthodox Insights Concerning the Material World," *Abba: The Tradition of Orthodoxy in the West: Festschrift for Bishop Kallistos (Ware) of Diokleia*, eds. John Behr, Andrew Louth, Dimitri Conomos (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 2003) p. 231.

[340] Alexander Schmemann, *The Eucharist: Sacrament of the Kingdom* (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1974) p. 118.

[341] Omnipresent.

[342] Cosmic liturgy.

[343] Pauly Maniyattu, *Heaven on Earth: The Theology of Liturgical Spacetime in the Eastern Syrian Qurbana* (Rome: Mar Thoma Yogam [St. Thomas Christian Fellowship], 1995) p. 89.

[344] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 6፡፡

[345] Heaven on earth.

[346] Getatchew Haile, "An Amharic Study on the Liturgy and Symbolism of the Ethiopian Church," EMML 1157, f. 215v, p.87.

ሥርዓተ አምልኮ ልባችንንና አሳባችንን በሙሉ ወደ ሰማያዊው ዓለም የሚወስድ ነው፡፡

## ፩. ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እና ቅዱሳት ሥዕላት

የቤተ ክርስቲያንን ሰማያዊ ውበት የተረዱ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን፥ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ብትታነጽም የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ምሳሌ እንደሆነችና አምልኮዋም ሰማያዊ እንደሆነ አስተምረውናል፡፡ ይህንንም አስመልክተው ሲዘምሩ ቤተ ክርስቲያንን ሥሮቿ በምድር ውስጥ በተተከሉና የቅጠሎቿ ጫፍ ሰማይ በደረሰ የወይን ሐረግ እየመሰሉ፡- "እንተ በምድር ሥረዊሃ፥ ወበሰማይ አዕፁቂሃ፥ ሐረገ ወይን እንተ በሥሉስ ትትገመድ" በማለት ዘምረዋል፡፡[347] "እንተ በሥሉስ ትትገመድ" የሚለው አገላለጽ የቤተ ክርስቲያን ዶግማ መሠረት የሆነውን ምሥጢረ ሥላሴን ያመለክታል፡፡ ስለሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ውበት በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 21 ላይ የተጻፈውን ዋቢ በማድረግና ይህን ሰማያዊ ውበት ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ማኅሌታውያን የቅዱስ ያሬድ ልጆች የዘመሩት ዝማሬ ከላይ የተጠቀሱ ነጥቦችን እውነታ ያረጋግጣል፡-

> *ሐነጽዋ ወሣረርዋ ለቤተ ክርስቲያን ከመ ትኩን አርዓያ ዘበሰማያት . . . ዳዊትኒ ይቤ "ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም"፡፡ [እስመ] ተሐንጸት በስሙ፤ ወተቀደሰት በደሙ፡፡ . . . በዕንቈ ሰንፔር ወበከርከዴን ሥርጉት ዓረፋቲሃ ለጽዮን፡፡ ወይቤላ ሠናይት አግዓዚት፤ ወካዕበ ይቤላ ነቢይ ማኅደረ ስብሐት፥ ደብተራ ፍጽምት፡፡*[348]

> *በሰማይ ያለችው [ኢየሩሳሌም] ምሳሌ ትሆን ዘንድ ቤተ ክርስቲያንን አነጺት፤ መሠረቷትም፡፡ ዳዊትም፡- "ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት" (መዝ. 131/132፥14) አለ፤ [በጌታ ስም] ታንጻለችና፥ በደሙም ተቀድሳለችና፡፡ የጽዮን [ቤተ ክርስቲያን] ግድግዳዎች ሰንፔርና ከርከዴን (ራእ. 21፥19) በተባሉ ዕንቍዎች ያጌጠ ነው፡፡ "ያማረች (ውብ) እና ነጻ የምታወጣ" አላት፤ ዳግመኛ ነቢይ "የምስጋና ማደሪያ፥ ሕጸጽ ነውር የሌለባት ድንኳን" አላት፡፡*[349]

---

[347] "ዚቅ ዘዘመነ ጽጌ" *መጽሐፈ ዚቅ ወመዝሙር* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.) ገጽ 39.

[348] "ዚቅ ዘሰኔ ማርያም" *መጽሐፈ ዚቅ ወመዝሙር*፣ ገጽ 192::

[349] ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጉም የእኔ፡፡

ከዘመነ አክሱም ጀምሮ ምድራዊቷን ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊት ኢየሩሳሌም ምሳሌ ማድረግና መንፈሳዊ ውበቷን እያደነቁ መዘመር ኢትዮጵያዊ ትውፊት እንደሆነ የሚያመለክቱ መረጃዎች አሉ፡፡ ከተስዐቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን አንዱ የሆኑት አቡነ አረጋዊ፥ ታላቁ የዜማና የቅኔ ሊቅ ቅዱስ ያሬድን የዳሞ ተራራ ጫፍ ላይ ወደታነጸችው ቤተ ክርስቲያን ሲወስዱት ሊቁ፡-

> ይሔውጽዋ መላእክት እንተ በሰማያት፥ ይሔውጽዋ መላእክት እስመ ማኅደረ መለኮት [ይእቲ]፤ ያድከዋ፥ ያድከዋ፥ ያድከዋ ወርኢኩ ሥነ ሕንጼሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡፡ ምስአል ወምስጋድ ወምስትሥራየ ኃጢአት ይእቲ ቅድስት ደብተራ፤

> በሰማያት ያሉ መላእክት [ይጎበኟታል]፤ የመለኮት ማደሪያ ናትና መላእክት [ይጎበኟታል]፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን [ዞርኳት፥ዞርኳት፥ ዞርኳት] የሕንጻዋንም ማማር [ውበት] አየሁ፡፡ [እርስዋ] መጸለያ፥ መስገጃና የኃጢአት ማስተሥረያ ቅድስት ድንኳን ናት[350]

በማለት እንደዘመረ ተዘግቧል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ክብሩን በተለያዩ ተራሮች ላይ እንደገለጸ እናነባለን፤ ለሕዝቡ መልእክት ይነገር ዘንድ ሙሴን ወደ ሲና ተራራ ጫፍ በጠራው ጊዜ "እግዚአብሔር በእሳት ስለ ወረደበት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር" ተብሎ ተጽፏል (ዘጸ. 19፥ 18)፡፡ በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስቱን ደቀ መዛሙርት (ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስን) ወደ ረጅም ተራራ ካወጣቸው በኋላ ፊቱ እንደ ፀሐይ እንዳበራና ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ እንደሆነ ወንጌላውያኑ ጽፈውልናል (ማቴ. 17፥1-2፤ ማር. 9፥2-3፤ ሉቃ. 9፥ 28-29)፡፡ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ የተረዱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን አብዛኞቹን አብያተ ክርስቲያን ያነጹት በብዙ ድካም በሚደረስባቸው ተራራዎች ላይ ነው፡፡ በዘመነ አብርሃ ወአጽብሐ በምድረ አክሱም የታነጸችው የመጀመሪያዋ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እ.አ.አ. በ340 ኢየሩሳሌም ውስጥ በንጉሥ ማክሲመስ [351] የታነጸችው የጽዮን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነበረች፡፡ [352] ይህ

---

[350] ኤልያስ አብርሃ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና ፀዋትወ ዜማ" *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ (2000) ዓ.ም.* (አዲስ አበባ፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡ 2000 ዓ.ም.) ገጽ 100.

[351] Maximus of Jerusalem.

[352] Marilyn Heldman, "Architectural Symbolism, Sacred Geography and the Ethiopian Church," *Journal of Religion in Africa*, Vol. 22, No. 3 (1992)" p. 227.

ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከተማቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ምሳሌ ለማድረግ የነበራቸውን ፍላጎት ያመለክታል፡፡ ለዚህም ነው የታቦተ ጽዮን ማረፊያ የሆነችው አክሱም "አዲሲቷ ኢየሩሳሌም"[353] ወይም "ዳግማዊት ጽዮን"[354] የተሰኙ ስያሜዎችን ያገኘችው፡፡

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፥ አክሱም ጽዮን፥ የአክሱም ሐውልቶች የተቀረፁበትን ሥነ ጥበብ የሚያንጸባርቁ ባሕርያትን የያዘችና ከትልቅ ዐለት ተፈልፍላ የተሠራች ነበረች፡፡[355] ትግራይ ውስጥ የሚገኙት የውቅር አብያተ ክርስቲያን (ለምሳሌ ውቅሮ ቂርቆስ) እና ብርቅዬዎቹ ከአንድ-ወጥ[356] ትልቅ ድንጋይ ተፈልፍለው የተሠሩት የላሊበላ አብያተ ክርስቲያን[357] እጅግ ጥንታዊ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ዘዴ መገለጫዎች ናቸው፡፡[358] ሁለተኛውና ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን አሠራር ዘዴ፥ የመጀመሪያዎች ክርስቲያኖች በሮማውያን ቄሣሮች በሚሰደዱበት ጊዜ በግበበ ምድር[359] እና በዋሻ ውስጥ ይፈጽሙት የነበረውን አምልኮ ለማስታወስ የሚሠራው የዋሻ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ለእንደዚህ አይነቱ አሠራር ጥሩ ምሳሌዎች የሚሆኑን ይምርሐነ ክርስቶስ፥ አዲስ ዘመን አካባቢ ያለው ዋሻ እንድርያስ እና ላሊበላ አካባቢ ያለው ነአኵቶ ለአብ ናቸው፡፡[360] በብዛት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ፥ አልፎ አልፎም በከተሞች፥ የምናገኘው ሦስተኛው የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አይነት በውስጡ ሦስት ክፍሎች ያሉት ክብ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ የመጨረሻውና አራተኛው፥ በብዛት በታላላቅ የአገራችን ከተሞች

[353] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 225፡፡

[354] Mario Di Salvo, "The Typology of Ethiopian Churches from the Basilica to the Centrally Planned Churches in Their Structural and Symbolic Aspects," *Churches of Ethiopia: The Monastery of Nārgā Śellāsē,* eds. Stanislaw Chojnacki and Osvaldo Raineri (Milano: Skira Editore S.P.A., 1999) p. 64.

[355] Sylvia Pankhurst, *Ethiopia: A Cultural History* (Norwich: Fletcher and Son Ltd., 1955) p. 132.

[356] "ጥ" ጠብቆ ይነበብ፡፡

[357] Monolithic churches.

[358] Di Salvo "The Typology of Ethiopian Churches," p. 63.

[359] Catacombs.

[360] Emmanuel Fritsch, "Ethiopian Liturgy and Church Architecture," *Ethiopian Review of Cultures,* Vol. XIV (2011) pp. 80-81.

ውስጥ የምናየውና ከምዕራባውያን የተወሰደው ባለ አራት ማእዘን[361] ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡[362]

በአብዛኛው አገራችን ውስጥ የሚገኘው የክብ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሕንጻ የሰሎሞን ቤተ መቅደስን አሠራር የተከተለ እንደሆነ ይታመናል (1 ነገ. 6፥5-6፤ 2 ዜና መዋ. 3፥7)፡፡[363] ክቡ ቤተ ክርስቲያን፥ በውስጥ አንድ ላይ የተያያዙ ሦስት ክፍሎች ሲኖሩት፥ ለማኅሌትና ሰዓታት አገልግሎት የሚውለው የመጀመሪያው ክፍል ቅኔ ማኅሌት ይባላል፡፡ ይህ ክፍል *ሃሴር* የተባለውን የደብተራ ኦሪት (የኦሪት ድንኳን) የመጀመሪያ ክፍል ወይም *ኡላም* የተሰኘውን የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ውጪያዊ ክፍል ታሳቢ በማድረግ የሚሠራ ነው፡፡[364] ሁለተኛው ክበብ ደግሞ፥ ምእመናን ቅዱስ ቍርባን የሚቀበሉበት ሲሆን ቅድስት[365] ይባላል፤ ይህም የምስክሪቱ ድንኳን *ቆዴሽ* ወይም የሰሎሞን ቤተ መቅደስ *ሄካል* ምሳሌ ነው፡፡[366] ውስጠኛውና ታቦቱ የሚቀመጥበት የተቀደሰ ሥፍራ መቅደስ ወይም ቅድስተ ቅዱሳን ተብሎ ይጠራል፤ ወደዚህ ክፍል የሚገቡት ለክህነት አገልገሎት የተሾሙ (ዲያቆናት፥ ካህናት እና ጳጳሳት) ብቻ ናቸው፡፡ ይህም ክፍል የደብተራ ኦሪትን *ቆዴሽ ሃቆዳሺም* ወይም የሰሎሞን ቤተ መቅደስን *ደብር* ያስታውሰናል፡፡[367] በዚህ መልኩ የምትታነጸው ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ከሚካሄደው ሥርዓተ ቅዳሴ የተነሣ የምድርና የሰማይ መገናኛ ስፍራ ትሆናለች፡፡ ቅዳሴውም የፍጡራን በሙሉ (በዓይን የማይታዩ ቅዱሳን መላእክት፥ የጻድቃን ነፍሳትና የምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን አባላት)

---

361 Basilican type.

362 Di Salvo "The Typology of Ethiopian Churches," p. 59.

363 Edward Ullendorff, "Hebraic-Jewish Elements in Abyssinian (Monophysite) Christianity," *JSS*, Vol. 1 (1957) p. 235.

364 ዝኒ ከማሁ፡፡

365 አባ አማኑኤል ከ13ኛው ምዕት ዓመት በፊት የተሠሩ ጥንታውያን የአገራችን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ "ቅድስት" የሚባለው ክፍል ላይ በምዕራብ በኩል የተለየ platform እንደነበርና በይዘትም በሶርያ ቤተ ክርስቲያን *bêma* ከሚባለው ጋር እንደሚመሳሰል በጥናታዊ ጽሑፋቸው አስረድተዋል፡፡ Emmanuel Fritsch, "Ethiopian Liturgy and Church Architecture," pp. 79 & 86.

366 Edward Ullendorff, "Hebraic-Jewish Elements in Abyssinian (Monophysite) Christianity," p. 235.

367 ዝኒ ከማሁ፡፡

ኅብረት ስለሆነ ለሰው ልጆች እና ለእንስሳት ደኅንነት፤ ለምድሩ ፍሬ እና ለመከሩ በረከት፤ እንዲሁም አየሩ፥ ዝናቡና ወንዞች ይባረኩ ዘንድ ልመናን ያቀርባል፡፡[368]

በመለኮታዊ ጥበብ የተፈጠረው ይህ ግሩምና ድንቅ ዓለም የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚያውጅ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል (መዝ. 18/19፥ 1፤ ሮሜ 1፥21)፡፡ በዚህ ምድር የምትታነጸው ቤተ ክርስቲያን ከዓለሙ የሥጋ ሥራ የተለየችና ውብ የሆነው የእግዚአብሔር ፍጥረት መገለጫ ናት፡፡[369] ስለዚህ ቅድስተ ቅዱሳን[370] የተባለው የቤተ ክርስቲያን ክፍል ሰማይን፥ ቅድስት እና የተቀረው ክፍል[371] ደግሞ ምድርን ያመለክታል፡፡ በቅድስተ ቅዱሳን (መቅደስ) ውስጥ የሚገኘው መንበር[372] ወንጌላዊው ዮሐንስ ያየውና የወርቅ መሠዊያ በፊቱ የተቀመጠ ሰማያዊ ዙፋን ምሳሌ ነው (ራእ. 8፥ 3)፡፡ የካህኑ ጸሎተ እንፎራ ላይ እንደተጠቀሰው፥ መንበሩ ላይ የሚቀመጠው ፃሕል የክርስቶስ መቃብር ምሳሌ ነው፡- "ሦስት መዓልት፥ ሦስት ሌሊት በውስጡ በኖርህበት መቃብር አምሳል [ኅብስቱን] በዚህ ፃሕል ላይ አኖርን"፡፡[373] ካህኑ ኅብስቱን የሚሸፍንበት ማኅፈድ ደግሞ ጌታ የተገነዘበት ንጹሕ በፍታ (ማቴ. 27፥59) ወይም የተልባ እግር ልብስ (ዮሐ. 19፥40) ምሳሌ ነው፡፡ በምድር የሚከናወነው ሰማያዊ አገልግሎት (ቅዳሴ) ልኡካን የሆኑ ካህናት "ሱራፌል" በተባሉ ነገደ መላእክት፥ ዲያቆናት ደግሞ በኪሩቤል ይመሰላሉ፡፡[374] በክቡ ቤተ ክርስቲያን የምናገኛቸው የምሥራቅ፥ የምዕራብና የሰሜን በሮች የሦስቱ ዓለመ መላእክት፡- ኢዮር፥ ራማ እና ኤረር ምሳሌዎች ናቸው፡፡[375] የቤተ ክርስቲያን የውጭ እና የውስጥ አእማድ (አምዶች) በትምህርታቸው ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ

[368] "ጸሎት ዘንፍቅ ካህን" እና "ጸሎተ ቡራኬ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 195-201፣ ገጽ 69፤ ቍ. 13፣ ገጽ 89፡፡

[369] ጸሐፊው በእንግሊዝኛ፡- "an icon of the whole cosmos" የሚል አገላለጽ ተጠቅመዋል፡፡ Archimandrite Vasileios, *Hymn of Entry: Liturgy and Life in the Orthodox Church*, trans. Elizabeth Briere (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1984) p. 71.

[370] Holy of holies/ sanctuary.

[371] Nave and narthex.

[372] Altar.

[373] "ጸሎተ አንፎራ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 51-201፣ ገጽ 36፡፡

[374] *መጽሐፈ ሰዓታት ወኵሉ ፀዋትዊሁ ምስለ ባሕረ ሐሳብ*፡ አርታዒ፡ ሞገስ ዕቍበ ጊዮርጊስ (አስመራ፡ ኮከበ ጽባህ ማተሚያ ቤት፡ 1959 ዓ.ም.) ገጽ 90.

[375] ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ሊቀ ካህናት)፡ *ሥርዓተ ቤተክርስቲያን*፣ ገጽ 20፡፡

መሠረት የሆኑ ነቢያትና ሐዋርያት ምሳሌ ሲሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናበራቸው ሻማዎች ደግሞ ልበ-ብሩሃን የሆኑ መምህራንን ያስታውሱናል፡፡[376]

በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያን የማይገኝ የአገራችን ብቸኛ ትውፊት በገጠር አብያተ ክርስቲያን ጉልላት ሥር የሚሰቀለው የሰጎን ዕንቁላል ነው፡፡ ሰጎን ጫጩቶቿን የምትፈለፍለው ዕንቁላሏን ትክ ብላ በመመልከት ስለሆነ፥ የሚሰቀለው የሰጎን ዕንቁላል ከአማንያን የሚጠበቀውን የእምነት ጽናት ያመለክታል፡፡ ዲያቆናቱ ኅብስትና ወይን የሚያዘጋጁባት ትንሽ ቤት (ቤተልሔም = ቤተ ኅብስት) በመቅደሱ ትይዩ በምሥራቅ በኩል ትሠራለች፡፡ በምሥራቅ በኩል ያለው የጉልላቱ መስኮትም የጠዋት ፀሐይ ወደ መቅደሱ እንዲገባ ክፍቱን ይተዋል፤[377] ዲያቆኑም በቅዳሴ "ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ"[378] የሚል ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ይህ ሁሉ በምሥራቅ በኩል የነበረችውን የቀድሞዋን ቤታችንን (ገነትን) ያስታውሰናል (ዘፍ. 2፥8)፡፡ አዳምና ሔዋን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ያጡትን የሕይወት ዛፍ ፍሬ፥ በምሥራቅ በኩል ካለው ቤተልሔም በሚዘጋጀው ኅብስተ ሕይወት እናገኘዋለን፤ "ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወደሙ ክቡር" (ዳግመኛ ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን፡፡ ይኸውም እኛን ስለ መውደድ ሰው ሆኖ ያዳነን የክርስቶስ ክቡር ሥጋው፡ ክቡር ደሙ ነው) እንዲል ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም፡፡ [379] በተጨማሪም "መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል" ተብሎ እንደተጻፈ (ማቴ. 24፥27) የሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያን ናፍቆት የሆነውን የሙሽራዋ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትን ያመለክታል፡፡ "የሚያበራ የንጋት ኮከብ ነኝ" ያለውና (ራእ. 22፥ 16) "ፀሐየ ጽድቅ አርያማዊ"[380] (ሰማያዊ የእውነት ፀሐይ) ተብሎ የሚመሰገነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለማዊ መንግሥቱን ተስፋ ሰጥቶናል፡፡ በማለዳ ፀሐይ በምሥራቅ ወጥታ ውብ

---

[376] "የቅዳሴ ታሪክ" *መጽሐፈ ቅዳሴ አንድምታ* (1991 ዓ.ም.) ገጽ 8፡፡
[377] Emmanuel Fritsch, "Ethiopian Liturgy and Church Architecture," p. 82::
[378] "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 26፣ ገጽ 92፡፡
[379] *ውዳሴ ማርያም ቅዱስ ኤፍሬም የደረሰው፡ ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው* (አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፡ 1983 ዓ.ም.) ገጽ 121፡፡
[380] *መጽሐፈ ሰዓታት ወኪሉ ፀዋትዊሁ ምስለ ባሕረ ሐሳብ፣* 1959 ዓ.ም. ገጽ 111፡፡

የሆነ ብርሃንዋን በፈነጠቀች ቍጥር፥ "መንግሥትህ ትምጣ" እያልን ወደ ምሥራቅ በመመልከት እንጸልያለን፡፡

## ቅዱሳት ሥዕላት

ኦርቶዶክሳዊ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን "በምድር ላይ ያለ ሰማይ" ከሚያስብሉት ነገሮች መካከል የውስጡ ውበት የሆኑት ቅዱሳት ሥዕላት[381] ናቸው፡፡ በተለያዩ ሥዕለ ቅዱሳንና የጌታችን የማዳን ሥራ ትዕይንት ያጌጠው የቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ ገጽታ፥ ፍጥረት ሁሉ በክርስቶስ ከተጠቀለለ በኋላ (ኤፌ. 1፥10) የሚገለጠውን አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን በዓይነ ሕሊና እንድናስብ ያደርገናል፡፡[382] ስለዚህ ለኦርቶዶክሳውያን ካህናትና ምእመናን፥ ቅዱሳት ሥዕላት የማይታየውንና መንፈሳዊውን ዓለም ከዚህ ቁስ-አካላዊ ዓለም ጋር የሚያገናኙ ምሥጢራዊ ድልድዮች ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናያቸው ሥዕሎች ከምድራዊ ነገሮች የተሠሩ ቢሆኑም በቅብዓ ሜሮን ከከበሩ በኋላ በዓይነ ልቡና ሰማያዊውን ዓለም ለማየት የሚያስችሉ መስኮቶች ተብለዋል፡፡[383] ኦርቶዶክሳዊው ሊቀ ጳጳስ ካሊስቶስ ይህን አስተምህሮ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፡-

> ቤተ ክርስቲያንን [ሞልተው የምናያቸው] ሥዕሎች የሰማይና ምድር መገናኛ ሥፍራ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በየእሑዱ የእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት በሥዕለ ክርስቶስ፥ በቅዱሳንና በመላእክት ሥዕሎች ተከብበው በሚጸልዩበት ጊዜ፥ እነዚህ የሚታዩ ሥዕላት በቅዳሴ ሰዓት የሚገኙትንና የማይታዩ ቅዱሳን ኅብረትን ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ግድግዳዎች ወደ ዘላለማዊነት እንደተከፈቱ ሊያስቡ ይችላሉ፤ ምድራዊው ቅዳሴ ከሰማያዊው ቅዳሴ ጋር አንድ እንደሆነም ይገነዘባሉ፡፡ ቍጥራቸው ብዙ የሆነ ቅዱሳት ሥዕላት፥ "በምድር ላይ ያለ ሰማይ" የተባለውን ስሜት በሚታይ መልኩ እውን ያደርጉልናል፡፡[384]

---

[381] Holy icons.

[382] Marc Metzger, "Liturgy and Cosmos," *Concilium: Liturgy and the Body,* eds. Louis-Marie Chauvet and François Kabasele Lumbala (London: SCM, 1995) p. 43.

[383] በእንግሊዝኛ፡- "windows to heaven" - Mariamna Fortounatto and Mary B. Cunningham, "Theology of the Icon," *The Cambridge Companion to Orthodox Christian Theology*, eds. Mary Cunningham and Elizabeth Theokritoff (Cambridge: Cambridge University Press, 2008) pp. 136-137.

[384] Kallistos Ware, *The Orthodox Way* (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1995) pp. 271-272.

ከዚህ በተጨማሪ ቅዱሳት ሥዕላት፥ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር እስኪደርስ ድረስ በመቃተትና በምጥ ያለው ፍጥረት (ሮሜ 8፥ 21-22) ተስፋ የሚያደርገውን ሰማያዊ ክብር አስቀድመን በዚህ ምድር እንድናስበው ያደርጉናል፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት በጨርቅ ወይም ግድግዳ ላይ የሚሳሉ የጌታችንና የቅዱሳን ሥዕሎች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይቀደሱ ዘንድ ጸሎት ይደረግላቸዋል፡፡[385] በሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የሚሰቀሉትም ሆነ በተለያዩ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ላይ የሚሳሉ ሥዕሎች መንፈሳዊና የትምህርተ ሃይማኖት መልእክቶችን የማስተላለፍ ብቃት አላቸው፡፡ የመድኃኒችን ኢየሱስ ክርስቶስን አጠቃላይ የማዳን ሥራ፡-[386] ብሥራት፥ ልደት፥ ጥምቀት፥ የተራራው ስብከት፥ ሆሣዕና፥ ስቅለት፥ ትንሣኤ፥ ዕርገት፥ በዓለ ጰራቅሊጦስ እና ምጽአት በልዩ ጥበብ የሚገልጹ ቅዱሳት ሥዕላት በቅዳሴ ሰዓት ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ የሚከናወነውን የቀዳማዊ ምጽአቱን ተግባር በሚገባንና በሚታይ መልኩ ያስተምሩናል፡፡ በተጨማሪም እኛ በምንረዳው መልኩ በቅዱሳት ሥዕላት የሚገለጹት ቅዱሳን መላእክት፥ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ ገነት፥ ሲኦል ወዘተ. ምድራዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊት ምሥጢር መሆንዋን በሚገባ ያመለክታሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን በተለየ ጥበብና ጸጋ በተሣሉ ሥዕላት የተሞላው የደብረ ዳሞ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ ክፍል[387] እና እጅግ ደንቅ በሆኑ ሥዕላተ-ኪሩብ ያጌጠው ደብረ ብርሃን ሥላሴ[388] ናቸው፡፡ ስለዚህ የተለየ መንፈሳዊ ውበትን የተላበሰው ኦርቶዶክሳዊ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን፥ ዕይታችንን የተቀደሰ ከሚያደርጉት

---

[385] Seifesellassie Yohannis, “Holy Images in the Church,” *Ethiopian Church Treasures and Faith,* ed. Jacques Mercier (Paris: L’archange Minotaure, 2009) p. 59.

[386] The Christ- event.

[387] Sylvia Pankhurst, *Ethiopia: A Cultural History* (Norwich: Fletcher and Son Ltd., 1955) p. 144.

[388] David Buxton, *The Abyssinians* (Southampton: Camelot Press Ltd., 1970) p. 151.

ቅዱሳት ሥዕላት ጋር፥ ፍጥረታት በሙሉ ፈጣሪያቸውን ለማመስገን የሚሰባሰቡበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር (ራእ. 21፥1) ምሳሌ ይሆናል፡፡[389]

## ፪. ምሳሌያት ዘቅዳሴ[390]

ካህናቱና ዲያቆናቱ በቅዳሴው አገልግሎት የሚያከናውኑት ማንኛውም አይነት ድርጊት በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን የራሱ የሆነ ምሳሌያዊ ትርጒም አለው፡፡ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራዎችን (ልደቱ፥ ጥምቀቱ፥ ሞቱ፥ ትንሣኤውና ዕርገቱ) በምሳሌና በትርጒም ለእኛ እውን የሚያደርጉልን ሁነቶች (ክንውኖች) በሥርዓተ ቅዳሴው ውስጥ ተካተዋል፡፡ በቅዳሴው የተገኙ ምእመናንም ለዲያቆኑ ትእዛዛትና ለተለያዩ ዝማሬያት መልስ ከመስጠት ጀምሮ በሙሉ የስሜት ሕዋሳቶቻቸው የሥርዓተ አምልኮው ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጋበዛሉ፡፡ ዓይኖቻችን ቅዱሳት ሥዕላትን፥ የቤተ መቅደሱን ውበትና የሥርዓተ ቅዳሴውን ሂደት በመመልከት ይቀደሳሉ፡፡ የቅዳሴው ሁለተኛ ክፍል ውስጥ የሚነበቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና የአገልግሎቱ ያማረ ዜማ ለጆሮዎቻችን የተለየ ጣዕም ይሰጧቸዋል፡፡ በአፍንጫችን የዕጣኑን መዓዛ እያሸተትን ሐሤት እናደርጋለን፡፡ በእጆቻችን ወንጌሉንና ቅዱሳት ሥዕላትን እየዳሰስን እንሳለማለን፡፡ በመጨረሻም የቅዱስ ቍርባንን ጣዕም ቀምሰን "ከአምላካዊ ምሥጢር በተቀበልሁ በእኔ፥ በአንደበቴ ምስጋናህን፥ በልቡናዬ ሐሤትን፥ በሰውነቴም ደስታና ምላ"[391] እንላለን፡፡ ለቅዳሴው አገልገሎት የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳት (ፃሕል፥ ጽዋ፥ ዕርፈ መስቀል፥ ማኅፈዳት፥ ወዘተ.)፥ ሠራዒው ካህን የሚያከናውነው ሥርዓተ ፈትቶ፥ የዲያቆኑ ትእዛዛት (ተንሥኡ ለጸሎት፥ ስግዱ በፍርሃት፥ አድንኑ፥ ተአምኑ፥ ነጽር ወዘተ.)፥ በቅዳሴው ሰዓት የሚሰሙ ደወሎች፥ የተለያዩ ድርጊቶች[392] እና የሚፈጸሙባቸው የቤተ ክርስቲያኑ ክፍሎች (መቅደስ/ቅድስተ ቅዱሳን፥ ቅድስት) በውስጣቸው የያዙትን ምሳሌና ትርጒም በዝርዝር ለማስረዳት ራሱን የቻለ መጽሐፍ ያስፈልገዋል፤ በዚህ ክፍል የተወሰኑትን ብቻ እንመለከታለን፡፡

---

[389] Leonid Ouspensky, *Theology of the Icon,* trans. Anthony Gythiel, Vol. I (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1992) p. 30.

[390] Liturgical Symbolism.

[391] "ጸሎት እምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 119፣ ገጽ 111፡፡

[392] Gestures and processions.

## ልኡካን

ለቅዳሴ አገልግሎት አምስት ልኡካን ያስፈልጋሉ፤ ቅዳሴውን የሚመራው ካህን (ሠራዒ ወይም ገባሬ ሠናይ ካህን)፥ የካህኑ ረዳት (ንፍቅ ካህን)፥ የመጾር መስቀል ይዞ ተንሥኡ፡ ጸልዩ በማለት አብዛኞቹን ትእዛዛት የሚያስተላልፈውና በዕርፈ መስቀል ከጽዋው ደሙን ለምእመናን የሚያቀብለው ሠራዒ ወይም ገባሬ ሠናይ ዲያቆን፥ ጧፍ በመያዝ የቅዳሴውን ዑደቶች የሚመራው ንፍቅ ዲያቆን እና ከቅዱሳት መጻሕፍት የሚነበቡትን ንባባት የሚያዘጋጀው ዲያቆን (ፍሬ ሰሞነኛ) ናቸው፡፡ በስደት አገር ያሉት አብያተ ክርስቲያን አምስቱንም ልኡካን ተሟልተው ስለማያገኟቸው ከዚህ ባነሰ ቍጥር (በአንድ ቄስና ዲያቆን፥ በአንድ ቄስና ሁለት ዲያቆናት ወዘተ.) ይቀድሳሉ፡፡

ሠራዒውና ንፍቁ ካህን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የገነዙት የዮሴፍና ኒቆዲሞስ (ዮሐ. 19፥ 38-39) ምሳሌ ናቸው፤ አግብኦተ ግብር ላይ ንፍቁ ካህን ኅብስቱን ከሠራዒው በማኅፈድ ይቀበልና፡- "የካህናት አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በበፍታ ልብስና በሽቱ እንደገነዙህ እንደ ወደድህላቸውም እንዲሁ ውደድልን" ይላል፡፡[393] በቅዳሴ ማርያም ሠራዒው ካህን እርሱ እንደ ኒቆዲሞስ፥ ንፍቁ ካህን ደግሞ እንደ ዮሴፍ ይሆኑ ዘንድ እንዲህ በማለት ይጸልያል፡- "በዚህ ምሥጢር እየተራዳኝ ከእኔ ጋር ያለ ይህንን ካህን እርሱንም እኔንም ሥጋህን እንደ ገነዙት አንደ ዮሴፍና እንደ ኒቆዲሞስ አድርገን"፡፡[394] ሠራዒው ዲያቆን የቅዱስ እስጢፋኖስ ምሳሌ ነው፡፡ ጌታችን ክርስቶስ ስለሰቀሉት ሰዎች "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው" (ሉቃ. 23፥34) በማለት እንደጸለየ፥ ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ የሆነው እስጢፋኖስም (የሐዋ. 6፥ 5-6) በድንጋይ ይወግሩት ስለነበሩ ሰዎች "ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው" (የሐ. ሥራ 7፥60) ብሎ በመጸለይ ጌታውን መስሎታል፡፡ ይህን የመስቀል ጉዞ ለማመልከት ሠራዒው ዲያቆን በቅዳሴ ሰዓት የመፆር መስቀል ይይዛል፡፡ ንፍቁ ዲያቆን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት መንገድ ጠራጊ የነበረው የቅዱስ

393 "ሥርዓተ ቅዳሴ" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 12፣ ገጽ 26፡፡

394 "ቅዳሴ ማርያም" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 115፣ ገጽ 180፡፡

ዮሐንስ መጥምቅ ምሳሌ ነው፡፡ ጌታ ስለዮሐንስ “እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ” (ዮሐ. 5፥35) ያለውን ለማመልከት ንፍቁ ዲያቆን ጧፍ አብርቶ የቅዳሴውን ዑደት ይመራል፡፡

## ዕጣን

ዕጣን ለእግዚአብሔር ክብር የሚቀርብ የአምልኮ መግለጫ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሙሴን በምስክሩ ታቦት ፊት “አሮን የጣፋጭ ሽቱ ዕጣን ይጠንበት፤ በማለዳ በማለዳ መብራቶቹን ሲያዘጋጅ ይጠነው” ሲል እንዳዘዘው እናነባለን (ዘጸ. 30፥7)፡፡ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ አባት ካህኑ ዘካርያስም እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ዕጣን እንዲያጥን ተራ እንደደረሰውና “በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ” እንደነበር በቅዱስ ወንጌል ተጽፏል (ሉቃ. 1፥8-10)፡፡ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊት መሠረት በማድረግ በቤተ ክርስቲያናችን ካህናት ዘወትር በነግህ እና በሠርክ (ጠዋትና ማታ) ጸሎተ ዕጣንን እየጸለዩ አምልኮ የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነው አምላክ ዕጣንን ያሳርጋሉ፡፡ በእነዚህ የጸሎት ጊዜያትና በቅዳሴ ጊዜ ካህናት ጥና (ጽንሐሕ) ውስጥ ጨምረው የሚያሳርጉት ዕጣን የሚከተሉት ምሳሌያትና መልእክቶች አሉት፡-

1) የዕጣኑ ጣፋጭ መዓዛ ስለእኛ ኃጢአት ያማረና የተወደደ መሥዋዕት የሆነው ክርስቶስን ያመለክታል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ፡- “እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለእናንተ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ” ብሏል (5፥1-2)፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን በቅዳሴዋ “ዕፍረት ምዑዝ ኢየሱስ ክርስቶስ” (ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ያለው ሽቱ ነው)[395] እያለች የምታመሰግነው ጌታ “ራሱን ያማረ መሥዋዕትና ዕጣን አድርጎ ለአባቱ ያሳረገ”[396] እንደሆነ ትመሰክራለች፡፡

[395] “ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 162፣ ገጽ 62፡፡

[396] “ማዕጠንት ዘወርቅ” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 122፣ ገጽ 51፡፡ (ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ፡ ወመሥዋዕተ ሥሙረ)፡፡

2) የክርስቲያኖችን ሕይወት ያመለከታል፡፡ የዕጣኑ መዓዛ ለአፍንጫችን ጣፋጭ እንደሆነ ሁሉ፥ ክርስቲያኖችም ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ሰውን የሚማርክ መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከእግዚአብሔር የተወለዱ፥ በክርስቶስ ክርስቶሳውያን (መሢሐውያን) የተባሉ የክርስቲያኖች ሕይወት ክርስቶስን ለሌሎች የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ በዕጣን የተመሰለው፥ ራሱን ስለእኛ ለአባቱ ያማረ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ጌታ፥ መዓዛው በእኛ ውስጥ ሌሎችን ሊማርክ ይገባል፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- “በሚድኑትና በሚጠፉት ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና” እንዲል (2 ቆሮ. 2፥15)፡፡

3) የቅዱሳን ጸሎት ምሳሌ ነው፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት፡- “ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ” ሲል እንደጸለየው (መዝ. 140/141፥2) በቤተ ክርስቲያናችን የአምልኮ ጊዜ ወደ ላይ የሚያርገው[397] የዕጣኑ ደመና የክርስቲያኖች የኅብረት ጸሎት ምሳሌ ነው፡፡ በቅዳሴ ሰዓት “ማርያም ዕጣን ናት፤ ከተመረጠ ዕጣን ሁሉ [የሚበልጥ መዓዛ ያለው] እና በማኅፀንዋ ያደረው እርሱ (ጌታ) ነው”[398] እያልን እንደምንዘምረው በውስጧ ያደረው አምላክ የተለየ መንፈሳዊ ውበትና መዓዛ የሰጣት ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን፥ በክርስቶስ ካገኙት ጸጋ የተነሣ እንደ አምላካቸው ውብና የተቀደሰ ሕይወት ያላቸው ቅዱሳን እና ያለማቋረጥ በሰማያት እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት ቅዱሳን መላእክት ከእኛ ጋር አብረው ስለሚያመልኩ፥ የምድራዊቷ እና የሰማያዊቷ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት በአንድ ላይ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ሰማያዊ ዙፋን ያርጋል፡፡ ዮሐንስ በራእዩ ያየው መልአክ ይህንን እውነታ ያረጋግጥልናል፡- “ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፡፡ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ” (ራእ. 8፥3-4)፡፡

4) የካህናትን ክብር ለማሳየት፡፡ ቀዳሹ ካህን “የክርስቶስ መልእክተኞች” (2 ቆሮ. 5፥20) የሆኑትን ካህናት የተጠሩለትን የክህነት ክብር ከግንዛቤ በማስገባት፥ በቅዳሴው ሰዓት የተገኘውን እያንዳንዱን ካህን “እስእለከ አ አቡየ ቀሲስ ከመ

[397] “ር” ጠብቆ ይነበብ፡፡

[398] “ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት” መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 161፣ ገጽ 62፡፡

ትዘከረኒ በጸሎትከ ቅድስት" (አባቴ ቀሲስ ሆይ ክብርት በምትሆን ጸሎትህ ታስበኝ ዘንድ እለምንሃለሁ) እያለ ያጥነዋል፡፡ ካህናቱም፡- "[የመልከጼዴቅን መሥዋዕት፥ በበኵር ቤተ ክርስቲያን[399] የሚኖሩ የአሮንና የዘካርያስን ዕጣን እንደተቀበለ]፡ እግዚአብሔር መሥዋዕትህን ይቀበል፤ ክህነትህንም በእውነት ይጠብቃት፤ የዕጣንህንም መዓዛ ያሸትት (ይቀበል)" በማለት ይመልሱለታል፡፡[400]

5) በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለውን አርአያ እግዚአብሔር[401] ለማክበር፡፡ ዕጣን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የአምልኮ መግለጫ ነው ብለናል፡፡ በቅዳሴ ሰዓት ካህናቱ ምእመናንን የሚያጥኑበት ምክንያት "እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" ተብሎ እንደተጻፈ (ዘፍ. 1፥27) በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ለተሣለው አርአያ እግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ነው፡፡ እንዲሁም ክርስቲያኖች በጥምቀት ክርስቶስን ስለለበሱት፥ ክርስቶስን የመሰለ ሕይወት እንዳላቸው ለማመልከት ካህናቱ ምእመናንን በክብር ያጥኗቸዋል፡፡

## መንጦላዕት

ከላይ ስለሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌያዊ ትርጕም በመጠኑ ባጠናንበት ክፍል፥ ቅድስተ ቅዱሳን (መቅደስ) የተሰኘው የቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ ክፍል በሰማይ፥ ቀሪው የቤተ ክርስቲያኑ ክፍል ደግሞ በምድር እንደሚመሰሉ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ በሁለቱ መካከል ያለው መጋረጃ (መንጦላዕት) የጠፈር[402] ምሳሌ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ቅዳሴው እንደተጀመረ መጋረጃ የሚከፈትበት ምክንያት ሰማይ መከፈቱን እና ወደ ሰማያዊ ምሥጢር ለመግባት በዝግጅት ላይ መሆናችንን ለማመልከት ነው፡፡[403] ጌታችን ኢየሱስ ስለእኛ ቤዛነት የተሰቀለው ስድስት ሰዓት ላይ እንደነበርና እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ እንደሆነ በቅዱስ ወንጌል እናነባለን (ሉቃ. 23፥ 33-45)፡፡ ጌታ የተቀበረውም ሆነ ሞትን ድል አድርጎ

---

[399] "ቤተ ክርስቲያን ዘበኵር" የሚለው በብሉይ ኪዳን የነበሩ የእግዚብሔር ካህናትና የተመረጡ ሕዝቦች ኅብረትን ያመለክታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን፡- በሰማያት ያሉ ቅዱሳን መላእክት፥ በብሉይ ኪዳን የነበሩ የእምነት ምስክሮች (ዕብ. 11፥32-12፥1) እና የአዲስ ኪዳን አማንያን ጉባኤ (ኅብረት) ናት (ዕብ. 12፥22-24)፡፡
[400] "*ሥርዓተ ቅዳሴ*" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 124፣ ገጽ 52፡፡
[401] Image of God.
[402] Firmament or sky.
[403] Varghese, *The Living Sacrifice*, p. 185.

የተነሣው በጨለማ ነው (ማቴ. 27፥57- 28፥6፤ ሉቃ. 23፥50-24፥1-5)። ስለዚህ የጌታ ሕማሙ፥ ሞቱና ትንሣኤው ወደሚታሰብበት[404] የቅዳሴው ሦስተኛ ክፍል ስንደርስ (ሠራዒው ካህን ሥርዓተ ፈትቶ በሚያከናውንበት ጊዜ)[405] የመቅደሱ መጋረጃ ይዘጋል።

## ፭ወ፪ቱ ቡራኬያት

ሠራዒው ካህን 21 የውስጥ ቡራኬያትን በኅብስቱና በወይኑ ላይ፤ 21 የአፍአ (የውጭ) ቡራኬያትን[406] በምእመናንና ካህናት ላይ (በአጠቃላይ 42 ቡራኬያትን) ያደርጋል።[407] የውስጥ ቡራኬያት የሚከናወኑት በእጅ (ካህኑ ጣቶቹን አመሳቅሎ) ሲሆን፥ የውጭ ቡራኬያትን ደግሞ በእጅ መስቀል ይባርካል። የውስጥ ቡራኬያት 21 የሆኑበት ምክንያት የአስቆሩቱ ይሁዳ ጌታን ኀሙስ ማታ (ከምሽቱ 3 ሰዓት) አሳልፎ ከሰጠው በኋላ ሌሊቱን በሙሉ ለ 9 ሰዓታት ያህል ጌታችን መከራ መስቀልን ሲቀበል አድሯል። በማግስቱ ዓርብ ነፍሱ ከሥጋው እስከተለየችበት 9 ሰዓት ድረስ (ማር. 15፥34-37) ተጨማሪ መከራ መስቀልን ሲቀበል ውሏል፤ ሁለቱን ስንደምር 18 ሰዓታትን እናገኛለን። ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ በመስቀል ላይ ለሁለት ሰዓታት ያህል ቆይቷል፤ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ 11 ሰዓት ላይ ከመስቀል አውርደው፥ ገንዘው እስኪቀብሩት ድረስ ተጨማሪ አንድ ሰዓት ወስደዋል። በመከራና በሕማም ያሳለፈባቸው 18 ሰዓታት ላይ እነዚህን 3 ሰዓታት ስንደምር 21 ሰዓታትን እናገኛለን። ስለዚህ "በ21ዱ ሰዓት በተቀበለው መከራ ካሳ

---

[404] "ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ፥ ወትንሣኤከ ቅድስተ፥ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ፤ ንሴብሐከ፥ ወንትአመነከ፥ ንስእለከ፥ ወናስተበቍዐከ አ እግዚእነ ወአምላክነ። . . . ይእዜኒ እግዚኦ እንዘ ንዜክር ሞተከ፥ ወትንሣኤከ፤ ንትአመነከ፥ ወናቄርብ ለከ ዘንተ ኅብስተ . . . ።" - "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 47-48፣ ገጽ 95።

[405] "ሀበነ ንኅበር በዘዚከ መንፈስ ቅዱስ . . ." (ያንተ በሚሆን መንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን . . . ) የሚለውን እያዜመ ፈትቶውን (fraction) ያካሂዳል። "ቅዳሴ ሐዋርያት" መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. ገጽ 96።

[406] ቄሱ በሚቀድስበት ጊዜ ጳጳስ (ሊቀ ጳጳስ) ወይም የደብሩ አስተዳዳሪ (የገዳሙ አበ ምኔት) ከእነዚህ አንዱ ከተገኘ፥ በተለምዶ በሠራዒው (ቀዳሹ) ካህን ፋንታ የውጭ ቡራኬውን ይባርካል። የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ ቅዳሴ ግን አንድም ቦታ ይህንን አያዝም።

[407] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 382።

ስለተፈጸመ፥ ዓለምም ስለተባረከችና ስለተቀደሰች"[408] በመሥዋዕቱ (በኅብስቱና በወይኑ ላይ) የሚደረጉት ቡራኬያት ይህን ለማሰብ ሲባል ቍጥራቸው 21 ሆነ፡፡ ካህኑ የውስጥ ቡራኬያትን የሚፈጽምባቸው ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው[409]፡-

፩) ቡራኬ ዘአግብኦተ ግብር

1) "ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ" ሲል እጁን (ጣቶቹን አመሳቅሎ) በኅብስቱ ራስ ላይ ያስቀምጣል፤ "ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ" ሲል እጁን ከታች ያስቀምጣል፤ "ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሒ ኵልነ" እያለ በኅብስቱ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ ያመሳቅላል፡፡ ይህ የመጀመሪያው ቡራኬ ነው፡፡

2) በኅብስቱ ላይ እንዳደረገው ጽዋውንም ይባርካል፡፡

3) "ስብሐት ወክብር ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ፤ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ . . ." እያለ በአንድነት ኅብስቱንና ጽዋውን ይባርካል፡፡[410]

፪) በጸሎተ እንፎራ

4) "ባርኮ ለዝንቱ ኅብስት" ሲል ኅብስቱን፥

5) "ወቀድሶ ለዝንቱ ጽዋዕ" ሲል ጽዋውን ይባርካል፤

6) "ወአንጽሖሙ ለክልኤሆሙ"[411] ሲል ኅብስቱንና ጽዋውን (ሁለቱንም አንድ ላይ) ይባርካል፡፡

፫) በሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ

7) "አእኰተ"

8) "ባረከ"

---

[408] Getatchew Haile, "An Amharic Study on the Liturgy and Symbolism of the Ethiopian Church," EMML 1157, f. 220 vv, p. 93.

[409] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 92፡፡

[410] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 20-21፣ ገጽ 28፡፡

[411] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 48፣ ገጽ 35፡፡

9) "*ወፈተተ*"[412] እያለ 3 ጊዜ ኅብስቱን ይባርካል፤ ከዚያም በኅብስቱ ራስ፥ እግር፥ ግራና ቀኝ እና ጐድኑ ላይ በጣቱ ወጋ እያደረገ የቀኖት (ጌታ በሚስማር የተቸነከረበትን) ምልክት ያደርጋል፡፡[413]

10) በኅብስቱ ላይ እንዳደረገው በጽዋውም ላይ፡- "አእኵቶ"

11) "ባሪኮ"

12) "ወቀዲሶ"[414] እያለ ሦስት ጊዜ ይባርካል፡፡

፬) በጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኅብስት ወወይን

13) "ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፈኑ መንፈሰ ቅዱሰ ወኃይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ ይረስዮ *ሥጋሁ* ወደሞ . . ." እያለ አንድ ጊዜ በኅብስቱ ላይ፥

14) አንድ ጊዜ በጽዋው ላይ ባርኮ፥

15) ሁለቱንም አንድ ላይ ይባርካል፡፡[415]

፭) "አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን . . ." ሲል

16) "አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ . . ." ሲል፥

17) "አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን ከመ ኢተፈልጠ መለኮቱ እምትስብእቱ. . ." ሲል፥

18) "አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን ከመ ዝንቱ ውእቱ *ሥጋሁ* ወደሙ . . ." ሲል የመስቀል ምልክት ያለበትን የ*ሥጋ*ውን መካከለኛ ክፍል (*ዴስፖቲኮን*) ይዞ፥ ደሙን አስነክቶ *ሥጋ*ውን ሦስት ጊዜ ይባርካል፡፡

19) "ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ"

20) "ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ"

---

[412] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 41፣ ገጽ 94፡፡

[413] Getatchew Haile, "An Amharic Study on the Liturgy and Symbolism of the Ethiopian Church," EMML 1157, f. 220 vv, p. 92፤ *መጽሐፈ ቅዳሴ*ውም፡- "ከዚያም በኋላ [ሦስት ጊዜ ከባረከ በኋላ] ኅብስቱን ሳይለየው ከአምስት ላይ ጥቂት ያንቃው" ይላል፡፡ *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 41፣ ገጽ 94፡፡

[414] *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 44፣ ገጽ 94፡፡

[415] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 48-49፣ ገጽ 95፡፡

21) "ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጳራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሔ ኲልነ፤ ስብሐት ወክብር ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ፤ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ . . ." እያለ በሥጋው መካከለኛ ክፍል ጽዋውን ሦስት ጊዜ ይባርካል፡፡[416]

ካህኑ በመስቀል ምእመናንን፥ ካህናትንና ዲያቆናትን የሚባርክባቸው 21 የአፍኣ (የውጭ) ቡራኬያት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

፩) በጸሎት አኰቴት

1) "አርኅቅ እግዚኦ እምኔየ" ሲል ራሱን ይባርካል፤

2) "ወእምነ ኲሉ ሕዝብከ" እያለ ምእመናንን ይባርካል፤

3) "ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ ዘዚአከ" ሲል መቅደስ ውስጥ ያሉትን ካህናትንና ዲያቆናትን ይባርካል፡፡[417]

፪) በፍትሐት ዘወልድ[418]

4) "አግብርቲከ እለ ተልዕኩ በዛቲ ዕለት ቀሲስ ወዲያቆን ወካህናት" ሲል ካህናቱንና ዲያቆናቱን ይባርካል፤

5) "ወኲሉ ሕዝብ" ሲል ሕዝቡን (ምእመናንን) ይባርካል፤

6) "ወምስኪነትየኒ አነ ገብርከ"ሲል ራሱን ይባርካል፡፡[419]

፫) በትምህርት ክፍል

7) "ወዕቀባ ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት እንተ ሣረርካ በእንቲአሆሙ" ሲል ራሱን ይባርካል፤

8) "ወባርክ ላዕለ አባግዐ መርዔትከ" ሲል ሕዝቡን ይባርካል፤

9) "ወአብዝኃ ለዛቲ ዐፀደ ወይን" ሲል በመንበሩ ዙሪያ (መቅደሱ ውስጥ) ያሉትን ይባርካል፡፡[420]

---

416 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 104፣ ገጽ 107፡፡

417 ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 38፣ ገጽ 32፡፡

418 ፍትሐት ዘወልድን የሚደግመው ንፍቁ ካህን ነው፤ ነገር ግን ንፍቁ ካህን ምንም አይነት ቡራኬ ስለማያደርግ፥ ቡራኬ በሚያስፈልጋቸው ሦስት ቦታዎች ላይ ሠራዒው ካህን ከንፍቁ ጀርባ ሆኖ መባረክ አለበት፡፡ እንዲሁም በጸሎተ ቡራኬ "ንፍቅ ቄስ 'ባርክ' [ባለ] ቍጥር ሠራዒው ቄስ በየስልቱ ይባርክ" የሚል ትእዛዝ መጽሐፈ ቅዳሴው ውስጥ እናነባለን - መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 10፣ ገጽ 89፡፡ ነገር ግን ንፍቁ ቄስ ፍትሐት ዘወልድንም ሆነ ጸሎተ ቡራኬን በሚደግምበት ጊዜ በተለምዶ መስቀል ይዞ ሲባርክ እናያለን፡፡

419 መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 61፣ ገጽ 39::

፬) በጸዋትው

10) "ኵሎ ሕዝበ ወኵሎ መራዕየ ባርኮሙ" ሲል ሕዝቡን ይባርካል፤

11) "ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ ባርኮሙ" ሲል ሕዝቡን ይባርካል፡፡[421]

፭) በጸሎተ ቡራኬ

12) "ባርክ ዲበ ሕዝብከ ፍቁራን ክርስቶሳውያን በበረከተ ሰማያውያን ወምድራውያን" ሲል ሕዝቡን ይባርካል፤

13) "ወባርክ እለ ያስተነትኑ" ሲል ሕዝቡን ይባርካል፤

14) "ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ፡ ወባርክ ርስተከ" ሲል ሕዝቡን ይባርካል፡፡[422]

፮) በጸሎተ ንስሓ

15) "ኦ እግዚኦ ረስየነ ፍቱሓነ"

16) "ወግዑዛነ"

17) "ወለኵሎሙ ሕዝብከ ፍትሖሙ" እያለ ፊቱን ወደ ምእመናን መልሶ ሦስት ጊዜ ይባርካቸዋል፡፡[423]

፯) ድርገት ላይ (ምእመናንን ለማቀኍረብ ከመቅደስ ሲወጣ)

18) "እለ ጸዋዕከ እግዚኦ፡ ወእለ ቀደስከ . . ." የሚለውን ጸሎት እየጸለየ በፃሕሉ ላይ አንድ ጊዜ ይባርካል፡፡[424]

---

[420] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 147፣ ገጽ 58፡፡ ካህኑ ወንጌል ሲያነብ "ባርክ እግዚኦ ነገረ ዘእምወንጌለ . . ." ይላል፤ ነገር ግን ምንም አይነት ቡራኬ አያደርግም፡፡ ወንጌልን ከማንበቡ በፊትም "እግዚአብሔር ልዑል ይባርክ ላዕለ ኵልነ . . ." እያለ በአራቱ መዓዝነ ዓለም ይባርካል፡፡ እነዚህ ቡራኬያት በሕዝቡ ላይ የሚደረጉ ስላልሆኑ "የአፍኣ ቡራኬያት" ዝርዝር ውስጥ አይገቡም፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 187፣ ገጽ 65 እና ቍ. 212፣ ገጽ 71 ይመልከቱ፡፡

[421] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 9፣ ገጽ 76 እና ቍ. 24፣ ገጽ 79 ይመልከቱ፡፡

[422] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 10፥17 እና 21፣ ገጽ 89-91፡፡ በጸሎተ ቡራኬ ንፍቁ ካህን "ባርክ ነፋሳተ ሰማይ" እና "[ወባርክ] ዝናማተ ወፍሬያተ ምድር" ሲል ሠራዒው ካህን ወደ ሰማይና ወደምድር እያመለከተ ቡራኬ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን አነዚህ ቡራኬያት በሕዝቡ ላይ የሚደረጉ ስላልሆኑ ከ21ዱ የአፍኣ (የውጭ) ቡራኬያት ውስጥ አይገቡም፡፡

[423] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 82፣ ገጽ 101፡፡ ካህኑ "ዘኮነ ንጹሐ . . ." የሚለውን አውጀ እጁን ከታጠበ በኋላ መስቀል ስለማይነካ፥ እነዚህን ቡራኬያትና ምእመናንን ለማቀኍረብ ከመቅደስ ሲወጣ "እለ ጸዋዕከ እግዚኦ ወእለ ቀደስከ . . ." እያለ በፃሕሉ ላይ በእጁ ይባርካል፡፡

[424] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 128፣ ገጽ 113፡፡

፰) ሥርሖተ ሕዝብ ላይ (ሕዝቡን ሲያሰናብት)

19) "ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ"

20) "ወባርክ ርስተከ"

21) "ረዓዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም"[425] እያለ ምእመናንን በመጾር መስቀል ሦስት ጊዜ ይባርካቸዋል፡፡

## ፲ወ፩ዱ እማሬያት

"እማሬ" የሚለው የግእዝ ቃል አመረ = አመለከተ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን፥ ማመልከት ማለት ነው፡፡ ሠራዒው ካህን በቅዳሴ ሰዓት 21 የውስጥ ቡራኬያትን በኅብስቱና በወይኑ ላይ እንደሚያከናውን ተመልክተናል፡፡ ቡራኬ የሚያስፈልጋቸው ቦታዎችን በማስተዋል ከመባረክ ጋር፥ "ይህን ኅብስት" እና "ይህን ጽዋ" የሚሉ ሐረጎች በተጠቀሱበት የቅዳሴው ጸሎታት ላይም ወደ ኅብስቱና ወደ ጽዋው በእጁ ያመለክታል፡፡ ይህንንም 11 ጊዜ ስለሚያደርግ፥ ቅዳሴ 11 እማሬያት[426] (በኅብስቱና በጽዋው ላይ የማመልከት ድርጊት) አሉት ማለት ነው፡፡ ካህኑ 11ዱን እማሬያት የሚያደርግባቸው ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው፡-[427]

፩) በጸሎተ እንፎራ

1) "አርኢ ገጸከ ላዕለ ዝንቱ ዝንቱ ኅብስት" ሲል በኅብስቱ ላይ፤

2) "ወዲበ ዝንቱ ጽዋዕ" ሲል በጽዋው ላይ ያመለክታል፡፡[428]

---

[425] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 160፣ ገጽ 121፡፡

[426] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 382፡፡ ካህኑ አግብኦተ ግብር (offertory) ላይ "ከማሁ ረስዮ ለዝንቱ ወይን" ሲል እና ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ (*anamnesis*) ላይ "ይእዜኒ እግዚኦ እንዘ ንዜከር ሞተከ ወትንሣኤከ . . . ናቄርብ ለከ ዘንተ ኅብስተ፡ ወዘንተ ጽዋዐ" ሲል ሦስት እማሬያትን ማድረግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን ስለእማሬያት በመጽሐፈ ቅዳሴው የተሰጠው ሐተታ፥ እነዚህን ሦስት እማሬያት ከ11ዱ እማሬያት ውስጥ አላስገባቸውም፡፡ መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 16፣ ገጽ 27፤ ቍ. 48፣ ገጽ 95 እና ገጽ 382 ይመልከቱ፡፡

[427] ዝኒ ከማሁ፡፡

[428] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 47፣ ገጽ 35፡፡ እዚሁ ክፍል ላይ "ወሚጦ ለዝንቱ ኅብስት" ሲል በኅብስቱ ላይ፤ "ወዘተደመረ ውስተ ዝንቱ ጽዋዕ" ሲል በጽዋው ላይ ማመልከት እንዳለበት መጽሐፈ ቅዳሴው ይጠቁማል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁለት እማሬያት ከ11ዱ የቅዳሴ እማሬያት አልተካተቱም - መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ገጽ 382 ይመልከቱ፡፡

፪) በሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ

3) “ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ” ሲል በኅብስቱ ላይ

4) “ወይቤሎሙ ንሥኡ ስተዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ” ሲል በጽዋው ላይ ያመለክታል፡፡[429]

፫) በጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ

5) “ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፈኑ መንፈስ ቅዱስ ወኃይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት” ሲል በኅብስቱ ላይ ያመለክታል፡፡

6) “ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ” ሲል ደግሞ በጽዋው ላይ ያመለክታል፡፡[430]

፬) “አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን . . .” ሲል

7) “ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን” ሲል በሥጋው ላይ፤

8) “ደም ክቡር ዘበአማን” ሲል በጽዋው ላይ፤

9) “እስመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን” ሲል በሁለቱም ላይ ያመለክታል፡፡[431]

10) በመጀመሪያው “አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ” ሲል በሥጋውና በደሙ ላይ፤

11) በሦስተኛው “አአምን” በሥጋውና በደሙ ላይ እያመለከተ፡- “አአምን፥ አአምን፥ አአምን፥ ወእትአመን ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ . . . ” ይላል፡፡[432]

## ፺ቱ ዑደታት

በቅዳሴው የዝግጅት ክፍል ዲያቆኑ “በእንተ ቅድሳት” በማለት የሚጀምረውን ጸሎት በሚደግምበት ጊዜ ሠራዒው ካህን “ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ . . .” የሚለውን ጸሎት እየጸለየ መንበሩን ሦስት ጊዜ ይዞራል (ዑደት ያደርጋል)፡፡[433] በሁለተኛው የቅዳሴ ክፍል ንፍቁ ካህን ከግብረ ሐዋርያት መጽሐፍ አንብቦ እንደጨረሰ፥ በድጋሚ ሠራዒው ካህን ይህንኑ ጸሎት እየጸለየ መንበሩን ሦስት ጊዜ

[429] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቍ. 42 እና 44፣ ገጽ 94፡፡

[430] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 48፣ ገጽ 95፡፡

[431] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 98፥ 99 እና 100፣ ገጽ 105፡፡

[432] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 101 እና 100፣ ገጽ 105-106፡፡

[433] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 110፣ ገጽ 48፡፡

ይዞራል፡፡[434] "ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ …" እያለ በአራቱ የቤተ ክርስቲያኑ ማዕዘን ምእመናኑን ጨምሮ ካጠነ በኋላ በመንበሩ ደቡባዊ አቅጣጫ ወደ መቅደስ (ቅድስተ ቅዱሳን) ገብቶ ሰባተኛውን ዑደት ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚከተለውን ጸሎት ይጸልያል፡-

> አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በባርያህ በነዌ ልጅ በኢያሱ እጅ ቀድሞ የኢያሪኮን ቅጥር እንዳፈረስህ፥ እንዲሁ የእኔን [የኃጢአቴን ቅጥር] እና የሕዝቡንም ሁሉ ኃጢአት በእኔ በባርያህ [እጅ አፍርስ]፡፡[435]

የእስራኤል ልጆች በኢያሱ መሪነት ለሰባት ቀናት ያህል የኢያሪኮን ቅጥር እንደዞሩ፤ ሰባተኛው ቀን ቅጥሩን ሰባት ጊዜ ዞረው፥ ሰባት ቀንደ መለከት የያዙ ካህናት የቀንደ መለከቱን ድምፅ ካሰሙ በኋላ በሕዝቡ ጩኸት የኢያሪኮ ቅጥር እንደፈረሰ በመጽሐፈ ኢያሱ (7፥ 12-20) ተዘግቧል፡፡ ካህኑ ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ጠቅሶ ሰባተኛውን ዑደት በሚያጠናቅቅበት ጊዜ በፈቃዳችን የገነባነውንና እኛን ከአምላካችን የለየንን የኃጢአት ግንብ ልዑል እግዚአብሔር እንዲያፈርሰው ልመና ያቀርባል፡፡ ንፍቁም ካህን፡- ከግብረ ሐዋርያት መጽሐፍ አንብቦ ወደ መቅደስ ሲገባ፥ "ክቡር የሚሆን የወንጌልህን ቃል እንሰማ ዘንድ …" የሚለውን ጸሎት ከጸለየ በኋላ፥ ከንፍቁ ዲያቆንና ከሕዝቡ ጋር "ሠራዊተ መላእክቲሁ …" የሚለውን ዜማ ብሎ ወደ መቅደስ ከገባ በኋላ ሦስት ዑደታትን ያደርጋል፡፡ በቅዳሴ አትናቴዎስ ገባሬ ሠናዩ ካህን "የኀዝኑ በእንተ ፍጥረተ ሰብእ"[436] ሲል፥ በቅዳሴ ባስልዮስ ደግሞ "ወይፈድዮ ለኵሉ ለለአሐዱ አሐዱ በከመ ምግባሩ"[437] ሲል ንፍቁ ካህን ዑደት እንዲያደርግ መጽሐፈ ቅዳሴው ያዛል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ንባባት በሁሉም ቅዳሴያት ስለማይገኙ ከቍጥር አይገቡም፡፡[438]

---

[434] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 154፣ ገጽ 60፡፡
[435] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 127፣ ገጽ 53፡፡
[436] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 92፣ ገጽ 228፡፡
[437] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. 25፣ ገጽ 246፡፡
[438] ዝኒ ከማሁ፥ ቍ. ገጽ 382፡፡

## መደምደሚያ

በዚህ ምዕራፍ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በየዘመናቱ የተነሡ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሥርዓተ ቅዳሴ ዘእስክንድርያ [439] በሚል ስያሜ ከሚታወቀው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ የይዘትና የቅርጽ ለውጥ እንዳደረጉ ተመልክተናል፡፡ ለዚህም በዋነኝነት በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ ትልቅ ቦታ የተሰጣቸውን መጽሐፈ ሲኖዶስ እና መጽሐፈ ኪዳንን ተጠቅመዋል፡፡ ከእነዚህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍተ ሥርዓት እና ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የተለያዩ ጸሎታትን በመውሰድ፥ እንዲሁም በራሳቸው ግንዛቤ ለጸሎታቱ ተገቢ ነው ያሉትን ቦታ በመስጠት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ የራሱ የሆነ ይዘት እንዲኖረው አድርገዋል፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ መሠረቱ የኮፕቲክ ቅዳሴ ቢሆንም ሊቃውንቱ አባቶቻችን ኢትዮጵያዊ ዝማሬያትን (ለምሳሌ “እምነ በኀ”፥ “መስቀል አብርሃ በከዋክብት”፥ “ሠራዊተ መላእክቲሁ” ወዘተ.) በመጨመርና ግብፆች የታዉትን ዝማሬ (ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት) ጥንታዊ ቦታውን እንደያዘ ለትውልድ በማቆየት አባቶቻችን የሚደነቅ ሥራ ሠርተዋል፡፡ በመጽሐፈ ቅዳሴው ውስጥ የምናነባቸው ትእዛዛት [440] እና በሥርዓተ ቅዳሴው ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶችን (ሥርዓተ ፈትቶ፥ ቡራኬያት፥ እማሬያት፥ ዑደታት ወዘተ.) አስመልክቶ የተሰጡ ገለጻዎች በአባቶቻችን የሥርዓተ ቅዳሴ ግንዛቤ[441] እንድንኮራ ያደርገናል፡፡ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለትሕትና ሲሉ አባቶቻችን ስማቸውን ሳይነግሩንና በመጽሐፈ ቅዳሴውም ሆነ በመጽሐፈ ግጻዌ ዝግጅት የነበራቸውን ድርሻ ሳያሳውቁን በዝምታ እየሠሩ፥ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘኢትዮጵያ[442] ተብሎ ሊጠራ የሚችል ልዩና አስደናቂ ሥርዓተ አምልኮ ባለቤቶች አድርገውናል፡፡ ለእነዚህ ሊቃውንት ማስተዋሉን ለሰጠ ለአባቶቻችን አምላክ ክብርና ምስጋና፥ አምልኮና ውዳሴ፡ ዛሬም ዘወትርም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ይሁን፡፡

[439] Alexandrian Liturgical Rite.

[440] Rubrics.

[441] Liturgical consciousness.

[442] Ethiopian Liturgical Rite.

# ማጠቃለያ

በዓለም ያሉት የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ በመጠበቅና ከአበው የተቀበሉትን ትውፊት በማስቀጠል ይታወቃሉ፡፡ ኦርቶዶክሳዊው ቅዳሴ በየዘመናቱ እድገትና ለውጥ ቢያሳይም በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምእት ዓመታት የነበረውን መሠረታዊ ቅርጽ አልለቀቀም፡፡ ይህንንም እውነት የምሥራቅ ሥርዓተ ቅዳሴያት[1] የተሰኘው ዐቢይ ርእስ ሥር የሚካተቱትን የሱርስት (ምዕራብና ምሥራቅ ሶርያ)፥ የእስክንድርያ፥ የኢትዮጵያ፥ የአርመንና ጽርእ (ግሪክ) ሥርዓተ ቅዳሴያትን ይዘት በማነጻጸር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሁሉም ቅዳሴያት በአይሁድ የማዕድ ቡራኬ (*ቢርካት ሃማዞን*) ውስጥ ያሉት መሠረታዊ ጽንሰ አሳቦች (ተዝካር[2] እና ጽዋን የመባረክ ሥርዓት)፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ቊርባንን የመሠረተባቸው ቃላት (ሠራዕያን ቃላት)፥ *ዮጼር* ከሚባለው ጸሎተ አይሁድ የተወሰደው ዝማሬ ሱራፌል፥ መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና ጽዋው ላይ እንዲወርድ የሚጠይቀው ጸሎት እና የአማንያን የተቀደሰ ሰላምታን ይዘዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያን የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ከመጠበቅ ባሻገር፥ በውስጡ የሚከናወነውን ምሥጢር ክብርና ቅድስና በመረዳት የአምልኮአቸው ማዕከል አድርገውታል፡፡ ስለሆነም ለእያንዳንዲቱ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ቅዳሴ በልምድ የሚከናወን ሥርዓት ሳይሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት ጣዕም አስቀድማ የምትቀምስበት ሰማያዊ አምልኮ ነው፡፡

የክርስትና እምነት ከመግባቱ በፊት አገራችን ኢትዮጵያ ኦሪትን ስለተቀበለች፥ የአይሁድን ሥርዓተ አምልኮና የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዎች በዝርዝር የሚገልጹ መጻሕፍተ ሥርዓት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ "ሰመንቱ መጻሕፍተ ቀሌምንጦስ"[3] (መጽሐፈ ሲኖዶስ) እና መጽሐፈ ዲድስቅልያ ስለአይሁድ ሰንበት አከባበር ተደጋጋሚ ትእዛዞችን የያዙ

[1] Eastern Liturgical Rites.

[2] Remembrance.

[3] *Il Senodos Etiopico Canoni pseudoapostolici: Canoni dopo l'Ascensione, Canoni di Simone Cananeo, Canoni Apostolici, Lettera di Pietro*, CSCO*,* Vol. 552, Tom. 101, Scriptores Aethiopici, ed. Alessandro Bausi (Lovain: In Adeibus Peeters, 1995) p. 3.

ሲሆን፥ ከሌላው የክርስትና ዓለም ለየት ባለ መልኩ የመጽሐፈ ሲኖዶስ ትእዛዛትና አብጥሊሳት[4] እንዲሁም ዲድስቅልያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ገብተዋል፡፡ መጽሐፈ ኪዳንን ጨምሮ እነዚህን መጻሕፍተ-ሥርዓተ-ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን የተቀበሉትን ሥርዓተ ቅዳሴ ብሔራዊ (ኢትዮጵያዊ) መልክ ለማስያዝ ስለተጠቀሙባቸው፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ብርቅዬ ሀብታት ናቸው፡፡ እነዚህ መጻሕፍተ ሥርዓት፥ በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ የተሰጣቸውን ትልቅ ቦታ ለመረዳት መጽሐፈ ቅዳሴያችን ውስጥ “ቀኖና” በሚል ርእስ ለጳጳሳት፥ ካህናት እና ዲያቆናት የተሰጠውን ትእዛዝ ማንበብ በቂ ነው፡-

> ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን፤ [መጽሐፈ ኪዳንን] እና ሲኖዶስን፥ ዲድስቅልያንና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት እስከ መጨረሻ ያልተማረ፥ ወደ ሕይወት መንገድ የሚያደርሱ እውነተኞች የሆኑ ሕጎቹንም ሁሉ ያልተማረና ያላወቀ ቢሆን ለአገልግሎት ሥራ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይግባ፡፡ ምን አለብኝ በማለትና በመድፈር ቢገባም [ከማዕረጉ] ይለይ፤ ከቤተ ክርስቲያን ይሰደድ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ፈጽሞ ያስተዋለ ቢሆን [ግን] የአብጥሊሳትን[5] ትእዛዝ አውቆ ለማገልገል ይግባ፡፡[6]

የመጽሐፈ ሲኖዶስ የተወሰኑ ክፍሎችና መጽሐፈ ኪዳን ከግሪክ እና ሶርያ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ በተተረጐሙባቸው ጊዜያት (ከ4ኛው-5ኛው ምእት ዓመት) እጅግ ጥንታውያን ከሚባሉት ቅዳሴያት መካከል ሁለቱ (ቅዳሴ ማርቆስ እና ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ) ወደ አገራችን ገብተዋል፡፡ የግእዙ ቅዳሴ ማርቆስ በግሪክ ቋንቋ ከሚገኘውና በዚሁ ሐዋርያ ስም ከሚጠራው ቅዳሴ ቅድምና እንዳለው የሚጠቁም ጥናት አለ፡፡[7] ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናችን በእነዚህ ጥንታውያን ሀብቶቿ ተጠቃሚ አልሆነችም፡፡ ቅዳሴ ማርቆስን፥ ቅዳሴ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ (የጌታ ወንድም) እና መዓዛ ቅዳሴን ቤተ ክርስቲያናችን ካሳተመቻቸው አሥራ አራት ቅዳሴያት ጋር (በአጠቃላይ አሥራ ሰባት ቅዳሴያት) ሮም የሚገኘው የቫቲካን

[4] መጽሐፈ ሲኖዶስ ውስጥ ከሚገኙት መጻሕፈት መካከል አንዱ “አብጥሊስ ሲኖዶስ” የሚባለው ነው፤ “አብጥሊሳት” የሚለው ቃል የዚህን መጽሐፍ የተለያዩ ክፍሎች ያመለክታል፡፡

[5] ከላይ የተገለጸውን የኅዳግ ማስታወሻ ቍ. 4 ይመልከቱ፡፡

[6] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994 ቍ. 62፣ ገጽ 20፡፡

[7] Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras,* p. 166.

ማተሚያ ቤት እ.አ.አ. በ1945 አሳትሟቸዋል፡፡[8] ሌሎች (ባዕዳን) የእኛ ንብረት ተጠቃሚዎች ሲሆኑ እኛ ግን ለቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ጽሑፋዊ ሀብት እንግዳ መሆናችን በእጅጉ ያስቆጫል፡፡ የአውሮፓ ምሁራን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጥንታውያን መዛግብት ባለቤት መሆኗን አውቀው፥ የግእዝን ቋንቋ ተምረው፥ በዚህ ቋንቋ የሚገኙ ጥንታውያን ምንጮች ላይ ጥናት ሲያካሂዱ እኛ ቁጭ ብለን የእነርሱ ጥናት ተመጽዋቾች መሆን የለብንም፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ቅዱስ ሲኖዶስ ባልታተሙት ስድስት ቅዳሴያት[9] ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ሰፊ ጥናት አድርገውና ከግእዝ ወደ አማርኛ ተርጒመው እንዲያሳትሟቸው መመሪያ ቢሰጥና ተፈጻሚነቱንም ቢከታተል ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከውጭ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተተረጐሙ ሥራዎችን የማድነቅ፥ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱትን ግን የማቃለል አጉል ልማድ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ "መጽሐፈ ሰዓታት ዘግብጽ" በ14ኛው ምእት ዓመት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጒሞ ለተወሰኑ ጊዜያት አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ ይህ መጽሐፍ በሰባቱ የጸሎት ጊዜያት የሚጸለዩ የመዝሙረ ዳዊት ጸሎታትን እና የአዲስ ኪዳን ምንባባትን የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (ዘሰግላ) መጽሐፈ ሰዓታት ዘግብፅን የተካ እና ለሀያ አራቱ ሰዓታት አገልግሎት የሚሰጥ "መጽሐፈ ብርሃን" ወይም "ስብሐታተ መኃልይ"[10] የሚል ርእስ የሰጠውን መጽሐፍ አዘጋጀ፡፡ ነገር ግን ይህ የአባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት በቀላሉ ተቀባይነትን አላገኘም፡፡ በተለይ አንድ የገዳም አበ ምኔት የአባ ጊዮርጊስን ድርሰት ከመጥላቱ የተነሳ መጽሐፉን በመንቀፍ ወደ ገዳሙ እንዳይገባ ይከለክል ነበር፡፡[11] ይህ አሳዛኝ ልምድ እያደገ መጥቶ የአባቶቻችንን ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ከማድነቅ ይልቅ ባዕዳን ለጻፏቸው ጽሑፎች እውቅና እንሰጣለን፡፡ እንዲያውም ሊቃውንቱ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የተለያዩ ቅዳሴያት ደርሰው ስለትሕትና በዝነኞቹ የቤተ

[8] *Missale Ethiopicum.* Rome: Vatican Printing Press, 1945.
[9] ዝርዝራቸውን በምዕራፍ ሦስት ገጽ 231-232 ላይ ይመልከቱ፡፡
[10] EMML, 204, f. 39a.
[11] Getatchew Haile, "On the Writings of Abba Giyorgis Säglawi from Two Unedited Miracles of Mary," *OCP,* Vol. 40 (1982) p. 70.

ክርስቲያን አባቶች ስም (በቅዱስ አትናቴዎስ፥ በቅዱስ ቄርሎስ፥ በቅዱስ ዲዮስቆሮስ ወዘተ.) ስለሰየሟቸው፥ የአባቶቻችንን ሥራዎች ለግብፃውያን ሰጥተን የእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት በሙሉ ከግብፅ እንደመጡ አምነን ተቀምጠናል፡፡ ይህንን የሚያውቀውና በ1950ዎቹ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ውስጥ ያስተምር የነበረው ግብፃዊው ቄስ ማርቆስ ዳውድ፥ ቤተ ክርስቲያናችን አሥራ አራቱን ቅዳሴያት ከኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን እንደተቀበለችና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ይህንኑ እንደሚያምኑ በድፍረት ጽፏል፡፡[12]

እንደዚህ አይነቱን ያለማስረጃ በደፈናው የሚቀርብ መላምት በጥናታዊ ጽሑፎች የምናጋልጥበትና የምናፈርስበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያሏት ሀያ ቅዳሴያት የተደረሱበት ሁኔታና ለድርሰቶቹ ግብአት በመሆን ያገለገሉ ሥነ ጽሑፋዊ ምንጮች በቤተ ክርስቲያናችን ልጆች ሊጠኑ ይገባል፡፡ ከ4ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ከግሪክ (ጽርእ)፥ ሱርስትና ዐረብኛ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተመለሱ በርካታ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ቢኖሩም ሊቃውንቱ አባቶቻችን እነዚህን መጻሕፍት እንደወረዱ አላስቀመጧቸውም፡፡ ሲተረጉሙ እንኳን የራሳቸውን አስተዋጽኦ በመጨመርና ከአገራችን ትውፊት ጋር በማስማማት ትርጉሞቹ ከጥንቶቻቸው (የትርጉሞቹ ምንጭ ከሆኑት) የማይገናኙ እስኪመስሉ ድረስ የተለየ መልክና ቅርጽ ይሰጧቸው ነበር፡፡ እንዲሁም ከውጭ ቋንቋዎች የተተረጐሙትን ቅዳሴያት መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የነገረ መለኮት እሳቤን በግልጽ የሚያሳዩ ቅዳሴያት ደርሰዋል፡፡ ስለዚህ ለአባቶቻችን ሥራዎች እውቅና ልንሰጥና ባስረከቡን ብሔራዊ ሥርዓተ አምልኮ ልንኮራ ይገባል፡፡

ለትሕትና ብለው ስማቸውን ባልገለጹልን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተደረሱት አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴያት፥ በ14ኛው እና 15ኛው ምእት ዓመታት አገራችን ውስጥ የተነሡ የነገረ መለኮት ክርክሮች[13] ውጤት እንደሆኑ በምዕራፍ ሦስት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ቅዳሴያት ከጸሎታተ ቍርባን ገጽታቸው ይልቅ የነገረ መለኮት ይዘታቸው ጎልቶ ይታያል፡፡ በቤተ ክርስያናችን ቅዳሴያት ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነ ጥናት ያደረገው ጀርመናዊው

[12] "Foreword," *The Liturgy of the Ethiopian Church,* trans. Marcos Daoud (London: Kegan Paul, 2005).
[13] Theological controversies.

ሃመርሽሚት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት አስደናቂ የነገረ መለኮት አስተምህሮንና ሥነ ጽሑፋዊ ውበትን እንደያዙ መስክሯል፡፡[14] መጽሐፈ ቅዳሴ የሥርዓተ አምልኮ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያናችን ዶግማ (ትምህርተ ሃይማኖት) ዋነኛ መገለጫ ስለሆነ፥ በውስጡ ያሉት የነገረ መለኮት እሳቤዎች[15] በሊቃውንቱ ሊጠኑና ጥናቶቻቸውም ለሕዝብ ዕይታ ወደ አደባባይ ሊወጡ ይገባል፡፡ “የምናምነውን እንጸልያለን፥ የምንጸልየው የምናምነውን ነው”[16] የሚለው የሥርዓተ አምልኮ ምሁራኑ ብሂል፥ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ፥ ዋነኛ የዶግማዋ ምንጭ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ሥርዓተ ቅዳሴው በተግባር የተገለጸ አሚን (እምነት) ስለሆነ በውስጡ የያዛቸው ምሥጢራዊ ምሳሌያትና ትርጉሞች ከቅዳሴያቱ ጥልቅና አእማድ አስተምህሮዎች (ምሥጢረ ሥላሴ፥ ትምህርተ ሥጋዌ/ተዋሕዶ፥ ነገረ ማርያም፥ ነገረ ምጽአት፥ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ወዘተ.)[17] ጋር ተጠንቶ በቃልም በመጽሐፍም የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን (አማንያን) ሊማሩት ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴንና አገልግሎቱ የሚከናወንባቸውን መጻሕፍት (መጽሐፈ ቅዳሴና መጽሐፈ ግጻዌ) ስናጠና ይህን ብሔራዊ ሥርዓተ አምልኮ በመቅረጽ ታላቅ ሚና በተጫወቱ አባቶቻችን ሥራ እንደነቃለን፡፡ ቅዳሴው በተቀናጀ መልኩ እንዲከናወን ያዘጋጇቸው ትእዛዛት፥[18] ከላይ ከተጠቀሱት መጻሕፍተ ሥርዓትና ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት የመረጧቸው ዝማሬያትና በአገራችን አራት ዓመታዊ ወቅቶች በምድሪቱ የሚታየውን የእግዚአብሔር መግቦት እያደነቁ ያዘጋጁት መጽሐፈ ግጻዌ በኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የሥርዓተ አምልኮ ግንዛቤ[19] እንድንኮራ ያደርገናል፡፡ በአጠቃላይ፥ ከውጭ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ

[14] ጉልበት ያላቸውን የሃመርሽሚት ቃላት ለመጠቀም ያህል፡- “[The Ethiopic Anaphoras] contain a surprising exuberance of theological thought and liturgical poetry.” Hammerschmidt, *Studies in the Ethiopic Anaphoras,* p. 166.

[15] Theological thoughts.

[16] ተቀራራቢው የላቲኑ አገላለጽ፡- *lex orandi est lex credendi* ይላል፡፡

[17] የነገረ መለኮት (theology) ምሁራን በእንግሊዝኛ ሲጽፉ፡- Tridology (Trinitarian theology), Theology of the Incarnation, Mariology, Eschatology, Ecclesiology የሚሉ አርእስት ይሰጧቸዋል፡፡

[18] Rubrics.

[19] Liturgical consciousness.

የተተረጐሙትን የሥርዓተ አምልኮ ምንጮች[20] ከአገራችን ባህል ጋር አስማምቶ በመጠቀም፥ የሥርዓተ ቅዳሴውን ቅደም ተከተል[21] በማሰናዳት፥ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን የጠፉ ዝማሬያትን (ለምሳሌ “ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት” በማለት የሚጀምረው) በመጠበቅ የራሱ የሆነ መለያ ባሕርያት ያሉትን ኢትዮጵያዊ ሥርዓተ አምልኮ አስረክበውን አልፈዋል፡፡ ለአባቶቻችን አስደናቂ ሥራዎች እውቅና መሥጠትና የእነርሱን አሠረ ፍኖት በመከተል በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ ጥልቅ ጥናቶችን ማካሄድ የዚህ ትውልድ ድርሻ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ይትባረከ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ።
ስቡሕኒ ውእቱ፥ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም።

ተፈጸመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳፻፲ወ፪ ዓ.ም.
አመ ፲ወ፪ ለወርኃ ኅዳር ቡሩክ
በመካነ ትምህርት ዘቅድስት ሥላሴ፥ አዲስ አበባ፡፡

[20] Liturgical sources/ writings.
[21] Liturgical structure.

# መፍትሔ ቃላት (የቃላት መፍቻ)[1]

ሊጦን፡- *ሊታኒያ* (λιτανεία) ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን የተለያዩ ልመናዎችን የያዘ ጸሎትን ያመለክታል፤ በብዙ ቍጥር ሊጦናት (litanies) ይባላሉ፡፡

ልኡካን፡- መልእክተኞች፤ በዚህ መጽሐፍ ግን ቃሉ የሚያመለክተው ለቅዳሴ አገልግሎት የተዘጋጁ ካህናትንና ዲያቆናትን ነው፡፡

ሐዋርያዊ ሕግጋት፡- ከ360-380 ዓ.እ. እንደተደረሰ የሚነገርለት የሥርዓተ አምልኮ መድበል፤ በውስጡ ስምንት መጻሕፍተ ሥርዓትንና የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ የሚያስረዳ አኰቴተ ቍርባን (Clementine Liturgy) የያዘ ሲሆን በእንግሊዝኛ Apostolic Constitutions ይባላል፡፡

ሐዋርያዊ ትውፊት፡- በሦስተኛው ምእት ዓመት የተደረሰ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት (Apostolic Tradition):: የግእዙ ትርጕም፥ "ትእዛዝ ሲኖዶስ" በመባል የሚታወቀው የመጽሐፈ ሲኖዶስ ክፍል ውስጥ ይገኛል፡፡

ሐዳፌ ነፍስ፡- "ነፍስን የምታሻግር" ማለት ነው፡፡ በሥርዓተ ቅዳሴ አገላለጽ ግን ቅዱስ ቍርባንን ከመቀበል በኋላ ያለውን የምስጋና ክፍል ያመለክታል፡፡

መስተብቍዕ፡- የልመና ጸሎት (intercessory prayer).

መንበር፡- የቅዳሴው መሥዋዕት የሚቀርብበት ምሥዋዕ/መሠዊያ (altar)፤ "ቀዊሞ ቅድመ ምሥዋዕ - ከመሠዊያው ፊት ቁሞ"[2] እንዲል መጽሐፈ ቅዳሴ፡፡ ታቦቱ የሚቀመጠው መንበሩ ላይ ስለሆነ "መንበረ ታቦት" ተብሎም ይጠራል፡፡

መንጦላዕት፡- የቤተ ክርስቲያንን ውስጠኛ ክፍል (መቅደስ/ ቅድስተ ቅዱሳን) የሚሸፍን መጋረጃ (chancel/veil).

መድፍነ ኑፋቄያት[3]፡- "መዳን በዕውቀት ነው" የሚሉ የኖስቲኮችን ኑፋቄ (የክህደት ትምህርት) በማውገዝ የተጻፉ የቅዱስ ሄሬኔዎስ መጻሕፍት (Against Heresies/ *Adversus haereses*).

መጻሕፍተ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን፡- የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ አምልኮ ለማከናወን የሚያገለግሉ መጻሕፍት (Church orders).

---

[1] ይህ መፍትሔ ቃላት የተዘጋጀው በዚህ መጽሐፍ ለተጠቀሱት የነገረ መለኮት ቃላት እና የሥርዓተ አምልኮ ስያሜያት (liturgical terminologies) አጭር ማብራሪያ ለመስጠት ነው፤ ከቃላቱ ጋር ለማይተዋወቁ አንባብያን እገዛ ከማድረጉ በተጨማሪ መጽሐፉን በተሻለ መልኩ ተነባቢ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡

[2] መጽሐፈ ቅዳሴ፤ 1994፣ ቁ. 151፣ ገጽ. 59.

[3] ይህን ስያሜ የጠቆመኝ መምህር በአማን ነጸረ ነው፡፡

መጽሐፈ ሲኖዶስ፡- በ5ኛው ምእት ዓመት ከግሪክ ወደ ግእዝ የተረጐሙ (ትእዛዝ ሲኖዶስ፥ አብጥሊስ፥ ሥርዓተ ጽዮን ወዘተ.) የተባሉ ክፍሎችንና ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተመለሱ የተለያዩ ጉባዔያት ቀኖናትን ሰብስቦ የያዘ መድበል፡፡

መጽሐፈ ኪዳን፡- በ5ኛው ምእት ዓመት ሶርያ ውስጥ እንደተደረሰ የሚነገርለትና ወደ ግእዝ የተተረጐመ መጽሐፈ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን (*Testamentum Domini/ The Testament of our Lord*)፡፡ "ሰባቱ ኪዳናት"[4] በመባል የሚታወቁት ጸሎታት የተወሰዱት ከዚህ መጽሐፍ ነው፡፡

መጽሐፈ ግጻዌ፡- በቅዳሴና በማኅሌት ለሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥቅስ ማውጫ (lectionary).

መጾር፡- ለቡራኬ የሚያገለግል ትልቅ መስቀል መያዣ (መሸከሚያ)፤ በቅዳሴ ሰዓት የመጾር መስቀል የሚይዘው ሠራዒው ዲያቆን ነው፡፡

ማኅፈድ (ለብዙ "ማኅፈዳት")፡- በቅዳሴ ሰዓት ኅብስቱ የሚሸፈንበትና ጌታችን የተገነዘበት ንጹሕ በፍታ (ማቴ. 27፥59) ወይም የተልባ እግር ልብስ (ዮሐ. 19፥40) ምሳሌ፡፡

ምእት ዓመት፡- አንድ መቶ ዓመታት (Century).

ሠለስቱ ቅዳስያት፡- "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው . . ." የሚለው ዝማሬ፡፡ በግሪኩ *Trisagion* ይባላል፤ ሦስት ጊዜ ቅዱስ (thrice holy) ማለት ነው፡፡

ሠራዒ ካህን፡- "አሐዱ አብ . . ." ብሎ የሚቀድሰውና ቅዳሴውን የሚመራው ካህን (celebrant)፤ በተጨማሪ "ገባሬ ሠናይ ካህን" ይባላል፡፡

ሠራዒ ዲያቆን፡- የመጾር መስቀል ይዞ "ተንሥኡ፥ ጸልዩ" እያለ ምእመናን በንቃት የቅዳሴው ተሳታፊ እንዲሆኑ ትእዛዛትን የሚያስተላልፈው ዲያቆን፤ "ገባሬ ሠናይ ዲያቆን" ተብሎም ይጠራል፡፡

ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ፡- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን ባርኮና ቈርሶ "እንካችሁ፥ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው"፤ ጽዋውንም አመስግኖ "ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" በማለት ምሥጢረ ቍርባንን የመሠረተባቸው ቃላት፡፡ ሠራዒው ካህን እነዚህን ቃላት የሚጠቅስበት የአኰቴተ ቍርባን ክፍል፤ Institution Narrative (ሠራዔ ቃል ዘእግዚእነ) ይባላል፡፡

[4] ዝርዝራቸውን ከላይ ምዕራፍ 3፣ ገጽ 175-176 ላይ ይመልከቱ፡፡

ሡርሖተ ሕዝብ፡- "ሡርሐ"/ አሰናበተ ከሚለው ግስ የተገኘ፤[5] የቅዳሴው መጨረሻ ላይ የሚከናወን ምእመናንን የማሰናበት *ሥርዓት* (Dismissal).

ሱርስት፡- የሶርያ ቋንቋ (Syriac).

ቀኖና፡- የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መንፈሳዊ ሕይወት የሚመራበት ሕግ፥ *ሥርዓት* (Canon law).

ቊርባን፡- *ቊርባኖ* (*Qurbano*) ከሚለው የሱርስት ቃል የተወሰደ፤ *መሥዋዕት* ሆኖ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ፡፡ የጌታችን *ሥጋ*ና ደም ቅዱስ ቊርባን (Holy Eucharist) ይባላል፡፡

ቃለ ምዕዳን፡- ምክር አዘል መልእክት፤ ምዕደ = መከረ ከሚለው ግስ የተወሰደ፡፡

ቅብጥ፡- ግብፅ/ኮፕት ፤ (ኮፕቲክ/ Coptic) የጥንት ግብፃውያን ቋንቋ፡፡

ቅዳሴ ተሰጥዎ፡- የቅዳሴው ተሳታፊ የሆኑ ምእመናን ለዲያቆኑ ትእዛዛትና ለካህኑ ቡራኬያት በዜማ የሚሰጡት መልስ፡፡

ቅድሳት ለቅዱሳን፡- *ሠራዒ*ው ካህን "ቅድሳት" የተባለው የጌታ *ሥጋ*ና ደም ለአማንያን (ለተቀደሱ ሰዎች) የተዘ*ጋ*ጀ መሆኑን እያወጀ ምእመናንን ወደ ቅዱስ ቊርባን የሚጠራበት ቃላት፡፡ የላቲኑ አቻ *Sancta sanctis* ወይም በእንግሊዝኛ Holy things for the holy ones ይላል፡፡

ተዝካረ ቅዱሳን ወጸሎት በእንተ እለ ኖሙ፡- በዐጸደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳን የሚዘከሩበት፥ በሕይወት ላሉና ላረፉት የቤተ ክርስቲያን አባላት የምልጃ ጸሎት የሚቀርብበት የአኰቴተ ቊርባን ክፍል (*Diptychs/* intercessions).

ተ*ጋ*ብኦተ ቊርባን፡- አማንያን (ምእመናን) ቅዱስ ቊርባንን ለመቀበል የሚያደርጉት ጉባኤ (ተ*ጋ*ብኦ፥ ኅብረት)፤ በእንግሊዝኛ Eucharistic synaxis ይባላል፡፡

ታቦት፡- የጽላት ማኅደር (ማስቀመጫ)፤ ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት፥ በቅዳሴ ሰዓት ኅብስቱና ወይኑ የሚከብርበት (የጌታ *ሥጋ*ና ደም የሚቀርብበት) ጽላት በዘልማድ ታቦት ይባላል፡፡

ትምህርተ ንኡስ ክርስቲያን፡- ለመጠመቅ በዝግጅት ላይ ያሉ ሰዎች ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚማሩት ትምህርት፤ በግሪኩ *ሚስታጎጊያ* (Μυσταγωγία - interpretation of mysteries) ይባላል፡፡ "ትምህርተ ኅቡኣት" የሚል ርእስ የተሰጠው የመጽሐፈ ኪዳን ክፍል ለጥምቀት በዝግጅት ላይ ላሉ ሰዎች ማስተማሪያ እንዲሆን የተዘ*ጋ*ጀ ነበር፡፡

[5] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ* ፣ ገጽ 677፡፡

ትእዛዛት፡- ሠራዒው ካህን ሥርዓተ ቅዳሴውን እንዴት እንደሚያከናውን የሚያስረዱ በመጽሐፈ ቅዳሴ የሚገኙ አጫጭር መግለጫዎች (rubrics).

ንኡሰ ክርስቲያን፡- በጥምቀት የማኅበረ ምእመናን (ቤተ ክርስቲያን) አባላት ለመሆን በዝግጅት ላይ ያሉ ሰዎች (Catechumens).

ንዋያተ ቅድሳት፡- "ቅድሳት" የተባሉት የጌታ ሥጋና ደም የሚቀርብባቸው፥ በቅብዓ ሜሮን የከበሩና የተቀደሱ ዕቃዎች (ፃሕል፥ ጽዋ፥ ዕርፈ መስቀል ወዘተ.)፡፡ በእንግሊዝኛ፡- Sacred Vessels/ Ecclesiastical Objects ይባላሉ፡፡

ንፍቅ ካህን፡- በቅዳሴ ሠራዒውን (ቀዳሹን ካህን) የሚራዳ ካህን (ቄስ/ ቀሲስ)፡፡

ንፍቅ ዲያቆን፡- በቅዳሴ ጧፍ ይዞ ዑደቱን የሚመራ ዲያቆን፡፡

አመክንዮ ዘሐዋርያት፡- በሐዋርያት ስም የተሰየመና Apostolic Constitutions ውስጥ የሚገኝ የእምነት መግለጫ (Apostolic Creed).

አስተናጽሖ፡- ከሥርዓተ ቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ ፃሕሉንና ጽዋውን በጥንቃቄ የማጠብ ሥርዓት (ablution)፤ "እምድኅረ ተፈጸመ አስተናጽሖ"[6] እንዲል መጽሐፈ ቅዳሴ፡፡

አበ ምኔት፡- የገዳም አለቃ፤ ታላቅ አባት (Abbot).

አብያተ ክርስቲያን፡- "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው በብዙ ቍጥር ሲነገር "አብያተ ክርስቲያን" ይሆናል፡፡ በልምድ ግን "አብያተ ክርስቲያናት" ሲባል እንሰማለን፡፡[7]

አንብሮ እድ፡- እጅ መጫን (ማስቀመጥ)፤ በሁሉም የቤተ ክርስቲያናችን ጸሎታተ ቍርባን (ቅዳሴያት) መጨረሻ ላይ "አንብሮ እድ" የሚል የጸሎት ክፍል ይገኛል፡፡

አኰቴተ ቍርባን፡- የቍርባን ምስጋና፤ ጸሎተ ቍርባን (Eucharistic prayer/ anaphora).

አውሎግያ፡- አኰቴት (የተባረከ ኅብስት)፤ *ኤቭሎጊያ* (*evlogia*) ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ፡፡

አውሥኦ፡- በሠራዒው ካህንና በምእመናን መካከል የሚደረግ ምልልስ (Dailogue)፤ የአኰቴተ ቍርባን መጀመሪያ (መክፈቻ)፡፡

[6] መጽሐፈ ቅዳሴ፡ 1994፣ ቁ. 143፣ ገጽ. 116.

[7] ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው መጠሪያ ቃል ውስጥ "ቤት" የሚለውን "አብያት" ብለን ካበዛን በኋላ "ክርስቲያናት" ማለት እንደማያስፈልግ አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል ብዙ ቍጥር "አብያተ ክርስቲያን" ነው፡፡

አዕርጎተ ዕጣን፡- ዕጣንን የማሳረግ ሥርዓት (Offering/ raising of incense).

አጋፔ፡- Αγάπη (ኢጋፒ) ከሚለውና "ፍቅር" የሚል ትርጒም ካለው የግሪክ ቃል የተወሰደ፤ የፍቅር ማዕድ (love feast) ማለት ነው፡፡

አግብኦተ ግብር፡- የቅዳሴው መጀመሪያ ላይ ኅብስቱና ወይኑ ከቤተ ልሔም ወደ መቅደስ ገብተው መንበሩ ላይ የሚቀርቡበት ሥርዓት (Offering):: በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ኅብስቱና ወይኑ *postophorion* የተባለ የማዘጋጃ ክፍል ውስጥ ቆይተው ወደ መንበሩ የሚወሰዱት ንኡሰ ክርስቲያን ከተሰናበቱ በኋላ (አኰቴተቍርባኑ) የሚጀምርበት ቦታ ላይ ነበር፡፡

ኤክሊሲያ ግሪክ፡- *ἐκκλησία*/ ecclēsia፤ የአማንያን ኅብረት፥ ጉባኤ ምእመናን (ቤተክርስቲያን) ማለት ነው፡፡ መጽሐፈ ድጓ "አቅሌስያ" የሚለውን ቃል እንደሚጠቅስ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጠቊመዋል፡፡[8]

ኪርያላይሶን፡- ጌታ ሆይ ማረኝ/ን፤ በግሪክ ቋንቋ Κύριος (ኪሪዮስ) "ጌታ" ማለት ሲሆን፥ Κύριε ἐλέησόν (ኪሪኤ ኤሌኢሶን) ደግሞ "ጌታ ሆይ ማረኝ/ ማረን" ማለት ነው፡፡

ዐቃብያነ እምነት፡- የእምነት ጠባቂዎች/ጠበቆች (apologists).

ዑደት፡- የቅዳሴው ልኡካን (ካህናቱና ዲያቆናቱ) መንበረ ታቦቱን እና የቤተ ክርስቲያኑን አራት ማዕዘናት የሚዞሩበት ሥርዓት (procession).

ዓስበ ዲያቆን፡- "*ዴስፖቲኮን*" የሚለውን ይመልከቱ፡፡

ዕርፈ መስቀል፡- የማንኪያ ቅርጽ ያለውና መያዣው ላይ የመስቀል ምልክት የሚደረግበት የክርስቶስ ደም ማቀበያ (cross-spoon)፤ ከንዋያተ ቅድሳት (ቅዱሳት ንዋያት) አንዱ ነው፡፡

ዝማሬ ሱራፌል፡- "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች" (ት. ኢሳ. 6፥3) የሚለው የቅዱሳን መላእክት ዝማሬ፡፡ በላቲን ቋንቋ *Sanctus* ይባላል፤ አኰቴተ ቍርባን የተሰኘው የቅዳሴ ሦስተኛ ክፍል ውስጥ ይገኛል፡፡

ዝክረ ሞቱ ወትንሣኤሁ ለእግዚእነ፡- ጌታ ሥርዓተ ቍርባንን በሠራበት ምሽት (ምሴተ ኀሙስ) ለደቀ መዛሙርቱ "ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" (ሉቃ. 22፥ 19) እንዳላቸው የጌታን ሕማም፥ ሞትና ትንሣኤ የምናስብበት የአኰቴተ ቍርባን ክፍል ነው፡፡ *አናምኒሲ* (Ανάμνηση) ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደው

[8] *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ* ፥ ገጽ 238፡፡

ስያሜ (*Anamnesis*)= remembrance/ recollection (ተዝካር/ መታሰቢያ) የሚል ትርጉም አለው፡፡

ዲዳኬ፡- *ዲዳኪ* (Διδαχὴ) ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ሥልጠና (ትምህርት) ማለት ነው፡፡ በመጀመሪያው ምእት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የተደረሰ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሥርዓት ነው፤ መግቢያው ላይ "ትምህርተ ሐዋርያት" የሚል ርእስ ተሰጥቶታል፡፡

ዲድስቅልያ፡- የመጀመሪያዎቹን የሐዋርያዊ ሕግጋት (Apostolic Constitutions) ስድስት መጻሕፍት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ፤ የግእዙ ዲድስቅልያ ከዐረብኛው *Didascalia* የተተረጐመ ሲሆን 43 ምዕራፎች አሉት፡፡

*ዲፕቲክስ*፡- በግሪኩ *ዲፕቲኮን* (*Diptichon*) ከሚለው ቃል የተገኘ ነው፡፡ (*ዲፕቲክስ* - *Diptychs*)፥ መሃል ላይ የተያያዙና የሚታጠፉ ሁለት ሰሌዳዎችን ያመለክታል። በክርስትና የመካከለኛው ዘመን *Diptychs* የሚባሉ ያረፉ ቅዱሳን እና በሕይወት ያሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስሞችን የያዙ ሰሌዳዎች ነበሩ፡፡ ታላቁ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም "ዲብዲቆን" የሚለው ቃል መሠረቱ ጽርእ (ግሪክ) መሆኑን ጠቅሰው "መጽሐፈ ተዝካር፥ የሙታን ወይም የሕያዋን ስሞች የሚጻፍበት ሰሌዳ" በማለት ፈትተውታል፡፡ [9] በአሁኑ ሰዓት *Diptychs* የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስም መጻፊያ ሰሌዳዎችን ሳይሆን በሕይወት ላሉና ላረፉ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚደረጉ የምልጃ ጸሎቶችን ነው፡፡

*ዴስፖቲኮን*፡- *Despotikon* የሚለው የግሪክ ቃል የጌታ ሥጋ ማለት ነው፤ የጌታ ሥጋ ወደመሆን የተለወጠው፥ የመስቀል ምልክት ያለበትና በአርአያ ኅብስት የምናየው የመሀሉ ክፍል *ዴስፖቲኮን* ይባላል፡፡ ነገር ግን በተርጓሚ ስሕተት "ዓስበ ዲያቆን" ተብሎ "ለዲያቆን የሚገባ" የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

ድርሳን፡- ትምህርተ ሃይማኖትን የሚመለከት ጽሑፍ (homily/theological treatise).

ድርገት፡- ደርገ = አበረ፥ አንድ ሆነ ከሚለው የግእዝ ግስ የተወሰደ ቃል፡፡ በሥርዓተ ቅዳሴ ካህናቱና ዲያቆናቱ የጌታችንን ሥጋና ደም ለምእመናን ለማቀበል ከመቅደስ ወደ ቅድስት የሚወርዱበት ሥርዓት "ድርገት" ይባላል፡፡

*ዶክሶሎጂ*፡- Δόξα (ዶክሳ = ክብር፥ ምስጋና) እና λόγια (ሎጊያ= ቃላት፥ ንግግር) ከሚሉ ሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘው *ዶክሶሎጂ* (*Doxology*) ለእግዚአብሔር ክብር የሚቀርብ አጭር ምስጋናን ያመለክታል፡፡

---

[9] *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ* ፥ ገጽ 335፡፡

ጵርስፎራ፡- በግሪኩ *ፕሮስፎራ* (*Prosfora*) ወይም *ፕሮስፎሮን* (*Prosforon*)[10] ከሚሉት ቃላት የተወሰደው ይህ ቃል፥ ኅብስት (ቍርባን) የሚል ትርጉም አለው።

ጸሎተ መባእ፡- በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለቍርባን የሚሆነውን ኅብስት ለሚያመጡ ምእመናን የሚጸለይ ጸሎት፤ በአሁኑ ሰዓት ዐሥራታቸውን (የደመወዛቸውን አንድ ዐሥረኛ) ለቤተ ክርስቲያን ለሚሰጡ እና የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳትን (ቅዱሳት ንዋያትን) ለሚያመጡ ምእመናን የሚጸለይ ጸሎት ነው፡፡

ጸባዖት፡- በዕብራይስጥ *Tzevaot* ወይም *Saba-oth* የሚለው ቃል የሰማይ ሠራዊትን ያመለክታል፡፡ በዚህ ቋንቋ ለልዑል እግዚአብሔር ከተሰጡ እጅግ የከበሩ ስሞች መካከል "የሠራዊት ጌታ - Lord of Hosts" (ት.ኢሳ 6፥3) የሚል ነው፡፡

ጽላት (ጽሌ)፡- ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት፥ በቅዳሴ ሰዓት ኅብስቱን የያዘው ፃሕል እና ጽዋው የሚቀመጥበት የመሥዋዕቱ ማከበሪያ፡፡

ጽርእ፡- ግሪክ፤ የአገሩና የቋንቋው ስም፡፡

ጽንሐሕ (መጸንሕሕ)፡- ጥና (ራእ. 8፥3)፤ ዕጣን የሚቃጠልበት የፍሕም ማስቀመጫ፡፡ "ጽንሐሕ" የሚለው የግእዝ ቃል፥ "ማዕጠንት"የተሰኘ አቻ ቃልም አለው። "ማዕጠንት ዘወርቅ አንተ ዖርኪ ፍሕመ እሳት - የእሳትን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ጥና"[11] እንዲል መጽሐፈ ቅዳሴ።

ጽዋ፡- በግእዙ "ጽዋዕ"፤ ከመለወጡ በፊት ወይኑ፥ ከተለወጠ በኋላ ደመ ክርስቶስ የሚቀርብበት ቅዱስ ንዋይ (ዕቃ)፡፡

ጽዋዔ መንፈስ ቅዱስ፡- ሠራዒው ካህን መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና ወይኑ ላይ ወርዶ የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋ*ና ደም ያደርጋቸው ዘንድ የሚጠይቅበት ጸሎት፤ *ኤፒክሊሲ* (επίκλιση) ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደው *Epiclesis* "invocation of the Holy Spirit" የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

ፃሕል፡- ከወርቅ፥ ከብር፥ ከነሐስ ወይም ከብረት የሚሠራና ከመለወጡ በፊት ኅብስቱ፥ ከተለወጠ በኋላ *ሥጋ*ው የሚቀመጥበት ንዋይ ቅዱስ (የተቀደሰ ዕቃ)፡፡

ፍሬ ቅዳሴ፡- ኅብስቱና ወይኑ የጌታ *ሥጋ*ና ደም ወደመሆን የሚለወጥበት የቅዳሴው ሦስተኛውና ዋነኛው ክፍል፡፡

---

[10] See Foteny Economon Ninos, *The Divine Liturgy: Analysis, Exegesis and Commentary* (Minneapolis, MN: Light and Life Publishing Company: 1987) 176.
[11] "*ሥርዓተ ቅዳሴ*" *መጽሐፈ ቅዳሴ*፡ 1994፣ ቍ. 122፣ ገጽ. 51.

# ዋቢ መጻሕፍት

## የግእዝ እና የአማርኛ መጻሕፍት ዝርዝር

## Primary Sources


ሁጎ ድዌንሲንግ/ Hugo Duensing (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ *[ሐዋርያዊ ትውፊት ዘአቡሊዲስ]*፤ *Der Aethiopische Text der kirchenordnung des Hippolyt*. Göttingen: Vandenhoeck and Ruprecht, 1946.

*ሃይማኖተ አበው* ፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1986 ዓ.ም.

ሆርነር/ G. Horner (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ *[ቀኖናተ ሐዋርያት]*፤ *The Statutes of the Apostles or Canones Ecclesiastici*]. London: Williams and Norgate, 1904.

*መልክዐ ሕማማተ መስቀል፥ መልክዐ መድኃኔ ዓለም፥ መልክዐ ቍርባን፥ ወመልክዐ እግዚአብሔር አብ*፤ [የታተመበት ከተማ ያልተጠቀሰ]፡ ቀይ ባሕር ማተሚያ ቤት፡ 1977 ዓ.ም.

መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት/ አርታዒ)፤ *መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ* ፤ አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ 1951 ዓ.ም.

*መዝሙረ ዳዊት፡ ማኅሌተ ጽጌ፥ ሰቆቃወ ድንግል በልሳነ ግዕዝ*፤ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.

*መጻሕፍተ መነኮሳት፡- ማር ይስሐቅ፥ ፊልክስዩስ (ገብረ ክርስቶስ)፥ አረጋዊ መንፈሳዊ*፤ አዲስ አበባ፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1988 ዓ.ም.

*መጽሐፈ ሰዓታት ምስለ ኵሉ ጸዋትዊሁ ወባሕረ ሐሳብ፤ አሥመራ*፡ ኮከበ ጽባሕ ቤተ ማኅተም፡ 1975 ዓ.ም.

*[መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊት ወዘመዓልት ዘሰመዮ አባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ብርሃን አው ስብሐታተ መኃልይ]*. EMML*, Addis Ababa and the Monastic Manuscript Library, Collegeville*. EMML,Project Numbers 204 and 4493.

*መጽሐፈ ሰዓታት [ዘግብፅ]*፤ ሮም፡ ቫቲካን ማተሚያ ቤት: 1944 ዓ.ም. (1952 European Calendar).

መጽሐፈ ስንክሳር፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ 1994 ዓ.ም.

*መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝ እና በአማርኛ ከነምልክቱ*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡ 1994 እና 2000 ዓ.ም.

*መጽሐፈ ቅዳሴ፡ ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው*፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡ 1988 ዓ.ም.

*[መጽሐፈ ቅዳሴ ዘኢትዮጵያ]*፤ *Missale Ethiopicum*፤ ሮም፡ ቫቲካን ማተሚያ ቤት: 1937 ዓ.ም. (1945 European Calendar).

*መጽሐፈ ክርስትና*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማቲሚያ ድርጅት፡ 1994 ዓ.ም.

*መጽሐፈ ዚቅ ወመዝሙር*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.

*መጽሐፈ ግጻዌ ከነምልክቱ ዘይትነበብ እምዓመት እስከ ዓመት ወዘሰናብት ዘየንብር ምስለ መዝሙራት*፤ አሳታሚ፡- መምህር አባ ጥዑመ ልሳን ኪዳነ ማርያም፤ አዲስ አበባ፡ አክሱም ማተሚያ ቤት፡ 1994 ዓ.ም.

*ሥርዓተ ሰሙነ ሕማማት ወሰላምታ ከነምልክቱ*፤ አሳታሚ፡- መምህር አባ ጥዑመ ልሳን ኪዳነ ማርያም፤ አዲስ አበባ፡ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ: 1996 ዓ.ም.

ሮበርት ባይሎ/ Robert Beylot (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ *[መጽሐፈ ኪዳን]*፤ *Testamentum domini éthiopien*. Louvain: Peeters, 1984.

*ሰዓታት ዘሌሊት ወዘነግህ* ፤ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1989 ዓ.ም

*ቅዳሴ ማርያም አባ ሕርያቆስ የደረሰው፡ ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደ ተረጎሙት* ፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፡ 1983 ዓ.ም.

*ተአምረ ማርያም* ፤ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ 1988 ዓ.ም.

*ተአምረ ማርያም ግዕዝ እና አማርኛ* ፤ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1984 ዓ.ም.

ተስፋ ጽዮን (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ *[ሐዲስ ኪዳን ወመጽሐፈ ቅዳሴ]*፤ *Testamentum Novum [...] Missale cum benediction incensi, cerae [...] quae omnia Fr. Petrus Ethyops asuxilio piorum sedente Paulo III pont. Max. et Claudio illius regni imperatore imprimis curvit [Romae] anno sal.* MDXLVIII [1548] fols. 158-67.

አሌሳንድሮ ባውሲ/ Alessandro Bausi (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤*[መጽሐፈ ሲኖዶስ]*፤ *Il Senodos Etiopico: Canoni pseudoapostolici: Canoni dopo l'Ascensione, Canoni di Simone Cananeo, Canoni Apostolici, Lettera di Pietro,* CSCO, Vol. 552, Scriptores Aethiopici, Tom. 101. Ed. Alessandro Bausi. Louvain: Aedibus Peeters, 1995.

____________________፤*[ሐዋርያዊ ትውፊት ሐዲስ]*፤ *LA NUOVA VERSIONE ETIOPICA DELLA TRADITIO APOSTOLICA: EDIZIONE E TRADUZIONE PRELIMINARE*. Studia Ephemeridis Augustinianum. Vol. 125 (2011) pp. 19-69.

ኤንሪኮ ቼሩሊ/ Enrico Cerulli (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ [ፍካሬ መለኮት]፤ *Scritti teologici etiopici dei secoli XVI-XVII*: *Tre opuscoli dei Mikaeliti,* Vol. 1. Ed. Enrico Cerulli. Vatican: Biblioteca Apostolica Vaticana, 1958. PP. 3-63.

አስቫልዶ ሬይነሪ/ Osvaldo Raineri (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ [*ቅዳሴ ማርያም ዘጎርጎርዮስ*]፤ *L'anafora etiopica inedita di Maria*. Miscellanae Bibliothecae Apostolicae Vaticanae. Vol. VII (2000) pp. 337-354.

ኩርት ዌንድት/ Kurt Wendt (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ [*መጽሐፈ ሚላድ እና መጽሐፈ ሥላሴ ዘአፄ ዘርአ ያዕቆብ*]፤ *Das Maṣḥafa Milād (Liber Nativitatis) und Maṣḥafa Sellāsē (Liber Trinitatis) Des Kaisers Zar'a Yā'qob*. CSCO, Vol. 235, Tom 43. Scriptores Aethiopici. Louvain: 1963.

ኮንቲ ሮሲኒ/ Conti Rossini (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤*[መጽሐፈ አክሱም]*፤ *Book of Aksum*. CSCO, Tom. 54. Louvain: 1909.

ኮንቲ ሮሲኒ እና ሪሲ/ Conti Rossini and L. Ricci (ተርጓምያን ወአርታዕያን)፤ [*መጽሐፈ ብርሃን ዘአፄ ዘርአ ያዕቆብ*]፤ *Il Libro Della Luce Del Negus Zar'a Yā'qob: Maṣḥafa Berhān*. CSCO, Vol. 261, Tom. 51. Scriptores Aethiopici.. Louvain: 1965.

*ወንጌል ቅዱስ ዘእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘዜነዉ ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ዮሐንስ፡ ከቀድሞ አባቶቻችን ጀምሮ ቃል ለቃል ሲነገር የመጣው ንባቡና ትርጓሜው፤ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደ ተረጐሙት* ፤ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1985 ዓ.ም.

*ውዳሴ ማርያም ቅዱስ ኤፍሬም የደረሰው፡ ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፡ 1983 ዓ.ም.

ዕዝራ ሐዲስ (ሊቀ ሊቃውንት፤ አዘጋጅና አሳታሚ)፤ "ተረፈ ቄርሎስ ምዕራፍ ፲፰፡ ድርሳን ዘጵርቅሎስ [ኤራቅሊስ] ዘሀገረ ቂዝቆስ ዘደረሰ በቈስጠንጢኑ [በቊስጥንጥንያ]"፤ *ድርሳነ ቄርሎስ ወጸላድዮስ ምስለ ተረፈ ቄርሎስ፡ ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲነበብና ሲተረጐም የመጣው ንባቡና ትርጓሜው በአንድምታ* (ጎንደር፡ [ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ]፡ 2008 ዓ.ም.) ገጽ 735-745.

*የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1988 ዓ.ም.

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ*፤ ሎስ አንጀለስ፡ ፊደል ማተሚያ ቤት፡ 1995 ዓ.ም.

ያዕቆብ በየነ (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ [*መጽሐፈ ምሥጢር ዘአባ ጊዮርጊስ ዘሰግላ*]፤ *Il Libro del Mistero: Maṣḥafa Mesṭir* (Parte Prima [Part One]). CSCO, Vol. 515, Tom. 89. Scriptores Aethiopici. Louvain: Aedibus E. Peeters, 1990.

*ድርሳናት ዘበዓላት ዐበይት ዘደረሰ ርቱዓ ሃይማኖት*፤ EMML, *Addis Ababa and the Monastic Manuscript Library, Collegeville*. EMML, Project Numbers 2375 and 7028.

*ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ*፤ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.

ጀራርድ ኮሊን/ Gérard Colin (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤*[ገድለ ጊዮርጊስ ዘሰግላ]*፤ *Vie de Georges de Saglā*. CSCO, Vol. 492*,* Tom, 81. Scriptores Aethiopici. Louvain: Aedibus E. Peeters, 1987.

________________________________፤[*ስንክሳር ዘጥር*]፤ *Le synaxaire éthiopien*. Ed. Colin, Gérard. PO*,* Tome 45 (1990) pp. 214-230.

ጉሬር እና ግሬቦ/ L. Guerrier and S. Grébaut (ተርጓምያን ወአርታዕያን)፤ *[መጽሐፈ ኪዳን ዘገሊላ]*፤ *Le Testament en Galilée de Notre-Seigneur Jésus Christ*. PO*,* Vol. 9. Paris: Firmin-Didot, 1913. PP. 177-232.

ጌታቸው ኃይሌ (ተርጓሚ ወአርታዒ)፤ [*ጦማር ዘአፄ ዘርአ ያዕቆብ በእንተ ክብረ ዮሐንስ ወንጌላዊ*]፤ The Homily of Zär'a Yaʿəqob in Honour of St. John the Evangelist. *OC*. Vol. 67 (1983) pp. 144-166.

________________________፤[*ድርሳን ዘብፁዕ ኤጲስ ቆጶስ አባ ኤልያስ ዘደረሰ በእንተ ብፁዕ መነኮስ አባ መጣዕ ዘውእቱ ሊባኖስ ብእሴ እግዚአብሔር*]፤ *The Homily of Abba Eləyas, Bishop of Aksum on Mäṭṭa*. Analecta Bolladiana, Vol. 108/1-2 (1990) pp. 29-47.

________________________፤*ደቂቀ እስጢፋኖስ፡ በሕግ አምላክ*፤ ኮሌጅቪል፡ ሚኒሶታ፡ 1996 ዓ.ም.

________________________፤*የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፡ ኦሮሞችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር*፤ ኮሌጅቪል፡ ሚኒሶታ፡ 1995 ዓ.ም.

*ጸሎተ ዕጣን* ፤ አዲስ አባባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1987 ዓ.ም.

*ጾመ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ* ፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ አጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1994 ዓ.ም.

## Secondary Sources

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፤ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፤ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ 1963 ዓ.ም.

ሀብተሚካኤል ኪዳነ (ዶ/ር)፤ *ታሪኻዊ ኣመጻጽኣን ምዕባለን ናይ "ሥርዓተ ቅዳሴ ግዕዝ"*፤ ኣሥመራ፡ ፍራንሲስካና ማተሚያ ቤት፡ 1997/98 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 2005).

*መጽሐፈ ጥበብ ዘአስተጋብእዎ አኀው ማኅበረ ቢዘን* ፤ አሥመራ፡ ማኅተመ ኮከበ ጽባሕ፡ 1969 ዓ.ም.

ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን)፤ *መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት፡ ሁለተኛ እትም*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1988 ዓ.ም.

ስቡሕ ዳምጤ፤ *ሺህ ዓመትና ሐሳዊ መሲሕ*፤ አዲስ አበባ፡ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት፡ 1997 ዓ.ም.

አባ መልከጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፤ *የቅዳሴያችን ይዘት*፤ ቶሮንቶ፡ ጣና ማተሚያ ቤት፡ 2003 ዓ.ም.

አባ ቄርሎስ (ሊቀ ጳጳስ)፤ *ፍሬ ሃይማኖት*፤ አሥመራ፡ ኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ማተሚያ ቤት፡ 1976 ዓ.ም.

አባ ገብርኤል (ሊቀ ጳጳስ)፤ *ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊ*፡ ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ፤ አዲስ አበባ፡ አዲስ አሳታሚዎች፡ 1993 ዓ.ም.

አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1991 ዓ.ም.

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፤ *መድሎተ አሚን፡ የሃይማኖት ሚዛን፡* ሁለተኛ እትም፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1990 ዓ.ም.

አግዛቸው ተፈራ፤ *ጥላና አካል*፤ አዲስ አበባ፡ [የማተሚያ ቤቱ ስም ያልተጠቀሰ] 1995 ዓ.ም.

ኤልያስ አብርሃ (ንቡረ እድ)፤ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ጸዋትወ ዜማ"፥ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም (2000)*፤ አዲስ አበባ፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡ 2000 ዓ.ም. 95-128.

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፤ አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ 1948 ዓ.ም.

ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ሊቀ ካህናት)፤ *ሥርዓተ ቤተክርስቲያን*፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡ 1983 ዓ.ም.

ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር)፤ *ባሕረ ሐሳብ: የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር*፤ ኮሌጅቪል፡ 1993 ዓ.ም.

____________________፤ *ስለ ግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የተሰበሰቡ አንዳንድ ማስታወሻዎች*፤ ኒው ዮርክ፡ 2010 ዓ.ም.

## የእንግሊዝኛ መጻሕፍት እና ጥናታዊ ጽሑፎች

## Primary Sources

*The Anaphoras of the Ethiopic Liturgy*. Trans. J. M. Harden. Translations of Christian Literature. Vol. III: Liturgical Texts. London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1928.

*Ancient Christian Writers: St. Justin Martyr: The First and Second Apologies.* Trans. Leslie Willian Barnard. New York: Paulist Press, 1997.

*Ancient Liturgies: Being Reprint of the Texts, either Original or Translated, of the Most Representative Liturgies of the Church from Various*

*Sources.* Ed. C. E. Hammond and F. E. Brightman. New Jersey: Gorgias Press, 2006.

*Apologia ad Constantium* [By St. Athanasius of Alexandria]*,* Section 31. http://www.newadvent. org/fathers/2813.htm. Accessed on Novemer 10, 2019.

*Apologia of St. John of Damascus Against Those who Decry Holy Images.* Accessed on April 18, 2019: http://www.ccel.org/ccel/damascus/ icons.html.

*The Apostolic Constitutions (Constitutions of the Holy Apostles): The Work Claiming to Be the Constitutions of the Holy Apostles including the Canons*. Eds. Irah and Otto Krabbe. D. Appleton and Company, 1848.

*The Apostolic Tradition of Hippolytus*. Trans. Burton S. Easton. Cambridge: Cambridge University Press, 1934.

Basil the Great. *Hexaemeron.* A Select Library of Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christian Church, Vol. 8. Ed. Philip Schaff and Henry Wace. Michigan: Eerdmans Publishing Company 1989.

______________. *De Spiritu Sancto*. A Select Library of Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christian Church. Vol. 8. Ed. Philip Schaff and Henry Wace. Michigan: Eerdmans Publishing Company, 1989.

*The Canons of Gabriel Ibn Turaik, LXX Patriarch of Alexandria*. Trans.O. H. E. Burmester. OCP. Vol. 1 (1935) 5-45.

*The Church History of Rufinus of Aquileia,* Books 10 and 11. Trans. Philip R. Amidon, S.J. Oxford: Oxford University Press, 1997.

*The Coptic Orthodox Horologion: The Book of the Seven Nocturnal and Daylight Canonical Prayers*. Trans. Fayek M. Ishak. Toronto: Coptologia Spiritual Publications, 1992.

*Dadisho Qaṭraya's Compendious Commentary on the Paradise of the Egyptian Fathers in Garshuni.* Eds. and trans. Mario Kozah, Abdulrahim Abu-Husayn and Suleiman Mourad. New Jersey: Gorgias Press, 2016.

*Die äthipischen Anaphoren des HI.Evangelisten Johannes des Donner sohnes und des HI. Jacobus von Sarug*." Ed. and trans. S. Euringer. OCa*,* 33/1 (1934) 79-122.

*The Didache: Text, Translation, Analysis, and Commentary*. Trans. Aaron Milavec. Collegeville: Liturgical Press, 2003.

*Dionysius Bar Salibi: Commentary on the Eucharist*. Trans. Baby Varghese. Kottayam: Anaswara Printers, 1998.

*The Discourses of Philoxenus of Mabbug.* Trans. Robert A. Kitchen. Collegeville, MN: Cistercian Publications, 2013.

*The Divine Liturgies of Saints Basil, Gregory, and Cyril*. Los Angeles: Coptic Orthodox Diocese of Southern United States, 2001.

*The Divine Liturgy of Our Fathers Among the Saints John Chrysostom.* No Place given: Ad Usum Privatum, 2015.

*An Entire Syriac Text of the Apostolic Church Order*. JTS. Ed. J. P. Arendzen. Vol. 3 (1902) 59-80.

*Eusebius*: *The Church History, A New Translation with Commentary*. Trans. Paul L. Maier. Baltimore: Kregel Publications, 1999.

*Hippolytus: A Text for Students with Introduction, Translation, Commentary and Notes*. Trans. Geoffrey J. Cuming. Grove Liturgical Studies, Vol. 8. Nottingham: Grove Books Limited, 1987.

*Holy Euchologion.* Kitchener: St. Mary's Coptic Orthodox Church, 2004.

*Holy Qurbono: The Divine Liturgy of Saint Jacob Bar Ṣalibi According to the Rite of the Syriac Orthodox Church of Antioch.* Eds. His Eminence Mor Cyril Aphrem Karim et al (and others). New Jersey, Beth Antioch Press and Gorgias Press, 2009.

*The Homilies of St. John Chrysostom on the Gospel of Matthew*. Homily 82, Part V. Trans. Members of the English Church. Oxford: John Henry Parker, 1851.

Irenaeus of Lyons (St.). *Against Heresies, Book V, XXXIII* The Ante-Nicene Fathers: Translations of the Writings of the Fathers Down to A.D. 325, Vol. 1. Eds. Alexander Roberts and James Donaldson. Michigan: W.M.B. Eerdmans Publishing Company, 1993.

*Jacob of Sarug's Homily on the Creation of Adam and the Resurrection of the Dead.* Trans. Edward G. Mathews. Piscataway, NJ: Gorgias Press, 2014

*John Chrysostom (St.): Six Books on the Priesthood.* Book VI: No. 4. Trans. Graham Neville. London: S.P.C.K., 1964.

*The Letters of John of Dalyatha*. Trans. Mary T. Hansbury. New Jersey: Gorgias Press, 2006.

*The Liturgical Portions of the Didascalia.* Ed. Sebastian Brock and Michael Vasey. Bramcote: Grove Books, 1982.

*The Liturgy of the Eighth Book of 'The Apostolic Constitutions' Commonly Called the Clementine Liturgy.* Trans. R. H. Cresswell. London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1924.

*The Liturgy of the Ethiopian* Church. Trans. Marcos Daoud. London: Kegan Paul, 2005.

*A New Eusebius: Documents Illustrative of the History of the Church to A.D.* 337. Ed. J. Stevenson. London: SPCK, 1983.

*The New Testament Greek and English: The Greek Text prepared by the United Bible Societies*. Eds. Kurt Aland and others, 2nd ed. New York: American Bible Society, 1981.

*Proclus of Constantinople and the Cult of the Virgin in Late Antiquity, Homilies 1-5, Texts and Translations*. Ed. Nicholas Constas. Leiden, Boston: Brill, 2003.

*The Testament of Our Lord: Translated into English from the Syriac with Notes*. Trans. James Cooper and Arthur John Maclean. Edinburgh: T. & T. Clark, 1902.

*The Testamentum Domini: A Text for Students, with Introduction, Translation, and Notes.* Trans. Grant Sperry-White. Alcuin Club Liturgical Studies. No. 19, 1991.

## Secondary Sources (Books and Articles)

A. T. M [Abba Takla-Mariam] Semharay-Selim. "Notae circa liturgiam aethiopicam: Liturgia S. Marci Evangelistae et S. Iacobi Apostoli in lingua gheez." *Ephemerides Liturgicae*. Vol. 42 (1928) pp. 440-441.

Arranz, Miguel. "The Functions of the Christian Assembly in the Testament of the Lord." *Roles in the Liturgical Assembly: The Twenty-third Liturgical Conference, Saint Serge*. Trans. Matthew J. O'Connell. New York: Pueblo Publishing Company, 1976. PP. 29-59.

Balicka-Witakowska, Ewa. "Täʾammərä Maryam." *EA*. Eds. Siegbert Uhlig and Alessandro Bausi. Wiesbaden: Harrassowitz, 2007 (Vol. IV) pp. 789-783.

Bausi, Alessandro. “The ‘so-called *Traditio apostolica’*: preliminary observation on the new Ethiopic evidence.” *Volksglaube im antiken Christentum: Festschrift für Theofried.* Eds. Heike Grieser and Andreas Merkt 2009. PP. 291-321.

_______________.“The Aksumite Background of the Ethiopic “Corpus Canonum”.” *Aethiopistische Forschungen: Proceedings of the XVth International Conference of Ethiopian Studies, Hamburg July 20-25,* 2003. Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrassowitz Verlag, 2006. PP. 532-541.

_______________.“Hippolytus.” *EA*. Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrass owitz, 2007 (Vol. 3) pp. 35-36.

_______________. “Qəddase: Mäṣḥafä Qəddase.” *EA*. Eds. Siegbert Uhlig and Alessandro Bausi. Wiesbaden: Harrassowitz, 2007 (Vol. IV) pp. 279-281.

Beylot, Robert. “Sermon éthiopien anonyme sur l’Eucharistie.”*Abbay,* Vol. 12 (1983-1984) pp. 113-116.

Böll, Verena. “Ǝrgäta lämaryam.” *EA.* Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrassowitz, 2005 (Vol, 2) pp. 354-355.

Bradshaw, Paul F. *Eucharistic Origins.* Oxford: Oxford University Press, 2004.

_______________. “Redating the Apostolic Tradition: Some Preliminary Steps.” *Rule of Prayer, Rule of Faith: Essays in Honor of Aidan Kavanagh, O.S.B.* Eds. Nathan Mitchell and John F. Baldovin. Collegeville, MN: The Liturgical Press, 1996. PP. 3-17.

_______________, ed. *Essays on Early Eastern Eucharistic Prayers.* Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1997.

Bradshaw, Paul F. and Maxwell E. Johnson, *The Eucharistic Liturgies: Their Evolution and Interpretation*. London: SPCK, 2012.

Brakmann, Heinzgerd. “Le déroulement de la Messe copte: Structure et histoire,” *LeEucharistie: Célébrations, rites, piétés* (BEL.S 79). Eds. Achille M. Triacca and Alessandro Pistoia, Rome 1995.

Buxton, David. *The Abyssinians.* Southampton: Camelot Press Ltd., 1970.

Cerulli, E. “Ethiopic Languages and Literature.” *NCE,* Vol. 5. Eds. Catholic University of America Editorial Staff. New York: McGraw-Hill, 1967. PP. 590- 592.

Connolly, R. Hugh. *The So-called Egyptian Church Order and Derived Documents*. Cambridge: Cambridge University Press, 1916.

Coquin, Renē-Georges. “Cyriacus.” *CE,* Vol. 3 (1991) pp. 669-671.

Cowley, Roger W. *Ethiopian Biblical Interpretation: A Study in Exegetical Tradition and Hermeneutics*. Cambridge: Cambridge University Press, 1988.

Dalmais, Irénée-Henri. *Eastern Liturgies*. New York: Hawtorn Publishers, 1960.

_________________. “The Eastern Liturgical Families.” *The Church at Prayer: Principles of the Liturgy*, I. Eds. Irénée-Henri Dalmais, Pierre Marie Gy, Pierre Jounel, and Aimé Geoges Martimort. Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1987. PP. 27-43.

Di Salvo, Mario. “The Typology of Ethiopian Churches from the Basilica to the Centrally Planned Churches in Their Structural and Symbolic Aspects.” *Churches of Ethiopia: The Monastery of Nārgā Śellāsē.* Eds. Stanislaw Chojnacki and Osvaldo Raineri. Milano: Skira Editore S.P.A., 1999. PP. 57-95.

Dix, Gregory. *The Shape of the Liturgy*: *New Edition with an Introduction by Simon Jones*. London: Bloomsbury T&T Clark, 2015.

Farley, Lawrence (Fr.). *Let Us Attend: A Journey through the Orthodox Divine Liturgy*. Chesteron, Indiana: Conciliar Press, 2007.

Fiaccadori, Gianfranco. “Ewosṭatewos.” *EA.* Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrassowitz, 2005 (Vol. 2) pp. 469-472.

Fink, Peter. “Liturgical Traditions in the East.” *The New Dictionary of Sacramental Worship*. Ed, Peter Fink. Collegeville, MN: The Liturgical Press, 1990. PP. 1269-1274.

Fortounatto, Mariamna and Mary B. Cunningham. “Theology of the Icon.” *The Cambridge Companion to Orthodox Christian Theology*. Eds. Mary Cunningham and Elizabeth Theokritoff. Cambridge: Cambridge University Press, 2008. PP. 136-149.

Fritsch, Emmanuel. "The 'Order of the Mystery': An Ancient Catechesis Preserved in BnF Ethiopic ms. d'Abbadie 66-66bis (Fifteenth Century) with a Liturgical Commentary." *Eastern Christian Studies, 28: Studies in Oriental Liturgy: Proceedings of the Fifth International Congress of the Society of Orinetal Liturgy, New York, 10-15, June 2014*. Eds. Bert Groen et al (and others). Leuven : Peeters, 2019. PP. 195-263.

________________."The Anaphoras of the Ge'ez Churches: A Challenging Orthodoxy." *The Anaphoral Genesis of the Institution Narrative in Light of the Anaphora of Addai and Mari: Acts of the International Liturgy Congress.* OCA, 295 (2013) pp. 275-316.

________________."The Preparation of the Gifts and the Pre-Anaphora in the Ethiopian Eucharistic Liturgy in around 1100 A.D." *Rites and Rituals of the East: Proceedings of the Fourth International Congress of the Society of Oriental Liturgy, Beirut, Lebanon, 10-15 July,2012*. Eds. Bert Groen, Daniel Galadza, Nina Glibetić and Gabriel Radle. Eastern Christian Studies, 22. Leuven: Peeters Publishing House, 2014. PP. 163-194.

_________________."Ethiopian Liturgy and Church Architecture." *Ethiopian Review of Cultures.* Vol. 14 (2011) pp. 75-103.

________________. "Une hymne eucharistique éthiopinne: le Malk'a Q$^{w}$erban ou 'Portrait de l'Eucharistie.'" *Irénikon,* no. 2-3 (2002) pp. 195-229.

________________. "Qəddase." *EA*. Eds. Siegbert Uhlig and Alessandro Bausi. Wiesbaden: Harrassowitz, 2007 (Vol. IV) pp. 271-275.

Getatchew Haile. "Ethiopian Heresies and Theological Controversies." *CE,* Vol. 3. Ed. Aziz S. Atiya. New York: Macmillan Publishing Company, 1991. PP. 984-987.

______________. "Ethiopic Literature." *African Zion*: *The Sacred Art of Ethiopia*. Ed. Roderick Grierson. Milan: Amilcare Pizzi, 1993. PP. 47-56.

______________. "On the Identity of Silondis and the Composition of the Anaphora of Mary Ascribed to Hərəyaqos of Bəhənsa." *OCP*, 49/2 (1983) pp. 366-389.

______________. "On the Writings of Abba Giyorgis Säglawi from Two Unedited Miracles of Mary." *OCP,* Vol. 40 (1982) pp. 65-91.

______________. "Religious Controversies and the Growth of Ethiopic Literature in the Fourteenth and Fifteenth Centuries." *OC*, 65 (1981) pp. 102-136.

______________. "The Cause of the Ǝsṭifanosites: A Fundamental Sect in the Church of Ethiopia." *Paideuma,* Vol. 29 (1983) pp. 93-119.

______________. "The Homily in Honour of St. Frumentius Bishop of Axum." *Analecta Bolladiana: Revue Critique D'hagiographie*. Tome 97 (1979) pp. 309-318.

______________. *Ethiopian Studies in Honour of Amha Asfaw.* New York: 2017.

______________. *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville*, Vol. X: Project Numbers 4001-5000. Collegeville: MN: HMML, 1993.

Getatchew Haile and William F. Macomber. *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. V: Project Numbers 1501-2000*. Collegeville, MN: HMML, 1981.

______________________________________. *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. VI, Project Numbers 2001-2500*. Collegeville, MN: HMML, 1982.

______________________________________. *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscript Microfilm Library, Addis Ababa and for the Hill Monastic Manuscript Library, Collegeville, Vol. VII: Project Numbers 2501-3000.* Collegeville, MN: HMML, 1983.

Gregorios, (Hieromonk). *The Divine Liturgy: A Commentary in the Light of the Fathers*. Trans. Elizabeth Theokritoff. Mount Athos: Cell of St. John the Theologian, Koutloumousiou Monastery, 2009.

Grillmeier, Aloys SJ. *Christ in Christian Tradition*: *The Church of Alexandria with Nubia and Ethiopia after 451.* Vol. 2, Part 4, trans. O. C. Dean Jr. London: Mowbray, 1996.

Habtemichael Kidane. “A Note on the Aspects of the Epiclesis of the Gəʼəz Anaphora of St. James of Sərug.” *Rites and Rituals of the Christian East.* Eds. Bert Groen, Daniel Galadza, Nina Glibetick and Gabriel Radle, Eastern Christian Studies. Vol. 22, Leuven: Peeters, 2014. PP. 153-180.

__________________. “The Institution Narrative-Anamnesis in the Ethiopian Anaphora of James of Sərug.” *‘Faire mémoire’: l’anamnése dans la* liturgie. Eds. André Lossky and Manlio Sodi. Menumenta Studiea Instrumenta Liturgical. Vol. 63, Vatican City: 2011. PP. 119-148.

__________________. “Does the Ethiopian Pre-Anaphora Maintain the Egyptian Preparatory Service? Towards a Study of the Sərəʼata Qəddase.” *Proceedings of the First International Conference on Ethiopian Texts*. Eds. Daniel Assefa and Hiruy Abdu. Addis Ababa: CFRRC Press, 2016.

__________________.“Maḫletä Ṣəge.” *EA.* Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harras-sowitz, 2007 (Vol. 3) pp. 660-661.

__________________.“Anaphoras.” *EA.* Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrass-owitz, 2003 (Vol. 1) pp. 251-253.

__________________.“Ethiopian (or Gəʿəz) Worship.” *The New Westminster Dictionary of Liturgy and Worship.* Ed. Paul Bradshaw. London: Westminster John Knox Press, 2002. PP. 169- 172.

Haffner, August. “Das Hexaëmeros des Pseudo-Epiphanius.” *Oriens Christianus: Halbjahrshefte für die Kunde des Christlichen Oreints*. Ed. A. Baumstark Leipzig: Otto Harrassowitz, 1923. PP. 91-145.

Hammerschmidt, Ernst. *Studies in the Ethiopic Anaphoras*. Stuttgart : Franz Steiner Verlan Wiesbaden GMBH, 1987.

Harakas, Stanley S. *Living the Liturgy: A Practical Guide for Participating in the Divine Liturgy of the Eastern Orthodox Church*. Minneapolis, MN: Light and Life Publishing Company, 1974.

Hatzidakis, Emmanuel (Fr.). *The Heavenly Banquet: Understanding the Divine Liturgy*. Chicago: Orthodox Witness, 2010.

Heldman, Marilyn. “Architectural Symbolism, Sacred Geography and the Ethiopian Church.” *Journal of Religion in Africa.* Vol. 22/No. 3 (1992) pp. 222-241.

Hess, Robert. *Ethiopia.* Illinois: Northwestern University, 1970.

Hien, Ewald and Brigitte Kleidt. *Ethiopia – Christian Africa: Art*, *Churches and Culture*. Trans. John M. Deasy. Retingen: Melina-Verlag, 1999.

Irwin, Kevin W. "The Sacramentality of Creation and the Role of Creation in Liturgy and Sacraments." *And God Saw That It Was Good*: *Catholic Theology and the Environment*. Eds. Drew Christiansen and Walter Grazer. Washington, D.C.: United States Catholic Conference, 1996. PP. 105-146.

Iskander, Athanasius (Fr.). *Understanding the Liturgy.* Kitchener: St. Mary's Coptic Orthodox Church, 1997.

Jasper, R.C.D. and G. J. Cuming. *Prayers of the Eucharist: Early and Reformed Texts translated and edited with Commentary,* 3rd ed. Collegeville, Minnesota, 1990.

Jeffery, Peter. "The Liturgical Year in the Ethiopian Deggʷā" *ΕΥΛΟΓΗΜΑ: Studies in Honour of Robert Taft, S.J.* Eds. E. Carr, S. Parenti, A. Thiermeyer, E. Velkovska. Rome: Centro Studi S. Anselmo, 1993. PP. 199-234.

Lossky, Vladimir. *The Mystical Theology of the Eastern Church*. London: James Clarke and Co. Ltd., 1957.

Lourié, Basil. "Cyriacus of Jerusalem." *EA*. Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrassowitz, 2003. Vol. 1. 843-844. Lusini, Gianfrancesco. "Eschatology." *EA,* Vol. 2. Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrassowitz Verlag, 2003. PP. 379-382.

Macomber, William F. "Ethiopian Liturgy." *CE*, Vol. 3. Ed. Aziz S. Atiya. New York: Macmillan Publishing Company, 1991. PP. 987-990.

Maniyattu, Pauly. *Heaven on Earth: The Theology of Liturgical Spacetime in the Eastern Syrian Qurbana.* Rome: Mar Thoma Yogam [St. Thomas Christian Fellowship], 1995.

Mazza, Enrico. *The Origins of the Eucharistic Prayer.* Collegeville, Minnesota: The Liturgical Press, 1995.

Mebratu Kiros. "Anaphoras of the Ethiopian Church: A Historical Introduction." *Ephrem's Theological Journal*. Vol 5 (October 2001) pp. 203-220.

Meßner, Reinard and Martin Lang. "Ethiopian Anaphoras Status and Tasks in Current Research via an Edition of the Ethiopian Anaphora of the

Apostles." *Jewish and Christian Liturgy and Worship: New Insights into Its History and Interaction*. Eds. Albert Gerhards and Clemens Leonhard. Leiden: Brill, 2007. PP. 185-206.

Metzger, Marc. "Liturgy and Cosmos." *Concilium: Liturgy and the Body*. Eds. Louis-Marie Chauvet and François Kabasele Lumbala. London: SCM, 1995. PP. 40-47.

Ninos, Foteny Economon. *The Divine Liturgy: Analysis, Exegesis and Commentary*. Minneapolis, MN: Light and Life Publishing Company: 1987.

Ouspensky, Leonid. *Theology of the Icon.* Trans. Anthony Gythiel, Vol. I. New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1992.

Pankhurst, Sylvia. *Ethiopia: A Cultural History.* Norwich: Fletcher and Son Ltd., 1955.

Paulos Tzadua. *The Divine Liturgy According to the Rite of the Ethiopian Church*. Addis Ababa: Wien Ltd., 1973.

Ricci, Lanfranco. "Ethiopian Christian Literature." *CE,* Vol. 3. Ed. Aziz S. Atiya. NewYork: Macmillan Publishing Company, 1991. PP. 975-982.

Rofail, Antonios. "The Eucharistic Liturgy in the Coptic Orthodox Church." *The Logos.* Vol. 9/2 (1996) pp. 6-11.

Rordorf, Willy. "Sunday: The Fullness of Christian Liturgical Time." *Studia Liturgica*. Vol. 14/1 (1980/1981) pp. 90-96.

Schmemann, Alexander. *The Eucharist: Sacrament of the Kingdom*. Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1974.

____________________. *For the Life of the World: Sacramnets and Orthodoxy*. New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1982.

Sergew Hable Sellassie. *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270.* Addis Ababa: Haile Sellassie I University, 1972.

Sima, Alexander. "Cosmas Indicopleustes." Ed. Siegbert Uhlig. Wiesbaden: Harrassowitz, 2007 (Vol. I) pp. 806-807.

Spinks, Bryan D. *Do This in Remembrance of Me: The Eucharist from the Early Church to the Present Day.* London: SCM Press, 2013.

Stewart-Sykes, Alistair and Judith H. Newman. *Early Jewish Liturgy: A Sourcebook for use by Students of Early Christian Liturgy.*

Alcuin/GROW Joint Liturgical Studies. Vol. 51 (Cambridge: Grove Books Limited, 2001.

Strelcyn, Stefan. "L'action de grâce de n.de. Marie et l'anaphore de n.d. Marie dite Mä'aza Qəddase dans la liturgie éthiopienne." *JSS,* Vol. 24/2 (1979) pp. 241-249.

Suciu, Alin. *The Berlin-Stasbourg Apocryphon: A Coptic Apostolic Memoir*. No Place Given: Mohr Siebeck, 2017.

Sumner, Claude. "The Ethiopic Liturgy: An Analysis." *JES*, Vol. 1 (1963) pp. 35-45.

Taddesse Tamrat. *Church and State in Ethiopia 1270-1527.* Oxford: Clarendon Press, 1972.

Tafla, Bairu. "Ethiopian Orthodox Church," *CE*, Vol. 3, ed. Aziz S. Atiya. New York: Macmillan Publishing Company, 1991. PP. 995-999.

Taft, Robert. *Beyond East and West: Problems in Liturgical Understanding*. Washington: Pastoral Press, 1989.

__________. "From logos to spirit: On the early history of the epiclesis." *GRATIAS AGAMUS: Studien zum eucharistischen Hochgebet,* Basel: Verlag Herder, 1992. PP. 489-502.

Tedros Abraha, O.F.M. Cap. "Jacob of Serug in the Ethiopic Tradition under Review and New Clues about the Background of the Ge'ez Anaphora Ascribed to Jacob of Serug." *OCA,* Vol. 298 (2015) pp. 463-478.

Theokritoff, Elizabeth. "Embodied Word and New Creation: Some Modern Orthodox Insights Concerning the Material World." *Abba: The Tradition of Orthodoxy in the West: Festschrift for Bishop Kallistos (Ware) of Diokleia*. Eds. John Behr, Andrew Louth, Dimitri Conomos. New York: St. Vladimir's Seminary Press, 2003. PP. 211-238.

Trimingham, J. S. *Islam in Ethiopia.* London: Oxford University Press, 1952.

Tsirpanlis, Constantine N. *The Liturgical and Mystical Theology of Nicolas Cabasilas*. New York, [No Publisher], 1979.

Ullendorff, Edward. "Hebraic-Jewish Elements in Abyssinian (Monophysite) [*sic*] Christianity." *JSS*. Vol. 1 (1957) pp. 216-256.

________________. *Ethiopia and the Bible.* London: Oxford University Press, 1968.

Urdániz, José L. Bandrés (M. Afr.). *A Glance Behind the Curtain: Reflections on the Ethiopian Celebration of the Eucharist*. Adigrat: Master Printing Press P.L.C., 2008.

________________."The Ethiopian Anaphora of the Apostles: Historical Considerations." *Proche-Orient Chretien,* Vol. 34 (1986) pp. 3-13.

Varghese, C. K. *The Living Sacrifice: The Holy Qurbanakramam: Interpretation, Meaning of Songs, Biblical Quotations.* Kerala: Thuruthel Press and Book Depot [Seventh Edition], 2005.

Vasileios (Archimandrite). *Hymn of Entry: Liturgy and Life in the Orthodox Church*. Trans. Elizabeth Briere. New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1984.

Ware, Kallistos. *The Orthodox Way*. Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1995.

Witakowski, Witold. "Filekseyus, the Ethiopic Version of the Syriac Dadisho Qatraya's Commentary on the Paradise of the Fathers." *Rocznik Orientalistyczny*. Vol. 95/1 (2006) pp. 281-292.

Zanetti, Ugo. "Is the Ethiopian Holy Week Service Translated from Sahidic? Towards a Study of the Gebra Ḥemamat." *Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies.* Vol. I (1994) pp. 770-780.

____________. "Voici le temps de la bénédiction . . .": Origine copte d'une hymme liturgique éthiopienne." *OCP*, Vol. 1 (2009) pp. 25-50.

Zemene Abuhay. *Brief Introduction to the History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church.* San Jose, California: Mekane Rama Qidus Gebriel Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, 2005.

Zizioulas, John D. (Metropolitan). "The Eucharist and the Kingdom of God, Part II" *Sourozh: A Journal of Orthodox Life and Thought*. Vol. 59 (1995) pp. 22-38.

________________. *Eucharist, Bishop, Church.* Brookline, MA: Holy Cross Orthodox Press, 2001.

# ማስታወሻ

# ማስታወሻ

# ማስታወሻ



## <u>የአሳታሚው ማስታወሻ</u>

*ቀሲስ ዶ/ር መብራቱ ኪሮስ ገብሩ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በ 1993 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 2001) የመጀመሪያ ዲግሪ ፥ University of Toronto ሥር ከሚገኘው University of St. Michael's College በነገረ መለኮት (theology) የማስትሬትና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ለማስትሬት ዲግሪ ማሟያ በ1997 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 2005) የጻፉት የምረቃ ጽሑፍ (thesis)፡- "Miaphysite Christology: An Ethiopian Perspective" በሚል ርእስ በአሜሪካ ኒው ጀርሲ ከተማ ውስጥ በሚገኘው Gorgias Press በ 2002 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 2010) በመጽሐፍ መልክ ታትሟል። በ2004 ዓ.ም. (እ.አ.አ. 2012) ለዶክትሬት ዲግሪ (Ph.D. in theology) ማሟያ ለዩኒቨርሲቲው ያቀረቡት የምረቃ ጽሑፍ (thesis)፡- "Liturgical Cosmology: The Theological and Sacramental Dimensions of Creation in the Ethiopian Liturgy" የሚል ነው።*

*ቀሲስ ዶክተር መብራቱ ኪሮስ ገብሩ ይህን **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ታሪክ እና ይዘት** ለማዘጋጀት ያደረገው ምርምር ምን እንደሚመስል ለማወቅ የሚፈልግ ገና የመጀመሪያውን ገጽ ሲያነብ ሊረዳ ይችላል። ዋናውን ክፍል ትተን የኅዳግ ማብራሪያዎቹን ብቻ እንኳን ብናስተውላቸው፥ እንደ ትምህርት ቤት፥ እንደ ቤተ መጻሕፍት የሚቈጠሩ ሆነው እናገኛቸዋለን። የዋቢ መጻሕፍቱ ዝርዝርም በሰፊው የማይታወቁ ጠቃሚ ምንጮችን ይዟል። ወደ ዋናው ክፍል ስንገባ፥ የሥነ ቅዳሴው ውበትና ምሥጢር ወለል ብሎ ይታያል። ሥርዓቱ ከሲኖዶስ፥ ከመጽሐፈ ኪዳን፥ ከአበው ትርጓሜ ጋር ያለውን ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ግንኙነት **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ታሪክ እና ይዘት** ያብራራልናል። የሥርዓቱ ጥንታዊነት ሲጠበቅ፥ በቤተ ክርስቲያኗ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚታዩ፥ ግን ከሥርዓተ ቅዳሴው ጋር የሚገናኙ የማይመስሉ ነገሮች ሲገናኙ እናያለን።*

*የመብራቱን ጥረት እንደኔ የሚያውቅ በዚህ ጥናት ጥልቀትና ስፋት አይገረምም። የዶክትሬቱን፥ ከዚያ በፊትና ከዚያ በኋላም የደረሳቸውን የጥናት ጽሑፎች አውቃቸዋለሁ። የማያልፍበት፥ የማይሻር ጥናት እንደሚያደርግ መስክረውልኛል። አሁንም **በአኰቴተ ቍርባን፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ታሪክ እና ይዘት** ደግሞታል። አባቶቻችን ከውጪው ዓለም ጋር እየተገናኙ በዘመናቸው በሠሩት ሥራ እኛን እንዳኰሩንና እኛም እንደምናከብራቸው፥ እንደ ቀሲስ ዶክተር መብራቱ ያሉ ያባቶቻችንን ፈለግ ተከትለው ትውልዳቸውን አስተምረው፥ የሚቀጥለውን ትውልድ የሚያኰሩና ትውልዱም የሚያከብራቸው ወጣት ምሁራን መነሣታቸውን ስናይ አምላካችንን እናመሰግናለን። ቤተ ክርስቲያንም አባቶቻችንን በሥራቸው እንደምታከብር መብራቱንም በሥራው እንደምታከብረው አምናለሁ። በጥረቱ ተጠቃሚዎችን ያብዛልን።*

†††

*ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ*

*ይህ መጽሐፍ የምንኮራበትና በመንፈሳዊ ረገድ የምናድግበት፥ የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓተ አምልኮ እንድናውቀው፥ አውቀን እንድንወደውና እንድንኮራበት የሚረዳን መጽሐፍ ነው እላለሁ። ይህንን መጽሐፍ ስለ ቅዳሴያችን በአማርኛ ታትመው ከወጡ መጻሕፍት በዋነኝነት የሚለየው፥ ጥናታዊ መንገድን የተከተለ በመሆኑ ነው። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓተ ቅዳሴ ከሌሎች የምሥራቅ ሥርዓተ ቅዳሴያት ጋር በማነጻጸር የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ቅዳሴያችንን በሚገባ ለሚያውቁት ሊቃውንትም ሆነ፥ በነገረ መለኮት ጥናት ላይ ላሉ የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎች በአገራችን ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ ተጨማሪ ጥናቶችን እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸውና የሚረዳቸው መሆኑን እመሰክራለሁ። አንባብያን ይህን መጽሐፍ አንብበው ከጨረሱ በኋላ "ለካ የሥርዓተ አምልኳችን ታሪክና ምሥጢር እንደዚህ ነው?" ብለው እንደሚደነቁና መንፈሳዊ ኃይልም እንደሚሰማቸው አምናለሁ።*

*ዶ/ር ሀብተሚካኤል ኪዳነ*

ISBN 978-99944-77-59-3

9 789994 477593 >

**ዋጋው፡ $25 USD**